*መጽሐፍ ቅዱስን መረዳት ትችላለህ*

# የስምነተኛ መቶ ክፍለ ዘመን
# ደቂቀ ነብያት፡-
# አሞፅ፣ ሆሴዕ፣
# ዮናስ እና ሚልክያስ


ቦብ አትሊ

የትርጓሜ ሊቅ (ፕሮፌሰር)

(የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ)



*የጥናት መመሪያ ሐተታዊ ጽሑፍ*

*ብሉይ ኪዳን፣ ቅጽ 10*

ዓለም አቀፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት፣ ማርሻል፣ ቴክሳስ

2006

# ማውጫ

በዚህ ሐተታ ውስጥ ጥቅም ላይ  የዋሉ ሞያዊ ቃላት አጭር መግለጫ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . i
ትርጓሜው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ የዕብራይስጥ ግሣዊ ቅርጾች አጭር ማብራሪያ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ii
ሐተታው ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ አሕጽሮተ ቃላት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . vi
የጸሐፊው መልእክት፡ይህ ሐተታ እንዴት ይረዳዎታል? . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . vii
ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ፡ የተፈተነ እውነትን በግል ለመፈለግ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ix
የአሞፅ መግቢያ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1
አሞፅ 1 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 6
አሞፅ 2 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 18
አሞፅ 3. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 28
አሞፅ 4 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 40
አሞፅ 5 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 48
አሞፅ 6 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 57
አሞፅ 7 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 64
አሞፅ 8 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 71
አሞፅ 9 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 76
የሆሴዕ መግቢያ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 86
ሆሴዕ 1 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 89
ሆሴዕ 2 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 94
ሆሴዕ 3 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 104
ሆሴዕ 4 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 108
ሆሴዕ 5 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 115
ሆሴዕ 6 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 121
ሆሴዕ 7 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 125
ሆሴዕ 8 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 131
ሆሴዕ 9. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 136
ሆሴዕ 10 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 142
ሆሴዕ 11 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 148
ሆሴዕ 12 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 153
ሆሴዕ 13 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 157
ሆሴዕ 14 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 161
የዮናስ መግቢያ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 165
ዮናስ 1. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 167
ዮናስ 2 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 175

ዮናስ 3 .......... 179
ዮናስ 4 .......... 184
የሚልክያስ መግቢያ .......... 187
ሚልክያስ 1 .......... 190
ሚልክያስ 2 .......... 197
ሚልክያስ 3 .......... 203
ሚልክያስ 4 .......... 208
ሚልክያስ 5 .......... 217
ሚልክያስ 6 .......... 226
ሚልክያስ 7 .......... 234
ተጨማሪ መግለጫ አንድ: የባቢሎናዊያን የፋርስና የግሪክ ነገስታት ስርወ-መንግስት እና ክስተቶች .......... 241
ተጨማሪ መግለጫ ሁለት: የመስፖታሚያን ኃያላን ግልጽ ታሪካዊ ዳሰሳ .......... 244
ተጨማሪ መግለጫ ሦስት: የሙሉው ብሉይ ኪዳን ሰንጠረዥ .......... 250

# ልዩ ርዕሶች የይዘት ማውጫ


የእብራይስጥ ሥነ-ግጥም፣ አሞፅ 1:2 . . . 8

የመለኮት ስሞች፣ አሞፅ 1:2 . . . 9

ንስሃ መግባት በብሉይ ኪዳን፣ አሞፅ 1:3 . . . 12

የጥንቱ ቅርብ ምስራቅ የመራባት አምልኮ አሞፅ 1:9 . . . 15

ማቃጠል አሞፅ 2:1 . . . 19

ጽድቅ  አሞፅ 2:6 . . . 21

ቅዱስ፣ አሞፅ 2:7 . . . 24

አሞራዊ፣ አሞፅ 2:9 . . . 25

በጥንታዊያን ቅርብ ምስራቅ የመስዋዕት ሥርዓት  አሞፅ 3:14 . . . 33

መጽሐፍ ቅዱሳዊ አዝማሚያ በአልኮል እና በአልኮለኝነት 6:6. . . . 59

እሳት፣ አሞፅ 7:4 . . . 66

በነብይ ላይ የሚነገሩ የተለያዩ የእብራዊያን ቃላት አሞፅ 7:12 . . . 68

የጥንት ቅርብ ምስራቅ ክብደት እና መጠን (ሥነ-ልኬት) አሞፅ 8:5 . . . 73

ሙታን የት ናቸው? አሞፅ 9:2 . . . 77

“ወጥረቶች”(በራዕይ ከተሰራው የኔ ሃተታ ላይ አስፈላጊ መግቢያ ጥራዝ 12 የተወሰደ) ፣ አሞፅ 9:7 . . . 79

ኪዳን፣ ሆሴዕ 2:18 . . . 99

ኦላም (ዘላለም)ሆሴዕ 2:19 . . . 100

ደግነት (ሄሰድ*HESED)* ሆሴዕ 2:19 . . . 102

ተራፊም ፣ ሆሴዕ 3:4 . . . 106

ይህ ዘመንና ሊመጣ ያለው ዘመን. . . . 107

አናብስት በብሉይ ኪዳን፣ ሆሴዕ 5:14 . . . 119

መዋጀት/መቤዠት፣ ሆሴዕ 7:13 . . . 128

ልብ   ሆሴዕ 10:1 . . . 143

ቀድሞ የተወሰነ (ካልቫኒዝም) ወይም የሰው ነጻ ፍቃድ (አርሜኒያኒዝም). . . . 171

እምነት፣ ማመን ወይም ተአማኒ (ፒስቲስ (ስም) ፣ ፒቴዎ (ግስ) ፣ ፒስቶስ (ገላጭ)  3:5 . . . 181

ቅሬታ፣ ሦስት መልኮች፣ ሚልክያስ  2:12 . . . 202

የብሉይ ኪዳን ስለወደፊት ትንቢቶች እና የአዲስ ኪዳን ትንቢቶች፣ ሚልክያስ  4:7 . . . 212

ሥላሴ፣ ሚልክያስ  5:2 . . . 220

የቦብ ወንጌላዊነት ቅድመ ዝንባሌዎች፣ ሚልክያስ  5:7 . . . 222

ሴቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ ሚልክያስ  6:4 . . . 228

*ይህ መጽሐፍ መተሰቢያነቱ*

*ለ ኦ. እም. ኤስ(OMS) መጽሐፍ ቅዱስ ሴሚናሪ*

*እና*

*ወንጌልን በማሰራጨት  እና  ለሃይቲ ማህበረሰብ*

*ለስጋቸውም የሚያስፈልገውን በማድረግ አስደናቂ ስራ ለሰሩና*

*እየሰሩም ላሉት ለሀይቲ ኤማኡስ ቤተክርስቲያን ነው፡፡*

# "መጽሐፍ ቅዱስን መረዳት ትችላለህ"
# በሚለው የብሉይ ኪዳን ተከታታይ ትርጓሜ ሐተታ
# ጥቅም ላይ የዋሉ ሞያዊ ቃላት አጭር መግለጫ

I. የቃላት

በርካታ በጣም ጥሩ የሆኑ የጥንታዊ ዕብራይስጥ መዝገበ ቃላት ይገኛሉ።

ሀ. የዕብራይስጥና እንግሊዝኛ የብሉይ ኪዳን የቃላት ዝርዝር በ ፍራንሲስ ብራውን፣ ኤስ. አር. ድራይቨር፣ እና ቻርለስ ኤ. ብሪግስ። እሱም የተመሠረተው በጀርመን የቃላት ዝርዝር በዊሊየም ጌሴኒዩስ። **እሱም ቢዲቢ በሚል ምሕጻረ ቃል ይታወቃል።**

ለ. የዕብራይስጥና አራማዊ የብሉይ ኪዳን የቃላት ዝርዝር በሉድዊንግ ኮህለር እና ዋልተር ባዩምጋርትነር፣ በኤም. ኢ. ጄ. ሪቻርድሰን የተተረጎመ። **እሱም ኬቢ በሚል ምሕጻረ ቃል ይታወቃል።**

ሐ. የዕብራይስጥና አራማዊ የብሉይ ኪዳን የቃላት ዝርዝር በዊሊየም ኤል. ሆላዴይ እናም ከላይ ካለው የጀርመን የቃላት ዝርዝር ላይ የተመሠረተ።

መ. አዲሱ ባለ አምስት ቅጽ ሥነ መለኮታዊ የቃላት ጥናት አዲሱ ዓለም አቀፍ የብሉይ ኪዳን ሥነ መለኮት እና ትርጓሜ፣ በዊሊየም ኤ. ቫን ጄመራን። **እሱም ኒዶቲ በሚል ምሕጻረ ቃል ይታወቃል።**

ትርጉም ያለው የቃላት ልዩነት በሚኖርበት ጊዜ በርካታ የእንግሊዝኛ ትርጉሞችን ለማሳየት ሞክሬአለሁ (አአመመቅ፣ አኪጀት፣ አየተመት፣ አእት፣ አኢመቅ) ከሁለቱም "ቃል በቃል" እና "የተለወጠ አቻ" ትርጓሜዎችን (ጎርዶን ፊ እና ዳግላስ ስቱዋርት፣ *መጽሐፍ ቅዱስን ከነሙሉ ጠቀሜታው እንዴት ማንበብ ይቻላል*፣ ገጽ 28-44)።

II. ሰዋሰዋዊ

ሰዋሰዋዊ መለያው ዘወትር የተመሠረተው በጆን ጆሴፍ ኦውንስ *የብሉይ ኪዳን የትንታኔ ቁልፍ* በአራት ቅጽ ነው። ይህም በቤንጃሚን ዴቪድሰን *የብሉይ ኪዳን ትንታኔ፣ የዕብራይስጥና ከለዳውያን የቃላት ዝርዝር* በሚለው እንዲቃኝ ተደርጓል።

ሌለኛው ጠቃሚ ምንጭ፣ ለሰዋሰዋዊውም ሆነ ለአገባብ መልኩ፣ እሱም "መጽሐፍ ቅዱስን ልትረዳው ትችላለህ" በሚለው ተከታታይ ጽሑፍ በአብዛኞቹ የብኪ ቅጾች ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን፣ እሱም "ለተርጓሚዎች ተከታታይ ጽሑፍ ጠቀሜታ"፣ ከተባበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ሶሳይቲ ነው።

III. ጽሑፋዊ

እኔ ተመስጧዊ ለሆነው ለዕብራይስጥ ተናባቢ ጽሑፍ አትኩሮት አለኝ (ለምሥጢራዊ ጽሑፍ አናባቢ ሳይሆን፣ ለማመልከትም ሆነ አስተያየት ለመስጠት)። በሁሉም የእጅ ጽሑፎች፣ ጥንታዊ ጽሑፎች አጠያያቂ ምንባቦች አሏቸው። ይህም የሆነበት ምክንያት

ሀ. ሃፓክስ ሌጎሜና (በዕብራይስጥ ብኪ አንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የዋለ)

ለ. ፈሊጣዊ ቃላት (ቃላትና ሐረጋት፣ ጥሬ ትርጉማቸው የጠፋ)

ሐ. ታሪካዊ ርግጠኝነት የሌላቸው (ስለ ጥንታዊው ዓለም ያለን መረጃ እጥረት ስላለበት)

መ. ብዙሐ-ሴማዊ የፍቺ መስክ ውስን የዕብራይስጥ መዝገበ ቃላት መኖሩ

ሠ. የቀድሞዎቹ ጸሐፍት የእጅ ጽሑፍ፣ በጥንታዊ የዕብራይስጥ ጽሑፎች ላይ የተያያዙ ችግሮች

ረ. የዕብራይስጥ ጸሐፊዎች በግብፅ የሠለጠኑት፣ እነሱም ጽሑፎቹን ለማሻሻል ነጻነት የሚሰማቸው፣ በሚቀዱበት ጊዜ ለዘመናቸው የተሟላ እንዲሆኑና የሚረዱ እንዲሆኑ በማድርጋቸው (ኒዶቴ ገጽ 52-54)።

በርካታ የዕብራይስጥ ቃላት እና ጽሑፎች ምንጮች ከምሥጢራዊ ጽሑፋዊ ባህል ውጭ ይገኛሉ።

ሀ. ሰማሪያዊ ፔንታቲዩች

ለ. የሙት ባሕር ጥቅሎች

ሐ. አንዳንድ የኋለኛ ሳንቲሞች፣ ደብዳቤዎች፣ እና ሸክላ (ለጽሑፍ ያገለግሉ የነበሩ ያልተተኮሱ የሸክላ ስብርባሪዎች)

ነገር ግን በአብዛኛው ክፍል፣ በብኪ የእጅ ጽሑፍ ምድቦች የሉም፣ በግሪክ አኪ የእጅ ጽሑፎች እንዳሉት። አጠር ላለ ጽሑፍ፣ በጽሑፉ ተጨባጭነት፣ እሱም በምሥጢራዊ ጽሑፍ (የ900 ዓ.ም) "የብሉይ ኪዳን ጽሑፍ ተጨባጭነት" በብሩስ ኬ. ዋልተኬ በኒዶቴ፣ ቅጽ 1፣ ገጽ 51-67 ተመልከት።

ጥቅም ላይ የዋለው የዕብራይስጡ ጽሑፍ ቢብሊያ ሔብራይካ ስቱትጋርቴንሲያ ከጀርመን የመጽሐፍ ቅዱስ ሶሳይቲ፣ 1997፣ እሱም በሌኒንግራድ ኮዴክስ ላይ የተመሠረተ ነው (1009 ዓ.ም)። ከጊዜ ወደ ጊዜ የጥንት ትርጉሞች (ግሪክ፣ ሴፕቱዋጂንት፣ አዋሚክ ታርጉምስ፣ ሶሪያዊ ፔሺታ፣ እና ላቲን ቫልጌት) ተቃኝተዋል፣ ዕብራይስጡ አሻሚ ወይም በግልጽ አወዛጋዊ ሲሆን።

# ትርጓሜው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ የዕብራይስጥ ግሣዊ ቅርጾች ግልጽ ማብራሪያ

I. የዕብራይስጥ አጭር ታሪካዊ እድገት

ዕብራይስጥ የሼማቲክ (ሴማዊ) የደቡባዊ ምዕራብ እስያ ቋንቋ ቤተሰብ ክፍል ነው። ስሙ (በዘመናዊ ሊቃውንት የተሰጠው) የመጣው ከኖኅ ልጅ ከሴም ነው (ዘፍ. 5፡32፤ 6፡10)። የሴም ዝርያዎች በዘፍ. 10፡21-31 ተዘርዝረዋል፣ እንደ ዓረቦች፣ ዕብራውያን፣ ሶርያውያን፣ አርማናውያን፣ እና ሴሪናውያን። በተጨባጭ፣ አንዳንድ ሴማዊ ቋንቋዎች በካም የዘር ሐረግ በተዘረዘሩት ሕዝቦች ይነገሩ ነበር (ዘፍ. 10፡6-14)፣ ከነዓን፣ ፍንቄአዊ፣ እና ኢትዮጵያ።

ዕብራይስጥ የእነዚህ ሰሜን ምዕራብ ምድብ ሴማዊ ቋንቋዎች ክፍል ነው። ዘመናዊ ሊቃውንት የዚህ የጥንት የቋንቋ ምድብ ናሙናዎችን ያገኙት፡

ሀ. አሞራውያን (የማሪ የገበታ ጽሑፎች ከ18ኛ ክፍለ ዘመን ዓ.ዓ በአካድያን)

ለ. ከነዓናዊ (ራስ ሻምራ የገበታ ጽሑፎች ከ15ኛ ክፍለ ዘመን በዩጋሪቲክ)

ሐ. ከነዓናዊ (አማርና ደብዳቤዎች ከ14ኛ ክፍለ ዘመን በከነዓናዊ አካዲያን)

መ. ፍንቄአውያን (ዕብራይስጥ የፎንቄውያንን ፊደላት ይጠቀማል)

ሠ. ሞአባዊ (ሜሻ ድንጋይ፣ 840 ዓ.ዓ)

ረ. አራምኛ (የፋርስ ሰፊ ግዛት ብሔራዊ ቋንቋ ነበር ዘፍ. 31፡47 ጥቅም ላይ የዋለ [2 ቃላት]፤ ኤር. 10፡11፤ ዳን. 2፡4ለ-6፤ 7፡28፤ እዝራ 4፡8-6፡18፤ 7፡12-26 እንዲሁም በአይሁድ ይነገር ነበር፣ በአንደኛው ክፍለ ዘመን በፍልስጥኤም)

የዕብራይስጡ ቋንቋ "የከነዓን ከንፈር" ተብሎ ይጠራል በኢሳ. 19፡18። እሱም በመጀመሪያ የሚጠራው "ዕብራይስጥ" ተብሎ ነው፣ በጥበብ መጽሐፍ መግቢያ ላይ (የቢን ሲራክ ጥበብ) በግምት 180 ዓ.ዓ (እና ሌሎች የጥንት ስፍራዎች፣ *መልሕቅ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት*፣ ቅጽ 4፣ ገጽ 205)። እሱም በእጅጉን የሚዛመደው ከሞአባዊ እና በዩጋሪቲ በሚነገረው ቋንቋ ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ የሚገኙት ጥንታዊ ዕብራይስጥ ምሳሌዎች የሚሆኑት

1. የጋዚር ዘመን መቁጠሪያ፣ 925 ዓ.ዓ (የትምህርት ቤት ልጅ ጽሑፍ)
2. የሲሎም ጽሑፍ፣ 705 ዓ.ዓ (የዋሻ ጽሑፎች)
3. ሰማሪያዊ ኦስትራካ፣ 770 ዓ.ዓ (በተሰባበረ ሸክላ የግብር መዝገቦች)
4. ላቺሽ ደብዳቤዎች፣ 587 ዓ.ዓ (የጦርነት መገናኛዎች)
5. የመቃብያን ሳንቲሞች እና ማኅተሞች
6. አንዳንድ የሙት ባሕር ጥቅል ጽሑፎች
7. የቁጥር ጽሑፎች ("ቋንቋዎች [ዕብራይስጥ]፣ ኤቢዲ 4፡203)

እሱ፣ እንደሌሎቹ ሴማዊ ቋንቋዎች፣ ከሦስት ተናባቢዎች የተመሠረቱ ቃላት ባሕርይ ያለው ነው (የሦስት ተናባቢ ሥሮች)። እሱ የማይተጣጠፍ ቋንቋ ነው። ባለ ሦስት ተናባቢ የቃሉን ዋነኛ ፍቺ ይይዛል፣ ቅድመ ቅጥያ፣ ድሕረ ቅጥያ ወይም የውስጥ ምዕላዶች (ተጨማማሪዎች) ሲደረጉበት፣ ይሄም የአገባቡን ተግባር ያመለክታል (አናባቢዎች ኋላ ላይ ነው የሚጨመሩት፣ ሱ ግሪን፣ የሥነ ቋንቋ (ሊንጉስቲክ) ትንታኔ የዕብራይስጥ ቅዱሳት መጻሕፍት፣ ገጽ 46-49)።

የዕብራይስጥ መዝገበ ቃላት በስድ ንባብና በቅኔ መካከል ልዩነትን ያመለክታል። የቃላት ትርጉሞች ከቃላዊ ሥርወ ቃል ጋር ይያያዛል (ከሥነ ቋንቋዊ መነሻ ያልሆነ)። የቃላት አግባብ እና የድምጽ አግባብ የተለመዱ ናቸው (ፓሮኖማሲያ)።

II. የአንቀጽ ገጽታዎች

ሀ. ግሦች

ሁነኛው የቃላት ቅደም ተከተል የሚሆነው ግሥ፣ ተውላጠ ስም፣ ባለቤት (ከአጉሊዎች ጋር)፣ ተሳቢ (ከአጉሊዎች ጋር)። መሠረታዊው ምልክት አልባ ግሥ የተጠናቀቀው ነው፣ ተባዕታይ ጾታ፣ ነጠላ ቁጥር ቅርጽ ነው። የዕብራይስጥና አራማዊ የቃላት ዝርዝሮች የተቀመሩት እንዲህ ነው። ግሦች ረብተው የሚያሳዩት

1. ቁጥር— ነጠላ፣ የብዙ፣ ሁለቱንም
2. ጾታ— ተባዕታይ እና አንስታይ (ገለልተኛ የለውም)
3. ሁኔታን— አመላካች፣ ሁኔታን ገላጭ፣ ተተኳሪ (አስገዳጅ) በምስያነት ከዘመናዊው የምዕራባውያን ቋንቋ ጋር፣ የድርጊቱ ዝምድና ከተጨባጩ ጋር ነው)
4. ጊዜ (ገጽታ)

   ሀ. የተጠናቀቀ፣ ይህም የሚያሳየው የተጠናቀቀ፣ የሱም አግባብ አጀማመሩን፣ ቀጣይነቱን፣ እና አደማደሙን ነው የአንድን ድርጊት። ይህ ቅርጽ ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው ለሀላፊ ጊዜ ነው፣ ነገሩ የተደረገበት።

   ጄ. ዋሽ ዋትስ፣ *በዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን አገባብ ጥናት* ላይ፣ የሚለው

   "በተጠናቀቀ የተገለጠ የነጠላ አጠቃሎሽ እንደ ትክክለኛ ይወሰዳል። ያልተጠናቀቀ ምናልባት ሊሆን የሚችለውን የምስል ሁኔታ ያሳያል ወይም የሚፈለገውን ወይም ተስፋ የሚደረገውን ነው፣ ነገር ግን የተጠናቀቀው እንደ ትክክለኛ፣ እውናዊና ርግጠኛነት ያመለክታል" (ገጽ 36)።

   ኤስ. አር. ድራይቨር፣ *የዕብራይስጥ ጊዜያት አጠቃቀም ጽሑፍ* እንዲህ ይገልጸዋል፡

   "የተጠናቀቀው ጥቅም ላይ የሚውለው ድርጊትን ለማመልከት ነው፣ እሱም ወደፊት ሊያዝ የሚችለውን ሲሆን፣ ግን የሚታየው ጥገኛ ሆኖ ነው፣ በዚህ በማይለወጥ ውሳኔ ያለው ፍቃድ፣ እሱም ምናልባት የሚናገረው በርግጥ የተከናወነውን ነው፡ እንዲህም ውሳኔው፣ ተስፋው፣ ወይም ደንቡ፣ በተለይም መለኮታዊ የሆነው፣ በተደጋጋሚ የሚነገረው በተጠናቀቀ ጊዜ ነው" ገጽ17፣ ምሳ. የተጠናቀቀ ትንቢታዊ)።

   ሮበርት ቢ. ቺሾልም፣ ጁኣር. ከማብራሪያ እስከ መግለጫ፣ ይሄንን የግሥ ቅርጽ በዚህ መንገድ ይገልጸዋል፡

   "...ሁኔታውን ከውጭ በኩል ይመለከተዋል፣ በጥቅሉ። ቀላል ሐቅን እንደሚገልጽ፣ ድርጊትም ቢሆን ወይም ሁኔታ (የሕላዌ ነገር ወይም የአዕምሮ)። ለድርጊቶች ጥቅም ላይ ሲውል፣ እሱ ዘወትር ድርጊትን የሚመለከተው እንደ ተጠናቀቀ ነው፣ ከአንደበተ ርቱዕነት አኳያ፣ ከተናጋሪው ወይም ከተራኪው (እሱም ቢሆንም ሆነ ባይሆንም፣ የተጠናቀቀ ሐቅ ወይም

እውነታ ዋናው ነጥብ አይደለም)። የተጠናቀቀው የድርጊት/ሁኔታ ኢጋዥ ሊሆን ይችላል፣ ያለፈውን፣ የአሁኑን ወይም የወደፊቱን። ከላይ እንደተጠቀሰው፣ የጊዜ ቅምብብ፣ እሱም፣ ማንም የተጠናቀቀውን የሚተረጉምበት ላይ ተጽዕኖ የሚኖረው፣ ወደ እንግሊዝኛ መሰል፣ ጊዜ-ተኮር ቋንቋ፣ የግድ መወሰን የሚኖርበት ከዐውደ ጽሑፉ ነው" (ገጽ 86)።

ለ. ያልተጠናቀቀ፣ ይህ የሚያሳየው በእድገት ላይ ያለ ድርጊትን ነው (ያልተጠናቀቀ፣ ተደጋጋሚ፣ ቀጣይ ወይም ተያያዥነት ያለው)፣ የዘወትር እንቅስቃሴው ወደ ግቡ ነው። ይህ ቅርጽ ጥቅም ላይ የሚውለው ለአሁንና ለትንቢት ድርጊት ነው።

ጂ. ዋሽ ዋትስ፣ *በዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን አገባብ ጥናት* ላይ፣ የሚለው

"ሁሉም ያልተጠናቀቁት የሚወክሉት ያልተጠናቀቀ ሁኔታን ነው። እነሱም አንድም የተደጋገሙ ወይም በእድገት ላይ ያሉ ወይም ተያያዥ የሆኑ ናቸው። በሌላ አገላለጽ፣ ወይም በከፊል እድገት ያለው፣ ወይም በከፊል የተረጋገጠ። በሁሉም ጉዳዮች እነሱ ከፊል ናቸው፣ በተወሰነ መልኩ፣ ማለትም ያልተጠናቀቀ" (ገጽ 55)።

ሮበርት ቢ. ቺሾልም፣ ጁኒየር. ከማብራሪያ እስከ *መግለጫ*፣ የሚለው

"ያልተጠናቀቀን ጠቀሜታ በነጠላ ጽንሰ ሐሳብ ለመቀነስ አስቸጋሪ ነው፣ እሱም ሁለቱንም ገጽታዎችና ሁኔታዎች ስለሚያካልል። አንዳንድ ጊዜ ያልተጠናቀቀ ጥቅም ላይ የሚውለው በአመላካች ሁኔታ ነው እናም ተጨባጭ መግለጫ ይሰጣል። በሌላ ጊዜ እሱ አንድን ድርጊት የሚመለከተው በተያያዥነት፣ በመላምታዊ፣ በተያያዥ፣ ሊሆን በሚችል እና በመሳሰለው ነው" (ገጽ 89)።

ሐ. ተጨማሪ የሆነው ዋው፣ እሱም ግሡን ያያዘው ከፊተኛው ግሥ(ሦች) ድርጊት ጋር ነው።

መ. ተተኳሪ፣ እሱም የተመሠረተው በተናጋሪው ፍቃድ ላይ እና በሰሚው ብቃታዊ ድርጊት ላይ ነው።

ሠ. የጥንታዊ ዕብራይስጥ ትልቁ ጽሑፍ ብቻ ሥልጣናዊ የሆነ የጊዜ አስረጅዎችን ሊወስን የሚችለው።

ለ. ሰባቱ የአረባብ ቅርጾች እና የእነሱ መሠረታዊ ፍቺ። በተጨባጭ እነዚህ ቅርጾች የሚሠሩት እርስ በርሳቸው በጽሑፍ በመያያዝ ነው፣ እናም መለያየት አይኖርባቸውም።

1. (ቃል)፣ ዋነኛው የተለመደውና መሠረታዊ የሆነ የሁሉም ቅርጾች። እሱም የሚገልጸው ቀላል ድርጊትን ወይም የመሆን ሁኔታን ነው። ምንም ዓይነት ምክንያታዊነት ወይም የተለየነት አልተደረገም።
2. ኒፋል፣ ሁለተኛው በጣም የተለመደው ቅርጽ። እሱም ዘወትር ተገብሮ ነው፣ ግን ይህ ቅርጽ እንደ ተገላቢጦሽና አገናዛቢ ይሠራል። እሱም ደግሞ ምንም ምክንያታዊነት ወይም የተለየነት አልተደረገበትም።
3. ፒኤል፣ ይህ ቅርጽ ድርጊታዊ ሲሆን የአንድን ድርጊት ወደ ተግባር መምጣት የሚገልጽ ነው። መሠረታዊ የሆነው የቃል ግንድ ወደ ሕላዌ አቋም ያድጋል ወይም ይስፋፋል።
4. ፑአል፣ ይህ ተገብሮ ሲሆን የፒኤል ተቃርኖ አካል ነው። እሱም ዘወትር የሚገለጸው በቦዝ አንቀጽ ነው።
5. ሂዝፒል፣ እሱም አገናዛቢ ወይም የተገላቢጦስ ግንድ (የግሥ) ነው። እሱም የሚገልጸው የፒል ግንድን የድርጊት ደጋጋሚነት ወይም የጊዜ መጠን ነው። አልፎ አልፎ የተገብሮ ቅርጽ ሆዝፓል ተብሎ ይጠራል።
6. ሂፊል፣ የምክንያታዊው ግንድ የድርጊት ቅርጽ ከፒል ጋር ይቃረናል። የፈቃጅነት ገጽታ ሊኖረው ይችላል፣ ግን ዘወትር የሚያመለክተው የአንድን ሁነት ምክንያት ነው። ኤርነስት ጄኒ፣ የጀርመን ዕብራይስጥ ሰዋሰዋዊ ፣ እንደሚያምነው ፒኤል አንድ ነገር ወደ መሆን እንደሚመጣ ሲገልጽ ሂፋል የሚያሳየው እንዴት እንደሆነ ነው።
7. ሆፋል፣ ተገብሮ የሂፋል ተቃርኗዊ አካል ነው። እነዚህ የመጨረሻዎቹ ሁለት ግንዶች ከሰባቱ ግንዶች በአነስተኛ ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው።

አብዛኛው ይህ መረጃ የመጣው *የዕብራይስጥ ቅዱስ መጽሐፋዊ አገባብ መግቢያ*፣ በብሩስ ኬ. ዋልትኬ እና ኤም. አ ኮኖር፣ ገጽ 343-452 ላይ ነው።

የወኪልና የምክንያት መግለጫ። የዕብራይስጥን የግሥ ሥርዓት ለመረዳት አንደኛው ቁልፍ፣ እሱን እንደ የድምጸት ዝምድና ፈርጅ መመልከት ነው። አንዳንድ ግንዶች ከሌሎች ግንዶች ጋር ይቃረናሉ (ማለትም፣ ቃል - ኒፋል፤ ፒኤል - ሂፋል)

ከታች ያለው መግለጫ የግሥ ግንዶችን መሠረታዊ ተግባር ከምክንያትነት አኳያ ለማሳየት ይሞክራል፡፡

| **ድምጸት ወይም ርዕሰ ጉዳይ** | **ሁለተኛ ወኪል የሌለው ወኪል** | **ንቁ ሁለተኛ ሁለተኛ ወኪል** | **ተገብሯዊ ሁለተኛ ወኪል** |
|---|---|---|---|
| የድርጊት | *ቃል* | *ሂፊል* | *ፒይል* |
| መካከለኛ ተገብሮ | *ኒፋል* | *ሆፋል* | *ፑኣል* |
| አገናዛቢ/የተገላቢጦሽ | *ኒፋል* | *ኒፊል* | *ሂዝፒል* |

ይህ መግለጫ የተወሰደው በጣም ጥሩ ከሆነው ማብራሪያ ከግሣዊ ሥርዓት ሲሆን፣ በአዲሱ የአካዲያን ጥናት እይታ ነው (ብሩስ ኬ. ዋልትኬ፣ ኤም. አ ኮነር፣ *የዕብራይስጥ ቅዱስ መጽሐፋዊ አገባብ መግቢያ*፣ ገጽ 354-359)።

አር. ኤች. ኬኒት፣ የዕብራይስጥ ጊዜያት አጭር ሐተታ፣ አስፈላጊውን ማስጠንቀቂያ ይሰጠናል።

"በማስተማር ላይ እንዳገኘሁት፣የተማሪዎች ዋነኛ ችግራቸው በዕብራይስጥ ግሦች የሚሆነው፣ ፍችዎቻቸውን ማግኘት ነው፣ በራሳቸው በዕብራውያን አዕምሮ ውስጥ ያለውን፤ ይህም ማለት፣ ለእያንዳንዱ የዕብራይስጥ ጊዜ (የግሥ) የሆነ ቁጥር ያለው የላቲን ወይም እንግሊዝኛ ቅርጾችን የመጠቀም ዝንባሌ መኖሩ ነው፣ እኩል ይሆናል ተብሎ የሚገመተውን፣ እሱም ያ የተለየ ጊዜ ምናልባት እንደሁኔታው የሚተረጎም ይሆናል። ውጤቱም በርካቶቹን የትርጉም ድባቦች መሳት ነው፣ እሱም ሕይወትና ጥንካሬ ለብሉይ ኪዳን የሚሰጠውን።

የዕብራይስጡን ግሦች አጠቃቀም አስቸጋሪ የሚያደርገው በአንጻር ላይ ብቻ ነው፤ ስለዚህም ከእኛ ፈጽሞ ይለያል፣ እሱም ዕብራውያን አንድን ድርጊት ከሚመለከቱበት፤ ጊዜው፣ ከእኛ ጋር ያለው ቀዳሚ ግምት ውስጥ የሚገባ ነው፣ እሱም በዛው ቃል፣ 'ጊዜ' የሚያሳየው ለእነሱ እንደ ሁለተኛ ጠቀሜታ ነው። እሱም፣ የሚጠቅመው ተማሪው ጥርት አድርጎ እንዲረዳ ያደርገዋል፣ ይህም የላቲኑንም ሆነ የእንግሊዝኛውን ቅርጽ ሳይሆን፣ እነሱም እያንዳንዱን የዕብራይስጥ ጊዜ ለመተርጎም፣ ነገር ግን የእያንዳንዱ ድርጊት ገጽታ፣ ልክ በዕብራዊው አዕምሮ እንደታሰበው ባለ መልኩ።

'ጊዜያት' የሚለው ስም በዕብራይስጥ ግሦች ጥቅም ላይ ሲውል ያሳስታል። የዕብራይስጥ 'ጊዜያት' ጊዜውን የሚገልጽ አይደለም ነገር ግን የአንድን ድርጊት ሁኔታ ነው። በርግጥ እዚህጋ ለማደናገር አይደለም፣ 'ሁኔታ' የሚለውን ቃል በምንጠቀምበት ጊዜ፣ እሱም በስምም ሆነ በግሥ ላይ፣ 'ሁኔታዎች' ከ'ጊዜያት' በተሻለ መልኩ ያሳያሉ። ዘወትር መታሰብ ያለበት የዕብራይስጥን ግሥ አንዳች ገደብ ሳያደርጉበት ወደ እንግሊዝኛ ለመተርጎም አለመቻሉን ነው፣ (ጊዜን በተመለከተ) ይህም ሙሉ ለሙሉ በዕብራይስጥ የሌለ ነው። ጥንታዊዎቹ ዕብራውያን አንድን ድርጊት በሀላፊ ጊዜ፣ በአሁን ጊዜ፣ ወይም በትንቢት ጊዜ አያውቁትም፣ በተጠናቀቀ እንጂ፤ ማለትም፣ የተጠናቀቀ ወይም ያልተጠናቀቀ ማለትም፣ በእድገት ሂደት ላይ እንዳለ። አንድ የዕብራይስጥ ጊዜ (የግሥ) ከተጠናቀቀ፣ የሀላፊ የተጠናቀቀ፣ ወይም የእንግሊዝኛ የትንቢት ጊዜ ጋር የመሳሰሏል በምንልበት ጊዜ፣ የእሱ የዕብራውያን አስተሳሰብ፣ እንደ የተጠናቀቀ፣ የሀላፊ የተጠናቀቀ፣ ወይም የትንቢት ማለታችን አይደለም፣ ነገር ግን እንዲያው በእንግሊዝኛ ተተርጉሟል ማለታችን ነው። የአንድን ድርጊት ጊዜ ዕብራውያን በምንም ዓይነት የግሥ ቅርጽ ሊገልጹት አይሞክሩም" (መቅድም እና ገጽ 1)።

ለሁለተኛው መልካም ማስጠንቀቂያ፣ ሱ ግሩም፣ የዕብራይስጥ ቅዱስ መጽሐፋዊ ሥነ-ቋንቋ ትንታኔ፣ የሚያሳስበን፣

"ምንም ዓይነት የማወቂያ መንገድ የለውም፣ የዘመናዊ ሊቃውንት የሴማዊ መስኮችን ዳግም ግንባታ ቢሆን እንዲሁም የጥንታዊ ምውት ቋንቋዎች የአገባብ ዝምድናዎች ቢሆን፣ የራሳቸው የስሜት ነጸብራቅ፣ ወይም የገዛ ራሳቸው አፍ መፍቻ ቋንቋ፣ ወይንም ደግሞ እነዚህ መስኮች በጥንታዊ ዕብራይስጥ ይኖሩ እንደሆነ" (ገጽ 128)።

ሐ. ሁኔታዎች (እነዚህ ከዘመናዊ የምዕራባውያን ቋንቋዎች የተቀዱ ምስያዎች ናቸው)

1. እሱ ሆኗል፣ እየሆነም ነው (አመላካች)፣ ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው (የተጠናቀቀ ጊዜ ወይም ቦዝ አንቀጽ (ሁሉም ቦዝ አንቀጾች አመላካች ናቸው)።
2. ይሆናል፣ ሊሆን ይችላል (ሁኔታ ገላጭ)

ሀ. የተመለከተ ያልተጠናቀቀ ጊዜን ይጠቀማል

(1) ውህደት ያለው (ኤች የተጨመረበት)፣ አንደኛ መደብ ያልተጠናቀቀ እሱም በእውነቱ ፍላጎትን፣ ጥያቄን፣ በራስ መተማመንን የሚገልጽ (ማለትም፣ በተናጋሪው ፍላጎት የሆነ ድርጊት)

(2) የግሥ ቅርጽ (ውስጣዊ ለውጥ) ሦስተኛ መደብ ያልተጠናቀቀ (ሦስተኛ መደብም ሊሆን ይችላል፣ በአሉታዊ ዓረፍተ ነገሮች) እሱም በተለምዶ የሚገልጸው ጥያቄን፣ ፍቃድን፣ ማስጠንቀቂያን፣ ወይም ምክርን ነው

ለ. የተጠናቀቀ ጊዜን ይጠቀማል ከሉ እና ሉሊ ጋር

እነዚህ ግንባታዎች ከሁለተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች፣ በኮኔ ግሪክ ተመሳሳይ ናቸው። የሐሰት መግለጫ (protasis ፕሮቴሲስ) የሚፈጠረው ከተሳሳተ ድምዳሜ ነው (apodosis አፖዶሲስ)።

ሐ. ያልተጠናቀቀ ጊዜንና ሉን ይጠቀማል

ይዘትና ሉ፣ እንዲሁም የትንቢት ማሳያ፣ ይሄንን ሁኔታ ገላጭ አጠቃቀም ምልክት ያደርጋል። ከጄ. ዋሽ ዋትስ ጥቂት ምሳሌ፣ የዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን ሰዋሰዋዊ አገባብ ጥናት ዘፍ. 13፡6፤ዘዳ. 1፡12፤ 1ኛ ነገሥ. 13፡8፤ መዝ. 24፡3፤ ኢሳ. 1፡18 (ዝኪ. 76-77)።

መ. ዋው - የተገላቢጦሽ/ተከታታይ/አገናዛቢ። ይህ የተለየ የዕብራይስጥ (ከነዓናዊ) የሰዋሰው አገባብ ለዓመታት ታላቅ ውዥንብር ፈጥሯል። እሱም ጥቅም ላይ የዋለው ጽሑፋዊ-ዘውግን በተከተሉ የተለያዩ መንገዶችን በመከተል ነው። የውዥንብሩ ምክንያት የድሮ ሊቃውንት አውሮጳዊ መሆናቸውና ትርጓሜአቸውም በራሳቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ቅኝት በመሆኑ ነው። ይሄም ሲረጋገጥ፣ ለችግሩ የሚጠይቁት የዕብራይስጥ "ታሳቢ" ጥንታዊ፣ የድሮውን ቋንቋ ነው። የአውሮጳ ቋንቋዎች ጊዜ (ጊዜ) ተኮር ግሦች ናቸው። አንዳንዱ ልዩነት እና ሰዋሰዋዊ አንድምታዎች የሚለዩት ዋው በሚለው ፊደል ነው፣ እሱም በተጠናቀቀው ወይም ባልተጠናቀቀ የግሥ ግንድ ላይ ነው። ይህም ድርጊቱ የታየበትን መንገድ ይቀይረዋል።

1. በታሪካዊ ትረካ ግሦቹ አንድ ላይ የሚያያዙት በመደበኛ ፈርጅ ባለ ሰንሰለት ነው።
2. የዋው ቅድመ-ቅጥያ ቀደም ሲል ከነበረው ግሥ (ሦች) የተለየ ዝምድና ያሳያል።
3. ትልቁ ጽሑፍ የሚሆነው ዘወትር የግሡን ሰንሰለት ለማስረዳት ቁልፍ የሆነው ነው። ሴማዊ ግሦች ተለይተው ሊተነተኑ አይችሉም።

ጄ. ዋሽ ዋትስ፣ በዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን የሰዋሰዋዊ አግባብ ቅኝት፣ የሚያስረዳው የዕብራይስጥን የዋው አጠቃቀም ከተጠናቀቀና ካልተጠናቀቀ በፊት ነው (ገጽ 52-53)። የተጠናቀቀ የሀላፊ ሐሳብ መሠረታዊነት እንዳለው፣ የዋው ተጨማሪነትም እሱን ዘወትር ወደ ትንቢት ጊዜ ገጽታ ያመራዋል። ይህም ደግሞ ባልተጠናቀቀውም እውነት ነው፣ እሱም መሠረታዊ ሐሳቡ የአሁን ወይም የትንቢት ጊዜ የሆነው፤ የዋው መጨመር ወደ ሀላፊ ያደርገዋል። ይህ ያልተለመደ የጊዜ ለውጥ ነው፣ የዋው ተጨማሪን የሚገልጸው እንጂ፣ በግሡ በራሱ ላይ የሆነ የመሠረታዊ ትርጉም ለውጥ አይደለም። የዋው የተጠናቀቁ በትንቢት ላይ በደንብ የሚሠሩ ሲሆን፣ የዋው ያልተጠናቀቁ ደግሞ ከትረካ ጋር ደኅና ይሠራሉ (ገጽ 54፣ 68)።

ዋትስ ገለጻውን ይቀጥላል፣

"በዋው መስተዋድድና በዋው ተከታታይ መካከል ላለው መሠረታዊ ልዩነት የሚከተሉት ትርጓሜዎች ቀርበዋል፡

1. ዋው መስተዋድድ ዘወትር የሚከሰተው ትይዩዎችን ለማመላከት ነው።
2. ዋው ተከታታይ ዘወትር የሚከሰተው ቅደም ተከተልን ለማመላከት ነው። እሱም በተከታታይ ያልተጠናቀቁ ላይ ጥቅም ላይ የዋለ ብቸኛ ቅርጽ ነው። ባልተጠናቀቁ መካከል ያለው ዝምድና በእሱ የተያያዘው ምናልባት በጊዜ ቅደም ተከተል፣ በአመክኖአዊ (ሎጂክ) ውጤት፣ በአመክኖአዊ ሳቢያ፣ ወይም በአመክኖአዊ ተቃርኖ ነው። በሁሉም ጉዳዮች ቅድም ተከተል አለ" (ገጽ 103)።

ሠ. ያልተጠናቀቀ - ሁለት ዓይነት ያልተጠናቀቁ አሉ

1. ፍጹም ያልተጠናቀቀ፣ እነሱም "ጠንካራ፣ ነጻ፣ አስገራሚ ገለጻዎች እነሱም ለድራማዊ ውጤት ጥቅም ላይ የዋሉ… እንደ ባለቤት፣ እሱ የተጻፈ ግሥ የለውም፣ 'የመሆን' ግሥ፣ በርግጥ ግልጽ ነው፣ ነገር ግን ቃሉ በድራማዊ መልኩ ብቻውን ነው የቆመው፣" (ጄ. ዋሽ ዋትስ፣ በዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን የሰዋሰዋዊ አገባብ ቅኝት፣" ገጽ 92)።
2. ያልተጠናቀቀ አገነባብ፣ እነሱም "በሰዋሰዋዊ የሚዛመዱት በዓረፍተ ነገራቸው ከመስተዋድድ፣ አገናዛቢ ተውላጠ ስም፣ እና ያገነባብ ዝምድናዎች ጋር ነው" ገጽ 91)።
   ጄ. ዌንግሪን፣ *ለጥንታዊ ዕብራይስጥ ተግባራዊ ሰዋሰው፣* ተቃርኗዊውን አቋም ይገልጻል፡
   > "ሁለት (ወይም ከዚያም በላይ) ቃላት በጣም በሚያያዙበት ጊዜ፣ ሁለቱ አንድ የተዋሐደ ሐሳብ ይፈጥራሉ፣ ጥገኛው ቃል (ቃላት) የሚሆነው (የሚሆኑት) በግንባታ አቋም ላይ ናቸው ይባላል" (ገጽ 44)።

ረ. ጠያቂዎች
1. እነሱ ዘወትር በዓረፍተ ነገር መጀመሪያ ላይ ይከሰታሉ።
2. ትርጓሜአዊ ጠቀሜታ
   ሀ. ሃ - ምላሽን አይጠብቅም
   ለ. ሃሎ - ጸሐፊው "አዎን" የሚል ምላሽን ይጠብቃል

አሉታዎች
1. እነሱም ዘወትር ከሚቃረኑት ቃላት በፊት ይከሰታሉ።
2. በጣም የታወቀው አሉታ ሎ ነው።
3. አል የሚለው ቃል ያለው ተያያዥ ፍቺ አለው፣ እሱም ጥቅም ላይ የሚውለው ከውህደታዊ እና ከግሥ ቅደም ተከተል ጋር ነው።
4. ሌብሂልቲ የሚለው ቃል፣ ፍቺው "በመሠረቱ… አይደለም፣" የሚል ሲሆን ካልተወሰኑ ጋር ጥቅም ላይ ይውላል።
5. ኢን የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የሚውለው ከቦዝ አንቀጽ ጋር ነው።

ሰ. ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች
1. አራት ዓይነት ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች ሲኖሩ እነሱም በመሠረቱ ከኮኔ ግሪክ ጋር ትይዩ ናቸው።
   ሀ. አንድ ነገር ሊፈጸም እንደሚሆን ወይም እንደሚታሰብ አድርጎ መገመት (አንደኛ መደብ በግሪክ)
   ለ. አንድ ነገር ከሐቅ ጋር የተቃረነ፣ የሱም ፍጻሜ የማይቻል (ሁለተኛ መደብ)
   ሐ. አንድ ነገር የሚቻል፣ እንዲያውም ደግሞ የመሆን ዕድል ያለው (ሦስተኛ መደብ)
   መ. አንድ ነገር ያነሰ የመሆን ዕድል ያለው፣ ስለዚህም፣ መፈጸሙ የሚያጠራጥር (አራተኛ መደብ)
2. ሰዋሰዋዊ መለያዎች
   ሀ. እውነተኛ ወይም ርግጠኛ ሁኔታው ይሆናል ብሎ የሚገመተው፣ አመልካች የተጠናቀቀ ወይም ቦዝ አንቀጽ ዘወትር ሲጠቀም ነው፣ እንዲሁም ቀዳሚ ቃሉ የሚታወቀው በ
      (1) ኢም
      (2) ኪ (ወይም አሸር)
      (3) ሂን ወይም ሂኔህ
   ለ. ከሐቅ ጋር የሚቃረነው ሁኔታ ዘወትር የሚጠቀመው የተጠናቀቀ ገጽታ ግሥ ወይም ቦዝ አንቀጽ እሱም ከሉ ወይም ሉሊ መቅድማዊ ቦዝ አንቀጽ ጋር ይሆናል
   ሐ. በጣም የይሆናሉ ሁኔታ ዘወትር የሚጠቀመው ያልተጠናቀቀ ግሥ ወይም በቅድመ ቃሉ ያለ ቦዝ አንቀጽ ሲሆን፣ ዘወትር፣ ኢም ወይም ኪ እንደ መግቢያ ቦዝ አንቀጾች ጥቅም ላይ ይውላሉ
   መ. በአነስተኛ የይሆናሉ ሁኔታ የሚጠቀመው ያልተጠናቀቀ ሁኔታ ገላጭ፣ እሱም በቅድመ ቃሉ እና ዘወትር የሚጠቀመውም ኢም እንደ መቅድማዊ አገባብ ነው፡፡

# ሐተታው ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ አሕጽሮተ ቃላት

| | |
|---|---|
| AB | መልሕቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ሐተታ፣ ዊሊያም ፎክስ ዌል ኦልብራይት እና ዳቪድ ኖኤል ፍሪደም ያዘጋጁት |
| ABD | መልሕቅ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት (6ቅጾች)፣ ዴቪድ ኖኤል ፍሪደም ያዘጋጀው |
| AKOT | ትንተናዊ ቁልፍ የብሉይ ኪዳን በጆን ጆሴፍ አውንስ |
| ANET | ጥንታዊ የቅርብ ምስራቅ ጽሑፎች፣ ጀምስ ቢ. ፕሪቻርድ |
| BDB | እብራይስጥ እና እንግሊዝኛ ሥርወ-ቃል በብሉይ ኪዳን በኤፍ. ብራውን፣ ኤስ. አር. ድራይቨር እና ሲ. ኤ. ብሪግስ |
| ቢሄስ | ቢብላ ሄብሪካ ስቱትጋርቴንሲያ፣ ጂቢስ፣ 1997 |
| IDB | የተርጓሚ መዝገበ ቃላት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ (4 ቅጾች)፣ አዘጋጅ ጆርጅ ኤ. በትሪክ |
| ISBE | ዓለም አቀፍ መደበኛ የመጽሐፍ ቅዱስ እንሳይክሎፔድያ (5 ቅጾች) አዘጋጅ ጀምስ ኦር |
| JB | የሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ |
| JPSOA | ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ማሶረቲክ ጽሑፍ፡ አዲስ ትርጉም (የአይሁድ የሕትመት ማኅበረሰብ የአሜሪካ) |
| KB | የእብራይስና የአራማዊ ሥርወ-ቃል የብሉይ ኪዳን በሉድዊግ ኮህለር እና ዋልተር ባዉምጋርትነር |
| LAM | መጽሐፍ ቅዱስ ከጥንታዊ የምስራቅ የብራና ጽሑፎች (ፓሺታ) በጆርጅ ኤም ላምሳ |
| LXX | ሰባ ሴፕቱዋጊንት (የግሪክ እንግሊዝኛ) በ ዞንደርቫን፣ 1970 |
| MOF | አዲሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በጀምስ ሞፋት |
| MT | ማሶረቲክ እብራይስጥ ጽሑፍ |
| NAB | አዲሱ የአሜሪካ መጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፍ |
| NASB | አዲሱ የአሜሪካ መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ |
| NEB | አዲሱ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ |
| NET | አእትመጽሐፍ ቅዱስ፡ አዲሱ የእንግሊዝኛ ትርርጉም፣ ሁለተኛ ቤታ ትርጉም፡፡ |
| NIDOTTE | አዲሱ ዓለም አቀፍ መዝገበ ቃላት የብሉይ ኪዳን ሥነመለኮት እና ትርጓሜ (5 ቅጾች)፣ አዘጋጅ ዊሊም ኤ. ቫንጀሚረን |
| NRSV | አዲሱ የተከለሰው መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ |
| NIV | አዲሱ ዓለም አቀፍ ቅጂ |
| NJB | አዲሱ የየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ |
| OTPG | የብሉይ ኪዳን የምስጋና መመሪያ በቶድ ኤስ. ቤል፣ ዊሊየም ኤ. ባንክስ እና ኮሊን ስሚዝ |
| REB | የተከለሰ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ |
| RSV | የተከለሰ መደበኛ ቅጂ |
| SEPT | ሴፕትዋጊንት (ግሪክ-እንግሊዝኛ) በዞንደርቫን፣ 1970 |
| TEV | የአሁን እንግሊዝኛ ቅጂ ከተባበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ኅብረተሰብ |
| YLT | የወጣቶች ጽሑፋዊ ትርጉም የመጽሐፍ ቅዱስ በሮበርት ያንግ |
| ZPBE | ዞንደርቫን ስእላዊ መጽሐፍ ቅዱስ እንሳይክሎፔድያ (5ቅጽ)፣ አዘጋጅ ሜሪል ሲ. ቴኒ |

# የጸሐፊው መልእክት፡ይህ ሐተታ እንዴት ይረዳዎታል?

*መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጓሜ አስተውሎት እና መንፈሳዊ ሂደት ያለበት የጥንቱን ተመስጧዊ ጸሐፍት በዚህ መልኩ ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን መልእክት በዘመናችን ለመረዳትና ለመተግበር የተዘጋጀ ነው።*

*መንፈሳዊ ሂደቱ ወሳኝ እና ለመግለጽ አስቸጋሪ ነው። ለእግዚአብሔር መሰጠትንና ግልጽነትን ይጠይቃል።*(1) *ለእሱ፣* (2) *እሱን ለማወቅ እና* (3) *እሱን ለማገልገል ጉጉትን ይፈልጋል። ይህ ሂደት ደግሞ ጸሎት፣ ንስሐ እና የሕይወትን አኗኗር ለመለወጥ ፍቃደኝነትን ይጠይቃል። በትርጓሜ ሂደት መንፈስ ወሳኝ ነው፣ ዳሩግን ትሑታንና፣ የእግዚአብሔር ሰዎች የሆኑ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን በተለየ መልኩ እንደሚረዱት ምስጢር ነው።*

*የማስተዋሉን ሂደት ለመግለጽ ቀላል ነው። እኛ ለጽሑፉ የማናወላውልና ተገቢ ልንሆን፣ በራሳችን ወይም በእምነት ክፍላችን አስተሳሰብ ላንወሰድ ይገባል። ሁላችንም በታሪካዊ ሁኔታዎች ውስጥ ነን። ማናችንም ብንሆን ጉዳዩ የማይነካንና ገለልተኛ ተርጓሚዎች አይደለንም። ይህ ሐተታ በጥንቃቄ ማስተዋል ሂደት የተቀመረ ሦስት የትርጓሜ መርሖዎችን አዋቅሮ የያዘና አድልዎአዊ የሆኑ አስተሳሰቦቻችንን ለመቅረፍ የሚረዳ ነው።*

## የመጀመሪያው መርሕ

*የመጀመሪያው መርሕ የቅዱሱ መጽሐፍ ክፍል የተጻፈበትን ታሪካዊ መቼት ማጤን ነው፤ እንዲሁም የጸሐፊውም የወቅቱ ታሪካዊ ሁኔታ ይታያል። ዋነኛው ጸሐፊ ለማስተላለፍ የፈለገው ተግባርም ሆነ መልእክት አለው። ጽሑፉ ለእኛ አንዳች የሚሆን ዋነኛው፣ ጥንታዊው፣ ተመስጧዊው ጸሐፊ የጻፈው አይደለም ማለት ፈጽሞ አይደለም። የእሱ ፍላጎት የእኛ ታሪካዊ፣ ስሜታዊ፣ ባህላዊ፣ ግላዊም ሆነ ክፍለ ሃይማኖታዊ ፍላጎት ይደለም ቁልፉ ነው። ተግባር ዋነኛው ጓደኛ ነው፣ በትርጓሜ ሰዓት፣ ዳሩግን ሁልጊዜ ትክክለኛ ትርጓሜ ተግባርን መቅደም ይኖርበታል። እሱም ግሞ የሚያጠናክረው እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፍ አንድ እና አንድ ብቻ ፍቺ እንዲኖረው ነው። ይህም ፍቺ የሚሆነው ዋነኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊ በመንፈስ ተመርቶ በዘመኑ ሊለው የፈለገውና ሊገናኝበት ያለውን ነው። ይሄው አንዱ ፍቺ ምናልባት በርካታ አማራጭ አግባቦች ለተለያዩ ባህሎችና ሁኔታዎች ሊኖረው ይችላል። እነዚህ አገባቦች ግን ከዋነኛው ጸሐፊ ማእከላዊ እውነት ጋር የተገናኙ መሆን ይኖርባቸዋል። በዚህን ምክንያት፣ ይህ የጥናት መመሪያ ሐተታ የተነደፈው ለእያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ መግቢያ እንዲሆን ነው።*

## ሁለተኛው መርሕ

*ሁለተኛው መርሕ ሥነ ጽሑፋዊ አሀዶችን መለየት ነው። እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ሙሉ ዶሴ ነው። ተርጓሚዎች አንደኛውን የእውነት ገጽታ ሌሎች የመነጠል መብት የላቸውም። ስለሆነም እያንዳንዱን የመጽ/ፍ ቅዱስ ክፍል ከመተርጎማችን በፊት የሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ ዓላማ መረዳት ይኖርብናል። ተናጠላዊ የሆኑት ክፍሎች ማለትም ምእራፎች፣ አንቀፆች፣ ወይም ቁጥሮች ሙሉው ክፍል ያላለውን የማይሉ ላይሆኑ ይችላሉ። ርጓሜ ከሙሉ አጠቃላይ አቀራረብ ወደ ዝርዝር ክፍላዊ አቀራረብ መሆን ይኖርበታል። ስለሆነም የዚህ የጥናት መመሪያ ሐተታ የተነደፈው ተማሪዎች የእያንዳንዱን ጽሑፋዊ ክፍል በአንቀጽ በመተንተን እንዲገነዘቡት ለመርዳት ነው። የአንቀጽን ሆነ የምእራፍ ክፍሎች ተመስጧዊ አይደሉም፤ ነገር ግን የዋና ሐሳብ ክፍሎችን ለመገንዘብ ያስችሉናል። ዓረፍተ ነገርን፣ ንዑስ አንቀጽን፣ ሐረግን ወይም በቃል ደረጃ ሳይሆን በሙሉ አንቀጽ ደረጃ መተርጎም፣ የመጽሐፍ ቅዱሱን ጸሐፊ ዋነኛ ሐሳብ መረዳት ቁልፉ ነገር ነው። አንቀጾች ብዙውን ጊዜ የተመሠረቱት አንድነት ባለው ርእስ፣ ማለትም ጭብጥ ወይም መሪ ዓረፍተ ነገር በሚባለው ነው።*

*ያንዳንዱ ቃል፣ ሐረግ፣ ንዑስ አንቀጽ፣ እና ዓረፍተ ነገር በአንቀጹ ስጥ ያለው፣ ይብዛም ይነስም ከዋነኛው ጭብጥ ጋር ይገናኛል። ይወስኑታል፣ ስፋፉታል፣ ያብራሩታል፣ ብሎም/ወይም ይጠይቁታል። ለትክክለኛ ትርጓሜ ቁልፉ ነገር የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ መከተል ሆኖ አንቀጽ በአንቀጽ ላይ በተመሠረተ አካሄድ የመጽሐፍ ቅዱሱን መጽሐፍ ባስገኙት በተናጠላዊ የጽሑፍ ክፍል በሚደረግ አግባብ ነው። ይህ የጥናት መመሪያ የሆነ ሐተታ ተዘጋጀው ተማሪዎች አዲሶቹን የእንግሊዝኛ ትርጉሞች እያነጻጸሩ እንዲያዩ ለመርዳት ጭምር ነው። እነዚህ ትርጓሜዎች ተመራጭ የሆኑበት ክንያት የተለያዩ የትርጓሜ ንድፈ-ሐሳቦችን በመጠቀማቸው ነው፡*

1. የተባበሩት መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበረሰብ የግሪክ ቅጂ የተለከሰው አራተኛ እትም የተመጽማ)። ይህ ጽሑፍ በዘመናዊ የጽሑፍ ሊቃውንት አንቀጹ ተሰናድቶለታል።
2. አዲሱ የኪንግ ጀምስ ቅጂ (አኪጀቅ) ቃል በቃል የተደረገ ጥሬ ርጉም ሲሆን የተመሠረተውም የግሪክ የእጅ ጽሑፍ ባህል በሆነው ቴክስተስ ሪሴፕትስ በሚባለው ነው። የአንቀጽ አደራደሩ ከሌሎቹ ትርጉሞች ረዘም ይላል። እነዚህ ረጃጅም ክፍሎች ተማሪዎች የተዋሐዱትን ርእሶች እንዲረዱ ያስችላቸዋል።
3. አዲሱ የተከለሰው መደበኛ ትርጉም (አየተመት) ልታዊ የሆነ የቃል በቃል ትርጉም ነው። እሱም የሚከተሉት ሁለት ዘመናዊ ቅጅዎች ማእከላዊ የሆነ ነጥብ ይዟል። የአንቀጽ አደራደሩ ርእሰ ጉዳዮችን ለመገንዘብ በእጅጉን ይረዳል።
4. የጊዜው እንግሊዝኛ ትርጉም (የጊእት) ዋነኛ አቻ ትርጉም ሲሆን በተባበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ሶሳይቲ (ማኅበረሰብ) የታተመ ነው። የመጽሐፍ ቅዱሱ ትርጉም የሚሞክረውም ዘመናዊ እንግሊዝኛ አንባቢ ወይም ተናጋሪ የግሪኩን ትርጉም እንዲረዳው ማድረግ ነው። በተለይ ደግሞ የወንጌላትን አንቀጾች የሚደረድረው በርእሰ-ጉዳዩ ሳይሆን በተናጋሪው ቃል ነው የሚደረድረው፣ በአኢ ት እንደተደረገው። ተርጓሚዎች ተግባር ይሄኛው የሚረዳ አይሆንም። እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ሁለቱም (የተየመቅሶ) እና (የጊእት) የታተሙት በአንድ ዓይነት ሀድ ሆኖ አንቀጻቸው ይለያያል።

5. የኢየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ (ኢ መቅ) ዋነኛው አቻ ትርጉም ሲሆን በፈረንሳይ ካቶሊክ ትርጉም ላይ ነው። የአውሮጳውያንን የአንቀጽ አደራደር ስልት ለማነጻጸር በእጅጉን ይረዳል።
6. በ1995 የታተመው የተሻሻለው አዲሱ የአሜሪካን መደበኛ መጽሐፍ ዱስ (አአመመቅ)፣ የቃል በቃል ትርጉም ነው። ይህንን የአንቀጽ አደራደር ተከትሎም የየቁጥሩ አስተያየቶች ሰፍረዋል።

## ሦስተኛው መርሕ

ሦስተኛው መርሕ ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስን የተለያዩ ትርጉሞችን በማንበብ ሰፋ ያለ የትርጉም አገባቦችን ማወቅ ይቻላል (በትርጉም መስክ) መጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ወይም ሐረጎች የያዙትን። ብዙ ጊዜ የግሪክ ሐረግ ወይም ቃል በተለያየ መንገድ ነው መረዳት የሚቻለው። እነዚህ የተለያዩ ትርጉሞች እነዚህን አማራጮች በማቅረብ የተለያዩ የግሪክ አማራጭ ጽሑፎችን ለመለየት ያስችላሉ። ይህም መሠረተ እምነትን አይጻረርም፣ ዳሩግን ተመልሶ ወደ ዋናው ጽሑፍ በመውሰድ በተመስጦ የጻፈው የጥንቱ ጸሐፊ ጋ እንድንጓዝ ይረዱናል። ይህ ሐተታ፣ ፈጠን ባለ ሁኔታ፣ ተማሪ የራሱን ትርጉሞች ይመረምር ዘንድ እንዲረዳው የታሰበ ነው። ይህም ማለት ግብ ሙሉ ለሙሉ ፍጹም ነው ማለት ሳይሆን መረጃ ሰጪ እና በጥልቀት እንድናስብ የሚያነቃቃ ነው። እርግጥ ሌሎች አማራጭ ትርጉሞችም ይረዱናል፣ አስተጋቢ፣ ቀኖናዊ፣ ወይም በመሠረተ እምነት የታጠርን እንዳንሆን። ተርጓሚዎች ሰፋ ያለ የትርጉም ዳርቻዎች እና አማራጮች ያሺቸዋል፣ የጥንቶቹ ጽሑፎች የቱን ያህል አሻሚ እንደነበሩ ለመረዳት። በጣም የሚረብሸው ነገር መጽሐፍ ቅዱስ የእውነት ምንጫችን ነው የሚሉት ክርስቲያኖችም ያላቸው ስምምነት ጥቂት መሆኑ ነው።

እነዚህ መርሖዎች ብዙዎቹን ታሪካዊ ችግሮቼን እንዳሸንፍ ረድተውኛል፣ ከጥንቱ ጽሑፍ ጋር እንድተጋ በማስገደድ። እርሶንም ደግሞ ደሚባርክዎት ተስፋ አደርጋለው።

ቦብ አተላይ
ኢስት ቴክሳስ ባብትስት ዩኒቨርሲቲ
ሰኔ 27፣ 1996

# ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ፡ የተፈተነ እውነትን በግል ለመፈለግ

እውነትን ለማወቅ እንችላለን? የት ይገኛል? ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ለማረጋገጥ እንችላለን? የመጨረሻ ወሳኝ ይኖር ይሆን? ሕይወታችንንም ሆነ ዓለማችንን ሊመሩ የሚችሉ የተሟሉ (ፍጹማን) ይኖራሉ? ለሕይወት ትርጉም አለው? እዚህ መሆናችን ለምድነው? የትስ እንሄዳለን? እነዚህ ጥያቄዎች፣ አስተዋይ ሰዎች የሚሰላስሏቸውና ከዘመናት መጀመሪያ አንሥቶ የሰዎችን እውቀት የሚፈትሹ ናቸው (መክ. 1፡13-18፤ 3፡9- 11)። የኔን ግላዊ ጥናት የማስታውሰው የሕይወቴ ዋነኛ ማእከል አድርጌ ነው። በየሱስ አማኝ የሆንኩት በወጣትነት ጊዜዬ ነው፤ በቅድሚያም በዋነኛነት በሌሎች የቤተሰቤ አባላት ምስክርነት። እየጎለመስኩ ስመጣ ስለራሴም ሆነ ስለ ዓለሜ ያሉኝ ጥያቄዎች እያደጉ መጡ። ተራ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ድግግሞሾች ስለ አነበብኳቸውና ስለተረዳኋቸው የሕይወት ልምዶች፣ ትርጉም ሊሰጡ አልቻሉም። የውዥንብር ፤ የምርምር፣ የመናፈቅ እና ብዙውን ጊዜም ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ነበር፣ በምኖርበት በድን በሆነው ደንዳና ዓለም ውስጥ።

ለእነዚህ ዋነኛ ጥያቄዎች ብዙዎች ምላሽ እንዳላቸው ይናገራሉ፣ ነገር ግን ከፍተኛ እና ከማገናዘብ በኋላ የእነሱ መልሶች የተመሠረቱት (1) በግል የሕይወት ፍልስፍናዎች፣ (2) በጥንታዊ አፈ-ታሪኮች፣ (3) በግል የሕይወት ልምዶች፣ ወይም (4) በሥነልቦናዊ ቅድመ እይታዎች ላይ ነው። በማስተዋል የሆነና ስለ ዓለም ያለኝ አመለካከት መሠረት፣ የሕይወቴ ዋነኛ ማእከል፣ የመኖሬ ዋነኛ ምክንያት ላይ ማረጋገጫ አስፈልጎኝ ነበር፣ ማስረጃ። እነዚህን መጽሐፍ ቅዱስን ሳጠና አገኘኋቸው።

ታማኝ እንዲሆንም ማስረጃ መፈለጌን ጀምሬ ያገኘሁትም፣ (1) በጥንታዊ ቅርስ ምርምር ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የተገኘው ታሪካዊ ማረጋገጫ፣ (2) የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ትክክለኛለት፣ (3) በአስራ ስድስት መቶ የመጻፍ ጊዜው ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ የመልእክት ኅብርና መኖር እና (4) ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ከተገናኙ በኋላ ፍጹም የሕይወት ለውጥ ያገኙት ሰዎች የግል ምስክርነት ናቸው። ክርስትና ኅብር እንዳለው የእምነትና የሃይማኖት ሥርዓት የሰው ልጆችን ውስብስብ ጥያቄዎች የመመለስ ችሎታ አላቸው። ይህን ማድረግም የማስተዋል ውቅር ብቻ አይሰጥም፣ ነገር ግን በፍትነታዊ ገጽታው የመጽሐፍ ቅዱስ እምነት የስሜት ደስታ እና መረጋጋትን ይሰጣል።

እንደማስበው፣ የሕይወቴን ዋነኛ ማእከል— ክርስቶስን በቃሉ ውስጥ አግኝቼዋለሁ። በሕይወት ልምዴ ንቁ እና ስሜተ-ስሱ ነበርኩ። ቢሆንም እስካሁን ድረስ የማስታውሰው ወገግ ሊልልኝ ሲል የነበረብኝን ነውጥ እና ሥቃይ ሲሆን፣ የቱን ያህል የመጽሐፉ ትርጓሜዎች እንደሚከራከሩና፣ አልፎ አልፎም በአንድ አብያተ ክርስቲያን እና አስተምህሮዎች እንዳሉ ሳይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን የተመስጦ መሆንና ጠቃሚነቱን ማረጋገጥ የመጨረሻው ሳይሆን የመጀመሪያው ብቻ ነው። የተለያዩ እና ተቃርኖ ያላቸውን የመጽሐፉን ከባባድ አንቀጾች ትርጓሜዎች፣ ሁሉም ትክክለኛ እና በሥልጣን ነን እያሉ እንዴት አድርጌ እንደምቀበል ወይም እንደምተው ላውቅ እችላለሁ? ይህም ተግባር የሕይወቴ ግብ እና የእምነቴ ምናኔ ሆነ። የተረዳሁት ነገር በክርስቶስ ያለኝ እምነት፣ (1) ታላቅ ሰላምና ደስታ እንዳመጣልኝ፣ (2) የተቀናቃኝ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች (የዓለም ሃይማኖቶች) ቀኖናዊነት፤ እና (3) የአንድ ክፍል ሃይማኖት እብሪተኝነት እንዳለበት ተረድቻለሁ።

የጥንታዊውን ሥነ ጽሑፍ ትርጓሜ ተገቢ ዋጋ ያለው ፍለጋዬን ሳካሂድ ያስደነቀኝ ነገር ቢኖር የራሴን የግሌን ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ክፍለ ሃይማኖታዊ እና በሕይወት ልምድ አድልዖዎች መለየት ነው። የራሴን አመለካከት ለማጠናከር መጽሐፍ ቅዱስን እንደዋዛ አዘውትሬ አነባለሁ። የራሴን ያልተሟላ ዋስትናና የብቃት ማነስ ያመላከተኝ ሌሎችን የማጠቃበት ቀኖናዊ ምንጭ አድርጌ እወስደዋለሁ። ይህንን ሀቅ መረዳት ለእኔ የቱን ያህል አስቸጋሪ ነበር! ምንም እንኳ የተሟላ ተጨባጭነት ባይኖረኝም የመጽሐፍ ቅዱስ ደኅና አንባቢ ለመሆን እችላለሁ። ያሉብኝን አድሏዊነቶች ለመለየትና እንዳሉም እውቅና በመስጠት የተወሰኑ ላደርጋቸው እችላለሁ። ከእነሱ ገና አሁንም ነጻ አይደለሁም፣ ነገር ግን ከራሴ ድክመት ተሟግቻለሁ። ተርጓሚ ዘወትር የመልካም መጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ጠላት እንደሆነ ነው! እስቲ ጥቂት ቅድመ ግምቶችን፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቴ ገኘኋቸውን እርሶ አንባቢው ከእኔ ጋር ሆነው ይመረምሯቸው ዘንድ ልዘርዝራቸው፡

## I. ቅድመ ግምቶች

(1) መጽሐፍ ቅዱስ ተመስጧዊ የሆነ የእውነተኛው አምላክ የራሱ መገለጥ መሆኑን አምናለሁ። ስለሆነም፣ መተርጎም ያለበት በዋነኛው መነሻ ብርሃን ለኮታዊ ጸሐፊ (መንፈስ) ሆኖ በተወሰነ ታሪካዊ ወቅት በነበረ ሰው ጸሐፊነት ነው።

(2) መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ለተራ ሰዎች፣ ለሁሉም ሰዎች እንደተጻፈ አምናለሁ! እግዚአብሔር ለእኛ በግልጽ ለመናገር በታሪካዊና በባህላዊ ግባብ ራሱን አዘጋጅቶልናል። እግዚአብሔር እውነትን አይሸሽግም— እንድንረዳው ይፈልጋል! ስለሆነም በእኛ ሳይሆን በራሱ ጊዜ ብርሃን የግድ ተርጎም አለበት። መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ ከሰሙት ወይም ካነበቡት በተለየ መንገድ የምንረዳው ማለት አይደለም። በተራ ሰው ልቦና ሊረዱት የሚችል እና ተገቢ የሆነ የሰው ልጆች መግባቢያ አግባቦችና ስልቶችን የሚጠቀም ነው።

(3) መጽሐፍ ቅዱስ ኅብር ያለው መልእክትና ተግባር እንዳለው አምናለሁ። ምንም እንኳ አያአዎአዊ የሆኑ አንቀጾች ቢኖሩትም ራሱን በራሱ ይቃረንም። ስለሆነም፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ዋነኛው ተርጓሚ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ነው።


(4) እያንዳንዱ አንቀጽ (ትንቢታትን ጨምሮ) አንድ እና አንድ ብቻ ትርጉም እንዳላቸውና ይህም በዓይነተኛው ተመስጧዊ ጸሐፊ መነሻ ሐሳብ ሆኑን አምናለሁ። ምንም እንኳ ፍጹም ርግጠኞች ባንሆንም የዓይነተኛውን ጸሐፊ ሐሳብ እንረዳዋለን፣ ብዙ ጠቋሚዎች አቅጣጫውን ስለሚያመላክቱን፡

ሀ. የዘውግ (የሥነ ጽሑፋዊ) ዓይነቱ፣ መልእክቱን ለማስተላለፍ የተፈለገበት
ለ. ጽሑፉ ሊያወጣ የፈለገው እውነት ታሪካዊ ዳራ እና /ወይም የተለየ አውድ
ሐ.የአጠቃላይ የመጽሐፉ ሥነ ጽሑፋዊ ሁኔታ እና እንዲሁም የእያንዳንዱ የጽሑፍ አሀድ
መ. ጽሑፋዊ ንድፉ (ዋና ዋና ይዘቱ) ማለትም እያንዳንዱ ጽሑፍ አሀድ ከአጠቃላይ መልእክቱ ጋር ያለው ዝምድና
ሠ. መልእክቱን ለማስተላለፍ የተጠቀመበት የተለየ ሰዋሰዋዊ ባሕርይ
ረ. መልእክቱን ለማቅረብ የተመረጡት ቃላት ትይዩ አንቀጾች


በእነዚህ በእያንዳንዳቸው  አካባቢ የሚደረገው ጥናት በአንቀጽ ላይ የምናደርገው ጥናት  ላማ ሆኗል።ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚሆነውን የእኔን ዘዴ ከመግለጤ በፊት ጥቂት ተገቢ ያልሆኑ በአሁን ጊዜ ጥቅም ላይ በመዋል ላይ ያሉትንና በርካታ የተለያዩ ትርጉሞች እንዲፈጠሩ ያደረጉትና  ግድ መወገድ ያለባቸውን ላመላክት፡

# II. ተገቢ ያልሆኑ ዘዴዎች

1) የመጽሐፍ ቅዱስን መጻሕፍት ሥነጽሑፋዊ አውድ ችላ በማለት  እያንዳንዱን ዓረፍተ ነገር፣ ሐረግ እንዲያውም ግለሰባዊ ቃላትን እንደ እውነታዊ  ግለጫ፣ ከጸሐፊው ዓላማ ባልተገናኘ መልኩ ወይም ከሰፊው የጽሑፉ ክፍል ጋር ባልተያያዘ ሁኔታ መውሰድ። ይህም ዘወትር “የጽሑፍ ማጣቀሻ” ይባላል።
2) የመጻሕፍቱን ታሪካዊ አውድ ችላ በማለት እና በግምታዊ ታሪካዊ ዳራ በመቀየር ከጽሑፉ ጋር መጠነኛ ግንኙነት ወይም ምንም ዓይነት ድጋፍ በሌላቸው ጋር ማያያዝ
3) የመጻሕፍቱን ታሪካዊ አውድ ችላ በማለት እንደ አካባቢያዊ የጧት ጋዜጣ ዓይነት ቀድኖውኑ ለዘመናዊ ክርስቲያን እንደተጻፈ ዓይነት ማንበብ
4) የመጻሕፍቱን ታሪካዊ አውድ ችላ በማለት ለጽሑፉ ተምሳሌታዊ ፍቺ በመስጠት ፍልስፍናዊ/ሥነ- መለኮታዊ በማድረግ በመጀመሪያ ቃሉን ከሰሙት እና ዋናው ጸሐፊ ሊል ከፈለገው ሐሳብ በማይገናኝ መልኩ መያዝ
5) ዋነኛውን መልእክት ችላ በማለትና የራስን የሥነ-መለኮት ሥርዓት፣ አባባይ መሠረተ- እምነት፣ ወይም የወቅቱን ጉዳይ በመቀየር፣ እና ከማይገናኝ ጋር በማያያዝና፣ ዋናው ጸሐፊ ሊል ከፈለገው ቁምነገርና ከተቀመጠው መልእክት መውጣት። ይህ የአካሄድ ክስተትም ዘወትር የሚደረገው የተናጋዊውን ሐሳብ ለማጠናከር በቅድሚያ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማንበብን ነው። ይህን ዘወትር፣ “የአንባቢ ምላሽ” (“ጽሑፉ ለእኔ የሚሰጠኝ” ትርጉም ተብሎ ይታወቃል። በሰዎች የጽሑፍ መግባቢያ ላይ ቢያንስ ሦስት አካላት ያስፈልጋሉ፡




ቀደም ሲል የተለያዩ የምንባብ ስልቶች ከሦስቱ በአንደኛው ክፍሎች አተኩረው ነበር። ነገር ግን በእውነት ለማጽናት ልዩ የሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ  መስጠ የተሻሻለው ንድፍ ይበልጥ ተገቢነት አለው።




እንደ እውነቱ ሦስቱም አካሎች በትርጓሜ ሂደት የግድ መካተት ይኖርባቸዋል። ለማረጋገጥ ያህልም የእኔ ትርጓሜ ያተኮረው በቀዳሚዎቹ በሁለቱ  ካላት ላይ ነው፡ ዋነኛው ጸሐፊ እና ጽሑፉ። ምናልባት የእኔ ተቃርኖ ባስተዋልኩት ተገቢ ያልሆነ ሁኔታ ላይ ይሆናል። (1) ተምሳሌታዊ ወይም መንፈሳዊ በተደረጉ ጽሑፎች እና (2) “የአንባቢ ምላሽ” (ለእኔ የሚረዳኝ) ትርጓሜዎች። በዛባት በሁሉም ደረጃ ላይ ሊከሰት ይችላል። ዘወትር የእኛን መሻት፣ አድሏዊነት፣ አግባብ፣ እና አፈጻጸማችንን መመርመር ይኖርብናል። ምንም ዓይነት ወሰኖች ለትርጉሞች በሌሉበትና፣ ገደብና መስፈርት በሌለበት  እንዴት  አድርገን መፈተሽ  እንችላለን?  ለዚህ ነው የጸሐፊው መነሻ ሐሳብና የጽሑፉ አወቃቀር የተወሰኑ መስፈርቶችን ሰጥቶኝ ዳራውን ለመወሰንና ተገቢ የሆነ ይሁንታ ያለው ትርጓሜ እንዳደርግ ያስቻለኝ።

በእነዚህም ተገቢ ባልሆኑ ስልቶች ጭላንጭል ምን ዓይነት ታሳቢ አግባቦች ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ እና ትርጓሜ በተረጋገጠ ደረጃ የሚያመጡ እና ቋሚነት ያላቸው ሊኖሩ ይችላሉ?

# III. ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ተገቢ አገባቦች

በዚህ ነጥብ የተወሰኑ የትርጓሜ ዘውጎችን የተለዩ ስልቶችን  አላብራራም፤ ነገር ግን ለሁሉም ዓይነት የቅዱሳን መጻሕፍት  አጠቃላይ የጽሑፍ ትርጓሜ ተገቢ መርሖዎች ላይ ነው። ለተወሰነ ዘውጋዊ  አግባብ መልካም የሆነው መጽሐፍ፣ መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ ጠቀሜታው እንዴት እንደሚነበብ፣ በጎርደን ፊ እና ዳግላስ ስቱአርት፣ በዞንደርቫን የታተመው ነው። የኔ ዘዴ በመነሻው ያተኮረው  አንባቢ ለመንፈስ ቅዱስ መጽሐፍ ቅዱስን ያበራላቸው ዘንድ ሲፈቅዱ የሚያልፉባቸውን አራት የግል የንባብ ሀደቶችን ነው። ይህም መንፈስን፣ ጽሑፉን እና አንባቢውን ቀዳሚ ያደርጋቸዋል፣ ተከታይ ሳይሆን። ይህም ደግሞ አንባቢው በተንታኞች ሐሳብ አለቅጥ እንዳይወሰድ ያደርገዋል። ሲባል የሰማሁትም፣ “መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ ብርሃን በሐተታዎች ላይ ያበራል” የሚል ነው። ይህም ማለት ግን የጥናት መርጃዎችን ለማንኳሰስ አይደለም፣ ነገር ግን ለአጠቃቀማቸው ተገቢ ጊዜ ማስፈለጉን ለማመላከት ነው እንጂ። ትርጓሜዎቻችንን ከቃሉ ከራሱ ለማስደገፍ መቻል ይኖርብናል።

ስድስቱ አካባቢዎች ምናልባት የተወሰኑ የእውነት ማረጋገጫ ይሰጡናል፡ የዋናው ጸሐፊ

1) ታሪካዊ መቼት
2) ሥነ-ጽሑፋዊ አውድ
3) የዋናው ጸሐፊ ምርጫ
4) ሰዋሰዋዊ መዋቅር (አገባብ)
5) የተመሳሳይ ሥራዎች አጠቃቀም
6) የጽሑፍ ዓይነት (ዘውግ)

የእኛ ተገቢ የሆነውን የመረዳት ችሎታ ሀ. ጠቃሚ ትይዩ አንቀጾች የተጻፈው ጽሁፍ ዋነኞቹ ተቀባዮች ዋነኛው ጸሐፊ ሊል የፈለገው መንፈስ ቅዱስ የእጅ ጽሑፍ ልዩነቶች የተጻፈው መጽሐፍ ከትርጓሜአችን ጀርባ ምክንያቶችንና አመክኖዎችን (ሎጂክ) ማሳየት መቻል አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛው የእምነትና የድርጊት ምንጫችን ነው። ቢያሳዝን መልኩ፣ ክርስቲያኖች በሚያስተምረው ወይም በሚያጸናው ላይ ዘወትር አይስማሙም። ይህም መጽሐፍ ቅዱስ ተመስጧዊ መሆኑን ተቀብሎ ከዚያም አማኞች ለሚያስተምረውም ሆነ ለሚጠይቀው ላለመስማማት መቻል በራስ እንደመሸነፍ ነው!

አራቱ የንባብ ሀደቶች የተነደፉት የሚከተለውን ጠለቅ ያለ ትርጓሜ ለመስጠት ነው።

1) የመጀመሪያው የንባቡ ኡደት

ሀ) መጽሐፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ ያንብቡት። ከተለያዩ የትርጉም ንድፈ ሐሳቦች አገኛለሁ ብለው ተስፋ በማድረግ በድጋሚ በተለያዩ ትርጉሞች ያንብቡት

i. ቃል በቃል (አኪጀት፣ አአሶመቅ፣ አየተመት)
ii. ንቁ ቀጥተኛ (የአእቅ፣ ]መቅ)
iii. ማብራሪያ (ሕያው ቃል፣ የተብራራ መጽሐፍ ቅዱስ)

ለ) የሙሉ ንባቡን ማእከላዊ ሐሳብ ይፈልጉ። ጭብጡን ይግለጡት።

ሐ) የጽሑፋዊ አሀዱን (ከተቻለ) ይለዩት፤ ምእራፍ፣ አንቀጽ ወይም ዓረፍተ ነገር በትክክል ሊያብራራ የሚችለውን፣ የጭብጡን ማእከላዊ ሐሳብ ለማግኘት።

መ) ዋነኛውን ገገር የሥነ-ጽሑፋዊ ጭብጥ ዘውግ (ዓይነት) ይግለጡት

i. ብሉይ ኪዳን
  1) ይእብራይስጥ ትረካ
  2) የእብራይስጥ ቅኔ (መጽሐፈ- ጥበብ፣ መዝሙራት)
  3) የእብራይስጥ ትንቢት (ስድ ንባብ፣ ቅኔ)
  4) ሕግጋት
ii. አዲስ ኪዳን
  1) ተራኪ (ወንጌላት፣ ግብረ-ሐዋርያት)
  2) ምሳሌዎች (ወንጌላት)
  3) ደብዳቤዎች/መልእክቶች
  4) ትንቢታዊ ሥነ-ጽሑፍ

2) ሁለተኛው የንባብ ሀደት

ሀ. ሙሉ መጽሐፉን እንዳለ በድጋሚ ያንብቡት፣ ዋናውን ርልሰ-ጉዳይ፣ ቁም-ነገሮች ለመለየት ፈልጉ

ለ. ዋናዎቹን ርእሶች በዋና ሐሳብ ለይተው አጠር ባለ እና በቀላል መግለጫ ይዘቱን ያስቀምጡ

ሐ. የድርጊት መግለጫውን ይፈትሹና ሰፋ ያለ የርእሰ ጉዳይ ዝርዝር በጥናት መርጃ ይጠቀሙ

3) ሦስተኛው የንባብ ኡደት

ሀ) ሙሉ መጽሐፉን በድጋሚ ያንብቡት፣ ለጽሑፉ ታሪካዊ መቼትና የተለየ አውድ ለማግኘትና ለመለየት ከራሱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይሞክሩ

ለ) በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱትን ታሪካዊ ዓይነቶች ይዘርዝሩ

i. ጸሐፊው
ii. ዘመኑ
iii. ተቀባዮች
iv. ለመጻፍ የተለየ ምክንያት
v. ከመጽሐፉ ዓላማ ጋር የተያያዙ ባህላዊ መቼቶች ገጽታ
vi. ከታሪካዊ ሰዎችና ሁነቶች የሚጠቀሱ

ሐ) የምትተረጉመውን ያንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የዋና ፍሬ ሐሳቡን ዝርዝር ወደ አንቀጽ ደረጃ አስፋፉት። ዘወትር የሥነ ጽሑፉን አሀድ ለዩት፣ እንዲሁም የፍሬ ሐሳቡን ዝርዝር አውጡ። ይህም ምናልባት በርካታ ምእራፎች ወይም አንቀጾች ይሆናል። ይህም የዋናውን ጸሐፊ የሐሳብ ተገቢነት (ሎጂክ) ጽሑፋዊ ንድፍ ለመከተል ያስችልዎታል።xi

መ) የጥናት መረጃዎችን በመጠቀም የርሶን ታሪካዊ መቼት ይፈትሹ።

4) አራተኛው የንባብ ሀደት

ሀ. የተለየውን የጽሑፍ ክፍል በልዩ ልዩ ትርጉሞች ያንብቡት

i. ቃል በቃል (አኪጀት፣ አአሰመቅ፣ አየተመት)

ii. ንቁ አቻ (የአእቅ፣ ]መቅ)

iii. ማብራሪያ (ሕያው ቃል፣ የተብራራ መጽሐፍ ቅዱስ)

ለ. ሥነ-ጽሑፋዊ ወይም ሰዋሰዋዊ መዋቅሮችን ይፈልጉ

i. ተደጋጋሚ ሐረጎች፣ ኤፌ. 1፡6፣12፣13

ii. ተደጋጋሚ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮች፣ ሮሜ. 8፡31

iii. ተጻጻራሪ ጽንሰ-ሐሳቦች

ሐ. የሚከተሉትን ዓይነቶች ይመዝግቡ

i. ወሳኝ ቃላት

ii. ያልተለመዱ ቃላት

iii. ዋነኞቹ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮች

iv. የተለዩ አስቸጋሪ ቃላት፣ ሐረጎች፣ እና ዓረፍተ ነገሮች

መ. ዋነኞቹን ትይዩ አንቀጾች ይለዩ

i. ከርእሰ ጉዳዩ ጋር በጣም ግልጽ የሆነውን የማስተማሪያ አንቀጽ ይፈልጉ

ሀ. "ስልታዊ ሥነ-መለኮት" መጻሕፍት

ለ. የማጣቀሻ መጽሐፍ ቅዱስ

ሐ. የቃላት ዝርዝር

ii. በርእሰ ሐሳብህ ዙሪያ ተስማሚ  አያዎአዊ ጥንዶችን ከጽሑፉ ይፈልጉ። አብዛኞቹ የቅዱሳት መጻሕፍት እውነታዎች ሚቀርቡት በአከራካሪ ጥንዶች ነው፤ በርካታ የመሠረተ እምነት ግጭቶች የሚመነጩት ከጽሑፍ አቃቂር ማውጣት  ለትም ከፊል ከሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ክርክሮች ነው። መላው መጽሐፍ ቅዱስ ተመስጧዊ ነው፣ እኛም የተሟላውን መልእክት በመፈለግ፣ የመጽሐፍ ቅዱስን ሚዛን በትርጓሜአችን መጠበቅ ይኖርብናል።

iii. በዛው በመጽሐፉ ውስጥ ፣ በዛው ጸሐፊ ወይም በዛው የሥነ ጽሐሁፍ ዓይነት፣ አቻዊ ትይዩ ይፈልጉ፤ መጽሐፍ ቅዱስ የራሱ ምርጥ ተርጓሚ ነው፤ ምክንያቱም፣ አንድ ብቸኛ ጸሐፊ ስላለው— መንፈስ ቅዱስ።

ሠ. ታሪካዊ መቼቱንና የተለየ አውዱን ለመፈተሽና ለማስተዋል የጥናት መረጃዎችን ይጠቀሙ።

i. የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ

ii. የመጽሐፍ ቅዱስ አውደ-ጥበባት፣ መምሪያ መጻሕፍ እና መዝገበ ቃላት

iii. የመጽሐፍ ቅዱስ መግቢያዎች

iv. የመጽሐፍ ቅዱስ ሐተታዎች (በዚህ ነጥብ ላይ በጥናትዎ፣  አማኝ የኅብረተሰብ ክፍሎችን፣ ለትም የቀደምቱም ሆኑ ያሁኖቹ የራስዎን ጥናት ለማገዝና ለማረም ይጠቀሙባቸው።)

# IV. የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ አተገባበር

በዚህ ነጥብ ወደ አተገባበር እንቃኛለን። ጽሑፉን ከዋናው መቼት አንጻር ለመረዳት ጊዜ ወስደዋል፤ አሁን ደግሞ ይሄንኑ በሕይወትዎ፣ በባህልዎ  ተገብሩት ይገባል። የመጽሐፍ ቅዱስ የመረዳት ሥልጣን ማለት በእኔ አገላለጽ፣  "ዋናው የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊ በእሱ ጊዜ ሊለው የፈለገውን መረዳትና ያንን በራሳችን ጊዜ መተርበር" ማለት ነው።   ድርጊት መከተል ያለበት የዋናውን ጸሐፊ የትርጓሜ ሐሳብ በጊዜም ሆነ በሎጂክ አኳያ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን  አንቀጽ በጊዜው ምን ለማለት  እንደፈለገ  እስካላወቅን ድረስ በዘመናችን ልንተገብረው  አንችልም! የመጽሐፍ ቅዱስ አንቀጽ  ለው ያልፈለገውን ፈጽሞ ሊሆን አይችልም!  የእርስዎ የተዘረዘረ የዋና ሐሳቦች ዝርዝር በአንቀጽ ደረጃ (የንባብ ሀደት ቁጥር 3)፣ የእርስዎ መመሪያ ይሆናል። ትግበራ መደረግ ያለበት በአንቀጽ ደረጃ  እንጂ በቃላት ደረጃ መሆን የለበትም። ቃላት ትርጉም የሚኖራቸው በከፊለ- ጽሑፍ ደረጃ ነው፤ ሐረጎች ትርጉም የሚኖራቸው በከፊለ- ጽሑፍ ደረጃ ነው፤ ዓረፍተ ነገሮች ትርጉም የሚኖራቸው በከፊለ- ጽሑፍ ደረጃ ነው።

ብቸኛው ተመስጧዊ ሰው በትርጓሜው ሂደት ውስጥ ዋነኛ ጸሐፊው ነው። በመንፈስ ቅዱስ  አብራሪነት  (ማብራሪያ)  የእሱን ምሪት ብቻ መከተል ይኖርብናል። ማብራሪያ ግን ተመስጦ ማለት አይደለም። "እግዚአብሔር እንደዚህ ይላል፣" ለማለት ከዋናው ጸሐፊ ሐሳብ ጋር የግድ መኖር አለበት። ትግበራ በተለይ መያያዝ ያለበት በሙሉ መጽሐፉ ሐሳብ ላይ ሲሆን፣ የተለየው የጽሑፍ አሀድ እና በአንቀጽ ደረጃ እያደገ በሚሄድ መልኩ።   የዘመናችን ጉዳዮች መጽሐፍ ቅዱስን እንዲተረጉሙ አትፍቀዱ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገር! ይህ ምናልባት የተወሰኑ ከጽሑፉ እንድናወጣ ይጠይቀን ይሆናል። ይህም ተገቢ  የሚሆነው ጽሑፉ ለመርሖቹ ድጋፍ ሲሆን ነው። በሚያሳዝን መልኩ ግን፣ ብዙውን ጊዜ የእኛ መርሖዎች፣ "የእኛ" መርሖዎች ናቸው— የጽሑፉ መርሕ በመሆን ፈንታ።

መጽሐፍ ቅዱስን ለመተግበር፣  (ከትንቢት ብቻ በቀር)  ማስታወስ የሚገባን ጠቃሚ ነገር ለእያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አንድና አንድ ብቻ  ርጉም እንዳለው ነው። ያም ትርጉም ግንኙነቱ ከዋናው ጸሐፊ ሐሳብ ጋር፣ እሱም የዘመኑን ውድቀትም ሆነ ፍላጎት እንዴት እንዳቀረበው ነው። በርካታ ተስማሚ ድርጊቶች ከዚህ ከአንዱ ትርጉም ሊመነጩ ይችላሉ። አተገባበሩም የሚመሠረተው በተቀባዮቹ መሻት ላይ ሆኖ፣ መገናኘት ያለበት ግን ከዋናው ጸሐፊ ሐሳብ ላይ ነው።

## V. የትርጓሜ መንፈሳዊ ገጽታዎች

እስካሁን አመክኖአዊ የሆነ እና የሥነ ጽሑፋዊ ሂደት በምን መልኩ በትርጉምና በአተገባበር ላይ መሆን እንዳለበት ለማብራራት ሞክሬአለሁ። አሁን ደግሞ ስለ ትርጉም መንፈሳዊ ገጽታ በአጭሩ ላብራራ። የሚከተሉት የመቆጣጠሪያ ዝርዝሮች ረድተውኛል፡

(1) ለመንፈስ ርዳታ ይጸልዩ (1ኛ ቆሮ. 1፡26-2፡16)።
(2) ከሚታወቅ ኃጢአት በግልዎ ምሕረትንና መንጻትን እንዲያገኙ ይጸልዩ (1ኛ ዮሐንስ 1፡9)።
(3) ስለ እግዚአብሔር ለማወቅ ከፍተኛ ፍላጎት እንዲያድርብዎ ይጸልዩ (መዝ. 19፡7-14፤ 42፡1፤ 119፡1)።
(4) አዲስ ማስተዋልን በሕይወትዎ ወዲያውኑ ይተግብሩ።
(5) ትሑትና ለመማር የተዘጋጁ ይሁኑ።

በሎጂካዊ ሂደት እና በመንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ መሪነት መካከል ያለውን ሚዛን ለመጠበቅ በጣም አዳጋች ነው። የሁለቱን ሚዛን ለመጠበቅ የሚከተሉት ጥቅሶች ረድተውኛል፡

(1) ከ ጀምስ ደብሊዩ. ሲር፣ ቃሉን መጠምዘዝ (ማጣመም) ገጽ 17-18

*"ማብራሪያ የሚመጣው ወደ እግዚአብሔር ሕዝቦች ሐሳብ ነው— ወደ መንፈሳዊ ምሑር ሳይሆን።በመጽሐፍ ቅዱስ ክርስትና የተለየ የመማሪያ ክፍል የለም፣ ምንም የተለየ የሚያብራራ፣ ተገቢው ትርጓሜ የሚመጣላቸው የተለዩ ሰዎች የሉም። እና ስለዚህ፣ መንፈስ ቅዱስ ልዩ የጥበብ፣ እውቀት፣ እና መንፈስን የመለየት ጸጋ ሲሰጥ፣ እነዚህ ባለጸጋ ክርስቲያኖች ብቻ የቃሉ ሥልጣናዊ ተርጓሚዎች እንዲሆኑ መመደቡ አይደለም። ሁሉም የራሱ ሕዝቦች ሊማሩ፣ ሊዳኙ እና ሊለዩ፣ በእነሱ፣ እግዚአብሔር የተለየ ችሎታ ለሰጣቸው እንኳ ሥልጣን ያለውን መጽሐፍ ቅዱስ መጥቀስ እንደሚችሉ ነው። ለማጠቃለል፣ በሙሉው መጽሐፍ ያቀረብኩት ሐሳቤ መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛው የእግዚአብሔር መገለጥ ለሰው ልጆች ሁሉ ነው፣ በሚናገረው ሁሉ የመጨረሻው ባለሥልጣን ነው፤ በጥቅሉ ምሥጢራዊ ሳይሆን በማንኛው ባህል ባሉ ተራ ሰዎች በበቂ መልኩ ለመረዳት የሚቻል ነው።"*

(2) በኬርከጋርድ፣ በቤርናንድ ራም በሚገኘው፣ የፕሮቴስታንት የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ፣ ገጽ 75፡

*እንደ ኬርከጋርድ ከሆነ ሰዋሰዋዊ፣ ቃላዊ፣ እና ታሪካዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች አስፈላጊ ናቸው፤ መቅደም ያለበት ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ልባዊ ንባብ ነው። "መጽሐፍ ቅዱስን እንደ እግዚአብሔር ቃል ለማንበብ፣ ማንም አፍ ከልብ ሆኖ፣ በተጠንቀቀ ሆኖ፣ በጉጉትና ተስፋ በማድረግ፣ ከእግዚአብሔር ጋር እየተነጋገረ ማንበብ አለበት። መጽሐፍ ቅዱስን በሐሳበ ቢስነት ወይም በግዴለሽነት ወይም እንደ ትምህርት ወይም እንደ ልዩ ሞያ ማንበብ መጽሐፍ ቅዱስን እንደ እግዚአብሔር ቃል ማንበብ አይደለም። አንዱ የፍቅር ደብዳቤ እንደሚነበብ የሚያነበው ከሆነ እሱ እንደ እግዚአብሔር ቃል እያነበበው ነው።"*

(3) ኤች. ኤች. ሮውሊ በየመጽሐፍ ቅዱስ ጠቀሜታ፣ ገጽ 19፡

*"የተሻለ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሑራዊ መረዳት፣ ምንም ያህል ፍጹም ቢሆን ሁሉንም ሀብቶች ሊያስገኝ አይችልም። ይህን መሰሉን መረዳት ዝቅ ለማድረግ አይደለም፣ ለፍጹም መረዳት አስፈላጊ ነው። ነገር ግን ፍጹም ይሆን ዘንድ ወደ መጽሐፉ መንፈሳዊ ሀብቶች የሚያመራ መንፈሳዊ መረዳት ማስፈለጉን ለማሳየት ነው። እናም ለዛ መንፈሳዊ መረዳት ከምሑራዊ ንቁነት የተሻለ ነገር ያስፈልጋል። መንፈሳዊ ነገሮች በመንፈሳዊነት የሚለዩ ናቸው፤ እናም የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ የመንፈሳዊ ተቀባይነት አዝማሚያ ሊኖረው ይገባል፣ ራሱን ይሰጥ ዘንድ እግዚአብሔርን ለመፈለግ ጉጉት ያለው፣ ከሳይንሳዊ ጥናቱ ባሻገር ወደ ተትረፈረፈ ሀብት ወራሽነት ወደሚያስገኝ ወደዚህ ከመጻሕፍት ሁሉ ታላቅ ወደ ሆነ።"*

## VI. የሐተታው ዘዴ

የጥናት መመሪያ ሐተታው የተሰናዳው የእርስዎን የትርጉም አግባብ በሚከተሉት መንገዶች ለማገዝ ነው፡

*ሀ.* እያንዳንዱን መጽሐፍ የሚያስተዋውቅ አጭር ታሪካዊ የዋና ሐሳብ መግለጫ። "የንባብ ሀደት ቁጥር 3" ካነበበቡ በኋላ ይህን መረጃ ያረጋግጡት።

*ለ.* ጽሑፋዊ ማብራሪያዎች በየአንዳንዱ ምእራፍ መጀመሪያ ላይ ይገኛል። ይህም ሥነ ጽሑፋዊ አሀዱ እንዴት እንደተዋቀረ ለመመልከት ይረዳል።

*ሐ.* በእያንዳንዱ ምእራፍ ወይም ሥነ ጽሑፋዊ አሀድ፣ የአንቀጽ ክፍሎች እና መግለጫ ጽሑፎች ከተለያዩ በርካታ ዘመናዊ ትርጉሞች ተሰጥተዋል፡

*ሀ)* የመጽሐፍ ቅዱስ ኅብረት ሶሳይቲ የግሪክ ጽሑፍ፣ አራተኛ እትም (የተመቅሶ)
*ለ)* አዲሱ የአሜሪካ መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ፣ 1995 የተሻሻለ (አአመመቅ)
*ሐ.)* አዲሱ ኪንግ ጀምስ እትም (አኪጀእ)
*መ)* አዲሱ የተከለሰው መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ (አየመመቅ)
*ሠ)* አዲሱ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ (አእመቅ)
*ረ)* የኢሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ (ኢመቅ)

የአንቀጽ ክፍሎች ተመስጧዊ አይደሉም። ከጽሑፉ መረጋገጥ ይኖርባቸዋል። ከተለያዩ የትርጉም ንድፈ ሐሳቦች እና ሥነመለኮታዊ አስተሳሰቦች የተለያዩ ዘመናዊ ትርጉሞችን በማወዳደር የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን ለመተንተን እንችላለን። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድ ዋነኛ እውነት ይዟል። ይህም "መሪ ዓረፍተ ነገር" ወይም "የጽሑፉ ማእከላዊ ሐሳብ" ተብሎ ይጠራል። ይህም ኅብር ያለው

ሐሳብ አግባብነት ላለው ታሪካዊ፣ ሰዋሰዋዊ  ርጉም ቁልፉ ነው። ማንም ከአንድ አንቀጽ ባነሰ መተርጎም፣ መስበክ ወይም ማስተማር ይኖርበትም!  በተጨማሪም እያንዳንዱ አንቀጽ ከአካባቢው አንቀጾች ጋር እንደሚዛመድ አስታውሱ። ለዚህ ነው በአንቀጽ ደረጃ ያለ የዋና ሐሳቦች   ርዝር ለሙሉ መጽሐፉ በጣም  አስፈላጊ የሆነው። በዋናው ተመስጧዊ ጸሐፊ የተገለጠውን ርእሰ ጉዳይ  አመክኖአዊ ፍሰት መከተል መቻል  ኖርብናል።

መ. የቦብ ማስታወሻዎች በትርጓሜ የሚከተሉት ቁጥር በቁጥር የሆነውን አግባብ ነው። ይህም የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ እንድንከተል ያስገድደናል። ማስታወሻዎቹ ከብዙ አካባቢዎች መረጃዎችን ይሰጡናል።

ሀ. ሥነ ጽሑፋዊ ተጓዳኝ ጽሑፍ
ለ. ታሪካዊ፣ ባህላዊ መረዳቶች
ሐ. ሰዋሰዋዊ መረጃ
መ. የቃላት ጥናቶች
ሠ. ጠቃሚ ትይዩ አንቀጾች

ሠ. በተወሰኑ ነጥቦች በሐተታው ውስጥ፣ አዲሱ የአሜሪካን መደበኛ ትርጉም (በ1995 የተሻሻለ) የኅትመትጽሑፍ፣ ከሌሎች በርካታ ዘመናዊ ትርጉሞች በደጋፊነት ይኖራሉ፡

ሀ. አዲሱ የኪንግ ጀምስ ቅጂ (አኪጀቅ)፣ የጽሑፋዊ  እጅ ጽሑፎችን ማለት  “ቴክስተስ ሪሴፕተስ” የሚከተል ነው።
ለ. አዲሱ የተከለሰው መደበኛ ቅጂ (አየተመቅ)፣ ማለትም ቃል በቃል የሆነ ትርጉም ሲሆን፣ እሱም የተከለሰው መደበኛ ትርጉም ከቤተክርስቲያን ብሔራዊ ምክር ቤት ነው።
ሐ. የጊዜው እንግሊዝኛ ትርጉም (የጊእት)፣ ከአሜሪካን የመጽሐፍ ቅዱስ ሶሳይቲ የተሻሻለ አቻ ትርጉም ነው።
መ. የየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ (የመቅ)፣ ከፈረንሳይ ካቶሊክ የተሻሻለ አቻ ትርጉም ላይ የተመሠረተ የእንግሊዝኛ ትርጉም ነው።

ረ. ግሪክኛን ለማያነቡ፣ ተነጻጻሪ  እንግሊዝኛ ትርጉሞች በጽሑፉ ውስጥ ያሉትን  አስቸጋሪ ክፍሎች ለመረዳት ይጠቅማሉ፡

ሀ. የእጅ ጽሑፍ ልዩነቶች
ለ. አማራጭ የቃላት ፍቺዎች
ሐ. ሰዋሰዋዊ አስቸጋሪ ጽሑፎችና አወቃቀሮች
መ. አሻሚ ጽሑፎች የእንግሊዝኛ ትርጉም እነዚህን ችግሮች ባያቃልልም እንኳ፣ ጠለቅ እና ውስጣዊ የሆነ ጥናት ይደረግ ዘንድ አላማና ስፍራውን ያሳያሉ።

ሰ.  በእያንዳንዱ ምእራፍ መዝጊያ ላይ ጠቃሚ የውይይት ጥያቄዎች ተሰጥተዋል፣ እነዚህም የምእራፉን ዋነኞቹን የትርጓሜ ጉዳዮች ነላማ ለማድረግ የሚሞክሩ።

# የአሞፅ መግቢያ

I. የመፅሐፉ ስም
   ሀ. መፅሐፍ ስሙን ያገኘው ከነብዩ ነው፡፡
   ለ. አሞፅ የሚለው ስም ሊሆን የሚችለው፡-
      1. "ሸክም ያለበት መሆን" (BDB 770፣ KB 846)
      2. "ሸክምን መሸከም" (BDB 770፣ KB 846)
      3. "ደጋፊ መሆን" (ሊሆን የሚችለው "YHWH ተሸክሞት የነበረው [KB 847]፣ምናልባትም የAmasiah አጭር አገላለፅ ሲሆን ትጉሙም "YHWH እሱ ምናልባት ሲያጥር "የህዌ ይሰማል" የሚል የአሜስያስ ስም ሊሆን ይችላል 2ዜና 17፡6)፡፡
      4. አንድ የራቢ ባህል አስረግጦ እንደሚናገረው የእሱን መልዕክት በሚቃወሙ ሰዎች የተሰጠ ሲሆን ይህም የሚያመለክተው በግልፅ ይናገር እንዳልነበረ ወይም ይንተባተብ እንደነበረ ነው፡፡
   መ. ይህ ከብሉይ ኪዳን ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ የተገኘ ነው፡፡ የኢሳይያስ አባት ""አሞጽ" ዝ.ከ. (ኢሳ 1፡1) በተለየ መልኩ የተቀመጠ ነው ፊደሉ፡፡ በሉቃስ 3፡25 ላይ ባለው የዘር ሀረግ ውስጥም ተጠቅሷል፡፡

II. ቅዱስ አጻጻፉ
   ሀ. ይህ የነብዩ መፅሐፍ በደቂቅ ነቢያት ክፍል የሚመደብ ነው፡፡
   ለ. ይህ ነብይ ከአስራ ሁለቱ ደቂቀ ነብያቶች አንዱ ነው (ይህም ማለት ከአጫጭሮቹ ትንቢታዊ መፅሐፎች)
   ሐ. የአስራ ሁለቱ ወይም የደቂቀ ነቢያቶች ቅደም ተከተል በብዙ አዋቂዎች ታሪካዊ ከሆኑ ሂደቶች የተገኘ ነበር፡፡ ነገር ግን ከዚህ አስተያየት ጋር የተያያዙ ችግሮች ነበሩ፡፡
      1. የመጀመሪያዎቹ ስድስት መጽሐፎች በማሶሬቲኩ እና የሰባ ሊቃናት ትርጉምመካከል ልዩነት አላቸው

| **ማሶሬቲኩ** | **LXX** |
|---|---|
| ሆሴዕ | ሆሴዕ |
| ኢዩኤል | አሞጽ |
| አሞፅ | ሚኪያስ |
| አብድዩ | ኢዩኤል |
| ዮናስ | አብድዩ |
| ሚኪያስ | ዮናስ |

      2. የጠለቁ መረጃዎች አሞፅን ከሆሴዕ በፊት ታሪካዊ ቦታ ይሰጡታል
      3. የኢዩኤል ጊዜ ከፍተኛ ክርክር አለው፡፡ እኔ ግን ኢዩአልን እንደ አብድዩ ከምርኮ በፊት ከነበሩ ነቢያቶች ጋር እመድበዋለሁ፡፡

III. ዘውጉ
   ሀ. ይህ መጽሐፍ ካላቸው ነቢያቶች የመጀመሪየው እና ቀጥለው ለሚመጡት ዘውግን ያስቀምጣል፡፡
   ለ. ይህም ማለት ጥንታዊ አስደናቂ ዕብራይስጥ ትንበያ ነው፡፡ ይህ ለዕብራይስጥ ሥነ-ግጥም እና ልበወለድ ጥሩ ምሳሌ ነው፡፡ ስለሂብሩ ግጥም በ 1፡2 ላይ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡፡
   ሐ. "የአሞፅ" ፅሁፎች ይህን ያህል ተዋቂ አይደሉም፡፡ የኋለኞቹ ነቢያቶች ከሚባለው አስገራሚ ፅሑፍ ጀምሮ፡፡ (ከኢሳያስ እስከ ሚልኪያስ) አሞፅ በስሜታዊነት የእግዚአብሔርን መጪ ፍርድ ለማሳወቅ የቀብር ስርዓት ሙሾ መለኪያን ተጠቅሟል፡፡ መልክ፤ መለኪያ እና ይዞት የፍርድ መልዕክት በሚገባ ለማስተላለፍ ይጠቅማሉ፡፡
   መ. ቀጥሎ የተዘረዘሩት የተወሰኑ ጥሩ ጥቅሶች ናቸው፡፡
      1. ለዚህ ጊዜ ነብዮች ጥሩ ማጠቃለያ በ Expositor's Bible commentary ጥራዝ 17፣ "አሞፅ" ውስጥ ይገኛሉ፡፡
         " ሆኖም ግን በተመሳሳይ ጊዜ የ18ኛው ክ/ዘመን ዓለም ከዚህ በፊት አውቆት የማያውቀውን በጣም ብቃት ያለው የግብረገብ ኃይል ማለትም በነብዮች ፅሑፍ እንደነበረ መስክረዋል፡፡ እንዚህ ሰዎች በጣም ሰፋት ካለው የተለያዩ ቅድመ ታሪክ ያለቸው ሲሆኑ እግዚአብሔር የጠራቸው ስለመሆኑ የጋራ ጠንካራ እምነት ነበራቸው፡፡ እነዚህም ነብዮች የተለያየ የአኗኗር ስልት ቢኖራቸውም ሁሉም ግን የፃፉት ሁሉን በሚችለው አምላክ የበላይነት ነው፡፡ ነብዮቹ በወቅቱ በነበረው ኃጥያቶች ላይ ተናግረዋል፡፡ በተጨማሪም ለሁለቱም አይሁድ እና አህዛብ ነፃ ስለመውጣት ሲናገሩ ወደፊት የሚመጣው ርቀው በተንበይ ነበር (ገጽ 269)
      2. Kyle M Yates በአሞጽ ላይ አጥንቷል፡፡
         "አሞጽ ፈፅሞ ሊሚተማመኑ የሚችሉበት ዓይነት ሰው አልነበረም፡፡ በእሱ እይታዎች አንድ ሰው ቢስማማም ባይስማማም የነብዩ መልዕክት የሚመጣው ለውጥ ግን ዘላቂነት ነበረው፡፡ ያለፈው 27ኛው ክፍለ ዘመን ይህን የሚያመጣውን ለውጥ አልሸፋፍነውም፡፡ የዚህን የእግዚያብሔር ሰው ባህሪ በጥልቀት የተመለከተ እና የነብዩን መልዕክተ በሚገባ ያጠና ማንኛውም ሰው ህይወቱ ከዚህ በፊት እንደነበረ አይሆንም፡፡ የዛሬውን ህብርተሰብ የተዛባ ፍርዶችን በቀላሉ አይቀበልም ወይም ደግሞ እግዚአብሔር ለሁሉም ልጆቹ ያለውን መልካም ነገር ማየት ይችላል፡፡"
      3. ደቂቀ ነብያቶች፤ Theo Laetsch
         በብሉይ ኪዳን ስነምድር አራቱ ታላቅ ኮከብ ነብዮች አሞፅ፣ ሆሴ፣ ኢሳያስ እና ሚኪያስ የእግዚያብሔር ህዝብ የከበበውን የኃጥያት ጎርፍ እና የማይመለስ መጥፎነታቸውን በግልፅ ለማሳየት የሞከሩ እውነተኛ ተጠቃሽ የእግዚአብሔር ሰዎች ናቸው፡፡
         በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሀብታሙን ከድህው፣ ወጣቱን ከሽማግሌው፣ የተጨቆኑ አማፂዎችን ከትምክተኞች አምባገነን ሳይለይ በታላቅ ታዛዥነት እና ፍላጎት የእግዚያብሔር ቅዱስ ህግ እንደነዚህ ነብዮች ተሰብኮ አይታወቅም፡፡ እንዲሁም ደግሞ በብሉይ ኪዳን ዘመን ውስጥ በየትኛውም ጊዜ ወንጌል በግልፅ ቋንቋ እና ጣፋጭ በሆነ መልኩ በእግዚያብሔር ምሪት ከነዚህ ሰዎች ውጭ ተሰብኮ እና ታውጀ አያውቅም፡፡ ሆኖም ግን የነዚህ ሰዎች ታማኝ ጥረት እና ለህዝባቸው ያላቸው ቅን ምኞት በቃላት ሊገለፅ ከማይችለው ኃጥያታቸው እና የማይሰሙ ሰዎችን ጠራርጎ ከሚወስደው የእግዚብሄር ፍርድ ከሆነውን የጥፋት ውሃ ሊመልሰው አልቻለም ነበር፡፡ እነዚህ ነብዮች ምንም እንኳን ያገኙት ስኬት የተወሰነ ቢሆንም ለመቶ ትውልድ የንሰሃ መግባት እና የነፃ መውጣት ጥሪያቸውን ቀጥለው የነበረ ሲሆን ከላይ ለሆነው ጥሪያቸውም ታማኝነታቸውንም አሳይተዋል፡፡ መልዕክታቸው ዛሬም

ለጊዜው አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ ከ 2500 ዓመታት በፊትም ያስፈልግ ነበር፡፡ ይህም ለዘላለም የሚፀና የእግዚያብሔር ቃል ነው (ገጽ 136)፡፡

IV. ደራሲው

ሀ. የአይሁድ ባህል ሁሌም እንዲያረጋግጠው ፀሃፊው የቴቁቁሔው አሞፅ እንደሆነ ነው፡፡

ለ. ሰውዬው

1. የቴቁሔው የሆነ አይሁዳዊ ነበር፡፡ ("አስተዋይ ሰዎች" ተብለው ከሚታወቁት ዝ.ከ. 2ተኛ ሳሙ14)
   ይህም ቦታ ከቤተልሄም በደቡብ ምስራቅ 5 ማይልስ ላይ ያለ ሲሆን የተቀመጠውም በክልሉ ተራራማ (2700) ቦታ ላይ ነው፡፡(The international Standard Bible Encyclopedia ጥራዝ 1 ገጽ 120)፡፡
2. እሱ ነብይ ወይም ከነቢያት ቤተሰቦች ወይም ደግሞ በህብረት የሚኖሩ ማህበረሰቦች አባል አልነበረም፡፡ ( 7:14)
   በመጀመሪያ ነቢያቶች ይኖሩ የነበሩት በህብረተሰብ ውስጥ በአንድ ላይ ነበር፡፡ በኋላ ግን የተወሰኑት በቤተመንገስት ውስጥ ሊታዩ ችለዋል፡፡
3. በግልፅ እንደሚታየው "የትንሽ በጎች" (አረባዊ) ጠባቂ ነበር፡፡ (BDB 667፤KB 719-720፣ 1:1 ሊሆን የሚችለው " የበግ ጠባቂ"፣ " የበግ ሻጭ " ወይም " የበግ ባለቤት" [ 2ተኛ ነገ 3፡4]) እረኛ (BDB 133) የተለየ እና የተለመደ ቃል ሲሆን በ7፡14 ውስጥ እሱን ለመግለፅ ተጠቅሷል፡፡
4. (1) የፍራፍሬ ዛፎች ባለቤት ነበር፡፡ ወይም (2) "የወርካ ለቃሚ" ( 7:14) ይህም ሊጠቁም የሚችለው በየሙቱ ወደ ሌላ ቦታዎች እንደሚንቀሳቀስ ነው፡፡ እነዚህ ዛፎ "የሾላ ፍሬ ዘር" ይባላሉ፡፡ የወርካ ፍሬው ባብዛኛው የሾላ ፍሬን ይመስላል፡፡ እያንዳንዱ "የሾላ ፍሬ" በአግባቡ እንዲበስል በተናጠል መበሳት ነበረባቸው፡፡ ይህ ለመዕራቢያውያን ሰዎች በጣም አስፈላጊ የእህል ዘራቸው ነበር፡፡ ዳዊት ራሱ እነዚህን የእህል ዘሮች እንዲጠብቁ ልዩ ተከታታዮችን አሰራቶ ነበር፡፡ ( 1ኛ ዜና 27፡28) ብዙዎቹ የአሞፅ ትንቢቶች መነሻ በግብርና ላይ ያሳለፈው ህይወቱ ነበር፡፡
   - ሀ. 1፡2
     - (1) የዱር እንስሳቶች 3፡3-8፤5፡19
     - (2) ለግጦሽ ማሰማሪያ መሬት
     - (3) ድርቅ
   - ለ. 2፡13 የተሞላ ሰረገላ
   - ሐ. 4፡6-9
     - (1) የእንጀራ እጥረት ቁ 6
     - (2) ለእህል ዘሮች ዝናብ የለም ቁ 7
     - (3) የሚጠጣ ውሃ የለም ቁ 8
     - (4) ደረቅ ንፋስ ቁ 9
     - (5) አረማሞ ቁ 9
     - (6) በራሪ ነፋሳቶች ቁ 9
   - መ. 5፡16-17
     - (1) አልቃሽ ገበሬዎች ቁ 16
     - (2) እየጠፉ ያለ የወይን ማሳ ቁ 17
   - ሠ. 7፡1-6
     - (1) የአንበጣ መንጋ ቁ 1-2
     - (2) እሳት ቁ 4
   - ረ. የቃርሚያ ፍሬ
   - ሰ. የግብርና ምርታማነት ወቅት የYHWHን መኖር እና ባርኮት አመላካች ናቸው፡፡
5. የአይድ ባህል እንደሚለው እርሱ ምርጥ የንግድ ሰው ነው፡፡ ይህ አባባል ግን "እርሱ የደሀ አገር ገበሬ" ከሚለው ከአሁኑ ጊዜ የተለመደ አመለካከት በእጅጉ የተለየ ነው፡፡ እርሱ ባለው የስነግጥም እና የስነ ፅሁፍ የበቃ ክሎት ምክንያት ግን የአይሁድ ባህል ልክ ሊሆን ይችላል፡፡ ከ2ኛ ሳሙ 14፡2ff እንደምናውቀው ከሆነ ቁቁሔ በአስተዋይ ዜጎቿ በተለየ ትታወቃለች፡፡ እርሱ መልእክቶቹ በአንድ ጥራዝ መፅሐፍ የተመዘገበለት የመጀመሪያው ነብይ ነበር፡፡የመጀመሪያ ሰው ተውላጠስ 5፡1፤7፤1-9፤8፡1፤ እና 9፡1 ውስጥ አስተውል፡፡
6. ስብከቱም ለሰሜናዊ የእስራኤል ግዛት ነው፡፡ ምንም እንኳን ብዙ የስብከት ቦታዎች ቢኖሩም በእርግጠኝነት እንደምናውቀው ቤተልሔም (ይህም ማለት ወርቃማው ጥጃ ያለበት ቦታ) የቤቴል ጣኦት ያለበት የስብከት ቦታው እንደ ነበር፡፡

ሐ. የጸሓፊው ችግሮች ግራ የሚያጋቡ ናቸው ምክንያቱም፡-

1. መፀሀፉ እንደሚያመለክተው እርሱ ደሀ የግብርና ሠራተኛ ነበር፡፡
2. የግጥሞቹ ስልትና ይዘት እጅግ በጣም ጥሩዎች ናቸው፡፡ ይህ የሚያመለክተውም በደንብ የተማረ ግለሠብን ነው፡፡
3. አስተምህሮቶቹ የሚተላለፉት በንግግር ቢሆንም ወዋሠውን የጠበቁና የተመጠኑ ናቸው፡፡ ይህም ሥነፅሁፋዊ መሆናቸውን ነው፡፡
4. ብዙ ምሁራን አሞፅ የፅሑፍ አዘጋጅና ፀሐፊ ድጋፍ እንደነበረው ታሳቢ ያደርጋሉ፡፡ ፀሐፊ እንደነበረው ማስረጃ የሚሆነውም 7፡10-17 ላይ የተገለፀውም በ3ተኛ ወገን ሰው ሲሆን፤ በ 7፡1-9፤8፡1-2፣ 9፡1 ደግሞ በመጀመሪያ ወገን ነው (The Expositor's Bible Commentary፣ ጥራዝ 7 ገፅ 271 ይመልከቱ)፡፡
5. እኛ የዚህ ዘመን ሠዎች እነዚህ ቅዱስ መፅሀፎች እንዴት እንደተፃፉና እንደተዋቀሩ ልክ እንደ ብሉይ ኪዳን ሰዎች አናውቅም፡፡ ሆኖም የበላይ ደራሲው የእግዚአብሔር መንፈስ ነው፡፡ እዚህ ላይ ዋናው አስፈላጊ ቁምነገር ሌላ ሣይሆን መፀሀፎቹ የያዙት ይዘት ነው፡፡ ቅዱሳን መፅሐፍቶች ከእግዚአብሔር ለሁሉም እድሜና ባህል የሚሆኑ በተለይም ደግሞ ሰው ሀብቱና እና ሃይሉ ሊያደርጋቸው የሚችሉ ናቸው፡፡

V. ጊዜው

ሀ. ይህ ትንቢት ከ750 ዓ ም 10 ዓመት በፊት ወይም ኋላ እንደተከወነ ለመናገር በአንፃራዊነት ቀላል ነው፡፡

ለ. የመጀመሪያው የአሞጽ ጥቅስ አረጅሙ እና ከማንኛውም የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ በጊዜ አገላለፁ በጣም ግልፅ ነው፡፡
1. ዖዚያን የነገሠው ከ783-742 አካባቢ ነው (ብራይት)
2. ኢዮርብአም የነገሠው ከ786-746 አካባቢ ነው(ብራይት)
3. የመሬት መንቀጥቀጥም የመፅሐፉን ጊዜ ለማወቅ ያስችል እንደሆነ ተሞክሯል (ዝ.ከ. 1:1፤8:8፤9:1፤5 ዘካ 14:5)፡፡ Josephus ይህን እውነት ከ 2ኛchr 26:16-21 ካለው ዖዚያን መሥዋትነትን ሲመርጥ ካለው እውነት ጋር ያያይዘዋል፡፡ በሀዞር የተካሄዱት የአርኪዎሎጂ ጥናቶች 760 አካባቢን ይጠቁማሉ(ያዲን 1964)፡፡

ሐ. በ 5:8 እና 8:9 ላይ ግርዶሽ ተጠቅሷል፡፡ ምንም እኳን Feb 9 784ከክርስቶስ ልደት በፊት ሙሉ ግርዶሽ ቢኖርም ይህ በ ሰኔ 15፤ 763 ከክርስቶስ ልደት በፊት በአሶሪን መዛግብት ከተገለፀው ግርዶሽ ገር ተመሣሣይ ሣይሆን አይቀርም፡፡

መ. አሞጽ ከአማሲያስ (በኢዮርብዓም አመራር ስር በነበረችው ቤተልሄም መሪ ካህን የነበረ) ጋር ተጋጨ፡፡ ይህም የመፀሀፉን ጊዜ ይጠቁማል፡፡

VI. ታሪካዊውን መቼት (መቼና የት) ለማመልከት ያሉት ምንጮች

ሀ. ጎን ለጎን የሚሄዱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ የሚገኘው
1. 2ኛ ነገ 14:3-17:6
2. 2ኛ ዜና 25-28
3. ሆሴ
4. ኢሳያስ
5. ሚኪያስ

ለ. በእግዚአብሔር ህዝብ ማዕከል ጣኦት የማምለክ ሁኔታ ቀላል የሆነ ማጠቃለያ በሄሴ ውስጥ ማየት ይቻላል፡፡
1. 2-16 "ዳግመኛ በኣሌ ብለሽ አትጠሪኝም"
2. 4:12-13 "ሴት ልጆቻችሁ ይጎለሙታሉ"
3. 4:17 "ኤፍሬም ከጣኦታት ጋር ተጋጠመ ፤ ተወው"
4. 13:2 "ሰዎች እምቦሳውን ይሳሙ" (ባህላዊ)

ሐ. የማህበራዊ መነሻ
1. ጊዜው ለእስራኤል እና ለአይሁድ የኢኮኖሚክ ብልፅግና እና የጦር ኃይል መስፋፋት የነበረበት ነበር፡፡ ሆኖም ግን ይህ ብልፅግና ጥቅሙ ለበለፀገው ክፍል ብቻ ነበር፡፡ ደሀው እና መካከለኛ ክፍሎች ይመዘበሩ እና ይጨቆኑ ነበር፡፡ ባጠቃለይ ነገሩ " ገንዘብ እና ሽጉጥ " ተጨማሪ ጣኦቶች የሆኑ ይመስል ነበር፡፡
2. የሁለቱም የእስራኤል እና የአይሁድ ማህበረሰብ መረጋጋት እና ንብረት ከተለያዩ መንሰኤዎች ጋር ይዛመዳል፡፡
   ሀ. በሰሜን የኢዮርዓም የረጅም እና የተትረፈረፈ ንግስና እንዲሁም በደቡብ የ ዖዝያን (783-742 )
   ለ. የግብፅ እና የመሶፖታሚያ ጊዜያዊ የሆነ መንሸራተት
   ሐ. ከክርስቶስ ልደት በፊት በ 805 በሶሪያ መሸነፍ
   መ. በእስራኤል እና በይሁዳ መካከል ግጭት ማነስ
   ሠ. ምንም እንኳን የባለፀጋ ክፍሉ አባካኝነትም ቢኖርም በፍልስጤም መሬት በኩል ከሰሜን ወደ ደቡብ ይካሄድ የነበረው አገባበር እና ብዝበዛ ላፈጣኑ የኢኮኖሚ ዕድገት ምክንያት ነበር፡፡
3. በኢዮርዓም 2ተኛ ንግስና ጊዜ የነበረው "የሰማሪያ ኦስትራካ" በሰለሞን ጊዜ እንደነበረው አስተዳዳራዊ ድርጅት እንደነበረ ያለክታል፡፡ ይህም ሊያረጋግጥልን የሚችለው ባላቸው እና በሌላቸው መሃከል ያለውን ክፍተት ነው፡፡
4. የባለፀገው አለመታመን "የህብረተሰብ ፍትህ ነብይ" በሚባለው አሞጽ ውስጥ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ በተያያዥነትም በሁለቱም በእስራኤል እና በይሁዳ የተለመደውን የፍትህ አካላት ማጭበርበርኝ እና የተዛባው የንግድ ተፅዕኖን ጥቃት ሊያሳዩ የሚችሉ ሁለት ምሳሌዎች ናቸው፡፡

መ. ሃይማኖታዊ መነሻ
1. ጊዜው ውሸት የሆነ ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ የሚታይበት ነበር፡፡ ነገር ግን ትንሽም ቢሆን እውነተኛ እምነት ነበር፡፡ እየሰፋ የመጣው የአህዛብ አምልኮ ሰርዓት በእስራኤል ኃይማኖት ሰርጾ ገብቶ ነበር፡፡ የተባበሩት ህዝቦቹ ጣኦት አምላኪዎች ነበሩ። ነገር ግን የYHWH ብለው ጠርተውታል፡፡ የእግዚሃብሄር ህዝቦች ወደ ፖለቲካው የማዘንበላቸው ልምምድ በሃይማኖት የለሽ አምልኮ እና ልምምዶች ውስጥ እንዲገቡ አድርጓቸዋል፡፡
2. የእስራኤል ጣኦት አምላኮነት መጨመሩ በ2ተኛ ነገ 17:7-18 ተገልፅዋል፡፡
   ሀ. ቁጥር 8 የአህዛብን የአምልኮ ልምምድ ተከትለዋል፡፡
      (1.) የብልጽግና አምልኮ
         (ሀ) ከፍታ ቦታዎች ቁ 9፤ 10፤ 11
         (ለ) የኃይማኖት ሃውልቶች (በኣል)ቁ 10፤16
         (ሐ) አሸሪም (Asherim) ቀ 16፣ እነዚህ የእንጨት ምልክቶች ሲሆኑ የሚወክሉትም የበኣል ሴት አስተዳዳሪን ነበር፡፡ የተጣመሙ እንጨቶች ወይም በህይወት ያሉ ዛፎች ነበሩ፡፡
      (2.) ምትሃታዊ ቁ 17፤ ይህ በዝርዝር በLev 19-20 እና ዘዳ 18 ተብራርቷል፡፡
   ለ. ቁጥር 16፤YHWHን በመተካት በዳን እና በቤተል ኢዮርብዓም ሁለተኛ ያስቀመጣቸውን ሁለቱን ወርቃማ የጎሽ

ምስሎች ማምለክ ቀጥለው ነበር፡፡(1ኛነገ 12:28-29)

ሐ. ቁጥር 16፤ የባቢሎንን የተፈጥሮ ጣኦቶችን ያመልኩ ነበር፡፡ ፀሀይ፣ ጨረቃ፣ ኮከቦች እና ስማ ያላቸውን ኮከቦች

መ. ቁጥር 18፤ የፊኖሺያ የብልፅግና እሳት ጣኦት Molech ያመልኩ ነበር (ዝ.ከ. Lev 18:21፤20:2-5)

3. በአሊዝም (ዝ.ከ. W F Albright's Archaeology and the Religion of Isrreal ገጽ 82FF)

ሀ. የእኛ ምርጥ ምንጭ "Ba'al Epic of Ugarit" ነው፡፡

(1.) በዓል ወቅቱን ጠበወቆ የሚነሳና የሚሞት ጣኦት እንደሆነ ይጠቁማል፡፡በ Mot ከተሸነፈ በኋላ ከሙታን አለም ተቀላቅሏል፡፡ ሁሉም በምድር ላይ የነበረው ህይወቱ ቆሟል፡፡ነገር ግን በሴቷ የሀሰት አምላክ እርዳታ ከሞት ይነሳና በያንዳንዱ ክረምት Motን ያሸንፍ ነበር፡፡በማስመሰያ ምትሃቶች የሚመለክ ሐሰተኛ የብልፅግና አምላክ ነበር፡፡

(2.) Hadad በመባልም ይታወቅ ነበር፡፡

ለ. ኤል የአህዛብ ህዝብ ዋና ሃሰተኛ አምላክ ሲሆን ነገር ግን የበኣል ዝነኝነት ቦታውን አስነጥቆታል፡፡

ሐ. እስራኤል በንጉስ ጣይር ልጅ በነበራቸው ጃዝቤል ከኢራን በአሊዝም ተፅዕኖ ይደረግባት ነበር፡፡ ኤልዛቤል ኦምሪ ለልጁ አሃብ የመረጣት ነበረች፡፡

መ. በእስራኤል ውስጥ በኣል በአካባቢው ከፍታ ቦታዎች ላይ ይመለክ ነበር፡፡ በኣልም ከፍታ ላይ ባለ ድንጋ ይወከል ይመለከት ነበር፡፡ አሸራ የእሱ ሚስት ስትሆን የተወከለችውም የህይወትን ዛፍ በሚወክል ከእንጨት በተሰራ ምስል ነው፡፡

4. ብዛት ያላቸው የጣኦት ዓምልኮ ዓይነቶች እና ምንጮች ተጠቅሰዋል

ሀ. YHWHን ለማምለክ በቤቴል እና ዳን ኢዮርብዓም II ያሰራቸው ወርቃማ ጎሾች

ለ. በአካባቢው ከፍታ ቦታዎች የኢራንን የብልፅግና ጣኦታት እና ጣኦቶችን ማምለክ

ሐ. በዚያን ጊዜ በፖለቲካው የነበረው ጠንካራ የጣኦት አምልኮ ግንኙነት

ሠ. በሰሜን ውስጥ የፓለቲካ መቼት

1. ኢዮርብዓም 2ተኛ የእስራኤል የመጨረሻው ጠንካራ ንጉስ ነበር፡፡ በአይሁድ የዘር ግንድ አራተኛ የነበረ እና የመጨረሻው እንደሊነግስ የተገመተለት ነበር(ዝ.ከ. 2ተኛ kgs 10:30) በፖለቲካው የተሣካለት እና ለረዝም ጊዜ የነገሰ ነበር (756-746 ከክርስቶስ ልደት በፊት)

2. ኢዮርብዓም 2ተኛ ሞት በኋላ በሃያ አምስት አመት ጊዜ ውስጥ ስድስት ንጉሶች ነበሩ፡፡

ሀ. ዘካሪያስ (2ተኛ ነግ 15 : 8-12) ስድስት ወራት ብቻ ከነገሰ በኋላ ነበር የተገደለው፡፡

ለ. ሻሎም (2ኛ ነገ 15:13-15) አንድ ወር ብቻ ከነገሰ በኋላ ነበር የተገደለው፡፡

ሐ. መናሂም (2ኛ ነገ 15:16-22) ለአስር አመታት ነግሶ ነበር ነገር ግን ለ... ከባድ ግብር ከፍሏል፡፡

መ. ርካሂን (2ኛ ነገ 15:23-26) ሁለት አመታት ከነገሰ በኋላ ተገድሏል፡፡

ሰ. ፐካ (2ኛ ነገ 15፡ 27-31) አምስት አመታት ከነገሠ በኋላ ተገድሏል፡፡ በአሶሪ ብዙ ከተሞችን ተነጥቋል፡፡

ረ. ሆሴዕ (2ኛ ነገ 15:3፤17:1-6) ለዘጠኛ አመታት ከነገሰ በኋላ ሰማሪያ ስትወድቅ በአሴሪያ በ722 ከአገሩ ተባሯል፡፡

3. በ18ኛው ክፍለ ዘመን ፍልስጤምን የነካው የአሶሪያ እና የባቢሎን ወረራዎች የተብራ ማጠቃለያ

ሀ. አራቱ የ18ኛው ክፍለ ዘመን ነቢያቶች በአሶሪያ የቲግሪስ-ኤፍራጥስ ግዛት በተነሳ ጊዜ ይንቀሳቀሱ ነበር፡፡ እስራኤልን በተመለከተ እግዚአብሔር ይህን ጨካኝ መንግስት በህዝቡ ላይ እንዲፈርዱ ማድረግ ይችል ነበር፡፡ "Syro-Ephramatic League" ተብሎ ሚጠራው የ ትራን ጆረዳን ፖለቲካ እና ወታደራዊ ሃይል ዝምድና መመስረት ተጠቃሹ ክስተት ነበር (735 ከክርስቶስ ልደት በፊት) ሶርያ እና እስራኤል በአሶር ላይ ለመነሳት ይሁዳን ለማስገደድ ሞክረው ነበር። ነገር ግን በተቃራኒው የጁዳ ንጉስ የነበረው አሃዝ እርዳታን የሚጠይቅ ደብዳቤ ለአሶሪ Qal፡፡ ግዛት የማስፋፋት ከፍተኛ ፍላጎት የነበረው ጠንካው የአሶሪያ Assyrian ንጉስ ተልገልተልፈልሶር(III) ለወታደራዊ ሀይል ችግር ምላሽ በመስጠት ሶሪያን ወረረ፡፡ ትንሽ ቆቶ በእስራኤል ውስጥ የነበረው የአሶሪ ተወካይ መንግስት ግብፅን በመመካት አመፀ፡፡ ሸልማነስተር Shalmanester 5th እንደገና እስራኤልን ወረረ፡፡ እስራኤል በቁጥጥር ስር ከመሆኗ በፊት ሞተ፡፡ ነገር ግን የሱ ተከታይ የነበረው ሳርጎን Sargon 2nd ከክስቶስ ልደት በፊት በ722 የእስራኤልን ዋና ከተማ ሰማያን ያዘ፡፡ በዚህ ወቅት ኦሶሪያ ከ27፤000 በላይ የሆኑ እስራኤሎችን ወደ ነበሩበት መልሳለች ምክንያቱም ትግላት ፓለሳር ከዚህ በፊት ከክርስቶስ ልደት በፊት በ732 በሺ የሚቆጠሩትን አስወጥቷቸው ነበር፡፡

ለ. አከአዝዝ (735-715 አከልበ ) ከሞተ በኋላ (ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ735-715) በአሶሪያ ላይ ሌላ የትራንስ ጆርዳን ሀገሮች እና ግብፅ የወተደራዊ ሃይል ጥምረት ተመስርቶ ነበር፡፡ ይህም "የአሽዶድ ማመጽ" ይባል ነበር አሶሪያ ስትወረር ብዙ የይሁዳ ከተሞች ወድመው ነበር፡፡ በመጀመሪያ Hezekia ይህን ጥምረት ደግፎት ነበር ኋላ ላይ ግን ያደርግ የነበረውን ድጋፍ አቋርጧል፡፡

ሐ. ሆኖም ግን እንደገና የአሶሪያን ጠንካራ ንጉስ ሳርጎን II፤ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ705 መሞት ተከትሎ በአሶሪያን ግዛ በአማፅያን ሌላ ጥምረት ተሞከሯል፡፡ ህዝቅያስ በዚህ አመፅ መሃል ሰናቸሪብ ከክርስቶስ ልደት በፊት (705-681) ፍልስጤምን በመውረር በእየሩሳሌም ከተማ አቅራቢያ ሰፍሮ ነበር (II ነግ 18-19፤ ኢሳ 36-39)፡፡ ነገር ግን የሰናከረሬብ ወታደሮች በእግዚአብሔር ታአምር ወድመዋል፡፡ ሰናከሬብ ምን ያህል ጊዜ ፍልስጤምን እንደወረረ በምሁራን መሀከል የተወሰነ ጥያቄ አለ (ለምሳሌ ዮሃንስ ብራይት አንዱ ወረራ እና ምናልባትም ሊሆን የሚችል አንዱ በ 688 ከክርስቶስ ልደት በፊት ዝ.ከ. ገጽ 270)፡፡ ህዝቅያስ ከአሶርን በሀይል መወረር ድኖ ነበር ግን የይሁዳን ሀብት ባቢሎን ከማሳየቱ ትዕቢት የተነሳ ኢሳይያስ የይሁዳን መውደቅ አመለከተ (39:1-8)፡፡ በ 587-586... እየሩሳሌም ናቡከደናጾር ላይ ወድቃለች

መ. በተጨማም ኢሳያስ እግዚአብሔር ህዝብ በቂሮስ II ስር እንደሚደራጁ ተንብዮ ነበር በፋርስና ሜዶን ገዥ (41:2-4፤ 44:28፤ 45:1፤ 56:11)፡፡ በ612 ነኔዌ ወደቀች በቢሎን ፣ ነገር ግን የባቢሎን ከተማ በ539 የቂሮስ ጦር እጅ ወድቃለች፡፡ ቂሮስ በ 538 አይሁዶችን ጨምሮ ሁሉም ከሃገራቸው የተባረሩ ወደ ሃገራቸው እንዲመለሱ የሚየዝ ትዕዛዝ አውጥቷል፡፡ በተጨማም ... ከበዛው ሀብቱ የሃገራቱን ቤተመቅደስ እንደገና ለመገንባት የሚያስችል የገንዘብ እርዳታ አድርጓል፡፡

VII. የስነፅሁፍ ምዕራፎች

ሀ. በህዝቦች ላይ የተደረገ ... 1:1-2:3 (ምናልባትም 2:16)

1. ሶሪያ (ዲማስቆ )፤ 1:3-5
2. ፍልስጥኤም (ጋዛ) ፤ 1:6-8
3. ፎነሺያ (ጋዛ)፤ 1:9-10
4. ኤዶም ፤ 1:11-12
5. አሞን 1:13-15
6. ሞአብ 2:1-3

ለ. በእግዚአብሔር ህዝብ ላይ ልዩ ክስ 2:4፤ 6:14
1. ይሁዳ 2፡ 4-5
2. እስራኤል 2:6-6፣ 14 (በእስራኤል ላይ

ሐ. የፍርድ ራዕይ 7:1-9፡ 10
1. የአንበጣ መንጋ 7:1-3
2. እሳት 7:4-6
3. ተጣሚ መስመር 7:7-17
4. የክረምት ፍሬ 8:1-14
5. የተቀደሰን ቦታ ማቆርቆዝ 9:1-10

መ. የመሲሁ ተስፋ 9:11-15 አንዳንድ ምሁራን እንደሚመከሩት ይህ ምክንያታዊ የስነፅሁፍ መዎቅር እንጂ ታካዊ ቅደም ተከተልን የያዘ መዋቅር አይደለም፡፡ አሞፅ የሰበከው ለአጭር የጊዜ ገደብ ነው፡፡ ይዘቶቹ የእሱ ናቸው ነገር ግን መዋቅሩ የአሞፅን ትንበያ መዝግቦ የያዘ የአንድ ፀሐፊ ሊሆን ይችላል፡፡

VIII. ዋና እውነቶች

ሀ. አሞፅ የእግዚአብሔር ን ቁጣ ከእስራኤል (እና የእስራኤል ጎረቤቶች) የሙሴን ህግጋት መተላለፍ ጋር ያዛምደዋል፡፡ እኛ በብሉይ ኪዳን የጋራ ኃላፊነት እና በግል ዕምነት መካከል ያለውን ዝምድና ማወቅ ይገባናል፡፡ እኛ እስራኤል እንዳደረገችው ማህበረሰቢዊ የሆነ ኃጢያትአሰጠን ሆኖም ግን በአህመሮአችን ሁለት ስርዓቶች ይሆራ፡፡
1. የግል ነፃ የሆነ ኑሮአችን እና እምነታችን
2. ህብረተሰባዊ የጋራ ኖሮአችን፡፡
    እስራኤል አሞፅ እንደተናገረው በከበቧት ጎረቤቶቿ (እና ባህላዊ ጠላቶች) ላይ በሚሆነው የያህዌን ፍርድ መደሰት ይኖርበታል፡፡ የእስራኤል ህዝብ የዳዊት እና የሰሎሞን ግዛት አካሎች ስለነበሩ የሙሴን ህግጋት እና የእስራኤልን አምላክ ማወቅ አለባቸው፡፡ እስራኤል ህዝብ አሞፅ የእግዚአብሔርን ፍርድ በተፎካካሪዋ የሁዳ ላይ በማምጣቱም ደግሞ መደሰት አለባቸው፡፡ ነገር ግን አሞፅ በእነዚህ የሰሜን ነገዶች ላይ ወደ ነበረው ኃጥአት ጊዜውን ጠብቆ ሲመለስ ስሜታዊ የነበረው አቀባበላቸው ወዲያውኑ ቆመ፡፡

ለ. የእግዚአብሔር በምድር ሁሉ ላይ መንገስ ከእስራኤል ውጪ ለነበረው ህዝብ ፍርድን ለሚሰጠው ያህዌ ከለላ ነበር፡፡ ይህ ለእስራኤል የእግዚአብሔር ን አንድነት መረጃ መሰረት ነው፡፡ ማጣቀሻ *(Encyclopedia Judaica)* ጥራዝ 2 ገፅ 889)
አፈጣጠር እና ተፈጥሮን ከመቆጣጠሩ ከያህዌ ጋር የሚዛመዱ ብዙ ገፅ ጽሁፎች አሉ፡፡ ዘኪ 4:13፣ 5:8-9፣ 8:8፣ 9:5-6) ይህም እግዚአብሔር የማምለኪያ ቃላትን ይፈጥራል፡፡ ይህ መፅሐፍ ፍጥረትን እንድ እግዚአብሔር መግለጫ ያየዋል (ማለት የመሬት መንቀጥቀጥ፣ ግዶሽ እና ዘዳ 27-29 እንደተመለከተው)፡፡

ሐ. በአሞፅ 2:9-12 እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ያደረገው ፍርድ በታከ ውስጥ የእግዚአብሔርን ማሀሪነት የሚያሳይ ሆኖ መታየት አለበት፡፡ የእግዚአብሔር እስራኤልን መምረጥ እና እርቅ ማድረጉ የእግዚአብሔር ን ኃይለኛ ፍርድ ርምጃ ስጀመረ ነው፡፡ ብዙ የተሰጠው ብዙ የጠበቅበታል (ማጣቀሻ ሉቃስ 12:48) የሚባለው መታወስ አለበት፡፡

መ. ምዕራፍ 5 እምነት እና ሕይወትን በማያያዝ የማይነጣጠሉ መሆናቸውን ያስረዳል አሞፅ ሃብታም በደሃው ላይ የሚያደርጉትን ብዝበዛ ለህዝብ ያውጃል፡፡

ሠ. እስራኤል በስህተት የምትተማመን የነበረው
1. በሃይማኖቷን 4:4-5፣ 5:21-23
2. የኢኮኖሚዋን መበልፀግ 6:1
3. የጦር ኃይሏን 2:14-16፣ 6:16፣ 13

ረ ምንም እንኳን የእስራኤል ሐሰት እምነት ውስጥ መሆንም ቢሆን በእግዚያብሔር እቅ ውስጥ ግን ተስፋ አለ ይህም የእግዚአብሔር መሲህ ነው፡፡ 9:8-15

# አሞፅ 1
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|
| | | በእስራኤል ጎረቤቶች ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ (1:1-2:5) | |
| | | | ማውጫ |
| *መግቢያ* 1:1-2 | ከላይ የሚጻፉ 1:1 | 1:1-2 | 1:1 |
| | የጎረቤት ህዝቦች፤ እስራኤልና ይሁዳ የክስ ማስረጃ (1:2-2:16) | | *መግቢያ* |
| | 1:2 | | 1:2 |
| ፍረድ በህዝቦች ላይ | | | ፍረድ በጎረቤት ህዝቦች ላይ እና በራስዋ በእስራኤል ላይ (1:3-2:16) |
| 1:3-5 | 1:3-5 | *ሶሪያ* 1:3-5 | ደማስቆ 1:3-5 |
| 1:6-8 | 1:6-8 | ፍልስጥኤም 1:6-8 | ጋዛና ፍልስጥኤም 1:6-8 |
| | | ጢሮስ 1:9-10 | ጢሮስ እና ፍልስጥኤም 1:9-10 |
| 1:9-10 | 1:9-10 | | |
| 1:11-12 | 1:11-12 | ኤዶም 1:11-12 | ኤዶም 1:11-12 |
| 1:13-14 | 1:13-14 | አሞን 1:13-14 | አሞን 1:13-14 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ vii ተመልከት)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

*ተመስጧዊ ባይሆኑም፣ የአንቀጽ ምድቦች የሚከተለውን የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ ለመረዳት ቁልፍ ናቸው። እያንዳንዱ ዘመናዊ ትርጉም አንቀጾቹን መድቦ ማጠቃለያውን እንዲያቀርብ ተደርጓል። እያንዳንዱ ቅጂ ያንን ርዕስ በራሱ የተለየ መንገድ አጽዕሮቱን አስፍሯል። ጽሑፉን ስታነበው፣ የትኛው ትርጉም በርዕሰ ጉዳይም ሆነ በቁጥር ምድቦች ከአንተ መረዳት ጋር እንደሚስማማ ራስህን ጠይቅ።

በእያንዳንዱ ምዕራፍ በቅድሚያ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ይኖርብናል፣ እንዲሁም ርዕሰ ጉዳዮቹን መለየት (አንቀጾቹን) ። ከዚያም የእኛን መረዳት ከአዲሶቹ ትርጉሞች ጋር ማወዳደር አለብን። መጽሐፍ ቅዱስን ልንረዳ የምንችለው የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ ምን እንደሆነ የሱን አመክኖአዊ (ሎጂክ) እና አቀራረቡን ስንረዳ ነው። ዋነኛው ጸሐፊ ብቻ ነው ተመስጧዊው— አንባብያን መልዕክቱን ለመቀየርም ሆነ ለማሻሻል መብት የላቸውም። የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢዎች ተመስጧዊውን እውነት በየዕለቱና በሕይወታቸው ሁሉ ተግባራዊ ለማድረግ ኋላፊነት አለባቸው።

**ማስታወሻ፡- ሁሉም ሙያዊ ቃላትና አጽሕሮተ ቃላት በሙሉ በቅጥያ አንድ፣ ሁለት፣ እና ሦስት ላይ ተብራርተዋል።**

---

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የአገባብ ስልት

ሀ. የመጀመሪያውና ሁለተኛው ምዕራፎች የእሥራኤል ሕዝብን ኃጥአት በግልፅ ያብራራሉ፡፡ (ዝ.ከ. 2፡6-12) ሁለቱ የመጀመሪያ ቁጥሮች የመጽሐፉ ዋና ሐሳብ ናቸው፡፡ የእሥራኤል ህዝብ (ማለትም የሰሜኖቹ አሥርቱ ጎሳዎች) ከያይዌህ ጋር የነበራቸው ልዩ ግንኙነት አመጸኞች አድርጎአቸዋል፡፡ (ዝ.ከ. ሉቃ 12፡48)፡፡ እነርሱ የቃል ኪዳን ሕዝብ ስለ ነበሩ የቃል ኪዳን ሥራም ነበራቸው፡፡

ለ. አሞጽ ስብከቱን የሚጀምረው በእሥራኤል ጠላት ላይ በተፈረደ ፍርድ ነው፡፡

1. በአከባቢው ላይ ያሉ ሕዝቦች
   ሀ. እምነት የሌላቸው
   ለ. ከአይሁዳዊያን ጋር ግንኙነት ያላቸው (ኤዶም በኤሳው፣ ሞአብ በሎጥ)
2. ዘመዶቿ፣ ይሁዳ

## የቃላትና የሐረጎች ጥናት

**አሞጽ 1፡1-2**

**[1] በቴቁሔ ከላም ጠባቂዎች መካከል የነበረ አሞጽ በይሁዳ ንጉሥ በዖዝያን ዘመን፥ በእስራኤልም ንጉሥ በዮአስ ልጅ በኢዮርብዓም ዘመን፥ የምድር መናወጥ ከሆነበቱ ከሁለት ዓመት በፊት ስለ እስራኤል ያየው ቃል ይህ ነው። እንዲህም አለ፦ እግዚአብሔር በጽዮን ሆኖ ድምፁን ከፍ አድርጎ ይጮኻል፥ በኢየሩሳሌምም ሆኖ ቃሉን ይሰጣል የእረኞችም ማሰማርያዎች ያለቅሳሉ፥ የቀርሜሎስም ራስ ይደርቃል።**

1.1 **"አሞጽ"** ለዚህ ብዙ ጊዜ ለማይታይ ስም ትርጉም መግቢያውን አንብብ፡፡

▣ **"እረኞች"** ይህ ቃል በብሉይ ኪዳን ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ የበጎች እረኛ ተብሎ ተጽፏል፡፡ የተጠቀሙትም ለመስሃ-ለሞአብ ንጉሥ ነው (ዝ.ከ. 2ኛነገ 3፡4)፡፡ ሥራዎቹም ከከብቶች ጋር ይያያዛል (BDB 667፤ KB 719-720)፡፡ የሚያመለክተውም የበጎች ልዩ ባለቤትነት ነው (BDB ፣838 ዝ.ከ. 7፡15)፡፡ አሞጽ (1) የአይሁድን ባህል ሲከተልና የበጎች እርባታን እንደ ንግድ ሥራ ሲሠራ ነበር (የአህዩድ መጽሐፍ ቅዱስ ማጥኛ ገጽ 1177)፡፡ (2) በተጨማሪም ይህ ሰው ደሃ እረኛና አርብቶ አደር ገበሬ ነበር፡፡

የእብራይስጥ ተነባቢ ሥሮው ቃል (*mqd KB 719-720*) ብዙ ትርጉሞች አሉት፡፡

1. *መምታት ወይም መውጋት፣ ሙብሳት*
2. *መጽዳት፣ ብርሃን መስጠት* (በአረቢኛ "*ነፃ ማውጣት*"፣ "*ማዳን*")
3. *ደሃ* (ምስኪን) የሆነ በግ
4. *ገንዘብ* (ትንሽ ሳንቲም)
5. *ጠቃጠቆ* (ዘፍ 30፡22) የተጠቀጠቀ
6. *እረኛ፣ጠባቂ፣ በግ አርቢ*
7. *ማዕረግ፣ ከፍተኛ ሥልጣን*

አገባብ ወሳኝ ነው፡፡ ለቃላት ትርጉም የምስጥ አገባብ ብቻ ነው፡፡ ተዛማች ትርጉሞች ወይም ቃላት የሚያስፈልጉት አልፎ አልፎ ነው፡፡ በአሞጽ መጽሐፍ ውስጥ እግዚአብሔር ሳይጠራው በፊት አሞጽ ሲሠራቸው የነበረውን ሥራዎች የሚገልጹ ብዙ ቃላቶች አሉ፡፡

1. *nqd*፤ 1፡1
2. *bqr*፤ 7፡14
3. *s'n*፤ 7፡15

▣ **"ቴቁሔ"** (BDB 1075) የቃሉ ፍቺ ድንኳን መትከል (ዝ.ከ. ዘፍ 31፡25፣ኤር 6፡3) ወይም ጥሩምባ (መለከት) መንፋት (ዝ.ከ. ሕዝ 7፡14) ማለት ነው፡፡ ተኮአ በአይሁድ ከተማ ውስጥ ያለች ከተማ የአይሁድ ጫካ ናት፡፡ በስተደቡብ ቤቴልየም በአምስት ማይልስ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ ስለዚህ ብዙዎቹ የእግዚአብሔር መሪዎች እንዴት ከአርብቶ አደርነት የሕይወት ዘይቤ እንደመጡ አይገርምም!

▣ ***"ያየው ቃል ይህ ነው"*** የቃሉ ግልፅ ትርጉም "*ያየው*" ማለት ነው (BDB 302፣ KB 301)፡፡ ቃሉ በመደበኛነት የሚጠቅመው እንደ አስደሳች (እንደሚያስፈነድቅ) ህልም ነው (ዘኁ 24፡4፣16፤ኢሳ 1፡1፤2፡ 1፣13፤ሕዝ 12፡27፤13፡16፤ሚክ 1፡1፤ ዕብ 1፡1)፡፡ ይህ ቃል ነብይን ለመጥቀም ከመጡት ሦስት ቃላት አንዱ ነው፡፡ (ማለትም "*ተመልካች*" ለምሳሌ አሞ 7፡12፤ 2ኛሳሙ 24፡11፤ 2ኛነገ 17፡13፤1ዜና 21፡9፤ 2ዜና9፡29፤ 12፡15፤19፡2፤ 29፡25-29፤33፡19፤ 35፡15፤ ኢሳ 29፡10፣25፤ 30፡10)፡፡

በእርግጠኝነት ቁጥር 1 የሚገልጸው ሁለቱም "*ቃላትና ህልም*" በቁጥር 1-6ና 7-9 ላይ የተገለጹትን ሁለት የተለያዩ ዓይነት የሆኑ ሐሳቦችን ያመለክታሉ፡፡ ይህ ይቻላል፤ ነገር ግን ከእርግጠኝነት የራቀ ነው፡፡

▣ ***"የአይሁድ ንጉሥ የኦዝያ ዘመን"*** ኦዝያ ከ783-748 ዓ ዓ በአይሁድ ላይ የነገሰ መልካም ንጉስ ነበር፡፡ (ለተገቢው ጊዜያት መግለጫን አንብብ) ስለ አይሁድ ንጉስ የተገለጸው በሙሉ በኢየሩሣሌም የነብዩን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት አቅጣጫ ያሳያል፡፡ ነብያት ሁልጊዜ በ922 ዓ ዓ የነበረውን የጎሣዎች መከፋፈልን ያወግወዛሉ (ዝ.ከ. 1ነገ 12፡16-20፤ 2ኛዜና 10)፡፡

▣ ***"የየሮብኣም -የእሥራኤል ንጉስ ዘመን"*** ይህ በአሥርቱ የሰሜናዊ ጎሳዎች ላይ ከ786-746 ዓ ዓ የነገሰውን የየሮብኣም ሁለተኛውን ያመለክታል (BDB 914) (ብዙ የተለያዩ ዘመናት ወይም ጊዜያት ስላሉ መግለጫን ይመልከቱ)፡፡ እሱ በጣም ስኬታማና ውጤታማ ንጉስ ነበር፡፡

በዚህ ጊዜ አይሁድና እስራኤል ብዙ በረከት ነበራቸው፡፡ ምክንያቱም አሶር የባህል ጠላታቸው በሰሜን ሶሪያ ተዋግታ ስለ ነበረ ነው፡፡ በተጨማሪም አሶርና ግብፅ በዚህ ወቅት ግዛት አስፋፊዎች አልነበሩም፡፡

▣ ***"የመሬት መንቀጥቀጥ ከመምጣቱ በፊት ሁለት ዓመት"*** ይህ ሀይለኛ የመሬት መንቀጥቀጥ መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም በዘካርያስ 14፡5 ላይ ከአንድ ዓመት በኋላ የተገለጸ ስለሆነ ነው፡፡ ምናልባት በ8ና በ9፡1 ላይም የተነገረ ሊሁን ይችላል፡፡ ጆሴፊስ (Antiq 9 225) እንዳለው ይህ ከኦዝያ መስዋዕት የማቅረብ ኃጥኣት ጋር ይያያዛል (ዝ.ከ. 2ኛዜና 26፡ 16-21)፡፡ ይህ (1) የአሞጽ የነብይነት ዘመናትን በትክክል ለመግለፅ የተሞከረ ታሪካዊ ንግግር (አገላለጽ) (አሞጽ 1፡1 በማንኛውም ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ዋነኛ ጊዜያትን የመግለፅ ሙከራ) ወይም (የአሞጽን የፍርድ መልዕክት ዋና ሐሳብን የማነሳሳት መንገድ ነው፡፡)

1.1. ይህ በአሞጽ መጽሐፍ የሚጀምረው የመጀመሪያ ግጥማዊ ክፍል ነው፤ የመጽሐፉ ማጠቃለያም ነው፡፡

## ልዩ ርዕስ፡- የእብራይስጥ ሥነ-ግጥም

I. *መግቢያ*
  - ሀ. የዚህ ዓይነት ሥነ-ጽሑፍ የብሉይ ኪዳንን አንድ-ሶስተኛን ይይዛል፡፡ በተለይ በነብያት ውስጥ የተለመደና የእብራይስጥ መመዘኛ የፅሑፍ ክፍል ነው፡፡ (ከሐጌና ከሚልክያስ ውጭ ሁሉም ግጥሞች አላቸው)፡፡
  - ለ. ከእንግሊዝኛ ሥነ-ግጥም የተለየ ነው፡፡ የእንግሊዝኛ ሥነ-ግጥም የመጣው ከግሪክና ላቲን ሥነ- ግጥም የመጣ ድምጽን ያማከለ ነው፡፡ የእንግሊዝኛ ሥነ-ግጥም ከከናዓናዊያን ሥነ-ግጥም ጋር ይቀራረባል፡፡ በመሠረቱም በሐሳብ ተመሥርቶ ሚዛኑን የጠበቀና በአጓዳኝ ስንኝ የሚሄድ ነው፡፡
  - ሐ. በሰሜን እሥራኤል በኡጋርት (ራስ ሽምራ) የተደረገው የቅሬታ አካል ጥናት ጠቢቦች የብሉይ ኪዳን ሥነ-ግጥም ግንዛቤን እንዲያገኙ ረድቶአቸዋል፡፡

II. የሥነ-ግጥም አጠቃላይ ባህርያት
  - ሀ. በጣም የተጣበቀ ነው (ጥብቅ ያለ ነው)፡፡
  - ለ. እውነትን፣ስሜትንና ልምድን በምሣሌያዊ ቋንቋ ለመግለፅ ይሞክራል፡፡
  - ሐ. በቀዳሚነት በጽሑፍ የሚቀርብ እንጂ በአፍ የሚቀርብ አይደለም፡፡ በጣም የተደራጁ ነው፡፡ ይህ አደረጃጀት የተገለጸው ፡-
    1. ሚዛኑን በጠበቀ ስንኝ
    2. የቃላት ጫወታ
    3. የድምፅ ጫወታ

III. አደረጃጀት (R K Harrison Introduction to Old Testament፤ pቁ 965-975)
  - ሀ. የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነ-ግጥም ባህርይን ሚዛኑን እንደጠበቀ ስንኝ አድርጎ Lectures on the Sacred Poetry of the Hebrews (1753) የተሰኘው መጽሐፉ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የገለጸው ጳጳስ ሮበርት ሎዊዝ ነው፡፡ አብዘኛዎቹ ዘመናዊ ሥነ-ግጥሞች የግጥምን ስንኞች ለማሳየት የተስተካከሉ ናቸው፡፡
    1. ተመሳሳይነት-ስንኞቹ አንድን ሐሳብ በተለያዩ ቃላት ይገልፃሉ፡፡
       - ሀ መዝ 3፡1፤49፡1፤83፡14፤103፡13
       - ለ ምሣ 19፡5፤ 20፡1
       - ሐ ኢሳ 1፡3፤10
       - መ አሞጽ 5፡24፤ 8፡10
    2. ተቀራኒያዊነት- ስንኞቹ ተቃራኒ ሐሳቦችን በተቃራኒያዊ መንገድ ይገልፃሉ፡፡
       - ሀ መዝ 1፡6፤90፡6
       - ለ ምሣ 1፡29፤ 10፡1፤ 12 ፤ 15፡1፤19፡4
    3. ሰው ሠራሽ- ቀጣዮቹ ሁለትና ሦስት ስንኞች ሐሳቡን ይገነባሉ፡፡ መዝ 1፡1-2፤ 19፡7-9፤ 29፡1-2
    4. ኪያዚምክ- መልዕክትን ከታች ወደ ላይና ከላይ ወደ ታች ቅደም ተከተል የሚገልጽ የሥነ-ግጥም ንድፍ ነው፡፡ ዋና ነጥቡ የሚገኘው በንድፈ ሐሳቡ መካከል ነው፡፡
  - ለ. Charles A Briggs General Introduction to the Study of Holy Scripture (1899)፤ በተሰኘው መጽሐፉ ውስጥ የሚቀጥለውን የእሥራኤልን የሥነ-ግጥም ትንተና ደረጃን አውጥተአል፡፡
    1. ምልክታዊ፡- አንድ ግልጽ ሐረግና ሁለተኛው ዘይቤያዊ የሆነ መዝ 42፡1፤ 103፡3
    2. አየር ንብረታዊ ደረጃ መሠል፡- እውነትን ከታች ወደላይ ቅደም ተከተል በሆነ ሁኔታ የሚገልፅ መዝ 19፡7-14፤29፡1-2፤ 103፡20-22
    3. የሐረጎች (ብዙ ጊዜ ቢያንስ አራት) በውስጣዊ አደረጃጀት ከስንኝ 1-4 እና ከ2-3 የተያያዙ፡፡ መዝ 30፡8-10
  - ሐ. G B Gray፤ The Forum of Hebrew Poetry (1915) በተባለው መጽሐፉ ውስጥ ሚዛናች የጠበቁ ሐረጎችን ሐሳብ አስፋፍቶአል፡፡
    1. ፍጹም ሚዛናዊ- በየትኛውም ቦታ በመጀመሪያ ስንኝ ውስጥ ያለው ቃል ሲደገም ወይም በሁለተኛው ስንኝ ውስጥ ካለው ቃል ጋር ስመጣጠን፡፡ መዝ 83፡14 እና ኢሳ 1፡3
    2. ያልተሟላ ሚዛን-ሐረጎች ተመሳሳይ ርዝማኔ ሳይኖራቸው ሲቀር፡፡ መዝ 59፡16፤75፡6
  - መ. በአሁኑ ጊዜ ኪያዚምክ የተባለውን የእብራይስጥ የሥነ-ግጥም አደረጃጀት ሁኔታ ግንዘቤው እያደገ መጥቶአል፡፡ ኪያዚምክ ብዙውን ጊዜ የሚያመላክተው ተጓዳኝ ስንኝ (ስንኞች)ነው፡፡ እነኚህ ስንኞች (ሀ፣ለ፣ለ፣ሀ፤ሀ፣ለ፣ሐ፣ለ፣ሀ)ን በመፍጠር ብዙውን ጊዜ የመካከለኛው ስንኝ ላይ ያተኩራል፡፡
  - ሠ. በምሥራቃዊ የሥነ-ግጥም ሳይሆን በአጠቃላይ በሥነ-ግጥም ውስጥ ያሉት የድምፅ መመሳሰል ዓይነቶች
    1. የፊደል ላይ ጫወታ (አክሮስቲክ) መዝ 9፡34፤37፤119፤ምሣ 31፡10፤ ሰቆ 1-4
    2. የአነባቢ ላይ ጫወታ (አልተረሸን) መዝ 6፡8፤27፡7፤122፡6፤ ኢሳ 1፡18-26

3. የተነባቢ ላይ ጫወታ (አሶናንስ) ዘፍ 16፡7፤ ዘፀ 14፡14፤ ሕዝ 27፡27
4. ተመሳሳይ የድምፅ ድግግሞሽ ያላቸውና የተለያየ ትርጉም ያላቸው ላይ የሚደረግ ጫወታ
5. ሲነባቡ ድምፅ መሰል ነገር የሚፈጥሩ ቃላት ጫወታ
6. ለየት ያለ አጀማመርና አጨራረስ (እንክሉሲብ)

ረ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ብዙ ዓይነት ሥነ-ግጥሞች አሉ፡፡ ጥቂቶቹ ከግጥሞቹ ርዕስ ጋር ሲያያዙ ጥቂቶቹ ደግሞ ከግጥሞቹ ቅርፅ ጋር ይያያዛሉ፡፡

1. የዓላማ መዝሙር- ዘኍ 21፡17-18
2. የሥራ መዝሙር- (በመሳፍንት 9፡27 ላይ የተነገረ ግን ያልተፃፈ) ፤ ኢሳ 16፡10፤ኤር 25፡30 ፤48፡33
3. የውዳሴ ግጥም- ዘኍ 21፡27-30 ፤ኢሳ 23፡16
4. የመጠጥ መዝሙር- ጎጂ ኢሳ 5፡11-13፤ አሞፅ 6፡4-7፤ እና ጠቃሚ ኢሳ 22፡13
5. የፍቅር መዝሙር- የመዝሙሮች መዝሙር፣ የጋብቻ እንቆቅልሽ- መሳ 14፡10-18፤ የሠርግ መዝሙር - መዝ 45
6. የሀዘን እንጉርጉሮ- (በ2ኛ ሳሙ 1፡17ና 2ዜና 35፡25 ላይ የተነገረ ግን ያልተፃፈ) ፤2ኛ ሳሙ 3፡33፤ መዝ 27፣28፤ኤር 9፡17-22፤ሕዝ 19፡1-14፤26፡17-18፤ ነህ 3፡15-19
7. የጦርነት መዝሙር- መዝ 4፡23-24፤ ዘፀ 15፡1-18፣20፤ ዘኍ 10፡35-36፤21፡14-15፤ኢያ 10፡13፤መሳ 5፡1-31፤11፡34፤1ኛሳሙ 1፡18፤ኢሳ 47፡1-15፤37፡21
8. ልዩ ቡራኬ ወይም የመሪዎች በረከት-ዘፍ 49፤ ዘኍ 6፡24-26፤ ዘዳ 32 2ኛሳሙ 23፡1-7
9. አስማታዊ ፅሑፎች- በለዓም ዘኍ 24፡3-9
10. ቅዱስ ግጥም-መዝሙረ ዳዊት
11. አክሮስትክ ግጥሞች-መዝ 9፣34፣37፣119፤ ምሣ 31፡10፤ ሰቆ 1-4
12. እርግማን-ዘኍ 21፡22-30
13. የስላቅ ግጥም- ኢሳ 14፡1-22፤ 47፡1-15፤ሕዝ 28፡1-23
14. የጦርነት ግጥም መጽሐፍ - ዘኍ 21፡14-15፤ኢያ 10፡12-13፤2ኛሳሙ 1፡18

IV. ***የእብራይስጥ ሥነ-ግጥም አተረጓጎም መመሪያ***

ሀ. በግጥሙ አዝማች ስንኝ ላይ ያለውን ዋነኛና እውነተኛ ሐሳብ መመልከት (ይህ በአንቀጽ ውስጥ ያለ ፅሑፍ ይመስላል)፡፡

ለ. ምሳላዊ ቋንቋን መለየትና በስድ ፅሑፍ መግለፅ፡፡ እንደዚህ ዓይነት ሥነ-ፅሑፍ የተጣበቀ ነው፡፡ ስለዚህ ብዙ ስራ ከአንባቢው ይጠበቃል፡፡

ሐ. ስለረኸርም ጉዳይ የሚገልጹትን ግጥሞች ከቀጥተኛ አገባብ ጋር ማያያዝ (ብዙ ጊዜ ሙሉውን መጽሐፍና ታሪካዊ ሀኔታቸውን ማያያዝ)

መ. መጽሐፈ-መሳፍንት 4ና5 ግጥም እንዴት ታሪክን እንደምገልፅ ለማየት ይጠቅማሉ፡፡ መጽሐፈ- መሳፍንት 4 ስድ ጽሑፍ ሲሆን መጽሐፈ-መሳፍንት 5 ደግሞ ግጥም ነው፡፡ (ከዘፀ 14 ና 15 ጋር አነፃፅር)

ሠ. የተጓዳኝነትን ዓይነት (ተመሳሳይ፣ተቀራኒ ወይም ሰው ሠራሽ መሆናቸውን) ለመለየት መሞከር፡፡ ይህ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

▣ **"እግዚአብሔርም አገሳ"** አገሳ የሚለው ቃል (BDB 980፣ KB 1367) እንደ ሙብረቅ ያለውን የእግዚአብሔርን ድምጽ ለመግለጽ የተጠቀመ ነው፡፡ ኢዮ 37፡3-5፤ኤር 25፡30፡፡ ይህ ስለ ኃጥኣታቸውና ስለ እግዚአብሔር ካላቸው ልማዳዊ ዕውቀት የተነሣ በእሥራኤላውያን ላይ የመጣውን ፍርድ ይገልፃል፡፡(ዝ.ከ. 3:8)። እዚህጋ የተገለፁት ሕዝቦች በሙሉ የዳዊትና የሰለሞን ዘር ስለሆኑ ስለ እግዚአብሔር ጥቂት እውቀት አላቸው፡፡ ይህ ከኢዩኤል 3፡16 ጋር ይመሳሰላል፡፡ መግሳት የአንበሳን የሞት ሁኔታን ማለትም የፍርድ ጊዜን ይገልፃል፡፡ ኢዩኤል (3፡16፤ ሆሰ 11፡10) ላይ እንደተገለው መዳንን ሊገልጽ ይችላል፡፡ በዚህ አገባብ ግን የእግዚአብሔርን ፍርድ ይገልፃል፡፡ እረኛው ዳዊት እንደ ቁጡ አጥቂ እየሆነ መጣ (መዝ 23)፡፡ ስለ ያይዌህ ከዚህ በታች የተገለጸውን ልዩ ርዕስ ተመልከት፡፡

## ልዩ ርዕስ፡ የመለኮት ስሞች

ሀ. ኢል BDB 42፣ KB 48)

1. ዋነኛው የዚህ ጥንታዊ ቃል ዘውጋዊ ትርጉም ለመለኮትእ ርግጠኝነት የለውም፣ ምንም እንኳ በርካታ ሊቃውንት ከአካድያን ሥርወቃል የመጣ ነው ብለው ቢያምኑም፣ እሱም "ጠንካራ መሆን" ወይም "ኃይለኛ መሆን" የተገኘ ነው ቢሉም (ዘፍጥረት 17፡1፤ ዘኍ 23፡19፤ ዘዳ 7፡21፤ መዝ 50፡1)።
2. በከነዓናውያን አፈ ታሪክ ታላቁ አማልክት ኢል ነው (ራስ ሻምራ ጽሑፎች)
3. በመጽሐፍ ቅዱስ፣ ኢል ዘወትር ከሌሎች ቃላት ጋር አይደባለቅም። እነዚህ መደባለቆች የእግዚአብሔርን ባሕርይ መግለጫ መንገድ ሆነዋል።
   ሀ. ኤል-ኢልዮን (እግዚአብሔር ቃላቁ ልዑል፣ BDB 42 እና 751 II)፣ ዘፍ 14፡18-22፤ ዘዳ 32፡8፤ ኢሳ 14፡14
   ለ. ኤል- ሮይ ("የሚያይ አምላክ" ወይም "ራሱን የሚገልጽ አምላክ፣" BDB 42 እና 909)፣ ዘፍ 16፡13
   ሐ. ኤል -ሻዳይ ("ሁሉን ቻይ አምላክ" ወይም "ፈጽሞ የሚራራ አምላክ" ወይም "የተራራው አምላክ፣" BDB 42 እና 994)፣ ዘፍ 17፡1፤ 35፡11፤ 43፡14፤ 49፡25፤ ዘጸ 6፡3
   መ. ኤል-ኦላም (ዘላለማዊው አምላክ፣ BDB 42 761)፣ ዘፍ 21፡33። ይህ ቃል ከሥነ መለኮት አኳያ የሚያያዘው እግዚአብሔር ለዳዊት ከሰጠው ተስፋ ጋር ነው፣ 2ኛ ሳሙ 7፡13፣16
   ሠ. ኤል -ቤሪት ("የቃል ኪዳን አምላክ፣"BDB 42 እና 136)፣ መሳ 9፡46
4. ኤል የሚያያዘው ከ

ሀ. ያህዌ መዝ 85፡8፤ ኢሳ 42፡5
ለ. ኤሎሂም ዘፍ 46፡3፤ ኢዮብ 5፡8፣ "እኔ ኤል ነኝ፣ የአባቶቻችሁ ኤሎሂም
ሐ. ሻዳይ ዘፍ 49፡25
መ. "ቀናተኛ" ዘጸ 34፡14፤ ዘዳ 4፡24፤ 5፡9፤ 6፡15
ሠ. "መሐሪ" ዘዳ 4፡31፤ ነህ 9፡31፤ "ታማኝ" ዘዳ 7፡9፤ 32፡4
ረ. "ታላቅና የሚያስፈራ" ዘዳ 7፡21፤ 10፡17፤ ነህ 1፡5፤ 9፡32፤ ዳን 9፡4
ሰ. "አዋቂ" 1ኛ ሳሚ 2፡3
ሸ. "ጠንካራ መጠጊያዬ" 2ኛ ሳሙ 22፡33
ቀ. "ተበቃዬ" 2ኛ ሳሙ 22፡48
በ. "ቅዱሱ" ኢሳ 5፡16
ተ. "ኃያሉ" ኢሳ 10፡21
ቸ. "አዳኜ" ኢሳ 12፡2
ኀ. "ታላቅና ኃይለኛ" ኤር 32፡18
ነ. "ፈራጅ"ሪ1፡56

5. የዋናዎቹ ብሉይ ኪዳን ሁሉም የእግዚአብሔር ስሞች ድብልቅ፣ በኢያሱ 22፡22 የሚገኙት (ኤል፣ ኤሎሂም፣ ያህዌህ፣ የተደገመ)

ለ. ኢሊዮን

1. የእሱ መሠረታዊ ፍች "ልዑል፣" "ከፍ ያለ፣" ወይም "ከፍ ያለ" (ዘፍ 40:17፤ I ነገሥ 9:8፤ II ነገሥ 18:17፤ ነህ፣ 3:25፤ ኤር፣ 20:2፤ 36:10፤ መዝ 18:13)።
2. እርሱም ከሌሎች በርካታ ስሞች ጋር በአቻዊ አገባብ ጥቅም ላይ ውሏል/ለእግዚአብሔር ስም።
   ሀ. ኤሎሄም - መዝ 47:1-2፤ 73:11፤ 107:11
   ለ. ያህዌህ - ዘፍ 14:22፤ II ሳሙ 22:14
   ሐ. ኤል-ሻዳይ - መዝ 91:1፣9
   መ. ኤል - ዘኁ 24:16
   ሠ. ኢላህ - ዘወትር ጥቅም ላይ የዋለው ዳንኤል 2-6 እና እዝራ 4-7፣ ከኢላር ጋር በመቀናጀት (በአራምኛ "ልዑል አምላክ") ዳን 3:26፤ 4:2፤ 5:18፣21
3. እርሱም ዘወትር እስራኤል ባልሆኑት ጥቅም ላይ ይውላል
   ሀ. መልከጼዴቅ፣ ዘፍ 14:18-22
   ለ. በለዓም፣ ዘኁ 24:16
   ሐ. ሙሴ፣ በዘዳ 32:8 ስለ ሕዝቦች የተናገረው።
   መ. የሉቃስ ወንጌል በአዲስ ኪዳን፣ ለአሕዛብ የተጻፈው፣ የግሪኩን አቻ ሁፐሲስቶስን ይጠቀማል (ዝ.ከ. 1:32፣35፣76፤ 6:35፤ 8:28፤ ሐዋ 7:48፤ 16:17)

ሐ. ኤሎሂም (ብዙ)፣ ኤሎህ (ነጠላ)፣ በቅድሚያ ጥቅም ላይ የዋለው በቅኔ ነው (BDB 43፣ KB 52

1. ይህ ቃል ከብሉይ ኪዳን ውጭ አይገኝም።
2. ይህ ቃል የሚያመለክተው የእስራኤል አምላክ ወይም የሕዝቦችን አማልክት ነው (ዘጸ 12፡12፤ 20፡3)። የአብርሃም ቤተሰቦች ብዙ አማልክት አምላኪዎች ነበሩ (ኢያሱ 24፡2)።
3. እርሱም ለሰው ፈራጆችም ይጠቀሳል (ዘጸ 21:6፤ መዝ 82:6)
4. ኤሎሂም የሚለው ቃል ለሌሎች መንፈሳዊ ሕላዌዎችም ጥቅም ላይ ይውላል (መላእክት፣ አጋንንት) እንደ ዘዳ 32:8 (LXX)፤ መዝ 8:5፤ ኢዮብ 1:6፤ 38:7።
5. በመጽሐፍ ቅዱስ እርሱ የመጀመሪያ ማዕርግ/የመለኮት ስም ነው (ዘፍ 1:1)። እርሱ እስከ ዘፍ 2፡4 ድረስ በአጠቃሎሽ አይቀርብም፣ ከዚያም ከያህዌ ጋር ይደባለቃል። እርሱ በመሠረቱ (በሥነ መለኮት) ለእግዚአብሔር የሚያመለክተው እንደ ፈጣሪ፣ ደጋፊ፣ እና ሰጪ ነው፣ በዚህ ምድር ላይ ላለ ሕይወት (መዝ 104)።

   እርሱም ተመሳሳይ ነው፣ ከኢል ጋር (ዘዳ 32:15-19)። እርሱም ደግሞ ከያህዌህ ጋር ትይዩ ነው፣ እንደ መዝ 14 (ኤሎሂም)፣ በትክክል መዝ 53ን ይመስላል (ያህዌህ)፣ መለኮታዊ ስሞቹ ከመቀየራቸው በቀር።
6. ምንም እንኳ የብዙ ቁጥር ቢሆንና ለሌሎች አማልክት ጥቅም ላይ ቢውልም፣ ይህ ቃል ዘወትር የሚገልጸው የእስራኤልን አምላክ ነው፤ ግን ዘወትር ነጠላ ግሥ ይይዛል፣ አሀዳዊ አጠቃቀምን ለማሳየት።
7. ይህ ቃል የሚገኘው እስራኤላዊ ካልሆኑ አንደበት ነው፣ እንደ መለኮት ስም።
   ሀ. መልከጼዴቅ፣ ዘፍ 14፡18-22
   ለ. በለዓም፣ ዘኁ 24፡2
   ሐ. ሙሴ፣ ስለ ሕዝቦች በተናገረበት ጊዜ፣ ዘዳ 32፡8
8. ያልተለመደ የሚሆነው የጥቅል ስም ለአንዱ የእስራኤል አምላክ በብዙ ቁጥር መሆኑ ነው! ምንም እንኳ እርግጠኝነት ባይኖርም፣ ንድፈ ሐሳቦቹ እነዚህ ናቸው።
   ሀ. ዕብራይስጥ በርካታ የብዙ ቁጥሮች አሉት፣ ዘወትር ለአጽንዖት የሚሆን። ከዚህ ጋር በቅርብ የሚዛመደው የዕብራይስጡ ሰዋሰዋዊ ተፈጥሮ የሚጠራው፣ "የግርማዊ ብዙ ቁጥር" ሲሆን፣ የብዙ ቁጥሩ ደግሞ ጥቅም ላይ የሚውለው ጽንሰ-ሐሳቡን ለማጉላት ነው።
   ለ. ይህ ምናልባት የሚገልጸው የመላእክትን ጉባዔ ነው፣ እርሱም እግዚአብሔር በሰማይ እንደሰበሰበና ትዕዛዙን እንደሰጠ ነው (I ነገሥ 22:19-23፤ ኢዮብ 1:6፤ መዝ 82:1፤ 89:5፣7።
   ሐ. ይህም ሊያመለክት የሚችለው የአኪን መገለጥ ነው፣ አንድ አምላክ በሦስት አካላት። በዘፍ 1:1 እግዚአብሔር ፈጠረ፤

ዘፍ 1፡2 መንፈሱ ሰፈፈ እናም በአኪ ኢየሱስ የእግዚአብሔር አብ ወኪል ነው፣፤ በፍጥረት ላይ (ዮሐንስ 1፡3፣10፤ ሮሜ 11፡36፤ 1 ቆሮ 8፡6፤ ቆላ 1፡15፤ ዕብ 1፡2፤ 2፡10)።

*መ.* ያህዌህ (BDB 217፣ KB 394)

1. ይህ ስም የሚያንጸባርቀው መለኮትን ሲሆን፣ ኪዳንን እንደሚመሰርት አምላክ ነው፤ እግዚአብሔር እንደ አዳኝ፣ ተቤዢ! ሰዎች ኪዳኑን አፈረሱ፣ እግዚአብሔር ግን ታማኝ ነው፣ ለቃሉ፣ ለተስፋው፣ ለኪዳኑ (መዝ 103)።

    ይህ ስም መጀመሪያ የተጠቀሰው ከኤሎሂም ጋር ተደባልቆ ነው፣ በዘፍ 2፡4። በዘፍ 1-2 ሁለት የተፈጥሮ ሐተታዎች የሉም፣ ግን ሁለት አጽንዖቶች፡ (1) እግዚአብሔር እንደ ዩኒቨርስ (ሥጋዊ) ፈጣሪ እና (2) እግዚአብሔር ልዩውን ፍጡር የሰው ልጅን ፈጥሯል። ዘፍጥረት 2፡4 የሚጀምረው በተለየ መገለጥ ነው፣ እድላዊ ሥልጣንና ተግባር ስላለው የሰው ልጅ የሚያሳይ፣ እንዲሁም የኃጢአትና የዐመጻኝነት ችግር ልዩ ከሆነው ሥልጣን ጋር ስለ መያያዙ።

2. በዘፍ 4፡26 የሚለው "ሰዎችም በእግዚአብሔር ስም መጠራት ጀመሩ" (ያህዌህ)። ሆኖም፣ ዘጸ 6፡3 የሚያመለክተው የቀድሞ የኪዳኑ ሕዝቦች (አባቶችና ቤተሰቦቻቸው) እግዚአብሔርን የሚያውቁት በኤል-ሻዳይነቱ ብቻ ነው። ያህዌህ የሚለው ስም በዘጸ 3፡13-16፣ በተለይም ቁ 14 አንድ ጊዜ ነው የተጠቀሰው። ሆኖም፣ የሙሴ ጽሑፎች ዘወትር ቃላትን የሚተረጉሙት በታወቁት የቃላት አግባቦች ነው እንጂ፣ በሥርወ ቃል አይደለም (ዘፍ 17፡5 27፡36፤ 29፡13-35)። የዚህን ስም ትርጓሜ በተመለከተ በርካታ ንድፈ ሐሳቦች አሉ (ከአይዲቢ የተወሰደ፣ ቅጽ 2፣ ገጽ 409-11)።
    - *ሀ.* ከዓረብ ሥርወቃል፣ "ፍጹም ፍቅርን ማሳየት"
    - *ለ.* ከዓረብ ሥርወቃል "መምታት" (ያህዌህ እንደ ማዕበላዊ አምላክ)
    - *ሐ.* ከዩጋርቲክ (ከነዓናዊ) ሥርወቃል "ቁንጮ ላይ መሆን"
    - *መ.* የፎንቄውያንን ጽሑፍ ተከትሎ፣ መነሻዊ ቦዝ አንቀጽ ሲሆን ፍችውም "አንዱ የሚደግፈው፣" ወይም "የሚያጸናው አንዱ" ማለት ነው።
    - *ሠ.* ከዕብራይስጡ ቃል "አንዱ የነበረው" ወይም "አንዱ ያለው" (በትንቢት ጊዜ ደግሞ፣ "አንዱ ወደፊት የሚኖረው")
    - *ረ.* ከዕብራይስጡ ሂፊል ከ "ወደ መኖር የሚያመጣው"
    - *ሰ.* ከዕብራይስጡ ሥርወቃል "መኖር" (ምሳ ዘፍ 3፡20)፣ ፍችውም "ለዘላለም የሚኖረው፣ ብቻውን ኗሪ"
    - *ሸ.* ከዘጸ ዐውደ ጽሑፍ 3፡13-16 ያልተጠናቀቀ ቅርጽ በተጠናቀቀ አግባብ ጥቅም ላይ የዋለ፣ "እየሆንኩኝ በነበርኩበት በቀጣይም እሆናለሁ" ወይም "ፊት በነበርኩበት በቀጣይም እሆናለሁ" (ጄ ዋሽ ዋትስ፣ *የብሉይ ኪዳን ሰዋሰው ጥናት፣* ገጽ 67) ሙሉው የያህዌህ ስም ዘወትር የሚገለጸው በአጽህሮተ ቃል ወይም በዋነኛ ቅርጹ ነው
        1) ያህ (ምሳ ሃሌሉ -ያህ፣ BDB 219፣ ዘጸ 15፡2፤ 17፡16፤ መዝ 89፡9፤ 104፡35)
        2) ያሁ ("ኢአህ" የስሞች መጨረሻ፣ ምሳ ኢሳይያስ)
        3) ዮ ("ጆ" የስሞች መጀመሪያ፣ ምሳ ኢያሱ ወይም ኢዩኤል)

3. በኋለኛው ይሁዲነት ይህ የኪዳን ስም በጣም ቅዱስ ስለሆነ (ቴትራግራማቶን) አይሁድ ለመናገር ይፈሩ ነበር፣ በዘጸ 20፡7፤ ዘዳ 5፡11፤ 6፡13፣ ያለውን ትዕዛዝ እንዳይጥሱ በመስጋት። ስለሆነም የዕብራይስጡን ቃል ቀየሩት፣ "ባለቤት፣" "ጌታ፣" "ባል፣" "ጌታ" —አዶን ወይም አዶናይ (የኔ ጌታ)። ወደ ያህዌህ ሲመጡ በብሉይ ኪዳን ጽሑፍ ንባባቸው "ጌታ" ብለው ያነባሉ። በዚህን ምክንያት ነው ያህዌህ በእንግሊዝኛ ትርጉሞች ጌታ የሚባለው።

4. ልክ እንደ ኢል፣ ያህዌህ ከሌሎች ቃላት ጋር ይደባለቃል፣ የእስራኤልን የኪዳን አምላክ አንዳንድ ባሕርያት አጽንዖት ለመስጠት። በርካታ የተደባለቁ ቃላት ሲኖሩ፣ ጥቂቶቹ እኒህ ናቸው።
    - *ሀ.* ያህዌህ - ዪሬህ (ያህዌህ ይሰጣል፣ BDB 217 እና 906)፣ ዘፍ 22፡14
    - *ለ.* ያህዌህ - ሮፌክሃ (ያህዌህ ፈዋሽህ ነው፣ BDB 217 እና 950፣ ቦዝ አንቀጽ)፣ ዘጸ 15፡26
    - *ሐ.* ያህዌህ - ኒሲ (ያህዌህ ዓርማዬ ነው፣ BDB 217 እና 651)፣ ዘጸ 17፡15
    - *መ.* ያህዌህ - ሜቃዲሽኬም (ያህዌህ የሚቀድስህ ነው፣ BDB 217 እና 872፣ ቦዝ አንቀጽ)፣ ዘጸ 31፡13
    - *ሠ.* ያህዌህ - ሻሎም (ያህዌህ ሰላም ነው፣ BDB 217 እና 1022)፣ መሳ 6፡24
    - *ረ.* ያህዌህ - ሳቦዝ (ያህዌህ የሠራዊት፣ BDB 217 878)፣ 1ኛ ሳሙ 1፡3፣11፤ 4፡4፤ 15፡2፤ ዘወትር በነቢያት)
    - *ሰ.* ያህዌህ - ሮ' አይ (ያህዌህ እረኛዬ ነው፣ BDB 217 እና 944፣ ቦዝ አንቀጽ)፣ መዝ 23፡1
    - *ሸ.* ያህዌህ - ሲድቄኑ (ያህዌህ ጽድቃችን ነው፣ BDB 217 እና 841)፣ ኤር 23፡6
    - *ቀ.* ያህዌህ - ሻማህ (ያህዌህ እዚያ አለ፣ BDB 217 እና 1027)፣ ሕዝ 48፡35

▣ **"ጽዮን...... ኢየሩሳሌም"** እነዚህ ሁለቱ ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸውና ተዛማች ግንኙነት አላቸው (በእብራውያን ግጥም 1፡2 ላይ ያለውን ልዩ ርእስ ተመልከት)፡፡ አህዩዳዊያን እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም ውስጥ ባለው ሞሪያ ተራራ ላይ እንደ የቅዱሳን ቅዱስ በክሩቤል ክንፍ መካከል በቃል ኪዳን ታቦት ላይ እንደሚኖር ያዩት ነበር (ዘፀ 25፡22)፡፡ ኢየሩሳሌም የተሠራች በሰባት ጋራዎች ላይ ነው፡፡

1. የጽዮን ተራራ የየቡሳዊያን ምሽግ የሚገኝበትና በዳዊት ዘመናት ያልተማረከ ተራራ ነበር (ዝ.ከ. ኢያ 15፡63፤ 2ኛሳሙ 5፡6-10)፡፡
2. የሞሪያ ተራራ ቤተ መቅደስ የተሠራበት ተራራ ነበር (ዝ.ከ. ዘፍ 22፡2፤1ዜና21፡1-22፤2ዜና3፡1)፡፡

የሁለቱም የጽዮንና (BDB 851) የኢየሩሳሌም (BDB 436) የመጀመሪያ ስም ትርጉም አጠራጣሪ ነው፡፡

▣ "**የእረኞችም ማሰማርያዎች ያለቅሳሉ፥ የቀርሜሎስም ራስ ይደርቃል**" እግዚአብሔር በሰው ልጆች ላይ ያመጣው ፍርድ ፍጥረትን ጎዳ፡፡(ዘፍ 3፤ዘዳ 27-28፤ ሮሜ 8፡18-25 የማህተሙና የጎድጓዳ ሳህን ራዕይ)፡፡ እግዚአብሔር ፍጥረትን የሰዎችን ትኩረት እንድስቡ አድርጎአቸው ይጠቀማቸዋል (መዝ 19፡1-6)፡፡

▣ "**ቀርመሎስ**"- ቀርመሎስ ከሰሜን እስራኤል ወደ ሜዲቴራኒያን የሚሄድ ስንሰለታማ ተራራ ነው፡፡ የስሙ ትርጓሜ "የእግዚአብሔር የወይን ቦታ" ማለት ነው(BDB 501)፡፡የለምለም ተክል ምሳሌያዊ አገላለፅ ነው፡፡

## አሞጽ 1፡3-5

**[3] እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ገለዓድን በብረት መንኰራኵር አሂዶአልና ስለ ሦስት ወይም ስለ አራት የደማስቆ ኃጢአት መቅሠፍቱን ከማድረግ አልመለስም። [4] በአዛሄል ቤት እሳትን እሰድዳለሁ፥ የወልደ አዴርንም አዳራሾች ትበላለች። [5] የደማስቆንም መወርወሪያ እሰብራለሁ፥ ተቀማጮችንም ከአዌን ሸለቆ አጠፋለሁ፥ በትር የያዘውንም ከዔደን ቤት አጠፋለሁ የሶርያም ሕዝብ ወደ ቂር ይማረካል፥ ይላል እግዚአብሔር፡-**

1፡3-2፡3 ይህ እንደ መንፈሳዊ ትምህርት የሚጠቅም የስነ-ፅሑፍ ምዕራፍ ነው፡፡

1. እግዚአብሔር (ያይዌህ) የምድር ሁሉ አምላክ ነው፡፡
2. ኃጥኣትን የሠሩ ሁሉ የእግዚአብሔር ቁጣ ያገኛቸዋል፡፡
3. ሕዝቡ ኃጥኣትን እየሠሩ ነው፤ ምክንያቱም እነርሱ የቃል ኪዳን ሕዝቦች ነበሩ (ዝ.ከ. ሉቃ12፡48)

ይህ ምዕራፍ በደስታ የተነበበ ወይም የተሰማ መሆን ነበረበት ልክ የእስራኤላውያን ደስታ በላያቸውና በጎረቤታቸው ላይ ፍርድን እንዳመጣ ማለት ነው (ዝ.ከ. 2፡4-5)፡፡ ነገር ግን በድንገትና በአስገራሚ ሁኔታ አሞጽ ወደ እስራኤላዊያን ኃጥኣት ይመለሳል (ዝ.ከ. 2፡6፤6-14)፡፡ ብልጽግናቸው፣ ወታደራዊ ኃይልና የመሬት መስፋፋት የእግዚአብሔር ቃልኪዳናዊ በረከት ምልክቶች አይደሉም (ዝ.ከ. ዘዳ 27-29)፡፡ የሙሴን ቃል ኪዳን የሚያጠናክረው አሞጽ ስኬትን የሚፈልግ ነበረ፡፡የእግዚአብሔር ቀናት የበረከት ቀናት ብቻ ላይሆኑ ይችላሉ፤ ነገር ግን እርግማን (ዝ.ከ. 5፡18-20)

**1፡3 "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል"** ይህ ትንቢታዊ አባባል መልዕክቱ የነብዩ ግለሰባዊ ሐሳብ አለመሆኑና የእግዚእሔር ቃል ብቻ መሆኑ የሚገለፅበት መንገድ ነው፡፡ ምን ያህል ቃላት ከትንቢት ተናጋሪው ሊሆኑ ይችላሉ የሚለው አጠራጣሪ ነው፡፡ የሀሳብ ማፍለቂያ መንገዱ አጠራጣሪና ልዩነት ሊኖረው ብችሊም አስፈላገው እውነት ግን የእግዚአብሔር መልዕክት መሆኑ ነው፡፡ ይህ መልዕክት ምንም እንኳን በተለያየ ቋንቋ፣ ታሪክና ባህል ቢገለፅም ከሁሉም ባህልና ጊዜ ጋር ግንኙነት አለው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓገም ሁሉም ምዕራፍ አንድ ትርጉም-እርሱም የመጀመሪያው ተናጋሪ ፀሐፊ ለማለት የፈለገ፤ ነገር ግን ተግባራዊነቱ በብዛት ከአንባቢው ወይም ከሰሚው ታሪካዊና ባህላዊ ሁኔታ ጋር ይያያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ተግባራዊነቱ በቀጥታ ከዋናውና ከመጀመሪያው ጸሐፊ ሀሳብ/መልዕክት ጋር መያያዝ አለበት፡፡ በዚህ አገባብ ቃሉ በሰዎች ላይ የሚደርሰውን የእግዚአብሔርን ፍርድ ነው (ዝ.ከ. ኤር 47፡2፤48፡1፤ሕዝ 25፡3፤ 30፡2፤አሞጽ1፡3፤2፡1፡፡

▣ **"ለሶስቱ ለደመስቆ መተላለፎችና ለአራቱ......"** ይህ በ አሞጽ (ዝ.ከ. 1፡3፣6፣9፣11፣13፤2፡1፣4፣6) ውስጥ የተገለጸዉ ደረጃውን የጠበቀ የመግቢያ ሐረግ ነው፡፡በሌሎች የምሥራቅ ሥነ-ፅሑፎች ውስጥም ይገኛል፡፡ ይህ ማለት እነዚህ ሕዝቦች ደጋግመው ኃጥኣት ሠሩ ማለት ነው፡፡

"አራት" የሚለውን ቃል አብዛኛውን ጊዜ በጥንቷ ምሥራቅ ይጠቀማሉ፡፡

1. አራት የጨረቃ ደረጃዎች
2. አራት የአመት ክፍፍል (NIDOTTE፤ቁ 1 ገጽ 495)

በብሉይ ኪዳን የሚወከለው፡-

1. የኮምፓስ አቅጣጫ (ማለትም ወደ ምስራቅ የዞረ ሰው)
2. የንፋስ አቅጣጫ (ለምሳሌ፡-ዳን 7፡2፤8፡8)
3. የምድር ማዕዘን (ለምሳሌ፡- ኢሳ 11፡12)

የቃሉ ድብቅ ትርጉሞች ከነዚህ ሙሉነት ወይም ፍጹምነት ካላቸው ሀሳቦች ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም ሶስትና አራት ቁጥሮች ሰባት ሲሆኑ የብሉይ ኪዳንን ሙሉነት በማመላከት የእነዚያ ህዝብ ኃጥኣት መሙላቱን ይገልፃል፡፡

"መተላለፍ" (BDB 833) የሚለው ቃል ኃጥኣትን ወይም አመፅን ለመግለፅ የሚጠቅም ከብዙዎቹ ከእብራይስጥ ቃላት አንዱ ነው፡፡ በአሞጽዉ ስጥ ይህ ቃል ማህበራዊ ኃጥኣትን ይገልፃል (ዝ.ከ. NIDOTTE ቅጽ፤3 ገጽ 708) እነዚህ ህዝቦች ጎረቤቶቻቸውንና ዘመዶቻቸውን በመጥላት አመጹ፡፡ ድርጊታቸው እግዚአብሔርን አለማወቃቸውን ያሳያል፡፡ እነዚህ ህዝቦች ከዳዊት ግዛት መካከል ስለነበሩ እግዚአብሔርን ለማወቅ አስችሎአቸዋል፡፡

ነብያቶች የእግዚአብሔርን ፍርድ በሰዎች ላይ ይናገራሉ (ዝ.ከ. ኢሳ 13-23፤ኤር 46-51፤ሕዝ 25-32)፡፡ የሶሪያ ሕዝቦች ከደመስቆ (ዋና ከተማ) ጋር አራማዊያን በመባል ይታወቃሉ፡፡ ዋና ከተማው በአጠቃላይ ለሁሉም ሕዝቦች ይቆማል፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **NASB፤ NRSV** | **"ቅጣታቸውን አልሸርም"** |
| **NKJV** | **"ቅጣታቸውን አልመልስም"** |
| **TEV** | **"በእርግጥ እቀጣቸዋለሁ"** |
| **NJB** | **"አዋጄን አስተላልፌያለሁ፤ አልምራቸውምም"** |

"ያልተለመደ" የሚለው አፍራሹ ግስ (BDB 996፣ KB 1427) በነብያት ውስጥ ንስሐ መግባትን ለመግለፅ ብሁም አይጠቅምም፡፡ በዚህ ሥፍራ እግዚአብሔርን ይገልፃል፡፡ እግዚአብሔርን ለመግለፅ የሚረዳን ብቸኛ ቃል ከሰው ልጆች ጋር ይያያዛል፡፡ እግዚአብሔር ዘላለማዊ መንፈስ ነው፡፡ እርሱን ለመግለፅ ሰብኣዊ ቃልን (antropomorphisms) እንጠቀማለን፤ነገር ግን እርሱን መግለፅ ከአቅማችን በላይ ነው፡፡

## ልዩ ርዕስ፡- ንስሃ መግባት በብሉይ ኪዳን

ይህ ሃሳብ ምንም እንኳን ወሳኝ ቢሆንም እንዲህ ነው ብሎ ለመፈረጅ ግን በጣም አዳጋች ነው፡፡ ብዙዎቻችን ያለን ትርጓሜ ካደረግንበት የእምነት ተቋም ጋር እናያይዘዋለን፡፡ ሆኖም ግን የ "ተቀመጠው" የመጽሐፍ ቅዱሳዊው ትምህርት ትርጓሜ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ባሉ ብዙ የእብራዊያን

(ግሪክ) ቃላት የ"ተቀመጠውን" ትርጉም በማያመለክት መልኩ ተጽዕኖ አድርገውበታል፡፡

የእብራዊያኑ ቃላቶች በዋናነት ሁለት ናቸው፡፡
1 *nhm* (BDB 636፤KB 688)
2 *swb* (BDB 996፤KB 1427)
የመጀመሪያው *nhm* ፤ ከምንጬ ስናየው በተለያየ መልኩ የሚገለጽ በጥልቅ መተንፈስ የሚል ትርጉም የሚሰጥ ይመስላል፡፡
1. "እረፍት" ወይም "ድሎት" (ለምሳሌ ዘፍ 5:29፣ 24:67፣ 27:42፣ 37:35፣ 38:12፣ 50:12፣ በተደጋጋሚ በስሞች ላይ ይገለጻል ፤ዝ.ከ. 2ኛነገ 15:14፣ 1ኛዜና4:19፣ ነህ 1:1፣ 7:7፣ ናሆ 1:1)
2 "መጸጸት" (ለምሳሌ ዘፍ 6:6፣7)
3 "ሃሳብን መለወጥ" (ለምሳሌ ዘጽ 13:17፣ 32:12፣14፣ ዘኊ 23:19)
4 "ርህራሄ" (ለምሳሌ ዘዳ 32:36)
ከላይ መረዳት እንደሚቻለው ሁሉም ጥልቅ ስሜትን ያመለክታሉ! ዋናው ነጥብ ይህ ነው፤ ወደ ተግባር የሚለወጥ ጥልቅ ስሜት፡፡ ይህ የተግባር ለውጥ በተደጋጋሚ ጊዜ ወደ ሌሎች ሰዎች የሚጠቁም ቢሆንም፤ነገር ግን ወደ እግዚአብሔርም ያመለክታል፡፡
ይህ ወደ እግዚአብሔር የተደረገ የአመለካከት እና የምግባር መታደስ ነው ቃሉን የመጽሐፍ ቅዱስዊ ትምህርት ፋይዳ እንዲኖረው ያደረገው፡፡እዚህ ላይ ግን ትልቅ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡ እግዚአብሔርም "አዘነ" ይባላል (ዝ.ከ. ዘፍ 6:6፣7፤ ዘፀ 32:14፤ መሳ 2:18፤ 1ኛሳሙ 15:11፣35፤ መዝ 106:45)፤ ነገር ግን ይህ ከመጸጸት ወይም ከኃጥያት የመጣ አይደለም፡፡ ይልቁንም ይህ የእግዚአብሔር ትልቅ ርህራሄ እና ጥበቃን የሚያሳይ ነው (ዝ.ከ. ዘኊ 23:19፣ 1ኛሳሙ 15:29፣ መዝ 110:4፣ ኤር 4:27-28፣ ሕዝ 24:14)፡፡ ኃጥያተኛው ከልቡ ቢጸጸት እና ከተግባሩም እራሱን አጽድቶ ወደ እግዚአብሔር ከተመለሰ የአመጻ እና የኃጥያተኝነት ቅጣት ይቀራል፡፡

ይህ ቃል ሰፋ ያለ የቋንቋ ትርጓሜ ዘርፍ አለው፡፡ የአንድ ምንባብ ዓውድ የታለመውን ትክክለኛ ትርጓሜ ለመረዳት ትልቅ ሚና አለው፡፡
ሁለተኛው ቃል *swb* ፤ "መመለስ" (ከሆነ ነገር መመለስ ፤ መዞር ፤ ወደ ሆነ ነገር መዞር ) ማለት ነው፡፡ "ንስሃ መግባት" እና "እምነት" (ለምሳሌ፤ማቴ 3:2፤ 4:17፤ ማር 1:4፣15፤ 2:17፤ ሉቃ 3:3፣8፤ 5:32፤ 13:3፣5፤ 15:7፤ 17:3) ሁለቱ ዋነኛ አስፈላጊ የቃል ኪዳኑ ነገሮች እንደሆኑ እውነት ከሆነ *nhm* የሚያመለክተው የራስን ኃጥያት በጥልቅ ተገንዝቦ ከሱም መመለስ መሆኑን ሲሆን *swb* ከኃጥያት ወደ እግዚአብሔር መመለስን ሊያሳይ ይችላል (ለነዚህ ሁለት መንፈሳዊ ተግባሮች አንዱ ምሳሌ አሞፅ 4:6-10 4:6-11፣ "ወደ እኔ አልተመለሳችሁም" [አምስት ጊዜ] እና አሞፅ 5:4፣6፣14፣ "እኔን ፈልጉ እግዚአብሔርን ፈልጉ መልካሙን እንጂ ክፋውን አትፈልጉ ")፡፡
የንስሃን ኃይል ጥቅም በተመለከተ የመጀመሪያወና ቀዳሚው ታላቅ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው ዳዊት ከቤርሳቤህን ጋር የፈጸመው ኃጥያት ነው (ዝ.ከ. 2ኛሳሙ 12፣ መዝ 32፣51)፡፡ በዚህም ምክንያት የተነሳ በዳዊት ፣ በቤተሰቡ እና በእስራኤል ላይ ብዙ ተከታታይ ነገሮች የተሰቱ ቢሆንም እንኳን ዳዊት ከእግዚአብሔር ጋር ወደ ነበረው ህብረት ተመልሷል! አመጸኛው ምናሴም
እናኳን ንስሃ መግባት እና ይቅርታን ማግኘት ይችላል(ዝ.ከ. 2ኛዜና 33:12-13)፡፡
እነዚህ ሁለት ቃላቶች በመዝ 90:13 ውስጥ በተያያዥነት ተጠቅሷል፡፡ ኃጥያተኛነትን መገንዘብ ፣ በእውነተኛ ማንነትም ከኃጥያተኝነት መመለስ እና እግዚአብሔርን እና ጽድቁን መፈለግ አስፈላጊ ነገሮች ናቸው (ዝ.ከ. ኢሳ 1:16-20)፡፡ንስሃ መግባት አዕምሮአዊ ፣ግላዊ እና ግብረገብአዊ ባህሪያት አሉት፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር አዲስ ግንኙነት ለመጀመር እና ለማጠናከር ሁሉም ሁሉም አስፈላጊዎች ናቸው፡፡ ጥልቅ የጸጸት ስሜት ወደ እግዚአብሔር መሰጠት ውስጥ እና ለእግዚአብሔር ወደ ማደር ውስጥ ያስገባናል!

**1:3 "ገለዓድን በብረት መንኰራኵር አሂዶአልና"** ይህ ሶሪያዊያንን ይገልፃል፡፡በ (BDB 190፤KB 218) ላይ ዕላቂ የሌሌው ግንባታ የሚላው ግስ በእርሻ ስራ ውስጥ ፍሬ ከቅርፊት የሚለይበት ሂደት ነው፡፡ በምሣሌያዊ አነጋገር ስንጠቀምበት (2ኛነገ 13:7፤ ኢሳ 21:10፤ኤር 50፡ 11፤ና ሆሰ 10:11) ላይ ያለውን ሀሳብ ይገልፃል፡፡ የእግዚአብሔርን ፍርድ ይገልፃል (ለምሣሌ:- ሚክ 4:13፤ ዕንባ 3:12)

እዚህ ላይ ቃሉ ዘይቢያዊ ሊሆን ይችላል ነገር ግን 2ኛሳሙ 12:31ን በተረጎመው መሰረት ቀትተኛ ሊሆን ይችላል፡፡ ቀትተኛም ሆነ ዘይቢያዊ ይህ የሚናገረው ሶሪያ እስራኤልን መበደልዋን ነው፡፡ (ምናልባትም ከ 2ተኛ ነገ 13:1-9 ጋር ይዛመዳል)

▣ **"ገለዓድን"** ይህ ስም (BDB 166) ለያዕቆብ ፤ ሮቤል እና ለጋድ ልጆች ተሰጥቶአቸው የነበረውን በ አሞን እና ያቦቅ ወንዞች መካከል በሰሜናዊ ዮርዳኖስ የሚገኘውን ቦታ የሚያመለክት ነው፡፡ የሶሪያ(Aram) ጭካኔ ከ 2ኛ ነገ 8:28-29 or 10:32-33 ሊዛመድ ይችላል፡፡

**1:4 "እሳትን እሰድዳለሁ"** ይህ ገላጭ ግስ (BDB 1018፤ KB 1511) *Piel ቀጥተኛ* ሲሆን ይህም ከ "ፍጆታ" ፤"ማቋረጥ" እና "ማለያየት " ከሚሉት ቃላት ጋር ተያይዞ የሚሄድ ነው፡፡እግዚአብሔር የአዛሄልንም(Syria፤ Aram) ቤተ ዘመድ እና ምሽግ ያጠፋል፡፡
እሳት በኃጥያትነት ላይ የእግዚአብሔር ን ፍርድ አመልካች ነው፡፡ (ለምሳሌ ኢሳ 30:27፤ ኤር 21:14፤ እዝ20:47-48፤ ሶፎ 1:18፤ 3:8፤ ሚል4:1) ስለ እሳት በ 7:4 ላይ ልዩርዕስ ተመልከት፡፡

▣ **"አዛሄል"**ይህ የሶሪያ አምባገነን ንጉስ ነበር (BDB 303፤ ዝ.ከ. 2ኛ ነገ 8:7-15) የነገሰውም ከ842-796 ከክርስቶስ ልደት በፊት(?) ድረስ ነበር፡፡ ይህ ንጉስ የአሶራዊያን ወደ ምዕራብ መስፋፋት የሚቃወም ሃይለኛ ወታደራዊ ሃይል የነበረው ነበር፡፡ሶሪያ በተደጋጋሚ ጊዜ ትወረር ነበር፤ነገር ግን ደማስቆ አልተወሰደችም ነበር (ይህም ማለት 841፤ 837፤ እና ምናልባትም 836 ከክርስቶስ ልደት በፊት )
በአንድ ሰሞን አዛሄል የደቡብ ጎለቤቶቹን ሲያጠቃ በነበረበት ወቅት የ አሶራዊያንn ጭንቅ ቀንሶ ነበር፡፡
1. ዮርዳኖስ አካባቢ 2ኛ ነገ 10:32-33
2. ፍልስጤም 2ኛ ነገ 12:17
3. ይሁዳ 2ኛ ነገ 12:17-18

▣ **"ምሽጎች"ይህ ቃል**(BDB 74) በተለያዩ መንገዶች ተተርጉሚል፡፡
1. ጠንካራ ይዞታ(ምሽግ)

2. በወታደሮች የተጠበቀ በተመንግስት ወይም ቤተ መቅደስ
3. መከላከያ ሃይል

የ Akkadian የተውሶቃል የሆነው *ቢሳ*፤ ከምርኮ በፊት በነበረው ስነፅሑፍ ጎን ለጎን ይጠቀስ ነበር (ለምሳሌ ጠንካራ ምሽግ 2ኛ ዜና17:12 27:4 ውስጥ እና ቤተ መቅደስ 1ኛዜና 29:1፤ ነህ 2:8 ውስጥ)

▣ **"ወልደ አዴር"** ይህ (BDB 122፤ ዝ.ከ. 2ኛ ነገ 13:3፤24-25) የአዛሄል ልጅ ነው፡፡ (797-775 ከክርስቶስ ልደት በፊት ?) ምናልባትም ይህ ስም የተሰጠው በአባቱ ሊሆን ይችላል(በታሪክ ውስጥ እንደ ወልደ አዴርIII) ምክንያቱም ይህ ስም(የንጉሳዊ ቤተሰብ ስያሜ) ለምሳሌ በግብፅ ፈርኦን ወይም በሮማ ቄሳር እንደሚባለው ሁሉ የሶሪያ ንጉሳዊ ቤተሰብም ባብዛኛው ይህን ስም እያዘወተሩ መጥተው ነበር፡፡
በተጨማሪም የማዕበል ዓምላክ የሚባለውን Hadad (*ባኣል* or *ሬሞን*፤ ዝ.ከ. 2ኛ ነገ 5:18) ማምለክን ሊያመለክት ይችላል፡፡
በዚህ ሁኔታ ሲታይ ጣዖት አምልኮን መቃወም ሊሆን ይችላል፡፡

**1:5 "የደማስቀንም መወርወሪያ"** በቀጥታ ይህ በሁለት ዋና መግቢያው የእንጨት በሮች ላይ የሚከረቸሙትን ትላልቅ ሁለት እንጨቶችን (ወይም አንዳንድ ጊዜ በብረት ዘንግ ዝ.ከ. 1ኛ ነገ 4:13) ያመለክታል፡፡
ዘይቤው ደግሞ የአራምን Aram) መንኮታኮት እና ከአገር መውጣትን ያመለክታል፡፡
▣

| | |
|---|---|
| **NASB፤ NKJV፤** | |
| **NJB** | **"ነዋሪው"** |
| **NRSV፤ TEV** | **"ነዋሪዎቹ"** |
| **NIV** | **"ንጉሱ"** |
| **NET** | **"መሪው"** |
| **JB** | **"የነገሰው"** |

ይህ *Qal ACTIVE PARTICIPLE (የድረጊት ቦዝ አንቀፅ)* ወንድ ነጠላ (BDB 442፤ KB 444) በእዚህ ቃል እና
1 ቁጥር 5ሐ፤ "እሱ በትረ መንግስቱን(በትሩን) የያዘው"
2 ቁጥር 8ለ፤ "እሱ በትረ መንግስቱን (በትሩን) የያዘው" መካከል ተመሳሳይነት እንዳለ ግልፅ ነው፡፡
*የRotherham's Emphasized Bible* "እሱ የተቀመጠው = የነገሰው" የሚል የግርጌ ማስታወሻ አለው፡፡(ገፅ 873)፡፡

▣ **"ከአዌን ሸለቆ"** የዚህ "አዌን" (BDB 19) የሚለው ቃል ትርጉም የመከተሉት ሊሆን ይችላል፡፡
1 ሽብር
2 ፀፀት
3 ኃጥያተኝነት
4 ጣዖት አምላኪነት
ይህም ከአሞጽ እስከ ሆሴ ባሉት መፅሃፍት ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡
1 የጣኦት አምልኮ ቦታ (አሞፅ)
2 ቤቴልን በሚጠቀም የዕብራይስጥ ቃል የተገለፀ (ማጣቀሻ ሆሴ 4፡15፣ 5፡8፣ 10፡5-8)
3 ሃጥያትን የሚጠቁም (ማጣቀሻ ሆሴ 6፡8፣ 10፡8፣ 12፡11)
4 ባዶነት (ይህ ማለት የጣኦት አምልኮ ከንቱነት ማጣቀሻ አሞፅ 5:5)
እዚህ ላይ ይህ የሚያመለክተው በሶሪያ ውስጥ አንድ ቦታን ነው፡፡*The Expositor's Bible Commentary*፤ ጥራዝ 7፤ ገፅ 284፤ እንደሚያስቀምጠው በግሪክ ጊዜ Heliopolis የሚባለውን የ አይሁድቃል በ Baalbek ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ McComiskey አስረግጦ እንደሚናገረው በሶሪያ እና በግብፅ መካከል በነበረው ግንኙነት ምክኒያት ይህ ከተማ ምናልበታትም አንድ የግብፃዊያንን የከተማ ስም *Onን* ሳይወስድ አይቀርም (ማጣቀሻthe በሰባ ሊቃናት ትርጉም)፡፡ የቦታው አቀማመጥ በስነ መልክዓ ምድር አልተረጋገጠም፡፡ ነገር ግን አብዛኞቹ እንደሚያምኑት ቦታው የ Bukaa ሸለቆ ነው፡፡ (ማጣቀሻ በሰባ ሊቃናት ትርጉም )

▣ **"እሱ በትረመንግስቱን የያዘው"**በመጀመሪያ በትረመንግስት(BDB 986) ያመለክት የነበረው ከእንጨት የተሠራ ለጦርነት የሚያገለግል መሳሪያን ነበር፡፡ በዛን ዘመን መሪዎች የነበሩት በደንብ ይዋጉ የነበሩት ነበሩ፡፡ ከእንጨት የተሰራው ይህ መሳሪያቸው የስልጣን፤ የመሪነት እና የሀይለኝነት ምልክት እየሆነ መጣ፡፡ ይህ በትረ መንግስት በኢሳ 14፡5፣ አሞፅ 1፡5፣8 ዘካ10፡11 ውስጥ እንደተገለፀው የማያምኑ ህዝቦች ነገስታት ተጠቅመውበታል፡፡ እንዲሁም እንደ እግዚአብሔር መሱ ኃይል ኢሳ11፡4 ውስጥ ጥቅም ላይ እንደዋለ ያሳያል፡፡

▣ **"ከኤደን ቤት"** ይህ ስም "የደስታ ቤት" ማለት ነው(CONSTRUCT BDB 108 እና112) ) ያልተረጋገጠ የስነ መልክአምድር ያለው ሲሆን ነገር ግን ይህ ቦታ ሊሆን የሚችለው (1) ከአራም (Aram) በስተሰሜን በኤፍራጥስ ወንዝ የተከበበ ሃገር (Assurnasirpal II እና ፣ በ Shalmaneser III ጊዜ) ወይም (2) በ Bukaa ሸለቆ ውስጥ የሚገኝ Baalbek (በTiglath-pileser III ጊዜ )

▣ **"ስለዚህ የሶሪያም ህዝብ ወዲ ቂር ይማረካል"** በ 9፡7 ላይ እንደምንማረው ይህ ቦታ የትውልድ ሀገራቸው ነበር፡፡ ኑሮዋአቸውን ከጀመሩበት ቦታ ይሰደዳሉ (BDB 885፤ ማጣቀሻ 2ኛ ነገ 16:9) ቢሆንም ግን የዚህ ቦታ ትክክለኛ ስፍራ አይታወቅም (ዝ.ከ. ኢሳ22:6) ኢሳ 22፡6) አብዛኞቹ በኢላም ውስጥ የሚገኝ ስፍራ እንደሆነ ይጠቁማሉ፡፡

## አሞፅ 1፡6-8

**[6]እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ለኤዶምያስ አሳልፈው ይሰጡአቸው ዘንድ ምርኮኞችን ሁሉ ማርከዋልና ስለ ሦስት ወይም ስለ አራት የጋዛ ኃጢአት መቅሠፍቴን ከማድረግ አልመለስም። [7] በጋዛ ቅጥር ላይ እሳትን እሰድዳለሁ፥ አዳራሾቸዋንም ትበላለች። [8] ተቀማጮችን ከአዛጦን አጠፋለሁ፥ በትር የያዘውንም ከአስቀሎና አጠፋለሁ እጄንም በአቃሮን ላይ እመልሳለሁ፥ ከፍልስጥኤማውያንም የቀሩት ይጠፋሉ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፡-**

1:6 **“ጋዛ”** ይህ ከተማ (BDB 738) የፍልስጤምን ህዝብ ለመግለፅ የሚያገለግል ከተማ ነበር፡፡እነዚህ ከአጊያን (Aegean) ደሴት የመጡ እና ግብፅን ለመውረር የሞከሩ የባህር ላይ ሰዎች ነበሩ፡፡ ነገር ግን በግብፅ ተሸንፈው በ1200 አካባቢ በፊልስጤም ደቡብ ምስራቅ በሚገኝ በባህር የተከበበ መሬት ላይ ሰፍረዋል፡፡ የብረት ዘመን ቴክኖሎጂ ይዘው ስለመጡ የአካባቢውን አብዛኛውን ቦታ በቁጥጥር ስር አውለውት ነበር፡፡ ከቁጥር 6-8 ባለው ወስጥ ካሏቸው አምስታ ዋና የከተማ ግዛታቸው አራቱ ተጠቅሰዋል፣ ኢሽዶር Ashdod ፣ ኢሽከሎን Ashkelon፤፣ኢክሮን Ekron እና ጋዛ፡፡

▣ **“ምርኮኞቹን ሁሉ ማርከዋልና”** በግልፅ እንደሚታየው ከኤሳው ዘር ግንድ የመጡት በፍልስጤም የተወሰዱትን የእብረዊያን ባሮችን በመግዛት ንቁ ሆነው ተሳትፈዋል፡፡ አጠቃለይ ህብረተሰቡ ተይዘው ይሸጡ ነበር፡፡ (ማጣቀሻ እዩ 3:3-8)

▣ **“ኤዶምያስ”** አዶም፣ ሞአብ እና አሞን ከአይሁድ ጋር ዘመዳሞች ነበሩ፡፡ ይኖሩ የነበሩትም በደቡብ ዮርዳኖስ ነበር፡፡

1:7 **“እሱ በትሩን የያዘው”** ዴቪድ አላን ሁባርድ፤ <u>ኢዩኤል እና አሞፅ</u> (ቲይንዳል የብይ ኪዳን አስተያየት ገፅ 133 እና 136) ላይ አሞፅን በሚመለከቱ የሚከተሉት ጉዳዮች ትክክል እንደነበረ በመግለፅ ታሪካዊ ነጥቦችን አስቀምጧል፡፡

1 የፍልስጤም ከተሞች የንጉሳዊ ከተማ ግዛቶች የነበሩ ሲሆን ይህን በትረ ስልጣን ይዘው በነበሩ ሌሎች ከተሞች የተከበቡ የንጉሳዊያን የከተማ ግዛቶች ነበሩ (ቁጥር7)

2 አሞናዊያን ንጉስ እና የንጉሱ ባለስላጣን ነበሯቸው ማጣቀሻ (ዝ.ከ. v 15፤ ሆሴ7:3፤5፤7፤16፤ 8:4)

1:8 **“ከፍልስጤማዊያን የቀሩት ይጠፋሉ”** (814) ከ ኢያሱ እስከ ዳዊት ባለው ጊዜ ፍልስጤማዊያን(BDB 814) የተለመዱ የይሁዳ ጠላቶች ነበሩ፡፡ እነሱም እንደ ህዝብ እና እነደ አንድ ሀገር ዜጋ ሙሉ ለሙሉ ይጠፋሉ፡፡

▣ **“እሱ ጌታ እግዚአብሔር”** ይህ ቀጥተኛ ትርጉሙ አዶን ሖዶን ያህዌ ነው፡፡ሁለቱም በአንድ ላይ ሲገኙ የሚሠጠው ትርጉም እንደ “ጌታ፤” ስለሆነ ያህዌ የሁሉም “GOD ” (እግዚአብሔር ) ፊደላት ትርጉም ነው፡፡ በ1፡2 ላይ የአማልክት ስሞች የሚለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት፡፡

**አሞፅ 1:9-10**

**[9] እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ምርኮኞችን ሁሉ ለኤዶምያስ አሳልፈው ሰጥተዋልና፥ የወንድሞችንም ቃል ኪዳን አላሰቡምና ስለ ሦስት ወይም ስለ አራት የጢሮስ ኃጢአት መቅሠፍቱን ከማድረግ አልመለስም።[10] በጢሮስ ቅጥር ላይ እሳትን እሰድዳለሁ፥ አዳራሾችዋንም ትበላለች።**

1:9 **“ጢሮስ”** ይህ (BDB 862) የሚያመለክተው ከንአናዊያን ዘሮች እና ከባህር ላይ ሰዎች የAegean ባህር የተገኙትን የፎኒሽያ ዘር ያላቸው ህብቦች ናቸው፡፡ እነዚህ ህዝቦች በኤልዛቤል ተፅዕኖ ምክኒያት በሰሜኑ አስር ነገደ ህዝቦች የገቡት የብልፅግና ጣኦታት አምላክ የነበሩትን የበአል ባኦል እና የኢሺር አስታሮት ምንጮች (ዋና መገኛ) ይሆነዋል፡፡(ዝ.ከ. 1ኛ ነገ 16:31-33፤ 18:19፤21)፡፡

## ልዩ ርዕስ፡ የጥንቱ ቅርብ ምስራቅ የመራባት አምልኮ

I. ምክንያቱ
   ሀ የጥንታዊው ሰዎች የጀመሩት እንደ አደን ሰብሳቢዎች ሲሆን ነገር ግን የዘላንነት ሕይወት እየተስፋፋ መጥቶ ለአዝዕርትና ከብር ርቢ ያለው ፍላጎት ጨመረ።
   ለ የጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ ነዋሪዎች በተፈጥሮ ኃይላት ሊጎዱ የሚችሉ ነበሩ። በዋነኞቹ የንጹሕ ውኃ አካላት አካባቢ ሥልጣኔ መስፋፋት ሲጀመር እነሱ በመደበኛው የወቅቶች ሥርዓት ላይ ጥገኞች ሆኑ።
   ሐ የተፈጥሮ ኃይላት አማልክት ሆኑ እነሱም የሚለመኑና የሚቆጣጠሩ
II. የትና ለምን
   ሀ የመራባት ሃይማኖት እያደገ የመጣው
      1. ግብፅ (ዐባይ)
      2. ሜሶፖታሚያ (ጤግሮስና ኤፍራጥስ)
      3. ከነዓን (ዮርዳኖስ)
   ለ መሠረታዊ የሆነ ተመሳሳይነት በጥንቱ ቅርብ ምስራቅ የመራባት አምልኮ መሐል አለ።
   ሐ ተለዋዋጭ የሆነውና ሊተነበይ የማይችለው ወቅትና የዓየር ሁኔታ ለአምልኮዎች ማደግ ምክንያት ሆነ፣ ይህም ሰዎችን/መለኮታዊ ምስያዎችን በመንፈሳዊ ግዛትና በምድርም ላይ እንደ ሕይወት መሠረት በመጠቀም ነው።
III. ማንና እንዴት
   ሀ. ማን (አማልክቶች እና አማልክቲቶች)
      1. ግብፅ
         ሀ. ኢሲስ (ሴት)
         ለ. ኦሲሪስ (ወንድ)
      2. ሜሶፖታሚያ
         ሀ. ኢሽታር/ኢናና (ሴት)
         ለ. ታሙዝ/ዱሙዚ (ወንድ)
      3. ከነዓን
         ሀ. በኣል (ወንድ)

ለ. አሼራህ፣ አስታርቲ፣ አናዝ (ሴት)

ለ. እነዚህ ጥንዶች እያንዳንዳቸው በተመሳሳይ መንገድ አፈ-ታሪኮች ተደርገዋል

1. አንደኛው ይሞታል
2. ሌለኛው ይመልሳል
3. የአማልክቱን ሞትና ትንሣኤ ፈርጅ የዓመቱን የተፈጥሮ ዑደት ይመስለዋል

ሐ. የማስመሰል ጥንቆላ የሰዎችን የግብረ-ሥጋ ተራክቦ የሚመለከተው (ማለትም፣ የአማልክት መጋባት) እንደ የአዝመራ፣ ከብቶች፣ እና ሰዎች መራባት ማረጋገጫ መንገድ ተደርጎ ነው።

IV. እስራኤላውያን

ሀ. የያህዌ ሕዝቦች ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል (ማለትም፣ ሌዋውያንና ዘዳግም) የመራባትን አምልኮ ያስወግዱ ዘንድ (በተለይም የከነዓንን)።

ለ. እነዚህ አምልኮዎች በጣም የታወቁ ነበሩ፣ ምክንያቱም በሰው ልጆች አፈ ታሪክና ተጨማማሪ በሆነው የግብረ - ሥጋ ግንኙነት ድርጊት።

ሐ. ዘማዊነት የሚታየው እንደ በረከት ሕይወት ነው፣ በአምልኮ ወይም በአምልኮ ሥርዓት መንገዶች፣ በያህዌ ላይ ከሚደረግ ግላዊ እምነት ወይም መታመን ይልቅ።

V. የንባብ ጥቆማዎች

ሀ. ደብሊዩ ኤፍ ኦልብራይት፣ *አርኪዎሎጂ እና የእስራኤል ሃይማኖት*

ለ. ጄ ኤች ብሬስትድ፣ *የሃይማኖትና የአስተሳሰብ ዕድገት በጥንታዊቷ ግብፅ*

ሐ. ጀምስ ጊ ፍሬዘር

1. አዶኒስ፣ አቲስ፣ ኦሲሪስ *Adonis፣ Attis፣ Osiris*
2. *በብሉይ ኪዳን ሥነ-ቃል Folklore in the Old Testament*
3. *ተፈጥሮን ማምለክ The Worship of Nature*

መ. C H Gordon፣ *Before the Bible*

ሠ. S N Kramer፣ *Mythologies of the Ancient World*

▣ **"ምርኮኞቹን ሁሉ ለኤዶሚያስ አሳልፈው ሰጥተዋልና** " Homer mentions Tyre's የጢሮስን የባሪ ንግድ *Odyssey* በሚለው መፅሐፉ ውስጥ ተጠቅሶታል 4:288ff፤ 15:473ff 23 ይህ አንድ የሆነ አይነት የውል ስምምነትን ያመለከታ ምናልባትም ከሰለሞን ጋር ከተደረገው ስምመነት ቀደም ብሎ (ማጣቀሻ 2ኛ ሳሙኤል 5፡11፣ ... 5፡1-18፣ 9፡1114)፡፡ ምናልባም ይህ አግባብ ያለሆነውን የአንዱን ጎረቤት ዜጎች ለባርነት የመሸጥ ባህሪ ሊመለከት ይችላል፡፡ በዚህ ንዑስ ክፍል የተጠቀሱት ሁሉም ሀጥያቶች የሰው ዘር በአገሩ ላይ የሚያደርገውን ኢሰብዓዊ ድርጊት ያሳየ ነው፡፡ሆሜር የጢሮስን የባሪያ ንግድ በ *Odyssey ላይ አስቀምጧል* 4:288ff፤ 15:473ff 23

▣ **"የወንድሞችንም ቃል ኪዳን አላሰቡም እና"** ይህ አንድ የሆነ አይነት የውል ስምምነትን ያመለክታል፡፡ ምናልባትም ከሰለሞን ጋር ከተደረገው ስምመነት ቀደም ብሎ (ዝ.ከ. 2ኛ ሳሙ 5: 11፤ 1ኛ ነገ 5:1-18፤ 9: 11- 14) ፡፡ ምናልባም ይህ አግባብ ያለሆነውን የአንዱን ጎረቤት ዜጎች ለባርነት የመሸጥ ባህሪ ሊመለከት ይችላል፡፡ በዚህ ንዑስ ክፍል የተጠቀሱት ሁሉም ሀጥያቶች የሰው ዘር በአገሩ ላይ የሚያደርገውን ኢሰብዓዊ ድርጊት ያሳየ ነው፡፡

1:10 **"በጢሮስ ቅጥር ላይ እሳትን እሰድዳለሁ አዳራሾችዋን ትበላለች"** ጢሮስ (የፎኒካ ዋና ከተማ ) በቀላሉ ሊደፈር የማይችል ምሽግ ያላት ደሴት ነበረች፡፡ ቢሆንም ግን ታላቁ እስከንድር ከክርስቶስ ልደት በፊት በ332 በፍልስጤም በኩል በሚያልፍ ጊዜ ሰበባት ወራት ከበባ በኋላ ጠላት ከተማዋ ስትወድም በተሰባበሩት ድንጋዮች አሸዋ መንገድ ሲሰራ ከተማዋ ተንኮታኮተች፡፡ ከታሪካዊ መዛግብት እንደምንማረው 6፤000 የሚሆኑ ተገለዋል፣ 2፤000 የሚሆኑ በስቅለት ወይም በስለት ተገለዋ እንዲሂም 30፤000 የሚሆነት በባነት ተሸጠዋል፡፡

## አሞፅ 1:11-12

**11 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ወንድሙን በሰይፍ አሳድዶታልና፥ ርኅራኄንም ሁሉ ጥሎአልና፥ ቍጣውም ሁልጊዜ ቀድዶአልና፥ መዓቱንም ለዘላለም ጠብቆአልና ስለ ሦስት ወይም ስለ አራት የኤዶምያስ ኃጢአት መቅሠፍቱን ከማድረግ አልመለስም። 12 በቴማን ላይ እሳትን እሰድዳለሁ፥ የባሶራንም አዳራሾች ትበላለች።**

1:11 **"ኤዶሚያስ"** ይህ (BDB 10) በኢያሱ በኩል በ ዘፍ 25:19-26፤ 36:1-19 እንደተጠቀሰው የእስራኤልን የቅርብ ዝምድና የሚያመለክት ነው፡፡ ኤዶምያስ እና እስራኤል ሁልጊዜ አይግባቡም ነበር፡፡ አዶምያስ የተበላሸ የቤተሰብ ጥንካሬ እና ስምምነት ምልክት እየሆነች መጣች፡፡ ኤዶምያስ በነብያት በተደጋጋሚ ጊዜ ትረገም ነበር (ዝ.ከ. ኢሳ34:5-17፤ 63:1-6፤ ኤር 49:7-22፤ Lam 4:21-22፤ እዝ25:12-14፤ 35:1- 15፤ ሚል1:2-4) Petra (ፔት) የኤዶምያስ ዋና ከተማ ነበረች (ዝ.ከ. መዝ137:7፤ እዝ25:12-14፤ Obad 10-15፤ ሚል1:2-4) ኤዶምያስ በይሁዳ በስተምስራቅ ዮርዳኖስ ክልል (የጊዜው መጠሪያ ጆርዳን) ውስጥ የሚገኝ ቦታ ነበር፡፡

◘

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"ርህራሄ"** |
| **NKJV፤ NRSV፤ NJB** | **"የሃዘን ስሜት"** |
| **TEV** | **"ምህረት"** |

ይህ ቃል (BDB 933) በተጨማም ከአጋር ሀገር ጋር የሚደረግ የውል ስምመነትን ሊያመለክትም ይችላል (ይህም ማለት "አገር ህዝብ ally፤" በNIV የግርጌ ማስታወሻ እና ... NET መፅሐፍ ቅዱስ)

▣ "ቁጣውንም ሁል ጊዜ ቀዷልና መዓቱንም ለዘላለም ጠብቋልና"
እነዚህ ሁለት ግጥማዊ ዓረፍተነገሮች (ሀረጎች) ተያያዥነት አላቸው፡፡ "ቁጣውንም" የሚያመለክተው የኦዶምስን በእስራኤል ላይ የማይቀየር እና የሚቀጥል ቁጣን ነው፡፡ (ዝ.ከ. NEB) እነደገና የእግዚአብሔር ፍርድ የመጣበት ምክኒያት በህዝቦቹ ላይ በዋናነት በዘመዳሞች ላይ በሚፈፀም ሀጥያት ነው፡፡

1:12 **"ቴማን"**ይህም(BDB 412) በሰሜን ኤዶምያስ ዋና ከተማዋም Bozrah (ቦዝራ) የነበረች የኤዶሚያስን ግዛት ያመለክት ነበር፡፡

▣ **"ባሶራ "** ይህ (B DB 131) የሚያመለክተው በሰሜን የኤዶሚያስ ከተሞች ትልቅ ከሚባሉት ውስጥ አንዱ ሲሆን "የንጉሱ የክብርመንገድ" (የዮርዳኖስ ከሰሜን አካባ ባህረ ሰላጤ ወደ ሶርያ በሚደረገው ንግድ ዙረት ) የተባለ ዋና ውብ ከተማን ነው፡፡ ይህ ቦታ ትልቅ ጥንታዊ ታሪክ የነበረው ከተማ ነበር(ዝ.ከ. ዘፍ 36:33፤ 1ኛዜና 1:44)

## አሞፅ 1:13-15

**[13] እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ዳርቻቸውን ያሰፉ ዘንድ የገለዓድን እርጉዞች ቀድደዋልና ስለ ሦስት ወይም ስለ አራት የአሞን ልጆች ኃጢአት መቅሠፍቴን ከማድረግ አልመለስም። [14] በረባት ቅጥር ላይ እሳትን አነድዳለሁ በሰልፍም ቀን በጩኸት በዐውሎ ነፋስም ቀን በሁከት አዳራሾችዋን ትበላለች፡ [15] ንጉሣቸውም ከአለቆቹ ጋር በአንድነት ይማረካል፥ ይላል እግዚአብሔር፡-**

1:13 **"አሞን"** ይህም (BDB 769) እንደዚሁ በሎጥ በኩል የእስራኤል ዘመድ ነው፡፡(ዝ.ከ. ዘፍ 19:30-38) እስራኤላዊያን ከግብፅ በወጡበት ጊዜ ዘመዳሞች ስለነበሩ አሞናዊያንን አልተቋወሟቸውም (ዝ.ከ. ዘዳ 2:19) አሞን በ ዮርዳኖስ area ውስጥ በአሞንእና ያቦቅ ወንዝ መካከል የሚገኝ ቦታ ነበር፡፡
▣ **"የገለዓድን እርጉዞች ቀድደዋልና"** Gilead (BDB 166) ገ በሰሜን ዮርዳኖስ አካባቢ ውስጥ የሚገኝ ቦታ ነው፡፡ለዚህ ለተጠቀሰው ክንውን ምንም ዓይነት ታካዊ ማጣቀሻ ባይኖርም ይህ አይነት ልምድ እንደነበረ በደንብ ይታወቃል(ዝ.ከ. 2ኛ ነገ 8:12፤ 15:16፤ ሆሴ 13:16) ፡፡ ምንም ቢሆን ግን በኃይለኛ (በረባሽ) የጦር ልምምዳቸው ምክኒያት የእግዚአብሔር ፍርድ በእነዚህ ህዝቦች ላይ ወርዷል፡፡

▣ **"ዳርቻቸውንም ያሰፉ ዘንድ"** ይህ የንፁሃን ሴቶች እና ሕፃናት ግድያ እስራኤላዊያን ኢያሪኮን አጥቅተውት እንደነበረው ዓይነት ቅዱስ ጦርነት ጋር አይዛመድም (ዝ.ከ. ኢያ 6) ነገር ግን በቀላሉ ብዙ መሬት የመያዝ ያልተገራ ፍላጎት ያነሳሳው ጦርነት ነበር፡፡
1:14 **"ራባትRabbah"** ይህ ቃል ትጉሙ "ቅልቁ" እንደ ማለት ነው (BDB 913) ይህ መጠሪያ በጃቦክ ያቦቅ የወንዝ ምንጭ የሚገኝኝ የአሞን ከተማን ለመግለፅ ይጠቅም ነበር፡፡(ዝ.ከ. ዘዳ3:11፤ 2ኛ ሳሙ 12:26፤ 17:27)

▣

| | |
|---|---|
| NASB፤ NJB | **"የጦርነት ለቅሶዎች"** |
| NKJV፤ NRSV፤ | |
| TEV | **"መጮህ"** |

ይህ መጠሪያ (ቃል) (BDB 929) ብዙ ተዛማጅ ዘርፎች አሉት

1. ጭሁወትን ማብዛት (መጨመር)
   ሀ. ለጥቃት
   ለ. ለድል አድራጊነት
   ሐ. ለአምልኮ
   መ. ለውድመት

2. ድንገተኛ ጩኸት (ፍንዳታ ) ማድረግ

በ ኢያ6:5፤10፤16፤20 ውስጥ እንደሚገኘው አብዛኛውን ጊዜ የትግል ለቅሶ ከሙዚቃ ጩኸት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ እያንዳነዱ የሀገር ህዝብ የራሱ የሆነ የጦርነት ለቅሶ ነበረው፡፡ (ዝ.ከ. 2:2፤ 1ኛሳሙ 17:20፤52 በተጨማም የRoland deVaux፤ጥንቷ እስራኤል ላይ ጥራዝ 1 ገፅ 9፣ 254ን ተመልከት)፡፡ እስራኤል ከ ያህዌያህዌ ጋር ተያይዞ ነበር (ዝ.ከ. መሳ 7:20-21)

# አሞፅ 2
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|
| ፍረድ በህዝቦች ላይ (1:3-2:3) | የጎረቤት ህዝቦች፤ እስራኤልና ይሁዳ የክስ ማስረጃ (1:2-2:16) | በእስራኤል ጎረቤቶች ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ (1:1-2:5) | ፍረድ በጎረቤት ህዝቦች ላይ እና በራስዋ በእስራኤል ላይ (1:3-2:16) |
| | | ሞአብ | ሞአብ |
| 2:1-3 | 2:1-3 | 2:1-3 | 2:1-3 |
| ፍረድ በይሁዳ ላይ 2:4-5 | 2:4-5 | ይሁዳ 2:4-5 | በይሁዳ 2:4-5 |
| ፍረድ በእስራኤል ላይ | | የእግዚአብሔር ፍረድ በእስራኤል ላይ | እስራኤል |
| 2:6-8 | 2:6-8 | 2:6-8 | 2:6-8 |
| 2:9-12 | 2:9-11 | 2:9-3:2 | 2:9-11 |
| | 2:12 | | 2:12-16 |
| 2:13-16 | 2:13-16 | | |

### የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ vii ተመልከት)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

### አሞፅ 2፡1-3

**[1]እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- የኤዶምያስን ንጉሥ አጥንት አመድ እስኪሆን ድረስ አቃጥሎታልና**
**ስለ ሦስት ወይም ስለ አራት የሞዓብ ኃጢአት መቅሠፍቴን ከማድረግ አልመለስም።**
**[2] በሞዓብ ላይ እሳትን እሰድዳለሁ፥ የቂርዮትንም አዳራሾች ትበላለች ሞዓብም በውካታና**
**በጩኸት በመለከትም ድምፅ ይሞታል**
**[3] ፈራጅንም ከመካከልዋ አጠፋለሁ፥ ከእርሱም ጋር አለቆችዋን ሁሉ እገድላለሁ፥ ይላል እግዚአብሔር፡-**

**2:1** በምዕራፍ አንድ የነበረው የፍርድ ሁኔታ በቀጥታ በምዕራፍ ሁለትም ቀጥሏል (ዝ.ከ. 1:3)።

▣ **"ሞኣብ"** እነዚህ በሎጥ በኩል ከእስራኤላዊያን ጋር ዝምድና ነበራቸው (ዝ.ከ. ዘፍ 19:30-38)፡፡ ሀገሪቱ በዮርዳኖስ ቦታ አሞን እና Zered ወንዞች መካከል በኤዶሚያስ በስተሰሜን ትገኛለችል፡፡

▣ **"የኤዶምያስን ንጉስ አጥንት አመድ እስኪሆን ድረስ አቃጥሎታልና"** እነዚህ ተግባት ማለትም 1) መቃብርን መክፈት 2)፤ የሞተውን ሰው አካል ማስወገድ፤ 3) እነዚህንም ማቃጠል፤ 4) እነዚህንም በመቀላቀል ለህንጻ የሚሆን ሲሚንቶ ወይም ፒላሰቲክ ([ግድግዳን ኖራ ለመቀባት]) መስራት አንድን ሰው እንደ ማዋረድ እና ከሞት በኋላ ያለውን ዕረፍት በመጥፎ መልኩ የሚነካ ሆኖ ይታይ ነበር፡፡

ይህን በባህል የተወገዘወን እና በሃይማኖት የተከለከለውን ነገር ሆን ብሎ መተላለፍ የነበረውን የመቃረን ደረጃ ያሳያል፡፡ ይህ ሬሳን ማቃጠል የሞተን ሰው ስጋን የማስወገጃ መንገድ ሳይሆን የሚነግረን የሃየማኖት ወይም የህብተሰብን ህግ እንደመጣስ መሆኑን ነው፡፡ያም ሆነ ይህ እኔን ሬሳን ስለማቃጠል ዘመናዊ አስተሳብ ላይ ጥናት እንዳካሄድ እድልን ሰጥቶኛል፡፡

የሞተን ሰው ማቃጠል ለሁሉም በምስራቃዊ አቅራቢያ ላሉ ህዝቦች ዘግናኝ ልምምድ ነበር፡፡ ይሄም በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ ከትልቅ ወንጀል ጋር ብቻ በማያያዝ ተገልፆአል (ዝ.ከ. ዘፍ 28:24፤ ዘሌ 20:14፤ 21:9፤ ኢያ7:15፤25) ተያያዥነት ባለው መልኩ ሞኣብ በጥላቻ የኤዶሚስን ንጉስ አጥንቶች አቃጠለና እነዚህንም ህንጻዎችን ለመገንባት ወይም ግድግዳዎች ለማጽኛ ፕላስተር መስሪያ (ኖራ የተቀባ ግድግዳ(Targums) እንዲሆኑ ከ ስሚንቶ ጋር ቀላቀላቸው (Targums)፡፡ ኖራ (BDB 966፤ ዝ.ከ. ኢሳ33:12) የ ስሚንቶ እና የፕላስተር ቅልቅል ነው፡፡

ይህ ተግባር ለአጠቃላይ ጥፋት መገለጫ ሊሆን የሚችል ነው (ይህም ማለት ቮልጌት)፡፡ግሶችን በቀጥተኛ እና ዘይቢያዊ ጥቅማቸው ለመተርጎም አስቸጋሪ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በዋናነት በአሞፅ መፅሀፍ ውስጥ እንዳሉት አይነት ግጥማዊ ምንባቦች እውነት ነው፡፡

## ልዩ ርዕስ፡ ማቃጠል

I. ብሉይ ኪዳን
   ሀ. ማቃጠል ከአራቱ የሞት ቅጣት መፈጸሚያ መንገዶች አንደኛው ነው፣ በሌዋውያን (ዝ.ከ. 20:14፤ 21:9፣ ምሳሌ፣ ዘፍ 28:24 እና ኢያ 7:15፣25)።
   ለ. የሳኦል ወዳጆች የሆኑ ሰዎች የሱን አስከሬንና የሦስት ልጆቹን ከፍልስጥኤም ይዘው አቃጠሏቸው፤ አጥንታቸውን በቢንያም ምድር ከመቅበራቸው በፊት (1ኛ ሳሙ 31፡12-13፣ በ1ኛ ዜና 10፡12 ትይዩ ላይ ተገድፏል)
   በሊቃውንት መካከል መጠነኛ አለመግባባት አለ፣ "ማቃጠል" በተቃርኖ "መቀባት" በሚለው አነባበብ ላይ። ይህ ጽሑፍ ብቸኛው አዎንታዊ ማቃጠል የሚመስል ነው፣ በብኪ (ኢንሳይክሎፔዲያ ጁዳሲያ፣ ቅጽ 5፣ ገጽ 1074)። እሱም ደግሞ ምናልባት የሚያመለክተው ቅመሞችን ማቃጠል ነው (2ኛ ዜና 16:14፤ 21:19፤ ኤር 34:5)።
   ሐ. ኋላ ላይ ይሁዳዊ ነቢይ የካህናቱን በቤቴል መቃጠል ተነበየ፣ በመሥዋዕት ማቅረቢያው መሠዊያ ላይ (1ኛ ነገሥ 13፡2)።
   መ. የማቃጠል ጉዳይ አንዳንድ ጊዜ በስህተት ከብኪ የፍርድ እሳት አጠቃቀም ዘይቤ ጋር ይያያዛል (ኢሳ 30፡33)። የማቃጠል ዘይቤዎች (ማለትም፣ "የማቃጠያ ግንድ") ለመጨረሻው የኩነኔ ፍርድ ማሳያ ጥቅም ላይ ይውላል።
   ሠ. ቀብር በጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ አገሮች ሁሉ የተለመደ ተግባር ነው (ሮላንድ ዴ ቫዩክስ፣ ጥንታዊ እስራኤል፣ ቅጽ 1፣ ገጽ 57)። ማቃጠል እንደ ማዋረድ ይታይ ነበር (አሞጽ 2፡1)።
II. ግሪክና ሮሜ
   ሀ. እነዚህ ሁለቱም ሥልጣኔዎች ማቃጠልን ያደርጉ ነበር።
      1. ግሪክ፣ በመደበኛነት (ሶፎክለስ፣ ኤሌክትራ፣ 1136-1139)
      2. ሮሜ፣ ይደረግ ነበር፣ የተለመደ ግን አይደለም፣ አማራጭ (ሲሴሮ፣ ዴሊግ 2፣22፣56)
   ለ. የሜዲትራኒያን ባህል ከጥንት ቅርብ ምስራቅ ባህል ይልቅ የተለየ አቋም አለው፣ በማቃጠል ላይ። ታሲተስ እንደጠቀሰው፣ አይሁድ ይቀብራሉ እንጂ አያቃጥሉም (ታሪክ 5 5)።
III. ራቢያዊ ይሁዲነት
   ሀ. አብዛኞቹ የጥንት ራቢዎች የሚሉት መቅበር በዘዳ 21፡23 ታዟል።
   ለ. መቃጠል በታልሙድ ተከልክሏል (ሳንህ 7፡2፤24ለ) እና ሚሽና (አቦዲአ ዛራ 1 3)።
   ሐ. ዘመናዊ ይሁዲነት፣ የተቃጠሉት በአይሁድ መቃብር እንዲያርፉ ይፈቅዳል (ኢንሳይክሎፔዲያ ጁጃይካ፣ ቅጽ 5፣ ገጽ 1074)።
IV. አዲስ ኪዳን
   ይህን ጉዳይ በተመለከተ በአኪ የተብራራ ወይም የተጠቀሰ ነገር የለም።
   ሥጋዊ አካል የሚታየው እንደ ጊዜያዊ መጠጊያ ነው (2ኛ ቆሮ 5)። ከአሮጌው አካል፣ ከአማኝ ጋር በዳግም ምጽዓቱ የሚሆን ነገር ይኖራል፣ ነገር ግን ምንም ዓይነት ዝርዝር ወይም ማብራሪያ የለም (1ኛ ተሰ 4፡13-18)። ይህ ለክርስቲያኖች የ"እምነት እና ልምምድ" ጉዳይ አይደለም። እንደ ብኪ አይሁድ፣ የአኪ አማኞች የሥጋ ትንሣኤን ያስረግጣሉ። የመጨረሻው ጊዜ አካላዊነት ይኖራል፣ ነገር ግን እንዴትና ለምኑ አልተለየም! የሥጋዊ ቅሪት ሁኔታና ስፍራ አማኞችን ከኢየሱስ ጋር ዳግም መገናኘትን አያግድም። ቁልፉ በክርስቶስ ያለ እምነት ነው እንጂ አካላዊ ቅሪት አይደለም!

**2:2 "እሳትን አወርዳለሁ"** ይህ ሀረግ የሚያመለክተው

3. የ ያህዌን ፍርድ
4. ከተሞችን ማቃጠል

በአሞፅ ውስጥ ይህ እንደገና የተጠቀሰው 1፡4፣ 7፣ 10፣ 14፣ 2፡2፣ 5 እና በሆሴ 8፡14 ነው፡፡ እሳት አብዛኛውን ጊዜ እንዲ የማጥራትነ ስራ አከናዋኝ እና የእግዚአብሔር ን የመገኘት ምልክት ሆኖ ይወርዳል፡፡ እሳት በ7፡4 ልዩ ርዕስ ተመልከት፡፡

▣ **"ምሽጎች"** በ 1፡4 ላይ ማስታወሻን ተመልከት፡፡

▣ **"ቂርያት"** ይህ የክልል ወይም የከተማ ስም ነው፡፡ NEB ከ የሰባ ሊቃናት ትርጉምቀጥሎ እንደ "ከተማ" ይተረጉመዋል (ምክንያቱም ዝ.ከ. ኤር 48:41) ነገር ግን የ NEB የታረመው እትም REB የሚባለው የቦታውን ስም ወደ አተረጓጓሙ ይመልሰዋል (ይህ ማለት "የቂርያት ቤተመንግስት")፡፡ ይህ ከተማ እንደገና በ ኤር 48:24፤41 ውስጥ ተጠቅሷል፡፡ ይህች ከተማ (ምናልባትም *ቂር*፤ ዝ.ከ. ፡ኢሳ 15:1) ለሞአባዊያን ዘር ሰጪ አማልክትን የማመለኪያ ዋና ቦታ ነበረች፡፡*ኬምሽ* (ዝ.ከ. *The Mesha Stone* L 12፤ 1ኛ ነገ 11:33)፡፡

▣ **"በሁካታ እና በጩኸት"** በ 1፡14 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት፡፡ የሁካታ ጩኸት እና የመለከት መነፋት አብዛኛውን ጊዜ በትግል ውስጥ እንደማንቂያ ይጠቅማሉ፡፡ በአንዳንድ ይዘቶች ያሉ ሃረጎች ድምጹ በትግል ጊዜ እንደ ግራመጋባት እና እነደ ፍራቻ ያስቀምጡታል፡፡

▣ **"በመለከትም ድምፅ"** መለከት በጦርነት ሜዳ ላይ ወታደሮችን ለማሰማራት ይጠቅም ነበር፡፡ በ1፡14 ላይ ለውን ማስታወሻ ተመልከት፡፡

**2:3 "ፈራጅንም"** ይህ በንጉሳዊ ዕይታ ነው የቀረበው፡፡ ንጉሱ እነደ ፈራጅ ሆኖ ነው የሚከውነው (ዝ.ከ. ሚል 5:2)፣ እንደ እግዚአብሔር ተወካይ ሆኖ (ዝ.ከ. ዘፍ 18:25፤ መሳ 11:27፤ መዝ50:6፤ 75:7፤ 94:2፤ ኢሳ 33:22)፡፡ ጎን ለጎን ያለው ሐረግ "ሁሉንም የእሷን አለቆችዋን" የንጉሳዊ ቤተሰብን ያመለክታል፡፡ ሞአብ እንደ አንድ ሀገር ህዝብ ሙሉ ለሙሉ የሚጠፋ ይሆናል፡፡(ዝ.ከ. Mal 1:2-5)

**አሞፅ፡2:4-5**
**4 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- የእግዚአብሔርን ሕግ ጥለዋልና፥ ትእዛዙንም አልጠበቁምና፥**
**አባቶቻቸውም የተከተሉት ሐሰታቸው አስቶአቸዋልና ስለ ሦስት ወይም**
**ስለ አራት የይሁዳ ኃጢአት መቅሠፍቴን ከማድረግ አልመለስም።**
**5 በይሁዳ ላይ እሳትን እሰድዳለሁ፥ የኢየሩሳሌምንም አዳራሾች ትበላለች።**

**2:4 "ይሁዳ›** በይሁዳ ላይ የተነሳው ክስ መፅሐፍ ቅዱሳዊ እንጂ ህብረተሰብሃዊ አይደለም፡፡ (የያህዌን ትዕዛዛቶች መጣል ፤ ይህም ማለት የሙሴን ህግጋቶች) ይሁዳ ክሶቹን ክዶ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን በተያያዥነትም እነዚሁኑ ኃጥያቶች በይሁዳ ስር ያሉት እስራኤላዊያን በ ያህዌ ላይ ፈፅመውታል፡፡ (ዝ.ከ. ኤር 3:6-10፤ ሕዝ 23:1-49)፡፡

▣ **"የእግዚአብሔር ንም ህግ ጥለዋልና"** "ጥለዋል" የሚለው ሐረግ (ግስ)(BDB 549፤ KB 540፤ *Qal* INFINITIVE CONSTRUCT) ተቃራኒ በሚመስሉ ሁለት መልኮች ቀርቧል፡፡

1. አንድ ሰው ወይም እንድን ነገር መጣል ወይም መቃወም (ይህም ማለት እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ን ህግ ነው፡፡)
2. የእግዚአብር ህዝቡን ለመተው አለመፈለግ፡፡ እነሱ እግዚአብሔር ን፣ የእግዚአብሔር ን ህግጋት (ዕርቅ)፣ ነብይ እና እግዚአብሔር ን ማምለክ ተቃውመዋል ነገር ግን ዕርቅ ፈልጊው እግዚአሄር ቀጣቸው እንጂ ሙሉ ለሙሉ አልጣላቸውም፡፡

እዚህ ላይ ያለው እውነት በእነዚህ ተከታታይ ቦታዎች በግልፅ ታይቷል፡፡ ኤር 6:30፤ 7:29፤ 14:19፤ and 31:37! በአሞፅ ውስጥ (ዝ.ከ. 2:4፤5:21) እና ሆሴ (ዝ.ከ. 4:6 [ድጋሚ]፤ 9:17) ያህዌ የአዝቦቹን ዘር ማነዘር እሱን እና ህግጋቱን በመተዋቸው ምክንያት ለዘመናት ትቷቸዋል፡፡ (ዝ.ከ. ሆሴ 4:6፤ 8:1፤12) ሁሉም የእስራኤል መጪ ትውልዶች እምነትን፣ንሰሀ መግባትን እና መታዘዝን ካልተለማመዱት በስተቀር ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት ፈፅሞ አልነበራቸውም

▣ **"ሐሰቶቻቸው አስቶአቸዋልና"** "ሐሰታቸው" (BDB 469) የሚለው ቃል ትጉሙ "ሐሰታቸው" "መዋሸት፤"ወይም "አሳሳች ነገር" NIDOTTE፤ ጥራዝ 2 ገፅ 619 የዚህን ቃል ባህሪያት በደንብ አስቀምጦታል፡፡
በሆነ መልኩ የእግዚአብሔር ባህሪ፤ ቃል ወይም ስራ በራሱ ነብዮቹ ወይም በፍጥረቶቹ ከተገለፀው ጋር የሚጣረር ሀሰት የሆነን ተግባር ወይም ቃል ላይ ማተኮር" መዝ 40:5 እና NIV ይህንን ሃሳብ ያንፀባርቃሉ፡፡ "ሀሰቶቻቹ" የሚለው ቃል የሀሰት ትምህርትን እና የሀሰት አማልክን ማምለክን ያመለክታል፡፡ (ዝ.ከ. ዕብ 2:18) ይሄው ተመሳሳይ ሃሳብ በአዲስ ኪዳን 1ኛ ዩሐንስ ውስጥ "ሐሰት" ከፍተኛ ሀጥያት የሆነውን እና ከህግጋት ኪዳን የማይገጥም ክርሰቶስን አለማመንን ያመለክታል፡፡

▣ **"አባቶቻቸውም የተከተሉት"** እዚህ ጋር የሚያስረዳው ይህ ትውልድ ልክ እነደ ቀድሞው ትውልድ በታማኝነት የካኖን ዘር ሰጪ አማልክትን ያመልኩ እንደነበር ነው፡፡ (ይህም ማለት፤ ባአል and *አሲታሮት/አስታሮት*)፡፡
ይህ የሚያመለክተው በሚመጡት ቀናት ከሀር የወጡት ባቢሎናዊያን ይሁዳ ላይ የሚሰፍሩ መሆኑን ነው፡፡ (ይህም ማቴ 586-539)።

**አሞፅ 2፡6-8**

**6 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ጻድቁን ስለ ብር፥ ችጋረኛውንም**
**ስለ አንድ ጥንድ ጫማ ሸጠውታልና ስለ ሦስት ወይም ስለ አራት**
**የእስራኤል ኃጢአት መቅሠፍቴን ከማድረግ አልመለስም።**
**7 የድሆችን ራስ በምድር ትቢያ ላይ ይረግጣሉ፥**
**የትሑታንንም መንገድ ያጣምማሉ ቅዱሱንም ስሜን ያረክሱ ዘንድ አባትና ልጁ ወደ አንዲት ሴት ይገባሉ**
**8 በመሠዊያውም ሁሉ አጠገብ ለመያዣነት በተወሰደው ልብስ ላይ ይተኛሉ**
**በአምላካቸውም ቤት ውስጥ በካሣ የተወሰደውን ወይን ጠጅ ይጠጣሉ።**

**2:6 "እስራኤል"** አሞፅ በመጀመሪያ የአድማጭን ትኩረት ያገኘው በአካባቢው ባሉ ጠላቶች ላይ ፍርድን ሲያውጅ ነበር፡፡ በመቀጠል ደግሞ በእስራኤል ወንድሞች ላይ ፍርድን ሲያውጅ ሲሆን አሁን ግን የእግዚአብሔርን ፍርድ ወደ እነሱ ሲያዞር አስደነገጣቸው፡፡

▣ **"ፃድቁን ስለ ብር ብለው ሸጠውታልና"** በኢዶሚያስ የነበረውን ባሪያ ንግድ በመመልከት ምናልባትም ይህ ለፍልስጤም(ዝ.ከ. 1:6) እና ለፎኒካነስ (ዝ.ከ. 1:9) የሀገራቸውን ሰው ለባርነት አሳልፈው ስለመሸጣቸው አመልካች ይሆናል፡፡

▣ **"መሸጥ"** (BDB 569፤ KB 581፤ *Qal* INFINITIVE CONSTRUCT) የሚለው ቃል በሁለት መልኮች ተገልፆአል፡፡ ለባርነት ለመሸጥ የታፈኑ ሰዎችን ወይም (2) አንድ ሰው ራሱን ለተወሰነ ጊዜ ለአበዳሪ መሸጥ፡፡ ይህ አገላለፅ ከህብረተሰቡ የገለሉትን እና ችግረኞችን የሚያጠቁትን ባለፀጎችን እንደሚኮንን እርግጥ ነው፡፡(ዝ.ከ. ምሳ 14:31፤ 17:5)

እዚህ ላይ "ፃድቅ" የሚለው መጠሪያ የተጠቀሰው ከ"ችግረኛ"(ቁጥር 6)፤ "ድሆች"(ቁጥር 7) እና "ትሁታን" ጋር ጎን ለጎን ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ዓውድ ትርጉም ሊወሰን እንደሚችል አስታውስ) ይህ ማህበረሰባዊ እንጂ መፅሀፍ ቅዱሳዊ እይታ የለውም፡፡ ፃድቅ ሰዎች ከያህዌ እና ከእሱ ህግ ጋር የተሳሰሩ ስለሆነ የአገር ዘመዶቻቸውንም በአግባቡ ይይዛሉ፡፡ በአሞፅ ውስጥ ፃድቅ መሆን ቀጥተኛ እና አግድም እይታ አላቸው፡፡

ይህ ቃል በሆሴ ውስጥ የበለጠ ሃይማኖታዊ ሆኖ ተቀምጧል (መፅሀፍ ቅዱሳዊ ወይም ቀጥተኛ እይታ)፡፡(ዝ.ከ. ሆሴ 2:19፤10:12፤ 14:9) በአቀራረቡ ለ *hesed* (ይህም ማለት የቃል ኪዳን ታማኝነት) ይቀርባል፡፡ ምክንያቱም ይህ የፍርድ ቤት አይነት አቀራረብ ስላለው ምናልባትም ቃሉ በህጋዊ ፍድ ቤት ዳኛውን ለማሳመን አቅም ያነሰውን ተከሳሽ የሚያመለክት ይሆናል፡፡

## ልዩ ርዕስ፡ ጽድቅ

"ጽድቅ" የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ የግድ ተከታታይ የሆነ የግል ጥናት በጽንሰ ሐሳቡ ላይ ማድረግ ያለበት ወሳኝ ርዕስ ነው።

በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ባሕርይ የሚገለጸው "ትክክለኛ" ወይም "ጻድቅ" በሚል ነው። ሜሶፖታሚያዊው ቃል ራሱ የመጣው ከወንዝ ዳር ሸንበቆ ሲሆን፣ የግድግዳና የአጥርን አግድሞሽ ቀጥተኛነት መለኪያ የሚሆን የግንባታ መሣርያ ነው። እግዚአብሔር ቃሉን በዘይቤነት ለራሱ ባሕርይ መጠሪያ እንዲሆን መርጦታል። እሱ ቀጥተኛ የሆነ (የማስመሪያ) ጫፍ ነው፣ በእሱም ሁሉም ነገር የሚመዘንበት። ይህ ጽንሰ ሐሳብ የእግዚአብሔርን ጽድቅ ይገልጻል፣ እንዲሁም ለመፍረድም ሥልጣን እንዳለው።

ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር አምሳል ነው (ዘፍ 1፡26-27፤ 5፡1፣3፤ 9፡6)። የሰው ልጅ የተፈጠረው ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲኖረው ነው። ሁሉም ፍጥረታት የተዘጋጀውና ያለው ለእግዚአብሔር እና ለሰው ልጆች መስተጋብር ተብሎ ነው። እግዚአብሔር ልዕለ ፍጡሩን ይፈልገዋል፣ የሰው ልጅ፣ እንዲያውቀው፣ እንዲወደው፣ እንዲያገለግለው፣ እንዲሁም እሱን እንዲመስል! የሰው ልጅ ታማኝነት ተፈትኗል (ዘፍ 3)፣ እናም ሁለቱ ዋነኛ ጥንዶች ፈተናውን ወድቀዋል። ይህም በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል ያለውን ግንኙነት አበላሽቶታል (ዘፍ 3፤ ሮሜ 5፡12-21)።

እግዚአብሔር ኅብረቱን ለማደስና ለመመለስ ቃል ገብቷል (ዘፍ 3፡15)። ይህንንም ያደረገው በራሱ ፍቃድና በራሱ ልጅ ነው። ሰዎች የተጣሰውን ሊመልሱት አልቻሉም (ሮሜ 1፡18-3፡20)።

ከውድቀት በኋላ፣ የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ርምጃ፣ ለተሐድሶው የኪዳናዊ ጽንሰ-ሐሳብ የተመሠረተው በእሱ ግብዣና በሰው ልጅ የንስሐ፣ የእምነት፣ የመታዘዝ ምላሽ ነው። በውድቀት ምክንያት፣ ሰዎች ተገቢ ድርጊት ለመፈጸም አልቻሉም (ሮሜ 3፡21-31፤ ገላትያ 3)። እግዚአብሔር ራሱ መነሻውን ወስዷል፣ ኪዳን አፍራሽ የሆኑትን የሰው ልጆች ለመመለስ። ይሄንንም ያደረገው

1 ኃጢአተኛውን ሰው በክርስቶስ ሥራ በኩል ጻድቅ አድርጎ <u>ማወጅ</u> (የፍርድ ጽድቅና)

2 <u>በነጻ የተሰጠ</u> የሰው ልጅ ጽድቅ በክርስቶስ ሥራ በኩል (የተሰጠ ጽድቅ)

3 <u>የተሰጠ</u> የሚያድረው መንፈስ ጽድቅን ይፈጥራል (ሥነ ምግባራዊ ጽድቅ) በሰው ልጆች።

4 <u>መመለስ</u> የኤደን ገነት ኅብረት በክርስቶስ የእግዚአብሔርን አምሳል መለሰ (ዘፍ 1፡26-27) በአማኞች (ግንኙነታዊ ጽድቅ)።

ሆኖም፣ እግዚአብሔር ኪዳናዊ ምላሽ ይፈልጋል። እግዚአብሔር አውጇል (በነጻ ሰጥቷል) እናም ይሰጣል፣ የሰው ልጆች ግን <u>የግድ</u> ምላሽ መስጠት አለባቸው እንዲሁም በምላሻቸው መቀጠል

1 ንስሐ

2 እምነት

3 በሕይወት ኑሮ መታዘዝ

4 መጽናት

ጽድቅ፣ ስለዚህ ኪዳናዊ ነው፣ በእግዚአብሔርና በልዕለ ፍጡሩ መካከል ያለ ሁለትዮሽ ድርጊት። እሱም የተመሠረተው በእግዚአብሔር ባሕርይ፣ በክርስቶስ ሥራ፣ በመንፈስ አስቻይነት፣ ይህም እያንዳንዱ ሰው በግሉ እና በቀጣይነት በተገቢው ምላሽ መስጠት ያለበት ነው። ጽንሰ ሐሳቡም "በእምነት መጽደቅ" ይባላል። ጽንሰ ሐሳቡ በወንጌላት ተገልጿል፣ ነገር ግን በእነዚህ ቃልት አይደለም። እሱም በመጀመሪያ የተገለጠው በጳውሎስ ሲሆን እሱም የግሪኩን ቃል "ጽድቅ" ን በተለያየ መልኩ ከ100 ጊዜ በላይ ተጠቅሟል።

ጳውሎስ የሠለጠነ ራቢ እንደ መሆኑ መጠን፣ ዲካዮሱኔ (dikaiosunē) የሚለውን ቃል በዕብራይስጥ አገባቡ SDQ በሴፕቱዋጀንት ጥቅም ላይ የዋለውን፣ ከግሪክ ሥነ ጽሑፍ ሳይሆን። በግሪክ ጽሑፎች ቃሉ የሚያያዘው፣ ለአንዱ የመለኮት ተስፋ በኅብረተሰቡ ዘንድ ለማረጋገጥ ነው። በዕብራይስጥ አግባቡ ዘወትር የሚያያዘው ከኪዳናዊ ቃላት ጋር ነው። ያህዌ ፍትሐዊ፣ ሥነምግባራዊ፣ ግብረገባዊ አምላክ ነው። እሱም ሕዝቦቹ የሱን ባሕርይ እንዲያንጸባርቁ ይሻል። የተቤዡ የሰው ልጅ አዲስ ፍጥረት ሆኗል። ይህ አዲስነት ውጤቱ አዲስ የመልካምነት የሕይወት ስልት ያሳያል (የሮማን ካቶሊክ የጸድቅ ትኩረት)። እስራኤል ቲዎክራሲያዊ (የአምላክ መንግሥት) እንደመሆኑ መጠን በሥጋዊ (የኅብረተሰቡ ደንቦች) እና በተቀደሰው (የእግዚአብሔር ፍቃድ) መካከል እንዲሁም "በጽድቅ" (ከሃይማኖት ጋር በተያያዘ) ግልጽ የሆነ መለያ የለውም። ይህ ልዩነት የሚገለጠው በዕብራይስጥና በግሪክ ቃላት ነው፣ እነርሱም ወደ እንግሊዝኛ ሲተረጎሙ "ፍትሕ" (ከኅብረተሰቡ ጋር በተያያዘ) እንዲሁም "ጽድቅ" (ከሃይማኖት ጋር በተያያዘ)።

ወንጌል (መልካም የምስራች) የኢየሱስ፣ የወደቀው የሰው ልጅ ወደ እግዚአብሔር ኅብረት መመለሱን ነው። የጳውሎስ አያዎ (ፓራዶክስ) የሚሆነው፣ እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል በደልን ማስወገዱ ነው። ይህም ሊገኝ የሚችለው በእግዚአብሔር ፍቅር፣ ምሕረት፣ እና ጸጋ ሲሆን፣ የልጁ ሕይወት፣ ሞት፣ እና ትንሣኤ፤ እንዲሁም የመንፈስ መቃትትና ወደ ወንጌል መሳብ ነው። ጽድቅ የእግዚአብሔር ነጻ ድርጊት ነው፣ ነገር ግን መልካምነትን ሊያመነጭ ይገባል (የአውግስጢኖስ አቋም፣ እሱም የሚያሳየው ሁለቱንም፣ የተሐድሶ አጽንኦት በነጻ ወንጌል ላይ እና የሮማን ካቶሊክ አጽንኦት በተለወጠ ሕይወት በፍቅርና በታማኝነት ላይ ነው)። ለባለ ተሐድሶዎች ቃሉ "የእግዚአብሔር ጽድቅ" ተጨባጭ ባለ መብትነትን ሲያሳይ (ማለትም፣ ኃጢአተኛውን የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ተቀባይነት እንዲያገኝ የማድረግ ሥራ [አቋማዊ ቅድስና])፣ ለካቶሊክ ደግሞ የተሳቢ ባለመብትነት ነው፣ ይህም እግዚአብሔርን የመምሰል ሂደት ነው፣ (ተሞክሯዊ ተራማጅ ቅድስና ነው)። በተጨባጭ ግን ሁለቱም ነው!!

በእኔ አስተያየት መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ ከዘፍ 4-ራዕይ 20 የተመዘገበው እግዚአብሔር የኤደንን ኅብረት እንደሚመልስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔርና በሰው ልጅ ኅብረት በምድራዊ መቼት ይጀምራል፣ (ዘፍ 1-2) እናም መጽሐፍ ቅዱስ በተመሳሳይ መቼት ነው የሚያበቃው (ራዕ 21-22)። የእግዚአብሔር አምሳልና ዓላማ ይመለሳል!

የላይኛውን ማብራሪያ ለማጠቃለል የሚከተሉትን የተመረጡ የአኪ ምንባቦችን የግሪኩ ቃለት ምድብ የሚያመላክቱትን እይ።
1 እግዚአብሔር ጻድቅ ነው (ዘወትር የሚያያዘው እግዚአብሔር እንደ ፈራጅ ነው)
ሀ ሮሜ 3፡26
ለ 2ኛ ተሰሎንቄ 1፡5-6
ሐ 2ኛ ጢሞቲዎስ 4፡8
መ ራዕይ 16፡5
2 ኢየሱስ ጻድቅ ነው
ሀ ሐዋርያት ሥራ 3፡14፤ 7፡52፤ 22፡14 (የመሲሕ ማዕርግ)
ለ ማቴ ዎስ 27፡19
ሐ 1ኛ ዮሐንስ 2፡1፣29፤ 3፡7
3 የእግዚአብሔር ሐሳብ ለፍጥረቱ ጽድቅ ነው
ሀ ሌዋውያን 19፡2
ለ ማቴ ዎስ 5፡48 (ዝ.ከ. 5፡17-20)
4 የእግዚአብሔር ጽድቅን የመስጠትና የመፍጠር አግባብ
ሀ ሮሜ 3፡21-31
ለ ሮሜ 4
ሐ ሮሜ 5፡6-11
መ ገላትያ 3፡6-14
ሠ በእግዚአብሔር የተሰጠ
1 ሮሜ 3፡24፤6፡23
2 1ኛ ቆሮንቶስ 1፡30
3 ኤፌሶን 2፡8-9
ረ በእምነት የሚቀበሉት
1) ሮሜ 1፡17፤3፡22፣26፤ 4፡3፣5፣13፤ 9፡30፤ 10፡4፣6፣10
2) 1ኛ ቆሮንቶስ 5፡21
ሰ በልጁ ሥራ በኩል
1 ሮሜ 5፡21-31
2 2ኛ ቆሮንቶስ 6፡14
3 ፊሊፐስዩስ 2፡6-11
5 የእግዚአብሔር ፍቃድ ተከታዮቹ ጻድቅ እንዲሆኑ ነው
ሀ ማቴዎስ 5፡3-48፤ 7፡24-27
ለ ሮሜ 2፡13፤ 5፡1-5፤ 6፡1-23
ሐ 2ኛ ቆሮንቶስ 6፡14
መ 1ኛ ጢሞቲዎስ 6፡11
ሠ 2ኛ ጢሞቲዎስ 2፡22፤ 3፡16
ረ 1ኛ ዮሐንስ 3፡7
ሰ 1ኛ ጴጥሮስ 2፡24
6 እግዚአብሔር ዓለምን በጽድቅ ይፈርዳል
1 ሐዋ 17፡31
2 2ኛ ጢሞቲዎስ 4፡8

ጽድቅ የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው፣ በክርስቶስ በኩል ለኃጢአተኛው የሰው ልጅ በነጻ የተሰጠ። እሱም
ሀ የእግዚአብሔር ደንብ
ለ የእግዚአብሔር ስጦታ
ሐ የክርስቶስ ድርጊት ነው።

ነገር ግን እሱ ደግሞ ጻድቅ የመሆን ሂደት፣ ያም በጽናት እና በብርታት መያዝ ያለበት ነው፤ አንድ ቀን በክርስቶስ ዳግም ምጽዓት የምንቀዳጀው። ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ኅብረት በደኅንነት ይመለሳል፣ ነገር ግን ሂደቱ በሕይወት ዘመን ሁሉ ፊት ለፊት ይገኛል በሞት ወይም <u>በፓሮሲያ!</u>

እዚህ መልካም ጥቅስ አለ፣ *ከጳውሎስና ጽሑፎቹ መዝገበ ቃላት* የተጠቀሰ አይ ቪ ፒ

“ካልቪን፣ ከሉተር ከፍ ባለ መልኩ አጽንዖት የሚሰጠው ግንኙነታዊ በሆነው የእግዚአብሔር ጽድቅ ገጽታ ላይ ነው። የሉተር አተያይ በእግዚአብሔር ጽድቅ ላይ፣ ከጥፋተኝነት ነጻ መሆንን ገጽታ የያዘ ይመስላል። ካልቪን አጽንዖት የሚሰጠው የእግዚአብሔርን ጽድቅ ለእኛ ያለውን አስደናቂ አፈጣጠር ከግንኙነት ወይም ከተካፋይነት አኳያ ነው” (ገጽ 834)።

እንደ እኔ የአማኝ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት ሦስት ገጽታዎች አሉት።
1 ወንጌል አካል ነው (የምስራቅ ቤተ ክርስቲያንና የካልቪን አጽንዖት)
2 ወንጌል እውነት ነው (የአውግስጢኖስና የሉተር አጽንዖት)
3 ወንጌል የተለወጠ ሕይወት ነው (የካቶሊክ አጽንዖት)

ሁሉም እውነት ናቸው እናም አንድ ላይ መያዝ ይኖርባቸዋል፣ ለጤናማ፣ ትርጉም ላለው፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና። ማንም በጣም አጽንዖት ከሰጠ ወይም ካንኳሰሰ ችግሮች ይፈጠራሉ።

ኢየሱስን መቀበል ይኖርብናል!
ወንጌልን ማመን ይኖርብናል!
ኢየሱስን መምሰል ይኖርብናል!

▣ **"እና ችግረኛውንም ስለ አንድ ጥንድ ጫማ"** ይህ በቀጥታ ሲተረጎም የሚኖረው ትርጉም(1) በጣም ትንሽ በሆነ ዋጋ ሰዎችን መግዛት እና መሸጥ (ዝ.ከ. 8:6) ወይም (2) ለእነዚህ ሀብታም ወንጀለኞች ህጋዊነትን ለመስጠት የሚደረግ ህጋዊ አካሄድ (ይህም ማለት ጫማዎችን መለወጥ ዝ.ከ. ሩት 4:7፤ ሮላንድ ዲቫኡክስ፤ ጥንታዊቷ እስራኤል ጥራዝ 1 ገፅ 169ኝንተመልከት፡፡) NIDOTTE ጥራዝ 1 ገፅ 228 "ችግረኞች፤"፣ "ደሀ" እና "ድህነት "ን በተመለከተ ጠቃሚ የማህበረሰባዊ አስተሳሰብ አረፍተ ነገሮች አሉት፡፡ "ምዕራብያዊያን ድህነትን ከኢኮኖሚ መቀዝቀዝ ጋር አያይዘው ሲያስቡ ANE ድህነትን የሚረዱት የውርደት እና ክብር ትርጉም በመስጠት ነው፡፡ ስለዚህ የመሬት ፣ የኃይል፣ የኢኮኖሚ፣ የጥበቃ እና የማህበረሰብ ተቀባይነት መኖር አንድን ሰው ሀብታም ሲደርጉት የእነዚህ መንስኤዎች አለመኖር ደግሞ አንድን ሰው ደሀ ያደርጉታል፡፡

**2:7**

| | |
|---|---|
| **NASB፤ NKJV** | ***"እስትንፋስ መውሰድ"*** |
| **NRSV፤ TEV** | ***"መረጋገጥ"*** |
| **NJB** | ***"መሰባበር"*** |

ይህ ቃል አተረጓጉወሙን በተመለከተ ብዙ መገለጫዎች አሉት (BDB 983፤ KB 1375፤ *Qal* ACTIVE PARTICIPLE) በ ቁጥር17 ውስጥ (1) NASB እና NKJV የሀብታውን ደስተኛ አለመሆን (መጥፎነት ) ያመለክታል (ይህም ማልት "ለአየር ትንፋሽ ማግኘት (አየር መሳብ)" KB 1375 ወይም ‹" ከፈጣን እስትንፋስ በኋላ" BDB 983 I፤ ለምሳሌ ኢዮብ 7:2፤ መዝ 119:131፤ መክ 1:5) ደሀዎች በኃዘን ጊዜ በጭንቅላታቸው ላይ የሚያስቀምጡት ትንሽ መጠን ያለው አቧራ (ማጋናን) ወይም (2) NRSV ከ በሰብቱ አጀንት እና ከ ሾልጌት ቀጥሎ ይህን ቃል "መረጋገጥ" ብለው ይተረጉሙታል (BDB 983 II፤ ለምሳሌ 8:4፤ መዝ56:2፤ እዝ36:3) ይህም የሚያመለክተው የሀብታሞችን እፍረት እና የደሀውን የበላይነት ነው፡፡ በዚህ ዓውድ "ፃድቁ" "ችግረኛው" "ደሀው" እና "ትሁቱ" የሚያመለክቱት ቋሚ ደሀውን ሳይሆን በመካከለኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ ገንዘብ እንዲበደሩ የተገደዱ እና በዚህም ምክኒያት የገዛ መሬታቸውን ፣ ገቢያቸውን፣ ክብራቸው እና በህብረተሰቡ የነበራቸው ቦታ ያጡ በመካከለኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ ገበሬዎች ወይም ነጋዴዎች ነበሩ፡፡

ስለ ሀብታም ና ደሀ ጥሩ ገለፃ በብሉይ ኪዳን ለማግኘት የ Roland deVaux ጥንታዊዋ እስራኤል የሚለውን ጥራዝ 1 ገፅ 72-74 ተመልከት፡፡

◘

| | |
|---|---|
| **NASB** | ***"የትሁታንም መንገድ ያጣምማሉ"*** |
| **NKJV** | ***"የትሁትን መንገድ ይከለክላሉ"*** |
| **NRSV** | ***"ፍቅር የተሞላውንም ይገፋሉ"*** |
| **TEV** | ***"ደሃውን ከ መንገድ ያስወጣሉ"*** |
| **NJB** | ***"የተጨቆነውን ሰው መብት ይገፋሉ"*** |

ይህ ግስ (BDB 639፤ KB 692፤ *Hiphil* IMPERFECT) በአሞፅ ውስጥ ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል፡፡

1. በ2፡7 እና 5፡12 ውስጥ ይህ ቃል የሚያመለክተው ባለፀጎች ዳኞችን በማጭበርበር (በመግዛት) ህጋዊ የሆነውን የፍርድ አሰጣጥ ስርዓት እንዴት እንዳበላሹት ነው፡፡ (ለምሳሌ ዘፀ 23:6፤ ዘዳ16:19፤ 24:17፤ 27:19፤ 1ኛ ሳሙ 8:3፤ ምሳ 17:23፤ ኢሳ10:2፤ Lam 3:35)
2. በ2፡8 ውስጥ ይህ የሚያመለክተው ከደሀው ላይ በመያዣነት በተወሰደው ልብስ ላይ ባለፀጎች እንደሚተኙበት ነው፡፡ የቃሉ ዋና ትርጉም "ወደጎን መዘርጋት" ወይም "ወደውጭ ማነጠፍ" ነው፡፡ ከላይ ባለው የመጀመሪያ ምሳሌ ዳኞች ለጉቦ እጃቸውን ዘርግተው አውጥተዋል፡፡ በሁለተኛው የደሀውን ልብስ በተመለከተው ምሳሌ ባለፀጋው እንዲጠቀምበት ወይም ምናልባት እዲተኛበት የደሀው ልብ ይነጠፋል፡፡ ይህም ሊያመለክት የሚችለው ጉልሙትና ይዘወተር እንደነበረ ነው፡፡

▣ **"አባትና ልጅ ወደ አንዲት ሴት ይገባሉ"** ሴት (BDB 655) የሚለው ቃል ምንም እንኳን ሃሳቡ የሴተኛ አዳሪነት (የጉልምትና) መለመድን የሚገልፅ ቢሆንም ቃሉ ግን ተለመደውን ሴተኛአዳሪነትን የሚገልፅ አይደለም፡፡ (ዝ.ከ. ዘዳ23:18፤ ታሪካዊ አመጣጡን ለማየት ሆሴ 4:12-14) በተጨማም ደግሞ ማንንም ሳታገባ አንድ ያላገባች ወጣት ደሃ ሴትን "በመሸጥ" በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ባሉ ወንዶች መጠቀሚያ እንድትሆን ማድረግን ሊያመለክት ይችላል፡፡(ዝ.ከ. TEV)፡፡ይህም በ(1) ዘሌ18:8፤ 20:11፤ ዘዳ22:30፤ 27:20 እና በ(2)ዘፀ 21:7-11 ያሉትን ጥቅሶች የሚጣረር ነው፡፡ የጽሑፍ አቀራረብ ደሃ እና ችግረኛን የመበደል ሃሳብ ስላለው ሁለተኛው አማራጭ ምርጥ ምርጫችን ይሆናል፡፡

ሌሎች ብዙ አተረጓገሞችም አሉ፡፡ ምንም እንኳን አጠቃላይ የፅሁፍ አቀራረብ ግልፅ ቢሆንም እነዚህን አተረጓገሞች በተመለከተ አንድ ሰው ስለ አገላለፃቸው እና ስለትክክለኛነታቸው እርግጠኛ መሆን ይከብደዋል፡፡ የሰው ልጆች ለእግዚአብሔር የቀረቡትንም ጨምሮ ሃጥያተኞች እና የእግዚአብሔር ን ህግ የሚተላለፉ ናቸው፡፡ እግዚብሄር ሃጥያትን እና ሃጥያተኞችን በይበልጥም ደግሞ እሱን አውቀው የሚተላለፉትን በቀላሉ አያያቸውም፡፡ (ይህም ማለት ይሁዳን እና እስራኤልን) የዘራነውን እንደምናጭድበት መጠን ሁሉ ያለን ብርሃኑም (ሃይል) ተመሳሳይ መጠን አለው፡፡

▣ **"ቅዱሱንም ስሜን ያረክሱ ዘንድ"** እነዚህ ድረጊቶች በመሰዊያ ቦታዎች (የኢዮርብአም 2ኛ የወርቅ ጥጃ) በቤቴል እና ዳን ባለው ላይ ይገለጣል (ዝ.ከ. ቁ 8)፡፡ ህጋዊነትና ሃይማኖታዊ ጠቀሜታ ያላቸው ይመስላል፣ ነገር ግን ማንም ሊሆን ያለውን ያውቃል፡፡

ይህ ቃላዊ አገላለጽ (BDB 320 III፤ KB 319፤ *Piel* INFINITIVE CONSTRUCT) *Piel* መልክ በብዙ መንገዶች ተገልፀዋል፡፡

1. ግብረ ስጋ ግንኙነትን ማርከስ፣ ዘሌ19:29፤ 21:9፤15

2. የአምልኮ ስርዓቶችን ማርከስ ዘሌ19:8፤ 21:12፤23፤ 22:9፤15
3. እግዚአብሔርን ስም ማርከስ ዘሌ18:21፤ 19:12፤ 20:3፤ 21:6፤ 22:2፤32፤ ኤር 34:16፤ እዝ20:39፤ 36:20-23፤ አሞፅ 2:7

እስራኤላዊያን እናመልከዋለን እና እናገለግለዋለን ብለው የሚናገሩትን ትክክለኛው እግዚአብሔርን፣ እያረከሱት እና ዝናውን እያወረዱት ነበር፡፡ ለግል ጥቅማቸው እና ስጋዊ አምሮታቸው ሲሉ የሙሴን ህግ እና ደንብ ችላ ብለዋል፡፡

አሞፅ (ልክ እንደ ሌሎች ነብያቶች ሁሉ) በሙሴ ህግ ላይ በሚሰሩ ሃጥያቶች ላይ ፍርድ ይሰጥ እንደነበር ግልጽ ነው፡፡

1. 2፡4 "የእግዚአብሔር ን ህግ" እና "ትዕዛዙን" የሚሉት ሃረጎችን የሙሴን ህግ እና ደንብ ለማመልከት
2. 2፡7 ከ ዘሌ18:8፤15፤ 20:11-12 ጋር ያዛምደዋል
3. 2፡8 ከ ዘዳ24:12-13ጋር ያዛምደዋ
4. 2፡9-11 ከ ዘፍ 15:12-21ጋር ያዛምደዋል
5. 2፡11-12 ከ ዘኀ 6 ጋር ያዛምደዋል

## ልዩ ርዕስ፡ ቅዱስ

I. የብሉይ ኪዳን አጠቃቀም
 ሀ. የቃሉ ትርጉም (*kadosh*፤ BDB 872)፡የተረጋገጠ አይደለም ከናናይት ሊሆን ይችላል፡፡ ምናልባትም የዋናው ቃል ክፍል (ይህም ማለት *kds*) ሲተረጎም "መከፋፈል" ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም "ለእግዚአብሔር ስራ መለየት" (ከአህዛብ ባህል ዝ.ከ. ዘዳ7:6፤ 14:2፤21፤ 26:19) ለሚለው ዋና አገላለፅ መሠረት ነው፡፡
 ለ. ቃሉ ርካሽ ነገሮችን ፣ ቦታዎችን ፣ ጊዜዎችን እና ሰዎችን የሚያያይዝ ነው፡፡ በ ዘፀ፤ በዘሌዋዊያን እና ዘዑልቁ ውስጥ ቃሉ የተለመደ ነው፡፡
 ሐ. በነብያት መፅሀፍት (ፅሁፎች) ውስጥ (በዋናነት ኢሳያስ እና ሆሴህ) ውስጥ በፊት የነበረ ትኩረት ግን ያልተሰጠው አሁን ደገሞ ቀዳሚ ተጠቃሽ የሆነ ግላዊ አካል አለው፡፡ ቃሉ የእግዚአብሔር ን ማንነት አመልካች መንገድ (ቃል) ሆኗል (ዝ.ከ. ኢሳ 6፡3)፡፡ እግኢአብሄር ቅዱስ ነው፡፡ ባህሪውን የሚገልፀው ስሙም ቅዱስ ነው፡፡ ህዝቦቹ ለችግረኛው ዓለም ባህሪውን የሚያሳዩ ቅዱሳን ናቸው፡፡(በእምነት የእግዚአብሔር ን እርቅ ከተቀበሉ፡፡)
 መ. የእግዚአብሔር ምረት እና ፍቅር መፅሀፍ ቅሳዊ ሃሳብ ከሆኑት እርቅ፣ ፍርድ እና አስፈላጊ ከሆኑት የእግዚአብሔር ባህሪያት የማይነጣጠል ነው፡፡ በዚህ ውስጥ እግዚአብሔር ቅዱስ ባልሆነው፣ በወደቀው እና በአመፀኛው የሰው ዘር ማንነት ላይ ውጥረት ውስጥ መሆኑን እናያለን፡፡በእግዚአብሔር "መሀሪነት" እና በእግዚአብሔር " ቅዱስና" መካከል ያለውን በጣም የሚስብ ግንኙነት በ Robert B Girdlestone፤ *Synonyms of the Old Testament*፤ ገፅ 112-113 ውስጥ ይገኛል፡፡

II. አዲስ ኪዳን
 ሀ. የአዲስ ኪዳን ፀሀፊዎች የዕብራይስጥ አስተሳሰብ ያላቸው ናቸው (ከሉቃስ በስተቀር )፡፡ ነገር ግን በ ግሪክ ቋንቃ (ይህም ማለት ተፅዕኖ ነበረባቸው፡፡) ቃላቶቻቸውን የግሪክ ስነፁሁፍ አስተሳሰብ ወይም ሃይማኖት ሳይሆን የተቆጣጠራቸው የብሉህ ኪዳን የግሪክ አተረጓገም ነው፡፡
 ለ. ኢየሱስ ቅዱስ ነው ከእግዚአብሔር የሆነ አምላክ ነው (ዝ.ከ. ሉቃ 1:35፤ 4:34፤ የሐዋ 3:14፤ 4:27፤30)፡፡ እየሱስ ቅዱስ እና ፃድቅ የሆነ ነው(ዝ.ከ. የሐዋ 3:14፤ 22:14)፡፡ ኢየሱስ ቅዱስ ነው ምክንያቱም ኃጥያት ስለሌለበት (ዝ.ከ. ዮሐ 8:46፤2ኛቆሮ 5:21፤ ዕብ 4:15፤ 7:26፤ 1ኛጴጥ 1:19፤ 2:22፤ 1 ዮሐ 3:5)፡፡
 ሐ. እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ ልጆቹም ቅዱስ መሆን ይገባቸዋል (ዝ.ከ. ዘሌ11:44-45፤ 19:2፤ 20:7፤26፤ ማቴ 5:48፤ 1Pet 1:16)፡፡ ኢየሱስ ቅዱስ ስለሆነ እሱን ተከታዮችም ቅዱስ መሆን ይገባቸዋል (ዝ.ከ. ሮሜ 8:28-29፤ 2ኛቆሮ 3:18፤ ገላ 4:19፤ Eph 1:4፤ 1ኛ ተሰ 3:13፤ 4:3፤ 1ኛጴጥ 1:15)፡፡ ክርስቲያኖች የዳኑት ክርስቶስን በመምሰል እንዲያገለግሉ ነው፡፡

**2:8 "በመሰዊያውም ሁሉ አጠገብ ለመያዣነት በተወሰደው ልብስ ላይ ይተኛሉ"** *ሀብታሞች የደሀውን*
የመተኛ ልብስ እንደ መያዣነት ይወሰዱና (በዘፀ 22:26-27፤ ዘዳ24:12-13 ውስጥ የተከላከለውን) የራሳቸው ያደርጉት ነበር፡፡(Roland deVaux፤ *Ancient Israel*፤ ጥንታዊቷ እስራኤል ጥራዝ ገፅ 171፣ዝ.ከ. ዘፅ 21:7፤26-28፤ ዘሌ 25:39-40፤ ዘዳ 24:10-13፤17፤ ምሳ 20:16፤ 27:13) ሊያመለክት የሚችለው በቁጥር 7 ላይ የተጠቀሰውን ልቅ ጉልምትናን (ሴተኛ አዳሪነትን) ወይም ደግሞ ከዘር ማፊያ ሃሰተኛ አምልኮት ጋር የተያያዘን ርኩሰት ያለበትን ምግብ ነው፡፡

"*መሠዊውም ሁሉ*፤" የሚለው ሃረግ በእያንዳንዱ ህብረተሰብ መስዋዕት የሚቀርብላቸው የተለመዱት የብልፅግና ሐሰተኛ አማልክት ለነበሩ በአል (ወንዱ) እና አስታሮት (ሴቷ) ይደረግላቸው ነበረውን ጣኦታዊ አምልኮ ያሳያል፡፡ ያህዌ የነበረው አንድ መሰዊያ ብቻ ነበር፡፡(ይህም፣ማሶሬቲኩ Moriah) ኢዮርብዓም (Jeroboam 1) የእሱን ሰዎች ለፊሽታ ቀናት ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይመለሱ በቤቴል እና በዳን ሁለት መሰዊያ ቦታዎችን ሰርቶ ነበር፡፡

▣ **"በአምላካቸውም ቤት ውስጥ በካሳ የተወሰደውን ወይን ጠጅ ይጠጣሉ፡፡"** ሊያስኬድ የሚችሉ ሁለት አተረጓገሞች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ (1) በ ዳን እና በቤቴል የባዕድ አምልኮ ቦታዎች ውስጥ ሃብታሞች ከድሃው በሚመዘበር ገቢ እየተመረዙ ነበር፡፡ (2) ከባዕድ አምልኮ ቤቶች የሚሰበሰበው ግብር የመጠጥ እና የግልሙትናን ልምድን አስፋፍቷል፡፡የተወሰኑ አተረጓገሞች ኤሎሂምን እንደ "ሃሰተኛ አማልክቶቻቸው" ወይም "ሃሰተኛ አምላካቸው" ብለው ይተረጉሙታል፡፡ ነገር ግን ይዘቱ የሚጠቁመን ያህዌ ለማመልከት እንደሆነ ነው (NASB፤ NRSV፤ TEV፤ JPSOA፤ NET)፡፡ ልዩ ርዕስ፡- የጣኦት ስም በ 1፡2 ላይ ተመልከት

## አሞፅ: 2:9-16

**9 እኔ ግን ቁመቱ እንደ ዝግባ ቁመት፥ ብርታቱም እንደ ኮምበል ዛፍ የነበረውን**
**አሞራዊውን ከፊታቸው አጠፋሁ ፍሬውንም ከላዩ፥ *ሥሩንም* ከታቹ አጠፋሁ።**
**10 የአሞራዊውንም ምድር ትወርሱ ዘንድ ከግብጽ ምድር አወጣኋችሁ፥**
**በምድረ በዳም አርባ ዓመት መራኋችሁ። 11 ከወንድ ልጆቻችሁም ነቢያትን፥**
**ከጕበዛዝቶቻችሁም ናዝራውያንን አስነሣሁ እናንተ የእስራኤል ልጆች ሆይ፥**
**ይህ እንደዚህ አይደለምን? ይላል እግዚአብሔር፦ 12 እናንተ ግን ናዝራውያኑን**
**የወይን ጠጅ አጠጣችኋቸው ነቢያቱንም። ትንቢትን አትናገሩ ብላችሁ አዘዛችኋቸው።**
**13 እነሆ፥ ነዶ የተሞላች ሰረገላ እንደምትደቀድቅ እንዲሁ እደቀድቃችኋለሁ።**
**14 ከርዋጪም ሽሽት ይጠፋል፥ ብርቱውም በብርታቱ አይበረታም፥ ኃያሉም ነፍሱን አያድንም**
**15 ቀስተኛውም አይቆምም፥ ፈጣኑም አይድንም፥ ፈረሰኛውም ነፍሱን አያድንም**
**16 በኃያላኑም መካከል ልበ ሙሉው በዚያ ቀን ዕራቁቱን ሆኖ ይሸሻል፥ ይላል እግዚአብሔር**

**2:9-12** ይህ የእስራኤልን የፍርድ ሂደት ያስጀመረ የእግዚአብሔር ን ታሪካዊ የክብር ስራ የያዘ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ህዝብ የእግዚአብሔር ን ህግጋት ሲጥስ አዲስ ነገር አልነበረም እንዲያውም ይህ መተላለፋቸውን ቀጥለዋል፡፡ (ዝ.ከ. ነህ 9፤ የሐዋ 7)

**2:9 "አሞራዊውን ከፊታቸው አጠፋሁ"** ይህ ያህዌ ከህዝቡ ጎን ሆኖ የሚዋጋ መሆኑን የሚመያለክተው "ቅዱስ ጦርነት" የሚባለውን ቃል ነው፡፡ (FIRST PERSON SINGULAR PRONOUN በቁጥር 9፣10፣13 ውስጥ አስተውል) ድሉ የእሱ ነበር፡፡ (ለምሳሌ"ተርቦች፤"ዘፀ 23:28፤ ዘዳ7:20፤ ኢያ24:12 "የበረዶ ድንጋይ" (ዮሐ 10:11)

## ልዩ ርዕስ፡ አሞራዊ

"አሞራዊ" የሚለው ቃል በሶስት መልኮች ተገልፀዋል፡፡

1. 1 ብዙ ከሆኑት አገር በቀል የከነዓን ነገዶች አንዱ ነው፡፡ (ለምሳሌ ዘፍ 10:16፤ 15:18-21፤ ዘፀ 3:17፤ ኢያ 24:11፤ ዕዝራ 9:1፤ ነህ 9:8[ዘላን ነገዶች ከ አካዲያን ፅሑፍ])
2. በ ምዕራብ ባቢሎን የሚገኙ ሰዎች አጠቃላይ መጠሪያ ነው፡፡ (ዝ.ከ. v 10፤ ዘፍ 15:16፤ መሳ 6:10፤ 2ኛ ነገ 21:11፤ እዝ16:3፤ በተጨማሪም ከ አሶራዊያን እናባቢሎናዊያን ፅሁፎች)
3. ዝቅተኛ ቦታዎችን ከያዙት ከንአናዊያን በተቀራኒ በከፍታ ቦታዎች ሚኖሩ ነዋሪዎች(ዝ.ከ. ዘዳ
4. 1:7፤19፤20፤ 3:2)
5. 4 ሁለቱም ካናናይት እና አሞራዊው የፍልስጤምን/ከነአንን የአንድ ሃገር ነገዶች ለማመልከት የሚጠቅሙ ናቸው፡፡

▣ **"ቁመቱ እንደዝግባ"** ይህ በቀላሉ ዛፎችን በመጠቀም ኃይልን (BDB 147) መቅረፅ (ዝግባ ወደ ላይ እስከ 100ሜ ሊያድግ ይችላል፡፡) )ወይም የአንዳንድ የአሞራዊያንን ቁመት በቀጥታ ሊያመለክት ይችላል፡፡ ደግሞ እንደ የባሳን ኦግ እና የኬብሮን አናኪም (ዝ.ከ. ዘኁ 13:28፤ 33፤ ዘዳ 1:28፤ 9:2፤ ኢያ 11:21-22)፡፡

▣ **"ፍሬውንም ከላዩ *ሥሩንም* ከታቹ አጠፋለሁ"** ይህ የአሞራዊያንን ሙሉ ለሙሉ መጥፋትን የሚያመለክት ዘይቤ ነው፡፡ ቁጥር 9-10 መውጣትንና እና መውረስን ያመለክታ፡፡

**2:10 "ከግብፅ ምድር አወጣኃችሁ"** ከግብፅ የመውጣታቸው ጉዳይ ለአብርሃም ቀድሞየተነገረ ነበር፡፡ (ዝ.ከ. ዘፍ 15:12-21) እንደዚህ ዓይነቱ የቅደሙት አባቶች ከአምላክ ጋር የሚያደርጉት ልዩ ግንኙነት አጠቃለይ ህዝቡ የሚያምኑበት ጉዳይ እንደነበር በዘፀ 19-20 ውስጥ አረጋግጠዋል፡፡ ነገር ግን የ ያህዌን መልካምነት በመተው ህዝቡ በአጠቃላ ፊቱን አዞረ (ዝ.ከ. ሆሴ13:4-6)፡፡ እስራኤል ከሌሎች ህዝቦች የበለጠ መንፈሳዊ ብርሃን በርቶላት ስለነበር ኃላፊነቱ ሁሉ የሷ ነበር (ዝ.ከ. ሉቃ 12:48) 12፡48)፡፡

▣ **"በምድረበዳም አርባ አመት መራኃችሁ"** ይህ የምድረበዳውን አስገራሚ ጊዜ የሚያመለክት ነው፡፡ በብሉህ ኪዳን ውስጥ 40 "አርባ" የሚለው ቃል የተጠጋጋ ቁጥር ነው፡፡ እዚህ ላይ ይህ የሚያመለክተው ከቃዴስ በርኔ ወደ ተስፋይቱ ምድር (በዮርዳኖስ በኩል) ተደረገውን ሰላሳ አመታት የፈጀ ጉዞን ነው፡፡

▣ **"የአሞራዊውንም ምድር ትወርሱ ዘንድ"** ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር በዘፍ15፡12-21 ውስጥ ለአብርሃም የገባወ ቃልኪዳን ነው፡፡ "አሞራዊው" የሚለው ቃል የሚያመለክተው በቁጥር 16 ውስጥ ሁሉንም ከነዓንዊያን እና በቁጥ 21 ውስጥ ደግሞ ብዙ ከሆኑት ያንድ አገር ነገዶች አንዱን ነው፡፡ በቁጥ 9 ያለውን ማስታወሻ ተመልከት፡፡

**2:11-12 "ከወንድ ልጆቻችሁም ነብያቶችን ... ናዝራዊያንን"** እግዚአብሔር እንደነዚህ ያሉ ልዩ መንፈሳዊ መሪዎች በመምረጡ እግዚአብሔር ለእስራኤል ያለውን ልዩ ፍቅር አሳይቷል፡፡ ነገር ግን እስራኤል እነዚህን ወንድ ልጆች (ሴትንም ሊሆን ይችላል፣ ዝ.ከ. ዘኁ 6:2) ኃጥያት እንደሰሩ እድርጋለች (ቁት 12)፡፡ እነሱም የእግዚአብሔር ስጦቻዎች ነበሩ ነገር ግን የእግዚአብሔር ህዝቦች የተሰጣቸውን ስጦታ አባክነዋል፡፡ "ናዝራውያንን" በዘኁ 6 ውስጥ ተገልፀዋል፡፡ ናዝራውያን ወንድ ወይም ሴት ሊሆኑ ይችላሉ (ዝ.ከ. ቁ 2)፡፡ የእነዚህ ሰዎች መጠራት እንዴት መቀጠል እንዳለበት የሚያሳዩ ብዙ ልዩ መመሪያዎች ነበሩ፡፡

1. የማንኛውም የወይን ተክል ምርት መመገብ አይችሉም ቁ ከ3-4

2. ፀጉሩ (ፀጉሯ) መቆረጥ የለበትም ቁ 5
3. የሞተን ሰው አካል መንካ አይችሉም (ይህም ማለት የተወዳጅ ቤተሰባቸወን የቀብር ስርዓት) ቁ ከ 6-7

ይህ ልዩ ቃልኪዳን (ጊዜያዊ ([ለምሳሌ፤ዘኀ 6:13-20፤ የሐዋ 18:18፤ 21:23] ወይም ለህይወት ዘመን ([መሳ 13:7፤ 1ኛ ሳሙ 1:1፤Luke 7:33]) ካህን ወይም ሌዋዊ ያልሆኑ ሰዎች እራሳቸውን በልዩ ስሜት ለ ያህዌ ለማስገዛት የሚጠቀሙበት መንገድ ነበር፡፡ የወንዶች የበላይነት በነገሰባት ጥንታዊቷ እስራኤል የተወሰኑ ሴት ናዝራዊያን (ነብያት) እንዲኖሩ ተፈቅዶ ነበር፡፡ ለጥሩ የተብራ ገለጻ Roland deVaux፤፣ ጥንታዊቷ እስራኤል ጥራዝ 2፤ ገፅ 466-467 ተመልከት

**2:11** “ይህ እንደዚህ አይደለምን” እግዚአብሔር የወቀሳ ቃሎቹን እውነትነት እንዲያረጋግጡለት እየፈተናቸው ነው፡፡ ነገር ግን በተጨማሪ ይህ ከአምላካቸው የተላከ ሀዘን የተሞላበት መልዕክት ነው፡፡ “የእስራኤል ልጆች” የሚለው ሀረግ የአብርሃም ኪዳን እንዳለው አመልካች ነው፡፡ እግዚአብሔር አሁንም ቢሆን ህዝቡን ይወዳል ለህዝቡም ይጠነቀቃል፡፡ (የእግዚአብሔር እውነተኛ ህዝቦች የሱን ባህሪ ያንፀባርቃሉ፡፡)

▣ ***“ጌታን ማወጅ”*** ይህ ለእግዚአብሔር መገለፅ ልዩ ሃረግ ነው(ዝ.ከ. 2:11፤ 16፤ 3:10፤13፤15፤ 4:1፤5-6፤ 8-11፤ 6:6፤ 14፤ 9:7-8፤12፤13)

▣ ***“ጌታን ማወጅ”*** ይህ ለእግዚአብሔር መገለፅ ልዩ ሃረግ ነው(ዝ.ከ. 2:11፤ 16፤ 3:10፤13፤15፤ 4:1፤5-6፤ 8-11፤ 6:6፤ 14፤ 9:7-8፤12፤13)

**2:13** ይህን ቁጥር ሁለት ዓይነት መንገዶች መረዳት እንችላለን፡፡

1. ያህዌ በእዝቦቹ ሃጥያት ልክ እንደተጫነች ሰረገላ እንደተ በሳጨ ያመለክታል (ከአረብ ምንጭ ዝ.ከ. ኢሳ43:24፤ እና በ NASB፤ NKJV፤ NET፤ NIV፤ REB አተረጓጎም)፡፡
2. ያህዌ እዝቦቹ “ወደታች መጫን” ያመለክታል(ይህም ማለት በመፍረዱ)(ከአረብ ምንጭ ዝ.ከ. ኢሳ28:27-28፤እና በ NRSV፤ TEV፤ NJB አተረጓገም ወይም “በቀስታ” JPSOA)፡፡

ልዩነቶቹ የሚዛመዱት ግስ በተገኘበት ስር ቃል መሰረት ነው (BDB 734፤ KB 802፤ *Hiphil* PERFECT and *Hiphil* IMPERFECT) በዚህ ሁኔታ እርግጠኛ መሆን አስቸጋሪ ነው፡፡

The UBS፤ *A Translator's Handbook on the Book of Amos* የሚመከረው በ#2ኛውን አማራጭ አተረጓገም ነው፡- የእስራኤል ህዝብም ልክ እንደተጫነ ሰረገላ በእግዚያብሄረ ፍርድ ኢቃስተዋልና ገፅ 55-56 2፡16፡፡

**2:14-16** ይህ የእስራኤላዊያን ጦር ያለ ምክንያት ከ አሶራዊያንns የሚያፈገፍግ መሆኑን ነው፡፡ ያህዌ በ ዘፀ እና Conquest ከእነሱ ጋር የነበረ ሲሆን አሁን ግን የእሱ መገኘት ለነፃነት ሳይሆን ለፍርድ ነበር፡፡ እሱ የእስራኤልን ምርጥ ወታደሮች ልቦና በፍርሃት እና ጥርጣሬ መቷቸዋል፡፡ ይህም የ“ቅዱስ ጦርነት”ትክክለኛ ግልባጭ ነው፡፡

**2:16** “ተዋጊዎችም ዕራቁታቸውን ሆነው ይሸሻሉ” ይህ የሚያመለክተው ሁሉንም መሳሪያ እና አላስፈላጊ ልብሶችን መወርወር ሲሆን ይህ ደግሞ ወታደሮች በበለጠ ፍጥነት እንዲሸሹ ያደርጋቸው ነበር

▣ ***“በዚያ ቀን”***፣ ይህ “በዚያ ቀን” ወይም “በዚያኛው ቀን”፣ የሚለው ሀረግ የ18ኛው ክፍለ ዘመን ነቢዮች ለፍርድ እና ለተሃድሶ የእግዚአብሔርን ጉብኝት(መገኘት)ለመግለፅ የሚጠቀሙበት ነበር፡፡

| **ሆሴዕ** | | **አሞጽ** | | | **ሚክያስ** | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| <u>አዎነታዊ አሉታዊ</u> | <u>አዎነታዊ አሉታዊ</u> | | <u>አዎነታዊ አሉታዊ</u> | | | |
| 1:11 | 1:5 | | 1:14(2) | | 2:4 | |
| | 2:3 | | 2:16 | | | 3:6 |
| 2:15 | | | 3:14 | 4:6 | | |
| 2:16 | | | 3:18(2) | | 5:10 | |
| 2:21 | | | 3:20 | | | 7:4 |
| | 5:9 | | 6:3 | 7:11(2) | | |
| | 7:5 | | 8:3 | 7:12 | | |
| | 9:5 | | 8:9(2) | | | |
| | 10:14 | | 8:10 | | | |
| | | 9:11 | 8:13 | | | |

ይህ ምሳሌ በነቢያት ዘንድ የተለመደ ነው፡፡ እግዚአብሔር ከጊዜ በኋላ በኃተጢአት ድርጊት ላይ ምላሽ ይሰጣል፡፡ ግን በተጨማሪም ለባቸውንና ድረጊታቸውን ለሚቀይሩ የንስሀንና የይቅርታን ቀን ይሰጣቸዋል! የእግዚአብሔር የማዳን እና የማደስ ዓለማ ይፈጸማል! ባህሪይውን የሚያንጸባርቁ ህዝቦች ይኖሩታል፡፡ የፍጥረት አላማ (ከእግዚአብሔር እና ከሰው ልጅ መሀከል ያለው ህብረት) ይፈጸማል፡፡

| | |
|---|---|
| **NASB** | **“ይላል ጌታ”** |
| **NKJV፣ NRSV** | **“ጌታ ይላል”** |
| **TEV** | **“ጌታ ተናግሯል”** |
| **NJB** | **“ያህዌ ይላል”** |

ይህ ቃል በቃል የሆነ ክፍል (1:3-2:16) “ይላል” የሚለውን ቃል ይደጋግማል (BDB 55፣ KB 65፣ *Qal* PERFECT)፣ እነዚህ ፍርዶች ከአሞጽ ሳይሆኑ ከያህዌ መሆናቸውን ያሳያል፡፡

| **አስፈላጊ** | **ማጠቃለያ** |
|---|---|
| 1:3 | 1:5 |
| 1:6 | 1:8 |
| 1:9 | |
| 1:11 | |
| 1:13 | 1:15 |
| 2:1 | 2:3 |
| 2:4 | |
| 2:6 | |

የ (BDB 610 እና 217 CONSTRUCT) ትይዩ መልክ በ 2:11 እና 2:16 ውስጥ ነው (ለምሳሌ፤ 3:13፤ 4:3፤ 6:8፣14፤ 8:3፣9፣11) አሞጽ ያህዌ ራሱ ግልጽ የሆነ መልእክት እነደተናገረው እና እሱም በትክክል እነዳስተላለፈ ያምናል፡፡

# አሞፅ 3

## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|
| የነቢያት መልክት ሥልጣን | የእስራኤል ኃጢአተኝነትና የእግዚአብሔር ቅጣት (3:1-6:14) | የእግዚአብሔር ፍረድ በእስራኤል ላይ (2:6-3:2) | እስራኤል ማስጠንቀቂያና መስፈራሪያ ተሰጣት (3:1-6:14) |
| | የመመረጥ እድሎች ትልቅ ኃላፊነትን ፈጠሩ | | መመረጥና ቅጣት |
| 3:1-8 | 3:1-2 | | 3:1-2 |
| | | የነቢዩ ተግባር | ትንቢታዊ ጥሪን መከላከል አይቻልም |
| | 3:3-8 | 3:3-8 | 3:3-8 |
| | | | 3:7-8 |
| የእስራኤል ኃጢአት ቅጣት (3:9-4:5) | | የሰማርያ ክፉ ቀን | ሰማርያ ከፋትዋ የተነሳ ትተፋለች |
| 3:9-10 | 3:9-11 | 3:9-11 | 3:9-11 |
| | | 3:10-11 | |
| 3:11-15 | | | |
| | 3:12-15 | 3:12-4:3 | 3:12 |
| | | | በለቤቴልና ደማስቆ ድሎት ላይ |
| | | | 3:13-15 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ vii ተመልከት)**

*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

**የአግባብ ምልከታ**

ሀ እስራኤል በአሞጽ ምዕራፍ 1-2 በተዘረዘሩት የአሞጽ የግሳጼ ቃላቶች በጣም የተስማሙ ሲሆኑ ፤ በህዝባቸው ላይ በምዕራፍ 2፡6-6፡14 ወይም 2፡6-9፡14 ለመቀበል ግን የተዘጋጁ አይመስልም፡፡

ለ የዚህ ምዕራፍ ታሪካዊ ዳራ በዘዳግም 27-29 የሚገኘው የኪዳን ማደስ ስነ-ሰርዓት ነው፡፡ በምዕራፍ 4፡6-11 እናንተ ግን ወደ እኔ አልተመለሳችሁም የሚል ሀረግ በተጠቀሙ ቁጥር እስራኤል ላይ በመጡት አምስት መርገሞች ውስጥ ይህ በግልጽ ይታያል፡፡

## የቃልና የሀረግ ጥናት

**አሞጽ 3፡1-8**

**1 የእስራኤል ልጆች ሆይ፥ እግዚአብሔር በእናንተ፥ ከግብጽ ምድር ባወጣሁት ወገን ሁሉ ላይ የተናገረውን ይህን ቃል ስሙ**

**እንዲህም ብሎአል። እኔ ከምድር ወገን ሁሉ እናንተን ብቻችሁን አውቄአችኋለሁ**
**ስለዚህ ስለ ኃጢአታችሁ ሁሉ እበቀላችኋለሁ።**
**3 በውኑ ሁለት ሰዎች ሳይስማሙ በአንድነት ይሄዳሉን?**
**4 ወይስ አንበሳ የሚነጥቀው ነገር ሳያገኝ በጫካ ውስጥ ያገሣልን?**
**ወይስ የአንበሳ ደቦል አንዳች ሳይዝ በመደቡ ሆኖ ይጮኻልን?**
**5 ወይስ ወፍ፥ አጥማጅ ከሌለው፥ በምድር ላይ በወጥመድ ይያዛልን?**
**ወይስ ወስፈንጠር አንዳች ሳይዝ ከምድር ይፈነጠራልን?**
**6ወይስ በከተማ ውስጥ መለከት ሲነፋ ሕዝቡ አይፈራምን?**
**ወይስ ክፉ ነገር በከተማ ላይ የመጣ እንደ ሆነ ያደረገው እግዚአብሔር አይደለምን?**
**7በእውነት ጌታ እግዚአብሔር ምሥጢሩን ለባሪያዎቹ ለነቢያት ካልነገረ በቀር ምንም አያደርግም።**
**8 አንበሳው አገሣ የማይፈራ ማን ነው? ጌታ እግዚአብሔር ተናገረ ትንቢት የማይናገር ማን ነው?**

**3፡ 1-15፡** የምዕራፍ አራት አቀማመጥን አስተውል።

1. አሞጽ በእስራል ቤት ላይ ሲናገር ቁ 1
2. ያህዌ/እግዚአብሔር ለህዝቡ ሲናገር ቁ2
3. አሞጽ ንግግራዊ ጥያቄዎችን ሲጠይቅና መደምደሚያ ሲያደርግ ቁ 3-8
4. ያህዌ ሲናገር ቁ 9-15

**3፡1-23** “UBS A translators handbook on the Book of Amos” ተባለው መጽሐፍ የምዕራፍ 1-2 የሚደመድም መቋጫ ምዕራፍ አድርጎ ይወስዳል። ይሁን እንጂ የትኛውም ዘመናዊ የእንግሊዝኛ ትርጉም ይህንን አቅጣጫ አይከተልም፡፡

**3፡1 “ስማ”** ይህ “ሽማ” ከሚለው የዕብራውያን ግሥ ሲሆን ይህ ማለት እንደምናደርግ መስማት ማለት ነው። (ዘዳ 5፡1፤ 6፡4) እግዚአብሔርን መታዘዝን ይይዛል።(1፡13፤ 4፡11፤5፡1፤8፡4)። የኪዳን ጥቅሞችና መመዘኛዎች አሉ፡፡

▣ **“የእስራኤል ልጆች ሆይ”** እግዚአብሔር በእናንተ የተናገረውን በመላው ቤተሰብ ላይ “አሞጽ አስቀድሞ በእስራኤል ዞሪያ ይሁዳን ጨምሮ በመገሰጽ እስራኤልን ይገስጻል።

| | |
|---|---|
| **NRSB** | **“የእስራኤል ልጆች”** |
| **NKJV** | **“የእስራኤል ልጆች ሆይ”** |
| **NRSV** | **“የእስራኤል ህዝብ ሆይ”** |
| **TEV** | **“ህዝብ ሁሉ”** |

በዚህ ሀረግ ውስጥ ዓላማ ያለው ማደናበር አለ። በአንድ በኩል ሁሉንም የእስራኤል ነገዶች የሚያመለክት ሲሆን በሌላ በኩል በ922 ዓ ዓ በኢዮርባአም ቀዳማዊ ጊዜ የተገነጠሉት በሰሜኑ የሚገኙን አስሩ ጐሳዎችን ይመለከታል። ቁጥር 2 በግልጽ ሁሉንም የያዕቆብ ልጆችን የሚያጠቃልል ነው።

▣ **“በወገኑ ሁሉ ላይ”** የዘመኑ መምዕራባውያን ብሉህ ኪዳንን መረዳት ያልቻሉበት አንዱ ምክንያት ምዕራባውያን በግለሰብ ሙብት ላይ ሲያተኩሩ መጽሐፍ ቅዱስ ግን በጅምላ ላይ ማተኮሩ ነው። የጥንት ሰዎች አብረው ኖረው አብረው ነበር የሞቱት። ለማህበራዊ ኑሮ በመልካም ኖረዋል።

የዚህ የወል ስሜት ለዘመናዊ ሰው መረዳት ይከብደዋል። ይህ የወል ኃጢአትና ጥፋተኛነት ስሜትን ያጠቃልላል። ግን የወል ጽድቅን አያጠቃልልም። ጽድቅ የእያንዳንዱ የግል እምነት፣ የኑዛዜ፣ መታዘዝና አምልኮ ጉዳይ ነበር። የእግዚአብሔር ፍርድ ኃጢአተኛውንም ሆነ በጻድቁ ህዝብን በሙሉ ነክቷል። ይህ ጽንሰ ሀሳብ ወደ ዘመናችን ሲናመጣው የሰው ልጆች ከእግዚአብሔር ጋር ስላላቸው የግል ግንኙነት የሚጠየቁበትና የህበረተሰባቸውን ጥፋት የሚካፈሉ መሆናቸውን ለመረዳት ይጠይቃል። ኃጢአት ማድረግንም አለማድረግንም ያጠቃልላል። ኃጢአተኞችን ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ ቤሔራዊና ጊዜያዊ ፍርዶች መኖራቸውን ያሳያል።(ዘዳ 27-29)

▣ **“ከግብጽ ምድር ባወጣቸው”** ግሡ “hiphil” ፍጹም ማለት ነው። የዘጸአት ክስተተት የጀመረው በአይውዳዊያን ብሔራዊ ልምምድ ነበር።(2፡10፤ 9፡7) እግዚአብሔር ታማኝ ነበር። ግን ይህ በቀጣይነት ባለው የእስራኤልና የይሁዳ ልጆች አለመታመን በተዛማጅ ነበር። “ወገን በሙሉ” ነህሚያ 9፤ ሐዋ ሥ 7)

**3፡2 “እኔ ከምድር ወገን ሁሉ እናንተን ብቻችሁን መርጫችኃለሁ።”** ይህ እግዚአብሔር የአብርሐም ዘሮችን በሌዩ ምርጫ ለልዩ አገልግሎት መምረጣቸውን ያሳያል። (ዘፍ 12፡1-3፤ 18፡18፡ ዘፀ 19፡5-6፤ ዘዳ 7፡6-8፤ ሆሴዕ 2፡20) ይህ ለህዝቦች ሁሉ ወንገልን ማዳረስ ያጠቃልላል። ሁሉም የሰው ልጆች በእግዚአብሔር ምስል የተፈጠሩ ከሆነ(ዘፍ 1፡26-27) እና ዘፍ 3፡15 የመዋጀታቸው የተስፋ ቃል ከሆነ የአብርሐም ጥሪ ሁሉን የሰው ልጆች ወደ እግዚአብሕር ማምጣት ነው።

የተመረጠ የሚለው ቃል ትርጉሙ የታወቀ መሆኑንና ግላዊ ግንኙነት የሚያሳይ ነው።(ዘፍ 4፡1፤ 29፡5፤ ዘፀ 1፡8፤ ዘዳ 11፡28፤ 1ነገ 8፡39፤ መዝ 139፡4፤ ሆሴዕ 5፡3) ይህ እግዚአብሔር ከቃሉ ጋር የቀረበ ግንኙነት (ዘዳ 34፡10)ኃጢያታቸው በጣም አስፀያፊ ያደርጋል። ጌታ እግዚአብሔር የመረጣቸው የዕውቀት ማስተላለፊያ ቧንቧ ሊያደርጋቸው የበረከትና የመዳን ለአዳም ወንድና ሴት ልጆች ሁሉ ነበር። እስራኤል ግን ልዩ ጥሪዋን፤ ግንኙነቷንና ዕውቀቷን እንደ ልዩ መጠቀሚያ አደረገች፡፡

▣ **“ስለዚህ ስለ ኃጢአታችሁ ሁሉ እበቀላችኋለሁ” ይህ ቃል ስለ ኃጢአታችሁ** (BDB 730) በአሞጽ መጽሐፍ ላይ በዚህ ቦታ ብቻ ነው ጥቅም ላይ የዋለው፤ ግን በብዛት በሆሴዕ ውስጥ በብዛት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡(ዝ.ከ. 4፡8፣ 5፡5፣ 7፡1፣ 8፡13፣ 9፡7፣9፣ 10፡10፣ 12፡8፣ 13፡12፣ 14፡1፣2) እና ሁለት ዚዜ በሚክያስ(ዝ.ከ. 7፡18፣19)፡፡ በምእራፍ አንድ እና ሁለት ላይ በደል፤ መተላለፍ ወይንም ስለ ኃጢአት ቅጣት ተብሏል፡፡ (ለምሳሌ

“መተላለፍ” BDB 833) ለ ኃጢአት ጥቅም ላይ ውሏል በሰው ልጅ ውድቀት ላይ ትኩረት ያደረገ፡፡በምእራፍ ሶስት ውስጥ የክፋት ዋጋ ነው(ለምሳሌ የኃጢአት ቅጣት) እነዚያ አጽእኖት ተደርጎባቸዋል፡፡ ፀጋ ነጻ ነው፣ ግን ትልቅ ኃላፊነትን ያመጣል፡፡

የአይሁዳውያን የተመረጡት ለመነፋትና ለጥቅም አልነበረም ግን አገልጋዮችን እና ካህናት አለምን ለመድረስ (ዘፍ 12:3 ዘጸ 19:4-6 ዮሐ 3:16 1ዮሐ 2:2 ፤4:14) የዘዳግም የኪዳን ውጤቶች እውን እየሆነ ነው። መመረጣችንና የመመረጣችን ውጤቶች ሁለቱ ተቀወባይነት ያላቸው ስነመለኮታዊ ምሰሶዎች ናቸው። መፀሐፍ ቅዱሳዊ ለመሆን ሁለቱን መቀበል አለብን እንጂ አንዱን መምረጥ አይደለም።

ግሱ (BDB 823፣ KB 955፣ *Qal* IMPERFECT) ቅጣት ማለት ይቻላል ( ለምሳሌ ሆሴዕ 1:4፤2:15፤8:13፤9:9) ወይም መጎብኘት እስራኤላውያን እግዚአብሔር በኪዳን በረከት እንደሚጎበኛቸው ጠብቆ ነበር። እግዚአብሔር ግን ኪዳንን በመጣሳቸው ሊቀጣቸው መጣ። (5:18-20) የኪዳን ጥሰቶች አደገኛ የኪዳን ጥሰት እርግማንን ያመጣሉ (ዘዳ 27-29) ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲረዱ የተሻለ ምሳሌ እግዚአብሔር ክሴት መምጣት ነው። የእግዚአብሔር ቤተሰባዊ ፍቅር ሀጢያት እርሱ ከልጆቹ ጋር ያለውን ግንኙነት እንዲያቋርጥበት አይፈቅድም ድሲፕሊን (ፍርድም) አንዱ የፍቅሩና የይቅርታው መንገድ ነው። ይህ ዓላማ ፈጽሞ የአጭር ጊዜ መጽናናትና ብልጽግና አይደለም ግን የእረጅም ጊዜ ህብረትና ቅርበት እንጂ፡፡

**3:3-8** እነዚህ ቁጥሮች ምንም ሲሆን አያሳዩም። ውጤት ያለው እቅድና ዓላማ አለ። ይህ አግባብ የእግዚአብሔርና የእስራኤል የኪዳን ግንኙነት ወይም እግዚአብሔር በነቢያቶቹ እየተናገረ መሆኑን ያሳያል። እነዚህ የጥያቄ ዝርዝሮች የመንስኤና ውጤት ግንኙነት እና የእግዚአብሔርና የእስራኤል የኪዳን ግንኙነት (ዘዳ 27-29)

**3:3 *“መስማማት”*** ይህ የዕብራዊያን ቃል (BDB 416፣ KB 419፣ *Niphal* PERFECT) በመሰረቱ ቅድመ ዝግጅት ያለ ቀጠሮ ማለት ነው(ኢያ 11:5፤ ነህ 6:10፤ ኢዮ 2:11) እነዚህ የተጠቀሱት ሰዎች (1) እግዚአብሔርንና ነቢያትን እንደሚያሳዩ (ቁጥር 7)፤ (2) እግዚአብሔርና እስራኤል (ቁጥር 2) ይህ ከሆነ ለቃሉ አከራካሪ ትርጉም ይወስዳል ዝ.ከ. NIDOTTE፣ ቅጽ 2፣ ገጽ 484)፡ ወይም (3) በየየእለት አንዋንዋር ቀዋሚ ምሳሌ፡፡

**3:5** ጥሩ ለሆነ የእንሰሳት ወጥመድን በተመለከተ (JAMES M FREE MAN፣ MANERS AND CUSTOMS OF THE BIBLE P 228 ) የሚለው መፅሐፍ ላይ በቂ ግንዛቤ ማግኘት ይቻላል።

**3:6 “*መለከት በከተማ ውስጥ ሲነፋ*”** በእኛ ዘመን እንደ ማስጠንቀቂያ ይታያል (ዝ.ከ. ሕዝ 33:2-5)።

▣ ***ህዝቡ አይፈራምን?*** ይህ ግስ በፍርሀት መንቀጥቀጥ ማለት ነው በብዙ አግባብ ተጠቅሟል።
1) የእግዚአብሔር በርግጥ መገኘት (ለምሳሌ ዘፀ 19:16-18)
2) የእግዚአብሔር ለፍርድ መምጣት(ለምሳሌ ኢሳ 10:29፤10:16፤32:11፤41:5)
3) መጥፎ ዜና በሰዎች ላይ የሚያመጣው ውጤት(ለምሳሌዘፍ 27:33፤42:28፤1ነገ 1:49)

በአሞፅ #3 አገባብን በደንብ ሲገጥም ቁጥር #1 እና #2 ግን በአዕምሮ ውስጥ ናቸው፡፡

▣ ***ክፉ ነገር በከተማላይ የመጣ እንደሆነ ያደረገው እግዚአብሔር አይደለምን?*** የእነዚህ የቃል ኪዳን ውጤቶች ምሳሌ (ዘዳ 27-29) በ4:6-11 ላይ ይገኛል። ብሉይ ኪዳን በሁሉም ነገር ላይ የእግዚአብሔርን ሉአላዊነት ያረጋግጣል።(ያውም በዩኒቨርስ ውስጥ ለሚከሰት ምሳሌ 2ዜኛ 20:6፤መክብብ 7:14፤ኢሳ 14:24-27፤ 43:13፤45:7፤54:16፤ኤር18:11፤ሰቆኤር3:33-38) ስለ እግዚአብሔርና ስለ ክፋት በበለጠ ለመረዳት #HARD SAYINGS OF THE BIBLE P 305-306 ፤ የተባለውን መፅሐፍ አንብብ፡፡

**3:7-8** እነዚህ ቁጥሮች እግዚአብሔር በነቢያቶቹ በኩል ህዝቡን አስቀድሞ ያስጠነቀቀበት በጣም አስፈላጊ ቁጥሮች ናቸው። ህዝቡ የእግዚአብሔርን ቃልና ፈቃድ ስለሚያውቁና (4:13) ግን ስላልተቀበሉት ተጠያቂዎች ናቸው።
ይህ የወደፊቱን የሚናገር የትንቢት ፅንሰ ሐሳብ የመፅሐፍ ቅዱስ የተለየ መሆኑንና በእግዚአብሔር መንፈስ የተፃፈ መሆኑ ለዘመናዊ ሰው የምናስረዳበት ዋናው ማሳመኛ መንገድ ነው። የየትኛውም የአለም የሀይማኖት መፅሐፍ ስለ ወደፊት የሚናገር ትንቢት የለውም። የተለያዩ የትንቢት አይነቶች እንደ በተለያየ ደረጃ የሚፈፀሙ 'ምሳሌያዊ (TYPOLOGICAL) አፖካሊፋዊ (APOCALIPTIC) ለሉ ከእናዚህ የተነሳው ግን ቀጥተኛ 'የተወሰነ 'ታሪካዊ ትንቢቶች በሚኪያስ 5:2 እንዳ ያለው ነው። የወደፊቱን የሚናገር ትንቢት እግዚአብሔር በሁሉ ነገር ላይ (አለማቀፋዊ አገራዊ ግለሰባዊ) ተቆጣጣሪ መሆኑን ለማረጋገጥ ለህዝቡ የሰጠው ስጦታ ነው። የሚያምንበትን ለመወሰን ማስረጃ ለሚፈልግ ዘመናዊ ሰው ይህ ሀይለኛ ምስክር ነው።
ትንቢት እግዚአብሔር የጊዜንና የሕዋን ጀማሪና ፈፃሚ መሆኑን ያሳያል። ለብሉይ ኪዳን አማኝ #የመጀመሪያና የመጨረሻ፤ እንደማይነጣጠሉ ተያይዘዋል።

**3:8*ሀ*** ይህ በዝርዝር ስለተነሱት ጥያቄዎች ወቅታዊ እውነት ነው። ስለ ትንቢት አጀማመር ያመለክታል።(1:2) እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ጉዳይ ውስጥ በቀጥታ ተሳትፏል። እስራኤልን ለአላማ መረጠ። እነሱ ግን አላማውን ጥሰዋል። ስለዚህ ፍርድ የእርሱ የይቅርታ ድርጊት አላማው እነርሱን ወደኪዳኑ ቅድስናና አላማ መልሶ ማምጣት ነው።(9:7-15)
አንድ የአምጽ ትክሎጂካዊ ጥያቄ ለማን ይፈረዳል የሚል ነው?
1. እስራኤል በሙሉ (9፡8)
2. የእስራኤል ሃጢአተኞች (9፡10)
3. እስራኤልና ይሁዳ (3፡1)

የወቀችሁን የዳዊት ድንኳን አነሣላሁ /9፡11/ ይህ የኪዳኑ ዓላማ እንደሚቀጥል ያሳያል፡፡

**3፡8ለ** ይህ የአሞጽ የግል እይታው ነው፡፡ ይህ ሁሉም ሰዎች በእግዙአብሔር ለእርሱ ለመናገር ሲጠሩ የሚሰማቸውን ስሜትን ይገልፃል፡፡ ኢሳያስ "ጠፍቻለሁና ወየውል" (ኢሳ 6፡5) በማለት ጮኸ። ኤርሚያስ በአጥንቶች ውስጥ እንደገባ እንደሚነድድ እሳት በማለት ተናገረ /ኤር 20፡9/

## አሞጽ: 3:9-10

**9 በአዛጦን አዳራሾችና በግብጽ ምድር አዳራሾች አውሩና።**
**በሰማርያ ተራሮች ላይ ተሰብሰቡ፥ በውስጥዋም የሆነውን ታላቁን ውካታ፥**
**በመካከልዋም ያለውን ግፍ ተመልከቱ በሉ።**
**10 ግፍንና ቅሚያን በአዳራሾቻቸው የሚያከማቹት ቅን ነገርን ያደርጉ ዘንድ አያውቁም፥ ይላል እግዚአብሔር፦**

**3፡9-10** በዚህ ውስጥ የተያዩ ወሳኝ ነጥቦች አሉ፡፡

1. አውሩ (BDB 1033፣ KB 1570)፣ *Hiphil* IMPERATIVE
2. በሉ (BDB 55፣ KB 65)፣ *Qal IMPERATIVEIMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)*
3. ተሰብሰቡ (BDB 62፣ KB 74)፣ *Niphal* IMPERATIVE
4. እዩ (BDB 906፣ KB 1157)፣ *Qal IMPERATIVEIMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)*

አህዛብ ነገሥታት (ፍልስጤምና ግብጽ) በእስራአል ኃጢአት እንዲመሰክሩና እንዲፈርዱ ተጠሩ፡፡ እነዚህ ለእግዚአብሔርና ለሰው ልጅ ግልጽ ናቸው፡፡

▣ **"አሽዶድ"** አሽዶድ በማሶሬቲክ ፅሁፍ በአረማይክ ትርጉምና በላቲን ቩልጌት የሚገኝ ቃል ነው (NASB፣ NRSV፣ REB፣ NIV)። ከአምስቱ የፍልስጤም ከተማዎች መንግስታት አንዱ ነው ሁሉም ፍልስጤምን የሚወክል ነው በሌሎች የመፅሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች አሶሪያ ተብሎ ተተርጉሟል። ምክንያቱም የተሸለ የግብጽ ትይዩ በቁጥር 9 የተጠቀሰውን ስለሚወክል ነው። ሆሴ 7:7፣11 አሽዶድ ግብጽና ሰማሪያ ሀጢያት እንዲመሰክሩና በህዝቡከላይ ያለውን ምስክርነት እንዲያፀኑ የተጠሩ ሁለት ምስክሮች ናቸው።(ዘዳ 19:15) ይህንን በቁጥር 13 በግልጽ እንመለከታለን። ይህም የቃል ኪዳን የፍርድ ወንበር ነው።

▣ **"የሰማሪያ ተራሮች"** ይህ ነጠላ ሀረግ በ4:6 እና በ6:1 ተጠቅሟል። ይህ የሰሜኑ የአስሩ ጎሳዎች ዋና ከተማ ከኦምት መንገስ በኋላ። ይህ በምሳሌያዊ ከህዝቡ የፖለቲካ ሕይወት ገር ይያያዛል። ቤቴል (3:14) የህዝቡን መንፈሳዊ ሕይወት ያሳያል። ፍልስጤምና ግብጽም በእስራኤል ተራሮች ተሰብስበው የእስራኤልን በሀጢአቷ መቀጣት እንዲመለከቱ ተጋብዘዋል፡፡ ግፍና ቅሚያን አከማችቶ ነበር በተመሳሳይ በግፍ ትበዘበዛለች (2:6-8-3፤ 3፡10ለ)፡፡

▣ **"ታላቅ ሁካታ"** ይህ ቃል በዘዳግም 7:23 እግዚአብሔር የህዝቡን ጠላቶች እንደሚያሳፈር የተናገረው ነው።(ዘጸ 23:27) ይሁን እንጂ በመርገምና በበረከት ክፍል (ዘዳግም 27-29) ይህ ቃል አንዱ እግዚአብሔር እርሱን ባልታዘዙት ህዝቦች ከሚያመጣቸው መርገሞች መካከል ነው።(ዘዳ 28:20)

**3:10** ***"ግን ቅን ነገርን ያደርጉ ዘንድ አያውቁም"*** ቅን የሚለው ቃል ትርጉሙ ቀጥታ የሚለው ነው። ይህ የመሶፖታሚያ የሕንፃ ሥራ መለኪያ መሳሪያ ሲሆን ለእግዚአብሔር ባህርይ ምሳሌ ሆኖ ተወስዷል። ስለዚህ ሀጥያት ሁሉ ከእግዚአብሔር የደረጃ መለኪያ መለየት ማለት ነው (ሆሴ 4:6)!

## አሞጽ: 3:11-15

**11 ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በምድሪቱ ዙሪያ ጠላት ይመጣል**
**ብርታትሽንም ከአንቺ ያወርዳል፥ አዳራሾችሽም ይበዘበዛሉ።**
**12 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እረኛ ከአንበሳ አፍ ሁለት እግርን ወይም የጆሮን ጫፍ እንደሚያድን፥**
**እንዲሁ በሰማርያ በአልጋ ማዕዘን፥ በደማስቆም በምንጣፍ ላይ የተቀመጡት የእስራኤል ልጆች ይድናሉ።**
**13 ስሙ፥ በያዕቆብም ቤት ላይ መስክሩ፥ ይላል የሠራዊት አምላክ ጌታ እግዚአብሔር፦**
**14 እስራኤልን ስለ ኃጢአቱ በምበቀልበት ቀን የቤቴልን መሠዊያዎች ደግሞ እበቀላለሁ**
**የመሠዊያው ቀንዶች ይሰበራሉ፥ ወደ ምድርም ይወድቃሉ።**
**15 የክረምቱንና የበጋውን ቤት እመታለሁ በዝሆንም ጥርስ የተለበጡት ቤቶች ይጠፋሉ፥**
**ታላላቆችም ቤቶች ይፈርሳሉ፥ ይላል እግዚአብሔር፦**

**3:11 ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣** ይህ ሐረግ ልዩ መገለጥን የሚወክል ሐረግ ነው፡፡ (ምሳሌ 3:11-12) በምዕራፍ 1ና2 በተደጋጋሚ የተጠቀሙበት ክፍሉ ይላል እግዚአብሔር፤ በሚል ሐረግ እንደሚያበቃ ማስተዋል አስፈላጊ ነው (3:13-15) ጌታ እግዚአብሔር፣ የሚለው የዕብራዊያን ሁለት መለኮታዊ ሰዎችን ያንጸባርቃል። እነሱም 1) አዶን 2) ያህዌ ናቸው።

የመለኮት ስሞች የሚ፤ልውን ልዩ ርእስ በ1፡2 ላይ ተመልከት

▣ **ጠላት** ይህ የአሶሪያ መንግስት በአሞጽ አንዴ እንኳ ያልተጠቀሰ እና በሆሴዕ ብዙ ጊዜ ተጠቅሶ የሚታይ ሲሆን በ922 ዓ ዓለም አሥሩን የሰሜኑ የእስራኤል ጎሳዎችን የወሰደ ነበር። የእስራኤል ዋና ከተማ የነበረች ሰማሪያ ከረዥም ጊዜ ከበባ በኋላ ነበር የተወሰደችው።

▣ **ብርታትሽንም ከአንቺ ያወርዳል፣** ይህ የዕብራዊያን ቃል (1) ቁሳዊ ብርታት ወይም (2) ቁሳዊ ምሽግ ሊሆን ይችላል።

NASB "አዳራሻችሁ ይበዘበዛል"
NKJV "አዳራሻችሁ ይበዘበዛል"
NRSV "ምሽጎቻችሁ ይበዘበዛል"
TEV "ቤታቸውን ይበዘበዛል"
NJB "አዳራሻችሁ ይበዘበዛል"

ለአዳራሾች የተሻለ መረጃ ፤ በ 1:4 ማስታወሻ አንብቡ።

ይዘረፋል የሚለው ግስ ከተሸነፈው ጠላት ተወርሶ በድል አድራጊ ወታደሮች መካከል የሚከፋፈል ምርኮን ያመለክታል፡፡ ይህ ምርኮ ሁሉንም የተሸነፉ ቡድን ንብረቶች (ሰዎች'ከብቶች'አልባሳቶች፣ የከበሩ ዕቃዎችን፣ ወዘተ) ያጠቃልላል፡፡ በቁጥር 10 እንደሚታየው #ግፍንና ቅምያን በአዳራሾቻቸው የሚያከማቹ፣ እስራኤላዊን ነበሩ፡፡ አሁን በግፍ ያከማቹ ምርኮአቸው ከእነርሱ ይወሰድባቸዋል፡፡ የዘሩትን ያጭዳሉ፡፡ ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርዕ ነው፡፡(ኢዮ 34:11፤ መዝ 28:3፤ 62:12፤ ምሳሌ 24:12፤ መክብብ 12:14፤ ኤር 17:10፤32:19 ማቴ 16:27፤25:31-46፤ ሮሜ 2:6፤ 14:12፤ 1ቆሮ 3:8፤ 2ቆሮ 5:10፤ ገላ 6:7፤ 2ጢሞ 4:2፤ 1ጴጥ 1:17፤ ራዕ 2:23፤ 20:12፤ 22:12)

**3:12** ብቻውን ራሱን ችሎ ትርጉም የሚሰጥ ቁጥር ነው፡፡ አዲሱ የተከለለ መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ ሌሎች በዙሪያው ያሉት ቁጥሮች በቅኔ መልክ ሲቀመጡ ለዚህ ግን የተለየ የአጻጻፍ ዘይቤን ይጠቀማል፡፡ የዛሬውን እንግሊዘኛ ትርጉም እና አዲሱ ኢየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ የተለየ አቀማመጥ ይጠቀማሉ፡፡ ይህ የሚጋጭ ቁጥር የሰሜኑ አስር የእስራኤል ነገዶች አጠቃላይ መደምሰስን ያመለክታል፡፡ ጥቅት የቆሰለ ቅሪት ብቻ ከመላው መንግስቱ ይተርፋል፡፡(5:15፤ 9:8) በሌላ በኩል ይህ ዘጸ22:1-13 ያለወን ያመለክታል፡፡ እንደዚያ ከሆነ ደግሞ ይህ የሚመለሱ ቅሬታዎች ምሳሌ ሳይሆኑ የመጨረሻና ፍጹም መደምሰስ ምሳሌ ነው፡፡ እረኛው አንደኛውን አማራጭ ያሳያል፡፡

ይህ የጸሐፊው ግምት ሲሆን የሚያደንቀው ግን እግዚአብሔር፣ የሚለው ቃል በሚያመልኩ በመከለኮት ፊት መንበርከካቸውን ለማሳየት ተጠቅሟል፡፡ ይህ የእስራኤል በእግዚአብሔር ስም የተቀረጸ ምስል ማምለከን የሚየመለክት ድርብ ትርጉምን ያሳያል፡፡

ይህ ድርብ ትርጉም ይቀማል ተቀማ፣ ወደሚለው ሊቀጥል ይችላል፡፡ አንደኛው #Niphil፣ ፍጹም እና ሁለተኛው #Hiphil፣ ፍጹም ያልሆነን ያመለክታል፡፡ ይህን ቃል በብዛት ሚጠቀሙት ነፃ ለማውጣት ነው፡፡ (ለምሳሌ ሚኪያስ 4:10) ስለዚህ ማዳን አገባብ በእስራኤል ፍርድ ተቃራኒ ተጠቅሞበታል፡፡ አሞጽን ኃይለኛ ባለቅኔ ያደረገው ይህ የቃላት ጫዋተው ነው፡፡

▣ **የደማስቆ ምንጣፍ፣** ይህን ቃል ለመተርጎም በጣም ያስቸገረ የዕብራውያን ቃል ነው፡፡ ብዙ ትዮሪዎች አሉ፡፡

1. በደማስቆ የማስረትክ ጽሑፍ በ70 በያዕቆብ ትርጉምና በአዲሱ ኢንተርናሽናል ትርጉም የተከተሉት LXX፣ Peshitta፤፣ ነው፡፡ በደማስቆ የዕብራዊያን ተነባቢዎች #አንድ እግር፣ በማለት መተርጎም ይቻላል፡፡
2. ከደማስቆ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ልዩ ልብስንም ሊያመለክት ይችላል፡፡ ሱፍ እና ቀጭን የተልባ እግር በመባል ተተርጉሞአል፡፡ የአሜሪካ መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስና እና አዲሱ የአሜሪካ መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስና በእንዲህ ዓይነት ተርጉሟል፡፡
3. የአልጋ ክፍል፣ (የተከለለ መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ፤ አዲሱ የተከለለ መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ እና ከዚሁ ጋር በቅርበት የተያያዘው የዛሬው እንግሊዘኛ መጽሐፍ ቅዱስ #የአልጋ እግር ኮሞፖርሳቶ፣ በማለት ሲተረጉም በመካከላኛው ዘመን የሚኖሩ የአይሁድ ተንታኞች ራሺና ክምችን የተባሉ ተጠቅመውበታል፡፡

ይህ በጣም ውድ የሆነ የቤት ዕቃ የሚሳይ እና የሰማሪያን ሁኔታ የሚገልጽ ሲሆን ከዚህ በጣም የማይጠቅም ቅሬታ እንደሚቀር ያመለክታል፡፡ ይህ ንጽጽር የበግ ባለቤት ቁራጭ በግ ከአንበሳ እንደሚያተርፍ የእስራኤልም ቅሬታ እንደዚያው እንደምሆን ለማሳየት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ፍርድ ትክክለኛ የቃሉ ህጋዊ ፍጻሜ ማግኛ ምልክት ነው፡፡(ዘዳ 27-29) የእግዚአብሔር የማዳን ቃሉ እንደሚታመን ሁሉ የቃል ኪዳኑን አለመታዘዝ የሚያመጣው ውጤትም እንደዚያው የታመነ ነው፡፡

**3:13 "ስሙ፤ በያዕቆብም ቤት ላይ መስክሩ"** ሁለቱ ግሶች (BDB 1033 እና 729) IMPERATIVES ወይም ትዕዛዞች ናቸው፡፡ ሀረጉ ከ3:9 ጋር ትይዩ ነው፡፡ ይህ ቃል ግልጽ የችሎት ቃል ነው፡፡ ሁለቱ የነገስታት አእዛብ ነገስታት ፍሊስጤም(አሽዶድ)ና ግብጽ እንደ ሁለት ተፈላጊ ምስክሮች እግዚአብሐሔር በህዝቡ ሲፈርድ የሚመለከቱ ናቸው። (ዘዳ 17:6፤19:15)
በድጋሚ የያዕቆብ ቤት፣ ማንን ያመለክታል? (1) በሰሜኑ የሚገኙትን አስሩን ነጎዶች ወይስ (2) ሁሉም የያዕቆብ ዘሮች (እስራኤልና ይሁዳ)? እንደ ቁጥር 12 አሞጽ ብዙ አገባብ ያለውን ቃል ይጠቀማል። መስክሩ ማለት

1. አስጠንቅቁ መተማመኛ ስጡ፣ (ዘፍ 43:3፤ ዘፀ 21:29፤1ነገ 2:42፤ ነህ 13:15፣ 21)
2. እዘዙ፣ ከልክሉ፣ የሚል ከያህዌ ጋር የተያያዘ ኪዳን (ዘፀ19:23፤ዘዳ 32:46)
3. እዚህ በእስራኤል ላይ ስለሚመሰክሩ ሁለት ምስክሮች ሊሆን ይችላል። (1ነገ 21:10፣13፤2ዜና 24:19) ያህዌ በአሞጽ በኩል እስራኤልን ማህበራዊና ሀይማኖታዊ ቃልኪዳን ስለመጣሳቸው ይከሳቸዋል፡፡ አሁንም የአሞጽን ቅኔ ኃይለኛ ያደረገው የቃል አጠቃቀሙ ነው፡፡

▣ **የሰራዊት አምላክ ጌታ እግዚአብሔር#** እነዚህ ሶስት እግዚአብሔርን የሚያሳዩ ዋንኛ አባባሎች በአንድነት የገቡበት ቦታ በብሉይ ኪዳን እዚህ ብቻ ነው።

1. ጌታ፣ Adon-አዶን፣ የሚለው ቃል
2. እግዚአብሔር፣ ያሕዌ፣ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ስም
3. አምላክ፣ ኤሎሂም፣ የሚለው ስም የእግዚአብሔር አጠቃላይ ስም
4. የሰራዊት፣ የሰማይ ሰራዊት አዛዥ ወይም የሰማይ የፍርድ ዙፋን መሪ (3:13፤5:14-16፤6:8)

የመለኮት ስሞች የሚ፤ልውን ልዩ ርእስ በ1:2 ላይ ተመልከት

**3:14 በዚያ ቀን፣** ይህ የፍርድ ቀንን ያመለክታል፡፡(2:16)

▣ **የቤተልን መሰዊያዎች፣** ቤቴል ኢዮርብዓም የጥጃን ምስል ሊያመልክበት በደቡብ በኩል ያቋቋመው የአምልኮ ቦታ ነው፡፡(1ነገ 12፡26-33) ከእየሩሳሌም በስተሰሜን በ10 ማይል ርቀት የሚገኝ የጥንት የተቀደሰ የዕብራዊያን አምልኮ ስፍራ ነው። ያዕቆብ ለእግዚአብሔር መሰዊያን አዘጋጅቶ የነበረበት ስፍራ ነው፡፡(ዘፍ 28፡10-22)

**ልዩ ርዕስ፡ በጥንታዊያን ቅርብ ምስራቅ የመስዋዕት ሥርዓት**

(እነዚህ ማሰታወሻዎች ከእኔ የብሉይ ኪዳን አሰሳ ማሰታወሻ ደብተሮች ክፍል ናቸው)

I. *ሥነ-ሥርዓታዊ ህጎች በመሰፖታምያ*
   *ሀ.* መስዋዕቱ በመጀመሪያ ለአማልክት የሚቀርብ ምግብ ነበር። መሰዊያው ለአማልክት ምግብ የሚቀመጥበት ጠረጴዛ ነበር። ከጎኑ ያምላክን ትኩረት ለመሳብ ዕጣን የሚቀርብበት የከሰል ማንደጃ ነበር። በደም ውስጥ ሥነ-ሥርዓታዊ መግለጫዎች የሉም። ቢላዋ የተሸከመ የእንስሳውን ጉሮሮ ይቆርጣል። ምግቡ በአማልክት፤ ቢላዋ በተሸከመውና በንጉስ ካህን እንዲሁም በታዳሚዎች መሀከል ይከፋፈላል። መስዋዕት አቅራቢው ምንም አይቀበልም።
   *ለ.* ለስርዬት የሚሆን መስዋዕት አልነበረም።
   *ሐ.* ህመም ወይም ሥቃይ ከአማልክት ቅጣት ነበሩ። እንስሳው ቀርቦ ይታረድ ነበር፤ ይህ ለአቅራቢው እንደ ምትክ ይደረግ ነበር።
   *መ.* የእስራኤላውያን ሥነ-ሥርዓት የተለየ ነበር። ሰው ለእግዚአብሔር ከድካሙ ድረሻ ላስፈላጊ ምግብ መልሶ ከመስጠት የተገኘ ይመስላል (ዘፍ 4፡1-4፤ 8፡20-22) ።
II. *ሥነ-ሥርዓታዊ ህጎች በከነአን (ከእስራኤላውያን ጋር በጣም ተመሳሳይ)*
   *ሀ. ምንጮች*
      1. *መጽሐፍ ቅዱሳዊ መግለጫዎች*
      2. *የሶፈርንቃዊያን ሥነ-ጽሑፎች*
      3. ከከኡጋሪት የሆነ የራስ ሻማራ ጽላቶች የከነአናዊያን አማልክት እና አፈ-ታሪክ ቅድመ ክርስቶስ ልደት ወደ 1400
   *ለ.* የእስራኤላውያን እና የከነአን የመስዋዕት ሥርዓት በጣም ተመሳሳይ ነው። ነገር ግን በከነአን የመስዋዕት ሥርዓቶች ላይ በተጎጂው ደም ላይ አጽእኖት የተሰጠበት ነገር የለውም።
III. *ሥነ-ሥርዓታዊ ህጎች በግብፅ*
   *ሀ.* መስዋዕት ይቀርቡ ነበር ነገር ግን አጽእኖት አልተደረገባቸውም።
   *ለ.* መስዋዕት አስፈላጊ አልነበረም ነገር ግን መስዋዕት አቅራቢው ባህሪይ አስፈላጊ ነበር።
   *ሐ.* መስዋዕት የሚደረጉት የአማልክትን ቁጣ ለማቆም ነበር።
   *መ.* መስዋዕት አቅራቢው ይቅርታንና ነፃ መውጣርን ተስፋ ያደርግ ነበር።
IV. የእስራኤል *ሥነ-ሥርዓታዊ ህጎች-* የእስራኤላውያን የመስዋዕት ሥርዓት ከከነአናዊያን ጋር በጣም የሚቀርቡ ነበሩ ነገር ግን ተያያዥነት አለው ማለት አይደለም።
   *ሀ. ገላጭ ሀረጎች*
      1. *መስዋዕት የሰው ልጅ እግዚአብሔርን ሲፈልግ በድካነት የሚታይ መግለጫ ነበር።*
      2. *መስዋዕትን የሚወስን የብሉይ ኪዳን ሕግ መስዋዕትን ለማነሳሳት ሊባል አይችልም* (ዘፍ፡ 7፡8፤ 8፡20)።
      3. *መስዋዕት ሥጦታ ነበር* (የእንስሳ ወይም እህል)።
      4. *ለእግዚአብሔር ክብር ሲባል ሙሉ በሙሉ ወይም በግማሽ በመሰዊያው ላይ የሚጠፋ ሥጦታ መሆን አለበት።*
      5. *መሰዊያው መስዋእት የሚደረግበት ቦታና የእግዚአብሔርን መገኘት በምሳሌ የሚያሳይ ነበር።*
      6. *መስዋዕት በውጪ የሚደረግ አምለኮን የሚያሳይ ድረጊት ነበር* (የሚታይ ጸሎት)።
      7. *የጸሎት ትረጉም "የሚደረግ ጸሎት" ወይንም "ሥነ-ሥርዓታዊ ጸሎት።" ሥነ-ሥርዓታዊ የሆነ ነገር አስፈላጊነቱና በርሱ ላይ ሚደረግ የባህላችን አድልዎ* Gordon J Wenham (Tyndale፤ *Numbers*፤ *ገጽ* 25-39) *ላይ ተገለጧል*
      *ዘለዋዊያን እና ዘኍልቅ ሁለቱም ለሙሴና ለእስኤል እነዚህን ነገሮች የሚመስሉ ትላልቅ ነገሮችን ይዘዋል።*
   *ለ. መስዋዕት የሚያካትተው፡-*
      1. *ለእግዚአብሔር የሚሰጥ ሥጦታ*
         *ሀ.* *ምድር ሁሉ የጌታ መሆንዋን እውቅና መስጠትን ያካትታል*
         *ለ.* *አንድ ሰው ያለው ማንኛውም ነገር ለእግዚአብሔር ይገባል*
         *ሐ.* *ስለዚህ፡ ሰዎች ግብርን ለእግዚአብሔር ማምጣታቸው የተገባ ነው*
         *መ.* *ልዩ የሆነ ሥጦታ ወይንም ግብር ነበር። ሰው የራሱን ህይወት ቆይታ ያራዝም ዘንድ የሚያስፈልገው ጉዳይ ነበር። የሆነ ነገር ከመስጠት የበለጠ ነበር፤ እርሱ የሚፈልገው ነገርም ነበር። የራሱን ድርሻ ለእግዚአብሔር መስጠትም ነበር።*
         *ሠ.* *ሥጦታውን በማጥፋት ዳግመኛ የራስ እነደሆነ መወጅ አይቻልም።*
         *ረ.* *የሚቃጠል ሥጦታ ሊታይ አይችልም ወደ እግዚአብሔር ግዛት*(realm) *ይሄዳል።*
         *ሰ.* *የቀደሙት የመሰዊያ ቦታዎች እግዚአብሔር በሚገኝበት ቦታ ይተከሉ ነበር። መሰዊያ ቦታዎች እነደ ቅዱስ ቦታዎች የታዩ ነበር፤ ስለዚህ ሥጦታው እዚያ ይወሰድ ነበር።*
      2. *የአንድ ሰው ህይወት ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር መሰጠትን ያሳይ ነበር*
         *ሀ.* *የሚቃጠል ስጦታ በፈቃደኝነት ከሚቀርቡ ሶስት ስጦታዎች አንዱ ነበር።*
         *ለ.* *ለእግዚአብሔር ያለንን የጠለቀ የማክበር ስሜታችንን ለመግለጽ እንስሳው ሙሉ በሙሉ ይቃጠል ነበር።*
         *ሐ.* *ይህ ለእግዚአብሔር ለሚሰጥ ስጦታ እጅግ ጥሩ ማሳያ ነበር።*
      3. *ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ማድረግ*
         *ሀ.* *ህብረትን የሚያሳይ መስዋዕት።*
         *ለ.* *ምሳሌው እግዚአብሔር እና ሰዎች ህብረት እንዳላቸው የሚያሳይ የደህንነት መስዋዕት ሊሆን ይችላል።*

ሐ. መስዋዕቱ ይህን ህብረት ዳግመኛ መልሶ ለማግኘት ይደረግ ነበር።

4. ለኃጢአት ስርየት
   ሀ. ሰው ኃጢአት ሲያደርግ ግንኙነቱን (ቃል-ኪዳኑን) ሰው ሰበረውን ያድስ ዘንድ እግዚአብሔርን መጠየቅ ይገባው ነበር።
   ለ. ከተሰበረው ግንኙነት ምክንያት የተነሳ በበደል መስዋዕት የህብረት ምግብ አይኖርም።
   ሐ. የደም አስፈላጊነት
      (1) ስለ ሰው በመሰዊያው ላይ ደረጋል
      (2) ስለካህኑ በመጋረጃው ላይ ይደረጋል
      (3) ስለ ሊቀካህኑ እና ስለ ህዝቡበስርየት መክደኛው ላይ ይደረጋል (ሌዋ 16)
   መ. ሁለት ዓይነት የኃጢአት መስዋእቶች አሉ። ሁለተኛው የበደል ወይም የመተላለፍ መስዋዕት ተብሎ ይጠራል። በዚህ ውስጥ በዳዩ ተወስዶ ወይም ተጎድቶ የነበረውን ወገኑን እስራኤላዊ ለማደስ የእንስሳ መስዋእት ይዞ ይቀርባል።
   ሠ. ቀድሞ ለታሰበሰበት ወይም ሆን ብሎ ለተደረገ ኃጢአት ምንም መስዋት አልነበረም 4:1፤ 22፤ 27፤ 5:15-18፤ 22:14።

V. ለተለያዩ መስዋዕቶች ሥርዓት ከሌዋዊያን
 ሀ. ሌዋዊያን 1
  1. የመግቢያ ደንቦች "እግዚአብሔር ለሙሴ ተናገረ" 1:1-2፤ 4:1፤ 5:14፤ 6:1፤19፤7:22፤ 28
     ሀ. ከመንጋ
     ለ. "መቼ፡" ቁ 2፡ ይህ ግዴታ ሳይሆን ፈቃደኝነትን ያሳያል።
  2. የሚቃጠል መስዋዕት ቁ 3-17 (6:8-13)
     ሀ. መሰዊያ
        (1) የናስ መሰዊያ፤ የሚቃጠል መስዋዕት ማቀረቢያ ተብሎም ይጠራል፤ በመገናኛ ድንኳን ደጃፍ ያለ መሰዊያ ወይንም በናስ የተሸፈነ ከግራር እንጨት የተሰራ (ዘጸ፡ 27)።
        (2) ይህ በቅድስት ካለ ከዕጣን መሰዊያ (የወርቅ መሰዊያ) ለየት ያደርገዋል (ዘጸ፡ 30)።
        (3) ፍም ከናስ መሰዊያ ወደ ዕጣን መሰዊያ ይወሰድ ነበር።
        (4) የናስ መሰዊያ ከመገናኛ ድንኳን መግቢያ መሀከል በቀኝ በኩል ነበር።
        (5) መሰዊያው በጣም ቅዱስ ክፍል የሆነ ቀነዶች ነበረው። ደም በቀነዶቹ ለይ ይደረጋል (ዘጸ፡ 30፡10)።
        (6) ቀነዶቹ ሊሆኑ የሚችሉት
           (ሀ) መሰዋዕቱን የምይዙ የምሳሌ እጆች
           (ለ) የጥንካሬ ምሳሌ ወይንም የሚበዛ ኃይል ምሳሌ
           (ሐ) በኋላ የመሰዊያውን ቀነዶቹን የያዘ ማነም ጉዳዩ በሸንጎ ፍርድ እስኪታይ ድረስ ደህንነቱ ይጠበቃል(1 ነግ 1:50-51፡ 2:28)
     ለ. መስዋዕቱ
        (1) እንከን የለሌበት ተባዕት ወይፈን መጀመሪያ የተጠቀሰበት ምክንያት ስላስፈላጊነቱና ዋጋው ነው (ዘሌ 1፡3)
        (2) የፍየል ወይም የበግ ተባዕት (ዘሌ 1፡10)
        (3) ዋኖስ ወይም የርግብ ጫጩት (ዘሌ 1፡14) (ለድሃ የተዘጋጀ)
     ሐ. የሚቃጠል መስዋዕት ቦታ ከመገናኛ ድንኳን ደጃፍ ነበር።
     መ. እጆችን መጫን-ይህ ወይፈን ላይ እንጂ በፍየል ወይም በበግ በዋኖስ ወይም በርግብ ጫጩት ላይ አይደረግም (ቁ 4)
        (1) መስዋዕት አቅራቢው ይህንን ለራሱ አደረገው (ካህኑ አይደለም)
        (2) ብዙዎች ይህ በደልን የማስተላለፍ ምሳሌያዊ አገላለጽ እነደ ነበር ያስባሉ
        (3) ሌሎች ይህ ምን ማለት እነደሆነ ሲናገሩ፡-
           (ሀ) ይህ እንስሳ የሚመጣው ከግለሰቡ እንደሆነ ይናገራሉ
           (ለ) መስዋእቱ የሚቀርበው በአቅራቢው ስም እነደነበር ያስባሉ
           (ሐ) የዚህ መስዋእት ፍሬ በእንስሳው ላይ እጁን ለሚጭን እነደሚሆን ያስባሉ
     ሠ. ማረድ
        (1) ኮርማ - "በጌታ ፊት" በሚሰዋው ሰው እጅ። ያቀረበው እንስሳውን መግደል፤ ቆዳውን መግፈፍ እና መበለት አለበት። ካህኑ ተግባር (በአደባባይ ከሚደረገው መስዋዕት በስተቀር) የሚጀምረው ሰውዬው መስዋእቱን በመሰዊያ ላይ ሲያቀርብ ነው።
        (2) በግ ወይም ፍዬል ቁ 11 - "በመሰዊያው በስተሰሜን በኩል በጌታ ፊት።" ይህ ለእነዚህ ትናንሽ እንስሳት በተለየ መልኩ የተዘጋጀ ነው።
        (3) ወፎች - ይህን መስዋእት ካህኑ ገድሎ ያቀርባል። አቅራቢው የወፍን ገሮሮ መቁረት
     ረ. የደም አያያዝ
        (1) እንስሳ
           (ሀ) ካህኑ ደሙን ወደ መሰዊያ ይረጫል፤ በመሰዊያው ዙርያም ይረጫል።
           (ለ) የእንስሳው ነፍስ በደሙ ውስጥ ነው። (ዝ.ከ. ዘፍ 9:4፤ ሌዋ 17:11)። ህይወት ቀድሞውኑ የእግዚአብሔር ነው፤ ስለዚህ ደም ሰው ለእግዚአብሔር እነደ ሥጦታ ሊያቀርብ አይችልም።
           (ሐ) የወፎች ደም በመሰዊያው ላይ ይደርቃል እንጂ በእሳት አይቃጠልም
     ሰ. የስጋ አያያዝ
        (1) ኮርማ ቁ፤ 6
           (ሀ) ያቀረበው ሰው የእንስሳው ቆዳ ይገፍፋል። ካህኑ ቆዳዉን መጠበቅ ይኖርበታል (ዝ.ከ.፤ 7:8)

(ለ) ያቀረበው በየብልት ብልቱ ይከፋፍላል

(ሐ) ካህኑ ልክ እንስሳው በህይወት በነበረበት ጊዜ እነደሚኖረው የብልት አቀማመጥ አድርጎ በመሰውያው ላይ ያስቀምጣል።

(መ) እግሩ እና የውስጥ የሆድ እቃው በመታጠቢያ ሰን ላይ ይታጠቡ ነበር።

(ሠ) ካህኑ ሙሉውን እንስሳ በመሰዊያ ላይ ያቃጥላል

3. የሚቃጠል መስዋዕት ጊዜያት
   - ሀ. የመገነኛ ድንኳን በአል፡ የዳስ በዓል
   - ለ. የማስተሰሪያ ቀን
   - ሐ. የበኩራት እና የበአለ ሃምሳ በዓል
   - መ. የመለከት በዓል
   - ሠ. የመወዝወዝ በዓል (ሌዋ 23)
   - ረ. የቂጣ ወይም የፋሲካ በዓል
   - ሰ. የወር የመባቻ በዓል
   - ሸ. ሰንበት
4. የሚቃጠል መስዋእት አስፈላጊነት
   - ሀ. ለእግዚአብሔር ስጦታ
   - ለ. በጣም ዋጋ እነዳለው መስዋእት ይታያል
   - ሐ. ዘፍጥረት ላይ ባለው የኃጢአትሀሳብ ወይም ምስጋና ጋር የሚያያዝ ይመስላል
   - መ. የመስዋእትን ሀሳብ ፍጹም በሆነ መልኩ ያሳያል
   - ሠ. የእንድን ህይወት በምሳሌያዊ መልክ ማቅረብ
   - ረ. ለእግዚአብሔር አገልግሎት የገለሰብን ህይወት ፍጹም በሆነ መልኩ ማቅረብ
   - ሰ. የመስዋእቱ ደረጃ አወጣጥ
     - (1) ኮርማ
     - (2) በግ - ፍዬል
     - (3) ወፎች
   - ሸ. ይህ ማንም ለመንፈሳዊ ፍላጎቱ ወደ እግዚአብሔር እነደሚቀርብ ያሳያል።የእግዚአብሔር ለሁሉም ሰው ማዘጋጀቱን ያሳያል።
5. ለካህናት ተለየ መመሪያ 6:8-12
   - ሀ. የሚቃጠል መስዋእት ሌሊቱን በሙሉ በመሰዊያው ምድጃ ላይ ይሆናል
   - ለ. ከሚቃጠል መስዋእት በታች እሳቱ ሳይቋረጥ መንደድ አለበት
   - ሐ. መመሪያው የካህናትን አለባበስንም ይጨምራል
   - መ. መመሪያው አመድን ማስወገድንም

ለ. ሌዋዊያን 2:1-16 (6:14-23)

1. መግቢያ
   - ሀ. ይህ ምእራፍ ስለ የእህል ቊርባን ይናገራል
   - ለ. የእህል ቊርባን ከስርወ ቃሉ "ስጦታ" ነበር። እርሱ እንስሳ ላልሆኑ ወይም ለእህል ስጦታ ሙያዊ ቃል ሆነ
   - ሐ. ከምርኮ በኋላ የእህል ቊርባን ለሚቃጠል መስዋእት እና ለደህንነት መስዋእት እነደ ማሟያ ሆነ ረቢዎች ወይም መምህራን በጣ ድሆች የሆኑ ለብቻው መቅረብ ይችላሉ አሉ።
   - መ. በዘኁ 18፡ 19 እና 2ዜና 13:5 በተጨማሪም የጨው ቃል ኪዳን ተጠቅሶ ነበር። ጨው የ ሊጥ ተቃራኒ ነው። ለየእግዚአብሔር ቃል ኪዳን እነደ ምሳሌ ጥቅም ላይ ውሎ ነበር ምክንያቱም የማበሰብስና ለሁል ጊዜም የሞኖር ነውና።
2. የእህል ቊርባን የአንድ ሰው ድካም ለየእግዚአብሔር መሰጠቱን የጠቃልላል።
   - ሀ. እርሱ ከየየለት የህዝብ ምግብ ለየእግዚአብሔር የሚሰጥ መስዋእት ነበር
   - ለ እርሱ ባጠቃላይ ማሟያ ነበር(በተለይ ከምርኮ በኋላ ባሉ ጊዜያት) ለሚቃጠል ወየንም ለደህንነት ስጦታ።
   - ሐ. መስዋዕት ለካህናት እግዚአብሔር የዘጋጀው ነበር። ከአጠቃለዩ ጥቂቱ ብቻ ለመታሰቢያነት ይቀርብ ነበር
   - መ. "መታሰቢያ" የሚለው ቃል የመስዋእቱን ክፍል ወይንም ሁሉን በእግዚአብሔር ፊት የቀረበውን ክፍል የሚያመለክት ነው።
   - ሠ. የአዲስ ኪዳን "ቅዱስ ቁርባን" ሀሳብ እነደ "መታሰቢያ" በመሆን ይህንን የብሉይ ኪዳን ሃሳብ ያመለክታል።
   - ረ. "ቅዱስ" ከሚለውና "በጣም ቅዱስ" በሚለው ቃላት መካከል ያሉት ልዩነቶች፡-
     - (1) "ቅዱስ" -ካህናት እና ቤተሰብ በማንኛውም ቅዱስ ስፍራ ሙብላት ይችላሉ
     - (2) "በጣም ቅዱስ" - በካህናት ብቻ በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ሊበላ ይችላል
3. አይነቶች
   - ሀ. ከመልካም ዱቄት (ለሃብታም)፤ 2:1-3
   - ለ. የተጋገረ ወይንም ኬክ፤ 2:4-11
   - ሐ. የተጠበሰና የተፈተገ የእህል እሸት (ለድሆች)፤ 2:12-16
     - (1) ከመልካም ዱቄት የላቀ መስዋዕት ነበር። የስንዴ ዱቄት መልካሙ ነበር።
     - (2) የተጋገረ
       - (ሀ) በዱቄቱ ውስጥ ዘይት ነበር
       - (ለ) በእቶን የተጋገረ ነበር ቁ 4

(ሐ) በምጣድ የተጋገረ ቁ 5
(መ) በመቀቀያ የበሰለ ቁ 7
(3) በእሳት የተጠበሰና የተፈተገ ስንዴ ወይም በቆሎ እሸት
(ሀ) ድርቅ ማለት አለበት
(ለ) መቆራረስ አለበት
(ሐ) ለእንግዶች እንደሚዘጋጀ ምግብ
4. በውስጡ የያዛቸው
ሀ. መልካም ዱቄት ነውር ከሌለው እንስሳ ጋር ግንኙነት አለው
ለ. ዘይት የበረከት ምሳሌ ነበር እና ስለዚህ የእግዚአብሔር መገኘት ምሳሌ ነበር
(1) ለምግብነት ለመስዋዕትነት፤ ለመድኃኒትነት እና ለቅባት ያገለግላል
(2) ምናልባት የቅባት ጥቅም የቅባትን መስዋዕት ለማስቀረት ይሆናል
ሐ. ዕጣን ከህንድ ወይም ከአረብ ነበር
(1) በጣም ንጹህና አስደናቂ ሽታ እንዳለው ይታያል
(2) ጸሎትንና ምስጋናን ያመለክታል
መ. ጨው
(1) የማቆየትና ህይወት የመስጠት ብቃት ያለው
(2) ብዙ ጊዜ ለማቆያነት ሳይሆን ምግብነት ሊያገለግል ይችላል
ሠ. በውስጡ የማይጨመሩ ነገሮች
(1) እርሾ አይገባበትም፤ ቁ 11
(ሀ) ምክንያቱ ሊያቦካው ስለሚችል ይሆናል
(ለ) እርሾ ከመበስበስ ጋር የተያያዘ ነው
(ሐ) ከበኩራት ጋር እና ለካህናት ሊቀርብ ይችላል
(2) ማር አይገባበትም፤
(ሀ) ጣፋጭ መጠጥ ከአተክልት ነው እንጂ ከንብ ማር አይደለም
(ለ) ምናልባት በከነዓናዊያን ሥርዓት ጥቅም ላይ ይውል ስለ ነበር ይሆናል
5. የመስዋዕት ሥርዓት
ሀ. ወደ ካህን የቀርብ ነበር፡፡ ሁሉንም ሥርዓት እርሱ ይይዛል፡፡ (2:2፤ 9፤ 16)
ለ. ከመስዋዕቱ በተቀደሰው ሥፍራ በካህናት ይበላ ነበ፡፡ በጣም የተቀደሰ ሥፍራ ነበር፡፡
6. አስፈላጊነቱ
ሀ. ከበታች ለከበላዩ ይቀርባል
ለ. የተወሰነውን መጠን ከርሱ ላይ ማቃጠል አንድ ሰው ከተግባሩ ተወሰነን ድረሻ ለእግዚአብሔር መስቱን ይወክላል
ሐ. ግልጽ ትርጉም
(1) የሚቃጠል መስዋዕት - የአንድ ሰው ህይወት መሰጠት
(2) የእህል ቁርባን መስዋዕት -የአንድ ሰው የየለት ተግባር መሰጠት
7. ለእህል ቍርባን መስዋዕት፤ ልዩ መመሪያ 6:14-23
ሀ. በመሠዊያው ፊት ያቀርቡታል
ለ. ሰራተኛው ለእግዚአብሔር ሥጦታን ያቀርባል፤ግን እውነታው ሲታይ ለካህናት ጥቅም ነው
ሐ. ሌዋዊያን 3:1-17 (7:13-34)፤ የደህንነት መስዋእት
1. መግቢያ
ሀ. ለምን
(1) የጋራ መስዋዕት
(2) የቃል ኪዳን መስዋዕት
(3) የህብረት መስዋዕት
(4) የማጠቃለያ መስዋዕት
ለ. ከእግዚአብሔር፤ ከቤተሰብና ከጓደኛ ጋር ላለው ህብርት ምክንያት ለእግዚአብሔር ምስጋናን ያሳያል፡፡
ሐ. በተከታታይ መስዋዕት የሚደረግበት ምህረት ተመስርቶ የነበረበት የመጨረሻ ድረጊት እንደ ነበር የተለመደ ነው፡፡
መ. የሚቃጠል መስዋዕት የመታዘዝን ውድነት ያሳያል፤የደህንነት መስዋዕት ግን ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት በማድረግ ያለንን ደሰታ እና ሀሴት ያሳያል
ሠ. ያለነውር የሆነ እንስት ወይም ተባእት
ረ. የተላያዩ መስዋዕቶች
(1) ከአእዋፍት፤ እንስት ወይም ተባእት
(2) በበጎችና በፍየሎች መካከል የተደረገው ልዩነት በበጎች ላት ያለው ስብ ምክንያት ነበር
(ሀ) ከመንጋው ጠቦት - እንስት ወይም ተባእት
(ለ) ከመንጋው ፍዬል - እንስት ወይም ተባእት
2. ሥነ-ሥርዓት
ሀ. የመስዋዕት አቀራረብ
(1) በመስዋዕቱ ላይ እጆችን ይጭናል
(2) በመገናኛ ድንኳን ደጃፍ ያርዳል።

(3) መስዋዕቱን መለየት ከሚቃጠል መስዋዕት ጋር አንድ አይነት ነበር
(4) በመሰዊያ ዙሪያ ደምን መርጨት
(5) ምርጡን ክፍል በመሰዊያው ላይ ማቃጠል
(ሀ) ስብ (በጎች ላት ስላላቸው) በረከትን ያሳያል
(ለ) ኩላሊት፤ የጉበት ክፍያ የስሜትና የፈቃድ መቀመጫን በምሳሌነት ያሳያል
(ሐ) ጮማው ክፍል በአቀራቢው የሚቃጠል መስዋዕት ላይ ወይም በማለደው የጠቦቱ መስዋዕት ላይ ይደረጋል

ለ. የምስጋና መስዋዕት የሚያጠቃልለው (7:11-14)
(1) በዘይት የተለወሰ የቂጣ እንጎቻ፥
(2) በዘይትም የተቀባ ስስ ቂጣ፥
(3) በዘይትም የተለወሰ መልካም ዱቄት

3. የካህኑ ድርሻ፤ ፤ 7:28-34
ሀ. ካህኑ ፍርምባው ይወዘውዘዋል
ለ. መወዘወዙም መስዋዕቱን ባቀረበው እጅ እና ካህኑ ላይ ማድረግን ያጠቃልላል፡፡ መስዋእቱ ለእግዚአብሔር መቅረቡን እንዲሁም እግዚአብሔር በካህኑ እጅ በኩል መቀበሉን ያመለክታል፡፡
ሐ. ቀኝ ወርቹን ለካህኑ ይሰጣል
መ የማንሣት ቁርባን ወደ እግዚአብሔር ይነሳና ካህኑ መልሶ ይቀበለዋል ቁ 14

4. የመስዋእት አቅራቢው ድርሻ፤ 7:15-18
ሀ. ለምስጋና የሚሆነው የደኅንነት መሥዋዕት ሥጋ በሚቀርብበት ቀን ይበሉታል ፤ቁ 15
ለ. የቍርባኑም መሥዋዕት የስእለት ወይም የፈቃድ ቢሆን፥ መሥዋዕቱ በሚቀርብበት ቀን ይብሉት ከእርሱም የቀረውን በነጋው ይብሉት ቁ 16
ሐ. እነዚህ ሁሉ ለእግዚአብሔር የሚሰጡ ሳይሆኑ እግዚአብሔር ለካህኑ የሚሰጠው ነው
መ. በዚህ መስዋዕት ውስጥ በምሳሌነቱ እግዚአብሔር ከአቅራቢው እና ከቤተሰቡ ጋር እንዲሁም ከጓደኞቹ ጋር ይበላል፡
ሠ. ይህ መስዋዕት የታደሰውን ህብረትና ግንኙነት ያጠናክራል፡፡

መ. ሌዋዊያን 4:1-5:13 (6:24-30) የኃጢአት መስዋዕት

1. መግቢያ
ሀ. ይህ ስርዬት ዋና ነገር ከሆነው የመጀመሪያ መስዋዕት ነበር።
ለ. ይህ መስዋዕት በሰው እና በእግዚአብሔር መሀከል ያለውን ኪዳን እንደገና ያድሳል። ህብረትን ያድሳል
ሐ. ይህ መስዋዕት የሚያካትታቸው:-
(1) ባለማወቅ ለተፈጸሙ ኃጢአቶች
(2) ድንገት ለተፈጸሙ ኃጢአቶች
(3) በስሜት ለተፈጸሙ ኃጢአቶች
(4) በስህተት ለተፈጸሙ ኃጢአቶች
(5) ሆን ተብሎ በእግዚአብሔር ላይ በማመጽ ለተፈጸሙ ኃጢአቶች ስርዬት አያስገኝም።
እያወቁ ችላ በማለት ታስቦበት ለተደረጉ ኃጢአቶች መስዋዕት የለም (ዝ.ከ. ዘኍ 15:27-31)።

2. ትርጉም
ሀ. ይህ መስዋዕት ስለኃጢአት በደለኝነትንና ቅጣትን ይደመስሳል።
ለ. ይህ በእግዚአብሔር በኩል ጸጋን እንዲሁም በሰው በኩል እምነትን ይፈልጋል።
ሐ. በተልመዶ በሚደረግ የመስዋእት ስርአት ብቻ የሚገኝ ነገር የለም። መስዋዕት። በድርጊቱ በስተጀርባ የመስወዋእት አቅራቢው እምነት አስፈላጊ ነው።
መ. አህንም፤ መስዋዕት ከአቅራቢው ስነ-ሥርዓታዊ ልማድ በላይ ነበር። ለርሱ አንድ ነገር ያደርጋል። በእግዚአብሔር መሀከል ያለውን ኪዳን እንደገና ያድሳል።
ሠ. ሥነ-ሥርዓት በእግዚአብሔር የተሰጠ ካሳ ነበር እነጂ የግለሰቡን እምነት የሚተካ አልነበረም።
ረ. እግዚአብሔር እምነት አብሮት ያልሆነውን ማንኛውንም ሃይማኖታዊ ሥነ-ሥርዓት ይቀወማል ኢሳ 1:10-20፤ አሞጽ 5:21-24፤ ሚክ 6:6-8

3. ሥነ-ሥርዓት
ሀ. ለሊቀ ካህኑ፤ ቁ 3-12
(1) ሊቀ ካህን - የተቀባ ካህን
(ሀ) ህዝቡን በተሳሳተ መንገድ በመምራት ፤ ኃጢአት
(ለ) በግልተፈጥሮ፤ ኃጢአት
(ሐ) ሊቀ ካህኑ፤ የማህረሰቡ መንፈሳዊ ጉዳይ ተወካይ ይሆናል። ኃጢአትን ቢያደርግ፤ ሁሉም በርሱ ኃጢአት ያደርጋል። አይሁዶች በጋራ ቅጣት ላይ ያለቸው አመለካከት ይህ ነበር (ዝ.ከ. ኢያ 7፤ ሮሜ 5:12)።
(2) ቅደም ተከተል
(ሀ)ሊቀ ካህኑ ነውር የሌለበት ወይፈን ወደ መሰዊያው
(ለ) በራሱ ላይ እጁን ይጭናል
(ሐ) ሊቀ ካህኑ እንስሳውን ያርዳል
(መ) ሊቀ ካህኑ በመጋረጃው ፊት 7 ጊዜ ይረጫል
i ይህ መገናኛውን ድንኳን ያነጻል

ii በምሳሌነቱ ወደ እግዚአብሔር መንገድን ይከፍታል፡፡
iii በዕጣን መሠዊያው ቀንዶች ላይ ከደሙ ይደርጋል
iv ከመስዋዕት የቀረውን በመሠዊያ በታች ያፈስሰዋል።
(ሠ) ሁሉም በመሰዊያው ላይ ይቀርባል
(ረ) ከየወይፈኑ የተረፈው ሁሉ ከሰፈሩ ወደ ውጭ አመድ ወደሚፈስስበት ወደ ንጹሕ ስፍራ ይወስደዋል፥ በእንጨትም ላይ በእሳት ያቃጥለዋል አመድ በሚፈስስበት ስፍራ ይቃጠላል ቁ 12፡፡

ለ. ማኅበር ቁ 13-21
(1) አትሥሩ ካላቸው ትእዛዛት ቢተላለፉ፤ ቁ 13-21።
(2) ቅደም ተከተሉ
(ሀ) የጉባኤውም ሽማግሌዎች ነውር የሌለበትን ወይፈን ያቀርባሉ።
(ለ) የጉባኤውም ሽማግሌዎች እጆቻቸውን በወይፈኑ ራስ ላይ ይጭናሉ ።
(ሐ) የጉባኤውም ሽማግሌዎች ወይፈኑን ያርደዱታል።
(መ) ካህኑም ጣቱን በደሙ ውስጥ ነክሮ በመጋረጃው ፊት ለፊት ሰባት ጊዜ ይረጨዋል።
i ይህ መገናኛውን ድንኳን ያነጻል
ii በምሳሌነቱ ወደ እግዚአብሔር መንገድን ይከፍታል፡፡
iii በዕጣን መሠዊያው ቀንዶች ላይ ከደሙ ይደርጋል
iv ከመስዋዕት የቀረውን በመሠዊያ በታች ያፈስሰዋል።
(ሠ) ሁሉም በመሰዊያው ላይ ይቀርባል
(ረ) ከየወይፈኑ የተረፈው ሁሉ ከሰፈሩ ወደ ውጭ አመድ ወደሚፈስስበት ወደ ንጹሕ ስፍራ ይወስደዋል፥ በእንጨትም ላይ በእሳት ያቃጥለዋል አመድ በሚፈስስበት ስፍራ ይቃጠላል ቁ 12፡፡

ሐ. ለመኰንን ፤ vv 22-26
(1) መኰንን (ገዥ) ቁ 22-26
(ሀ) የጎሳ መሪ
(ለ) በማህበረሰቡ ውስጥ ተጠያቂነትን የሚወስድ ሰው
(ሐ) ሽማግሌ
(2) ቅደም ተከተሉ
(ሀ) መኰንኑም ነውር የሌለበትን ተባት ፍየል ለቍርባኑ ያቀርበዋል
(ለ) መኰንኑም በፍየሉ ራስ ላይ እጁን ይጭናል።
(ሐ) መኰንኑም እንስሳውን ያርዳል።
(መ) ካህኑም ከኃጢአት መሥዋዕት ደም በጣቱ ወስዶ መሠዊያ ቀንዶች ያደርገዋል
(ሠ) ስቡ ሁሉ በመሠዊያው ላይ ያቃጠላል
(ረ) ካህናቱም የተረፈውን ይበላሉ።

መ. ለግለሰቡ፤ ቁ 27-35
(1) ለግለሰቡ- ኃጢአት እንዳደረገ ቢያውቅ እነዚህን መስዋዕቶች ማድረግ ይኖርበታል
(2) ቅደም ተከተሉ
(ሀ) ግለሰቡ፤ እንስት ፍየል ወይም በግ ያመጠል
(ለ) ግለሰቡ፤ እጁንም በኃጢአት መሥዋዕት ራስ ላይ ይጭናል
(ሐ) ግለሰቡ፤ የኃጢአትን መስዋዕት ያርዳል
(መ) ካህኑም ከደምዋ በጣቱ ወስዶ ለሚቃጠል መሥዋዕት በሚሆነው መሠዊያ ቀንዶች ላይ ያደርገዋል
(ሠ) ስቡንም ሁሉ ይወስዳል
(ረ) ካህናቱም የተረፈውን ይበላሉ።

ሠ. የኃጢአት መስዋዕት የሚያካትት ልዩ ሁኔታዎች ፤ 5:1-13 (እነዚህ በድንገት እና ባለማወቅ በቃልኪዳን በተሳሰሩ መሀከል  የተፈጸመ ኃጢአትን የሚያካትት ይመስላል
(1) ምስክር ቀርቦ የማይመሰክር ከሆነ (መረጃ መስጠት ባይቻል)፤ 5:1
(2) ርኩስ እንስሳ ቢነካ፤ 5:2
(3) የረከሰ ሰው ቢነካ ፤ 5:3
(4) ሳያስብ ቢምል 5:4
(5) ከላይ ላሉት ኃጢአቶች:
(ሀ) እንስት ፍዬል ወይንም በግ
(ለ) ሁለት የርግብ ግልገሎች ወይንም ዋኖስ
(ሐ)የኢፍ መስፈሪያ አሥረኛ ክፍል መልካም ዱቄት

ረ. የኃጢአት መስዋዕት ልማድ፤ 6:24-30
(1) ካህን የተረፈውን መብላት ይችላል።
(2) ደም ልብስን የነካው ቢሆን ልብሱ መታጠብ አለበት።
(3) ደሙ ከሸክላ የተሰራውን ዕቃ ቢነካ እቃው መሰበር አለበት።
(4) ደሙ ከነሐስ የተሰራውን ዕቃ ቢነካ ፤ እቃው የታጠብ ነበር።
(5) የሚቃጠል መስዋዕት ደሙ ወደቅድስተ ቅዱሳን የሚወሰድ ከሆነ ስጋው መቃጠል አለበት ከህናት እንዲበሉ አልተፈቀደም ነበር

ሰ. የኃጢአት መስዋዕት አስፈላጊነት
(1) እያወቁ ለተደረገው ኃጢአት መስዋዕት የለም— በድንገት እና ባለማወቅ ለተፈጸመ ኃጢአት ብቻ፤ 5:15፤ 18
(2) ይቅርታ ምን ያጠቃልላል:
(ሀ) የሰውን የእምነት ድርሻ
(ለ)እግዚአብሔር ድርሻ ምህረት ነው

ሠ. ሌዋዊያን 5:14-19 በደል ወይንም የመተላለፍ መስዋዕት
1. መግቢያ
ሀ. ግን የኃጢአት መስዋዕት ከተደረገው ኃጢአት ጋር ይያያዛል፤ የበደል መስዋዕት ደግሞ በቃል ኪዳን ከተሳሰሩት ጋር በተፈጸመው ጉዳት ላይና የሚገባውን ካሳ ከመክፈል ጋር ነበር የሚያያዘው።
ለ. የኃጢአትና የበደል መስወዕት በጣም ጠመሳሳይ ነበሩ
ሐ. የግለሰቡ መብት ከአሥርቱ ትዕዛዛት በ(ዘጸዓት 20፤ ዘዳግም 5)ላይ ተብራርቷል።
(1) ቤት
(2) የመልካም ጥርቅም
(3) ህይወት
መ. ይህ መስዋእት የመያተኩረው በወንድሞቻችን ላይ የተፈጸመውን በደል እና የጉዳቱን 1/5 ካሳ በላይ ዋጋ መክፈልን ነው።
2. መስዋእት የሚሹ ኃጢአቶች
ሀ በየእግዚአብሔር ላይ ወይንም የርሱ በሆነው ላይ
(1) በኩራት
(2) በኩር፤ 14-16
(3) አስራት
(4) በስህተት የተሰጠ ስጦታ
(5) የተሻለ ዋጋ ያለው ስጦታ
ለ. "ሰው ኃጢአት ቢፈጽም እና እንዳይደረጉ እግዚአብሔር የከለከላቸውን ማንኛውንም ነገር ቢያደርግ እና ባያውቃቸው እሰታሁንም እርሱ በደለኛ ነው በደሉን ይሸከም ዘንድ ይገባዋል።

ረ. የጥንቶቹ መስዋዕቶች ይቀርቡ የነበሩት
1. የተቆጡ አማልክትን ለመታረው
2. አማልክትን ለመመገብ
3. ከአማልክት ጋር ህብረት ለማድረግ
4. አማልክትን ለማመስገን
5. ይቅርታን ለማግኘት ወይንም ለእርቅ

▣ ***"የመሠዊያው ቀንዶች ይሰበራሉ"*** እነዚህ ቀንዶች ሊያመለክቱ የሚችሉት (1) የእንስሳ ቀንዶች ለኃይል እንደ ምሳሌ ነው (ለምሳሌ ፤ ኤር 48:25፤ ዳን 8:7፤ ዘካ 1:18-20) ወይም (2) ያመስዋዕት ለእግዚአብሔር ከፍ ይደረግ እንደነበርም በምሳሌነት ያሳያል፡፡ የመስዋእት እንስሳ ደም ተወስዶ በቀንዶቹ ላይ ይቀባል (ዝ.ከ. ዘጸ 29:12፤ ለዋ 8:15)፡፡ ይህ የጣዖት አምልኮ ስርአት ያ ኃጢአት ህይወትን የሚጠይቅ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ደም ህይወትን በምሳሌነት ያሳያል (ዝ.ከ. ሌዋ 17:11፤14)፡፡ ስለዚህ እነዚህ ቀንዶች የመሰዊያው እጅግ ቅዱሱ ክፍል ነበሩ፤ ይህ ሐረግ ስለዚህ ሊሆን የሚችለው (1) መስዋዕታቸው ብርታት የለውም ወይንም (2) እንዚህ ቀንዶች እንደ ደህንነት ስፍራ ያገለግሉ ስለነበር(በዘጸ 21:14፤ እና ለየት ባለመልኩ በ1ነገ 1:50፤ 2:28 ውስጥ ተዘርዝረው እንዳሉ)፤ አሁን ግን የደህንነት ቦታ ሊሆኑ አይችሉም!

**3:15 "የክረምቱንና የበጋውን ቤት እመታለሁ በዝሆንም ጥርስ የተለበጡት ቤቶች"** እነዚህ ሐረጎች የሚያመለክቱት (1) ብዙ አይነት የሀብታሞች መኖሪያዎች ቤቶችን ያመለክታል (አንድ ምሳሌ የአከአብ ሁለቱ ቦታዎች፤ ዝ.ከ. 1ነገ 21:1፤18፤ NJB "ብዙትላልቅ ቤቶች") ወይንም (2) ሁለት የመጋዝን ቤቶች፤ ምድርቤቱ ለክረምት ሰገነቱ ለበጋ የሚያገለግል (TEV፤ "ማንኛውም ትልቅ ቤት")፡፡ ከነዚህ ብዙዎቹ በዝሆን ጥርስ የተሰሩ ነበሩ (ለምሳሌ ፤ ያጌጡ፤ ዝ.ከ. 1 ነገ 10:18፤ 22:39) የግብፃዊያንና የአሦራዊያን ማልከት፡፡ እስራኤል ራስዋን (1) በቁሳቁስና (2) በጣዖት ራስዋን ጥላለች!

▣ **"ታላላቆችም ቤቶች ይፈርሳሉ"** የሰባ ሊቃናት ትርጉም ትርጉም "ሌሎች ቤቶች ሁሉ" የሚል ትርጉም አለው፡፡ የእብርይስጡ ቃል (BDB 912 I) (1) "ታላቅ" ወይንም (2) "ብዙ " ማለት ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ሀረግ የተለየ ዓይነት ቤት ሳይሆን የማጠቃለያ ዐረፍተ ነገር ይመስላል፡፡

**"ይላል እግዚአብሔር"** ከላይ በቁ 11 ላይ ያሉትን ማስታወሻዎች ተመልከት፡፡ በዚህ በአሞጽ ክፍል ውስጥ የዚህ መልእክት መለኮታዊ ሥልጣን በንደዚህ አይነት ወይንም ተመሳሳይ ሀረግ ያለመቋረጥ ይቀጥላል (ዝ.ከ.3:1፣5፣6፣8፣910፣11፣12፣13፣15; 2:1፣3፣4፣6፣16;4:3፣5፣6፣8፣10፣11; 5:17).)

# አሞፅ 4
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|
| የእስራኤል ኃጢአት ቅጣት (3:9-4:5) | የእስራኤል ኃጢአተኝነትና የእግዚአብሔር ቅጣት (3:1-6:14) | የሰማርያ ክፉ ቀን (3:9-4:3) | እስራኤል ማስጠንቀቂያና መስፈራሪያ ተሰጣት (3:1-6:14) |
| | የእስራኤል የተትረፈረፈ ድሎትና ከንቱ ኃይማኖተኝነት 3:1-2 | 3:12-4:3 | በሰማሪያ ሴት ላይ |
| 4:1-3 | 4:1-3 | | 4:1-3 |
| | | የእስራኤል መማር አለመቻል | የእስራኤል ራስን ማታለል እልህና ቅጣት |
| 4:4-5 | 4:4-5 | 4:4-5 | 4:4-5 |
| እስራኤል ማስተካከያ መቀበል አልቻለችም 4:6-11 | 4:6 | 4:6-11 | 4:6-11 |
| | 4:7-8 | | |
| | 4:9 | 4:9 | 4:9 |
| | 4:10 | 4:10 | 4:10 |
| | 4:11 | 4:11 | 4:11 |
| 4:12-13 | 4:12 | | 4:12 |
| | | | ምስጋና |
| | | 4:13 | 4:13 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ vii ተመልከት)**

*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ

2. ሁለተኛው አንቀጽ

3. ሦስተኛ አንቀጽ

4. ወዘተርፈ

**የቃልና የሐረግ ጥናት**

**አሞፅ 4:1-3**

**1 በሰማርያ ተራራ የምትኖሩ፥ ድሆችንም የምትበድሉ፥ ችጋረኞችንም የምታሰጨንቁ፥ ጌቶቻቸውንም።**

**አምጡ እንጠጣ የምትሉ እናንተ የባሳን ላሞች ሆይ፥ ይህን ቃል ስሙ።**
**2 ጌታ እግዚአብሔር፦ እናንተን በሰልፍ ዕቃ፥ ቅሬታችሁንም በመቃጥን የሚወስዱበት ቀን፥**
**እነሆ፥ በላያችሁ ይመጣል ብሎ በቅዱስነቱ ምሎአል።**
**3 እያንዳንዳችሁ በየፊታችሁ በተነደለ ስፍራ ትወጣላችሁ በሬማንም ትጣላላችሁ፥ ይላል እግዚአብሔር**

**4:1-13** የዚህን ምዕረፍ ይዘት አስተውል፡፡

1 አሞፅ የእስራኤልን ባለፀጋ ሴቶች በማስመልከት ይናገራል (ይህም ማለት፤ሁሉንም የእስራኤል ማህበረሰብ በዝባዥ አካላትን ነው፡፡v ከ1-3

2 የያህዌ እምነታቸውን በተመለከተ የሰጠው መራራ ምላሽ፣ v ከ 4-5

3 የያህዌ በዘዳ27-29 ላይ ያሉትን እርግማኖች መስተላለፍ፤ነገር ግን አሁንም ቢሆን ንስሃ አለ መግባታቸውን v ከ 6-11

4 ያህዌ በግለሰብ ገረጃ እና በአጠቃላይ ለህብረተሰቡ የሰጠው ማስጠንቀቂያ v 12

5 የአሞፅ ስለ ፈጣሪነቱን እና ትክክለኛ ፍርድ ሰጪነቱ ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረቡ v 13

ይህ አጠቃላይ ማብራሪያ የሚያሳየን የነብያትን ግጥምያዊ መልዕክት መመርመር ምን ያህል አሰቸጋሪ እንደሆነ ነው፡፡ነብዩ ሲናገር አስተያየት እየሰጠ እንደሆነና እና ያህዌ የሰጠውን መልዕክት እየጠቀሰ እንደሆነ መለየት በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ የመልዕክቱ መገለጥ በጣም ጠንካራ ከመሆኑ የተነሳ የነብዩ ቃላት ከያህዌ ቃላት ጋር የተዋሃደ ነበር! መልዕክቱን ከመዘርዘር ይልቅ አጠቃላይ መልዕክቱ የአንባቢያን ስሜት ላይ የሚያመጣውን ለውጥ ማየት የበለጠ ጠቀሜታ አለው!

**4:1 *"ይህን ቃል ስሙ"*** *ግሱ* (BDB 1033፣ KB 1570) የ Qal IMPERATIVEIMPERATIVES (*ትዕዛዝ አንቀፅ*) ነው(በ 3:1 ላይ ያለውን መስታወሻ ተመልከት፡፡ግሱ በተጨማሪም በ 5:1 ላይ ተገልፅዋል) የዚህ አይነት የነብያት አገላለፅ በተደጋጋሚ ጊዜ በአሞፅ ውስጥ ተጠቅሷል፡፡(ለምሳሌ 3:1፤ 4:1፤ 5:1) ይህ እግዚአብሔር ለሕዝቦቹ የላከው መልዕክት ነው፡፡ የቃልኪዳን መተላለፍ ውጤቱ የቃልኪዳን ፍርድ ነው (ዝ.ከ. ዘዳ27-29)፡፡

▣ **"የበሳን ላሞች"** ይህ አሞፅ ለራሳቸው ድሎት ሲሉ ደሃዎችን የሚበድሉ የማህበረሰቡ ቀነኛጅት ሴቶችን ለመኮነን የተጠቀመበት ነው፡፡ Bashan በገሊላ ባህር በሰሜን ምዕራብ ከ ሄርሞን ተራራ እስከ ያርሙክ ወንዝ ድረስ ያለ ቦታ ነበር፡፡ይህ ቦታ በሚያምሩ (በደለቡ) ጋማ ከብቶች የታወቀ ቦታ ነበር (ይህም ማለት፣ የባለፀጋ ሚስቶች) ይህ መጥፎ(የተቃርኖ) ዓረፍተነገር አይደለም ነገር ግን በደንብ የተያዙ እና በደንብ የተቀለቡ ፍላጎትን የሚያረኩ ከብቶችን የሚገልፅ ዘይቢያዊ ዓረፍተ ነገር ሊሆን ይችላል፡፡ፍላጎትን ማርካት የደሃውን ጉልበት በመበዝበዝ የሚገኝ ትርፍ ሆኖ ነበር(BDB 195)! በሌላ ጎኑ ደግሞ ለመታረድ የተዘጋጁ የደለቡ ከብቶችን ሊያመለክት ይችላል! አሞፅ ከበጎች ጠባቂነቱ ባገኘው ልምድ መሰረት ብዙ ዘይቢያዊ አነጋገሮችን ይጠቀማል፡፡

አሁንም ቢሆን ሌላ ተጨማሪ የትርጉም አማራጭ አለን፡፡ይህም ነውር ያለበትን የግብረ ስጋ ግንኙነት ጓደኝነትን ሊያመለክት ይችላል፡፡

1 "ሚስቶች" ተብለው የማይጠሩ

2 በሰማሪያ ተራራ ላይ የሚባል (በቤቴል ለተቋቋመው መሰዊያ አመልካች ሊሆን የሚችል)

3 ወንዶቻቸው "ባሎች" ተብለው አይጠሩም ነገርግን "ጌቶች" ተብለው ይጠራሉ (v 1c)

4 ላሞች በቀድሞዋ እስራኤል እና ግብፅ የብዙህነት እና የጥንካሬ ሐሰተኛ አማልክትን ማመልከቻ ሆነው ይታዩ ነበር፡፡(ዝ.ከ. ዘጽ 32) ላሞቹ ለባአልም ምልክት ሆነው ነበር (ይህም ማለት በዳን እና በቤቴል የነበሩት ወርቃማ የጎሽ ምስሎች)

5 በተዘዋዋሪ በ 2:7-8 ውስጥ አመንዝራነትን የማምለክ (የማዝወተር) ተግባራት ተጠቅሷል፡፡እግዚአብሒር በቅዱስነቱ መማሉ 2:7ን ሊያመለክት ይችላል፡፡

▣ **"በሰማሪያ ተራራ ላይ"** ይህ በደንብ የተዘጋጀውን የእስራኤልን ዋና ከተማ ያመለክታል፡፡ይህም ኦማሪ (Omri )በ መሳ (mesa )ጫፍ ላይ የገነባው ነበር፡፡ይህ ቦታ ወደ ጫፍ የሚወስዱ ደረጃዎች የነበሩት ሲሆን አንድ ዋና መግቢያ ብቻ ነበረው፡፡

▣ **"ድሆችንም የምትበድሉ ችጋረኞችንም የምታስጨንቁ"** እነዚህ ሁለቱ *Qal PARTICIPLE (ቦዝ አንቀፅ) S (ቦዝ አንቀፅ)* (BDB 798፣ KB 897 and BDB 954፣ KB 1285) ተያያዥነት ያላቸው ሲሆን የባለፀጋ ሴቶችን ተግባራት ይገልፃሉ፡፡ ያህዌ በልዩ ሁኔታ (ይህም ማለት፣ ከሌሎች የጥንት ምስራቅ አቅራቢያ ህግ ረቂቆች ጋር በማወዳደር) በእነዚህ ሰዎች ላይ ስለነበረው ቃል ኪዳን መጨነቁ (በዋናነት ዘዳግም "ወላጅ አልባ እና ባል የሞተባቸው የማያታወቁ" ዝ.ከ. 10:18፤ 14:29፤ 16:11፤ 24:14፣17፣19፤ 26:12፣13፤ 27:19) ስለዚህ ይህ ለሙሴ ህግጋት ሌላ ፍንጭ ሰጪ ነው፡፡ነብያቶቹ ከባርኮታቸው እና ከእርግማናቸው ጋር በማያያዝ የሙሴን የቃል ኪዳን ህግጋት(ዝ.ከ. ኤር 7:6) እንዲጠበቁ በተደጋጋሚ አሳወቁ እንጂ አዲስ የስነምግባር ስርዓት አልፈጠሩም ወይም አላስተዋወቁም ነበር፡፡(ይህም ማለት ዘዳ 27-29)

▣ **"ጌቶቻቸውንም"** ይህ ቃል ለባል የተለመደ አገላለፅ አይደለም፡፡ቃሉ የማይዘወተር ጥንታዊ ሲሆን ትርጉሙም "ጌታ"(BDB 10)ማለት ነው፡፡እዚህ ላይ ግን በ"ባል" ስሜት ነው የቀረበው (ለምሳሌ ዘፍ 18:12፤ መሳ 19:26-27) "ጌቶቹ" ትዕዛዝ ተላልፎላአዋል ስለዚህ የአባባሉ ወርቅ እዚህ ላይ ተገልፅዋል!

▣ **"አምጡ፤እንጠጣ የምትሉ"** ይህ ሃረግ ሁለት የትዕዛዝ ግሶች አሉት (BDB 97፣ KB 112፣ *Hiphal* IMPERATIv E and BDB 1059፣ KB 1667፣ Qal COHORTATIVE) እነዚህ ሴቶች መጠጣት እና የራሳቸውን ስሜት ማርካት የተለመደው ተግባራቸው ሲሆን አኗኗራቸው በድሎት የተንፈላሰሰ ነበር፡፡የእነዚህ ሴቶች መርህም "በማንኛውም ወጪ ለኔ ደጋግመህ ቅዳ!" ሳይሆን አልቀረም ነበር፡፡

**4:2 "ጌታ እግዚአብሔር በቅዱስነቱ ምሎአል"** ግሱ(BDB 989፣ KB 1396) *Niphal* PERFECT ነው፡፡ይህ እግኢአብሔር በረሱ ስም የማለበት ብዙ የማይጠቀስ እና የሚያስፈራ ዓረፍተ ነገር ነው፡፡(ዝ.ከ. 6:8፤ መዝ 89:35) ያህዌ ስርዓትን የሚጠብቅ አምላክ ነው፡፡ መዋደድ እና እውነተኛ ህብረት ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ ሳይሆን የሚያስፈልገው ከሌሎች የቃል ኪዳኑ አጋሮች ጋርም አስፈላጊ ነው፡፡ እውነተኛ መፅሐፍ ቅድሳዊ እምነት አግድምያዊ ባህሪ (እግዚአብሔር) እና ቀጥተኛ ባህሪ (ሌሎች) አለው፡፡

▣ **"የሚወስዱበት ቀን እነሆ በላያችሁ ይመጣል"** ይህ የፍረድ ቀንን የሚያመለክት ነው፡፡በ 2:16 ላይ ያለውን ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት፡፡ ይህም የሚያመለክተን፤ (1) "በዚያች ቀን" 2:16፤ 8:3፣ 9፣ 13፤ 9:11 እና (2) "የእግዚአብሐርን ቀን" በ 5:18 እና 20 ውሰጥ እንዳለው፡፡ ይህ አባባል በቀደምት ነብያትም የተለመደ ነው፡፡ እስራኤል የያህዌን ጉብኝት የእግዚአብሐርን በረከት የምትቀበልበት ቀን እንደሆነ ታያለች፤ ነገር ግን አሞፅ ቀኑ የእግዚአብሔር ቀጣ እና ፍርድ የሚገለፅበት እንደሆነ ያየዋል፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB | "ስጋመቃጥኖች የአሳ መቃጥኖች" |
| NKJv | "አሳመቃጥን የአሳ መቃጥኖች" |
| NRSv | "መቃጥኖች የአሳ መቃጥኖች" |
| TEv | "መቃጥኖች በመቃጥን ላይ ያለ ዓሳ" |
| NJB፣ Young's Lit | "መቃጥኖች የአሳ-መቃጥኖች" |
| JPSOA | "በቅርጫቶች ውስጥ በአሳ ቅርጫቶች ውስጥ" |

የመጀመሪያው ቃል (BDB 856 I፣ KB 1036) "መቃጥኖች" በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኘው እዚህ ላይ ብቻ ነው፡፡ ይህ ቃል ከእብራዊያን "ሹል ጫፍ" "ጩቤ፣" ወይም "ጦር" ዋና ቃላት ጋር የሚዛመድ ይመስላል፡፡ በርግጥ እነዚህ ማህበረሰቦች ሴቶቹ እና ልጆቻቸው በአሶራዊያን ወታደሮች መቃጥን በታችኛው ከንፈራቸው ላይ ይቀመጥባቸውና ራቁታቸውን (ሰባ ሊቃናት ትርጉም)በአንድ ላይ እርስ በርሳቸው ታስረው ልክ ተረበሸ የከብት መንጋ ከከተማ እየተነዱ እንዲወጡ ይደረግ ነበር፡፡ ሁለተኛው ቃል (BDB 186፣ KB 215) ከአንድ አሳ ማጥመጃ መሳሪያ ጋር የሚዛመድ ነው፡፡ ምክንያቱም ከ"መቃጥኞች" ጋር ተያያዥነት ስላለው፡፡ ኤርሚያስ (ዝ.ከ. 16:16) "ዓሳ ማጥመድ"ን የፍርድ ዘይቢያዊ አነጋገር አድርጎ ተጠቅሞበታል፡፡ ቃሉ ዘይቢያዊ ነው ወይስ ቀጥተኛ?" ይህ ስለዚህ ቁጥር አንድ ሰው ሊጠይቀው የሚችለው ጥያቄ ነው፡፡አሶራዊያን መቃጥኖችን ወይም በታችኛው ከንፈር የሚደረግ ቀለበትን በመጠቀም ስደተኞችን ወደ ሃገራቸው በሚመልሱበት ጊዜ እንደ ማስፈራሪያ በመቁጠር ያያይዟቸው ነበር፡፡(ዝ.ከ. 2ኛ ዜና 33:11 የአሶራዊያን እና ዕብ 1:15 የባቢሎናዊያን)

REB ሁለቱንም ቃላት በተለያየ መልኩ ይተረጉመዋል፡፡የመጀመሪያው እንደ "ሽፋን፣" ሲተረጉመው ይህም ጥንታዊ ዕትሞች ቃሉን ከተረጎሙት ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡

1. ሰባ ሊቃናት ትርጉም /LXX/ - "የጦር መሳሪያዎች"
2. ፔሽታ - "የጦር መሳሪያዎች"

ሁለተኛውን ቃል "የዓሳ-ቅርጫት" ብሎ ይተረጉመዋል፡፡ (ዝ.ከ. NET መጽሐፍ ቅዱስ) ሰባ ሊቃናት ትርጉም "ማሞቂያ ጋን " የሚል ትርጓሜ አለው፡፡የእብረዊያን ዋና ቃል ብዙም ያልተለመደ ስለሆነ ትርጉሙ ላይ እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡ሆኖም ግን ታሪካዊ እና ፅሑፋዊ ዓውዱን ለመጠበቅ ተመሳሳዩን ዋና ቃል እና ከዚሁ ቃል የተገኘውን ቃል ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ ዋናው ቁም ነገር ግን ብጥብጡ እና አሳፋሪው መባረር ነበር!
ለኔ ግን ምናቡ የሚናገረው ስለ "Bashan ላሞች" ስለ ሆነ እንዲሁም ደግሞ አሞፅ የገጠር ኑሮ ያሳለፈ ስለነበር ቃሎቹ ከከብት እገዳ ጋር የሚዛመዱ ይመስለኛል፡፡ አሞፅ ዘይቤዎቹን ቀይሯቸው ሊሆን ይችላል፤ነገር ግን የእብረዊያን ቃሎች ብዙም ያልተለመዱ ስለሆነ ከብቶችን ለመቆጣጠር እና ለማንቀሳቀስ "መግፋት" እና "መቃጥን" ምርጥ የሚሆኑ ይመስላል፡፡

▣ **"እንዳንዳቹ"** ይህ "መጨረሻ"(BDB 31)የሚለው ቃል ሊያመለክት የሚችለው

1. 1 ከናንተ መጨረሻ የሚቀረው(ዝ.ከ. 1:8፤ 8:10፤ 9:1)
2. ጥቂት ቀሪዎች
3. መጪ ትውልዶች ወይንም ዝሪያ

ዓውዱ የሚያመለክተው ቁጥር #1ን ነው፡፡

**4:3 "በየፊታችሁ"** ይህ "በየፊታችሁ" የሚለው ሀረግ የከተማውን መከላከያ ግንብ ሙሉ ለሙሉ የሚውደም መሆኑን የሚገልፅ ዘይቤ ነው፡፡ህዝቦቹ ባጠቃላይ ታስረው ወደ ሩቅ ምስራቅ ተባረዋል፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB | "በሬ ማገንም ትጣላላችሁ" |
| NKJv | "ወደ ሬማንም ትጣላላችሁ" |
| NRSv | "ወደ ሬማን መሸቀንጠር" |
| TEv | "ትወረወራላችሁ" (ቃል ተዘሏል) |
| NJB | "ወደ ሬማንም ትነዳላችሁ" |
| NAB | "ወደ ጭቃ ውስጥ ትጣላለችሁ" |

| | |
|---|---|
| JPSOA | "በተከለከለው ክምር ላይ መሽቀንጠር" |
| REB | "በእንስሳት እዳሪ ክምር ላይ መወርወር" |

ይህ ግስ (BDB 1020፣ KB 1527፣ *Hiphil* PERFECT) በተደጋጋሚ ጊዜ እግዚአብሔር ሓጥያተኞችን ከእሱ *መገኘት* የሚያስወጣቸው ስለመሆኑ አመልካች ሆኖ ይታያል፡፡(ዝ.ከ. 2ኛ ነገ 17:20፤ 24:20፤ መዝ51:11፤ 71:9፤ 102:10፤ ኤር 7:15) ሆኖም ግን በጥሩ ጎኑ ደግሞ በቃል ኪዳን ስምምነት መልኩ ሲጠቀስ በ 2ኛ ነገ 13:23 ውስጥ እናያለን፡፡ ምንም እንኳን የአሞፅ ቀጥተኛ ዓውድ ስለ አሶራዊያን ማስወጣት ቢያመለክትም ቃሉ በራሱ መለኮታዊ ቁጣን አመልካች ነገር አለው፡፡ አሶራዊያን እስራኤልን ያስወጧት ባላቸው ኃይል ሳይሆን እስራኤል በሰራችው ሃጥያት እና በእግዚአብሔር ፍርድ መሰረት ነው!

በዚህ ሃረግ ትርጉም/የቃላት አደራደር ላይ ብዙ ጥናቶች ሲደረጉ ቆይቷል፡፡

1. 1 ቦታው ያልታወቀ የአንድ ቦታ ስም ነው፡፡ሰብቱአጅንተ ይህን የሬሞን ወይም የሮማን ተራራ ብሎ ይጠራዋል፡፡
2. የሄርሞን ተራራ የተሳሳተ የፊደል አደራደር ነው፡፡(ዝ.ከ. NJB and UBS፣ *Translator's Handbook*፣ ቁ 234) እናም በዚህ ምክንያት ቀድሞ ከነበረው ሃረግ "ደማስቆ ጀርባ" ከሚለው ጋር ተያያዥነት ሲኖረው ወደ አሶራዊያን በሚወጡበት መንገድ ላይ ነው ለማለት የተፈለገውም፡፡
3. JPSOA እና REB ይህን የእብራዊያን ፅሑፍ ወደ ተመሳሳዩ የእብራዊያን ቃል (BDB 199) "የእንስሳት ዕዳሪ ክምር" ብለው አሻሽለውታል፡፡(ዝ.ከ. ኢሳ25:10)፣ይህም በዚህ ዓውድ ውስጥ የሞተን አካል መጣያ ቦታ ሊያመለክት ይችላል(ስለዚህ "መቃጥኖቹ" የሞቱትን አካሎች ለማመላለስ ይጠቀማሉ)፡፡ አተረጓማቸው ሲነበብ "በተከለከለው ክምር ላይ መሽቀንጠር"
4. የአረማይክ Targum እና የተወሰኑ የሶሪያ ትርጉሞች "ከአርሞኒየም ተራሮች ጀርባ" ሲሉት ይህም ከ5:27 ጋር ተያያዥነት አለው፡፡
5. የእብረዊያን ፅሑፍ በተለየ መንገድ በመከፋፈል "አ የጭቆና ተራራ ውጣ" የሚለውን ማግኘት ይቻላል፡፡(ዝ.ከ. NIv STUDY BIBLE የግርጌ ማስታወሻ ቁ 1352)፡፡

▣ **"ይላል እግዚአብሔር"** ይህ ተደጋጋሚ ሃረግ 1:5፣8፣15፤ 2:3፣11፣16፤ 3:10፣13፣14፤ 4:3፣5፣6፣8፣10፣11 እና 5:17 ከእነዚህ ዓረፍተነግሮች ጀርባ የማን ስልጣን ፤ኃይል እና ጉልበት እንደቆመ ያሳያል፡፡

## አሞፅ 4:4-5

**4 የእስራኤል ልጆች ሆይ፥ ይህን ወድዳችኋልና ወደ ቤቴል ኑና ኃጢአትን *ሥሩ***
**ወደ ጌልገላ ኑና ኃጢአትን አብዙ በየማለዳውም *መሥዋዕታችሁን*፥ በየሦስተኛውም ቀን *አሥራታችሁን* አቅርቡ**
**5 እርሾ ካለበትም የምስጋናውን *መሥዋዕት* አቅርቡ፥ በፈቃዳችሁም የምታቀርቡትን አውጁና አውሩ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፦**

**4:4 "ኑና"** ይህ(BDB 97፣ KB 112) *Qal IMPERATIVEIMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ) IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)* ነው፡፡ ቁጥር 4 እና 5 ተከታታይ የሆነ *IMPERATIVE ትዕዛዝ አንቀፅ)* አላቸው፡፡(3 *Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)* ፤ 3 *Hiphil* ትዕዛዝ አንቀፅS IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ) )፡፡

▣ **"ቤቴል ጌልገላ"** እነዚህ የቀድሞ ጣኦት አምልኮ ማዕከላት ናቸው፡፡(ቤቴል ዘፍ 12:8፤ 28:10-22 እና ጌልጌላኢያ 4)፡፡
እነዚህ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ18ኛው ክፍለ ዘመን ታዋቂ የአምልኮ ቦታዎች ነበሩ፡፡(ዝ.ከ. ሆሴ 4:15፤ 9:15 እና 12:11) ቁጥር 4 እና 5 ከፍተኛ ወቀሳዎች ናቸው (ዝ.ከ. 5:5-6)፡፡
ከ ቁ 4-5 ያሉት የያህዌ የወቀሳ ዓረፍተ ነገሮች በሚከተሉት ምክንያቶች ሊሆን ይችላል፡፡

1. የእስራኤል በመጥፎ የኑሮ ዘይቤ እየኖሩ የተለምዶ አምልኮ መውደዳቸው
2. እግዚሃብሔር እየሩሳሌምን የተቀደሰች ከተማ አድርጎ በሚመርጣት ጊዜ እስራኤላዊያን በነብያቶች የተጣለባቸው ክስ (ለምሳሌ፣ ዘዳ 12:5፣11፣13፣14፣18፣26፤ 14:23፣24፣25፤ 16:2፣6፣7፣16)፡፡

በዚህ ዓውድ ወስጥ አማራጭ#1 ምርጥ ምርጫ ነው፡፡
እዚህ ቦታ ላይ የትኛዋ ጌልገላ እንደ ተጠቀመች እርግጠኛ መሆን አስቸጋሪ ነው፡፡ አራት የተለያዩ ጌልገላዎች አሉ፡፡(ይህም ማለትይህም፣ "ክብ" of stones፣The Anchor Bible Dictionary ቅጽ 2፣ ገጽ 1022-23 ተመልከት) Hard Sayings of the Bible እንደሚሉት ይህ ቦታ ለቤቴል የቀረበ ሲሆን Anchor Dictionary #2) ነገር ግን በኢያሱ 4 ውስጥ የተጠቀሰው አይደለም፡፡

▣ **"በየማለዳውም መስዋዕታችሁንም በየሦስተኛውም ቀን አሥራታችሁን አቅርቡ"** ይህን ቀጥር በተመለከተ ሦስት ዓይነት ጥናቶች አሉ፡፡ (1) ከቅጥ ያለፈ የሃይማኖት ስርዓታቸውን ያሳያል (2) ወደ ተመረጡ የዓምልኮ ቦታዎች በመሄድ የተለመደ የአምልኮ ስርዓት ያካሂዱ እንደነበር ያሳያል (ይህም ማለት በመጀመሪያው ቀን ቦታው ይደርሳሉ፤በሁለተኛው ቀን መስዋዕታቸውን ያቀርባሉ፤በሶስተኛው ቀን ደግሞ አስራታቸውን ይሰጣሉ ዝ.ከ. REB)፤ ወይም (3) ለአንድ ደሃ አስራት ማለት የሦስተኛው ዓመት አስራት ነው፡፡(ይህም ማለት፤ ለሙሴ የቃል ኪዳን ህግ ሌላ ማጣቀሻ ነው ዝ.ከ. ዘዳ14:28፤ 26:12፣ "ቀን" ምናልባትም በ"ዓመት" ሊታሰብ ይችላል)፡፡

**4:5 "እርሾ ካለበትም የምስጋናውን መስዋዕት አቅርቡ"** ይህን ቁጥር በተመለከተ ሁለት ዓይነት ጥናቶች አሉ፡፡ (1) እርሾ የተከለከለ ነበር ስለዚህ ይህም አለመታዘዛቸውን ያሳያል(ዝ.ከ. ዘጽ 23:18፤ 34:15፤ ዘሌ2:11፤ 6:17) ወይም (2) "የእንጀራ መስዋዕት" የሚል አወንደሆነ መታወቅ አለበት(ዝ.ከ. NRSv ፣ TEv )፣ ይህም አስፈላጊ አልነበረም ነገር ግን የበለጠ መሰጠትን ያመለክታል፡፡ በዘሌዋዊያን 7:13 ውስጥ እርሾ ለደህንነት መስዋዕት እንዲሆን ይፈቅዳል፡፡ሁል ጊዜ የመትፎነት ዘይቤ አይደለም፡፡

▣ *"አውጁና አውሩ"* ግሶቹ *Qal* IMPERATIv E (BDB 894፣ KB 1128) እና *Hiphil* IMPERATIv E (BDB 1033፣ KB 1570) ናቸው፡፡ የአምልኮ ተግባሮቻቸው ሌላውን ለመሳብ ህዝብ በሚያይባለው ቦታዎች ይደረግ ነበር፡፡(ዝ.ከ. Matt 6:2)፡፡

▣ *"የእስራኤል ልጆች ሆይ ይህን ወዳችኋልና"* ያህዌ ላይ ባላቸው የግል እምነት የተመሰረተ የማህበረሰብ የፍርድ ስርዓት ሳይሆን ሙብዛት እንዲሁም የሚነገርለት የአምልኮ ስርዓት የእምነታቸው መገለጫ ሆኖ ነበር፡፡ ሃይማኖታቸውን እርስ በርሳቸው ለማውራት ይፈልጉ ነበር! እምነት የየዕለት ኑሮን ያስተዳጉላለA!

▣ *"ይላል ጌታ እግዚአብሔር"* በ 3:1 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት፡፡

## አሞፅ 4:6-13

**6 በከተማችሁ ሁሉ ጥርስን ማጥራት፥ በስፍራችሁም ሁሉ እንጀራን ማጣት ሰጠኋችሁ**
**እናንተ ግን ወደ እኔ አልተመለሳችሁም፥ ይላል እግዚአብሔር፡-**
**7 መከር ሳይደርስ ገና ከሦስት ወር በፊት ዝናብ ከለከልኋችሁ በአንድም ከተማ ላይ አዘነብሁ፥**
**በሌላውም ከተማ ላይ እንዳይዘንብ አደረግሁ በአንድ ወገን ዘነበ፥ ያልዘነበበትም ወገን ደረቀ።**
**8 የሁለት ወይም የሦስት ከተሞች ሰዎች ወደ አንዲት ከተማ ወኃ ይጠጡ ዘንድ ሄዱ፥**
**ነገር ግን አልረኩም እናንተ ግን ወደ እኔ አልተመለሳችሁም፥ ይላል እግዚአብሔር፡-**
**9 በዋግና በአረማሞ መታኋችሁ የአታክልቶቻችሁንም ብዛት**
**ወይኖቻችሁንም በለሶቻችሁንም ወይራዎቻችሁንም ተምች በልቶአል**
**እናንተ ግን ወደ እኔ አልተመለሳችሁም፥ ይላል እግዚአብሔር፡-**
**10 በግብጽ እንደ ነበረው ቸነፈርን ሰደድሁባችሁ ጐበዛዝቶቻችሁን በሰይፍ ገደልሁ፥**
**ፈረሶቻችሁንም አስማረከሁ የሰፈራችሁንም ግማት**
**ወደ አፍንጫችሁ አወጣሁ እናንተ ግን ወደ እኔ አልተመለሳችሁም፥ ይላል እግዚአብሔር፡-**
**11 ሰዶምንና ገሞራን እግዚአብሔር እንደ ገለበጣቸው፥ እንዲሁ ገለበጥኋችሁ፥**
**እናንተም ከእሳት ውስጥ እንደ ተነጠቀ ትንታግ ሆናችሁ ነገር ግን ወደ እኔ አልተመለሳችሁም፥ ይላል እግዚአብሔር፡-**
**12 ስለዚህ፥ እስራኤል ሆይ፥ እንደዚህ አደርግብሃለሁ እስራኤልም ሆይ፥**
**እንደዚህ ስለማደርግብህ አምላክህን ለመገናኘት ተዘጋጅ።**
**13 እነሆ፥ ተራሮችን የሠራ፥ ነፋስንም የፈጠረ፥ የልቡንም አሳብ ለሰው የሚነግር፥**
**ንጋትን ጨለማ የሚያደርግ፥ በምድርም ከፍታዎች ላይ የሚረግጥ፥ ስሙ የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር ነው።**

**4:6-11** እነዚህ ቁጥሮች እስራኤል የእግዚአብሔርን ቃልኪዳን ቸል በማለቷ ምክንያት የሚገጥሟትን አደጋዎች(ዕርግማኖች) የሚገልፁ ናቸው፡፡ (ዝ.ከ. ዘዳ27-29) እነዚህ እግዚአብሔር ያመጣባቸው ፍርዶች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፡፡

1. 1 ርሃብ (እንጀራን ማጣት) ቁ፣ v 6 (ዝ.ከ. ዘዳ 28:16-17)፡፡
2. ዝናብ ማጣት vv 7-8 (ዝ.ከ. ዘዳ28:23-24)
3. ደረቅ ንፋስ፣ v 9
4. ደረቅ ብስባሽ ቁ፤9 (ዝ.ከ. ዘዳ28:22)
5. ተምች ቁ፤ (ዝ.ከ. ዘዳ28:21፣38-39)
6. ቸነፈር ቁ 10
7. ጦርነት ቁ 10 (ዝ.ከ. ዘዳ28:22፣49-52)

**4:6** የመጀመሪያዎቹ ሁለት ጥቅሶች ተያያዥነት አላቸው፡፡ጥርስን ማጥራት የጥርስ ችግር አይደለም ነገር ግን የሚበላ ምግብ ያለመኖሩ ውጤት ነው!
"እኔ" የተባለው ተውላጠ ስም ትኩረት ተሰጥቶበታል፡፡ ይህም እነዚህን የቃል ኪዳን ዕርግማኖች "የሰደደው"(BDB 678፣ KB 733፣ *Qal* PERFECT) ራሱ ያህዌ ነው፡፡ (ዝ.ከ. ዘዳ27-29)፡፡

▣ *"ሰጠዋኋችሁ"*የሚለው ቃል ትኩረት (ጠንካራ)(አንክሮ)የተሰጠው ነው፡፡ እግዚአብሔር ህዝቦቹን ወደ ቃል ኪዳኑ ለመመለስ ያደረጋቸው አደጋዎች ናቸው፡፡

▣ *"እናንተ ግን ወደ እኔ አልተመለሳችሁም"* የነዚህ አደጋዎች አላማ መቀጣጫ ብቻ ሳይሆን የመታደግም(ዝ.ከ. vv 6፣8፣9፣19፣11)አላማ ነበራቸው፡፡ የንስሃ መግባት ፍላጎት በአስተሳሰብ ለውጥ (ግሪክ ቃል) በመቀጠል ደግሞ በተግባር ለወጥ የሚገለፅ ነው፡፡(የእብረዊያን ቃል ለምሳሌ ኤር 3:22-4:2) በ 1:3 ላይ ንስሃ መግባት ልዩ ርዕስ ተመልከት፡፡

**4:7** *"ዝናብ ከለከልኳችሁ"* የመጀመሪያዎቹ ሁለት መስመሮች የሚያመለክቱት በሃምሌ (March) እና በነሃሴ (April) ውስጥ ተክሎች ከመድረሳቸው(ከሙብቀያቸው) ጊዜ በፊት ቆይቶ የሚመጣውን ዝናብ ነው፡፡ ሙብዛት በያህዌ ቁጥጥር ውስጥ እንጂ በባኦል አይደለም! ከ 3-6 ያሉት ጥቅሶች እግዚአብሔር በፍጥረታት ላይ ያለውን የበላይነት የሚያሳዩ መጽሐፍ ቅዱሳ ዊ መንገዶች ናቸው፡፡ (ዝ.ከ. ቁ 8) ዕርግማኖችን ወደ ተወሰኑ ከተማዎች እና አካባቢዎች (ዝ.ከ. ዘሌ26:19፤ ዘዳ28:12፣23-24)መምራት የሚችል ነው፡፡ይህም ከ

ግብፃዊያን ቸነፈር ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡የመጀመሪያ ዘጠኞቹ የወደቁት በግብፃዊያን መሬት ላይ ወድቀዋል፤ነገር ግን እብራዊያን Goshen ውስጥ በየትኛውም ቦታ አልኖሩም፡፡

**4:8** እነዚህ ቅጥሮች የቁ 7ን ትኩረት ቀጥለዉበታል፡፡ ህይወታቸውን ለማቆየት በቂ የሚሆን ባያገኙም ከተሞች ውሃ በሚፈልጉ ሰዎች ተሞልቷል፡፡
"መቅበዝበዝ"(BDB 631፣ KB 681፣ *Qal* PERFECT) የሚለው ቃል (BDB 631፣ KB 681፣ *Qal* PERFECT) በእግዚአብሔር ፍርድ ምክንያት የመንገዳገድ ወይም የመሽከርከር ስሜትን ያመለክታል፡፡(ዝ.ከ. 8:12፤ ዘፍ 4:12፣14፤ ዘዑ 32:13፤ ኤር 14:10፤ ሰቆ 4:15)፡፡
(ዝ.ከ. 8:12፤ ዘፍ 4:12፣14፤ ዘዑ 32:13፤ ኤር 14:10፤ ሰቆ 4:15)፡፡

▣ **"እናንተ ግን ወደ እኔ አልተመለሳችሁም"** ይህ ተደጋጋሚው የንስሃ መግባት ጥሪ ነው(ዝ.ከ. ቁ 6፣8፣9፣10፣11)፡፡
ግለሰዋዊነት ላይ ትኩረት መሰጠቱን አስተውል፡፡ ወደ እግዚአብሔር ሊመለሱ ነው፡፡ ወደ አምላካቸው፡፡እሱ ከእነሱ ጋር ለዩ ቃልኪዳን መስርቷል፡፡(ዝ.ከ. ቁ 2) የእነሱ ድርሻ መሰጠት እና መታዘዝ ነበር፡፡ የፍጥረታት ዓላማ የነበረው ህብረት ነው፡፡ እግዚአብሔር እሱን ከሚመስል (ዝ.ከ. ዘፍ 1:26-27) ስጋዊ አካል ጋር ህብረትን ለማድረግ ፈልጎ ነበር፡፡ ይህ ህብረት /ዝምድና የእግዚአብሔርን ተፈጥሮ እና ባህሪ ያገናዘበ መሆን አለበት፡፡ይህን የፍቅር ህብረት መተላለፍ ነው የውድቀቱ (ዝ.ከ. ዘፍ 3) መንስኤ እና የመዳን አላማ የሆነው (ይህም ማለት፤ በሰው ልጅ አመፃ ምክንያት የወደመውን የእግዚአብሔርን ምስል መመለስ)፡፡

**4:9**

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"የሚለበልብ ንፋስ"** |
| **NKJv ፣ NRSv ፣** | |
| **NJB** | **"ዋግ"** |
| **TEv** | **"የሚለበልብ ንፋስ"** |

BDB (995) በ ዘዳ 28:22፣ 1ኛነገ 8:37፣ 2ኛዜና 6:28 ፣ እና ኃጌ፣2:17 ላይ ያሉትን ምሳሌዎች በመጥቀስ ይህን ቃል እንደ "የእርሻ ተክሎች" አድርጎ ይገልፀዋል፡፡ሆኖም ግን Holladay's *Lexicon* (361) ተመሳሳይ ምሳሌ በመስጠት "የሚያቃጥል" ብሎ ይገልጸዋል፡፡ NASB እና TEV ይህን የሚረዱት "እርጥበት ያለው ሞቃታማው አየር" ተብሎ የሚጠራውን ሞቃታማ በረሃን ለማመልከት የተገለፀው ብለው ነው፡፡(ለምሳሌ ዘፍ41:6፣23 ፣27)፡፡

▣ **"አረማሞ"** ይህ ቃል (BDB 439) ከላይ በምሳሌ ከተገለፁት ሁሉም ቃሎች ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ BDB "መሻገት" ብሎ ተርጉሞታል፡፡እንዲሁም ደግሞ ቃሉ "መገርጣት" ማለት ነው፡፡(ዝ.ከ. ኤር 30:6) ይህ ሻጋታ የመጣው በከፍተኛ እርጥበት ሳይሆን የመጣው የእጥረት በሚያመጣው whitish powdery መሰል ነገር ነው፡፡

▣ **"ትናንሽ ተባይዎች"** የቃል ኪዳኑን ስምምነት በመተላለፍ ምክንያት በያህዌ ፍርድ ምክንያት የመጣውን የተባይ መንጋ (ይህም ማለት አንበጣዎች [BDB 160]፣ ዝ.ከ. እዩ 1:4፤ 2:25) በ ዘዳ 28:38-40 ውስጥ ማየት ይቻላል፡፡ ይህ መንጋ መቅሰፍቱም (1) ራሳቸው አንበጣዎች ወይም ደግሞ (2) የአንበጣዎች እንቁላሎች ሊሆኑ ይችላል፡፡

**4:10 "በግብፅ እንደ ነበረው ቸነፈርን ሰደድሁባችሁ"** ይህ "ቸነፈር" (BDB 184) የሚለው ቃል እንደሚከተሉት ሆኖ ማገልገል ይችላል፡፡

1. በ ዘፀ 9:3፣15 ውስጥ ከተገለፁት የግብፅ ቸነፈሮች አንዱ
2. በ ዘፀ 5:3፤ ዘሌ 26:23-25፤ ዘጸ 14:12፤ ዘዳ 28:21 ውስጥ እንደተገለፀው እግዚአብሔር በራሱ ሕዝብ ላይ ለሚያመጣው ፍርድ ማስጠንቀቂያ የሚሆን

እብራዊያን ለ"ቸነፈር" የሚጠቀሙት ተነባቢ ፊደላት ከእግዚአብሔር "ቃል " ጋር መመሳሰሉ ማራኪ ነው፡፡ምናልባት አለምዓቀፍ ቃል ሊኖር ይችላል፡፡እስራኤል የእግዚአብሔርን "ቃል" ቸል ብላለችና የእግዚአብሔርን "ቸነፈር" አጭዳለች፡፡ ወደ እግዚአብሔር እና ወደ ቃሉ መመለስ ወደ ሕይወት መመለስ እና ሙብዛት ነው!

▣ **"ፈረሶቻችሁንም አስማረከሁ"** ይህ የጦር ኃይል መሳሪያን ሊያመለክት ይችላል ነገር ግን ይህን በሁለት ዓይነት መንገድ መረዳት ይቻላል፡፡ (1) እነሱ ድል ማድረግን ነበር ያሰቡት፤ ይህም አስተሳሰባቸው የመጣው ከፍተኛ ጥንካሬ የሚሰጧቸው ፈረሶች እና ሰረገሎች ስለነበሯቸው ነበር፡፡ነገር ግን እግዚአብሔር ሁሉንም እንዲወሰዱ እና እንዲማረኩ አድርጓል (NEB) ወይም (2) ጠላት ፈረሶቻቸውን ይዞ የእነሱን የጦር ኃይል ጥንካሬ ባዶ አድርጎታል፡፡ (ዝ.ከ. NRSv ፣ TEv ፣ NJB) አብዛኞቹ የእንግሊዘኛ ትርጉሞች አማራጭ #2ን ይጠቀማሉ፡፡

▣ **"የሰፈራችሁንም ግማት"** ይህ የሚያመለክተው (ዝ.ከ. ኢሳ34:3) በጦርነቱ ወቀት የሞቱትን ወጣት የእስራኤላዊያን ወንዶች ያልተቀበረ አካልን ነው፡፡

▣ **"ወደ አፍንጫችሁ አወጣሁ"** ይህ በቀላሉ የበሰበሰን የሞትን ሰው አካል መግለጫ ወይም የሙሴን ቃል ኪዳን መግለጫ ሌላ መንገድ ሊሆን ይችላል፡፡ ያህዌ ይቀበል የነበረው ተመራጭ መስዋዕት ለመጠቀም የሚያገለግል አንዱ ዘይቤ "መልካሙን መዓዛ" የሚለው ነው፡፡(ዝ.ከ. ዘፍ8:21 ፣ ዘጽ 29:18 ፣25 ፣41 እና በዘሌዋዊያን እና በዘዑ ውስጥ ብዙ ጊዜ) ለአሉታዊ አጠቃቀም ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው ዘጽ 5:21 ነው፡፡

**4:11 "ሰዶምንና ገሞራን እግዚአብሔር እንደ ገለበጣቸው እንዲሁ ገለበጥኋችሁ"** ግሱ (BDB 245፣ KB 253፣ *Qal* PERFECT) ለጊዚያዊ (ዝ.ከ. ዘፍ 19:25 ፣ 2ኛነገ 21:13 ፣ ኤር 20:16) እና ለመጨረሻው ዘመን (ዝ.ከ. ሐጌ 2:21-22) የእግዚአብሔር ፍርድ መጠቀሚያ ነው፡፡ ቃሉ የሚያወራው በተፈጥሮ ወይም በመለኮታዊ ኃይል አጠቃላይ ሁለት ከተሞች ሙሉ ለሙሉ ስለ መውማቸው

ነው፡፡ በተመሳሳይ መንገድ እስራኤልን ህግ የማይጠብቁ "cities of the Plain" ብሎ ማመልከት ለእነዚህ የቃል ኪዳኑ ህዝቦች አስደንጋጭ ዘለፋ ይሆን ነበር፡፡ለ ዘዳ 27-29 ሌላ ተዘዋዋሪ መገለጫ ነው፡፡(ዝ.ከ. 29:23)፡፡

▣ **"እናንተም ከእሳት ውስጥ እንደ ተነጠቀ ትንታግ ሆናችሁ"** በዓውዱ ውስጥቱ TEv አተረጓገም ይህን ከእግዚአብሔር የቁጣ ፍርድ ለተረፉ ጥቂቶች ተጨማሪ መልዕክት አድርጎ ማየቱ ትክክል ሊደርገው ይችላል (ዝ.ከ. ዘካ 3:20) ነገር ግን ከዚህ ሁሉ የቃል ኪዳኑ እርግማንም (ዝ.ከ. ዘዳ27-29) በኋላ እነሱ ወደ እግዚአብሔር አልተመለሱም (ይህም ማለት ንስሃ አልገቡም) ነበር፡፡ እግዚአብሔር በተደጋጋሚ ቅጣት ሊመክራቸው ሞከሯል ፤ እነሱ ግን አልተመለሱም፡፡ የቀረው ነገር ቢኖር ሙሉ ፍርድ ነበር! ይህ ቁጥር ልክ እንደ 3:12 አጠቃላይ ውድመትን ያመለክታል፡፡ የወደፊት ተስፋ የሚገኘው በ9:8-15 ውስጥ ብቻ ነው፡፡

▣ **"ትንታግ"** የዋናው ቃል (BDB 15) የመጀመሪያ ትርጉም "መታጠፍ" ወይም "መዞር" ነው፡፡ ቃሉም እሳትን ለመቆስቆስ የሚጠቅመውን ዱላ ለማመልከት ያገለግል ነበር (ዝ.ከ. ኢሳ7:4፤ ዘካ 3:2)፡፡

▣ **"ነገር ግን ወደ እኔ አልተመለሳችሁም ይላል እግዚአብሔር"** በ 4:6 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት፡፡

**4:12 "እስሬኤል ሆይ አምላክህን ለመገናኘት ተዘጋጅ"** ግሱ (BDB 465, KB 464) Niphal IMPERATIVE ሲደመር Qal INFINITIVE CONSTRUCT ነው፡፡አብዛኛውን ጊዜ እግዚአብሔርን ለመገናኘት የሚያስፈልግን መንፈሳዊ ዝግጅት ለመጠቆም ያገለግላል፡፡(ዝ.ከ. 1ኛ ሳሙ 7:3፤ 2ኛ ዜና12:14፤ 27:6፤ ዕዝ 7:10) ይህ ግኑኝነት ጥሩ ጎን አለው (ዝ.ከ. ዘጽ 19:11-17)፡፡ ነገር ግን ሃጥያታቸው የእግዚአብሔርን ጉብኝት ወደ ቃል ኪዳኑ ፍርድ ለውጦታል፡፡(ዝ.ከ. 5:18-20)፡፡

ይህን ቀጥር በተመለከተ ሌላ ማራኪ አማራጭ የሚሆነው ኤሎሒም (Elohim ) የቃል ኪዳኑን ስም ያህዌን የሚያመለክት አለመሆኑ ማሳየቱ ወይም ደግሞ ኤሎሒም ዘፍ 1 ውስጥ እንዳለው የእግዚአብሔር ስምን እንደ ፈጣሪ ሳይሆን የሚገልፀው የእስራኤልን "ሃሰተኛ አማልክት"(ይህም ማለት ሃሰተኛ የዘር አማልክት) ለማመልከት የተቀመጠ መሆኑ ነው (ዝ.ከ. 5:26፤ 8:14፤ also esቁ 1ኛ ነገ 12:28) ኤሎሒም የሚለው ቃል ራሱ በአሞፅ ውስጥ ያለውን የእስራኤልን አምላክ ለማመልከት የሚያገለግል አይደለም፡፡ ያህዌ ኤሎሒም (Elohim ) (ዝ.ከ. ዘፍ 2:4) የሚለው የተያያዘ ቃል ብቻ ነው ያገለገለው፡፡ እዩ እና አሞፅ (Tyndale Old Testament Commentaries)፣በደቪድ አለን ሁባርድ፣ የእብራዊያን ተነባቢ ፊደላት የማይቀይረውን አማራጭ ትርጓሜ ነው(ይህም ማለት "እስሬኤል ሆይ አማልክቶቻችሁን ለመጥራት ተዘጋጁ" (ዝ.ከ. G W Ramsey፣ JBL፣ 89፣ ገፅ 187-191) ገፅ ቁ 162

ይህ ከሆነ ዘንድ የቁ 13 ምስጋና አቀራረብ አስራኤላዊያን በያህዌ ስም ከሚያመልኳቸው ሃሰተኛ አማልክት አደርገዋለው ከሚሉት ጋር ፊፅሞ የሚፃረር ነው፡፡ (ዝ.ከ. የባዕድ አጋር ከቁ 1-3፣ እንዲሁም ከ 5:26፤ 8:14 ጋር ተያይዞ እና የሆሴ መፅሃፍ)

**4:13** ይህ ቀጥር ግጥማዊ አወራረድ የምስጋና ቃል ወይም ደግሞ እግዚአብሔርን ስለፈጣሪነቱ እንዲሁም ደግሞ ስለ ፍርዱ የቀረበ ዜማ ይመስላል፡፡ አሞፅ ብዙ እንደነዚህ ዓይነት ኃይለኛ እግዚአብሔርን የሚያወድሱ ምስጋናዎች አሉት፡፡ (ዝ.ከ. 5:8፣8፤ 9:5-6)፡፡

▣ **"የሰራ"** ይህ ግስ(BDB 427፣ KB 428፣ *Qal PARTICIPLE (ቦዝ አንቀፅ)* ) ከሸክላ ሰሪው ሃሳብ የመጣ ነው፡፡ (ለምሳሌ ዘፍ 2:7፣19፤ ኢሳ29:19፤ 45:15፤ ኤር 33:2)፡፡

▣ **"ተራሮችን"** ተራሮች የጥንካሬ እና የዘለቄታ ምልክቶች ነበሩ፡፡

▣ **"የፈጠረ"** ይህ ግስ (BDB 135፣ KB 153፣ *Qal PARTICIPLE (ቦዝ አንቀፅ)* "ፈጣሪ" ከሚለው ጋር ተያያዥነት አለው፡፡ ይህ ግስ የእግዚአብሔርን የመፍጠር ችሎታን ሙሉ ለሙሉ ለመግለፅ የሚያገለግል ነው፡፡ ዋናው ትርጉሙ "ማበጀት ወይም በመቁረጥ መቅረፅ" ነው፡፡

▣ **"ነፋስንም"** ይህ የ እብረዊያን ቃል (BDB 924) "ንፋስ" ፣ "እስትንፋስ" ወይም "መንፈስ" ማለት ሊሆን ይችላል፡፡ እዚህ ላይ ያለው አውድ በስጋዊ እና መንፈሳዊ አለም ያለወን ልዩነት የሚያመለክት ነው (ተራራ ከ መንፈስ)፡፡

▣ **"የልቡንም አሳብ ለሰው የሚነግር"** "ሃሳቡን"የሚለው የእብረዊያን ቃል ነጠላ ሲሆን የሚጠቁመውም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ነው፡፡ ይህ ሊያመለክት የሚችለው፤

1. እግዚአብሔር ከፓትሪያርኮች እና ከእነሱ ተከታዮቻቸው ጋር የሚያደርገውን ልዩ የቃል ኪዳን ልዩ ግንኙነትን (ዝ.ከ. 3:2)
2. እግዚአብሐር ከሚወዳቸው የሰው ልጆች ጋር ግንኙት እንዲኖረው መፈለጉን(ዝ.ከ. ዘፍ 1:26፣27፤ 12:3)
3. "የሱን" የሚለው ተውላጠ ስም የሰው ዘርን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል፡፡ ብዙ የብሉይ ኪዳን ፅሑፎች እንደሚናገሩት እግዚአብሔር የእያንዳንዱን ሰው ሃሳብ ያውቃል፡፡
4. (ለምሳሌ ኢዮ 34:21-23፤ መዝ94:11፤[1ኛዜና 3:20]፤ ኤር 11:20፤17:10)

አመፀኛና በኃጥያት የወደቀውም የሰው ዘር ሙሉ በሙሉ ባይሆንም እግዚአብሔርን በማወቅ ከ እግዚአብሔር ጋር ሕብረት መፍጠር ይችላል፡፡ለእግዚአብሔር ያለንን ይህን ፍላጎት የሚያጠፋው ኃጥያት ነው (ይህም ማለት የሰው ነፃነት)! እግዚሃብሔር ፈጣሪ ብቻ አይደለም ፤ ጓደኛ እና አጋዥም ጭምር ነው፡፡

▣ **"ንጋትንም ጨለማ የሚያደርግ"** ይህን በተለያየ መንገድ መረዳት እንችላለን፡፡

1. ለ ዘፍ 1-2 ሌላ መገለጫ (ይህም ማለት (1) እግዚአብሔር ፈጣሪ ነው፡፡[ዝ.ከ. ሰባ ሊቃናት ትርጉም] ወይም (2) የተፈጥሮ የመጀመሪያ አቀማመጥ ዝ.ከ. 5:9)
2. የዚህ ዓውድ ከቀድሞው ጥቅስ ጋር የሚዛመድ ሲሆን የእግዚሃብሔርን መገለፅ ያመለክታል፡፡መንፈሳዊ እውነት የሰው ልጅ  የሚደርስበት ሳይሆን መለኮታዊ መገለፅ ነው፡፡

3. የእገግዚአብሄርን ፍርድ በእስራኤል ላይ የመጠቆሚያ መንገድ(ዝ.ከ. 5:8፣20፤ ኤር 13:16፤እዩ 2:2)
4. የ 5:8 (ለያህዌ እንደ ፈጣሪ ሌላ ውዳሴ) ትይዩ ሲሆን ይህም እግዚአብሔር በፍጡሮቹ ላይ ያለውን ኃይል የሚያሳይ ነው፡፡

▣ **"በምድርም ከፍታዎች ላይ የሚረግጥ"** ምናልባት ይህ ከ ዘዳግም (ይህም ማለት የሙሴ ቃል ኪዳን ዝ.ከ. ዘዳ32:13) ጋር ሌላ ግንኙነት ይኖረዋል፡፡እግዚአብሔርን እንደ ፈጣሪ የሚገልፅ ዘይቤ ነው፡፡(ዝ.ከ. ኢዮ9:8) በ ኢሳ58:4 እና ዕብ 3:19 ውስጥ በእግዚአብሐር ህዝብ ላይ የነበረውን የእግዚአብሔር በረከት አመልካች ነበር፡፡

▣ ይህ ባመሃ (bamah) የሚለው ቃል በከፍታዎች ላይ ይደረግ ከነበረው የባኦል (ዝ.ከ. 2:7-8) አምልኮ ጋር የሚዛመድ ነው፡፡(ለምሳሌ ሆሴ4:13፤ Roland devaux፣ ጥንታዊት *እስራኤል*፣ ጥራዝ 1፣ ገፅ284-288) ይህም ለከናኒያን የዘር ሃሰተኛ አማልክት የሚሰጠውን አምልኮ መቃወሚያ እና የያሕዌን ምሪት እና ፍቅር ማረጋገጫ ሌላ መንገድ ሊሆን ይችላል፡፡

▣ **"ስሙ የሰራዊት አምላክእግዚአብሔር ነው"** ይህ በ 3:13 ላይ ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ አሞፅ በዋል ኪዳኑ መሰረት ስለ ፍጥረታት፤ብዙህነት እና ስለ ፈራጁ እግዚአብሔር ተናግሯል፡፡ አሁን ደግሞ አሞፅ በቀጥታ እና በማያሻማ መልኩ አምላኩ የእስራኤል ያህዌ እንደሆነ ይገልፃል፡፡(ዝ.ከ. 5:8b) ልዩ ርዕስ ለ አማልክት ስሞች በ 1:2 ላይ ተመልከት፡፡

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. አሞፅ 3:2-8 የሚየተኩረው ምን ላይ ነው3:2-8?
2. ለምንድ ነው ነብያቶቹ በቤቴል እና በጌልገላ ላይ በሚደረጉ የባዕድ አምልኮ ተግባር ላይ የሚቀጡት?
3. ለምንድነው አሞፅ 4:4-5 ላይ ያለው የአምልኮ ስርዓት የተወገዘው?
4. እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ጥፈትን የመላኩ አላማ ምንድን ነው?

# አሞፅ 5
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|
| | የእስራኤል ኃጢአተኝነትና የእግዚአብሔር ቅጣት (3:1-6:14) | | እስራኤል ማስጠንቀቂያና መስፈራሪያ ተሰጣት (3:1-6:14) |
| ሰቆቃ ለእስራኤል | የእስራኤል አስፈሪነትና ተገቢ ቅጣት ተፈጻሚነት (5:1-6:14) | ለንስሐ ጥሪ | ሰቆቃ ለእስራኤል |
| 5:1-3 | 5:1-2 | 5:1-2 | 5:1-2 |
| | 5:3 | 5:3 | 5:3 |
| ለንስሐ ጥሪ | | | ያለንስሐ ድነት የለም |
| 5:4-9 | 5:4-5 | 5:4-5 | 5:4-7 |
| | 5:6-7 | 5:6-7 | ምስጋና |
| | 5:8-9 | 5:8-9 | 5:8-9 |
| | | | ማስፈራራት |
| 5:10-13 | 5:10-13 | 5:10-13 | 5:10-13 |
| | | | ማበረታት |
| 5:14-15 | 5:14-15 | 5:14-15 | 5:14-15 |
| የጌታ ቀን | | | ሊሆን ያለ ፍርድ |
| 5:16-17 | 5:16-17 | 5:16-17 | 5:16-17 |
| | | | የያይህዌ ቀን |
| 5:18-20 | 5:18-20 | 5:18-20 | 5:18-20 |
| | | | የተልምዶ አምልኮ ላይ |
| 5:21-24 | 5:21-24 | 5:21-24 | 5:21-24 |
| 5:25-27 | 5:25-27 | 5:25-27 | |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ vii ተመልከት)**

*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

## አሞፅ 5: 1-5

**1 የእስራኤል ቤት ሆይ፥ በእናንተ ላይ ለሙሾ የማነሣውን ይህን ቃል ስሙ።**
**2 የእስራኤል ድንግል ወደቀች፥ ከእንግዲህም ወዲህ አትነሣም በምድርዋ ላይ ተጣለች፥ የሚያስነሣትም የለም።**
**3 ጌታ እግዚአብሔርም እንዲህ ይላልና። ሺህ ከሚወጣባት ከተማ መቶ ይቀርላታል፥**
**መቶም ከሚወጣባት ከተማ ለእስራኤል ቤት አሥር ይቀርላታል።**
**4 እግዚአብሔርም ለእስራኤል ቤት እንዲህ ይላልና። እኔን ፈልጉ፥ በሕይወትም ትኖራላችሁ**
**5 ነገር ግን ቤቴልን አትፈልጉ፥ ወደ ጌልገላም አትግቡ፥ ወደ ቤርሳቤህም አትለፉ። ጌልገላ ፈጽሞ ትማረካለችና፥ ቤቴልም ከንቱ ትሆናለችና**

**5:1** **"ስሙ"** በ 3:1 ላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ፡፡

▣ ***"ሙሾ"*** ይህ ልዩ ግጥማዊ ይዘት ከ ቁ 2-6 እና ከ ቁ 16-17 ወስጥ ይገኛል፡፡ ይህ *"ሙሾ"* (BDB 884) የሚለው የእብራዊያን ቃል በዋናነት በ3-2 ውስጥ ያለውን የግጥማዊ ምት አደራደር የሚያመለክት ነው (ለምሳሌ 2ኛ ሳሙ 1:19-27፣ 3:33-34)፡፡በሰቆቃው ኤርሚያስ ወስጥ እንደተገፀው ዓይነት ሆኖ ያገለግላል፡፡ ይህ አቀራረብ የለቅሶ ዜማዎችን ወይም ቅዳሴዎችን ይገልፃል (ዝ.ከ. ከ ቁ 16-17፣18-20)፡፡እነዚህ ዜማዎች ያልተጠበቁ የቀብር አገልግሎቱ ክፍል ነበሩ፡፡

▣ **"የእስራኤል ቤት ሆይ"** ይህ "ቤት" (BDB 108) የሚለው ቃል በቤተሰባዊ ወይም በተወላጅ ስሜት የቀረበ ነው (ዝ.ከ. 1:4፣5፣ 7:9)፡፡ በአሞፅ ውስጥ (ዝ.ከ. 5:1፣3፣4፣25፣ 6:1፣14፣ 7:10፣16፣ 9:9) "የእስራኤል ቤት" የሚለው ሀረግ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ 922 በ ሮብአምም አገዛዝ ዘመን ውስጥ ከይሁዳ የተከፈሉ የሰሜን አስር ነገዶችን ለመግለጽ ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ እነዚህ ነገዶች ለራሳቸው የእብራዊያን ነገዶች አባት ስም የሆነውን "እስራኤል"(ያዕቆብ) ወስደው ነበር፡፡
በአሞፅ ውስጥ "የያዕቆብ ቤት" የሚለው ሐረግ ሁለት ጊዜ ተጠቅሷል (ዝ.ከ. 3:13፣9:8)፡፡ አብዛኛውን ጊዜ አሞፅ እነዚህን አስር ነገዶች ወይም ደግሞ ስለ አጠቃላይ የያዕቆብ/እስራኤል ተወላጅ እየገለፀ ስለመሆኑ መለየት አስቸጋሪ ነው፡፡

**5:2** ***"ወደቀች"*** ይህ (BDB 656፣ KB 709፣ *Qal* PERFECT) ወደ ፊት የሚፈፀም ሆኖ ነገር ግን ልክ እንደተፈፀመ የሚታይ ትንቢታዊ PERFECT አገላለፅ ነው፡፡ ቃሉ በጦርነት ውስት ሞትን ለመግለፅ ያገለግል ነበር፡፡ (ለምሳሌ ኤር 9:22፣ 46:12፣ ሰቆ ኤር 2:21፣ ሆሴ7:7)

▣ ***"ከእንግዲ ወዲህ አትነሳም"*** ሁለት ግሶች አሉ፡፡ እነዚህም (1) "ከእንግዲህ" (BDB 414፣ KB 418 *Hiphil* IMPERFECT ነው፡፡) እና (2) "መነሳት" (BDB 877፣ KB 1086፣ *Qal* INFINITIVE CONSTRUCT) ናቸው፡፡ በእስራኤል የተለያየ እምነት ላይ የያህዌ ፍርድ አጠቃላያ ፣ የተሟላ እና የአንዴ እና የመጨረሻሻ ፍርድ ነው( ዝ.ከ. 7:9)፡፡
ሆኖም ግን ፤ ይህ ተመሳሳይ ግስ የይሁዳን ንጉሳዊ ቤት ወደ ቀድሞ ሁኔታው ለመመለስ ተስፋ በሚሰጥ ሁኔታ በ 9:11 (ሁለቴ) ውስጥ ተገልጧል (ማለትም ፤ "የዳዊት የወደቀው ጎጆ") ስለዚህ እንደገና የመንፈሳዊው ትምህርቱ ሃሳብ ፤

1. የእግዚአብሔር መልክት ጥቁር እና ነጭ እውነታን በማነፃር ቀርቧል (የሚቃረኑ ዘዬዎች)
2. ምዕራፍ 9 የሚያመለክተው እስራኤልን ሳይሆን ይሁዳን ብቻ ነው

▣ ***"የእስራኤል ድንግል"*** ይህ ቃል ከ "የእስራኤል ቤት" ጋር ትይዩ ነው፡፡እግዚአብሔር ልክ እንዳላገባች ሴት ልጅ ወይም ሙሽራ ለእስራኤል ልዩ እንክብካቤ እና ጥበቃ ያደርግ ነበር (ዝ.ከ. ኤር 18:13፣ 31:4፣21)፡፡ ይህ እግዚአብሔርን እንደ ባል ፤ የቃል ኪዳኑን ህዝቡን ደግሞ እነደ ሚስት የሚያሳይ የጋብቻ ዘይቤ ነው(ለምሳሌ፤ ኢሳ 54:5፣ ሆሴ 2:19፣ ኤፌ 5:22-33)፡፡ የቀድሞዎቹ የአይሁድ የሃይማኖት መምህራን የበረሃውን የመንከራትተ ቆይታ እንደ ጫጉላ ጊዜ ያዩታል (ዝ.ከ. ኤር 2:2-3፣ ሆሴ2:16)፡፡ነገር ግን አሁን ዓውዱ የሚነግረን በአሶራዊያን ወረራ የእስራኤልን መደፈር እና መገደልን ነው፡፡

▣ ***"በምድሯም ላይ ተጣለች"*** የግሱ (BDB 643፣ KB 695) ትርጉም መተው ፣ ተበዝብዞ መጣል ማለት ነው፡፡ የተስፋው ምድር አሁን የፍርድ ቦታ ነው፡፡ በNIDOTTE፣ ጥራዝ 1፣ ገፅ ከ522-524 ላይ "ምድሩ" ለአብርሃም ተወላጆች የያህዌ ስጦታ እንደሆነ የሚያስረዳ በጣም ማራኪ ፅሑፍ መንፈሳዊ ትምህርት አለ (ዝ.ከ. ዘፍ 12:3)፡፡ አብዛኞቹ የሙሴ ደንቦች በዚህ ሃሳብ ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ እግዚአብሔርን ያስቆጣው የቃል ኪዳን አንድነት ያላቸውን ወንድሞች ከቤተሰባቸው/ ከነገዳቸው የማስወጣቱ ወንጀል ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ስለ ምድሩ ያለውን መቆርቆር "በሰባተኛው ዓመት" ("the Sabbath Year") እና "ኢዮቤልዩ አመት" አቆጣጠር ውስጥ ማየት ይቻላል፡፡
በመንፈሳዊ ትምህርት መሰረት የተስፋዊቷ ምድር ባለቤትነት እና ክፍፍል የያህዌን መሆኑን እነዚህ ባለፀጋ መሬት ነጣቂዎች ሙሉ ለሙሉ ቸል ብለዋል ወይም ደግሞ ሆን ብለው ተቃውመውት ነበር፡፡

▣ ***"የሚያስነሳትም የለም"*** ይህ ተመሳሳይ ግስ (BDB 877፣ KB 1086) ከዚህ በፊት በነበረዉ ቁጥር ውስጥ የተገለፀ ነው፡፡ ይህ እዚህ ላይ *Hiphil ቦዝ አንቀፅ ነው፡፡* ይህ የከነዓንዊያን ሃሰተኛ አማልክት (እስራኤል የምታመልካቸው) እስራኤልን ከእግዚአብሔር ፍርድ ሊያስጥሏት አለመቻላቸውን የሚያሳይ አሽሙራዊ አገላለፅ ይመስላል(ዝ.ከ. 5:6)፡፡ የከነዓንዊያን አማልክት አቅመ ቢስነት እና የማይችሉ መሆናቸው አስቂኝ ነበር!

**5:3** ይህ ከቃል ኪዳኑ እርግማኖች አንዱ ነበር ("ሺህ" [BDB 48] እና "መቶ" [BDB 547] የሚባሉት መጠሪያዎች ለጦር ሃይል ክፍሎች ነበር ፤ዝ.ከ. ዘዳ28:62)፡፡ በዚህ ቁጥር ውስጥ ያለው ትኩረት ስለ ተራፊዎቹ መመለስ ሳይሆን (ዝ.ከ. ኢሳ6:13) ፤ የሚደርሰውን በጣም ከፍተኛ የሆነ የጦር ኃይል ውድመትን ነው፡፡ የእስራኤል ሃገር ለዘለቄታው መኖር ታቆማለች፡፡

**አሞፅ: 5:4-7**

**4እግዚአብሔርም ለእስራኤል ቤት እንዲህ ይላልና።እኔን ፈልጉ፥ በሕይወትም ትኖራላችሁ**
**5 ነገር ግን ጌልገላ ፈጽሞ ትማረካለችና፥ ቤቴልም ከንቱ ትሆናለችና**
**ቤቴልን አትፈልጉ፥ ወደ ጌልገላም አትግቡ፥ ወደ ቤርሳቤህም አትለፉ።**
**6 በዮሴፍ ቤት እሳት እንዳትቃጠል፥ በቤቴል የሚያጠፋትም ሳይኖር እንዳትበላ፥**
**እግዚአብሔርን ፈልጉ፥ በሕይወትም ትኖራላችሁ።**
**7 ፍርድን ወደ እሬት የምትለውጡ፥ ጽድቅንም በምድር ላይ የምትጥሉ እናንተ ሆይ፥**
**ሰባቱን ከዋክብትና ኦሪዮን የተባለውን ኮከብ የፈጠረውን፥**
**የሞትን ጥላ ወደ ንጋት የሚለውጠውን፥ ቀኑንም በሌሊት የሚያጨልመውን፥**
**የባሕሩንም ውኆች ጠርቶ በምድር ፊት ላይ የሚያፈስሳቸውን፥**

**5:4 "እኔን ፈልጉ"** እዚህ ውስጥ ያለው ግስ (BDB 205፣ KB 233) *Qal ትዕዛዝ አንቀፅ* ነው(ዝ.ከ. ከv 6፣14-15)፡፡ የእብራዊያን ሃረግ *"መፈለግ"* ቅዱስ አፃፃፍ ወደ መቅደስ መሄድን ያካትታል ፤ ሆኖም ግን የቁ 5 ዓውድ እግዚአብሔርን መፈለግ ያለብን በግል ፤ እንዲሁም በህብረት (ዝ.ከ. ዘዳ 4:29-30፣ 30:1-3፣10) ሆነን እንጂ ለሃይማኖታዊ ስርዓት ብቻ መሆን እንደሌለበት ያስረዳናል፡፡ ዝንባሌያችን ፣ ፍላጎታችን እና የእምነት አኗኗራችን በጣም አስፈላጊዎች ናቸው፡፡ በዋናነት ይህ ያህዌን ለሚያውቁ (የቃል ኪዳኑን ሁኔታ) የንስሃ ጥሪ ነው፡፡ ከያህዌ ጋር ለሚደረግ ህብረት የሃቀኝነት ህይወት ያስፈልጋል፡፡በቁ 4 አሞፅ "እኔን ፈልጉ" ብሎ ይናገራል፡፡ ይህ ተመሳሳይ ግስ በቀ 14 ውስጥም ይገኛል ፤ "መልካሙን እንጂ ክፉውን አትፈልጉ"፡፡ እነዚህ ሶስቱ በመጠኑም ቢሆን ትይዩ ናቸው፡፡ ያህዌ ብዙ ጊዜ መልካም ተብሏል (ለምሳሌ፤ መዝ86:5፣ 100:5፣ 106:1፣107:1፣ 118:1፣29)፡፡ ስለዚህ "እኔን" እና "መልካሙን" መፈለግ ያህዌን ሊያመለክቱ ይችላሉ(የቁ 14ን ሁለተኛ መስመር አስተውል)፡፡ ተመሳሳይ አመለካከት በሆሴ 8:2-3 ውስጥ ተገልጧል፡፡
የእብረዊያን ቃል *"መፈለግ"* ብዙ ትርጉሞች አሉት፡፡

1. መጠየቅ
2. አማልክትን በፀሎት እና በአምልኮ ውስጥ መፈለግ
3. መመርመር (ልብን ማወቅ)
4. ፍላጎትን መጠየቅ

ለዚህ ዓውድ ውስጥ ቁጥር #2 ምርጥ ተመራጭ ነው (ዝ.ከ. ዘዳ4:29 ፣ ሆሴ 10:12፣ ኢሳ9:13፣ 31:1፣ 55:6፣ 65:10)፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"ትኖሩ ዘንድ"** |
| **NKJV ፣ NRSV** | **"እናም ኑሩ"** |
| **TEV** | **"ትኖራላችሁ"** |
| **NJB** | **"ትተርፋላችሁ"** |

የ NKJV እና የ NRSV አገላለጽ ቀጥተኛ ናቸው፡፡ ግሱ (BDB 310፣ KB 309) ከ *"መፈለግ"* ጋር የሚያያዝ *Qal ትዕዛዝ አንቀፅ* ነው፡፡ የ*ትዕዛዝ አንቀፅነት* ስሜቱ በNASB ፣ TEV ፣ እና NJB ውስጥ ይታያል፡፡እንደ ቃል ኪዳን ህዝብ የእስራኤል መኖር ዋናው ነጥብ ነው! ያህዌ መሃሪ ነው ፤ ወደ እሱ ቢመለሱ ፤ ይቀር ይላቸዋል ፣ ወደ ነበሩበት ሁኔታ ይመልሳቸዋል እነዲሁም ይጠብቃቸዋል (ማለትም ፤ ልክ እንደ ቅዱስ ጦርነቱ)፡፡
ይህ ምህረት የማድረግ ሁኔታ የቃል ኪዳን ህዝቡን ማጥፋት ከማይፈልገው እግዚአብሔር ልብ ፍላጎት የመጣ ነው (ዝ.ከ. ሆሴ11:8-11)፡፡

**5:5 "ቤቴልም ጌልገላ ቤርሳቤህ"** እነዚህ ሁሉም የተለመዱ የማምለኪያ ማዕከላት ናቸው፡፡ የመጀመሪያ ሁለቱ በእስራኤል ውስጥ ሶስተኛው ደግሞ በይሁዳ ውስጥ ነበሩ (ዝ.ከ. 2ኛ ነገ 23:8፣ ዘፍ 21:14፣ 31፣ 26:25፣33፣ 46:1)፡፡

▣ **"ቤርሳቤህ"** ይህ በደቡብ ይሁዳ ውስጥ የሚገኝ ከፓትሪያርኮች (አብርሃም ዘፍ 21:33፣ ይስሐቅ፣ ዘፍ 26:23-25፣ ያዕቆብ፣ ዘፍ 28:10፣ 46:1-7) ጋር የተያያዘ የተቀደሰ ጥንታዊ ቦታ ነበር፡፡

▣ **"ጌልገላ... ፈፅሞ... ትማረካለችና"** አሞፅ የግጥም ጥበበኛ ነው፡፡እዚህ ላይ አሞፅ በ"ጌልገላ" እና "ወደ ምርኮ መሄድ" (BDB 162፣ KB 191፣ የተመሳሳይ ቃል *Qal* INFINITIVE ABSOLUTE እና *Qal* IMPERFECT ) መሃከል መልካም የቃል አገላለፅን ተጠቅሟል፡፡ የእብራዊያን ቅኔ በተመሳሳይነታቸው ፣ ብዙ ትርጉም ባላቸው ቃላት እና በቃል አደራደራቸው ይታወቃሉ፡፡

▣ **"ቤቴልም ከንቱ ትሆናለችና"** ይህ በቤቴል (የእግዚአብሔር ቤት) እና ቤቴል እየሆነች በመጣችው (ጣዖታት የማምለኪያ ቤት፤ ዝ.ከ. ሆሴ4:15፣ 5:8፣ 10:5፣8) መካከል ያለው ንፅፅር ይመስላል፡፡የ"ከንቱ" (BDB 19) አንዱ ትርጉም ጣዖት አምላኪነት ሊሆን ይችላል (ማለትም ፣ "ምንም" ዝ.ከ. ኢሳ41:29፣ 66:3)፡፡

**5:6 "እግዚአብሔርን ፈልጉ በሕይወትም ትኖራላችሁ"** ይህ ከ ቁ 4 ጋር ትይዩ ነው፡፡

▣ **"እሳት እንዳትቃጠል"** ይህ የዘዳግም(ዝ.ከ. 4:24) ሌላ መገለጫ ሊሆን ይችላል፡፡እሳት የእግዛብሔርን የማንጫ ኃይል ወይም በሌላ መንገድ ሲታይ የእግዚአብሔርን ቅዱስነት የሚገልፅ ዘይቤ ነው፡፡ልዩ ርዕስ፤ እሳት በ7:4 ላይ ተመልከት፡፡

▣ **“በዮሴፍም ቤት ”** እስራኤል “በዮሴፍ ቤት” (ዝ.ከ. 6:6) ተብላ ስትጠራ ያልተለመደ ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ “የያዕቆብ ቤት” (ወይም “የእስራኤል ቤት” ለምሳሌ ቁ 1) ተብላ ነው የምትጠራው፡፡ ሆኖም ግን ኤፍሬም እና ምናሴ ፣ የዮሴፍ ሁለት ልጆች የሰሜኑን ግዛት ትልቁን መሬት የያዙ እና በህዝብ ብዛት የላቁ ነገዶች ናቸው፡፡

**5:7 “ፍርድን ወደ እሬት የምትለውጡ”** “ፍርድ” ከ *“ፅድቅ”* ጋር ትይዩ ነው፡፡እነዚህ ሁለት ቃላት በብሉ ኪዳን ውስጥ በተመሳሳይ ዓውድ አንድ ላይ ይታያሉ (ዝ.ከ. 2ኛ ሳሙ 8:15፣ 1ኛ ነገ 10:9፣ 1ኛዜና 18:14፣ 2ኛ ዜና9:8፣ መዝ99:4፣ ኢሳ1:21፣ 5:7፣ 9:7፣ 28:17፣ 32:1፣16፣ 33:5፣ 59:14፣ ኤር 4:2፣ 9:24፣ 22:3፣15፣ 23:5፣ 33:15፣ እዝ18:5፣19፣21፣27፣ 33:14፣16፣19፣ 45:9፣ አሞፅ 5:7፣24)፡፡ ይህ የአዲሱ ቃል ኪዳን ፅድቅ “በእምነት ማሳመን” ፤ ማመካኛ አይደለም ፤ ነገር ግን ያህዌ አንድ ሕዝብ የእሱን ባህሪ እንዲገልጹ የፈለገበት የድሮው ቃል ኪዳን የሚሰራው ስራ ነው (ዝ.ከ. ማቴ 5:19-20፣48)፡፡ ሆኖም ግን የቃል ኪዳኑ ሕዝብም ሆነ በሃጥያት የወደቀው የሰው ዘር የእግዚአብሔርን የቅድስና ኑሮ መኖር አልቻሉም! የቦዝ አንቀፁ (BDB 245፣ KB 253፣ *Qal* ቦዝ አንቀፅ) ትኩረት እስራኤል ስትሆን አንቀፁ በአሉታዊ ስሜት ተጠቅሷል(ዝ.ከ. 5:7፣ 6:12፣ ኤር 2:21)፡፡ አሞፅ በተመሳሳይ መነሻ ነገር ግን ያህዌ የድርጊቱ ባለቤት ሆኖ በ4:11 ውስጥ ሰዶም እና ገሞራ እንደ ተገለበጡ ጠቅሷል፡፡ እሬት (BDB 542) መንኛውንም ቆምጣጣ ተክልን ያመለክታል (ዝ.ከ. የUBS የመጽሐፍ ቅዱስ *እንስሳት እና ዕፅዋት* ገጽ 198)፡፡ባለሃብቱ ፍርድን ተከላክሏል፡፡የፍርድ አሰጣጡ ስርዓት ለድሃው መራራ እንጂ እረፍት የሚያገኝበት አልሆነም (ዝ.ከ. ቁ 12፣ 6:12)፡፡ይህ ምናልባትም በ ዘዳግም ውስጥ ያለውን ጣዖት አምልኮ በሌላ መልኩ እየገለፀ ሊሆን ይችላል (ዝ.ከ. 29:18፣ ኤር 9:14፣ 23:15)፡፡ የአረባዊው ተዛማች ትርጉም “እርግማን” ነው፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB | **“ፅድቅን ወደ መሬት መጣል”** |
| NKJV | **“ፅድቅ በመሬት ላይ እንዲሆን ማጋደም”** |
| NRSV | **“ፅድቅንዳ ምድር ማምጣት”** |
| TEV | **“የሰዎችን መብት መቀማት”** |
| NJB | **“ፅድቅን ወደ ምድር መወርወር”** |

እዚህ ላይ ያለው ሃሳብ መጣል (BDB 245፣ KB 253፣ *Qal* ቦዝ አንቀፅ) ከእግር ስር አድርጎ መረጋገጥ ወደ ሚለው ዕይታ ያዘነብላል (ዝ.ከ. ኢሳ 28:2-3)፡፡ እንደ ንጉስ ያሉ ዳኞች ያህዌን ይወክሉ ነበር፡፡“ትክክለኛ ፍርድ” እና “ፅድቅ” ትይዩ እንደሆኑ አስተውል (ዝ.ከ. ቁ 24፣ 6:12)፡፡ ለመፅሐፍ ቅዱሳዊ እምነት የሚተገበር ስነምግባራዊ ሁኔታ አለ!

## አሞፅ:5:8-9

**8 ሰባቱን ከዋክብትና ኦሪዮን የተባለውን ኮከብ የፈጠረውን፥ የሞትን ጥላ ወደ ንጋት የሚለውጠውን፥ ቀኑንም በሌሊት የሚያጨልመውን፥ የባሕሩንም ውኆች ጠርቶ በምድር ፊት ላይ የሚያፈስሳቸውን፥**
**9 አምባውም እንዲፈርስ በብርቱ ላይ የድንገት ጥፋት የሚያመጣውን ፈልጉ ስሙ እግዚአብሔር ነው።**

**5:8-9** ይህ እግዚአብሔርን ስለ ፈጣሪነቱ እና አዳኝነቱ የቀረበ ግጥማዊ ምስጋና ነው፡፡ በአሞፅ ውስጥ እንደዚህ አይነት አራት ምስጋናዎች አሉ (ዝ.ከ. 4: 4፣ 5:8-9፣ 9:5-6)፡፡

**5:8 “ሰባቱን ከዋክብት”** ይህ በቀጥታ “ክምር” ወይም “መንጋ” ነው(BDB 465፣ ዝ.ከ. ኢዮ 9:9፣ 38:31)፡፡በ ጦረስ ኅብረ ኮከብ ወስጥ ይህ በጣም ከሚያበሩት የኮከብ ግርዶሾች አንዱ ነው (ሂሶድ ይህን “ሰባቱ እህታማቾች” ብሎ ይጠራቸዋል) UBS፣*የተርጓሚዎች የመመሪያ መፅሐፍ*፡ ገፅ 105 ፣ 242 በፍልስጤም ውስጥ የአድማስ በታች ስርዓቱ ክረምትን ያመጣል፡፡ስለዚህ ይህ ግጥማዊ ንባብ እግዚአብሔር ፈጣሪ ብቻ ሳይሆን የፍጥረታት አሰራርንም እንደሚቆጣጠር (አርቆ እንደሚያስብ) አመልካች ነው፡፡

▣ **“ኦሪዮን”** ይህ ቃል በቃል በጠብ አጫሪነት ስሜት ሲታይ “መሞኘት” (BDB 493) ማለት ነው፡፡ አመፅን ለማመልከት ያገለግላል፡፡ ጥንጣዊያን ይህን ኅብረ ኮከብ በናምሩድ ይወክሉታል (ኃያሉ ፤ ዝ.ከ. ዘፍ 10:8-9)፡፡ በበጋ የሚታይ ነበር፡፡ ወቅቶችን የሚቆጣጠረው እግዚአብሔር ነው(ማለትም፤ የፍጥረታትን አለም አሰራር እና ፍርቀታቸውን)! በግልፅ እነደሚታየው በኮከቦች አምልኮ (ዝ.ከ. v 26) ዕይታ የእግዚአብሔር አፈጣጠር እና የኮከቦች ቁጥጥር (ዝ.ከ. ዘፍ 1:14-19) በጣም አስፈላጊ የመንፈሳዊ ትምህርት ዓረፍተ ነገር ነበር፡፡

▣ **“የሞትን ጥላ ወደ ንጋት የሚለውጠውን”** በዓውዱ መሰረት ይህ የሚናገረው በሰማይ አካላት ላይ ስላለው የእግዚአብሔር ቁጥጥር ነው (ዝ.ከ. መዝ19: 24)፡፡ ይህ ሃረግ በሃሳብ ደረጃ ከ 4:13ሐ ጋር ትይዩ ሊሆን ይችላል፡፡

▣ **“የባሕሩንም ውኆች ጠርቶ”** የዚህን ሃረግ ትርጉም በተመለከተ ብዙ ጥናቶች አሉ፡፡ (1) የውቂያኖስ ወሰኖችን ያመለክታል (ዝ.ከ. ዘፍ 1:9-10)፣ (2) የዝናብ ምንጭ ባአል ሳይሆን እግዚአብሔር እንደሆነ ያመለክታል (ማለትም ፤ እድገትን የሚደግፍ በረከት) ወይም (3) ምናልባትም የውሃው ጥፋት ሌላ መገለጫ ሊሆን ይችላል(የፍርድ ተልዕኮ ያለው፤ ዝ.ከ. ዘፍ 6) እግዚአብሔር ኮከቦችን እንደሚቆጣጠር ሁሉ የተፈጥሮ ውሃንም ይቀጣጠራል፡፡በዘፍ 1 ውስጥ ውሃ በእግዚአብሔር ቃል ወደ መኖር እንዲለወጥ ያልታዘዘ ብቸኛ ነገር ነው፡፡(ዝ.ከ. ዘፍ 1:2)

▣ **“ስሙም እግዚአብሔር ነው”** በእብረዊያን ውስጥ ስም የአንድን ግለሰብ ባህሪ ለመግለፅ በጣም አስፈላጊ ነበር፡፡ በ ዘፀ 3:14 “ያህዌ” የሚለው የእግዚአብሔር ስም ከ እብረዊያን ግስ “ያለ እና የሚኖር” ከሚለው የመጣ ነው፡፡ልዩ ርዕስ : የአማልክት ስሞች በ 1:2 ላይ ተመልከት፡፡

**5:9**

| | |
|---|---|
| NASB | **“ድንገት የሚያመጣውን”** |
| NKJV | **“የሚያዘንበው”** |
| NRSV | **“ድንገት”** |
| TEV ፣ NJB | **“የሚያመጣው”** |

የእብረዊያን ቃሉ (BDB 114፣ KB 132፣ *Hiphil* ቦዝ አንቀፅ) ትርጉም በጥርጣሬ ውስጥ ነው፡፡በኢዮብ እና በ መዝሙር ውስጥ ፍልቅልቅነት ወይም ደስታን (የአረባዊ ዋና ትርጉም) ያመለክታል፡፡ሆኖም ግን ፤ አሞፅ በአሽሙር ያህዌ የእስረኤል ጣዖት አምላኪነት እና የጦር ምሽግ መፈራረስ ደስ የሚያሰኘው መሆኑን እየተናገረ ካልሆነ በስተቀር ትርጉሙ ፈጽሞ አሞፅን አይገልጸውም፡፡ NASB "አንድ ነገር በድንገት እንዲናድ መፍቀድ" የሚለውን ሊሆን የሚችል ትርጓሜ ከ *ሂፊል*፣ ትርጉም ወስዷል (ዝ.ከ. NIDOTTE፣ ጥራዝ 1 ፤ ገፅ 660)፡፡

▣ **"በብርቱ"** ይህ ምናልባትም የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ኃይለኛነትን ሊያመለክት ይችላል (ዝ.ከ. ከቁ 10-13፣ 2:14)፡፡ የ "ደሃው" ሰው ተቃራኒ በድሆች ጉልበት ተጠቃሚ የሚሆነው ሰው ነው! ሆኖም ግን ከ"ትልቅ ምሽጎች" ባለው ተዛማችነት ምክንያት ምናልባትም የእስራኤልን ጦር ሃይል ሊያመለክት ይችላል፡፡

## አሞፅ: 5:10-13

**10 በበሩ አደባባይ የሚገሥጸውን ጠሉ፥ እውነትም የሚናገረውን ተጸየፉ።**
**11 ድሀውንም ደብድባችኋልና፥ የስንዴውንም ቀረጥ ከእርሱ ወስዳችኋልና**
**ከተጠረበ ድንጋይ ቤቶችን ሠርታችኋል፥ ነገር ግን አትቀመጡባቸውም ያማሩ የወይን ቦታዎች ተክላችኋል፥**
**ነገር ግን ከወይን ጠጃቸው አትጠጡም።**
**12 ጻድቁን የምታስጨንቁ፥ ጉቦንም የምትቀበሉ፥**
**በበሩም አደባባይ የችጋረኛውን ፍርድ የምታጣምሙ እናንተ ሆይ፥**
**በደላችሁ እንዴት እንደ በዛ፥ ኃጢአታችሁም እንዴት እንደ ጸና እኔ አውቃለሁና።**
**13 ስለዚህ ክፉ ዘመን ነውና በዚያ ዘመን አስተዋይ የሚሆን ዝም ይላል።**

**5:10 "በበሩ አደባባይ የሚገስጸውን ጠሉ"** እነዚያ (ሃቀኛ ዳኞች ፣ በእውነት የሚመሰክሩ) ለደሃው እና ለችግረኛው ለመቆም እና ለመሟገት የሞከሩ ሰዎች (በትክክል ይህ ማንን እንደሚያመለክት አልተረጋገጠም ፤ ህጋዊነትን የሚደግፉ ጥቂት ሰዎች) ሥልጣኑን በያዙ መሪዎች በኃይል ጥቃት ይደርስባቸው ነበር (ዝ.ከ. ኢሳ59:14-15)፡፡ ይህ የዘዳግምን እርግማን እና በረከት የሚገልፅ ሌላ ንዑስ ክፍል ነው(ዝ.ከ. ዘዳ27:25)፡፡ በሩ በጥንታዊ ምስራቅ አቅራቢያ ውስጥ ፍርድ የሚሰጥበት ቦታ ነበር (ዝ.ከ. ዘዳ25:1-3፣ ሩት 4:1-12)፡፡ ይህ በር የህብረተሰቡ ሽማግሌዎች መቀመጫ የነበረ ነው (ዝ.ከ. ዘዳ19:12፣ 21:3፣8፣19፣ 21:3፣8፣ 22:15፣ 25:7-8)፡፡ እነዚህ ሽማግሌዎች በአሞፅ ተገልጸዋል፡፡

▣ **"ተጸየፉ"** ይህ (BDB 1073፣ KB 1765፣ *Piel* IMPERFECT) ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ጣዖት አምልኮን እንደሚጠላ የሚያመለክት ጠንካራ ግስ ነው፡፡ በዚህ ዓውድ ከ"መጥላት" ጋር ትይዩዩ ነው፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"ፍጹም"** |
| **NKJV** | **"ቀጥተኛ"** |
| **NRSV ፣ NJB** | **"እውነቱ"** |
| **TEV** | **"አጠቃላይ እውነቱ"** |

የቃሉ (BDB 1071) ዋና ትርጉም ትክክል ወይም ቀጥተኛ ማለት ነው፡፡ ይህ የግብረገብ/የሥነ ምግባር ቀጥተኝነት ዘይቤ የተገኘው ከቴምር ዛፍ ነው፡፡

አጠቃቀሙን አስተውል፤

5. ኖህ፤ ዘፍ 6:9
6. አብርሃም፤ ዘፍ 17:1
7. የደኅንነት መስዋዕት ፤ ዘሌ22:21
8. ሃይማኖተኛ እስራኤላዊያን ዘዳ 18:13፣ ምሳ 2:7፣ 10:9
9. እግዚአብሔር፣ ዘዳ 32:4 ፣ 2ኛ ሳሙ 22:31፣33፣ መዝ18፣ 30፣32
10. ኢዮብ፤ ኢዮ 1:1፣8፣ 2:3
11. የእግዚአብሔር ቃል፤ መዝ19:7

**5:11ሀ-ለ** የዚህ ቁጠር የመጀመሪያዎቹ ሁለት ግጥማዊ ሃረጎች የደሃውን ብዝበዛዎች ይዘዋል፤

1 ከባድ ክፍያ (ማለትም፤ ከአካዲያን ዋና ቃል የተወሰደ) ወይም መረጋገጥ (ማለትም፤ ከእብራዊያን ዋና ቃል "መረጋገጥ" [BDB 143፣ KB 165፣ *Poel* INFINITIVE CONSTRUCT]፣ ዝ.ከ. NKJV ፣ NRSV ፣ NJB) የተወሰደ
2 በምግብ ላይ ቀረጥ
3 በፍርድ መስጫ ቦታ ጉቦ መብላት (ዝ.ከ. ቁ 12)

ደሃ(በ2:7 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት) "ባላገር ገበሬዎች"ን ያመለክታል (በNIDOTTE ጥራዝ 1 ፣ ገፅ 951 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት)፡፡

**5:11ሐ-ሠ** ይህ የሙሴን ቃል ኪዳን በመተላለፍ የመጣ ሌላ እርግማን ነው (ዝ.ከ. ዘዳ28:30፣39)፡፡ ሃብታሙ ደሃውን በመበዝበዝ የቅንጦት ቤቶችን("ከተጠረበ ድንጋይ") ገንብተው ነበር (ዝ.ከ. v ከ 11-12)፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር በሐሰት ባገኙት ጥቀም ይኖሩበት ዘንድ አልፈቀደም (ዝ.ከ. ሚል 6:15)፡፡ ይህ ለአሶራዊያን ግዞት መገለጫ ነው፡፡

**5:12** ይህ ቁጥር ልክ ከቁ 10-11 እንዳለው ባለፀጎች በደሃው (ምናልባትም ትናንሽ ገበሬዎች) እና በችግረኞች ላይ የሚፈፅሙትን ሃጥያቶች ይዘረዝራል፡፡ እነዚህ ስነ ምግባር ያላቸው ፣ ረጂ የሌላቸው እና ችግረኞች በመሆናቸው ምክንያት እግዚአብሔር የሚጠነቀቅላቸው ናቸው (ዝ.ከ. ዘዳ10:18፣ 14:29፣ 16:11፣ 24:17-22፣ 26:12-13፣ 27:19)፡፡ ይህ ሌላ ዘዳግማዊ የሆነ ትኩረት ነው፡፡ ነብያቶች ሁል ጊዜ ወደ ኋላ ተመልሰው የሙሴን ቃል ኪዳን ይጠቅሱ ነበር፡፡"ጉቦ" (BDB 497፣ ዝ.ከ. ዘፀ 23:8፣ ዘዳ16:19፣ 27:25፣ 1ኛ ሳሙ 12:3፣ ምሳ 6:35) ተብሎ የተተረጎመው ቃል እግዚአብሐር ለሃጥያት ያለውን "ሽፋን"፣"ተቃውሞ" የሚገልጸው ተመሳሳይ ቃል ነው፡፡ እዚህ ውስጥ ይህ አስፈላጊ የመንፈሳዊ ትምህርት

ቃል የአንድን ሰው እጅ ወይም አይኖች መሸፈን ከሚለው ስሜት የተገኘ አጠቃቀም አለው፡፡ይህ ድንቅ ለሆነው የመንፈሳዊ ትምህርት ቃል አስደንጋጭ አጠቃቀም ነው፡፡

**5:13** ይህ ነብዩ ራሱ ከሚደግፋቸው እና ከሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ በተቃራው የቀረበ ስለሚመስል በጣም አስቸጋሪ ቁጥር ነው፡፡ ይህ ምናልባት እንደገና "አስተዋይ የሚሆን" በሚለው (BDB 968፣ KB 1328፣ *Hiphil* ቦዝ አንቀፅ) ቦዝ አንቀፅ ላይ የቀረበ የትርጉም ጥናት ሊሆን ይችላል፡፡ *Hiphil የሚለው*

1. ማየት (ጥበበኛ ለማድረግ፣ ዝ.ከ. ዘፍ 3:6)
2. ማስተዋል (ለምሳሌ ዘዳ32:29)
3. እወረቀት የተሞላ (ለምሳሌ ዳን 1:4፣ 9:25)
4. መናገር ፤ ማስተማር (ለምሳሌ ፣ ዳን 9:22፣ 11:33፣35)
5. አስተዋይ መሆን (ለምሳሌ ፣ አሞፅ 5:13)
6. ከፍ ከፍ ማለት (ለምሳሌ ፣ ኢሳ52:13፣ ኤር 10:21)
7. መከናወን (ለምሳሌ ፣ ዘዳ29:9)

ይህ ቃል እንዴት የ#5 ወይም #6/#7 ትርጉም እንደሚሆነው በኤር 23:5 ላይ ጥሩ ምሳሌ ይመልከቱ፡፡በእንደዚህ ሁኔታ ካገለገለ ምናልባትም ይህ የ ዘዳግም ሌላ መገለጫ ሊሆን ይችላል (ማለትም 29:9)፡፡ ከፍ ከፍ እንዲሉ ይጠበቅ የነበረው በእግዚአብሔር በረከት (ዝ.ከ. ዘዳ27-29) ነበር ፤ ነገር ግን እነሱ ከፍ ከፍ የማለታቸው ምክንያት የሙሴን ህግ በመተላለፍ አቅም የሌላቸውን የራሳቸውን ህብረተሰብ እየበዘበዙ ነበር፡፡
በቁ 10 ውስጥ ከተጠቀሱት ሁለት ሰዎች ጋር የሚዛመድ ቁልፍ የቃላት ሕንፃ ማየት ይቻላል (UBS፣*የመመሪያ መፅሐፍ፣ ገፅ* 106-109)፡፡

1. "ጠሉ ተጸየፉ" ይህ ቡድን ከቁ 11-12 ውስጥ ተጠቅሷል
2. "የሚገስጸውን እውነትም የሚናገረውን" እነዚህ በቁ 13 ውስጥ ተጠቅሰው ነበር፡፡

## አሞፅ: 5:14-15

**14 በሕይወት ትኖሩ ዘንድ መልካሙን እንጂ ክፉውን አትፈልጉ**
**እንዲህም እናንተ እንደ ተናገራችሁ የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሆናል።**
**15 ክፉውን ጥሉ፥ መልካሙንም ውደዱ፥ በበሩም አደባባይ ፍርድን አጽኑ**
**ምናልባት የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር ለዮሴፍ ቅሬታ ይራራ ይሆናል።**

**5:14 "መልካሙን እንጂ ክፉውን አትፈልጉ"** የነብዩን የሰላ ንፅፅር አስተውል (ዝ.ከ. ቁ 15) ዘላለማዊ ለውጥ ያለው ምርጫ አለ፡፡ "*መፈለግ*" (BDB 205፣ KB 233፣ *Qal* ትዕዛዝ አንቀፅ) ሌላ ትዕዛዝ አንቀፅ ነው፡፡ የዚህን ትዕዛዝ አንቀፅ በቁ 4 እና በቁ 6 ውስጥ በሥነ ምግባራዊ ሕይወት ላይ ትኩረት ከሚያደርገው ጋር ያለውን ዝምድና አስተውል፡፡መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ሁለት ነገሮች ላይ ትኩረት እንዳለው መታወስ አለበት ፤ የፍቅር ግላዊ ግንኙነት እና ድርጊቶች (ዝ.ከ. ኤፌ 2:8-10 እና 1ኛዮሐ 3:23)፡፡ አሞፅ እስራኤልን "መልካሙን ፈልጉ" በማለት ይገስጻቸዋል፡፡ኢሳያስ ይህን ተመሳሳይ ግስ በመጠቀም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ፍርድን ፈልጉ በማለት ይገስጻቸዋል (ዝ.ከ. ኢሳ1:17)፡፡ ስለምንድን ነው የሚገደን?
ስለምንድን ነው የተራብነው? ምንድን ነው የምንፈልገው? የነዚህ ጥያቄዎች መልስ ማን እንደሆንን እና ማንን/ምን እንደምናገለግል ይነግረናል!

▣ **"የሰረዊት አምለከ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሆናል፡፡"** ይህ እግዚአብሔር ሊሰራው የሚችለው ትልቁ ቃል ኪዳን ነው (ዝ.ከ. መዝ23)፡፡ "የሰራዊት አምላከ እግዚአብሔር" የሚለው መጠሪያ በብሉ ኪዳን ውስጥ ሁለት የሚዛመዱ ትርጉሞች አሉት፤ (1) ያህዌ መልአካዊ ጦር አዛዥ እንደሆነ እና (2) ያህዌ መልአካዊ ኃይልን የሚወክሉ የኮከቦች አካል ተቆጣጣሪ እንደሆነ (የባቢሎን ጣዖት አምልኮ)፡፡ ልዩ ርዕስ: የአማልክት ስም በ 1:2 ተመልከት፡፡

▣ **"እንዲሁም እናንተ እንደ ተናገራችሁ "** አሞፅ ምናልባት እያመለከተ ያለው

1. 1 የተለመደውን የካህናት/የአይሁድ መምህር አስተምሮ
2. በብዛት የሚደረግ የአምልኮ ሥነ ሥርዓት /መዝሙር
3. እንደገና እስራኤል የተመረጠች ቅዱስ ሕዝብ እንደሆነች ማረጋገጫ (ለምሳሌ ፣ ዘፀ 19:5-6፣ ዘዳ7:6፣ 14:2)

**5:15 "ክፉውን ጥሉ መልካሙንም ውደዱ በበሩም አደባባይ ፍርድን አጽኑ"** እነዚህ ሶስት የእብራዊያን ትዕዛዝ አንቀፆች ናቸው፡፡

1. "ጥላቻ"(BDB 971፣ KB 1338፣ *Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)*
2. "ፍቅር " (BDB 12፣ KB 17፣ *Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)*
3. "ማፅናት"(BDB 426፣ KB 427፣ *Hiphil IMPERATIVES (*ትዕዛዝ አንቀፅ)

እነዚህ የሙሴን ቃል ኪዳን ያንጸባርቃሉ፡፡ ለአሞፅ በዓለማዊ እና በተቀደሰ መካከል ፤ በልብ እና በእጅ መካከል ልዩነት እንደሌላቸው አስተውል (ዝ.ከ. ሚክ 6:8)፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝብ የእግዚአብሔርን ባህሪ ማንጸባረቅ አለበት!
"ማፅናት" የሚለው ቃል ፍቱን፤ዓላማ ላለው ተግባር ቅዱስ አጻጻፍ አለው (ለምሳሌ ፣ ሆሴ2:3)፡፡ የእግዚአብሔር ታማኝነት በአዕምሮአቸው እና በልባቸው የፍርድ ፣ የጥሩነት እና የፍፁምነት አሸናፊነትን በሁኔታቸው ሊያረጋግጥላቸው ይገባል፡፡

▣ **"ምናልባት ጌታ ለዮሴፍ ቅሬታ ይራራ ይሆናል፡፡"** ነብዩ ለሚጸጸቱ እና እምነታቸውን ለሚተዉ (ማለትም፤ "እኔን ፈልጉ" ቁ 4፣ "እግዚአብሔርን ፈልጉ" ቁ 6) ጥቂት እስራኤላዊያን የተገደበ ተስፋን (ማለትም፤"ምናልባት" BDB 19) እያወጀ ነው፡፡

## አሞፅ: 5:16-17

**16 ስለዚህ ጌታ የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦**
**በየአደባባዩ ሁሉ ላይ ዋይታ ይሆናል በየመንገዱም ሁሉ ላይ ወዮ ወዮ ይባላል**
**ገበሬዎቹም ወደ ልቅሶ፥ አልቃሾቹም ወደ ዋይታ ይጠራሉ።**
**17 በመካከልህ አልፋለሁና በወይኑ ቦታ ሁሉ ልቅሶ ይሆናል፥ ይላል እግዚአብሔር**

**5:16 "ስለዚህ"** ይህ ከቁ 10-13 ካለው ጋር ይዛመዳል፡፡ ከቁ 4-6 ውስጥ ከሚጀምረው ንስሃ የመግባት ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ጋር የሚዛመድ አይደለም (ቁልፍ ቃል፤ "መፈለግ")፡፡

▣ **"በየአደባባዩ ሁሉ ላይ ዋይታ ይሆናል ' ወዮ!ወዮ ' ይባላል"** ነብዩ የቀብር ስርዓት ላይ የሚደረገውን ሙሾ በ 5:1 ውስጥ ጀምሮታል ፤ አሁን ፍርዱ ስለመጣ እያንዳንዱ ሰው ለቅሶ ላይ ነው፡፡ "አደባባይ" ከ"በየበሩ" ወይም "በየገበያውም" ጋር ትይዩ ሊሆን ይችላል፡፡ "መንገዶች" (BDB 299) የሚለው ቃል ራሱ አደባባይ ወይም ገበያ የሚል ትርጉም ሊኖረው ይችላል (ለምሳሌ 1ኛ ነገ 20:34)

▣ **"ገበሬዎቹም"** "ገበሬ" የሚለው ቃል "ደሃውን" እንደ ሚያመለክት አምናለሁ፡፡ በሰለጠነው ምዕራባዊ ባህል ውስጥ እንዳለው ደሃ ሳይሆን በቤተሰብ መሬት (ከያህዌ በተሰጠ) ላይ ሆኖ ሲበዘበዝ የቆየን ትንሹን ገበሬ ነው፡፡ በሰንበት አመት እና በኢቤል አመት ያለውን በሙሴ የተጠቀሰን ግዴታ ችላ የማለት እና መሬትን ለዘለቄታው የመውሰድ ሁኔታ ነበር፡፡

▣ **"አልቃሾቹም"** በመካከለኛው ምስራቅ አቅራቢያ ያሉ ሰዎች በጣም ገላጭ የሆነ የሃዘን ስርዓት አላቸው፡፡ ይህ የሃዘን አገላለፅ ባሕል እንዲጠበቅ የሚረዱ ስልጡን ሰዎች ነበሩ (ዝ.ከ. 2ኛ ዜና35:25፣ ኤር 9:17)፡፡ ጀምስ ኤም ፍሪማን ፤ የመፅሐፍ ቅዱስ ስርዓቶች እና ልምዶች፣ ገፅ 283-284 ይመልከቱ፡፡

**5:17 "በመካከልህ አልፋለሁና"** ይህ ተመሳሳይ ሃረግ የሞት መላዕክት ለፍርድ ግብፅ ውስጥ በ እግዚአብሔር ፋሲካ ምሽት ሲያልፍ በ ዘፀ 12:12 ላይ ተገልጿል፡፡
የእግዚአብሔር መምጣት ለፍርድ ወይም ለበረከት ሊሆን ይችላል (ዝ.ከ. v 18)፡፡ እስራኤል ለበረከት እንደሆነ እርግጠኛ ነበረች ፤ ነገር ግን አሞፅ ለፍርድ እንደሆነ ገልጾ ነበር፡፡አስገራሚ ምፀት፣ አሳዛኝ ተገላቢጦሽ (ዝ.ከ. v ከቁ 18-20)! በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ የሰው ዘር በሙሉ እግዚአብሔርን የመፈለግ ስሜት አላቸው (ዝ.ከ.ቁ 14ለ)፡፡ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር መሆን ይፈልጋል ፤ ነገር ግን የእኛ ሃጥያት ህብረት ሳይሆን ፍርድን አስፈላጊ እንዲሆን አድርጎታል!

## አሞፅ: 5:18-20

**18 የእግዚአብሔርን ቀን ለምትፈልጉ ወዮላችሁ! የእግዚአብሔርን ቀን ለምን ትፈልጋላችሁ?**
**ጨለማ ነው እንጂ ብርሃን አይደለም።**
**19 ከአንበሳ ፊት እንደ ሸሸ ድብም እንዳገኘው ሰው፥**
**ወይም ወደ ቤት ገብቶ እጁን በግድግዳ ላይ እንዳስደገፈና እባብ እንደ ነደፈው ሰው ነው።**
**20 የእግዚአብሔር ቀን ብርሃን ሳይሆን ጨለማ አይደለምን?**
**ፀዳል የሌለውም ድቅድቅ ጨለማ አይደለምን?**

▣ **"የእግዚአብሔርን ቀን ለምትፈልጉ"** ይህ ግስ(BDB 16፣ KB 20፣ *Hiphil* PARTICIPLE) "ለራሳቸው ፍላጎት" ማለት ነው፡፡እነዚህ ሰዎች የቃል ኪዳኑ ሕዝቦች ስለነበሩ የእግዚአብሔርን መምጣት (ማለትም፤ "የእግዚአብሔር ቀን") በረከትን እና ነፃነትን ሊያመጣ እነደሆነ ያስቡ ነበር (ዝ.ከ. 3:2)፡፡ ነገር ግን በዚሁ ምክንያት መሰረት ፍርድ ነበር የመጣው፡፡ ልባቸው በመታወሩ ምክንያት እግዚአብሔር ወደ እነሱ የሚመጣው እንደ ፈራጅ (ዝ.ከ. 3:14፣ 5:18፣ 8:3፣9፣11፣13) ሆኖ እንጂ እንደ አዳኝ (ዝ.ከ. 9:11፣13) አልነበረም፡፡ሃይማኖታቸው ውጤቱ አእርግማን ሆነ (ዝ.ከ. ዘዳ 27-29)፡፡
ከነብዮች ጸሐፊያን አሞፅ የመጀመሪያው ነው፤ እንዲሁም ደግሞ ይህ "የእግዚአብሔር ቀን" የሚለው ሃረግ የመጀመሪያ አጠቃቀም ነው (በ2:16 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት)፡፡ ምናልባትም ከ "ቅዱስ ጦርነት" ቀኖች የተገኘ ዘይቤ ሳይሆን አይቀርም (ማለትም፤ ኢያሱ እና Judges)፡፡ ያህዌ ያለና የነበረ የቃል ኪዳኑ ህዝብ ደጋፊ እና ጠባቂ ነበር ፤ ነገር ግን በግጭት ጊዜያት በታምራዊ መገለጡ የእሱን ህዝቦች ከአደጋ ጠብቋቸዋል፡፡ ሆኖም ግን እስራኤል ቃል ኪዳኑን ከመተላለፏ የተነሳ እጣ ፋንታዋ ወደ ፍረድ እና መጣል ተለውጧል (ዝ.ከ. እዩ 2)፡፡

▣ **"ጨለማ ነው እንጂ ብርሃን አይደለም፡፡"** ይህ በእነዚህ ቃላት መሃከል ያለውን ንፅፅር የቀጠለበት ሁኔታ ነው (ዝ.ከ. 4:13ሐ፣ 5:8ሐ፣20)፡፡
**5:19** ፈፅሞ ከእግዚአብሔር ፍርድ የሚመለጥበት ምንም ቦታ የለም፡፡
**5:20** አስገራሚ ምጸት! አስገራሚ ሃዘን!

▣ **"ድቅድቅ ጨለማ"** "ማብራት" (BDB 618) ምንልባትም የእግዚአብሔር ክብር ሌላ መገለጫ ሊሆን ይችላል፡፡

## አሞፅ: 5:21-24

**[21] ዓመት በዓላችሁን ጠልቼዋለሁ ተጸይፌውማለሁ የተቀደሰውም ጉባኤአችሁ ደስ አያሰኘኝም።**
**[22] የሚቃጠለውን መሥዋዕታችሁና የእህሉን ቍርባናችሁን ብታቀርቡልኝም እንኳ**
**አልቀበለውም ለምስጋና መሥዋዕት የምታቀርቡልኝን የሰቡትን እንስሶች አልመለከትም።**

> [23] የዝማሬህንም ጩኸት ከእኔ ዘንድ አርቅ የመሰንቆህንም ዜማ አላደምጥም።
> [24] ነገር ግን ፍርድ እንደ ውኃ፥ ጽድቅም እንደማይደርቅ ፈሳሽ ይፍሰስ።

**5:21-24** ይህ ቁጥር በዘሌዋዊያን 1-7 ውስጥ የቀረበውን የመስዋዕት ስረዓት እግዚአብሔር እንደተቃወመው ያሳያል? በነብያቶች መጽሃፍ ወስጥ እግዚአብሔር በሕዝቡ የመስዋዕት ሥርዓት ልምምድ ድስተኛ የማይሆንበት ሁኔታን የሚያሳዩ ብዙ ጠንካራ አንቀጾች አሉ (ዝ.ከ. ኢሳ1:11-17፣ ኤር 6:20፣ 7:21-23፣ ሆሴ6:6 ፣ አሞፅ 5:21-27፣ ሚል 6:8)፡፡የመስዋዕት ሥርዓቱ ያህዌ የሰው ልጅ ኃጥያትን የሚሸፍንበት እና ከሚወደው የሰው ልጅ ጋር ያለውን የፍቅር ፣ የግል እና የእምነት ግንኙነት የሚቀጥልበት እና የሚያዳብርበት መንገድ ነው፡፡ ሆኖም ግን እስራኤል ይህን ስርዓት የፀሎት ሥነ ሥርዓት ብቻ ከማድረግም አልፎ ከአረማዊ ልምዶች ጋር ቀላቅላዋለች፡፡ ያህዌ ህብረትን ይፈልጋል! ያህዌ የእሱን ባህሪ የሚያንጸባርቅ ህዝብ ይፈልጋል! ያህዌ ሁሉንም የሰው ዘር በተመረጠው ህዝብ በኩል መድረስ ይፈልጋል (ዝ.ከ. ዘፍ 12:3፣ Exod 19:5-6)፡፡

**5:21 "ዓመት በዓላችሁን ጠልቼዋለሁ ተጸይፌዉማለሁ ጉባኤአችሁ ደስ አያሰኘኝም፡፡"** እነዚህ ጠንካራ ቃላት ናቸው! በጣም ሃይማኖታዊ ነበሩ ፤ ነገር ግን ፍላጎታቸው እና ልባቸው ከእግዚአብሔር በጣም ርቀ ነበር፡፡
ሃይማኖታዊነታቸው ለእግዚአብሔር ያላቸውን ከፍተኛ ጥላቻ የሚያሳይ ነበር (ዝ.ከ. ኢሳ29:13)! የመጀመሪያዎቹ ሁለት ግሶች "ጠልቼዋለሁ" (BDB 971፣ KB 1338) እና "ተጼይፌዋለሁ" (BDB 549፣ KB 540) *Qal* PERFECTS ሲሆኑ የሚወክሉትም የተረጋጋ ፤ የተሟላ ዝንባሌን ነው፡፡

▣ **"ዓመት በዓል"** (BDB 290) የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ ሶስቱን ዋና አመታዊ ፌሽታዎችን ለማመልከት ያገለግላል(ዝ.ከ. ዘፀ 23:15-16፣ ዘሌ23)፡፡ እነዚህ ለሁሉም ወንዶች አስፈላጊ ፌሽታዎች ነበሩ፡፡

▣ **"ደስታ"** (BDB 926፣ KB 1280፣ *Hiphil* IMPERFECT) የሚለው ቃል በቃል ሲታይ "ሽታ" ማለት ሲሆን ይህም በያህዌ ተቀባይነትን ያገኘ መስዋዕት የሚታወቅበት የሙሴ ሃረግ የሆነውን "መልካሙ መዓዛ" የሚለውን ያመለክታል (ለምሳሌ፤ ዘፍ 8:21፣ ዘፀ 29:18፣25፣ ዘሌ26:31፣ 1ኛ ሳሙ 26:19)፡፡

**5:22** ህብረት የሌለበት ሃይማኖታዊነት ከፍተኛ ነውር ነው (ዝ.ከ. ኢሳ1: 10-20፣ ኤር 7)፡፡ ያህዌ የመስዋዕት ስርዓቱን ሙሉ ለሙሉ አልተቃወመውም ፤ ነገር ግን የመስዋዕት ስርዓቱን አላግባብ የመጠቀም ሁኔታን ተቃውሟል(ንስሃ በሌለበት እምነት የሚደረግ አምልኮ ፣ ያለአግባብ የተገነባ ዝንንባሌ)!

▣ **"አልመለከትም"** "መመልከት" (BDB 613፣ KB 661፣ *Hiphil* IMPERFECT) የሚለው ቃል በመቀበል ወይም በመስማማት ስሜት ቀርቧል፡፡

▣ **"የሰቡትን"** ይህ (BDB 597) ለመስዋዕትነት ለመቅረብ እንክብካቤ ይደረግለት የነበረን ወጣት እንስሳን ያመለክታል፡፡

**5:23 "የዝማሬህንም ጩኸት ከእኔ ዘንድ አርቅ"** ይህ (BDB 693፣ KB 747) *Hiphil* ትዕዛዝ አንቀፅ ነጠላ ተባዕታይ ጾታ ነው፡፡ አግባብ ባለው ፍላጎት ካልሆነ በስተቀር የተቀደሰ እና አስገራሚ መዝሙርም ቢሆንም እንኳን ቀልድን ፣ ግብዞዊነትን እና ለእግዚአብሔር ከፍተኛ ጥላቻ የሚያሳይ ነው፡፡ እግዚአብሔር መልክን ብቻ ሳይሆን ፍላጎትንም ይፈልጋል! ይህ ቁጥር የሰሜን ነገዶች በእየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ውስጥ (በዳዊት የተቀነባበረ ዝ.ከ. 2ኛ ሳሙ 6:5፣15) ይደረጉ የነበሩትን የአምልኮ መልኮች (ማለትም ፤ በነቢያት ጉባኤ የተቀነባበረ መዝሙር ዝ.ከ. 1ኛ ሳሙ 10:5) እንደወሰዱ ያሳያል፡፡
መሪዎቹ (ኢዮርብአም 1ኛ) የተላመዱት ሕዝቦች በመካከላቸው ልዩነት እንዳለ እንዳይሰማቸው እንዚህ የሰሜን መሰዊያዎች (ማለትም፤ ዳን እና ቤቴል) እንዲባዙ ይፈልጉ ነበር፡፡ግሶቹ ነጠላ መሆናቸው አስገሪሚ ነው፡፡ በርግጥ አሞፅ በቁ 23 ውስጥ በቤቴል ስላሉ ትላልቅ ካህናት እየተናገረ ነው፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **NASB፣ NRSV ፣** | |
| **TEV ፣ NIV** | **"በገናዎች"** |
| **NKJV ፣ NET** | **"የጅማት የሙዚቃ መሳሪያዎች "** |
| **NJB** | **"ክራሮች"** |
| **REV ፣ JPSOA** | **"ዋሽንት መሰል"** |

ብዙዎቹ የእንግሊዝኛ ትርጓሜዎች እንደሚያሳዩት ፤ ዘመነኞች ይህ ምን ዓይነት የተቃኘ የሙዚቃ መሳሪያ እንደሚያመለክት አያውቁትም፡፡ከየትኞቹ ሌሎች የሙዚቃ መሳሪያዎች ጋር እንደሚመደብ ማስታወሻ ለመውሰድ 2ኛ ሳሙ 6:5 እና መዝ 92:3 ይመልከቱ፡፡የአሶራዊያን የግድግዳ ስዕሎች እንደሚያመለክቱት ይህ መሳሪያ ልክ እንደ እኛ ቫዮሊን መጫወቻ ፤ ገመዶች በድምፅ ማውጫ ሳጥን ያሉት መሳሪያ ሊሆን ይችላል፡፡የጄምስ ኤም ፍሪማን ፤ የመፅሐፍ ቅዱስ ስርዓቶች እና ልምዶች ገፅ 221-222 ላይ ይመልከቱ፡፡

**5:24** ይህ በአሞፅ ወስጥ ታዋቂ ጥቅስ ነው፡፡እግዚአብሔር ሕዝቦቹ በተወሰኑ የአምልኮ ቀናት ብቻ ሳይሆን በእያንዳንዱ ቀን በማንነቱ ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ይፈልጋል፡፡ እውነተኛ እምነት የእኛ ማንነት እንጂ እኛ የምናደርገው ነገር አይደለም ፤ ነገር ግን የእኛ ማንነት በምናደርገው ነገር ፣ በምናደርግበት መንገድ እና በምናደርግበት ምክንያት ውስጥ በግልፅ ይታያል፡፡ምናደርገው ነገር እና ለምን እንደምንነደርገው (ዝ.ከ. ማቴ 7)፡፡ "ፍርድ" እና "ፅድቅ" በቁ 7 ውስጥ እንዳለው ተያያዥነት አላቸው፡፡ በዚህ ዓውድ ውስጥ ቃሎቹ የሙሴ ቃልኪዳን በእግዚአብሔር እና በአምላኪው መካከል አግባብ ያለው ግንኙነት ሲያሳይ እንደቆየ የሰው ልጁ መቀበሉን ያሳያሉ—ያመለክ እና አምላኪ፡፡
ይህ "መፍሰስ" (BDB 146፣ KB 193) የሚለው ግስ የትዕዛዛዊ አንቀፅ ስሜት የሚያመለክት *Niphal* JUSSIV E ነው፡፡

▣ **"እንደማይደርቅ ፈሳሽ"** ይህ (BDB 450) *መቼም የማይደርቅን ምንጭ ያመለክታል (ማለትም፤ ወቅታዊ አይደለም)፡፡ ይህ ንቁ የእምነት ህይወትን የሚገልጽ ጠንካራ ዘይቤ ነው፡፡*
(ዝ.ከ. ኤር22:3 ፣ እዝ45:9፣ ሚል 6:8)

**አሞፅ: 5:25-27**

**25 የእስራኤል ቤት ሆይ፥ በውኑ በምድረ በዳ አርባ ዓመት ሙሉ መሥዋዕትንና ቍርባንን አቅርባችሁልኛልን?**
**26 ለራሳችሁም የሠራችኋቸውን ምስሎች፥ የሞሎክን ድንኳንና የአምላካችሁን የሬፋን ኮከብ አነሣችሁ።**
**27 ስለዚህ ከደማስቆ ወደዚያ አስማርካችኋለሁ፥ ይላል ስሙ የሠራዊት አምላክ የተባለ እግዚአብሔር፡-**

**5:25** *ይህ ለመተርጎም በጣም አስቸጋሪ የሆነ ቁጥር ነው፡፡ጥያቄ (ከቁ 25 የቀጠለ) ወይም ማረጋገጫ (ከቁ 27 የሚያገናኘው፣ ዝ.ከ. TEV )፡፡ ሁለት የአተረጓገሞች አሉ (1) አሞፅ የእስራኤል ልጆች በምድረበዳ ወስጥ መስዋዕ እንዳላቀረቡ እየተናገረ (ዝ.ከ. ኤር 7:21-22 and NJB) ወይም (2) ምንም እንኳን በተወሰነ መንገድ መስዋዕት አቅርበው ቢሆንም (JB) የመስዋዕታቸው አላማ ወደ ምርኮ ይመሯቸው ለነበሩት (አሸሙር) የአሶራዊያን ሃሰተኛ አማልክት እንጂ ያህዌ አልነበረም፡፡*

**5:26** *በዚህ ቁጥር የጊዜ ሁኔታ ላይ ብዙ መላምቶች አሉ፡፡ የቁ 25ን አርባ አመት የምድረ በዳ ጉዞ ያመለክታል ወይስ የሚመጣውን የአሶራዊያን ግዞት መከራ? የተጠቀሱት የአሶራዊያን የኮከብ ጣዖቶች ስለሆኑ ይህ ቁጥር የጊዜውን ወይም የሚመጣውን ምርኮ የሚያመለክት ይመስላል ፤ ቁ 5 ደግሞ ከዘፀዓት በኋላ ከግብፅ ሲወጡ የነበረውን የምድረበዳ ጉዞን ያመለክታል፡፡ሌላው አማራጭ አስራኤላዊያን፤ ምንም እንኳን ከግብፅ ከወጡ በኋላ ለብዙ አመታት መፈጸም የማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ ስለነበሩ ሊፈፅሙት ባይችሉም የመስዋዕት ሥርዓቱን የመጨረሻ አድርገውት ነበር (ምንም የመሰዊያ ቦታ የለም)፡፡ በእነዚያ አመታት የእምነታቸው ትኩረት በእግዚአብሔር ፍቅር ፣ መገኘት እና ምሪት ግላዊ መተማመን እንጂ መስዋዕት ማቅረብ አልነበረም፡፡ ይህ የመስዋዕት ስርዓቱን የሚነቅፍ አይደለም፡፡ በእርግጠኝነት የእግዚአብሐር ፍቃድ ነበር ፤ ነገር ግን ዋና ግቡ አገልግሎቱ ፣ የአምልኮ ሥነ ሥርዓቱ እና አምልኮው ሳይሆን እግዚአብሔር እራሱ ነበር! ተነሳሽነት እና ዝንባሌ አስፈላጊ ናቸው!*
*የሓዋ 7:42-43 ውስጥ የስጢፋኖስን አሞፅ 5:25-27ን አጠቃቀስ ያስተውሉ፡፡ በመጀመሪያው ክፍል ዘመን ከክርስቶስ ልደት በኋላ የነበሩ አብዛኞቹ አይሁዶች የሰባ ሊቃናት ትርጉምን ብሉይ ኪዳን ትርጉም ይጠቀሙ ነበር፡፡ በአንዳንድ ቦታዎች ውስጥ ከ ማሶርቲክ ጽሑፍ የተለየ አካሄድ ተጠቅሟል፡፡ይህ አስቸጋሪ ነው! ሆኖም ግን በሁሉም ብሉይ ኪዳን መድብሎች (የሙት ባህር ጥቅሎች) ውስጥ ሁለቱም ባህሎች ይገኛሉ፡፡ ሁለቱም ቁጥሮች የእምነቱን ወይም የባህላዊ ልምምዱን እውነትነት ወይም ዘላቂነት የሚነኩ አይደሉም፡፡ እኛ በእብራዊያን ብሉ ኪዳን እና በእብራዊያን ብሉ ኪዳን ጥንታዊው የብራና ጽሑፍ መካከል ባለ ልዩነት ክርስቲያናዊነት እንደማይቆም ወይም እንደማይወድቅ መረዳት አለብን፡፡በግሊሰን አርቸር የመጽሐፍ ቅዱስ ክብደቶች ኢንስይክሎፒዲያ ገፅ 381-382 ውስጥ ያለውን መረጃ ይመልከቱ፡፡*

▣ **"የአምላካችሁን የሬፋንን"** ሰባ ሊቃናት ትርጉም "ድንኳን ማንሳት" የሚል አገላለጽ አለው ፤ ሆኖም ግን ይህ ቃልአዳር-መለክ-ሳተርን (በኦገርቲክ ኒኑርታ ይባላል) የሚባለውን የጦር ሃሰተኛ አምላክ ለማመልከት በአሶራዊያን መዝገብ ውስጥ ይገኛል፡፡ አማልክቱ "ንጉስ" ተብሎ እንደሚጠራ አስተውል ፤ ይህ ደግሞ በባህላዊው ታሪክ ያህዌ እንደ ንጉስ ይታይ እንደነበር የሚያሳይ ነው፡፡
▣

| | |
|---|---|
| NASB | **"ኪዩን"** |
| **NKJv** | **"ቺዩን"** |
| **NRSV ፣ TEV ፣** | |
| **NJB** | **"ኬዋን"** |
| **NIV ፣ REB** | **"እምድ"** |

*ይህም የአሶራዊያንን ኮከብ ጣዖት የሚያመለክት ሲሆን ሳተርን በሚባለው የፀሐይ ጭፍራ ይጠራል (BDB 475)፡፡*
*NASB ከኮከቡ ጣዖት ስም ተናባቢን እና የእብራዊያን ቃል ከሆነው "ከፍተኛ ጥላቻ" (BDB 1055) ደግሞ የድምፅ አናባቢን በመውሰድ የእብራዊያን የሆነውን የቃላት አጻጻፍ ይገልጻል፡፡ ይህ ለእብራዊያን ቁም ጸሐፊዎች በጣዖታት ስም ፣ በንጉሶች እና በሕዝብ ላይ ለመሳለቅ የሚጠቀሙበት የተለመደ መንገድ ነው(ለምሳሌ ፣ ሬፋን)፡፡የ "ኬዋን" ቃላት አጻጻፍ ከ አካዲያን ወይም ከአረብ የተገኘ ነው፡፡ቃሉ እንደ "እምድ" ሆኖ መተርጎሙ ቃሉ "ጽኑ መሆን" ከሚለው ዋና ቃል የመጣ ስለመሆኑ ፍንጭ ሰጪ ነው(kwn)፡፡*

**5:27 "ከደማስቆ ወደዚያ አስማርካችኋለሁ"** *ይህ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ 722 ከሰማሪያ ሶስት አመት ከበባ በኋላ የአሶራዊያንን ግዞት ያመ ልክታል (ዝ.ከ. የሚሆነው 4:3፣ እና ሆሴ9:3፣ 10:6፣ 11:5)፡፡ይህ እንደገና ስለ ዘዳ27-29ን እርግማን እና በረከት የሚያወሳ ንዑስ ክፍል ነው፡፡*

▣ **"ይላል ስሙ የሰራዊት አምላክ የተባለ እግዚአብሔር "** የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ከነበሩት ስሞች አንዱ "ያህዌ የሰራዊት ጌታ" ወይም "ያህዌ የሰማይ ሰራዊት ጌታ" ነው (ዝ.ከ. 1ኛ ሳሙ 1:3)፡፡ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ *ኤሎሄም* (*Elohim)* በያህዌ ተተክቷል፡፡እዚህ ላይ ርዕሱ እግዚአብሔር የሰማይ ሰራዊት ተቆጣጣሪ ከመሆኑ ጋር የተገናኘ ነው (ማለትም ፤ ኮከቦቹ)፡፡ ያህዌ የኮከቦች አማልክት አይደለም (ማለትም ፤ የአሶራዊያን ኮከብ ጣዖታት)፣ የእስራኤል ተስፋ እንጂ! በብዙ ጽሑፎች የሰማይ ብርሃናትን ማምለክ የተወገዘ ነው (ዝ.ከ. ዘዳ4:19፣ 8:2፣ 17:2-5፣ 2ኛ ነገ 23:4-5፣11፣ ኤር 8:2፣ 19:13፣ 32:29፣ ሶፎ1:5) ብሉ ኪዳን የሰማይ ብርሃናትን እግዚአብሔር እንደ ፈጠረ እና እንደሚቆጣጠር ይናገራል (ዝ.ከ. ዘፍ 1:14-19፣ መዝ19:1-6፣ ነህ 9:6)፡፡ "የሰራዊተ ጌታ" የሚለው የጣዖት አምልኮን የሚያወግዘው ከእነዚ ጽሑፎች ጋር ስለሚያያዝ ነው (የጣዖታትን/የመልዓክቶችን/በሰማይ ብርሃናት መናፍስትን ማምለክ ፤ ዝ.ከ. ሰባ ሊቃናት ትርጉም ዘዳ32:8)፡፡

# አሞፅ 6
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|
| | የእስራኤል ኃጢአተኝነትና የእግዚአብሔር ቅጣት (3:1-6:14) | | እስራኤል ማስጠንቀቂያና መስፈራሪያ ተሰጣት (3:1-6:14) |
| ለፅዮንና ለሰማሪያ ማስጠንቀቂያ | | የእስራኤል መፍረስ | በራስ መሞላቀቅ እና በነርሱ የውሸት ምንም አይደርስብንም የማለት ስሜት ላይ |
| 6:1-2 | | | |
| | 6:1-3 | 6:1-7 | 6:1-7 |
| 6:3-7 | | | |
| | | | ቅጣት:-ድርቅ፤የመሬት መናወጥ፤ ወረራ |
| 3:1-8 | | | |
| | 6:4-7 | | |
| | | | 6:8-11 |
| 6:8-11 | 6:8 | 6:8 | |
| | 6:9-10 | 6:9-10 | |
| | 6:11-14 | 6:11-14 | 6:12-14 |
| 6:12-14 | | | |
| | | 6:13 | |
| | | 6:14 | |

### የንባብ ምድብ ሦስት ዑደት (ገጽ vii ተመልከት)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

5. የመጀመሪያው አንቀጽ

6. ሁለተኛው አንቀጽ

7. ሦስተኛ አንቀጽ

8. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

### አሞፅ 6:1-3

**1 በጽዮን ላሉ ዓለመኞች፥ በሰማርያም ተራራ ላይ ተዘልለው ለተቀመጡ፥**
**የእስራኤልም ቤት ወደ እነርሱ ለመጡባቸው ለአሕዛብ አለቆች ወዮላቸው!**
**2 ወደ ካልኔ አልፋችሁ ተመልከቱ ከዚያም ወደ ታላቂቱ ሐማት ሂዱ**
**ከዚያም ወደ ፍልስጥኤም ጌት ውረዱ እነርሱ ከእነዚህ መንግሥታት ይሻላሉን?**
**ወይስ ድንበራቸው ከድንበራችሁ ይሰፋልን? 3 ከፉውን ቀን ከእናንተ ለምታርቁ፥ የግፍንም ወንበር ለምታቀርቡ፥**

**6:1 "ወዮላቸው"** የቃሉ አነባበብ በጣም የመበሳጨት ወይም የሃዘን ስሜት ያለው ይመስላል፡፡ ይህ ቃል ((BDB 222) የሰቆቃው ኤርሚያስ መፅሃፍን የሚገልፅ ነው፡፡(ዝ.ከ. 5:24) ነብዩ የእግዚአብሔርን አለመስማማት እና መጪ ፍርዱን ለመግለፅ የቀብር ስነስርዓት ሙሾን ቀጥተኛ

መልክ (የ 3-2 ምት) ተጠቅሟል፡፡ ይህ ቃል በኢሳያስ (ዝ.ከ. በ 1:4 ፣ 24 ፣ 5:8 ፣11፣18፣20፣21፣22 ፤ 10:1 ፤ 17:12 ፤ 18:1 ፤ 28:1 ፤ 29:1 ፣ 15 ፤ 30:1 ፤ 31:1 ፤ 33:1 ፤ 45:9 ፣ 10 ፤ ውስጥ በአሉታዊ መልኩ በ 10:5 በማያዳላ መልኩ እና በ 55:1 ውስጥ በአዎንታዊ መልኩ) እንዲሁም በኤርሚያስ (ዝ.ከ. 22:13 ፣ 18 ፤ 23:1 ፤ 30:7 ፤ 34:5 ፤ 47:6 ፤ 48:1 ፤ 50:27) ወስጥ ተጠቅሷል፡፡
ይህ ቃልአጋኖ እያንዳንዳቸው "ማልቀስ" የሚለውን ቃል የያዙ ተከታታይ ቦዝ አንቀፆች አሉት፡፡(ከ ቁ 1-7)፡፡

▣ ***"ተዘልለው ለተቀመጡ"*** ምንም ግስ የለውም፡፡ይህ ሃረግ ጊዜያዊ ባልሆነ መልኩ ተቀምጧል፡፡የ "ቸልተኛ ፣ የማይረባ እና ትዕቢተኛ" (BDB 983፣ ዝ.ከ. ኢሳ32:9፣11፤ ዘካ 1:15፤ and መዝ123:4) ትንቢታዊ ቅዱስ አፃፃፍ አለው፡፡
ቅንጦት ወይም ብልፅግና ወይም ደግሞ በማህበረሰቡ ያላቸው ቦታ አልነበረም ችግሩ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ይልቅ በነዚህ ነገሮች ላይ እምነት መጣላቸው እንጂ፡፡
በቀጣዮቹ ጥቂት ቁጥሮች ይህ በድን በተለያየ መንገዶች ይገለፃል፡፡

1. 1 ጥንካሬ የሚሰማቸው ቁ 1ለ
2. ክፉውን ቀን ከእናንተ ለምታርቁ ቁ 3
3. ከዝሆን ጥርስ በተሠራ አልጋ ላይ ለምትተኙ ቁ 4
4. ጭውውትን በግጥም የሚያቀርቡ (ከንቱ ዝማሬዎችን የሚዘምሩ)፣ ቁ 5
5. በፋጋ የወይን ጠጅ ለምትጠጡ ቁ 6

ሁሉም እነዚህ ሃረጎች የተወሰነ ምስተፃምር እንዲሁም ቦዝ አንቀፅ አላቸው፡፡

▣ **"በጽዮን"** ይህ ከ"በሰማሪያ ተራራ ውስጥ" (የሰሜኑ አስር ነገዶች ዋና ከተማ) ጋር የሚያያዝ ይመስላል፡፡ ሆኖም ግን ፂሆን ከ ሰባቱ የኢየሩሳሌም ከፍታዎች አንዱ ነው፡፡ስለዚህ ይህ ማለት፣

1. 1 የቃል ኪዳኑ ህዝብ ባጠቃላይ፣ 3:1፤ 6:8
2. ሁለቱም ይሁዳ እና እስራኤል ኃጥያተኞች እና ጥፋተኞች ነበሩ
3. ሲገለፁ የማይጓደኑ ነገር ግን ምንም ልዩነት እንዳይኖራቸው የታሰቡ

▣ **"አለቆች"** ይህ በቀጥታ"ጥሶ የሚገቡ ወንዶች" (BDB 666፤ KB ፣ 718፣ *Qal* ቦዝ አንቀፆች) ማለት ነው፡፡ የአረባዊ ስር ቃል "በጥንቃቄ የሚመረምሩ" (ይህም ማለት ፣ መሪዎች) የሚል ትርጉም አለው፡፡ ይህም የሚያመለክት የሚመስለው (1) እስራኤል ራሳቸውን ከእግዚአብሐር ፍርድ ለመጠበቅ ስምምነቶችን ያደርጉ የነበሩትን የቀድሞ መሪዎች (ይህም ማለት ወደ አሶራዊያን መሰደድ) ወይም (2) እነዚህ ሃብታም መሪዎች ስለራሳቸው የሚያስቡት ሃሳብ (ዝ.ከ. ቁ 13፤ አእት መፅሐፍ ቅዱስ ፤ ቲንዳል ትርጓሜ)

**6:2** አንድ ሰው ቁጥር 1 ን በተረዳበት መሰረት ላይ ተመስርቶ ይህ ቁጥር ሊሆን የሚችለው
1 የቃል ኪዳኑን ህዝብ እብሪተኛ አመራር የሚገልፁ የአሞፅ ቃላት (ይሁዳ እና እስራኤል) ከ 9:7 ጋር የሚመሳሰል፡፡
ሆኖም ግን ይህ የተወሰነ የፅሑፍ ማስተካከያዎች ተካተውበታል፡፡ (ዝ.ከ. UBS፣ የመምሪያ መጽሐፍ፣ #31፣ ገፅ 289)
2 ለህዝቡ መሪዎቹ የሰጡት አስተያየቶች(ዝ.ከ. አእት መጽሐፍ ቅዱስ ፣ ቲንዳል ትርጓሜ)፡፡

▣ **"ካልኔ"** ይህ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ 738 ትግሌዝ ፒልሰር 3ኛ ያጠፋት በሶሪያ ውስጥ የምትገኝ ጠንካራ ከተማ ነበረች (ዝ.ከ. ኢሳ10:6)፡፡ የመጪው የእስረኤልን ምርኮ ምሳሌ ሆኖ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት ነበር የእስራኤል ንጉስ የነበረው ምናህን ለአሶራዊያን ግብር መስጠት የጀመረው፡፡

▣ ***"ሐማት"****አንኮር መፅሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት (አንከር መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት)፣* ጥራዝ 3 ገፅ 33፣ ጥሩ የተብራራ አስተያየት አለው፡፡ "በደቡብ ጠርዝ ባብዛኛው የሰሜን እስራኤል ወሰን ተብላ ትታሰብ የነበረች በሶሪያ ውስጥ የምትገኝ ከተማ ነበረች (ዝ.ከ. 1ኛ ነገ 8:65፤ 1ኛዜና 13:5)፡፡ ከተማው አሶራዊያን ድል አድርገው መያዝ ይፈልጉት የነበረ ሲሆን (ኢሳ36:19) እንዲሁም ይኖሩባት የነበሩትም ተሰደው በእስራኤል ውስጥ ሰፍረው ነበር(2ኛ ነገ 17:24)፡፡" ይገኝ የነበረውም ከዳን ከተማ በስተሰሜን 150 ማይልስ ርቆ በኦራንተስ ወንዝ ላይ ነበር፡፡

▣ **"ጌት"** ፍልስጤማዊያን በደቡብ ምዕራብ ይሁዳ ውስጥ በየባህሩ በሚገኝ መሬት ላይ አምስት የከተማ ግዛቶችን መስርተው ነበር፡፡ከእነዚህ ውስጥ አራቱ በአሞፅ 1:6-8 ውስጥ ቀደም ብሎ ተገልፀዋል (ጋዛ ፣ አሽዶድ ፣ አሽከሎን እና ኤክሮን)፡፡ ጋጥ ደግሞ ሚል 1:10 ውስጥ ተጠቅሷል፡፡ ይህ ከተማ ከጊዜ በኋላ በአሶራዊያን ወድሟል፡፡

**6:3** ባለፀጋ መሪዎች የእግዚአብሔርን የጉብኝት ቀን በ(1) በመለኮታዊ ኃይል ወይም የዘዳ27-29 የቃል ኪዳን ወጤት በ(2) ቸል ለማለት በመሞከር (ዝ.ከ. TEV ) "ጥለው" (BDB 622፣ KB 672፣ *Piel* ቦዝ አንቀፆች ፣ ይህ ግስ በዚህ መልክ እዚህ ውስጥ ብቻ እንዲሁም በብሉ ኪዳን ውስጥ ሁለት ጊዜ ብቻ ዝ.ከ. ኢሳ66:5 ተገልጧል) ነበር፡፡ እዚህ ላይ ያለው ምፀት በሚያደርጉት ተግባራት ቀኑን እያፋጠኑት እንደነበር ነው!

▣ **"የግፍንም ወንወበር"** ይህ (1) የእስራኤልን መሪዎች ወይም (2) የአሶራዊያን መጪ ወረራ ሊያመለክት ይችላል፡፡
"ወንወበር" እንደ "ዘውድ" እንረዳዋለን ይህም የ"ንግስና" ዘይቤ ነው፡፡

## አሞፅ: 6:4-7

**4ከዝሆን ጥርስ በተሠራ አልጋ ላይ ለምትተኙ፥ በምንጣፋችሁም ላይ ተደላድላችሁ ለምትቀመጡ፥**
**ከበጎችም መንጋ ጠቦትን ከጋጥም ውስጥ ጥጃን ለምትበሉ፥**
**5 በመሰንቆም ድምፅ ለምትንጫጩ፥ እንደ ዳዊትም የዜማን ዕቃ ለምታዘጋጁ፥**
**6 በፋጋ የወይን ጠጅ ለምትጠጡ፥ እጅግ ባማረ ሽቱም ለምትቀቡ፥**
**ስለ ዮሴፍ መከራ ግን ለማታዝኑ ለእናንተ ወዮላችሁ!**

**7 ስለዚህ በምርኮ መጀመሪያ ይማረካሉ፥ ተደላድለው ከተቀመጡትም ዘንድ ዘፈን ይርቃል።**

**6:4-6** ይህ የሃብታምን የግል ፍላጎት ለማርካት ይደረግ የነበረን ሰፋ ያለ የመጠጥ ግብዣን የሚገልፅ ነው፡፡

**6:4 "ተደላድላችሁ"** ቃሉ (BDB 710፣ KB 756) በቁ 7 ውስጥ እንደገና ተገልጧል፡፡ አሉታዊ ቅዱስ አፃፃፍ አለው፡፡ ይህም ከ "ጋደም ማለት" (BDB 1011፣ KB 1486) ጋር ተያያዥነት ያለው ሲሆን በዚያን ጊዜ በፍልስጤም ውስጥ ያልተለመደ የአበላል መንገድ ሊሆን ይችላል፡፡ እንዲህ ከሆነ ዘንድ ሁለቱም አዲስ ፣ የውጪ እና ባህላዊ ያልሆኑ ተግባሮችን የሚያመለክቱ ናቸው (ይህም ማለት ፣ አረማዊ በእስራኤል መሪዎች ላይ የሚያደርጉት ተፅዕኖ)፡፡

**6:5 "እንደ ዳዊትም የዜማን ዕቃ ለምታዘጋጁ"** ይህ የዳዊትን ታሪካዊ የሙዚቃ ህይወት መግለጫ ነው፡፡

1. ዳዊት ራሱ
   - ሀ. ለሳኦል ተጫውቷል 1ኛ ሳሙ 16:16፣23፤ 18:10፤ 19:9
   - ለ. የዘለዋዊያንን ዘማሪዎች ሹሟል፣ 1ኛዜና 6:31፤ 15:1-16:43፤ 25:1-31፤ 2ኛ ዜና29:25-30
2. የዳዊት ሙዚቃ ምሳሌዎች
   - ሀ. 2ኛ ሳሙ 22
   - ለ. አብዛኛው የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ የመዝሙረ ዳዊት መጽሐፎች (ዝ.ከ. 72:72)
     - (1) ማሶሬቲኩ 73 መዝሙሮችን ያረጋግጣል
     - (2) ሰባ ሊቃናት ትርጉም 84 መዝሙሮችን ያረጋግጣል
     - (3) ቩልጌት 53 መዝሙሮችን ያረጋግጣል
   - ሐ. "የእስራኤል ጣፋጭ ዘማሪ" ተብሏል (ዝ.ከ. 2ኛ ሳሙ 23:1)

"ጭውውትን በግጥም መግለፅ" የሚለው ግስ (BDB 827፣ KB 967፣ *Qal* ቦዝ አንቀፆች) ትርጉሙ የተረጋገጠ አይደለም፡፡ በብሉ ኪዳን ውስጥ እዚህ ላይ ብቻ ይገኛል፡፡ በቀደምት እብረዊያን "ማቋረጥ" ወይም "መከፋፈል" ማለት ነው (ለምሳሌ፣ ከዛፍ ላይ ወይም ከደን ላይ የሚወድቅ ፍሬ)፡፡ "ማቀናበር" ወይም "ጭውውትን በግጥም መግለፅ" የሚለው ትርጉም ከአረባዊ ሃረግ የመጣ ነው፡፡
በዚህ ዓውድ ውስጥ ገላጮቹ የሚከተሉትን እያረከሱ ሊሆን ይችላል፡፡

1 የዳዊትን ቃናዎች፣ ግጥሞች

2 በቤተመቅደስ ውስጥ የነበሩ የሙዚቃ መሳሪያዎች

**6:6**

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"የመሰዊያ ጎድጓዳ ሳህኖች"** |
| **NKJv ፣ NRSv** | **"ጎድጓዳ ሳህኖች"** |
| **TEv ፣ NJB** | **"በጎድጓዳ ሳህኖች ሙሉ"** |

ይህ ከጠጪነታቸው ("ጎድጓዳ ሳህኖች ፣ ሲኒ አይደለም"፤ REB፣ "በጎድጓዳ ሳህን የተሞላ ወይን ትጠጣላችሁ") በላይ የቅዱስ እቃዎችን (ዝ.ከ. ዘጽ 4:6-8፤ ዘሁ 7:13) እርኩሰት ያለበት አጠቃቀምን (ዝ.ከ. ዳን 5:2) የሚገልፅ አይደለም፡፡ አንዳንዶች በኢሳ65:11 መሰረት ይህን እንደ አስማታዊ ልምምድ ያዩታል፡፡

## ልዩ ርዕስ፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አዝማሚያ በአልኮል እና በአልኮለኝነት

I. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት

ሀ. ብሉይ ኪዳን

1. ያይን - ይህ የወይን አጠቃላይ ቃል ነው (BDB 406)፣ እሱም 141 ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለ።ሥርወ ቃሉ ርግጠኛ አይደለም፣ ምክንያቱም ከዕብራይስጥ ሥርወ ቃል ስላልሆነ። እሱም የሚሆነው የኮመጠጠ የፍራፍሬ ጭማቂ፣ ባብዛኛውም ወይን ነው። ጥቂት ሁነኛ ምንባቦች፣ ዘፍ. 9፡21፤ ዘጸ. 29፡40፤ ዘኁ. 15፡5፣10።
2. ቲሮሽ - ይህ "ጉሽ የወይን ጠጅ" ነው (BDB 440)። በቅርብ ምስራቅ የዓየር ሁኔታ ምክንያት፣ ኩምጠጣ የሚጀምረው ጭማቂው ከተሰናዳ ከስድስት ሰዓት በኋላ ነው። ይህ ቃል የሚያመለክተው በመኮምጠጥ ሂደት ላይ ላለ ወይን ነው። ለሁነኛ ምንባቦች፣ ዘዳ. 12፡17፤ 18፡4፤ ኢሳ. 62፡8-9፤ ሆሴ. 4፡11 ተመልከት።
3. አሲስ - ይህ የአልኮል መጠጥ ነው፣ ("ጣፋጭ ወይን" BDB 7799፣ ምሳ. ኢዩኤል 1፡5፤ ኢሳ. 49፡26)።
4. ሴካር - ይህ "ጠንካራ መጠጥ" ነው (BDB 1016)። የዕብራይስጡ ሥር ጥቅም ላይ የሚውለው "ሰካራም" ወይም "ሰካር" በሚል ነው። እሱም አንዳች የተጨመረበት ይኖራል የበለጠ አስካሪ እንዲሆን። እሱም ከያይን ጋር ትይዩ ነው (ምሳ. 20፡1፤ 31፡6፤ ኢሳ. 28፡7)።

ለ. አዲስ ኪዳን

1. ኦዪኖስ - ከግሪኩ ያይን ጋር አቻ ነው
2. ኒኦስ ኦዪኖስ (ጉሽ ወይን) የግሪኩ አቻ ቲሮሽ (ማርቆስ 2፡22)
3. ግሊዩኮስ ቪኖስ (ጣፋጭ ወይን፣ ኤሲስ) - በአዲስነት መፍላት ላይ ያለ ወይን (ሐዋ. 2፡13)

II. መጽሐፍ ቅዱሳዊ አጠቃቀሙ

ሀ. ብሉይ ኪዳን

1. ወይን የእግዚአብሔር ስጦታ ነው (ዘፍ. 27፡28፤ መዝ. 104፡14-15፤ መክ. 9፡7፤ ሆሴ. 2፡8-9፤ ኢዩ. 2፡19፣24፤ አሞጽ 9፡13፤ ዘካ. 10፡7)።

2. ወይን የመሥዋዕታዊ ስጦታው አንደኛው አካል ነው (ዘጸ. 29፡40፤ ሌዋ. 23፡13፡ ዘኊ. 15፡7፣10፤ 28፡14፤ ዘዳ. 14፡26፤ መሳ 9፡13)።
3. ወይን እንደ መድኃኒት ያገለግላል (2ኛ ሳሙ. 16፡2፤ ምሳ. 31፡6-7)።
4. ወይን ተጨባጭ ችግር ሊሆን ይችላል (ኖህ - ዘፍ. 9፡21፤ ሎጥ- ዘፍ. 19፡33፣35፤ ሳምሶን- መሳ. 16፡19፤ ናባል- 1ኛ ሳሙ. 25፡36፤ ኦርዮ- 2ኛ ሳሙ. 11፡13፤ አምኖን- 2ኛ ሳሙ. 13፡28፤ ኢላህ- 1ኛ ነገሥ. 16፡9፤ ቤንሃዳድ- 1ኛ ነገሥ. 20፡12፤ ገዥዎች- አሞጽ 6፡6፤ እና ሴቶች- አሞጽ 4)።
5. ወይን ሊያዛባ ይችላል (ምሳ. 20፡1፤ 23፡29-35፤ 31፡4-5፤ ኢሳ. 5፡11፣22፤ 19፡14፤ 28፡7-8፤ ሆሴዕ 4፡11)።
6. ወይን ለተወሰኑ ወገኖች ክልክል ነው (ካህናት በሥራ ላይ፣ ሌዋ. 10፡9፤ ሕዝ. 44፡21፤ ናዝራውያን፣ ዘኊልቁ 6፤ እና ገዥዎች፣ ምሳ. 31፡4-5፤ ኢሳ.56፡11-12፤ ሆሴዕ 7፡5)።
7. ወይም እንደ የፍጻሜ መዳረሻነት መቼት ተደርጎ ተወስዷል፣ (አሞጽ 9፡13፤ አዩኤል 3፡18፤ ዘካ. 9፡17)።

ለ. ተረፈ መጽሐፍ ቅዱስ

1.ወይን በልኩ በጣም ይረዳል (መክብብ 31፡27-30)።
2. ራቢዎች የሚሉት፣ "ወይን ከመድኃኒት ሁሉ ታላቁ ነው፣ ወይን ሲያልቅ ነው ሌላ መድኃኒት የሚያስፈልገው።" (ባባ ባዝራ 58ለ)

ሐ. አዲስ ኪዳን

1. ኢየሱስ በርካታ ውኃ ወደ ወይን ቀይሯል (ዮሐንስ 2፡1-11)።
2. ኢየሱስ ወይን ጠጥቷል (ማቴ. 11፡18-19፤ ሉቃስ 7፡33-34፤ 22፡17)።
3. ጴጥሮስ በስካር ተከሷል፣ በጰንጠቆስጤ "ጉሽ ወይን"፣ (ሐዋ. 2፡13)።
4. ወይን እንደ መድኃኒት ያገለግላል (ማርቆስ15፡23፤ ሉቃስ 10፡34፤ 1ኛ ጢሞ. 5፡23)።
5. መሪዎች ጠጪ መሆን አይኖርባቸውም። ይህም ባጠቃላይ መጠጥን አለመቅመስ ማለት አይደለም (1ኛ ጢሞ. 3፡3፣8፤ ቲቶ 1፡7፤ 2፡3፤ 1ኛ ጴጥ. 4፡3)።
6. ወይን መንፈሳዊ ለሆነ መቼት ያገለግላል (ማቴ. 22፡1፤ ራዕ. 19፡9)።
7. ጠጪነት የተወገዘ ነው (ማቴ. 24፡49፤ ሉቃስ 12፡45፤ 21፡34፤ 1ኛ ቆሮ. 5፡11-13፤ 6፡10፤ ገላ. 5፡21፤ 1ኛ ጴጥ. 4፡3፤ ሮሜ 13፡13-14)።

ለ. ሥነ መለኮታዊ ይዘት

ሀ. ተቃርኗዊ ክርክር

1. ወይን የእግዚአብሔር ስጦታ ነው።
2. ሰካራምነት ዋነኛው ችግር ነው።
3. አማኞች በአንዳንድ ባህሎች ነጻነታቸውን መገደብ ይኖርባቸዋል፣ ለወንጌል ብለው (ማቴ. 15፡1-20፤ ማርቆስ 7፡1-23፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 8-10፤ ሮሜ 14)።

ለ. ከተወሰነው ገደብ በላይ የመውጣት ዝንባሌ

1. እግዚአብሔር የመልካም ነገር ሁሉ ምንጭ ነው።
2. የወደቀው የሰው ልጅ ሁሉንም የእግዚአብሔር ስጦታዎች እግዚአብሔር ካስቀመጠለት ገደብ በላይ በመውሰድ አበላሽቷቸዋል።

ሐ. ያላግባብ መጠቀሙ ከእኛ እንጂ ከነገሮች አይደለም። በሥጋዊ ተፈጥሮ ምንም ክፉ የለም (ማርቆስ 7፡18-23፤ ሮሜ 14፡14፣20፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡25-26፤ 1ኛ ጢሞ. 4፡4፤ ቲቶ 1፡15)።

III. የአንደኛው ክፍለ ዘመን የአይሁድ ባህልና አልኮል (ሆምጣጤ)

ሀ. መኮምጠጥ የሚጀምረው ወዲያው ነው፣ በግምት ከ6 ሰዓት በኋላ፣ ወይኑ ተረግጦ ሲያበቃ።

ለ. የአይሁድ ባህል እንደሚለው ከበስተላዩ ልከኛ አረፋ መታየት ሲጀምር (የመፍላት ምልክት)፣ የወይን መባ ለመስጠት ይደርሳል (ማ አሴሮዝ 1፡7)። እሱም "አዲስ ወይን" ወይም "ጣፋጭ ወይን" ይባላል።

ሐ. የመጀመሪያው አስካሪ ፍላት የሚያበቃው ከአንድ ሳምንት በኋላ ነው።

መ. ሁለተኛው ፍላት 40 ቀን ይወስዳል። በዚህ ጊዜ "ያረጀ ወይን" እንደ ሆነ ይቆጠራል፣ በመሠዊያው ላይም ለመሥዋዕትነት ይቀርባል (ኢድሁዮዝ 6፡1)።

ሠ. ሰፈፉ ላይ የረጋ ወይን (ያረጀ ወይን) መልካን እንደሆነ ይቆጠራል፣ ነገር ግን ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት መከለስ አለበት።

ረ. ወይን በተገቢው አረጀ የሚባለው ከፍላት ከአንድ ዓመት በኋላ ነው። ሦስት ዓመት ትልቁ ጊዜ ነው፣ ወይንን በተገቢው ለማስቀመጥ። እሱም "ያረጀ ወይን" ይባላል፣ ስለሆነም በውሀ መበረዝ ይኖርበታል።

ሰ. ባለፉት 100 ዓመታት በንጹሕ ቦታ እና ቅመም በመጨመር ኮምጣጥነቱን ማሻሻል ተችሏል። የጥንቱ ዓለም የኩምጠጣን ተፈጥሯዊ ሂደት ሊያስቀረው አልቻለም።

ለ. ሥነ መለኮታዊ ይዘት

ሀ. ተቃርኗዊ ክርክር

4. ወይን የእግዚአብሔር ስጦታ ነው።
5. ሰካራምነት ዋነኛው ችግር ነው።
6. አማኞች በአንዳንድ ባህሎች ነጻነታቸውን መገደብ ይኖርባቸዋል፣ ለወንጌል ብለው (ማቴ. 15፡1-20፤ ማርቆስ 7፡1-23፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 8-10፤ ሮሜ 14)።

ለ. ከተወሰነው ገደብ በላይ የመውጣት ዝንባሌ

3. እግዚአብሔር የመልካም ነገር ሁሉ ምንጭ ነው።
4. የወደቀው የሰው ልጅ ሁሉንም የእግዚአብሔር ስጦታዎች እግዚአብሔር ካስቀመጠለት ገደብ በላይ በመውሰድ አበላሽቷቸዋል።

ሐ. ያላግባብ መጠቀሙ ከእኛ እንጂ ከነገሮች አይደለም። በሥጋዊ ተፈጥሮ ምንም ክፉ የለም (ማርቆስ 7፡18-23፤ ሮሜ 14፡14፣20፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡25-26፤ 1ኛ ጢሞ. 4፡4፤ ቲቶ 1፡15)።

IV. የአንደኛው ክፍለ ዘመን የአይሁድ ባህልና አልኮል (ሆምጣጤ)

ሀ. መኮምጠጥ የሚጀምረው ወዲያው ነው፣ በግምት ከ6 ሰዓት በኋላ፣ ወይኑ ተረግጦ ሲያበቃ።

ለ. የአይሁድ ባህል እንደሚለው ከበስተላዩ ልከኛ አረፋ መታየት ሲጀምር (የመፍላት ምልክት)፣ የወይን መባ ለመስጠት ይደርሳል (ማ አሴሮዝ 1፡7)። እሱም "አዲስ ወይን" ወይም "ጣፋጭ ወይን" ይባላል።

ሐ. የመጀመሪያው አስካሪ ፍላት የሚያበቃው ከአንድ ሳምንት በኋላ ነው።

መ. ሁለተኛው ፍላት 40 ቀን ይወስዳል። በዚህ ጊዜ "ያረጀ ወይን" እንደ ሆነ ይቆጠራል፣ በመሠዊያው ላይም ለመሥዋዕትነት ይቀርባል (ኢድሁዮዝ 6፡1)።

ሠ. ሰፈፉ ላይ የረጋ ወይን (ያረጀ ወይን) መልካን እንደሆነ ይቆጠራል፣ ነገር ግን ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት መከለስ አለበት።

ረ. ወይን በተገቢው አረጀ የሚባለው ከፍላት ከአንድ ዓመት በኋላ ነው። ሦስት ዓመት ትልቁ ጊዜነው፣ ወይንን በተገቢው ለማስቀመጥ። እሱም "ያረጀ ወይን" ይባላል፣ ስለሆነም በውሀ መበረዝ ይኖርበታል።

ሰ. ባለፉት 100 ዓመታት በንጹሕ ቦታ እና ቅመም በመጨመር ኮምጣጥነቱን ማሻሻል ተችሏል። የጥንቱ ዓለም የኩምጠጣን ተፈጥሯዊ ሂደት ሊያስቀረው አልቻለም።

V. የመዝጊያ መግለጫ

ሀ. ያንተ ልምድ፣ ሥነ መለኮት፣ እና የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ የኢየሱስንና የአንደኛውን ክፍለ ዘመን አይሁድ/ወይም ክርስቲያናዊ ባህል እንዳያንኳስስ ተጠንቀቅ! እነሱ ጨርሰው አልኮል የማይቀምሱ አልነበሩም።

ለ. እኔ የአልኮል ማህበራዊ ጠቀሜታ ተከራካሪ አይደለሁም። ሆኖም፣ ብዙዎች በዚህ ጉዳይ ላይ የመጽሐፍ ቅዱስን አቋም ስለሚያጋንኑ እናም አሁን ልዕለ ጽድቅ የተመሠረተው በባህል/በመሠረተ እምነት ላይ ባለ አድሏዊነት በመሆኑ።

ሐ. ለእኔ፣ ሮሜ 14 እና 1ኛ ቆሮ. 8-10 በፍቅርና በአክብሮት ላይ የተመሠረተ ይዘትና መመሪያ ይሰጡኛል፣ ይህም ለአማኞችና ለወንጌል ስርጭት በሁሉም ባህል፣ ግለሰባዊ ነጻነት ወይም ፍርዳዊ ሂስ ሳይሆን። መጽሐፍ ቅዱስ ብቻውን የእምነትና የተግባር ምንጭ ከሆነ፣ እናም ሁላችንም ይሄንን ጉዳይ ዳግም ልናጤነው ይገባል።

መ. ጨርሶ መታቀብን እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ ብንወስደው፣ ስለ ኢየሱስ ምን እንላለን፣ እንዲሁም ስለ ዘመናዊዎቹ ባህሎች፣ በመደበኛነት ወይንን የሚጠቀሙ፣ (ለምሳሌ፣ አውሮጳ፣ እስራኤል፣ አርጀንቲና)?

▣ **"እጅግ ባማረ ሽቱም ለምትቀቡ"** ዘይትን በፊት ላይ እና በእጆች ላይ መቀባት የደስታ ምልክት ሆኖ ያገለግል ነበር፡፡ይህ የነሱ ተግባር ቀጥሎ ካለው ግጥማዊ አባባል ጋር የማይሄድ ነው፡፡ በተጎዳው ህዝባቸው ምክንያት ሃዘን ውስጥ መሆን ነበረባቸው፡፡

▣ **"ስለ ዮሴፍ መከራ"** ዮሴፍ ግብፃዊቷን አግብቶ ነበር፡፡እነሱም ያዕቆብ ያሳደጋቸው ሁለት ልጆች ነበሯቸው (እስራኤል፣ ዘ.ከ. ዘፍ 48:8-22)፡፡ ምንም እንኳን የመሲሁ የዘር ግንድ ከይሁዳ የመጣ ቢሆንም ዮሴፍ ከትልቁ ልጅ "እጥፍ ውርስ" ተቀብሏል፡፡ የዮሴፍ ሁለት ልጆች ኤፍሬም እና ምናሴ የሚባሉ ሁለት ትልቅ ነገዶች ሆነዋል፡፡እነሱም ከክርስቶስ ልደት በፊት በ922 ከሰለሞን ልጅ ሪሆባም የተገነጠሉ የሰሜኑ አስር ነገዶች አካል የነበሩ ሲሆን በኢዮርብአም I ስር አዲስ ግዛት ጀምረው ነበር፡፡እነዚህ አዲስ ግዛቶች በተለያዩ ስሞች ይታወቁ ነበር፣

1. እስራኤል (የያዕቀብ አዲስ ስም)
2. ሰማሪያ (ዋና ከተማ)
3. ኤፍሬም (ትልቁ ነገድ)

**6:7** ይህ እግዚአብሔርን እናውቃለን በሚሉ ነገር ግን ስለ ራሳቸው ብቻ የሚያስቡ ሰዎች ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ የሚያሳይ ነው! የተፈረደባቸውም ፍርድ ይኖሩ ከነበሩት ኑሮ ጋር ፈፅሞ ተቃራኒ ነው! በአባከኝነት እና በፌሽታ አንደኛ የነበሩ ለመማረክም አንደኛ ሆኑ!

▣ **"ግብዣ"** ይህ ቃል (BDB 931፣ KB 634) በብሉ ኪዳን ውስጥ ሁለት ጊዜ ብቻ ነው የሚገኘው(እዚህ እና በኤር 16:5)፡፡ የኤርምያ ፅሑፍ (እና አንድ የኡጋሪቲክ ፅሑፍ) ይህን ቃል የግል ፍላጎት ለማርካት ለሞተ ሰው ከሚደረግ ፌሽታ ጋር ያገናኘዋል! እንደዚህ ከሆነ የአሞፅ የአሽሙር ዓረፍተ ነገር ግልፅ ነው፡፡

## አሞፅ: 6:8-11

**6 ጌታ እግዚአብሔር፦ የያዕቆብን ትዕቢት ተጸይፌአለሁ፥**
**አዳራሾቹንም ጠልቻለሁ ስለዚህ ከተማይቱንና የሚኖሩባትን**
**ሁሉ አሳልፌ እሰጣለሁ ብሎ በራሱ ምሎአል፥ ይላል የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር፦**
**7 ስለዚህ በምርኮ መጀመሪያ ይማረካሉ፥ ተደላድለው ከተቀመጡትም ዘንድ ዘፈን ይርቃል።**
**8 ጌታ እግዚአብሔር፦ የያዕቆብን ትዕቢት ተጸይፌአለሁ፥ አዳራሾቹንም ጠልቻለሁ**
**ስለዚህ ከተማይቱንና የሚኖሩባትን ሁሉ አሳልፌ እሰጣለሁ ብሎ በራሱ ምሎአል፥ ይላል የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር፦**
**9 እንዲህም ይሆናል አሥር ሰዎች በአንድ ቤት ውስጥ ቢቀሩ እነርሱ ይሞታሉ።**
**10 አጥንቱንም ከቤቱ ያወጡ ዘንድ የሰው ዘመድና አቃጣዩ ባነሡት ጊዜ፥ በቤቱም ውስጥ ያለውን፦**
**እስከ አሁን ድረስ ገና ሰው በአንተ ዘንድ አለን? ባለው ጊዜ፥ እርሱም፦ ማንም የለም ባለ ጊዜ ያን ጊዜ።**
**የእግዚአብሔርን ስም እንጠራ ዘንድ አይገባንምና ዝም በል ይለዋል።**
**11 እነሆም፥ እግዚአብሔር ያዝዛል ታላቁንም ቤት በማፍረስ፥ ታናሹንም ቤት በመሰባበር ይመታል።**

**6:6-11** UBS፣ የተርጓሚዎች የመምሪያ መጽሐፍ ፣ ገፅ 131 እነዚህ ቀጥሮች ከ5:21-24 ጋር እንደሚጎዳኙ ጥሩ ነጥብ አስቀምጧል፡፡ በእግዚአብሔር ቁጣ (ዝ.ከ. ቁ 8፤ 5:24) የእግዚአብሔር ፍርድ ይመጣል!

**6:8 "ጌታ እግዚአብሔር በራሱ ምሏል"** በ 4:2 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት፡፡ በአሞፅ ውስጥ ይህ "መማል" (BDB 989፣ KB 1396) የሚለው ግስ ብዙ ጊዜ ያህዌ በሚከተሉት ነገሮች ሲምል ተጠቅሷል፡፡

1. በቅዱስነቱ 4:2
2. በራሱ 6:8
3. በያዕቆብ ክብር 8:7 ( ሽሙጥ፣ ምፀታዊ ወይም ፀፀት )

▣ **"የሰራዊት አምላክ እግዚአብሔር"** ለአማልከት ስሞች በ 1:2 ላይ ልዩ ርዕስ ተመልከት ያህዌን ለማመልከት የእነዚህ ሁለት ስሞች መደጋገም ይህን ትኩረት የሚደረግበት አጠራራር ያደርገዋል፡፡

▣ **"የያዕቆብን ትዕቢት ተጸይፌአለሁ"** ግሱ (BDB 1060 II፣ KB 1672፣ *Piel* ቦዝ አንቀፆች ) ብዙ ጊዜ የማይጠቀስ (በብሉ ኪዳን እዚህ ውስጥ ብቻ) ነገር ግን የመቃወሚያ ኃይለኛ ቃል ነው (ሁሉንም እትሞች ተመልከት)፡፡BDB "ጥላቻ" ፣KB "አስቀያሚ እርኩሰት ማድረግ "፡፡"ጥላቻ" (BDB 971፣ KB 1338፣ ዝ.ከ. 5:21) ከሚለው ቃል ጋር ተያይዞ የሚሄድ ነው፡፡
"እብሪት" (BDB 144) ማለት "ሐሴት" "ግርማ ሞገስ" ወይም "ከፍተኛ ችሎታ" ነው፡፡ በመዝ47:4 ውስጥ ወደ እስረኤል በአዎንታዊ መልኩ ቅርቧል፡፡ በዚህ ዓውድ ከቁ 4-6 ያለውን ያመለክታል፡፡ ተያያዥነት ያለውን አሽሙር በ 8:7 ላይ ተመልከት፡፡የእስራኤል አግባብ ያልሆነ "ክብር" የእግዚአብሔርን ፍርድ ተቀብሏል (ዝ.ከ. ሆሴ 5:5፤ 7:10)!

**6:9-10** ይህ ግጥማዊ ሳይሆን ስድ ንባብ ነው፡፡

**6:9 "አስር ሰዎች"** ይህ ቁጥር ለአይሁዳዊያን አስፈላጊ ነው ምክንያቱም ቀጥሩ ለአምልኮ እና ለሌላ ማህበራዊ ክስተቶች ፣ ምናልባትም ለወታደራዊ ኃይል ቡድኖች የሚስፈልገው ዝቅተኛ ቀጥር ስለሆነ፡፡ በአስር ቀጥር ጥቅም ምክንያት ይህ ፍርድ ከ 5:3 ጋር ሊዛመድ ይችላል፡፡

**6:10** ይህ ቁጥር የእስራኤል ዋና ከተማ ሰማሪያን መከበብ የሚገልፅ ይመስላል፡፡ብዙ የሚሞቱ ሰዎች እንዲሁም በሚያስጨንቅ ሁኔታ በሰፊው የሰው አካል በጅምላ የሚቃጠሉ ይሆናል (ዝ.ከ. 8:3)፡፡

▣ **"የሰው ዘመድና አቃጣዩ"** ይህን ሃረግ በተመለከተ ብዙ የሚነሱ ጥያቄዎች አሉ፡፡
1 እነዚህ ሁለት ሰዎች ናቸው ወይስ አንድ?
2 በ NASB "እሱ የሚያቃጥለው" ተብሎ የተተረጎመው "አቃጣዩ" የሚለው ቃል (BDB 976) ምን ማለት ነው?
ለጥያቄ ቁጥር 1 ረጉ የሚያመለክተው በተቀሩት ቁጥሮች እርስ በርሳቸው የሚነጋገሩ ሁለት የተለያዩ ሰዎችን ነው (ይህም ማለት፣ በማረፊያ ቤት ውስጥ ምንም የተረፈ ሰው አይኖርም)፡፡
ለጥያቄ ቁጥር 2 ብዙ ንድፈ ሃሳቦች ሲታዩ ቆይቷል፡፡

1. የሙታንን አካሎች የሚያቃጥል
2. ሙታንን በቅመማ ቅመሞች ወይም እንዳይበሰብቡ መዳኒት የሚቀባ
3. በሞተው ሰው በኩል ሆኖ እጣን የሚያጥን
4. በሞተው ሰው በኩል ሆኖ መስዋዕት የሚያቀርብ
5. ከነገስት አቀራቢያ ተያያዥነት ያለው መጠሪያ ፣ ለመጀመሪያው መጠሪያ ለእናት ወገን የቀረበ ዘመድ እና ለሁለተኛው መጠሪያ ደግሞ ለአባት ወገን የቀረበ ዘመድ ማለት ሊሆን ይችላል፡፡

ለእኔ ቁጥር 1 እና ቁጥር 5 ምርጥ ይመስሉኛል፡፡ነገር ግን ቁጥር 4 በቁ 6 ውስጥ ለሞተው ሰው ከሚደረገው ግብዣ ጋር የሚገናኝ ሊሆን ይችላል፡፡

▣ **"የእግዚአብሔርን ስም እንጠራ ዘንድ አይገባምና ዝም በል ይለዋል፡፡"** ይህ በመንፈሳዊ ትምርት ወረራውን ማን እንደ ላከው ማረጋገጫ ነው፡፡ከፍርዱ አደጋ በኋላ በእስራኤል ውስጥ ለረጅም ጊዜ ጠፍቶ የነበረው የያህዌ ቅዱስ ክብር መጥቷል፡፡"ዝም በል" (BDB 245፣ a እብረዊያን ቃለ አጋኖ) በያህዌ መገኘት (ዝ.ከ. ዕብ 2:20፤ ሶፎ1:7፤ Zech 2:13) እና ፍርድ (ዝ.ከ. 8:3) ዕድምታ ቀርቧል፡፡

**6:11** ይህ ከ ቁ 8-11 ላሉት የመደምደሚያ ነጥብ ነው፡፡ ፍርዱ (በውጪ አገር ፣ ይህም ማለት አሶራዊያን) በትልቁም በትንሹም ላይ ይወርዳል (ይህም ማለት፣ አጠቃላይ ህዝቡ ላይ)፡፡ ማንም ሊያመልጥ አይችልም(ዝ.ከ. 5:18-20)፡፡

▣ **"በማፍረስ በመሰባበር"** የመጀመሪያዉ ቃል (KB 1249) ትርጉም የተረጋገጠ አይደለመም፡፡

1. የዝናብ ነጠብጣቦች(መኃ 5:2)
2. ምግብ መክተፍ
3. መሰባበር ወይም መፍጨት

ሁለተኛው ቃል (KB 149) ትርጉሙ ለመክፈት መስበር (ዝ.ከ. መዝ141:7)፣ ልክ እንደ ግንብ (ዝ.ከ. ኢሳ 22:9) የግስ መልኩ ወደ ቁርጥራጭ መቀዳደድን ያመለክታል፡፡(*Piel*) David Allan Hubbard ፣ እዩ እና አሞፅ (የቲንዳል ብሉ ኪዳን ትርጓሜ) እንደሚያረጋግጡት እነዚህ ሁለት ቃላት ከወረራ ይልቅ ለመሬት መንቀጥቀጥ ይሆናሉ፡፡ በተጨማሪም በአሞፅ ውስጥ ሌላ ቦታ ለመሬት መንቀጥቀጥ ይሆናሉ ብሎ የሚያስባቸውን ፅሑፎች በገፅ 198 ላይ ዘርዝሯል፡፡(ዝ.ከ. 1:1፤ 2:13፤ 8:8፤ 9:1-6)፡፡

**አሞፅ: 6:12-14**

**12-13 ፍርድን ወደ ሐሞት፥ የጽድቅንም ፍሬ ወደ እሬት የለወጣችሁ፥ በከንቱም ነገር ደስ የሚላችሁ።**
**በኃይላችን ቀንድ የወሰድን አይደለምን? የምትሉ፥ እናንተ ሆይ፥ በውኑ ፈረሶች በጭንጫ ላይ ይጋልባሉን?**
**ወይስ በሬዎች በዚያ ላይ ያርሳሉን? 14 የእስራኤል ቤት ሆይ፥ እነሆ፥**
**እኔ ሕዝብን አስነሣባችኋለሁ፥ ይላል የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር**
**እነርሱም ከሐማት መግቢያ ጀምረው እስከ ዓረባ ወንዝ ድረስ ያስጨንቋችኋል።**

**6:12** በእብረዊያን ዉስጥ እነዚህ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ጥያቄዎች አስቸጋሪዎች ና ቸው ፣ ነገር ግን ያልተለመዱ ተግባሮችን እንደሚያመለክት ግልፅ ነው፡፡ ለእነዚህ ሁሉም የሽንገላ ጥያቄዎች የሚጠበቀው መልስ "አይደለም " ነው፡፡በተጨማሪም ለእግዚአብሔር ህዝብ ፍርድን ወደ ሐሞት መለወጥ ያለተለመደ ነው!

▣ **"በውኑ ፈረሶች በጭንጫ ላይ ይጋልባሉን"** "ጭንጫ" (BDB 700) ትልልቅ ድንጋዮችን ወይም ደግሞ በይበልጥ በከፍተኛ ድንጋያማ ጉብታ ወይም ቋጥኝ ላይ የሚጋልቡ ፈረሶችን የሚያመለክት ነው፡፡ በግልፅ እነደሚታየው መልሱ አይደለም ነው፡፡

▣ **"በሬዎች በዚያ ላይ ያርሳሉን"** የ ማሶሬቲኩ's ን ድምፅ አናባቢዎች "የባህር ሞገድ ማረሻ" ብሎ ለማንበብ መለወጥ ይቻላል፡፡ (ዝ.ከ. NRSV፣ TEV ፣ NJB) ይህም የሚሆነው የ "በሬዎች" የብዙ ቃል መጨረሻን እንደ ተነጠለ ቃል ፣ "ባህር" በመውሰድ ነው፡፡ ይህ ዓውዱን በተሸለ መልክ ይገልፀዋል፡፡ልክ እንደ እንደ 12ሀ የማይቻል ተግባር ለማለት ነው፡፡ለአራቱም ጥያቄዎች የሚጠበቀው መልስ "አይደለም" ነው፡፡

▣ **"ፍርድን የጽድቅንም ፍሬ"** በ 5:12 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት፡፡

**6:13 "ደስ የሚላችሁ"** ይህ የእብረዊያን ሃረግ የሚያመለክተው በሁለት የጦርነት ድሎች ምክንያት የእስራኤልን ኩራት እና ጀብደኝነትን ነው፡፡ እስራኤል በራሷ የጦር ኃይል ትኮራ እና ትተማመን ነበር ፣ ነገር ግን እግዚአብሔር በሌላ የተሻለ የጦር ኃይል እስራኤልን ያጠፋታል (ዝ.ከ. ቁ 14፣ በአሶራዊያን)! አሶራዊያን ከእነዚህ ከተገለፁት ሁለት ከተሞች በተመሳሳይ የስነምድር አቅጣጫ ማለትም ከሰሜን ይመጣሉ፡፡

▣ **"ሎድባር"** ይህ ከተማ በጆርዳን በስተምስራቅ ላይ በጊሊዓድ ቦታ ውሰጥ የሚገኝ ነበር፡፡ ይህ መጠሪያ (BDB 520) "ምንም ነገር" የሚል ትርጉም አለው፡፡

▣ **"በኃይላችን ቀንድ (ካሪም) የወሰድን አይደለምን"** ይህ በዮርዳኖስ ወስጥ የሚገኝ ሌላ ቦታ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ ይህ መጠሪያ (BDB 902) "ጥንድ ቀንዶች" ማለት ሲሆን የነበረውን ኃይል የሚያመለክት ሊሆን ይችላል፡፡እነዚህ ሁለቱም ከተሞች በኢዮርብአዓም 2ተኛ ተይዘው ነበር (782-753 ከክርስቶስ ልደት በፊት)፡፡
በመንፈሳዊ ትምህርት ዕይታ ይህ ሃረግ እስራኤል በራሷ የጦር ኃይል ይህን ከተማ በቁጥጥር ስር እንዳዋለች የሚጠቁም ሲሆን ይህ ደግሞ እንደገና ከቅዱስ ጦርነቱ በተቃራኒ መልኩ የተፈፀመ ነበር፡፡ በያህዌ ኃይል እና ጥንካሬ (ለምሳሌ ዘጽ 13:3፣14፣16) ነበር የያህዌ ህዝቦች ጦርነቱን እንዲያሸንፉ ያደረጋቸው፡፡ ይህ በራሳቸው ኃይል የተፈፀመ ማስመሰል የአስረኤላዊያን ሌላ የኩራታቸው እና የቃልኪ ኪዳኑ ቸልተኛነታቸው ምልክት ነው፡፡

**6:14 "እኔ ሕዝብን አስነሳበሰችኋለሁ"** ይህ የሚያመለክተው አሶራዊያንን ነው፡፡

▣ **"ከሐማት መግቢያ ጀምረው እስከ ዓረባ ወንዝ"** ይህ የድሮ የቃል ኪዳኗ መሬት መዳረሻ ነው (ዝ.ከ. ዘሁ 34:7-8፤ ኢያ13:5፤ መሳ 3:3፤ 1ኛ ነገ 8:65፤ 2ኛ ነገ 14:25)፡፡ ይሁዳም ላይ ለወጥ ያመጣል!

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት <u>*መመሪያ*</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ለምንድን እግዚአብሔር የሰሜን ነገዶችን መስዋዕት ያልተቀበለው?
2. ለምንድን ነው የእግዚአብሔር የመፍጠር ተግባሩ ትኩረት የተሰጠው? (ከ ቁ 8-9)
3. ለምንድን ነው አሞፅ 5:25-26 ን ለመጸርጎም ከባድ የሆነው?
4. አሞፅ እያወገዘ ያለው ሃብትን እና የመስወዕት ስርዓትን ነው ወይስ ሌላ ነገር? ምንድን ነው እሱ?

# አሞፅ 7
## የአዲሶቹ ትርጕሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|
| የአንበጦች ራዕይ | አምስቱ የእግዚአብሔር ፍርድ እና የተሀድሶ ትነቢት (7:1-9:15) | የአንበጦች ራዕይ | ራዕዮች (7:1-9:10) |
| 7:1-3 | 7:1-3 | 7:1-3 | የመጀመሪያው ራዕይ፡ አንበጣ 7:1-3 |
| የእሳት ራዕዮች | | የእሳት ራዕዮች | ስለ ድርቅ የመጀመሪያው ራዕይ |
| 7:4-6 | 7:4-6 | 7:4-6 | 7:4-6 |
| የቱነቢው ራዕይ | | የቱነቢው ራዕይ | ሦስተኛው የቱነቢው ራዕይ |
| 7:7-9 | 7:7-9 | 7:7-9 | 7:7-9 |
| የአሜስያስ ክስ | አሜስያስና አሞጽ | አሞጽ እና አሜስያስ | አሜስያስ የአሞጽን ትነቢት የመናገር መብት ተከራከረ |
| 7:10-13 | 7:10-13 | 7:10-13 | 7:10-13 |
| | | 7:12-13 | |
| 7:14-17 | | 7:14-17 | |

### የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ vii ተመልከት)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. *የመጀመሪያው አንቀጽ*

2. *ሁለተኛው አንቀጽ*

3. *ሦስተኛ አንቀጽ*

4. *ወዘተርፈ*

### ዓውዳዊ እይታዎች
ሀ. ከምዕራፍ 7-9 ያሉት የመጨረሻው የስነ ጽሑፍ ክፍሎች ናቸው፡፡መጽሐፉ በሦስት ክፍሎች ሊከፋፈል ይችላል፤ እነሱም (1) በሕዝቦች ላይ የተደረጉ ፍርዶች፣ (2) በይሁዳ እና በእስራኤል ላይ የተደረጉ ፍርዶች እና (3) የአሞፅ ራእዮች፡፡
1. የአሞፅ ራእዮች ዋና ዋና ክፍሎች እንደሚከተሉት ሆነው ሊዘረዘሩ ይችላሉ፤
   ሀ. ምዕራፍ 7 ፤ ሦስት ራእዮች
   ለ. ምዕረፍ 8 ፤ አንድ ራእይ
   ሐ. ምዕረፍ 9፤ አንድ ራእይ
2. የፍርድ ራእዮች
   ሀ. አንበጣ ፤ 7:1-3
   ለ. እሳት (ሊሆን የሚችለው ርሃብ፤ ዝ.ከ. 4:6-8፣ 8:11-13) ፤7:4-6
   ሐ. ቱንቢ (ሊሆን የሚችለው ደካማ ምሽግ)፤ 7:7-9
   መ. የቃርሚያ ፍሬ፤ 8:1-3
   ሠ. የምድር መናወጥ)፤9:1-2 (በተጨማሪም ሊሆን የሚችለው ም 8:ከቁ 7-10)

   እነዚህ ራእዮች በእርግጥ እግዚአብሔር አሞፅን ከእረኝነት ወደ ነብይነት የተጠራበት ትንቢታዊ መንገዶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ነብዩ ምህረትን ይጠይቃል (ራእዮች 1 እና 2)፤ ነገር ግን አመጻ ፣ ጣዖት አምላኪነት እና ንስሃ ያለመግባት ሁኔታዎች ፍርድ

ያስፈለሏጋቸዋል ነበር፡፡እስራኤላዊያን ይህን ፍርድ ወደ እነሱ ያመጣው ኃጥያታቸው እንጂ የእግዚአብሔር ድክመት ወይም ርህራሄ ማነስ እንዳልሆነ ሊነገራራቸው ይገባል (ለይሁዳም ጭምር ማስጠንቀቂያ እንደሆነም)፡፡

ለ. አሞፅ ም 7: ከቁ 10-17 ያለው የተለየ ነው፤ ምክንያቱም፡-

1. ስለ አሞፅ የሕይወት ታሪክ መረጃ ስለሚሰጥ (ከራዕዮቹ መካከል ምን ያህሉ ራእዮች ከግብርና ጋር የተያያዘ ነገር እንዳላቸው ያስተውሉ)
2. ሌሎቹ የመጽሐፉ ንዑስ ክፍሎች በአንደኛ ሰው ወገን የተጻፉ ሲሆኑ ይህ ንዑስ ክፍል ግን በሦስተኛ ሰው ወገን የተጻፈ ነው፡፡

## የቃል እና የሀረግ ጥናት

### አሞፅ: 7:1-3

**1 ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ አሳየኝ እነሆም፥ የኋለኛው ሣር በሚበቅልበት መጀመሪያ ላይ አንበጣን ፈጠረ**
**እነሆም፥ ከንጉሡ አጨዳ በኋላ የበቀለ የገቦ ነበረ።**
**2 የምድሩንም ሣር በልተው ከጨረሱ በኋላ፥ እኔ።**
**ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ ይቅር እንድትል እለምንሃለሁ ያዕቆብ ታናሽ ነውና እንዴት ይቆማል? አልሁ።**
**3 እግዚአብሔርም ስለዚህ ነገር ተጸጸተ ይህ አይሆንም፥ ይላል እግዚአብሔር፡-**

**7:1 "ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ አሳየኝ እነሆም"** ይህ መግቢያ የራዕዮቹን ተዛማችነት ያሳያል (ዝ.ከ. 7:1፤4፤7፣ 8:1፤ ነገር ግን 9:1-10 አይደለም)፡፡

▣ **"ፈጠረ"** እነዚህ ራእዮች እና ፍርዶች ከራሱ ከእግዚአብሔር የመጡ ነበሩ (BDB 427፤ KB 428፤ ኳል ቦዝአንቀጽ፤ ወንዳዊ ነጠለ)፡፡

▣ **"የአንበጣን መንጋ"** የዚህ አይነቱ ጭንቅ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሱን ትዕዛዛት ካልጠበቁ ይደርስባቸው ከነበሩት እርግማኖች አንዱ እንደነበር በዘጸ 10:12ረረ ውስጥ ተጠቅሷል፡፡ በእብራዊያን ቋንቋዋ "አንበጦች" የሚለውን ቃል የሚገልጹ ከ12 በላይ የተለያዩ ቃላቶች አሉ፡፡ይህም የሚያሳየው እነዚህ መከራዎች ምን ያህል የተለመዱ እና ይፈሩ እንደነበረ ነው፡፡ እነዚህ ቃላት የአንበጣውን አይነት ወይም የእድገታቸውን ሂደት የሚያሳዩ እንደሆነ የተረጋገጠ ነገር የለም (ዝ.ከ. ኢዩኤል 1:4፣ 2:25)፡፡

▣ **"የኋለኛው ሣር በሚበቅልበት መጀመሪያ ላይ"** ይህ በቀጥታ የሚያሳየው "የቀድሞውን እድገት" (BDB 545) ነው፡፡ይህ ሳርን ወይም ሰብልን ያመለክት እንደሆነ የተረጋጋገጠ ነገር የለም፡፡ በተጨማሪም ሁለተኛው እድገት ወይም ደግሞ እንደገና መትከል ማለት እንደሆነ የተረጋገጠ ነገር የለም፡፡ ይህ ከሚያዝያ በኋላ የሆነ ጊዜ ሊሆን ይችላል፡፡ የቀድሞው ዝናብ ዘሮቹ ከማቆጥቆጣቸው በፊት መዝነብ ነበረበት፡፡ይህ ሰብል ከተበላሸ እስከ ሚቀጥለው አመት ድረስ ሰብል አይኖርም!

▣ **"ከንጉሡ አጨዳ በኋላ"** ይህ በቀጥታ "ቆረጣዎች" (BDB 159) ማለት ነው፡፡ ይህ ሃረግ ንጉሱ የመሬቱን የመጀመሪያ አጨዳ እንደ ግብር መቀበሉን ለማሳወቅ የቀረበ አይደለም፡፡ በአጠቃላይ ብሉ ኪዳን ውስጥ የዚህ አይነት ድርሻ ለንጉስ የተሰጠው እዚህ ላይ ብቻ ነው፡፡ ሃረጉ ይህን ክስተት የሆነው በፀደይ ውስጥ መሆኑን ለማሳየት የቀረበ ዘዴ ነው፡፡

**7:2 "ከጨረሱ በኋላ"** ይህ ግስ (BDB 477፤ KB 476፤ ፒል የተቋጨ) የ"መፈጸም" ወይም የ"ማጥፋት" ቅዱሳዊ አጻጻፍ አለው (ኒዶት፤ ጥራዝ 2፤ገፅ 641)፡፡ እዚህ ላይ በሁለቱም ስሜቶች ያገለግላል፡፡

▣ **"እኔም አልሁ"** ምንም እንኳን ነብያት በተደጋጋሚ በእግዚአብሔር በኩል ሆነው ለቃል ኪዳኑ ሕዝብ የሚናገሩ ቢሆኑም በአብዛኛው ግን እንደ አማላጅ ሆነው ያገለግላሉ(ዝ.ከ. ዘጸ 32:11፣ ኤር 15:1፣ 18:20፣ ሕዝ 9:8፣ ዳን 9:15-19)፡፡

▣ **"ጌታ እግዚአብሔር"** ይህ *አዶን* እና ያህዌ (ዝ.ከ. ኤር 14:7፤20፤21፣ ሕዝ 9:8፣ 11:13) ነው፡፡ በ1:2 ላይ የአማልክት ስሞች የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

▣ **"ይቅር እንድትል እለምንሃለሁ"** ይህ (BDB 669፤ KB 757) *Qal IMPERFECT(ያልተቋጨ )*ግስ ነው፡፡ይህ ቃል ሁልጊዜ ለሰው ልጅ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ለመግለጽ የሚያገለግል ነው (የሮበርት ቢ. ጊርድልስቲንን ብሉይ ኪዳን ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ቃላት ከገፅ 135-136 ላይ ይመልከቱ)፡፡ አሞፅ፤ማህበረሰቡን የሚዳኛ ነብይ ምህረት ጠያቂ ሆነ! የፍርድ መልዕክቱ ውትወታ የፍርዱ መዘዝ ጎልቶ እንዲታይ አድርጎት ነበር! የአሞፅ እግዚአብሔርን ይቅርታ መጠየቅ ፋይዳ የለውም፡፡ ይህ (1) ፍርዱ ይቅር ወይም (2) ምንም ፍርድ አያስፈልግም ኃጥያታቸውን ይቅር በል ማለት ሊሆን ይችላል፡፡አሞፅ ለመጀመሪያወቹ ሁለት ራእዮች ይህንኑ ተመሳሳይ ጥያቄ አቅርቧል፡፡ሆኖም ግን አሞፅ ጸሎቱን ሲጸልይ ያህዌ እንደ ቁጥር 1 እንዲረዳው አስቦ ነው፡፡ሦስተኛው እና አራተኛው ራእዮች ሲገለጹ ምንም ምህረት በውስጣቸው አልተገለጸም ምክንያቱም ምንም ዓይነት ንስሃ የመግባት ሁኔታ አልነበረም! የእረፍት ጊዜውን ለባሰበት አመጻ እንጂ ለመንፈሳዊ መታደስ አልተጠቀሙበትም፡፡ትዕግስት እና ምህረት ወደ ቁጣ ተለውጠዋል (ዝ.ከ. 7:8፤9፣ 8:7፤10፤11)!

**7:2፤5 "ያዕቆብ ታናሽ ነውና"** የነብዩ ይግባኝ ማለት ለሕዝቡ "ፍላጎት" እንጂ ሕዝቡ ላለው "የቃል ኪዳን ዝምድና" እንዳልሆነ ያስተውሉ፡፡እግዚአብሔር የአብርሃም ዘር (1)እንደ ሰማይ ከዋክበት (ለምሳሌ፤ ዘፍ 15:5) ፣ (2) )እንደ ባህር ዳር እንዳለ አሸዋ (ለምሳሌ፤ ዘፍ 22:17) እና (3) እንደ ምድር አሸዋ (ለምሳሌ፤ ዘፍ 13:16) እንደሚያበዛው ቃል ገብቶ ነበር፤ ነገር ግን አሁን ያሉት ጥቂት ነበሩ!

**7:3**
**NASB፣ TEV** **"እግዚአብሔርም ስለዚህ ነገር ተጸጸተ"**

NKJV ፣ NRSV
NJB "እግዚአብሔር ይህን በተመለከተ ሃሳቡን ቀይሯል"

ይህ የአረብ መሰረት ያለው ቃል ትርጉሙ "በጥልቀት መተንፈስ" (BDB 636፤ KB 688፤ ኒፋል የተቋጨ) ማለት ነው፡፡ይህ ሰወኛ ዘይቤ ነው፡፡የዚህ ቃል መሰረት ጥልቅ ስሜትን ይገልጻል (Robert B Girdlestone Synonyms of the Old Testament ከገፅ 87-88 ላይ ይመልከቱ)፡፡

ይህ ቃል በነብዩ ናሆም ስም ላይ ተገልጽዋል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር ሃሳቡን እንደሚቀይር እና እንደሚታክት በተደጋጋሚ ጊዜ ተገልጽዋል(ዝ.ከ. ቁ 6፣ ዘፍ 18:22-32፣ ዘኍ 14:11-20፣ ኢያ 7:6- 13፣ 2ኛነገ 22:19-20፣ መዝ 106:45፣ ኤር 18:1-16፣ 26:3፤13፤19፣ዮናስ 3:10)፡፡ እግዚአብሔር (1) በጸሎታችን እና (2)በራሱ የርህሩነት እና የፍቅር ባህሪ (ዝ.ከ. ዘጸ 3:7፣ መሳ 2:18፣ ሆሴ 11:8-9፣ ኢዩ 2:13-14፣ አሞፅ 5:15) የተነሳ ሁኔታዎችን ሊለዋውጥ ይችላል፡፡ ሆኖም ግን ይህ የእግዚአብሔር ተፈጥሮው ወይም አላማው የሚዋዥቅ ነው ተብሎ መታየት የለበትም፡፡ እሱ አይለዋወጥም (ዝ.ከ. ዘኍ 23:19፣ 1ኛሳሙ 15:29፣ ሚል 3:6፣ እብ 13:8፣ ጴጥሮስ 1:17)፡፡

## አሞፅ: 7:4-6

**4 ጌታ እግዚአብሔርም እንዲህ አሳየኝ እነሆም፥ ጌታ እግዚአብሔር**
**በእሳት ለመፍረድ ጠራ እርስዋም ታላቁን ቀላይና ምድርን በላች።**
**5 እኔም። ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ እንድትተው እለምንሃለሁ ያዕቆብ ታናሽ ነውና እንዴት ይቆማል? አልሁ።**
**6 እግዚአብሔርም ስለዚህ ነገር ተጸጸተ ይህ ደግሞ አይሆንም፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፡-**
**እንዲህም አሳየኝ እነሆም፥ ጌታ ቱንቢውን ይዞ በቱንቢ በተሠራ ቅጥር ላይ ቆሞ ነበር።**

7:4
NASB "መጣላት"
NKJV "ግጭት"
NRSV (የግርጌ ማስታወሻ) "ፍርድ"
TEV "ለመቅጣት መዘጋጀት"
NJB "ለፍርድ መጥራት"

ይህ ቃል (BDB 936) በዚህ አውድ መሰረት በእስራኤል ላይ የተደረገን የክስ ጥሪን ያመለክታል (ለምሳሌ፤ ሆሴ 4:1፣ 12:2፣ ሚክ 6:1-2)፡፡

▣ "በእሳት" እሳት በተደጋጋሚ ጊዜ የፍርድ ምልክት ሆኖ ያገለግላል (ለምሳሌ፤ 2:5)፡፡ በዚህ ግብርና ነክ አውድ ውስጥ እሳት ምናልባትም የፀሃዩን አቃጣይ ሙቀት ወይም ደግሞ ተክሎቹ በአንበጦቹ ምክንያት ቅጠላቸው የረገፈ መሆኑን ሊያመለክት ይችላል (ማለትም፤ ምንጮች፣ወንዞች፣ዝናብ ወዘተ ዝ.ከ. 1:2፣ 4:6-8)፡፡

## ልዩ ርዕስ፡ እሳት

እሳት ሁለቱንም፣ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ፍችዎች አሉት፣ በመጽሐፍ ቅዱስ።
ሀ አዎንታዊ
1. ያሞቃል (ኢሳ 44:15፤ ዮሐንስ 18:18)
2. ብርሃን (ኢሳ 50:11፤ ማቴ 25:1-13)
3. ያበስላል (ዘጸ 12:8፤ ኢሳ 44:15-16፤ ዮሐንስ 21:9)
4. ያጠራል (ዘኍ 31:22-23፤ ምሳ 17:3፤ ኢሳ 1:25፤ 6:6-8፤ ኤር 6:29፤ ሚል 3:2-3)
5. ቅድስና (ዘፍ 15:17፤ ዘጸ 3:2፤ 19:18፤ ሕዝ 1:27፤ ዕብ 12:29)
6. የእግዚአብሔር አመራር(ዘጸ 13:21፤ ዘኍ 14:14፤ 1 ነገሥ 18:24)
7. የእግዚአብሔር ኃይል (ሐዋ 2:3)

ለ አሉታዊ
1. ያቃጥላል (ኢያ 6:24፤ 8:8፤ 11:11፤ ማቴ 22:7)
2. ያጠፋል (ዘፍ 19:24፤ ሌዋ 10:1-2)
3. ቁጣ (ዘኍ 21:28፤ ኢሳ 10:16፤ ዘካ 12:6)
4. ቅጣት (ዘፍ 38:24፤ ሌዋ 20:14፤ 21:9፤ ኢያ 7:15)
5. የተሳሳተ መናፍስትነት ምልክት (የፍጻሜ) (ራዕ 13:13)

ሐ የእግዚአብሔር ቁጣ በኃጢአት ላይ የሚገለጠው በእሳት ዘይቤዎች ነው
1. የእሱ ቁጣ ይነዳል (ሆሴ 8፡5፤ ሶፎ 3፡8)
2. እሱም እሳትን ያወጣል (ነህ 1፡6)
3. ዘላለማዊ እሳት (ኤር 15:14፤ 17:4)
4. የመጨረሻው ፍርድ (ማቴ 3:10፤ 13:40፤ ዮሐንስ 15:6፤ II ተሰ 1:7፤ II ጴጥ 3:7-10፤ ራዕ 8:7፤ 16:8)

መ በመጽሐፍ ቅዱስ እንዳሉ በርካታ ዘይቤዎች (ማለትም፣ እርሾ፣ አንበሳ) እሳትም በረከት ወይም መርገም ሊሆን ይችላል፣ በዐውደ ጽሑፉ ላይ በመመሥረት ነው።

▣ ***"ታላቁን ቀላይና ምድርን"*** ይህ በመሬት ስር የወንዞች ምንጭ የሆነን ውሃ ያመለክታል (ዝ.ከ. ዘፍ 1:2፣ 7:11፣ 49:15፣ መዝ 36:6፣ ኢሳ 51:10)፡፡ ይህ ከቀድሞው ታዋቂ የሜሶፖታሚያ(ባሁኑ ኢራቅ) ሕዝቦች ከሆኑት ሰናዖር ፣ እና ባቢሎን የተወሰደ የአፈ ታሪክ ቃል ሲሆን በብሉ ኪዳን ወስጥ ግን ይህ የአፈ ታሪክ ቅዱሳዊ አገላለጽ ሙለ ለሙሉ ቀርቷል፡፡ በዚህ አውድ ውስጥ ይህ የውጭ ወራሪዎች እስራኤልን እንዲያጠፏት እግዚአብሔር እየፈቀደላቸው መሆኑን ያመለክታል፡፡

**7:5 "እንድትተው እለምንሃለሁ"** ይህ (BDB 292፤ KB 292) ሌላ ኋል ትኩረት የሚሻ ግስ ነው፡፡ ሆኖም ግን ነብዩ እዚህ ላይ ለይቅርታ ይግባኝ እየጠየቀ ሳይሆን ፍርዱ እንዲቆም እየለመነ እንደሆነ ያስተውሉ፡፡ ያህዌ በምህረት የተሞላ ነው፤ነገር ግን ለትዕግስቱም መጨረሻ አለው (ዝ.ከ. ቁ 8፣ 8:1)፡፡

**7:6** በ7፡3 ላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ፡፡

## አሞፅ: 7:7-9

**7እንዲህም አሳየኝ እነሆም፥ ጌታ ቱንቢውን ይዞ በቱንቢ በተሠራ ቅጥር ላይ ቆሞ ነበር።**
**8 እግዚአብሔርም፦ አሞጽ ሆይ፥ የምታየው ምንድር ነው? አለኝ። እኔም።**
**ቱንቢ ነው አልሁ። ጌታም፦ እነሆ፥ በሕዝቤ በእስራኤል መካከል ቱንቢ አደርጋለሁ**
**ከእንግዲህም ወዲህ ደግሞ አላልፋቸውም 9 የይስሐቅም የኮረብታው መስገጃዎች ይፈርሳሉ፥**
**የእስራኤልም መቅደሶች ባድማ ይሆናሉ በኢዮርብዓምም ቤት ላይ በሰይፍ እነሣለሁ አለ።**

**7:7 "ጌታ በተሠራ በቱንቢ ቅጥር ላይ ቆሞ ነበር"** ይህ ከሜዳ ላይ በተወሰዱ ድንጋዮች የተሰራ ደካማ ግንብ የሚያመለክት ይመስላል፡፡ከጊዜ በኋላ እነዚህ ድንጋዮች ቦታቸውን ይስቱ እና ምንም የማይጸኑ እና የሚወድቁ ይሆናሉ፡፡

▣ **"ቱንቢ"** ይህ ልዩ ቃል (BDB 59፤ KB 71) በብሉ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሰው እዚህ ላይ ብቻ ነው፡፡ይህ የግንባታ መሳሪያ (በጫፉ ላይ ብረት የተደረገበት ሲባጎ) የነበረ ሲሆን የግንባታዎችን ቀጥተኛነት ለማረጋገጥ ይጠቅማል፡፡ይህ የሰው ዘር ከእግዚአብሔር መተዳደሪያ ደንብ በመለየቱ ምክንያት የመጣውን ፍርድ የሚገልጽ ዘይቤያዊ አጠቃቀም ነው (ዝ.ከ. 2ኛነገ 21:13፣ ኢሳ 28:17፣ 34:11፣ ሰቆ 2:8)፡፡
ምንም እንኳን አብዛኞቹ የእንግሊዝኛ ትርጓሜዎች ስለ "ቱንቢ" ከላይ የተጠቀሰውን አውዳዊ ትርጉም የሚቀበሉ ቢሆኑም ለዚህ የከለዳዊያን የትውስት ቃል "ናስ" ትክክለኛው ትርጉም ሊሆን እንደሚችል የመከራከሪያ ነጥብ ማንሳት ይቻላል፡፡ ይህ እንደዚህ ከሆነ የሚታሰበው "መከላከያው ቀላል" የሆነን የናስ ቅጥር (ማለትም፤በደካማ ብረት የተሰራ ግድግዳ፤ ናስ) የሚገልጽ ዘይቤ እንደሆነ ነው፡፡ ብዙ ነብያቶች የብረቱን አስተሳሰብ ይጠቀማሉ (ዝ.ከ. ኤር 15:20፣ ሕዝ 4:3)፡፡ ነገር ግን የትኛውም ቢሆን ይህ የፍርድ ራእይ ነው፡፡ እስራኤል በወታደራዊ ኃይሏ የተጠበቀች እና በመንፈሳዊ ሁኔታዋ ትክክል እንደሆነች ታስባለች ፤ ነገር ግን አይደለችም!

**7:8 "ከእንግዲህም ወዲህ ደግሞ አላልፋቸውም"** ይህ በቀጥታ "ከእንግዲህ ወዲህ (BDB 414፤ KB 418፤ *ሂፊል ያልተቋጨ*) ደግሞ አላልፋቸውም" (BDB 716፤ KB 778፤ *ኋል መጨረሻ የሌለው*) ማለት ነው፡፡አሞፅ የእስራኤልን የአመጻ ጥልቀት በመረዳቱ ለእሷ ማማለዱን አቁሟል፡፡

**7:9 "የኮረብታው መቅደሶች"** እነዚህ "ኮረብታዎች" (BDB 119) የሚያመለክቱት የአካባቢውን የርቢ አምልኮ ስፍራዎች ("ይፈርሳሉ" BDB 1030፤ KB 1053፤ *ኒፋል የተቋጨ*) ሲሆን "መቅደሶች" (BDB 874) የሚለው ደግሞ በኢዮርብዓም 1ኛ (ከክ ል በ 922) የተጀመሩትን በዳን እና በቤቴል ከተሞች የሚገኙ የአገሩ የአምልኮ ስፍራዎችን ("ባድማ ይሆናሉ" BDB 351፤ KB 349፤ *ኋል ያልተቋጨ*) ያመለክታል፡፡

▣ **"በኢዮርብዓምም ቤት"** ይህ ከክ ል በ በ922 በሰራተኛ እና በግብር ላይ በነበረው ጫና ምክንያት በሰለሞን ልጅ ሮብዓም ላይ ያመጹትን አስሩን የሰሜን ነገዶች የመራውን ኢዮርብዓም 1ኛን ያመለክታል፡፡ እውነተኛው ነጥብ የነበረው ንጉሱ የራሱን እጅግ ሃብታም የሩቅ ምስራቅ ቤተሰቦች ለመደገፍ በሕዝቡ ላይ ያደረገው ጭቆና ነበር (ዝ.ከ. 1ኛ ነገ 11)፡፡

▣ "በሰይፍ" ሰይፍ (ማለትም ጦርነት) ከቁ 1 የአንበጣው መንጋ ጭንቅ ጋር ተያይዞ የሚሄድ ነው፡፡እንዲሁም ቁ 4 ውስጥ ካለው የሚፋጅ እሳት ጋር የሚያያዝ ነው፡፡

## አሞፅ: 7:10-13

**10-11 የቤቴልም ካህን አሜስያስ ወደ እስራኤል ንጉሥ ወደ ኢዮርብዓም ልኮ አሞጽ ኢዮርብዓም በሰይፍ ይሞታል፥ እስራኤልም ከአገሩ ተማርኮ ይሄዳል ብሎአልና አሞጽ በእስራኤል ቤት መካከል ዐምፆብሃል ምድሪቱም ቃሉን ሁሉ ልትሸከም አትችልም አለ።**
**12 አሜስያስም አሞጽን። ባለ ራእዩ ሆይ፥ ሂድ ወደ ይሁዳም ምድር ሽሽ፥ በዚያም እንጀራን ብላ፥ 13 በዚያም ትንቢትን ተናገር ነገር ግን ቤቴል የንጉሥ መቅደስና የመንግሥት ቤት ናትና ከእንግዲህ ወዲህ በዚህ ደግሞ ትንቢት አትናገር አለው።**

**7:10-17**
የዚህ አይነቱ በእግዚአብሔር ተናጋሪ እና በቤቴል መቅደስ መሪ መካከል ያለው ገጠመኝ በተለያዩ የፍርድ አውዶች ሊከፋፈል ይችላል፡፡

1. አንበጦች ፤ 7:1-3
2. እሳት ወይም ድርቅ ፤ 7:4-6 (ዝ.ከ. 8:11-13)
3. ቱንቢ፤ 7:7-9

4. የቃርሚያ ፍሬ ፤ 8:1-3
5. የመሬት መንቀጥቀጥ ፤ 9:1-2 (ሊሆን የሚችለው 8:7-10)

**7:10 "ካህን አሜስያስ"** ይህ በቤቴል ብሔራዊ የወርቃማ ጥጆች የአምልኮ ስፍራ ላይ የነበረው ዋና ካህን (ታርጉምሰ) ነበር፡፡ እዚህ ላይ ሕዝቡ በሁለት የእግዚአብሔር ተወካዮች መገኘት ግራ ሲጋቡ እናያለን፡፡ ሁለቱም ካህኑ እና ነብዩ ለእግዚአብሔር እንደሚናገሩ እና ሁለቱም እግዚአብሔር ስልጣን እንደሰጣቸው ይናገራሉ፡፡

▣ **"ኢዮርብዓም"** ይህ በዚህ ጊዜ የነበረውን የእስራኤል ንጉስ ኢዮርብዓም 2ኛን (ዝ.ከ. 1:1) ያመለክታል፡፡ የንጉሱ የንግስና ጊዜ በተደጋጋሚ ጊዜ እንደሚታየው ከሊቅ እስከ ሊቅ ይለያያል፤

1. ጆን ብይራት ፤ 786-746 ከክ ል በ
2. ኢ. ጄ ያንግ ፤ 783-743 ከክ ል በ
3. አር ኬ ሃሪሰን፤ 782/81-753 ከክ ል በ

የብሉ ኪዳንን ታሪኮች የጊዜ ሁኔታ ጋር የተያያዙ ብዙ ችግሮች አሉ፤

1. በአለም ማህበረሰባዊ ታሪክ እና በብሉ ኪዳን መካከል የሚገኘው ብቸኛ ድልድይ ከክ ል በ 608 ውስጥ የነበረው የከርከሚሽ ጦርነት ነው፡፡
2. የንጉሶች ንግስና እርስ በራሳቸው ይጠላለፋሉ (በአንድ ላይ መንገስ)፡፡
3. ባቢሎናዊያን እና ፍልስጤሞች የንጉሶቻቸውን የንግስና ጊዜ አሰጣጣቸው የተለየ ነው (ማለትም፤የአመቱን ክፋይ የመቁጠር ወይም ያለመቁጠር)፡፡

▣ ***"አሞጽ ዐምፆብሃል"*** አሜሲያስ አሞፅን በፖለቲካ ክህደት ከሶታል (*"ዐመፅ"* BDB 905፤ KB 1153፤ *ጓል* የተቋጨ፤ለዚህ ቃል አጠቃቀም ምሳሌ 2ኛ ሳሙ 15:12፣ 2ኛነ 11:14፣ 15:15 ይመልከቱ)፡፡ በምስራቅ አቅራቢያ የነበሩ ንጉሶች ስለነብያቶቻቸው ንግግር እና በሕብረተሰቡ መካከል ስላላቸው ዕውቅና በጣም ንቁ የሆነ አመለካከት የነበራቸው ሲሆን መጥፎ ነገርን እንዳይተነብዩም ይፈሩ ነበር፡፡

▣ ***"ምድሪቱም ቃሉን ሁሉ ልትሸከም አትችልም"*** አሞፅ በቤቴል እየተናገረ ነው፡፡ ሁሉም የመጽሐፉ ስነ ምድራዊ አቅጣጫዎች የተሰጡት ከቤቴል አቀማመጥ በመነሳት ነው፡፡ ሆኖም ግን ይህ ሃረግ አሞፅ ቤቴል ላይ ብቻ ሳይሆን በሰሜን ብዙ ቦታዎች ላይ እንደተናገረ ያመለክታል፡፡ "ሸከም" (BDB 465፤ KB 463፤ *ሂፊል መጨረሻ የለሸ ስሪት*) የሚለው ግስ የያህዌን ቁጣ መሸከም እንደማለት ሆኖ ሊያገለግል ይችላል (ዝ.ከ. ኢዩኤል 2:11፣ ኤር 10:10)፡፡ እስራኤላዊያን አሞፅን አየሰሙት ነበር!

**7:11 "አሞጽ ኢዮርብዓም በሰይፍ ይሞታል፥ ብሎአልና"** ይህ ኢዮርብዓም 2ኛን ያመለክታል፡፡ አሜስያስ የአሞፅን ንግግር በመጠኑም ቢሆን አዛብቶ ተናግሯል፤ ነገር ግን እውነታው ይህ የእሱ መልዕክት ፍሬ ነገር ነበር፡፡

▣ **"እስራኤልም ከአገሩ ተማርኮ ይሄዳል"** ይህ የሚያሸብር የፍርድ እወጃ ነበር፡፡ የተስፋይቷ ምድር ከዚህ በኋላ በያህዌ ጥበቃ ስር አይደለችም! የሆነው ተቃራኒው ነገር ነው፤ የተሰፋይቷ ምድር በያህዌ ጥቃት ስር ነች፡፡እስራኤል የገበሬዎቿን የመሬት ድርሻዎች በባለስልጣና እንዲወርሱ ፈቅዳ ነበር (በሃብታሞች፣ በኃይለኞች እና በተጽዕኖ ፈጣሪዎች) ፤ እናም አሁን ያህዌ የተሰፋ ቃሉን ሸሯል! በአሞፅ የእስራኤላዊያን መማረክ ብዙ ጊዜ ጠቅሶታል (ዝ.ከ. 4:2-3፣ 5:5፤27፣ 6:7፣ 7:17፣ 9:4፤14)፡፡

**7:12 "ሂድ ሸሽ"** እነዚህ ሁለቱም ("ሂድ" BDB 229፤ KB 246፤ "ሸሽ" BDB 137፤ KB 156) *ጓል* ትኩረት የሚሹ ናቸው፡፡ ቀጥሎ በዚህ ቁጥር ውስጥ ሌላ ሦስተኛ *ጓል* ትኩረት የሚሹ ግሶች አሉ፤ "ብላ"(BDB 37፤ KB 46)፡፡ አሜስያስ አሞፅ ከመቅደሱ ፤ ከከተማው እና ከአገሩ እንዲወጣ ይፈልጋል!

▣ ***"ባለ ራእዩ ሆይ"*** አሜስያስ አሞፅን ባለ ራዕዩ ብሎ የሚጠራበት ምክንያት ምናልባትም አሞፅ ራዕዮቹን ለሕዝብ ያውጅ ስለ ነበር ሊሆን ይችላል፡፡ቃሉ ከ "ነብይ" ጋር ተመሳሳይ ትርጉም ያለው ነበር፡፡

## ልዩ ርዕስ በነብይ ላይ የሚነገሩ የተለያዩ የእብራዊያን ቃላት

*መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት*

1. *ሮሂ* = "ባለ ራእይ" (BDB 906)፤ 1ኛ ሳሙ 9:9፡፡ ይህ ማጣቀሻ "መጥራት" ከሚለው ዋና ቃል የመጣ ትርጉሙ "ነብይ" ወደ ሆነው *ናቢ* የተደረገን ሽግግር ያሳያል፡፡ "ሮሂ" ከተለመደው የእብራዊያን ቃል "መመልከት" ከሚለው የመጣ ነው፡፡ይህ ሰው የ እግዚአብሔርን መንገድ እና ዕቅድ በደንብ የተረዳ ስለነበር የ እግዚአብሔርን የወደፊት ፈቃድ በነገሮች ላይ ለማረጋገጥ ምክር ይጠየቅ ነበር፡፡
2. *ሆዜ* = "ባለ ራእይ" (BDB 302)፤ 2ኛ ሳሙ 24:11፣ አሞፅ 7:12፡፡ ይህ በዋናነት ከሮሂ ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው፡፡ይህ ካልተለመደው የእብራዊያን ሃረግ "በራእይ መመልከት" ከሚለው የመጣ ነው፡፡የቦዝ አንቀጽ መልኩ ባብዛኛው ነብያትን ለማመልከት ያገለግላል፡፡
3. *ናቢ* = "ነብይ"(BDB 611) ከከለዳዊያን ግስ ናቡ = "መጥራት" እና ከአረቢክ *ናባ* = "ማስታወቅ" ጋር የሚዛመድ ነው፡፡ ይህ ነብይን የሚወክል በጣም የተለመደ ብሉይ ኪዳን ቃል ነው፡፡ ከ300 ጊዜ በላይ ተጠቅሷል፡፡ትክክለኛ አመጣጡ የተረጋገጠ አይደለም፤ነገር ግን በአሁኑ ሁኔታ "መጥራት" የሚለው ቃል ተመራጩ የሚሆን ይመስላል፡፡ለዚህም የበለጠው መረዳት የሚገኘው ያህዌ የሙሴን ከፈርዖን
   እስከ አሮን ያለውን ዝምድና የገለጸበትን በመገንዘብ ነው(ዝ.ከ. ዘጸ 4:10-16፣ 7:1፣ ዘዳ 5:5)፡፡ነብይ ለእግዚአብሔር ሕዝብ የእግዚአብሔርን ነገር የሚናገር ነው(ዝ.ከ. አሞፅ 3:8፣ ኤር 1:7፤17፣ ሕዝ 3:4)፡፡

4. *ሦስቱም ቃላት* በሙሉ በ፲ኛ ዜና 29:29 የነብይ ጥቅም ውስጥ ሳሙኤል- *ሮሂ* ናታን -*ናቢ* እና ጋድ - *ሆዜ* በመባል ተገልጸዋል፡፡
5. *ኢሻህ - ሔሎሒም* "የእግዚአብሔር ሰው" የሚለው ሀረግ በተጨማሪም ለእግዚአብሔር ተናጋሪ የሆነን ለመግለጽ ሰፋ ያለ ቦታ አለው፡፡ይህም ቃል በተወሰነ መልኩ ከ76 ጊዜ በላይ በብሉ ኪዳን ውስጥ "ነብይን" በሚወክል ስሜት ተገልጸዋል፡፡
6. የአዲስ ኪዳኑ ቃል "ነብይ" መሰረቱ የግሪክ ነው፡፡ የመጣውም (1) *ፕሮ* ትርጉሙም "ቀደም ብሎ" ወይም "ለ" ማለት ነው (2) *ፌሚ* ትርጉሙም "መናገር" ማለት ከሆነው ነው፡፡

▣ **"ወደ ይሁዳም ምድር ሽሽ"** አሜስያስ አሞፅ በእስራኤል ላይ አድሎአዊ መሆኑን ወይም የወጭ ጣልቃ ገብ ነው ብሎ እየከሰሰው ሊሆን ይችላል፡፡

▣ **"በዚያም እንጀራን ብላ፥በዚያም ትንቢትን ተናገር"** በግልጽ እንደሚታየው የተወሰኑ ነብያት በመንግስት ሌሎች ደግሞ በሚሰብኩት ሕዝብ ነጻ ስጦታ ይደገፋሉ፡፡ አሜስያስ አሞፅ ለገንዘብ ነው የሚሰብክ ብሎ እየከሰሰው ነው፡፡ አሞፅ ደግሞ በቁ 14 ከዚህ በፊትም ቢሆን የገቢ ምንጭ እንደነበረው በመናገር ምላሽ እየሰጠ ይመስላል፡፡

**7:13 *"የንጉሥ መቅደስና የመንግሥት ቤት ናትና"*** አሜስያስ ይህ የእግዚአብሔር መቅደስ ሳይሆን የንጉሱ መሆኑን ሲገልጽ እውነቱን በምጸት እየገለጸ እንደነበረ ግልጽ ነው፡፡ በእርግጥ እዚህ ላይ ያለው አመልካች ነገር በኢዮርብዓም ፲ኛ ከተመሰረቱት አምልኮ ስፍራዎች አንዱ የሆነውን እና በሰሜኑን አስር ነገዶች የባለስልጣናት ሃይማኖታዊ ቦታ እየሆነ የመጣውን ስፍራ ነው፡፡ይህም ከጊዜ በኋላ በአክዓብ እና በኤልዛቤል (ዝ.ከ. ፲ኛ ነገ 18-21) ምክንያት ወደ ከነዓን የርቢ ጣዖታት አምልኮ የተበላሸው ስፍራ ነው፡፡

## አሞፅ: 7:14-17

**14 አሞጽም መልሶ አሜስያስን አለው። እኔ ላም ጠባቂና ወርካ ለቃሚ ነኝ እንጂ ነቢይ ወይም የነቢይ ልጅ አይደለሁም 15 እግዚአብሔርም በጎቹን ከመከተል ወሰደኝ፥ እግዚአብሔርም፦ ሂድ፥ ለሕዝቤም ለእስራኤል ትንቢት ተናገር አለኝ። 16 አሁንም የእግዚአብሔርን ቃል ስማ አንተ። በእስራኤል ላይ ትንቢት አትናገር፥ በይስሐቅም ቤት ላይ አትስበክ ብለሃል 17 ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ሚስትህ በከተማይቱ ውስጥ ጋለሞታ ትሆናለች፥ ወንዶችና ሴቶች ልጆችህም በሰይፍ ይወድቃሉ፥ ምድርህም በገመድ ትከፈላለች አንተም በረከሰች ምድር ትሞታለህ፥ እስራኤልም ከምድሩ ተማርኮ ይሄዳል።**

**7:14 "ነቢይ ወይም የነቢይ ልጅ አይደለሁም"** አሞፅ የእግዚአብሔር ጥሪ የሙያ (ዝ.ከ. ቁ 15) ጥሪ እንዳልሆነ አስረግጦ እየተናገረ ነበር፤ በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ ግስ መቅረብ አለበት፡፡ የአሁን ጊዜው ለዚህ አውድ ይሆነዋል፤ ለቁ 15 ግን አይሆነውም፡፡ ይህ አሁን ነብይ እንደሆንኩ በሚያመለክት ሁኔታ "ነብይ አልነበርኩም" ተብሎ ሊተረጎም ይችል ነበር፡፡ ይህ የአሞፅ አረፍተ ነገር "ነብይ" ከ"ነብይ ልጅ" ጋር ያለውን አሉታዊ ንጽጽር የሚያሳይ ይመስላል፡፡ እንደዚህ ከሆነ በግለሰብ ደረጃ ለእግዚአብሔር ለመናገር በተጠራ ግለሰብ እና በነብያት ማህበር አባል እንዲሆን በእግዚአብሔር በተጠራ ግለሰብ መካከል ያለውን ልዩነት የሚገልጽ ይሆናል(ማለትም ሳሙኤል፤፲ኛ ሳሙ 10:5፤6፤10፣ 19:20፣ ፲ኛ ነገ 20:35፣ 2ኛነገ 2:3-7፣ 4:38፣ 6:1)፡፡ቀደም ብሎ በተገለጸው ሁኔታ "ልጅ" የአንድ ማህበርን አባል እንጂ የቤተሰብ አባልን የሚያመለክት አይደለም፡፡

▣ **"እኔ ላም ጠባቂና ወርካ ለቃሚ ነኝ እንጂ"** በመግቢያው ውስጥ ያሉትን ሙሉ ማስታወሻች ይመልከቱ፡፡ በዚህ አውድ መሰረት ይህ የአሞፅን ሃብት ወይም ስራውን አመልካች መንገድ ሆኖ ሊጠቅም ይችላል፡፡ ለመብላት ትንቢት መናገር አያስፈልገውም ነበር!

**7:15 "በጎቹን ከመከተል ወሰደኝ"** ይህ ግስ (BDB 542፤ KB 534፤ ቋል ያልተቋጨ) የእግዚአብሔርን የስልጣን ምርጫ እና ተግባር የሚያሳይ ጠንካራ የመንፈሳዊ ትምህርት ቅዱሳዊ አጻጻፍ አለው (ለምሳሌ፤ ዘፀ 6:7፣ ዘዳ 4:20፤34፣ 2ኛ ሳሙ 7:8፣ ፲ኛ ነገ 11:37፣ ኤር 43:10)፡፡ እግዚአብሔር አሞፅን ለእሱ እንዲናገር ጠርቶታል! ይህ "እረኛ" በሚለው ቃል ላይ የተገለጸ ሲሆን ዘይቤያዊ በሆነ ሁኔታ (1) እግዚአብሔርን ራሱን (2) የእስራኤልን መሪዎች እና (3) በአመላካች ሁኔታ ሕዝቡን ለማሳየት የሚያገለግል ነው፡፡ እስራኤል እና ይሁዳ ባጠቃላይ የእግዚአብሔር በጎች ናቸው፡፡

▣ **"ለሕዝቤም ለእስራኤል ትንቢት ተናገር አለኝ"** በዚህ አውድ ውስጥ ብዙ ትኩረት የሚሹ ግሶች አሉ፡፡

1. "ሂድ፤" BDB 229፤ KB 246፤ ቋል ትኩረት የሚሻ
2. "ትንቢት ተናገር" BDB 612፤ KB 659፤ *ኒፋል* ትኩረት የሚሻ
3. "ስማ" ቁ 16፤ BDB 1033፤ KB 1570፤ ኳል ትኩረት የሚሻ

▣ **"ለሕዝቤም ለእስራኤል"** ይህ የያዕቆብን አዲስ ስም (ዝ.ከ. 7:8፤15፣ 8:2) የሚጠቀም የቃል ኪዳኑ ሃረግ ነው (ዝ.ከ. ዘፍ 32:28)፡፡
**7:16** ይህ ከያህዌ ተቃራኒ የነበሩትን የአሜስያስ ቃላቶች አሞፅ እዘረዘራቸው ነው፡፡

▣ **"በይስሐቅም ቤት ላይ"** ይህ በብሉ ኪዳን ውስጥ የዚህ ሃረግ ብቸኛ አገላለጽ ነው፡፡ ይህ ምናልባትም ከ"ያዕቆብ ቤት" (ዝ.ከ. 3:13) ወይም "የእስራኤል ቤት" (ዝ.ከ. 5:1፤3፤4፤25፣ 6:1) ጋር ትይዩ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ስለ አሞፅ በሰሜን መስበክ በአሜስያስ የቀረበ ቁንጽል ሃተታ ነበር፡፡

**7:17** አሞፅ የካህኑ ሚስት በሕዝብ ፊት እንደምትደፈር (እናም ታዋቂ ሴተኛ አዳሪ እንደምትሆን) ፣ ልጆቹ እንደሚገደሉ ፣ ንብረቶቹ ለሌሎች እንደሚከፋፈል እና ራሱ ካህኑ ለኑሮ ወደ አሦር እንደሚሰደድ ይናገራል፡፡ ካህኑም በሁሉም የእስራኤል መሪዎች ላይ ምን ሊደርስባቸው እንደሚችል ምሳሌ ይሆናል፡፡ በገሃዱ ስሜት ሲታይ እነዚህ በአሜስያስ ላይ የደረሱት እርግማኖች እሱ ወይም የእሱ ተወላጆች ነብያት እንደማይሆኑም ጨምሮ የሚያስረዳ ነው፡፡

1. ሚስት ለካህኑ የጋብቻ አጋር አትሆንም (ዝ.ከ. ዘዳ 22:23-24)

2. ምንም የሚተርፉለት ልጆች አይኖሩም
3. በካህንነቱ ምክንያት ማግኘት የሚገባውን ጥቅማ ጥቅሞች ማግኘት ሳይችል በውጭ አገር መሬት ላይ ይሞታል፡፡

(የዴቪድ ኤ ሁባርድ ኢዩኤል እና አሞፅ (የቲንዳል ብሉይ ኪዳን ሃተታገፅ 217 ላይ ይመልከቱ))፡፡

### የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልስህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. እግዚአብሔር ሃሳቡን ይቀይራል? እንዴት?
2. ንስሃ መግባት ከይቅርታ ጋር ያለው ዝምድና እንዴት ነው?
3. ለእግዚአብሔር በእውነት ማን እንደሚናገር ማወቅ ይችላሉ? (ነብይ ፣ ካህን ወይስ አዋቂ)
4. የእግዚአብሔር ፍርድ ዘላለማዊ ነው ወይስ ጊዜያዊ?

# አሞፅ 8
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|
| | አምስቱ የእግዚአብሔር ፍርድ እና የተሀድሶ ትንቢት (7:1-9:15) | የአንበጦች ራዕይ | ራዕዮች (7:1-9:10) |
| የቃርሚያ ፍሬ ራዕይ | አራተኛው ራዕይ | የፍሬ የዕንቅብ ራዕይ | አራተኛው ራዕይ፡ ፍሬ የሞላበት ዕንቅብ |
| 8:1-3 | 8:1-3 | 8:1-2ሀ | 8:1-3 |
| | | 8:2ለ-3 | |
| የእሳት ራዕዮች | የእስራኤል ክስ | የእስራኤል ጥፋት | በአጭበርባሪዎችና በበዝባገሮች ላይ |
| 8:4-10 | 8:4-6 | 8:4-6 | 8:4-7 |
| | 8:7-8 | 8:7-10 | |
| | | | 8:8 |
| | | | የቅጣት ትንበያ፡ ጨለማና ለቅሶ |
| | 8:9-10 | | 8:9-10 |
| | | | የእግዚአብሔርን ቃል ረሃብና ድርቅ |
| 8:11-14 | 8:11-12 | 8:11-14 | 8:11-12 |
| | | | ትኩስ የፍርድ ትንበያ |
| | 8:13-14 | | 8:13-14 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ vii ተመልከት)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃል እና የሃረግ ጥናት

### አሞፅ: : 8:1-3

**1 ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ አሳየኝ እነሆም፥ የቃርሚያ ፍሬ የሞላበት ዕንቅብ ነበረ። 2 እርሱም፦ አሞጽ ሆይ፥ የምታየው ምንድር ነው? አለኝ። እኔም። የቃርሚያ ፍሬ የሞላበት ዕንቅብ ነው አልሁት። እግዚአብሔርም አለኝ፦ ፍጻሜ በሕዝቤ በእስራኤል ላይ መጥቶአል ከእንግዲህ ወዲህ ደግሞ አላልፋቸውም።3 የመቅደሱ ዝማሬ በዚያ ቀን ዋይታ ይሆናል፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር የሰዎችም ሬሳ ይበዛል፥ በስፍራውም ሁሉ በዝምታ ይጣላል።**

**8:1 "ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ አሳየኝ እነሆም"** ይህ ሃረግ ቀርቦ የነበረው በምዕራፍ 7 ውስጥ የሚገኙትን የመጀመሪያ ሦስት ራዕዮች ለማስተዋወቅ ነበር፡፡በድጋሜ መገለጹ የራዕዮቹን ተዛማችነት ያሳያል (ዝ.ከ. 7:1፣4፣7፣ 8:1)፡፡

▣ **"የቃርሚያ ፍሬ የሞላበት ዕንቅብ"** በቀ 2 ውስጥ "ፍሬ" በሚለው ቃል እና "ፍጻሜ"(ዝ.ከ. ዳን 8:17፣19፣ 11:40፣ 12:4፣6) በሚለው ቃል መካከል የሚነገር የእብራዊያን ቃል አለ፡፡እነዚህ ሁለት ቃላት በተመሳሳይ መንገድ ይገለጹ ነበር (ዝ.ከ. ኒዶት፣ ጥራዝ 3፣ ገፅ 920)፡፡ የቃርሚያ ፍሬ (BDB 884) የወቅቱ የመጨረሻ ፍሬ ነው፡፡ ይህ ፍሬ በሙቀት ከመጠን በላይ የሚያበስል ሲሆን ለእስራኤልም ሕዝብ መንፈሳዊ ህይወት መበላሻት የሚገባ ዘይቤ ነበር፡፡እነሱም ከሚገባው በላይ ለፍርድ በስለው ነበር!

**8:2"'ፍጻሜ በሕዝቤ በእስራኤል ላይ መጥቶአል'"** ግሱ(BDB 97፣ KB 112፣ ኳል የተቋጨ) በእስራኤል እና በአብርሃም ተወላጆች መካከል የነበረው ቃል ኪዳን ከሰሜኑ ነገዶች ጋር ተጠቃሎ መሻሩን የሚወክል ነው፡፡የያህዌን ጥልቅ የስሜት ህመም "በሕዝቤ በእስራኤል"( ዝ.ከ. ሆሴ 11:1-4፣8) በሚለው ሃረግ ውስጥ ማየት ይቻላል፡፡ነገር ግን ይህ አባባል ሙሉ ለሙሉ የሚሻር አይሆንም፡፡ተስፋ አለ (ዝ.ከ. 9:7-15፣ ሆሴ 11:9-11)፡፡ቃል ኪዳኑ እንዳለ እንዲቀጥል መፍቀድ ጭካኔ ይሆን ነበር፡፡የያህዌ ፍርድ ምንም እንኳን የሚያሰቃይ ቢሆንም እንኳን ይህን ያደረገው ኃያል የሆነውን እውነተኛ የመታደስ ፍቅሩን ለማሳየት ነበር!

▣ **"ከእንግዲህ ወዲህ ደግሞ አላልፋቸውም"** ይህ ሃረግ በጣም የጎላ ነው፡፡ይህ በቀጥታ ሲታይ "ከእንግዲህ ወዲህ (BDB 414፣ KB 418፣ ሂፊል ያልተቋጨ) ደግሞ አላልፋቸውም" (BDB 716፣ KB 778፣ ኳል መጨረሻ የሌለው ስራት) ማለት ነው፡፡ ቃል ኪዳኑ ተሰብሯል (ዝ.ከ. 7:8)! የእግዚአብሔር ሕዝብ እሱን በመተው እንደገና ከከነዓን የርቢ አምልኮ ጋር ተባብረዋል፡፡ በዘፍ 15:16 አሞራውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር ያልተመለሱበት ምክንያት አምላክ የለሽ በሆነው እኩይ አኗኗራቸው ነበር፡፡አሁን ደግሞ የእግዚአብሔር የራሱ ሕዝብ በዚሁ ተመሳሳይ አኗኗር ምክንያት እንዲሁ ሆነባቸው፡፡ የእግዚአብሔር ትዕግስት ወደ ፍጻሜ እንደሚመጣ በኤር 15:5-9 እና በሕዝ 7:2-9 ውስጥም ተጠቅሷል፡፡

**8:3 "የመቅደሱ ዝማሬ"** ይህ "ዝማሬ" (BDB 1010) የሚለው ቃል የሴት ብዙ ቁጥር ሲሆን በችሎት ላይ ይዘምሩ የነበሩ ሴቶች የተዋጣላቸው አልቃሾች እንደሚሆኑ የሚያሳይ ምፀት ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን በጣም የበዙ በድኖች ስለነበሩ ብቸኛው ድምጽ ፀጥታ ነበር! (ስለ ለቅሶ ስርዓት የተብራራ ውይይት የሮናልድ ዲቫክስን ጥንታዊቷ እስራኤል ጥራዝ 1፣ ከገፅ 56-61 ላይ ይመልከቱ)፡፡
ሁለት ትረጉም ሊሆኑ የሚችሉ አማራጮች አሉ፤ እነሱም (1) "ቤተ መንግስት" (TEV፣ NJB፣ ዝ.ከ. 6:5) ወይም (2) "የአምልኮ ስፍራ" ወይም "መቅደስ" ናቸው፡፡ በቁ 10 (ዝ.ከ. 5:23) ምክንያት ቁጥር 2 ምርጥ አማራጭ ይመስላል፡፡

▣ **"ዋይታ ይሆናል"** ግሱ (BDB 410፣ KB 413፣ ሂፊል የተቋጨ) በኤርምያስ ክፍል ውስጥ ከአካባቢው ሕዝቦች ጋር በተያያዘ ፍርድ ብዙ ጊዜ ቀርቧል (ዝ.ከ. ኤር 47:2፣ 48:20፣31፣39፣ 49:3፣51:8)፡፡ እሱ የኢሳያስን አጠቃቀም የተከተለ ይመስላል (ዝ.ከ. ኢሳ 13:6፣ 14:31፣ 15:2፣3፣ 16:7[ሁለቴ]፣ 23:1፣6፣14)፡፡ "ለቅሶ" ፣ "ጩኸት" እና "የድንጋጤ ጩኸት" በሞት እና በውድመት ምክንያት ለመጣው ዋይታ ጥሩ ትርጓሜ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የስምንተኛው ክፍለ ዘመን ደቂቀ ነብያት ይህን ከያህዌ መጪ ፍርድ ጋር በማያያዝ ብዙ ጊዜ ተጠቅመውበታል፡፡

1. ሆሴ 7:14
2. ኢዩኤል 1:5፣11፣13
3. አሞፅ 8:3
4. ሚክያስ 1:8

▣ **"በዚያ ቀን"** ይህ በስምንተኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ ነብያት በተደጋጋሚ ጊዜ የሚጠቀሙበት የተለመደ የፍርድ ዘይቤ ነበር፡፡ያህዌ ሕዝቡን ለበረከት (ዝ.ከ. አሞፅ 9:11፣13) ወይም ለእርግማን (ዝ.ከ. አሞፅ 1:14፣ 2:16፣ 3:14፣ 4:2፣ 5:8፣18፣20፣ 6:3፣ 8:3፣9፣10፣11፣13) የሚጎበኝበት ጊዜ ይመጣል፡፡በ2:16 ላይ ያለውን ሙሉ ማስታወሻ ይመልከቱ፡፡

▣ **"በስፍራውም ሁሉ በዝምታ ይጣላል"** ይህ በጦርነቱ እና በከበባው ምክንያት የሚደረገውን ያልተለመደ የአቀባበር ስርዓትን ያመለክታል (ማለትም፤ ምንም ስልጡን አልቃሾች ወይም ባጠቃላይ ለቅሶ የሚባል አይኖርም)፡፡ይህ ሃረግ ከ6:10 ጋር ይዘመዳል(ተመሳሳይ ቃልአጋኖ ተጠቅሷል BDB 245፣ "ዝምታ")፡፡

## አሞፅ: : 8:4-6

**4 ችጋረኛውን የምትውጡ፥ የአገሩንም ድሀ የምታጠፉ እናንተ ሆይ። 5 እህልን እንሸጥ ዘንድ መባቻው መቼ ያልፋል? የኢፍ መስፈሪያውንም እያሳነስን፥ ሰቅሉንም እያበዛን፥ በሐሰተኛም ሚዛን እያታለልን፥ 6 ድሀውን በብር ችጋረኛውንም በአንድ ጥንድ ጫማ እንገዛ ዘንድ፥ የስንዴውን ግርድ እንሸጥ ዘንድ ስንዴውን እንድንሸምት ሰንበት መቼ ያልፋል? የምትሉ እናንተ ሆይ፥ ይህን ስሙ።**

**8:4 "ሆይ"** ይህ የእብራዊያኑ ቃል *ሽማዕ* (BDB 1033፣ KB 1570፣ ኳል ትኩረት የሚሻ) ነው፡፡ ትርጉሙም "ሰምቶ የሚያደርግ" ማለት ነው፡፡ይህ በዘዳ 6:4-6 ላይ ባለው አስፈላጊ ፀሎት ውስጥ የሚገኝ ቁልፍ ቃል ነው (ዝ.ከ. አሞፅ 3:1፣13፣ 4:1፣ 5:1)፡፡

▣ ቁጥር 4 በሃብታሙ እና የፖለቲካ ስልጣን ባላቸው ሰዎች ምክንያት ደሃው ("ችግረኛውን" ከ "የሃገሩንም ደሃ" እና "ደሃውን ችግረኛውን" ጋር ተያያዥ ነው ዝ.ከ. ቁ 6) መጨቆኑን ("የምትውጡ" ወይም "የምታጠፉ" BDB 983፣ KB 1375፣ ኳል *ቦዝ አንቀፅ*) ያመለክታል፡፡

**8:5** ባለጸጎች፣ኃይለኞች እና ተጽዕኖ የሚያደርጉ ሰዎች ህገወጥ፣ትክክል ያልሆነውን እና የተሳሳተ ተግባሮቻቸውን በደሃው ላይ ለመጫን ሲፈልጉ ሃይማኖታዊ ስብሰባዎች (ማለትም፣ "በመባቻ" ዝ.ከ. ዘኁ 28:11፣ 2ኛነገ 4:23 እና "ሰንበት" ዝ.ከ. ዘጸ 31:13-17) እስኪያልቁ እንኳን አይጠብቁም ነበር፤ (1) መስፈሪያውን ማሳነስ (2) ሰቅሉን እያበዙ (3) በሐሰተኛ ሚዛን እያታለሉ (4) የስንዴን ገለባ (እንደ ቆሻሻ የሚጣል የእህል ግርድ BDB

655 ወይም በወንፊት ውስጥ የሚወድቁ እድገታቸውን ያልጨረሱ እህሎች) ከስንዴው ጋር ቀላቅለው እየሸጡ፡፡ እነዚህ ሁሉ ደሀው ሕዝብ ምግብ ሲገዛ እንደሚጭበረበር የሚያመለክቱ ናቸው(ዝ.ከ. ዘሌ 19:35-36፣ ዘዳ 25:13-16፣ምሳ 20:10)፡፡
"መሸጥ"(BDB 991፣ KB 1404) እና "የኢፍ" (BDB 834፣ KB 986) የሚባሉት ግሶች ሁለቱም ተጓዳኝ ናቸው፡፡ የእነዚህ ነጋዴዎች የመበዝበዝ ፍላጎት ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ ተግባሮቻቸው በሙሉ በራሳቸው ፍላጎት ብቻ የሚነዱ ናቸው፡፡

## ልዩ ርዕስ፡ የጥንት ቅርብ ምስራቅ ክብደት እና መጠን (ሥነ-ልኬት)

ክብደቶችና መለኪያዎች በንግድ ጥቅም ላይ የሚውሉት በጥንታዊ የግብርና ኢኮኖሚ ወሳኞች ነበሩ። መጽሐፍ ቅዱስ አይሁድን ያስገነዝባል፣ እርስ በርስ ባላቸው ድርድር ፍትሓዊ እንዲሆኑ (ሌዋ 19፡35-36፤ ዘዳ 25:13-16፤ ምሳ 11:1፤ 16:11፤ 20:10)። ርግጠኛው ችግር ታማኝነት ብቻ አልነበረም፣ ነገር ግን ደረጃ ያልተበጀላቸው ቃላትና ሥርዓቱ ነው፣ በፍልስጥኤም ግልጋሎት ላይ የነበረው። ሁለት ዓይነት የክብደት ምድቦች የነበሩ ይመስላል፤ "ቀላል" እና "ከባድ" በእያንዳንዱ መጠን (የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚ መዝገበ ቃላት፣ ቅጽ 4፣ ገጽ 831 ተመልከት)። እንዲሁም የዴሲማል ሥርዓቱ (የ10 መደብ መሠረት)) የግብፅ ከሴክሳጌሲማል ጋር ተደባልቋል (ባለ 6 መደብ) የሞሶፖታሚያ።

አብዛኞቹ "ልኬቶች" እና "መጠኖች" ጥቅም ላይ ይውሉ የነበረው በሰዎች የአካል ክፍሎች፣ በእንስሳት የጭነት መጠኖች፣ በገበሬዎች መስፈሪያዎች ላይ ተመሥርተው ነበር፣ ማናቸውም ቢሆኑ ደረጃቸውን የጠበቁ አልነበሩም። ስለዚህ፣ ሰንጠረዦቹ ግምታዊና ጊዜያዊ ናቸው። ክብደቶችንና መስፈሪያዎችን ለማሳየት ቀላሉ መንገድ ተዛምዷዊ ሰንጠረዥ ነው።

I. *መጠን መለኪያ ቃላት ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውሉት*

*ሀ የጠጣር መለኪያዎች*

1. *ሆሜር* (BDB 330፣ "*ያህያ ጭነት*" *ሊሆን የሚችል*፣ BDB 331)፣ ምሳ ሌዋ 27፡16፤ *ሆሴዕ* 3፡2
2. ሌቲክ (*ወይም ሌቲች*፣ BDB 547፣ በ*ሆሴዕ* 3፡2 *የተጠቀሰው ሊሆን የሚችል*)
3. ኢፋህ (BDB 35)፣ ምሳ ዘጸ 16፡36፤ ሌዋ 19:36፤ ሕዝ 45:10-11፣13፣24
4. ሴህ (BDB 684)፣ ምሳ ዘፍ 18:6፤ I ሳሙ 25:18፤ I *ነገሥ* 18:32፤ II *ነገሥ* 7:1፣16፣18
5. ኦሜር (BDB 771 II፣ "አንድ ጭነት" ሊሆን የሚችል [የእህል ድርዳሮ (ዳውላ)]፣ BDB 771 I)፣ ምሳ ዘጸ 16:16፣22፣36፤ ሌዋ 23:10-15
6. ኢሳሮን (BDB 798፣ የኢፓፍ "አስረኛ ክፍል")፣ ምሳ ዘጸ 29:40፤ ሌዋ 14:21፤ ዘኁ 15:4፤ 28:5፣13
7. *ቃብ* (*ወይም* ካብ፣ BDB 866)፣ 2ኛ *ነገሥ* 6፡25

*ለ የፈሳሽ መለኪያዎች*

1. ቆር (BDB 499)፣ ምሳ ሕዝ 45፡14 (*የደረቅ መለኪያም ሊሆን ይችላል*፣ 2ኛ ዜና 2:10፤ 27:5)
2. ባዝ (BDB 144 II)፣ ምሳ I *ነገሥ* 7:26፣38፤ II ዜና 2:10፤ 4:5፤ ኢሳ 5:10፤ ሕዝ 45:10-11፣14
3. ሂን (BDB 228)፣ ምሳ ዘጸ 29:40፤ ሌዋ 19:36፤ ሕዝ 45:24
4. *ሎግ* (BDB 528)፣ ሌዋ 14:10፣12፣15፣21፣24

*ሐ ሰንጠረዥ* (ከሮናልድ ዲቫዩክስ፣ የጥንቱ እስራኤል፣ ቅጽ 1፣ ገጽ 201 እና ኢንሳይክሎፔዲያ ጁዳይካ፣ ቅጽ 16፣ ገጽ 379)

*ሆሜር* (ደረቅ) = ቆር (*ፈሳሽ ወይም* ጠጣር) 1
ኢፋህ (ጠጣር)= ባዝ (*ፈሳሽ*) 10 1
ሴአህ (ጠጣር) 30 3 1
ሂን (*ፈሳሽ*) 60 6 2 1
ኦሜር/ኢሳሮን (ጠጣር) 100 10 - - 1
*ቃቭ*/*ቃብ* (ጠጣር) 180 18 6 3 - 1
*ሎግ* (*ፈሳሽ*) 720 72 24 12 - 4 1

II. *የክብደት ቃላት ተዘውትረው ጥቅም ላይ የሚውሉት*

*ሀ. ሦስቱ የተለመዱት ክብደት መለኪያዎች ታለንት፣ ሼክል፣ እና ጌራህ ናቸው።*

1. በብሉይ ኪዳን ትልቁ ሚዛን ታለንት ነው። ከዘጸ 38፡25-26 አንድ ታለንት ከ3000 ሼክል እኩል መሆኑን እንረዳለን (*ማለትም*፣ "*የተጠጋጋ ሚዛን*፣" BDB 503)።
2. ሼክል የሚለው ቃል (BDB 1053፣ "ክብደት") አዘውትሮ ጥቅም ላይ እንደሚውል ይገመታል፣ ግን በጽሑፍ ላይ አልሰፈረም። በርካታ የሼክል ዋጋዎች በብሉይ ኪዳን ተጠቅሰዋል።
   ሀ "የንግድ መመዘኛ (ደረጃ)" (አአመመቅ ዘፍ 23፡16)
   ለ "የመቅደሱ ሼክል" (አአመመቅ ዘጸ 30፡13)
   ሐ "በንጉሥ ሚዛን" (አአመመቅ 2ኛ ሳሙ 14፡26)፣ እሱም ደግሞ "የንጉሣዊ ሚዛን" በኢለፋንታይን ወረቀት።
3. ጌራህ (BDB 176 II) ዋጋው 20 ነው፣ በእያንዳንዱ ሼክል (ዘጸ 30:13፤ ሌዋ 27:25፤ ዘኁ 3:47፤ 18:16፤ ሕዝ 45:12)። እነዚህ ተዋረዶች ከሞሶፖታሚያ እስከ ግብፅ ይለያያሉ። እስራኤል የተከተለው በከነዓን በእጅጉን ይዘወተር የነበረውን ግምጋሜ ነበር (ኡጋሪት)
4. ሚና (BDB 584) ዋጋው 50 ወይም 60 ሼክል ነው። ይህ ቃል ባመዛኙ የሚገኘው በኋለኞቹ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ነው (ማለትም፣ ሕዝ 45፡12፤ እዝራ 2፡69፤ ነህ 7፡70-71)። ሕዝቅኤል የተጠቀመው 60 ለ1 የሆነ ተዋረድን ሲሆን፣ ከነዓን ደግሞ የሚጠቀመው 50 ለ1 ተዋረድን ነው።
5. ቤካ (BDB 132፣ "የሼክል እኩሌታ፣" ዘፍ 24፡22) ጥቅም ላይ የዋለው በብሉይ ኪዳን ሁለቴ ነው (ዘፍ 24፡22፤ ዘጸ 38፡26) እናም ዋጋው የሼክል እኩሌታ ነው። ስሙም "መክፈል" ማለት ነው።

ለ. ሰንጠረዥ

1. ፔንታቲዩች ላይ በመመሥረት
ታለንት 1
ሚና 60 1
ሼክል 3፣000 50 1
ቤካ 6፣000 100 2 1
ጌራህ 60፣000 1፣000 20 10 1
2. ሕዝቅኤል ላይ በመመሥረት
ታለንት 1
ሚና 60 1
ሼክል 3፣600 60 1
ቤካ 7፣200 120 2 1
ጌራህ 72፣000 1፣200 20 10 1

▣ ***"መባቻው"*** ይህ በጥንት ባህል በመጀመሪያው ወር ላይ የሚደረግ ሃማኖታዊ ክብረ በዓልን ያመለክታል (ዝ.ከ. ዘኁ 28:11፣ 2ኛነገ 4:23)፡፡ አይሁዶች በጨረቃ ካላንደር ይመሩ እንደነበር ያስታውሱ፡፡

▣ ***"መስፈሪያውንም እያሳነስን"*** ይህ ስራት (BDB 24፣ 941) በዋናነት ደህው ላይ ያሉ ሚዛናቸውን ያልጠበቁ እና ሐሰተኛ የሆኑ የንግድ ተቋማትን የሚወክል ነው (ዝ.ከ. ሚክያስ 6:10-11)፡፡ እግዚአብሔር ይህን ሐሰተኛነት ይጠላል (ዝ.ከ. ምሳ 11:1)፡፡ ከእግዚአብሔር ወይም ከሕዝቡ ጋር "ከነገዱ በደንብ መነገድ ነው" የሚባል ነገር ሆኖ አያውቅም! ብዝበዛ በራስ ወዳድነት ፣ በስግብግብነት እና በውድቀት የተሞላ ልብን ያጋልጣል፡፡

**8:6** ይህ ቁጥር ምግብ የመግዛት አቅም ያልነበራቸው ችግረኛ ሕዝቦች ራሳቸውን ወይም ቤተሰቦቻቸውን በትንሽ ዋጋ ለባርነት የሚሸጡበትን (ማለትም፣ "በአንድ ጥንድ ጫማ" ዝ.ከ. 2:6) ሁኔታ በምሳሌ የሚያስረዳ ነው፡፡ እነዚህ ባለጸጋ ነጋዴዎች በጣም ከመዝቀጣቸው የተነሳ ከገለባ፣ ከቆሻሻ ፣ ከትናንሽ ድንጋዮች ወ ዘ ተ ጋር የተቀላቀለ እህል ይሸጡ ነበር፡፡ በዚህ የተጭበረበረ ሽያጭ በሚያገኙት ትርፍ ባሪያዎችን ገዝተዋል! ስለዚህ ፤ ችግረኛው ለችገራኛው ብዝበዛ ዋጋ ከፍሏል!

## አሞፅ: : 8:7-10

**7እግዚአብሔር በያዕቆብ ክብር እንዲህ ብሎ ምሎአል። *ሥራቸውን ሁሉ ለዘላለም ምንም አልረሳም።* 8 በውኑ ምድሪቱ ስለዚህ ነገር አትናወጥምን? በእርስዋም የሚኖር ሁሉ አያለቅስምን? ሙላዋም እንደ ወንዙ ትነሣለች እንደ ግብጽም ወንዝ ትነሣለች ደግሞም ትወርዳለች። 9 በዚያም ቀን ፀሐይ በቀትር እንድትገባ አደርጋለሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር በብርሃንም ቀን ምድሩን አጨልማለሁ። 10 ዓመት በዓላችሁንም ወደ ልቅሶ፥ ዝማሬአችሁንም ወደ ዋይታ እለውጣለሁ ማቅንም በወገብ ሁሉ፥ ራስ መንጨትንም በሁሉ ላይ አመጣለሁ እንደ አንድያ ልጅም ልቅሶ፥ ፍጻሜውንም እንደ መራራ ቀን አደርገዋለሁ።**

**8:7 "እግዚአብሔር በያዕቆብ ክብር ምሎአል"** በአሞፅ ውስጥ ያህዌ ቃሎቹ እውነት መሆናቸውን በሚያሳይ ሁኔታ ብዙ ጊዜ ምሏል፡፡
1. "ጌታ እግዚአብሔር በቅዱስነቱ ምሎአል" 4:2
2. "ጌታ እግዚአብሔር በራሱ ምሎአል" 6:8
3. "እግዚአብሔር በያዕቆብ ክብር ምሎአል" 8:7

ይህ ሃረግ ብዙ የሚያስኬዱ አማራጮች አሉት፤ (1) በያዕቆብ ተወላጆች ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ክብር (ዝ.ከ. 1ኛሳሙ 15:29) የTEV ይህን "ጌታ እግዚአብሔር የእስራኤል አምላክ ምሏል" ብሎ ተርጉሞታል ፣ (2) በሌላ ቦታ እግዚአብሔር በሰው ስም ሲምል ስላልታየ ፤ ይህ ምናልባትም "ጌታ እግዚአብሔር እስራኤል በምትኮራበት ላይ ምሏል" (የተመቅህ*የመመምሪያ መጽሐፍ ፤ ገፅ* 165) የሚል ትርጉም ሊኖረው ይችላል ወይም (3) የያዕቆብ ሕዝብ የማይለወጡ ኃጥያተኞች ሆነው ስለነበር እግዚአብሔር በዚህ የቆየ ሁኔታቸው መማሉ ሊሆን ይችላል (ዝ.ከ. 6:8)፡፡

▣ ***"ሥራቸውን ሁሉ ለዘላለም ምንም አልረሳም"*** ይህ በጣም ጠንካራ እና የጎላ አረፍተ ነገር ነው፡፡
1. ቅድመ ሁኔታ የተባለ ቅንጣት፤ (fa)
2. *Qal IMPERFECT(ያልተቋጨ )*ግስ ፤"ለመርሳት" (BDB 1013፣ KB 1489)
3. ስም የሆነው "ዘላለማዊ" "ለዘለቄታው" (BDB 664)

እነዚህ በዝባዥ ነጋዴዎች በቃል ኪዳን ወንድሞቻቸው እና እህቶቻቸው እንዲሁም ደግሞ በቃል ኪዳኑ እግዚአብሔር ላይ ለሰሩት ወንጀሎች መልስ የሚሰጡ ይሆናል!

**8:8** ይህ ጥያቄ "አዎንታዊ" ምላሽ ይጠብቃል፡፡ በግልጽ እንደሚታየው ይህ ጥቅስ ለሚከተሉት አስተሳሰቦች ጠቋሚ ነው (1) በ1፡1 ላይ የተገለጸውን የምድር መናወጥ ወይም (2) በግብጽ ውስጥ የሚገኘው የናይል ወንዝ በሚያደርሰው አመታዊ የውሃ ጎርፍ ምክንያት የመጣ ጥፋት (ዝ.ከ. 9:5፣ ኤር 46:7-8)፡፡ በዚህ ግስ (BDB 176፣ KB 204፣ *ኒፋል* የተቋጨ) ምክንያት ዮናስ ከያህዌ አይን የተጣለበትን (ዝ.ከ. ዮናስ 2:4) ሁኔታ ለመግለጽ ይጠቅማል ፤ ምናልባትም ከተስፋይቷ ምድር የሚደረግ ምርኮን የሚገልጽ ዘይቤ (ዝ.ከ. 9:1- 4፣5) ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ተመሳሳይ ቃል ያህዌ ከነዓንን ከተስፋይቷ ምድር ያስቀረበትን ሁኔታ ለመግለጽ አገልግሏል ፤ ነገር ግን አሁን እስራኤል በኃጥያቶቿ እና በጣዖት አምልኮዋ ምክንያት ተነጥላለች!

**8:9** ይህ ቁጥር በብዙ መንገዶች ሲታወቅ ቆይቷል፤ (1) እንደ ኢሳ 13:10፣ ኢዩኤል 2:2፣3:15፣ ሚክያስ 3:6 ባሉ የመጨረሻው ዘመን ቋንቋዎች (2) የዘዳ 27-29 እርግማኞችን መሰረት ያበጀውን የግብጽ መከራ ወይም (3) የፀሃይ ግርዶሽን የሚያመለክት ቀጥተኛ አገላለጽ (ዝ.ከ. 5:18-20)፡፡ የፍጥረት ፊሊካዊ ትርምስምስ የተመለስ ይመስላል፡፡ ያህዌ ከሰው ዘር ጋር ሊያደርገው የነበረው የህብረት ቅምር እንደገና ተበላሽቷል (ዝ.ከ. ሮሜ 8:19-22)፡፡ ፍጥረት በትርምስምስ ውስጥ ነው (ዝ.ከ. ሮሜ 8:19-22)፡፡ ውሃ የመጥፊያ ምክንያት (ማለትም፤ የውሃ ጥፋት) ወይም የእግዚአብሔር በረከት ምልክት (ዝ.ከ. 5:24) መሆን መቻሉ ምፀታዊ ነው፡፡ የሰው ዘር ከሁለት አንዱ ይደርስበታል! "ባህር"ን በተመለከተ ማራኪ ለሆነ ትንተና የኒዶት ጥራዝ 2፣ከገፅ 461-466 ላይ ይመልከቱ፡፡

▣ **"ፀሐይ በቀትር እንድትገባ አደርጋለሁ"** ይህ ግስ (BDB 364፣ KB 361፣ *ሂፊል* የተቋጨ) የእግዚአብሔርን ተግባር ያመለክታል፡፡ ምናልባትም ይህ በግብፅ ውስጥ የነበረውን ፅኑ ጨለማ ሊያመለክት ይችላል (ዝ.ከ. ዘጸ 10:21-22፣ መዝ 105:28)፡፡ እዚህ ላይ ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔር በሁለቱም ቀጥተኛ (ዝ.ከ. 5:8) እና ቀጥተኛ ባልሆነ (ዝ.ከ. ከቁ 11-12) መልክ ጨለማን እያመጣ እንደሆነ ነው፡፡ የ እስራኤል ብርሃን ጨልሟል (ዝ.ከ. ኤር 13:16)፡፡

**8:10** ይህ እግዚአብሔር በእስራኤል የአምልኮ ልምምዶች ላይ ባመጣቸው ፍርዶች ምክንያት የሚደረግ ተከታታይ የለቅሶ ስነ ስርዓት (ማለትም፤ የቀብር ስርዓት መዝሙሮች ፣ ማቅ ፣ ፀጉርን መንጨት) ነው፡፡ አምልኳቸው ልክ ብቸኛ ወንድ ልጁ እንደሞተበት ሰው ወደ መራራ ለቅሶ ይለወጣል (ዝ.ከ. ኤር 6:26፣ ዘካ 12: 10)፡፡

▣ ***"ራስ መንጨትንም"*** እስራኤል ከከነዓን የርቢ አምልኮ ጋር በነበራት ግንኙነት ምክንያት ይህ የአምልኮ ስርዓት ቅዱሳዊ አጻጻፍ ያላቸውን ሁሉንም "መላጨት" (ዝ.ከ. ሞአብ፣ ኢሳ 15:2፣ ኤር 48:37፣ ፍልስጤም ፣ ኤር 47:5፣ እና ፊንቄ፣ ሕዝ 27:31) ሊያመለክት ይችላል (ዝ.ከ. ዘሌ 21:5)! ነገር ግን በተጨማሪም ይህ የለቅሶ ምልክት እንዲሆን በሚያደርግ ሁኔታ የራስ ፀጉርን መንጨት ሊሆን ይችላል (ዝ.ከ. ሚክያስ 1:16፣ሕዝ 7:18)፡፡

▣ ***"መራራ ቀን"*** ይህ ቃል (BDB 600) በሞት ላይ ያለን ሃዘን ለማሳየት ያገለግላል (ዝ.ከ. 5:16-17)፡፡ እነሱ እየጠበቁ የነበሩት ተቃራኒውን ነው (ዝ.ከ. 5:18-20)! ይህ "በዚያች ቀን" ፤ "እግዚአብሔር ቀን" ለሚባሉት ሃረጎች ሰም ለበስ አገላለጽ ነው፡፡ በ2፡16 ላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ፡፡

## አሞፅ: : 8:11-14

**11 እነሆ፥ በምድር ላይ ራብን የምሰድድበት ዘመን ይመጣል፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር እርሱም የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማት እንጂ እንጀራን ከመራብና ውኃን ከመጠማት አይደለም። 12 ከባሕርም እስከ ባሕር ድረስ፥ ከሰሜንም እስከ ምሥራቅ ድረስ ይቅበዘበዛሉ የእግዚአብሔርን ቃል ለመሻት ይርዋርዋጣሉ፥ አያገኙትምም። 13 በዚያ ቀን መልካካሞች ደናግል ጐበዛዝትም በጥም ይዝላሉ። 14 በሰማርያ ኃጢአት የሚምሉና። ዳን ሆይ፥ ሕያው አምላክህን! ደግሞ። ሕያው የቤርሳቤህን መንገድ! ብለው የሚሉ፥ እነርሱ ይወድቃሉ፥ ደግሞም አይነሡም።**

**8:11** ይህ ብሉይ ኪዳን መሰረት ካለው የኢየሱስ ባርኮቶች (ዝ.ከ. ማቴ 5:6) አንዱ እና ኢየሱስ ዘዳ 8:3ን የጠቀሰበት የማቴ 4:4 ማጣቀሻ ሊሆን ይችላል፡፡ እስራኤል የምትፈልገው ሁሉ እንዳለት ታስብ ነበር ፤ ነገር ግን እኛ ሁላችንም በእውነት የሚያስፈልገን ነገር ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ማድረግ ነው!

**8:12** ይህ በስሜት የተሞላ ነገር ግን ምንም ውጤት የሌለውን እግዚአብሔር ፍለጋ ያሳል፡፡ ምን አይነት አስደንጋጭ ዘይቤ ነው! እግዚአብሔር የሰውን ልጅ በፍቅር ሲፈልግ ቆይቷል፤ ነገር ግን የሰው ልጆች እግዚአብሔርን ማግኘት የማይችሉበት ጊዜ ይመጣል፡፡ ሰዎች የተፈጠሩት ከእግዚአብሔር ጋር ህብረትን እንዲፈልጉ ነበር (ዝ.ከ. ዘፍ 1:26-27) ገሀነብ ከእግዚአብሔር ጋር የመሆንን አማራጭ የሚያስወግድ ነው!

▣ **"ከባሕርም እስከ ባሕር ድረስ"** በፍልስጤም ውስጥ ላለ ተናጋሪ ይህ ከሜዲትራንያን እስከ ሙት ባህር ያለውን ስፍራ የሚያመለክት ይሆን ነበር፡፡ ይህ በአቀማመጡ በጣም ሩቅ አይደለም ፤ ነገር ግን በአገሩ ከአንደኛው ጫፍ አስከ ወዳኛው ጫፍ ያለውን ይገልጻል፡፡

**8:13** ወጣቱም ቢሆን ብርቱውን እግዚአብሔር ማግኘት ያሳናቸዋል፡፡ የወጣቱ ሕዝብ መዛል የያህዌን ፍርድ የሚገልጽ ዘይቤ ነው (ዝ.ከ. ኢሳ 51:20)፡፡

**8:14 "በሰማርያ ኃጢአት"** ይህ በኢዮርብዓም 1ኛ (ከክ ል በ በ922) በዳን እና በቤቴል የተቋቋሙትን የወርቅ ጥጆች (ዝ.ከ. 1ኛነገ 12:28፣ ሆሴ 8:5-6፣ 10:5) ያመለክታል፡፡ ከእነሱ ይጠበቅ የነበረው በእየሩሳሌም የሚገኘውን ቤተ መቅደስ ያህዌ የሚመለክበት ስፍራ እንዲያደርጉት ነበር፡፡ ሁሉም የአስሩ ነገዶች ነገስታት በእነዚህ የአምልኮ ስፍራዎች የተነሳ በነብያት ይወገዙ ነበር፡፡ የሜዞርቲክን ጽሑፍ መሰረት ያደረገ ለዚህ ጽሑፍ ሌላ የአተረጓገም አማራጭ አለ፡፡ "የሰማሪያ አሲማት" የሚል ሃረግ አለው (ዝ.ከ. 2ኛነገ 17:30)፡፡ እንደዚህ ከሆነ ይህ የከነዓን ሴቷን የርቢ ጣዖት ሊያመለክት ይችላል፡፡ የትኛውም ጠቋሚ ትክክል ቢሆን፤ ይህ የሰሜኑ አስር ነገዶች ፤ የእስራኤል የተሳሳተ አምልኮ ያንጸባርቃል፡፡

▣ ***"ሕያው የቤርሳቤህን መንገድ"*** ይህ ያልተለመደ ማጣቀሻ ነው፡፡ቤርሳቤህ በደቡብ ይሁዳ የሚገኝ ከተማ ነው፡፡ቀደም ብሎ በ5፡5 ውስጥ ተጠቅሶ ነበር፡፡ ይህ ጉዞውን ራሱ ወይም ከአምልኮ ጋር የተገኛኘ ዙረት ወይም "መንገድ" የሚለው ቃል የስርዓት ወይም የመመሪያ ተምሳሌታዊ አነጋር ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ጣዖት አምልኮ ውስጥ እንዴት ወይም ምን እንደተካተተ የተረጋገጠ ነገር የለም፡፡ በርግጥ ይህ የከተማ አቀማመጥ ላይ የሚያተኩር አመላካች ሊሆን ይችላል (ማለትም፣ ከዳን እስከ ቤርሳቤህ፣ ዝ.ከ. መሳ 20:1፣ 1ኛሳሙ 3:20)፤ይህም ከቁ 12 ጋር የሚዛመድ ነው፡፡እነዚህ የቃል ኪዳን ሕዝቦች በአጠቃላይ የተስፋይቷ ምድር ላይ ጣዖት አምልኮን ፈጽመዋል ፤ አሁን ግን ባልተረጋጋ ሁኔታ በአጠቃላይ ምድሪቱ ላይ ይህዌን ይፈልጋሉ ነገር ግን እሱን አያገኙትም!

# አሞፅ 9
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|
| | አምስቱ የእግዚአብሔር ፍርድ እና የተሀድሶ ትንቢት (7:1-9:15) | የአንበጦች ራዕይ | ራዕዮች (7:1-9:10) |
| የእስራኤል መጥፋት | አምስተኛው ራዕይ | የጌታ ፍርድ | አምስተኛው ራዕይ መሰዊያው መፍረስ |
| 9:1-4 | 9:1-4 | 9:1-4 | 9:1-4 |
| | ሶስተኛው ምስጋና | | ምስጋና |
| 9:5-6 | 9:5-6 | 9:5-6 | 9:5-6 |
| | እስራኤል በግብረገብ ጉዳይ ዙሪያ የምታውጀው ምንም የተለየ ሙብት የላትም | | ኃጢአተኞች በሙሉ ይጠፋሉ |
| 9:7-10 | 9:7-8 | 9:7-8 | 9:7-8 |
| | 9:9-10 | 9:9-10 | |
| እስራኤል ትታደሳለች | የዳዊት ስርወ መንግስት መታደስ ትንቢት | የእስራኤል የወደፊት መታደስ | ትክክለኛ ትንቢት እና የመታደስ ምልከታ |
| 9:11-12 | 9:11-12 | 9:11-12 | 9:11-15 |
| የአሳት ራዕዮች | ትነቢት ስለሚመጣው ዘመን ክብር | | |
| 9:13-15 | 9:13-15 | 9:13-15 | |

### የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ vii ተመልከት)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ

2. ሁለተኛው አንቀጽ

3. ሦስተኛ አንቀጽ

4. ወዘተርፈ

## የቃል እና የሀረግ ጥናት

### አሞፅ: : 9:1-4

**[1] ጌታን በመሠዊያው አጠገብ ቆሞ አየሁት እርሱም እንዲህ አለ፦ መድረኮቹ ይናወጡ ዘንድ ጕልላቶቹን ምታ፥ በራሳቸውም ሁሉ ላይ ሰባብራቸው እኔም ከእነርሱ የቀሩትን በሰይፍ እገድላለሁ የሚሸሽ አያመልጥም፥ የሚያመልጥም አይድንም።[2] ወደ ሲኦል ቢወርዱ እጄ ከዚያ ታወጣቸዋለች ወደ ሰማይም ቢወጡ ከዚያ አወርዳቸዋለሁ [3] በቀርሜሎስም ራስ ውስጥ ቢሸሸጉ ፈልጌ ከዚያ አወጣቸዋለሁ በጥልቅ ባሕርም ውስጥ ከዓይኔ ቢደበቁ ከዚያ እባቡን አዝዛለሁ፥ እርሱም ይነድፋቸዋል[4] በጠላቶቻቸውም ፊት ተማርከው ቢሄዱ ከዚያ ሰይፍን አዝዛለሁ፥ እርሱም ይገድላቸዋል ዓይኔንም በእነርሱ ላይ ለክፋት እንጂ ለመልካም አላደርግም።**

**9:1** ይህ የተቀደሰውን የአምልኮ ቦታ ማውደምን ያመለክታል (ማለትም፤ መሰዊያው)፡፡ የማውደሚያውም ስልት የምድር መናወጥ ነበር (ዝ.ኪ. 1:1፤ 8:7-10፤ 9:1፤9)፡፡ እስራኤላዊያን ከያህዌ ጋር ያላቸውን የቃል ኪዳን ቁርኝት ይታመኑ ነበር፤ እግዚአብሔር ግን የተቀየጠ ሃይማኖታዊ አምልኮአቸውን አልተቀበላቸውም (ዝ.ኪ. 5:21-24፤ 8:10)፡፡

▣ ***"ጉልላቶቹን ምታ"*** ግሱ (BDB 645፤ KB 697) ኳል ትኩረት የሚሻ ነው፡፡ ይህ ጥቅስ ሁለት ትኩረት የሚሻ እና እንደ ትኩረት ሰጪ የሚያገለግል አንድ *Qal IMPERFECT(ያልተቋጨ )*ግስ አሉት (ማለትም፤ "መናወጥ" BDB 950፤ KB 1271)፡፡
"ጉልላት" የሚለው ቃል (BDB 499) የተጠረበውን የላይኛው ደጋፊ ህዳግ ያመለክታል፡፡

▣ ***"መድረኮቹ"*** ይህ "መድረኮቹ" (BDB 706) የሚለው ቃል የመቅደሱ በር የቆመበትን ጠንካራ ድጋፍ ያመለክታል (ዝ.ኪ. ኢሳ 6:4)፡፡

▣ ***"በራሳቸውም ሁሉ ላይ ሰባብራቸው"*** ይህ ልክ ሳምሶን በመሳ 16:23-30 ላይ የፍልስጤምን መቅደስ እንዳፈረሰው ሁሉ በመለኮታዊ ኃይል ምክንያት አምላኪዎችን መጥፋት የሚያመለክት ነው፡፡ እዚህ ላይ የማጥፊያው ዘዴ ከሰማያዊ አሰራር የታቀደ የመሬት መንቀጥቀጥ ይመስላል፡፡

▣ የቁ 1 የመጨረሻ ሦስት የጽሑፍ መስመሮች አጽኖት የሚሰጡት እስራኤላዊያኑ ከእግዚአብሔር ፍርድ በጭራሽ ማምለጥ እንደማይችሉ ነው (ዝ.ኪ. ከቁ 2-3)፡፡ከ 5፡19 ጋር የትርጉም ተመሳሳይነት አለው፡፡ የፍርድ ምንባቦችን ከምህረት ምንባቦች ጋር አጣምሮ መያዝ አንዱ የትንቢታዊ ስነ-ጽሑፍ ባህሪው ነው፡፡ ለዚህም ይህ ምዕራፍ ጥሩ ምሳሌ ነው፡፡

1. ከቁ 1-10፤ ፍርድ
2. ከቁ 11-15፤ ምህረት

ሁለቱም እውነት ናቸው፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ምህረት እና በሰው እምነት /ንስሃ መሰረት ብዙ ሁኔታዎች/አማራጮች አሉ፡፡ የአይሁድ ቅሪቶች የእግዚአብሔርን የማዳን አላማ ለመፈጸም ይኖራሉ!

**9:2-3** እነዚህ ጥቅሶች ከእግዚአብሔር ፍርድ ለማምለጥ የሚደረግን መፍጨርጨር ይገልጻሉ (ለምሳሌ፤ ኢዮብ 34:22፤ ኤር 23:24፤ ኢሳ 29:15)፡፡ የተጠቀሱት ዘይቤዎች ከመዝ 139:8፤ 9-12 (ብሎም ከምሳ 15:11) ጋር አንድ አይነት ናቸው፡፡

**9:2*"ወደ ሲኦል ቢወርዱ"*** *ሲኦል* (BDB 982፤ ለምሳሌ፤ ኢሳ 5:14፤ 14:9፤ 28:15፤18፤ 38:10) የሙታንን መኖሪያ ስፍራ ያሳያል፡፡ የተገለጸው ልክ መሬት ላይ እንዳለ ሆኖ ነው (ማለትም፤ ቢወርዱ)፡፡ ይህም በኢሳ 2:10፤19-21፤ ሉቃ 23:30፤ እና ራዕ 6:15-16 ላይ እንዳለው በዋሻ ውስጥ ለመደበቅ ከሚሞክሩት ሰዎች ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

## ልዩ ርዕስ፡ ሙታን የት ናቸው?

I. ብሉይ ኪዳን
   ሀ. ሁሉም ሰዎች ወደ ሲኦል ይወርዳሉ (ከሥርወ ቃል አኳያ ርግጠኛ ያልሆነ፣ BDB 1066)፣ እሱም ሞትን የሚያመለክት ወይም መቃብርን፣ ባብዛኛው በጥበብ ሥነ ጽሑፍ እና በኢሳይያስ። በብሉይ ኪዳን፣ ጥላማ፣ ንቁ፣ ነገር ግን ደስታ የሌለበት ሕላዌ ነበር (ኢዮብ 10፡21-22፤ 38፡17፤ መዝ 107፡10፤14)።
   ለ. ሲኦል በባሕርዩ
      1. ከእግዚአብሔር ፍርድ ጋር ይያያዛል (እሳት)፣ ዘዳ 32፡22
      2. ከፍርድ ቀን በፊት ካለው ቅጣት ጋር ይያያዛል፣ መዝ 18፡4-5
      3. ከአባዶን (ጥፋት) ጋር ይያያዛል፣ ነገር ግን ለእግዚአብሔር የታወቀ፣ ኢዮብ 26፡6፤ መዝ 139፡8፤ አሞጽ 9፡2
      4. ከ "ጉድጓድ" (ከመቃብር) ጋር ይያያዛል፣ መዝ 16፡10፤ ኢሳ 14፡15፤ ሕዝ 31፡15-17
      5. ከፉዎች ከነሕይወታቸው ወደ ሲኦል ይወርዳሉ፣ ዘኁ 16፡30፤33፤ መዝ 55፡15
      6. ዘወትር ሰውኛ የሚሆነው አፈ ሰፊ በሆነ እንስሳ ነው፣ ዘኁ 16፡30፤ ኢሳ 5፡14፤ 14፡9፤ ዕንባ 2፡5
      7. ሰዎች እዚያ ሪፋይም ተብለው ይጠራሉ፣ (ኢሳ 14፡9-11)

II. አዲስ ኪዳን
   ሀ. የዕብራይስጡ ሲኦል በግሪኩ ሀዳስ ነው የሚተረጎመው (ያልታየው ዓለም)
   ለ. ሃዳስ (ሲኦል) በባሕርዩ
      1. ሞትን ያመላክታል፣ ማቴ 16፡18
      2. ከሞት ጋር ይያያዛል፣ ራዕ 1፡18፤ 6፡8፤ 20፡13-14
      3. ዘወትር የሚመሰለው የቋሚ ቅጣት ስፍራ ነው (ገሃነም)፣ ማቴ 11፡23 (የብሉይ ኪዳን ጥቅስ)፤ ሉቃስ 10፡15፤ 16፡23-24
      4. ዘወትር የሚመሰለው ከመቃብር ጋር ነው፣ ሉቃስ 16፡23
   ሐ. ይከፋፈላል (ራቢዎች)
      1. የጻድቃኖች ክፍል ገነት ይባላል (በርግጥ የሰማይ ሌለኛው ስም፣ 2ኛ ቆሮ 12፡4፤ ራዕ 2፡7)፣ ሉቃስ 23፡43
      2. የክፉዎች ክፍል እንጦርጦስ ይባላል፣ 2ኛ ጴጥ 2፡4፤ እሱም ለክፉዎች መላእክት ማቆያ ስፍራ (ዘፍ 6፤ 1ኛ ሄኖክ)
   መ. ገሃነም
      1. የብሉይ ኪዳንን ሐረግ ያንጸባርቃል፣ "የሄኖም ልጆች ሸለቆ፣" (ከኢየሩሳሌም በስተደቡብ)። እሱም የፍንቄአውያን የእሳት ጣዖት፣ የሞሎክ አምልኮ የሚፈጸምበት (BDB 574)፣ የሕጻናት መሥዋዕት የሚቀርብበት ነበር፣ (2ኛ ነገሥ 16፡3፤ 21፡6፤ 2ኛ ዜና 28፡3፤ 33፡6)፣ እሱም በሌዋ 18፡21፤ 20፡2-5 የተከለከለው።
      2. ኤርምያስ እሱን ከጣዖት ማምለኪያነት ወደ ያህዌ የፍርድ ስፍራ ቀይሮታል (ኤር 7፡32፤ 19፡6-7)። እሱም የእሳት፣ የዘላለም ፍርድ ቦታ ሆኗል፣ 1ኛ ሄኖክ 90፡26-27 እና ሲብ 1፡103።

3. በኢየሱስ ጊዜ የነበሩት አይሁድ በአባቶቻቸው የሕጻናት መሥዋዕት ጣዖት አምልኮ በጣም ያፍሩ ስለነበር፣ ስፍራውን ለኢየሩሳሌም የቆሻሻ መጣያ ስፍራ አድርገውታል። አብዛኞቹ የኢየሱስ ዘይቤዎች፣ ስለ ዘላለማዊ ፍርድ የተገኙት ከዚህ ስፍራ (እሳት፣ ጭስ፣ ትሎች፣ ግማት፣ ነው፣ ማርቆስ 9፡44፤46)። ገሃነም የሚለው ቃል በኢየሱስ ብቻ ነው ጥቅም ላይ የዋለው (ከያዕቆብ 3፡6 በቀር)።
4. የኢየሱስ የገሃነም አጠቃቀም
   ሀ. እሳት፣ ማቴ 5፡22፤ 18፡9፤ ማርቆስ 9፡43
   ለ. ቋሚ፣ ማርቆስ 9፡48 (ማቲ 25፡46)
   ሐ. የጥፋት ስፍራ (የነፍስም የሥጋም)፣ ማቴ 10፡28
   መ. ከሲዖል ጋር ትይዩ ነው፣ ማቴ 5፡29-30፤ 18፡9
   ሠ. ክፉዎችን "የሲኦል ልጆች" በሚያስብል ባሕርይ፣ ማቴ 23፡15
   ረ. የፍርድ ውሳኔ ውጤት፣ ማቴ 23፡33፤ ሉቃስ 12፡5
   ሰ. የገሃነም ጽንሰ ሐሳብ የሁለተኛ ሞት ትይዩ ነው (ራዕ 2፡11፤ 20፡6፣14) ወይም የእሳት ባሕር (ማቴ 13፡42፣50፤ ራዕ 19፡20፤ 20፡10፣14-15፤ 21፡8)። እሱም ማለት የሚቻለው የእሳት ባሕር የሰዎች ቋሚ መኖርያ ስፍራ ተደርጎ ነው (ከሲዖል) እንዲሁም ክፉ መላእክት (ከእንጦርጦስ፣ 2ኛ ጴጥ 2፡4፤ ይሁዳ 6 ወይም ጥልቁ፣ ሉቃስ 8፡31)፤ ራዕ 9፡1-10፤ 20፡1፣3)።
   ሸ. ለሰዎች አልተሠራም ነበር፣ ነገር ግን ለሰይጣንና ለመላእክቱ፣ ማቴ 25፡41

ሠ. በሲዖል፣ በሀዳስ፣ እና በገሃነም መካከል መነባበር ስላለ ማለት የሚቻለው፣
1. በዋነኛነት ሁሉም ሰዎች ወደ ሲዖል/ሀዳስ ይወርዳሉ
2. እዚያም ያደረጉት ሥራ (መልካም ቢሆን ክፉ) ከፍርድ ቀን በኋላ ይብስባቸዋል፣ ነገር ግን የክፉዎች ስፍራ እንደዛው ይቀራል (በዚህን ምክንያት ነው ኪጀት ሃዳስን ሲተረጉም (መቃብር) ገሃነምን (ሲዖል) ያለው።
3. የአኪ ጽሑፍ ብቻ ነው ከፍርድ ቀን በፊት ያለው እሳት ምሳሌ መሆኑን የገለጠው፣ የሉቃስ 16፡19-31 (አልአዛርና ሃብታሙ ሰው)። ሲኦል ደግሞ እንደ አሁኑ ቅጣት ስፍራ ተገልጧል፣ (ዘዳ 32፡22፤ መዝ 18፡1-5)። ሆኖም፣ ማንም በምሳሌ ላይ መሠረተ እምነቱን አይጥልም።

III. በሞትና በትንሣኤ መካከል ያለ ማዕከላዊ ስፍራ
ሀ. አኪ "የነፍስን መዋቲነት" አያስተምርም፣ እሱም ከበርካታ ጥንታዊ የከሕይወት በኋላ አመለካከቶች አንዱ የሆነው።
1. የሰዎች ነፍሳት ከሥጋዊ አካል በፊት ነበር
2. የሰዎች ነፍሳት ከሥጋዊ ሞት በፊትም ሆነ በኋላ ዘላለማዊ ናቸው
3. ሥጋዊ አካል የሚታየው እንደ እስር ቤት ሲሆን፣ ሞት ደግሞ ወደ ቅድመ ተፈጥሮ ተፈትቶ መመለስ ነው

ለ. አኪ ከአካሉ ስለ ተለየ ሕይወት፣ በሞትና በትንሣኤ መካከል ስላለው ፍንጭ ይሰጣል
1. ኢየሱስ በሥጋና በነፍስ መካከል ስላለው ክፍል ተናግሯል፣ ማቴ 10፡28
2. አብርሃም አሁን ምናልባት አካል ሊኖረው ይችላል፣ ማርቆስ 12፡26-27፤ ሉቃስ 16፡23
3. ሙሴና ኤልያስ በመለወጥ ጊዜ ሥጋዊ አካል ነበራቸው፣ ማቲ 17
4. ጳውሎስ የሚለው በዳግም ምጽአት በኢየሱስ ያሉት ነፍሳት በመጀመሪያ አዲሱን አካላቸውን ይይዛሉ፣ 2ኛ ተሰ 4፡13-18
5. ጳውሎስ የሚለው አማኞች አዲሱን መንፈሳዊ አካል በትንሣኤ ቀን ያገኛሉ፣ 1ኛ ቆሮ 15፡23፣52
6. ጳውሎስ የሚለው አማኞች ወደ ሲዖል አይወርዱም ነው፣ ነገር ግን በሞት ከኢየሱስ ጋር ይሆናሉ፣ 2ኛ ቆሮ 5፡6፣8፤ ፊሊጵ 1፡23። ኢየሱስ ሞትን ድል ነሥቷል፣ እናም ጻድቁን ከእሱ ጋር ወደ ሰማይ ይወስደዋል፣ 1ኛ ጴጥ 3፡18-22።

IV. ሰማይ
ሀ. ይህ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ በሦስት መልኩ ጥቅም ላይ የሚውል ነው።
1. ከመሬት በላይ ያለው ከባቢ ዓየር፣ ዘፍ 1፡1፣8፤ ኢሳ 42፡5፤ 45፡18
2. ከዋክብታማ ሰማይ፣ ዘፍ 1፡14፤ ዘዳ 10፡14፤ መዝ 148፡4፤ ዕብ 4፡14፤ 7፡26
3. የእግዚአብሔር ዙፋን ስፍራ፣ ዘዳ 10፡14፤ 1ኛ ነገሥ 8፡27፤ መዝ 148፡4፤ ኤፌ 4፡10፤ ዕብ 9፡24 (ሦስተኛው ሰማይ፣ 2ኛ ቆሮ 12፡2)

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ከሕይወት በኋላ ብዙም አይገልጽ። ምናልባትም የወደቀው ሰው ነገሩን የመረዳት መንገዱም ሆነ አቅሙ ስለሌለው ይሆናል፣ (1ኛ ቆሮ 2፡9)።

ሐ. ሰማይ ስፍራም (ዮሐንስ 14፡2-3) እንዲሁም አካል ነው፣ (2ኛ ቆሮ 5፡6፣8)። ሰማይ ምናልባት የኤደን ገነት መመለስ ይሆናል፣ (ዘፍ 1-2፤ ራዕይ 21-22)። ምድር ትጸዳለች ትታደሳለችም (ሐዋ 3፡21፤ ሮሜ 8፡21፤ 2ኛ ጴጥ 3፡10)። የእግዚአብሔር አምሳል (ዘፍ 1፡26-27) በክርስቶስ ተመልሷል። አሁን የኤድን ገነት ወዳጃዊ ኅብረት ዳግም ተችሏል።
ሆኖም፣ ይህ ዘይቤአዊ ነው፣ (ሰማይ፣ እንደ ግዙፍ፣ ኩብ ከተማ የራዕይ 21፡9-27) እናም በጥሬ ቃሉ አይደለም። 1ኛ ቆሮንቶስ 15 የሚገልጸው የሥጋዊ አካልንና የመንፈሳዊ አካልን ልዩነት፣ እንደ ትልቅ ተክል ዘር አድርጎ ነው። ደግሞም 1ኛ ቆሮ 2፡9 (ከኢሳ 64፡4 እና 65፡17 የተጠቀሰ) ታላቅ ቃል ኪዳንና ተስፋ ነው! እሱን ስናየው እሱን እንደምንመስል አውቃለሁ፣ (1ኛ ዮሐንስ 3፡2)።

V. የመርጃ ምንጮች
ሀ. *William Hendriksen, The Bible On the Life Hereafter*
ለ. *Maurice Rawlings, Beyond Death's Door*

▣ **"ወደ ሰማይም ቢወጡ"** ይህ ሙሉ ለሙሉ የሲኦል ተቃራኒ ነው፡፡ የነዚህ ጥቅሶች አገላለጽ (ማለትም፤ ከቁ 1-4) በመዝ 139፡8 ያለውን ሁኔታ የሚያስታወስ ነው፡፡ከእግዚአብሔር የትም መደበቅ አይቻልም! በዚህ ጥቅስ ሰማይ ምናልባትም ከመሬት በላይ ያለውን ከባቢ አየር (ዝ.ከ. ዘፍ 1፡1፤14-19፤20) እንጂ የእግዚአብሔርን ዙፋን የሚያመለክት አይደለም (ምንም እንኳን ኢሳ 14፡12-14 በአንደኛ ሰማይ እና በሦስተኛ ሰማይ መካከል ያለውን የአይሁዶች ሃሳብ አንድ የሚያደርግ ቢመስልም)፡፡

**9:3 "በቀርሜሎስም ራስ ውስጥ ቢሸሸጉ"** ይህ ሥፍራ ምናልባት (1) በጣም ጥቅጥቅ እፅዋት (BDB 502 II) ከብዙ ዋሻዎች ጋር ያለው መሆኑን ወይም (2) የባህላዊ አምልኮ ስፍራ እንደ ነበር የሚያሳይ ጥምር ተምሳሌት ሊሆን ይችላል (ዝ.ከ. 1ኛ ነገ 18)፡፡

▣ **"በጥልቅ ባሕርም ውስጥ ከዓይኔ ቢደበቁ"** ይህ ኃጥያተኛው የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ለመደበቅ የሚያደርገውን ሙከራ የሚያሳይ ዘይቤ እንደሆነ ግልጽ ነው (ዝ.ከ. ኢዮብ 34:21-22፤ መዝ 139:9-12፤ ኤር 16:16-17)፡፡ እስራኤላዊያኑ የበረሃ ሕዝቦች ነበሩ፡፡ ሰፊና እና ጥልቅ ውሃን ይፈሩ ነበር፡፡ሊደበቁ የሚችሉበት የመጨረሻው ቦታ ጥልቁ ነው!

▣ **"እባቡን አዝዛለሁ፥ እርሱም ይነድፋቸዋል"** ይህ በተዘዋዋሪው የሚያወራው በአፈ ታሪክ ስለሚታወቀው ትልቅ የባህር አውሬ ሌዋታን (ዝ.ከ. ኢዮብ 3:8፤ 41:1፤ መዝ 74:13-14፤ 104:26፤ ኢሳ 27:1) ወይም ስለ ረዓብ (ዝ.ከ. ኢዮብ 9:13፤ 26:12፤ መዝ 89:10፤ ኢሳ 51:9) ነው፡፡ ሽብር የፈጠረውን አስፈሪ እባብ በእግዚአብሔር እንደ ታዘዘ (BDB 845፤ KB 1010፤ ፒል ያልተቋጨ) ያስተውሉ፡፡

**9:4** ይህ በጣም አስደንጋጭ ጥቅስ ነው፡፡የእግዚአብሔር ቁጣ እና ፍርድ በምርኮ ላይ ቢሆኑም ይከተላቸዋል፡፡ ልክ እንደ እንስሳት መንጋ ወደ ባዕድ አገር ይነዳሉ ነገር ግን እዚያም ቢሆን ሞት ይጠብቃቸዋል! እግዚአብሔር ምንም ርህራሔ አያሳይም (ዝ.ከ. ሆሴ 1:6፤ 2:4) ምክንያቱም ከእንግዲህ በኋላ የሱ የቃል ኪዳኑ ሕዝቦች አይደሉም (ዝ.ከ. ሆሴ 1:9፤ 2:23)፡፡ ይህ ጥቅስ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ባለመጠበቅ ምክንያት የሚመጣን ነገር ያንጸባርቃል (ዝ.ከ. ዘሌ 26፤ በዋናነት ቁ 33)፡፡

▣ **"ዓይኔንም በእነርሱ ላይ ለክፋት እንጂ ለመልካም አላደርግም"** ይህ ከቃል ኪዳኑ የተስፋ ቃል ጋር በትክክል ይቃረናል! ይህ ተመሳሳይ ዘይቤ እና ቃል ብዙ ጊዜ በኤርምያስ ውስጥ ተጠቅሷል (ዝ.ከ. 21:10፤ 39:16፤ 44:11፤27)፡፡ ይህ በዘሌዋውያን 26 እና በተለይም በዘዳግም 27-29 ውስጥ ያሉትን የእርግማን እና የባርኮት ክፍሎች ያንጸባርቃል፡፡ እግዚአብሔር ከተስፋይቷ ምድር ውጭ በሌሎች አማልክት ቁጥጥር እንደሆኑ በሚያስቡ ሕዝቦች ላይም የሚተገበሩ ትዕዛዞችን የማራመድ ስልጣን እንዳለው ያስተውሉ፡፡ እነዚህ ሌሎች አማልክቶች ከመታዘዝ ውጭ አማራጭ የላቸውም!

## አሞፅ: : 9:5-6

**[5] የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድርን ይዳስሳል እርስዋም ትቀልጣለች፥ የሚኖሩባትም ሁሉ ያለቅሳሉ ሙላዋም እንደ ግብጽ ወንዝ ትነሣለች፥ ደግሞ እንደ ግብጽ ወንዝ ትወርዳለች።[6] አዳራሹን በሰማይ የሠራ፥ ጠፈሩንም በምድር ላይ የመሠረተ፥ የባሕርንም ውኃ ጠርቶ በምድር ፊት ላይ የሚያፈስሰው እርሱ ነው ስሙም እግዚአብሔር ነው።**

**9:5-6** ይህ ያህዌ ስለ ፈጣሪነቱ ከቀረቡለት ሦስት ምስጋናዎች ፣ ውዳሴዎች ወይም ግጥሞች የመጨረሻው ነው (ዝ.ከ. 4:13 እና 5:8-9)፡፡

**9:5** ይህ ምናልባትም የምድር መናወጡ ሌላው ማጣቀሻ ሊሆን ይችላል፤ 1:1 ፣ 8:8-9 ፣ 9:1 (ማለትም፤ ምድሩ፣ እንደ አባይ ወንዝ ፣ መነሳት እና መውረድ)፡፡

▣ **"የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር"** ይህ መጠሪያ በ3:13፣4:13፣5:14፣16፣27፣6:8፣ 14 ላይ ይገኛል፡፡ ልዩ ርዕስ፡ በ1:2 ላይ የአማልክት ስሞች እና በ5:14 ላይ የተብራራ ማስታወሻን ይመልከቱ፡፡

**9:6** እነዚህ ለትርጉም አስቸጋሪ የሆኑ የመፍጠር ዘይቤዎች ናቸው፡፡እግዚአብሔር የሰማይ እና የምድር ፈጣሪ እንደሆነ ይናገራሉ (ዝ.ከ. ዘፍ 1 ፤ መዝ 104)፡፡ እሱ የሰማይ እና የምድር ውሃ አካላት፤ ሁሉቱንም ጨዋማ እና ንጹውን ተቆጣጣሪ ነው (ማለትም፤የተፈጥሮ ኃይል)፡፡ "ጠፈሩንም" (BDB 8) የሚለውን "እቃ ማከማቻ" ብሎ መተርጎም ይቻላል፤ እናም እንዲ ከሆነ ቁ 6ሀ የእግዚአብሔርን መቀመጫ ስፍራን እንዲሁም 6ለ የሰው ልጅን መቀመጫ ያመለክታል፤ ሁለቱም ግን በያህዌ የተፈጠሩ ናቸው (ዝ.ከ. ቁ 5ሀ፤ ቁ 6መ)፡፡

▣ **"ስሙም እግዚአብሔር ነው"** ልዩ ርዕስ ፡የአማልክት ስሞች በ1:2 ላይ ይመልከቱ፡፡

## አሞፅ: : 9:7-10

**[7] የእስራኤል ልጆች ሆይ፥ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን? ይላል እግዚአብሔር፦ እስራኤልን ከግብጽ ምድር፥ ፍልስጥኤማውያንንም ከከፍቶር፥ ሶርያውያንንም ከቂር አላወጣሁምን?[8] እነሆ፥ የጌታ የእግዚአብሔር ዓይኖች በኃጢአተኛ መንግሥት ላይ ናቸው፥ ከምድርም ፊት አጠፋታለሁ ነገር ግን የያዕቆብን ቤት ፈጽሜ አላጠፋም፥ ይላል እግዚአብሔር፦[9]እነሆ፥ አዝዛለሁ፥ እህልም በወንፊት እንዲነፋ የእስራኤልን ቤት በአሕዛብ ሁሉ መካከል እነፋለሁ ነገር ግን አንዲት ቅንጣት በምድር ላይ አትወድቅም። [10] ክፉው ነገር አይደርስብንም፥ አያገኘንምም የሚሉ የሕዝቤ ኃጢአተኞች ሁሉ በሰይፍ ይሞታሉ።**

**9:7-8** የተመቅህ፤ በሰማዕ የተርጓሚዎች የመመምሪያ መጽሐፍ ላይ በቁ 7 እና 8 መካከል ያለውን ዝምድና ማራኪ በሆነ አመለካከት አሳይቷል፡፡ ቁጥር 7 እስራኤል የተሻለች ፣ ልዩ እና ቅድሚያ የሚሰጣት እንዳልሆነች ይገልጻል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ቁ 8 እግዚአብሔር ለእሷ ያለውን ልዩ የቃል ኪዳን ጥበቃ ያሳያል (ዝ.ከ. ገፅ 181)፡፡ ይህ ተመሳሳይ ውጥረት በአዲስ ኪዳን ውስጥም ይገኛል፡፡

## ልዩ ርዕስ ፡ "ወጥረቶች"(በራዕይ ከተሰራው የኔ ሃተታ ላይ አስፈላጊ መግቢያ ጥራዝ 12 የተወሰደ)

**የመጀመሪያው ውጥረት** (ብሉይ ኪዳን የዘር፣የሃገራዊ እና የስነ ምድራዊ ምድቦች ከዓለም ላይ ከሚገኙ አማኞች ሁሉ ጋር)

ሁሉም ብሉይ ኪዳን ነብያት በፍልስጤም ወስጥ ኢየሩሳሌምን ማዕከል ያደረገ የአይሁዳዊ አገዛዝ እንደገና እንደሚመለስ እና የምድር ሕዝቦች የዳዊታዊ ስርዓት ገዢን ለማወደስ እና ለማገልገል ወደዚህ እንደሚሰበሰቡ ተንብየዋል፤ ነገር ግን ኢየሱስም ሆነ የአዲስ ኪዳን ሐዋሪያት በጭራሽ በዚህ ጉዳይ ላይ አላተኮሩም፡፡ ብሉይ ኪዳን አገላለጽ በመንፈስ አልተመራም (ዝ.ከ. ማቴ 5:17-19) ማለት ነው? ወይስ የአዲስ ኪዳን ጸሐፍቱ የፍጻሜውን ዋንኛ እውነቶች ዘሏቸዋል?

ስለ አለም ፍጻሜ የሚያወሱ አያሌ ምንጮች አሉ ፤

1. ብሉይ ኪዳን ነብያት (ኢሳያስ፣ሚክያስ፣ሚልክያስ)
2. ብሉይ ኪዳን የምጽአት ቀን ጸሐፍት (ዝ.ከ. ሕዝቄል 37-39፤ ዳንኤል 7-12፤ ዘካሪያስ)
3. የማጣቀሻዎች ፣ ቅዱሳዊ አጻጻፍ ያልሆኑ የአይሁድ የምጽዓት ቀን ጸሐፍት (እንደ 1ኛ ኢኖች ስለ አይሁድ የጻፈው)
4. ኢየሱስ ራሱ (ዝ.ከ. ማቴዎስ 24፤ ማርቆስ 13፤ ሉቃ 21)
5. የጳውሎስ ጽሑፎች (ዝ.ከ 1ኛ ቆሮንጦስ 15፤ 2ኛ ቆሮንጦስ 5፤ 1ኛተሰሎንቄ 4-5፤ 2ኛተሰሎንቄ 2)
6. የዮሐንስ ጽሑፎች (1 ዮሐ እና ራዕይ) ፡፡

እነዚህ በሙሉ ስለ ፍጻሜ ሃሳብ በግልጽ ያስተምራሉ(ክስተቶች፣ቅደም ተከተል ሰዎች)? ካልሆነ ለምን? በመንፈስ የተመሩ አይደሉም (ከአይሁዳዊያን ዘመን ኪዳን ጽሑፎች በስተቀር)?

በቃላት እና በምድብ ይረዱት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እውነቱን ለብሉ ኪዳን ጸሓፍት ገልጾላቸዋል፡፡ ሆኖም መንፈስ ቅዱስ እነዚህን ብሉይ ኪዳን መገለጦች የአለም መጨረሻ ሃሳብን እስኪያጠቃልል ድረስ አስፍቶታል ("የክርስቶስ ሚስጥር" ዝ.ከ. ኤፌ 2:11-3:13)፡፡

የሚከተሉት ተጨባጭ ምሳሌዎች ፣ መረጃዎች እንመልከት፤

1. በብሉ ኪዳን ውስጥ የኢየሩሳሌም ከተማ የእግዚአብሔርን ሕዝቦች (ፅዮን) የሚያመለክት ዘይቤ ሆና ተጠቅሳለች፤ ነገር ግን በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔርን አምኖ ንስሃ የሚገቡትን ሰዎች ሁሉ እንደሚቀበል የሚያሳይ አቀራረብ አለው(የራዕይ አዲስቷ ኢየሩሳሌም)፡፡ የስነ መለኮታዊ አስተምዕሮት ጽሑፋዊ እና አካላዊ የነበረችው ከተማ ወደ አዲሷ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከተማ መስፋት (የአይሁድ እና የፈሪሳዊያን አማኞች) ምንም አይሁዳዊያን እና የአይሁድ ከተማ ሳይኖር በፊት እግዚአብሔር የወደቀውን የሰው ዘር ለመቤዥት የገባው የተስፋ ቃል መሆኑ በዘፍ 3:15 ውስጥ ተገልጾ ይገኛል፡፡ የአብርሃም መጠራት እንኳን (ዝ.ከ. ዘፍ 12:1-3) ፈሪሳዊያንን አሳትፎ ነበር (ዝ.ከ. ዘፍ 12:3፤ ዘጸ 19:5)፡፡
2. በብሉ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች የነበሩት የአካባቢው ጥንታዊ የቅርብ ምስራቅ አገሮች ነበሩ ፤ ነገር ግን በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች የማያምኑ ፣ በሰይጣናዊ መንፈስ የሚመሩ እና ጸረ እግዚአብሔር ወደ ሆኑ ሰዎች እየሰፋ መጥቷል፡፡፡፡ጦርነቱ ከአካባቢው ፣ክልላዊ ግጭት ወደ አለም አቀፋዊ እና ፈላካዊ ግጭት ተሸጋግሯል (ዝ.ከ. ቆላሲያስ)፡፡
3. በብሉ ኪዳን ተመጥኖ የነበረው የምድሪቱ ተስፋ ቃል (የዘፍጥረት ፓትሪያርካዊ ቃል ኪዳኖች ዝ.ከ. ዘፍ 12:7፤ 13:15፤ 15:7-15፤ 17:8) አሁን ወደ መላዋ ምድር ሰፍቷል፡፡ አሁን አዲሲቷ ኢየሩሳሌም የቅርብ ምስራቋ ብቻ ወይም የተወሰነች ሳትሆን አዲስ እንደገና የተፈጠረች ምድር ሆናለች (ዝ.ከ. ራዕ 21-22)፡፡
4. እየሰፉ ከመጡ የብሉይ ኪዳን ትንቢታዊ ሃሳቦች መካከል የተወሰኑ ምሳሌዎች የሚሆኑት፡- (1) አሁን የአብርሃም ዘር መንፈሳዊሳዊ ነገሩ ተገርዟል (ዝ.ከ. ሮሜ 2:28-29) ፣ (2) አሁን የቃል ኪዳኑ ሕዝብ አሕዛብንም አካቷል (ዝ.ከ. ሆሴ 1:10፤ 2:23፤ በሮሜ 9:24-26 ተጠቅሷል በተጨማሪም ዘሌ 26:12፤ ዘጸ 29:45፤ በ2ኛ ቆሮ 6:16- 18 ተጠቅሷል እንዲሁም ዘጸ 19:5፤ ዘዳ 14:2፤ በቲቶ 2:14 ተጠቅሷል) (3) አሁን መቅደሱ ኢየሱስ ነው ፤ እናም በእርሱ በኩል የአካባቢው ቤተክርስቲያን (ዝ.ከ. 1ኛ ቆሮ 3:16) ወይም አማኙ ግለሰብ (ዝ.ከ. 1ኛ ቆሮ 6:19) ፤ እና (4) አሁን በብሉ ኪዳን ሃረጋት የተገለጸችው እስራኤል እና የእርሷ ባህሪያት በአጠቃላይ የሚያመለክቱት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ነው ናቸው (ማለትም፤ "እስራኤል" ዝ.ከ. ሮሜ 9:6፤ ገላ 6:16 ፤ "የካህናት መንግሥት" ዝ.ከ. 1ጴጥ 2:5፤ 9-10፤ ራዕ 1:6)

የትንቢታዊ አርዓያ ተፈጽሟል፣ተስፋፍቷል፣ እንዲሁም አሁን የበለጠ ሁሉንም የሚያካትት ሆኗል፡፡ ኢየሱስ እና የሐዋሪያት ጸሓፍት ስለ መጨረሻው ዘመን እንደ ብሉ ኪዳን ነብያት አስመስለው አላቀረቡም (ዝ.ከ. ማርቲን ዋይንጋርደን፤ *የወደፊቱ መንግስት ትንቢት ሕና ሕፈጻጸም*)፡፡

በብሉ ኪዳን ያለውን ስነ ጽሑፋዊ አረዓያ ወይም ቅርጽ የሚወስዱ ዘመናዊው ተርጓሚዎች ራዕይን የበለጠ የአይሁዳዊያንን መጽሐፍ የሚገልጽ እና የኢየሱስን እንዲሁም የጳውሎስን ሃረጋት አቶማይዝድ ፣ ግራ የሚያጋባ እንዲሆኑ በማድረግ ጠምዝዘውታል!

የአዲስ ኪዳን ጸሓፍት የብሉ ኪዳንን ነብያት ሃሳብ ታላቅ እና አለማቀፋዊ ክስቶችን አመላካች እንደሆኑ ያገልጻሉ እንጂ የሚቃረኑ አይደሉም፡፡የኢየሱስ ወይም የጳውሎስ የመጨረሻው ዘመን ሃተታዎች ምንም የተቀናጀ እና ሊሆኑ የሚችል ስርዓት አያስፈልጋቸውም፡፡ ዋነኛ አላማቸው መቤዠት እና ወይም መንፈሳዊ ትምህርት ነው፡፡

ሆኖም ግን በአዲስ ኪዳንም ውስጥም ቢሆን ውጥረት አለ፡፡ ስለ መጨረሻው ዘመን ሁኔታዎች ምንም አይነት የቅድመ ሁኔታወች ስርዓት የለም፡፡ ራዕይ በብዙ መንገድ ኢየሱስ ስለ መጨረሻው ዘመን ሲገልጽ ካስተማራቸው ትምህርት ይልቅ የብሉ ኪዳንን ተምሳሌቶች መጠቀሙ የሚያስገርም (ዝ.ከ. ማቴዎስ 24፤ ማርቆስ 13)! በሕዝቄል፣ ዳንኤል እና በዘካሪያስ የተጀመረውን የስነ ጽሑፍ ዘውግ ይከተላል፤ ነገር ግን በኪዳናዊ ዘመን ወቅት እያደገ መጥቷል (የአይሁድ የዘመን ፍጻሜ ስነ ጽሑፍ)፡፡

ይህ ምናልባትም ዮሐንስ አሮጌውን እና አዲሱን ቃል ኪዳኖች አንድ ያደረገበት መንገድ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ረጅም እድሜ ያለውን የሰው አመጻን እና የእግዚአብሔርን የማዳን ቁርጠኝነት ያሳያል! ምንም እንኳን አዲስ ኪዳን የብሉ ኪዳንን ቋንቋ ፣ ሰዎች እና ክስተቶች ቢጠቀምም ሁኔታዎቹን መልሶ የሚገልጸው ግን በሮም የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን እይታ ነው፡፡

**ሁለተኛው ውጥረት** (አንድ አምላክ ማመን ከ ተመረጡ ሕዝቦች ጋር)

የመጽሐፍ ቅዱሳዊው ትኩረት አንድ ማንነት ፣ መንፈሳዊነት ፣ ፈጣሪነት-ተቤዢነት ባለው እግዚአብሔር ላይ ነው (ዝ.ከ. ዘጸ 8:10፤ ኢሳ 44:24፤ 45:5-7፤14፤18፤21-22፤ 46:9፤ ኤር 10:6-7)፡፡ ብሉ ኪዳንን ልዩ የሚያደርገው በዘመኑ ስለ አንድ አምላክ መግለጹ ነው፡፡ በአካባቢው የነበሩት መንግስታት በሙሉ በብዙ አምላክት የሚያምኑ ነበሩ፡፡ ብሉይ ኪዳን መገለጥ የሚያሳየው እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ ነው((ዝ.ከ. ዘዳ 6:4)፡፡

ፍጥረት በእግዚአብሔር እና በራሱ መልክ እና ምሳሌ (ዝ.ከ. ዘፍ 1:26-27) በተፈጠረው ሰው መካከል ለታለመው ህብረት አንዱ ደረጃ ነው። ሆኖም ግን ሰው በእግዚአብሔር ፍቅር ፣ አመራር እና እቅድ ላይ ኃጥያት በመስራት አመጸ (ዝ.ከ. ዘፍ 3)። የእግዚአብሔር ፍቅር እና እቅድ በጣም ጠንካራ እና እውነት ከመሆኖ የተነሳ እግዚአብሔር የወደቀውን የሰው ዘር እንደሚቤዥ ቃል ገብቷል(ዝ.ከ. ዘፍ 3:15)!

ውጥረቱ የተባባሰው እግዚአብሔር የተቀረውን የሰው ዘር ለመድረስ አንድ ሰው ፣ አንድ ቤተሰብ ፣ አንድ ሕዝብን በመረጠበት ጊዜ ነው። የእግዚአብሔር አብርሃምን እና አይሁዶችን እንደ ካህናት መንግሥት(ዝ.ከ. ዘጸ 19:4-6) መምረጥ ከአገልግሎት ይልቅ ክብርን ፣ ከማካተት ይልቅ አለማካተትን አስከትሏል። እግዚአብሔር ለአብርሃም ያደረገው ጥሪ ሁሉንም የሰው ዘር ለመባረክ አቅዶ ነው (ዝ.ከ. ዘፍ 12:3)። ብሉይ ኪዳን ኪዳን ምርጫ የነበረው ለአገልግሎት እንጂ ለነጻነት እንዳልሆነ መታወስ እን ትኩረት የሚሰጠው መሆን አለበት። አጠቃላይ እስራኤላዊያን በግል እምነታቸው እና መታዘዛቸወው (ዝ.ከ. ዘፍ 15:6፤ በሮሜ 4 ውስጥ ተጠቅሷል) እንጂ ከእግዚአብሔር ጋር ስለ ሚስተካከሉ ፣ ዝም ብሎ በመወለድ መብታቸው ብቻ ፈጽሞ ለዘላለም የሚድኑ አይደሉም (ዝ.ከ. ዮሐ 8:31-59፤ ማቴ 3:9)። እስራኤል ተልዕኮዋን ስታለች፤ ኃላፊነቷን ወደ ጥቅም ፣ አገልግሎቷን ወደ ልዩ አቋም ለውጣለች! እግዚአብሔር ሁሉኑም ለመምረጥ አንድ መርጧል!

***ሦስተኛው ውጥረት*** ( በሁኔታዎች የሚወሰን ቃል ኪዳኖች conditional በሁኔታዎች ከማይወሰኑ unconditional ቃል ኪዳኖች ጋር)

በቅድመ ሁኔታ ባላቸው እና በሌላቸው ቃል ኪዳኖች መካከል በመንፈሳዊ ትምህርት ውጥረት ወይም የሚጋጭ አባባል አለ። የእግዚአብሔር የመቤዠት እቅድ/አላማ ቅድመ ሁኔታ የሌለው እንደሆነ እርግጥ ነው (ዝ.ከ. ዘፍ 15:12-21)። ሆኖም ግን ሰው ለተሰጠው ኃላፊነት ምላሹ ሁል ጊዜ ቅድመ ሁኔታ ያለው ነው!

በሁለቱም ብሉ ኪዳን እና አዲስ ኪዳን ውስጥ "እንዲህ ከሆነ...እንዲህ ይሆናል" አይነት አጻጻፍ ይታያል።እግዚአብሔር ታማኝ ነው ፤ የሰው ዘር ግን ታማኝ አይደለም። ይህ ውጥረት ብዙ ግራ መጋባቶችን አምጥቷል።ተርጓሚዎች  ከ "ከግራ መጋባቱ እምብርት" ወደ አንዱ ላይ ብቻ ትኩረት በማድረግ አዘንብለዋል ፤ የእግዚአብሔር ታማኝነት ወይም የሰው ጥረት ፣ የእግዚአብሔር የበላይነት ወይም የሰው ነጻ መሻት። ሁለቱም መጽሐፍ ቅዱሳዊ እና አስፈላጊ ናቸው።

ይህ እስከ መጨረሻው ዘመን እግዚአብሔር በብሉ ኪዳን ውስጥ ለእስራኤል ከሰጠው የተስፋ ቃል ጋር ይዛመዳል። እግዚአብሔር ይህን ተስፋ ቃል ከሰጠ ፤ እንዲፈጸም ያደርጋል ትክክል ነው? እግዚአብሔር ከተስፋ ቃሎቹ ጋር የተቆራኘ ነው ፤ ዝናውም አብሮት ይሄዳል (ዝ.ከ. ሕዝ 36:22-38)። ቅድመ ሁኔታ ላቸው እና የሌላቸው ቃል ኪዳኖች በክርስቶስ አንድ ይሆናሉ(ዝ.ከ. ኢሳ 53) እንጂ በእስራኤል አይደለም! የእግዚአብሔር ታላቅ ታማኝነት ንስሃ በሚገቡት እና በሚያምኑ ሁሉ ላይ የሚያደርገው ተቤዥነት ነው እንጂ አባቱ/እናቱ ማነው በሚለው አይደለም! ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን እና የተስፋ ቃሎች ቁልፍ ክርስቶስ እነጂ እስራኤል አይደለችም። በመንፈሳዊ ትምህርት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከዋናው ሃሳብ ተነጥሎ የሚታ ነገር ካለ ይህ ቤተክርስቲያን ሳይሆን እስራኤል ነው (ዝ.ከ. የሐዋ 7 እና ገላ 3)።

የአለም ወንጌል እወጃ ተልዕኮ ወደ ቤተክርስቲያን ተላልፏል(ዝ.ከ. ማቴ 28:19-20፤ ሉቃ 24:47 ፤ የሐዋ 1:8)። ይህ እስከ አሁን ቅድመ ሁኔታ ያለው ቃል ኪዳን ነው! ይህ ማለት እግዚአብሔር ሙሉ ለሙሉ አይሁዶችን ትቷቸዋል ማለት አይደለም (ዝ.ከ. ሮሜ 9-11)። በመጨረሻው-ጊዜ እስራኤልን ማመን ቦታ እና አላማ ሊኖረው ይችላል የሚችል (ዝ.ከ. ዘካ 12:10)።

***አራተኛው ወጥረት***(የቅርብ ምስረቅ የስነ ጽሑፍ ቅርጾች ከ ምዕራባዊያን ቅርጾች ጋር)

መጽሐፍ ቅዱስን በትክክል ለመተርጎም ስነ ጽሑፋዊ ስልቱ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። ቤተክርስቲያን እድገቷ በምዕራባዊያን (ግሪክ) ባህል መሰረት ነበር።የምስራቅ ስነ ጽሑፍ ከምዕራባዊያን ዘመናዊ የስነ ጽሑፍ ቅርጾች አጻጻፍ የበለጠ በጣም ገላጭ ፣ ዘይቤያዊ እና ምልክታዊ ነው። ከማህበረሰባዊ ታሳቢ እውነታዎች የበለጠ በሰዎች ፣ በገጠመኞች እና በክስተቶች ላይ ያተኩራል። ክርስቲያኖች የራሳቸውን ታሪክ እና የስነ ጽሑፍ ቅርጽ በመውሰድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢቶችን (በሁለቱም ብሉ ኪዳን እና አዲስኪዳን) ለመተርጎም መጠቀማቸው ጥፋተኛ ሲያደርጋቸው ቆይተዋል።እያንዳንዱ ትውልድ እና የስነ ምድር አካል ራእይን ለመተርጎም የራሱን ባህል ፣ ታሪክ እና አንኳር ነገር ተጠቅመዋል። ከእነሱ መሃል አንዱም ትክክል አልነበረም! መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢት በምዕራባዊያን ዘመነዊ ባህል ላይ ያተኮረ ነው ብሎ ማሰብ ስህተት ነው! ዋናው ፤ በመንፈስ የተመራው ጸሐፊ ለመጻፍ የመረጠው ስነ ጽሑፋዊ ስልት ከአንባቢው ሁኔታ ጋር በሚስማማ መልኩ ነው።

የራዕይ መጽሐፍ ታሪካዊ ትረካ አይደልም። መጽሐፉ የመልዕክት (ከምዕራፍ 1-3) ፣ የትንቢት እና በዋናነት ደግሞ የምጽዓት ቀን ስነ ጽሑፍ ቅልቅል ነው። መጽሐፍ ቅዱስን በዋናው ጸሐፊ ከታቀደው በላይ እንዲናገር ማድረግም ሆነ ጸሐፊ ካስቀመጠው በታችም እንዲሆን ማድረግ ስህተት ነው! የተርጓሚዎች እብሪት እና ቀኖናዊነት እንደ ራዕይ ባሉ መጽሐፎች ላይ የበለጠ አግባብነት ይጎለዋል። ቤተክርስቲያን በትክክለኛ አተረጓገም ተስማምታ አታውቅም። የእኔ ዋና ነጥብ መጽሐፍ ቅዱስን በከፊል ሳይሆን በሙሉ መስማት እና ማጥናት ላይ ነው። በምስራቃዊያን አስተሳሰብ መጽሐፍ ቅዱስ እውነትን ከውጥረት ጋር አጣምሮ ይዟል። እኛ ምዕራባዊያን በታሳቢ እውነት ላይ ያለን ልምድ ዋጋ ቢስ አይደለም፤ ነገር ግን የተመጣጠነ አይደለም! የእኔ አስተሳሰብ ራዕይ ሲተረጎም ለሚቀጥለው አማኝ ትውልድ ቢያንስ አስቻሪ ነገሮቹ የሚለወጡበትን አላማ ማስታወሻ በመስጠት ማስወገድ ይቻላል። ለአብዛኞቹ ተርጓሚዎች ራዕይ በራሱ የጊዜ አቀራረብ እና በራሱ የስነ ጽሑፍ ስልት መተርጎም እንዳለበት ግልጽ ነው። በራዕይ ላይ ታሪካዊ አቀራራብ ሲጻፍ የመጀመሪያ አንባቢዎች ምን ያውቁ እንደነበር ፣ ምን እንደሚያውቁ እና ምን እንደሚረዱ የሚያገናዝብ መሆን አለበት። በብዙ መንገዶች ዘመናዊ ተርጓሚዎች የመጽሐፉ ብዙ ምልክቶች ትርጉም ጠፍቷቸዋል። የራዕይ ዋና መነሻ ሃሳብ በስቃይ ላይ ያሉትን አማኞች ለማበረታታት ነበር። መጽሐፉ እግዚአብሔር ታሪክን እንደሚቆጣጠር አሳይቷል (ብሉይ ኪዳን ነብያት እንዳደረጉት)፤ ታሪክ ወደ ታለመለት የፍጻሜ ስፍራ እየሄደ እንደሆነ አረጋግጧል፤ ወደ ፍርድ ወይም ወደ በረከት(ብሉይ ኪዳን ነብያት እንዳደረጉት)። መጽሐፉ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን በአይሁዶች የምጽዓት ቀን ቃላት የእግዚአብሔርን ፍቅር ፣ ክብር ፣ ኃይል እና የበላይነት አረጋግጧል!

መጽሐፉ በእነዚ ተመሳሳይ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ዘዴዎች ለሁሉም አማኝ ትውልዶች ማገልገል አለበት።የበጎነትን እና የክፋትን ፈለካዊ ትግል ያስረዳል። የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ዝርዝር ሁኔታ ጠፍቶን ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ኃይለኞቹ እና ነጻ አውጪዎቹ እውነታዎች አይጠፉንም።  የምዕራባዊያኑ ዘመናዊ ተርጓሚዎች የራዕይን ዝርዝር ወደ ራሳቸው ታሪካዊ ሁኔታ ሲመሩት የአተረጓገሙ የተሳሳተ መልክ እየቀጠለ ይሄዳል!

የመጨረሻዎቹ አማኝ ትውልዶች የእግዚአብሔር ጠላት በሆነው መሪ (ዝ.ከ. 2ኛተሰሎንቄ 2) እና ባህል ምክንያት ስለሚሸበሩ የመጽሐፉን ዝርዝር ሁኔታ ስሜት በሚሰጥ መልኩ እንደገና ቀጥተኛ እንዲሆን ማድረግ ያቻላል (ልክ ብሉ ኪዳን ከክርስቶስ መወለድ፣ሕይወት፣ እና ሞት ጋር በተያያዘ እንዳደረገው)። የኢየሱስ ቃላት ታሪካዊ መረጃ እስከሆኑ ድረስ (ዝ.ከ. ማቴዎስ 24፤ ማርቆስ 13፤ እና ሉቃ 21) ስለ ራዕይ ጽሑፎች አፈጻጸም ማንም ሊያውቅ አይችልም። ግምታዊ መሆን ፣ በመረጃ አለመደገፍ እና ቀና አለመሆን ሁሉም አግባብ አይደሉም። የምጽዓት ቀን ስነ

ጽሑፍ ይህን ነጻነት ይፈቅዳል፡፡ ታሪካዊ ትረካዎችን ለሚልቁ ምስሎች እና ምልክቶች እግዚአብሔር ይመስገን! እግዚአብሔር ሁሉንም ተቆጣጥሯል ፣ ይነግሳል ፣ ይመጣልም!

አብዛኞቹ ዘመናዊ ሃተታ አቅራቢዎች ይህን የስነ ጽሑፉን ስልት ነጥብ ይስታሉ! ዘመናዊ የምዕራባዊያን ተርጓሚዎች የሚያሻማውን ፣ በምልክት የቀረበውን የአይሁዶች የምጽዓት ቀን ስነ ጽሑፋዊ ስልትን በአግባቡ ከመተንተን ይልቅ ግልጽ ፣ የሚቀል የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ስርዓትን ይፈልጋሉ፡፡

በኤል ሆዋርድ ማርሻል በተስተካከለው የራልፍ ፒ ማርቲን *የአዲስ ኪዳን አተረጓጎም* በሚለው መጽሐፍ ውስጥ "ለአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሃተታ አቀራረብ" በሚለው ጽሑፍ ላይ ይህ እውነት በደንብ ተገልጿል፤

"የዚህን ጽሁፍ ማራኪ የአቀራረብ ብቃትን ካልተረዳን እና ሃይማኖታዊ እውነታን ለመግለጽ የተጠቀመበትን የቋንቋ አቀራረብ እንደ ዋና መንገድ አድርገን ካልወሰድን በስተቀር ስለ ምጽዓት ቀን የሚኖረን መረዳት በአሳዛኝ ስህተት የሚሞላ ይሆናል ፤ እንዲሁም በውስጡ ያሉትን ራዕዮች ለመተርጎም ስንሞክር ልክ እንደ ስድ ንባብ መጽሐፍ የመቁጠር እና ተግባራዊ የሆኑትን እንዲሁም ጊዜውን በሚገልጹ ታሪካዊ ክስተቶች ላይ ብቻ የማተኮር ስህተት እንሰራለን፡፡ ቀደም ብሎ የተጠቀሰውን ሁኔታ መሞከር በአተረጓጎም ላይ ሁሉንም ሁኔታዎች ያካተተ ችግሮችን ያስከትላል፡፡የበለጠ በትኩረት ስናየው ይህ ስለ ምጽዓት ቀን የሚሰጠውን አስፈላጊ ትርጉም የሚያዘባ እና በአዲስ ኪዳን ክፍል በአስደናቂ ታሪካዊ ቋንቋ የተገለጸውን በክርስቶስ በኩል የሚመጣው የእግዚአብሔርን ዙፋን እንዲሁም በአገዛዙ ላይ ያሉትን የብርታት እና የፍቅር ሃሳቦች የሚያጋጭ ሁኔታ የሚፈጥር ይሆናል (ዝ.ከ. 5:5፤6፤ አንበሳው በጉ ነው)"(ገፅ 235)፡፡

ደብሊው ራንዶልፍ ታት (W Randolph Tate) *መጽሐፍ ቅድሳዊ አተረጓጎም* በሚለው መጽሐፉ ላይ እንደጠቀሰው፡ "በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳለው የምጽዓት ቀን ጽሑፍ ልብ የሚነካ እና ሃዘን የሚጭር ሌላ የስነ ጽሑፍ ስልት የለም ፤ በዋናነት የዳንኤል እና የራዕይ መጽሐፎች፡፡ ይህ ስነጽሑፋዊ ስልት የስነ ጽሑፋዊ መልኩን ፣ ይዘቱን እና አላማውን የያዙ አስፈላጊ ክፍሎች ባለመረዳት ምክንያት በታሪክ ውስጥ በጣም የሚያሳስቱ አጥፊ አተረጓጎሞች ደርሰውበታል፡፡ የምጽዓት ጊዜ ስነ ጽሑፋዊ ስልት ከጊዜ በኋላ ምን እንደሚሆን የሚናገር በመሆኑ ምክንያት ስለ ወደፊቱ ሁኔታ እንደ መመሪያ እና ንድፍ ሆኖ ሲታይ ቆይቷል፡፡ በዚህ እይታ ውስጥ ያለው አሳዛኝ ችግር የመጽሐፉ መመዘኛዎች ከጸሓፊዊ ይልቅ በአንባቢው የዛሬው ሁኔታ ላይ መመስረታቸው ነው፡፡ ይህ የተሳሳተ አመለካከት (በዋናነት ራዕይ ላይ) ይህን ጽሑፍ ሚስጥራዊ ትርጉም እንዳለው በማሳብ የጽሑፉን ምልክቶች ለመተርጎም የዛሬውን ሁኔታዎች መጠቀም እንዲቻል መንገድ ይከፍታል፡፡

" በመጀመሪያ ተርጓሚው የምጽዓት ቀን ስነጽሑፋዊ ስልት መልዕክቶቹን ለማስተላለፍ ምልክቶችን እንደሚጠቀም ማወቅ አለበት፡፡ ዘይቤያዊ ሆኖ ሳለ አንድ ምልክትን በቀጥታ መተርጎም በቀላሉ ወደ ተሳሳተ አተረጓጎም የሚያመራ ነው፡፡ ጉዳዩ በምጽዓት ቀን ስነ ጽሑፋዊ ስልት ውስጥ ያሉ ክስተቶች ታሪካዊ መሆን አለመሆናቸው አይደለም፡፡ ክስተቶቹ ታሪካዊ ሊሆኑ ይችላሉ ፣ በትክክልም ተከስተው ሊሆን ይችላል ወይም የሚከሰቱ ይሆናል፤ ነገር ግን ጸሐፊው ክስተቶችን የሚያቀርበው እና ትርጉሙን የሚያስተላልፈው በምስሎች እና በታሪካዊ ቅርጾች በኩል ነው" (ገፅ 137)፡፡

በሪኬን ፣ ዊልሆስት እና በሎንድማን 3ኛ ከተስተካከለው የመጽሐፍ ቅዱሳዊ Dictionary of Biblical Imagery፤

"የዛሬው አንባቢያን በዚህ ስነ ጽሑፋዊ ስልት ግራ ተጋብተዋል እንዲሁም ተስፋ ቆርጠዋል፡፡የማይጠበቀው አእምሮዋዊ ምስል እና ከዚህ አለም ወጣ ባለው የአገላለጽ ልምዳቸው ብዙዎቹን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች ግራ የሆኑ እና ያልተቀናጁ ያስመስላቸዋል፡፡ የዚህን ስነ ጽሑፍ በግልጽ የሚታውን ቁምነገር ብቻ መውሰድ ብዙዎቹን አንባቢያን በፍጥነት 'ቀጥሎ ምን ይሆናል' ወደ ሚለው ውሳኔ ያስኬዳቸዋል፤ይህ ደግሞ የምጽዓት ቀን መልዕክቱን ዋና ጭብጥ ያስታቸዋል"(ገፅ 35)

**አምስተኛው ውጥረት** (የእግዚአብሔር መንግስት አንደ ዛሬም አንደ ነገም)

የእግዚአብሔር መንግስት የዛሬም እንዲሁም የወደፊትም ነው፡፡ ይህ የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት የሚጋጭ ሃሳብ የመጨረሻው ዘመን ሁኔታ ላይ ትኩረት የሚያስፈልገው ሆኗል፡፡ አንድ ሰው በብሉ ኪዳን ለእስራኤል የነገሩ ሁሉንም ትንቢቶች ቀጥተኛ አፈጻጸማቸውን የሚጠብቅ ቢሆን መጪው መንግት ባብዛኛው ወደ ተወሰነው የእስራኤል ስነ ምድራዊ ቦታ የሚመለስ እና የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት በአግባቡ አለ መረዳት ይሆናል! ይህ ቤተክርስቲያንን በሚስጥር ከምዕራፍ 5 ላይ ማስወጣት እና የተቀሩትን ምዕራፎች ከእስራኤል ጋር እንዲዛመዱ ማድረግ አስፈላጊ እንዲሆን ያደርገው ነበር፡፡ ሆኖም ግን ትኩረቱ ቃል በተገባለት ብሉይ ኪዳን መሲህ በመሰረተው መንግስት ላይ ከሆነ ፤ ይህ የክርስቶስ የመጀመሪያ ምጽዓት ያሳያል ፤ በመቀጠልም ትኩረቱ የክርስቶስ ስጋ መልበስ ፣ ሕይወት ፣ አስተምዕሮት ፣ሞት እና ትንሳኤ ይሆናል ማለት ነው፡፡የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ልዩ ትኩረት ስለ ዛሬው ደህንነት ነው፡፡መንግስቱ መጥታለች ፤ብሉይ ኪዳን ተስፋ ክርስቶስ ለሁሉም የደህንነት ጥሪ በማድረጉ ተፈጽሟል ፤የሺ አመት ንግስናው በጥቂቶች ላይ ብቻ አይደለም! በእርግጥ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሁሉም የክርስቶስ ምጽዓቶች ይናገራል ፤ ነገር ግን ትኩረቱ መሆን ያለበት የትኛው ላይ ነው? ለእኔ እንደሚመስለኝ የብዙዎቹ ብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ትኩረት ስለ መሲሁ መንግስት መመስረት ስለሚናገረው የመጀመሪያው ምጽዓት ላይ ነው (ዝ.ከ. ዳንኤል 2)፡፡ ይህ መንግስት በብዙ ሁኔታ ከእግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግስት ጋር የሚመሳሰል ነው (ዝ.ከ. ዳንኤል 7)፡፡

በብሉ ኪዳን ውስጥ ያለው ትኩረቱ በዘላለማዊ የእግዚአብሔር መንግስት ላይ ነው ፤ ሆኖም የዚህ መንግስት ንግስና መገለጫ መንገድ የመሲሁ አገልግሎት ነው(ዝ.ከ. 1ኛ ቆሮ 15:26-27)፡፡ ጥያቄው የትኛው ነው እውነት የሚለው አይደለም ፤ ሁለቱም እውነት ናቸው ፤ ነገር ግን ጥያቄው ትኩሩቱ ያለው የቱ ላይ ነው? የሚለው ነው፡፡አንዳንድ ተርጓሚዎች በመሲሁ ሺ አመት ንግስና ላይ በጣም እያተኮሩ (ዝ.ከ. ራዕ 20) ከመምጣታቸው የተነሳ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትኩረት የሆነውን ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ንግስና እንዲስቱ አድርጓቸዋል ማለት ይቻላል፡፡ የክርስቶስ ንግስና ለመጪው ነገር ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ የሁለቱ የክርስቶስ አመጣጦች በብሉ ኪዳን ግልጽ ባይሆንም ሁለቱም ግን የመሲሁ ጊዜያዊ አገዛዝ አይደለም!

የኢየሱስ ስብከት እና ትምህርት ዋናው ትኩረት የእግዚአብሔር መንግስት ነው፡፡ ይህ የአሁን (ደህንነት እና አገልግሎት) እና የወደፊት ሙላት እና ኃይል)፡፡ ራዕይ ያተኮረው በመሲሁ የሺ አመት አገዛዝ ላይ ከሆነ (ዝ.ከ. ራዕይ 20) ቅድመ ሁኔታ እንጂ ፍጹማዊ አይደለም (ዝ.ከ. ራዕይ 21-22) ፡፡ በብሉ ኪዳን ጊዜያዊ አገዛዝ አስፈላጊ ስለመሆኑ በግልጽ አልተቀመጠም፤ሆኖም የዳንኤል 7 የመሲሁ ንግስና ዘላለማዊ እንጂ ጊዜያዊ አይደል፡፡

**ስድስተኛው ውጥረት** (ጫፍ ላይ ያለው የክርስቶስ መመለስ ከ ዘገየው ሁለተኛው ምጽዓት ጋር(*ፓሮሲአ*)

ብዙ አማኞች ኢየሱስ በቅርብ ጊዜ ፣ በድንገት እንዲሁም ሳይጠበቅ እንደሚመጣ ሲማሩ ቆይተዋል (ዝ.ከ. ማቴ 10:23፤ 24:27፤34፤44፤

ማርቆስ 9:1፤ 13:30) ፤ ነገር ግን ሁሉም ጠባቂ አማኝ ትውልድ እስከ አሁን ሲሳሳት ቆይቷል! የኢየሱስ ፈጥኖ መመለስ የሁሉም ትውልድ ሃያል የተስፋ ቃል ነው፤ ነገር ግን ብቸኛው እውነታ አንድ ነው (እናም ይህ አንዱ ነገር መከራን ለሚቀበል)፡፡ አማኞች ሲኖሩ ክርስቶስ ነገ እንደሚመጣ በማሰብ መሆን አለበት፤ ነገር ግን ምናልባትም ከዘገየ ታላቁን ኃላፊነት ማቀድ እና መተግበር አለባቸው(ዝ.ከ. ማቴ 28:19-20)፡፡በወንጌላት የተወሰኑ ገጾች ውስጥ (ዝ.ከ. ማርቆስ 13:10፤ ሉቃ 17:2፤ 18:8) እንዲሁም 1ኛ እና 2ኛ ተሰሎንቄ በዘገየው ሁለተኛው ምጽዓት ላይ የተመሰረቱ ናቸው (*ፓሮሲአ*)፡፡

*መጀመሪያ መፈጸም ያለባቸው ታሪካዊ ሁኔታዎች አሉ፤*

1. አለም አቀፍ የወንጌል ስብከት እንቅስቃሴ (ዝ.ከ. ማቴ 24:15፤ ማርቆስ 13:10)
2. "የኃጥያተኛው ሰው" መገለጥ (ዝ.ከ. ማቴ 24:15፤ 2ኛተሰሎንቄ 2፤ ራዕይ 13)
3. ታላቁ ስቃይ (ዝ.ከ. ማቴ 24:21፤24፤ ራዕይ 13) አላማ ያለው ግራ መጋባት አለ (ዝ.ከ. ማቴ 24:42-51፤ ማርቆስ 13:32-36) ፤ ዛሬ መጨረሻህ እንደሆነ በመሰብ ኑር ፤ ነገር ግን ለወደፊቱ የወንጌል አገልግሎት ማቀድ እና መሰልጠን አለብህ!

**9:7** የቁ 7 ሁሉም ጥያቄዎች "አዎ" የሚል መልስ ይጠብቃሉ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ እይታ እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ያደረገው ቃል ኪዳናዊ ምርጫ ቀንሷል፡፡ አንዱ እና ብቸኛው እግዚአብሔር ሁሉንም አገራት ከነበሩበት ስነ ምድራዊ ቦታዎች በመውሰድ እና በመመለስ መርቷቸዋል (ዝ.ከ. ዘዳ 32:8፤ እና ምናልባትም በ29:26 ውስጥ ተመልክቷል)፡፡ እስራኤል ከኢትዮጵያ፣ፍልስጤም እና ሶሪያ ጋር መነጻጸር በእርግጥ ለእስራኤል ህመም ፈጥሮባት ይሆናል፡፡ ይህ በመንፈሳዊ ትምህርት ምርጫ ከ3:2 ጋር አቻ ተቃርኖ ይፈጥራል! እስራኤል፤ እንደ ሁሉም አገራት ለኃጥታቸው መልስ ይሰጣሉ!

▣ **"እስራኤልን ከግብጽ ምድር"** ይህ እስራኤል እንደ አገር መታየት የተጀመረበትን ዘጸዓት ያመለክታል፡፡

▣ **"ከከፍቶር"**ይህ የፍልስጤማዊያን ተወላጆች መኖሪያ የነበረውን የከፍቶር ደሴት ያመለክታል (የአጊያን የባህር ላይ ሕዝቦች)፡፡

▣ **"ከቂር"**ይህ ምናልባትም (1) በኤላም አቅራቢያ የሜሶፖታሚያ አካልን ፣ (2) "ቅጥር" የሚል ፍች ያለው እና ነነዌ የሚለውን የሚወክል ቃል ፣(3) በአርሜንያ የሚገኝ ወንዝን (4) ከሶሪያ ሰሜናዊ ድንበር ጀምሮ የተዘረጋ ተራራን(ዝ.ከ. *ኣንኮር የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ጥራዝ 4፤ ገፅ 83*) ሊያመለክት ይችላል፡፡

**9:8** በኃጥያት በኩል እስራኤል እንደ ሌሎች ሕዝቦች እኩል ይዳኛሉ ነገር ግን ያህዌ የተስፋ ቃል የሰጣቸውን ሕዝቦቹን በሙሉ አያጠፋም (ዝ.ከ. 5:4-7፤14-15፤ 9:11-15)፡፡የያዕቆብ ቤት ጻድቅ ቅሪቶች ያርፋሉ! ይህ ጭብጥ በኤርምያስ ውስጥ ተደጋግሞ ተጠቅሷል፡፡

1. ይሁዳ ፈጽሞ አይጠፋም ፤ ኤር 4:27፤ 5:10፤18፤ 33:16
2. እስራኤል ፈጽሞ አይጠፋም፤ ኤር 30:11፤ 31:35-36

የእግዚአብሔር ዘላለማዊ የመቤዠት እቅድ (ማለትም፤ መሲሁ) በዚህ ላይ የተመሰረተ ነው!

▣ **"እነሆ፥ የጌታ የእግዚአብሔር ዓይኖች በኃጢአተኛ መንግሥት ላይ ናቸው"** ይህ "የጌታ የእግዚአብሔር ዓይኖች" የሚለው ተምሳሌታዊ አነጋገር እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ የሚያደርገውን የርህሩነት ጥበቃ የሚያመለክት ነው (ዝ.ከ. ዘዳ 11:12)፡፡ሆኖም ግን "በኃጥያት መንግስት" የሚለው ሃረግ መጨመር ግርታን ይፈጥራል፡፡ምናልባትም ይህን ሁኔታ የበለጠ ለመረዳት አንድ ወላጅ ልጁ የተጎሳቆለን ኑሮ ሲመርጥ የሚሰማውን ስሜት መውሰድ ምርጡ መንገድ ሊሆን ይችላል(ዝ.ከ. ሆሴ 11)፡፡እውነተኛ ፍቅር ያለው ወላጅ ደካማ የሆነውን የልጁ ምርጫ የሚያመጣቸውን የጤና ፣የደስታ እና የልጁን እድገት የረጅም ጊዜ መዘዞች በሙሉ ለመቀበል መፍቀድ አለበት፤ነገር ግን ይህ ለሁለቱም ወገኞች በጣም ገዳት ነው፡፡

▣ **"አጠፋታለሁ"** ይህ ቃል(BDB 1029፤ KB 1552) በዚህ ቁጥር ውስጥ ሦስት ግዜ ተጠቅሷል፡፡ ትርጉሙም "መደምሰስ" ፣ "ማጥፋት" ፣"ማቋረጥ" ማለት ነው፡፡ ይህ በዘዳ 33:26-29 ውስጥ እግዚአብሔር የሕዝቡን ጠላቶች እንደሚያጠፋ ከሚያመለክትው ተመሳሳይ ቃል ጋር የሚጻረር አገላለጽ ነው፡፡ እዚህ ላይ ባለው መሰረት ግን አሁን ራሳቸው ጠላቶች ናቸው (*ሂፊል* የተቋጨ)፡፡ እዚህ ላይ አሁንም ቢሆን የተስፋ ጭላንጭል አለ፤ "የያዕቆብን ቤት ፈጽሜ አላጠፋም"(*ሂፊል* መጨረሻ የሌለው ሙሉ እና *ሂፊል* ያልተቋጨ)፡፡ በቁ 11 ምክንያት ይህ ይሁዳን ለያመለክት የሚያመለክት ይመስላል!

**9:9-10** የእብራዊያኑ ጽሁፍ የተረጋገጠ አይደለም፡፡ በግልጽ እንደሚታየው ይህ የሆነ አይነት ለፍርድ (ማለትም፤ ጠጠር) ወይም ለደህንነት (ማለትም፤ የእህል ቅንጣት) የሚደረግ የመለየት ሂደትን ያመለክታል፡፡ አውዱ ጻድቅ ቅሪቶች እንደሚድኑ እና ከእነሱ መሃል አንዱም እንደማይጠፋ (ማለትም፤ ቁ 9መ) በተዘዋዋሪ ያመለክታል፡፡ነገር ግን ኃጥያተኞቹ እስራኤላዊያንን እግዚአብሔር ልክ እንደ ሌሎች ጣዖት አምላኪ ሕዝቦች ይዳኛቸዋል (ማለትም፤ ቁ 10)፡፡

"መንፋት" (BDB 631፤ KB 681፤ *ሂፊል* የተቋጨ) የሚለው ግስ ከዋናው እህል ጋር ሊቀላቀሉ የሚችሉትን ድንጋዮች ወይም ቆሻሻ አንኳሮችን ለመለየት በወንፊት ውስጥ ተደርገው የሚነፋትን እህሎች ያመለክታል፡፡ "ቅንጣት" (NASB NJB፤ ነገር ግን አኪጄ "ትናንሽ የእህል ፍሬዎች" ብሎታል) ተብሎ የተተረጎመው ቃል በተጨማሪም "ድንጋይ"(ዝ.ከ. 2ኛ ሳሙ 17:13፤ KB 459፤ NRSV) የሚል ትርጉም ሊኖረው ይችላል፡፡ ይህ ቃል (BDB 865) በተደጋጋሚ "ዕቃ"፣"ቦርሳ"፣"ቅርጫት" ወይም "ከረጢት" ተብሎ ይተረጎማል፡፡ እዚህ ላይ ይህ በሜዳ ላይ የእህል አገዳዎችን በአንድ ላይ የመሰብሰብ እና የማሰር (ምርት) ሂደት ላይ የሚያዝ እቃን ያመለክታል፡፡

"በአሕዛብ ሁሉ መካከል" የሚለው ሃረግ ምናልባትም ቀ 4 ውስጥ እንዳለው ያህዌ በምርኮ ላይ ባሉት እና በኃጥያት በተሞሉት እስራኤልዊያን ላይም ፍርድ እንደሚልክ ከሚገልጸው ሃሳብ ጋር የሚዛመድ ሊሆን ይችላል፡፡የእግዚአብሔር ፍርድ በሌሎች ሕዛቦች መካከል የሚገኙትን እምነት የጎደላቸው የቃል ኪዳን ሕዝቡንም ቢሆን ያጠፋል (ዝ.ከ. ቁ 10ለ)፡፡ ከእግዚአብሔር ቁጣ የሚሸሸበት ምንም ስፍራ የለም (ዝ.ከ. 5:19)፡፡

## አሞፅ: : 9:11-12

**[11] በዚያ ቀን የወደቀችውን የዳዊትን ድንኳን አነሣለሁ፥ የተናደውንም ቅጥርዋን እጠግናለሁ የፈረሰውንም አድሳለሁ፥ እንደ ቀደመውም ዘመን እሠራታለሁ[12] ይኸውም የኤዶምያስን ቅሬታ፥ ስሜም የተጠራባቸውን አሕዛብን ሁሉ ይወርሱ ዘንድ ነው፥ ይላል ይህን የሚያደርግ እግዚአብሔር፦**

**9:11-15** ይህ ምንባብ በየትኛውም ምድብ እንዳለ የተረጋገጠ ነገር የለም(ሁሉም የክፍሉ ምድቦች ወቀሳዎች እንጂ የሚገነቡ አይደሉም)፡፡ አውዱ በድንገት ከፍርድ ወደ መታደስ ተለወጠ(እንዲሁም ከሰማሪያ ወደ ኢየሩሳሌም)፡፡ ሆነም ቀረ የተስፋው መልዕክት የሚሆን ነው!

**9:11 "በዚያ ቀን"** ይህ ሃረግ ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል (ዝ.ከ. 2:16፤ 8:3፤9፤18)፡፡ በ2:16 ላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ፡፡ እስራኤል "በዚያ ቀን" የሚለው እግዚአብሔር ለበረከት የሚጎበኝበት ጊዜ እንደሚሆን አስባለች ፤ ነገር ግን አሞፅ የፍርድ ጊዜ እንደሆነ ተንብዮ ነበር(ለምሳሌ፤ 5:18-20)፡፡

እዚህ ላይ ግን አሞፅ የትንቢቱን አቅጣጫ ለውጦታል፡፡ ጻድቅ ቅሪቶች ለሆኑት "በዚያች ቀን" የሚለው ለዳዊት የተገቡት የቃል ኪዳን ተስፋዎች የሚታደሱበት ጊዜ ይሆናል (ዝ.ከ. 2ኛ ሳሙ 7)፡፡ ከቁ 13-14 ውስጥ ያሉት እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው ተስፋዎች በይበልጥም ደግሞ በዘዳ 28:1-14 ውስጥ ላለው ትኩረት የሚሰጡ ናቸው፡፡ሁል ጊዜ ብሉይ ኪዳን ነብያቶች የሙሴን የቃል ኪዳን ግዴታዎች ሲጠቅሱ ማየታችን በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ሙሴ (ዝ.ከ. ዘዳ 28:58-63፤ 29:25-28) ልክ እንደ ኢያሱ (ዝ.ከ. ኢያ 24:19) የፓተሪያርክ ተወላጆች ቃል ኪዳኑን መጠበቅ እንደማይችሉ አውቆ ነበር፡፡ ሆኖም ግን በእግዚአብሔር መሲህ በኩል የምህረት እና የመታደስ ተስፋ ያህዌ ባዘጋጀው ጊዜ እንደሚመጣ በዘዳግም ውስጥ ተጠቅሷል(ዝ.ከ. ዘዳ 30:5)፡፡ ነብያቶች ይህን ተስፋ በማንሳት ነው ወደ ዘላለማዊ ድል እና በረከት ያሰፉት እንጂ ፍርድን አይደለም!

▣ **"የወደቀችውን የዳዊትን ድንኳን አነሣለሁ"** ይህ ኢየሩሳሌምን ዋና ከተማ እና የመንፈሳዊ ማዕከል ያደረገውን የዳዊት መንግስት የሚያመለክት ተምሳሌታዊ አነጋገር ነው፡፡የወርቃማው ዘመን አንድ የሆነው ንጉሳዊ አገዛዝ (ማለትም፤ ከያህዌ የሚወከል ታማኝ ንጉስ) ከነብልጽናው ፣ ከነ ጥበቃው እና ከነሃይማኖታዊ ታማኝነቱ ጋር ተመስሏል፡፡ የመጪው መሲህ ትንቢት ሁል ጊዜ መነሻው ከይሁዳ ነው (ዝ.ከ. 2ኛ ሳሙ 7፤ ኢሳ 7:14፤ 9:6-7፤ 11:1-9፤ኤር 33:15፤17፤ ሚክያስ 4:1-5፤ 5:2-5ሀ)

▣ **"ቅጥርዋን"** ቁ 11 በቀጥታ የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች የሚያመለክት ነው፡፡ይህ የሴት ብዙ ቁጥር ሲሆን የእስራኤል እና የይሁዳን መዋሃድ አቅልሎ የሚያስረዳ ዘዴ ሊሆን ይችላል (ማለትም፤ አንደ ዋና ከተማ እና የአምልኮ ስፍራ)፡፡

**9:12** ይህ ቁጥር በዳዊት እና በሰለሞን የነበረው የጦር ኃይል እንደገና ወደ ተስፋይቷ ምድር መመለሱን የሚገልጽ ነው፡፡ይህ ዘላለማዊ የተስፋ ቃል በሐዋ 15:16-17 ውስጥ አለም አቀፋዊ አመላካች እንደሆነ ሲያስቀምጥ በሰባ ሊቃናት ትርጉም ውስጥ "ኤዶም" ወደ "አዳም" (ማለትም፡ የሰው ዘር) ተለውጧል፤ ይህንንም ጴጥሮስ ጠቅሶታል (በተጨማሪም ጳውሎስ በሮሜ 9:24-26 ውስጥ ሆሴ 1:10፤ 2:23ን መጠቀሙን ያስተውሉ)! ይህ አለማቀፋዊ አቀራረብ በአሞፅ 9:5-6፤7 ውስጥም ተንጸባርቋል (ዝ.ከ. ዘፍ 3:15፤ 12:3፤ ዘጸ 19:5-6፤ ኢሳ 42:1፤4፤6፤10-11፤ 49:6፤ 51:4)፡፡ ይህ የተስፋይቷ ምድር መታደስ (ለምሳሌ፤ ዘፍ 12:1-3፤ 13:14-17፤ 15:7) ከቁ 1-4፤9-10 ላይ ላሉት ሃሳቦች ቀጥተኛ ተጻራሪ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ከአብርሃም እና ከዘሮቹ ጋር ያለው ዝምድና በቃል ኪዳኑ መታዘዝ ላይ የተመሰረተ ነበር፡፡ በቃል ኪዳኑ መሰረት ካልታዘዙ ደግሞ፤

1. "የሚጠፉ" ይሆናሉ፤ ዘዳ 4:26፤ 6:15፤ ኢያ 23:15፤ 1ኛ ነገ 13:34፤ አሞፅ 9:8
2. ከሚገቡባት ምድር "የሚነቀሉ"ይሆናሉ፤ዘዳ 28:63
3. ከምድራቸው "የሚነቀሉ" ይሆናሉ፤ ዘዳ 29:28፤ 1ኛ ነገ 14:15፤ 1ኛ ዜና 7:20
4. አምላካቸው እግዚአብሔር ከሚሰጣቸው ምድር "የሚጠፉ" ይሆናሉ፤ ኢያ 23:13፤16
5. "የሚጣሉ" ይሆናሉ፤ 1ኛ ነገ 9:7
6. "የሚፈልሱ" ይሆናል፤ 2ኛነገ 17:6፤23፤ 18:9-11፤ 25:21 (በተጨማሪም 23:27)

ነገር ግን ከታዘዙ በምድራቸው ላይ ይቆያሉ፤ 2ኛነገ 18:12፤ 21:8፤ 1ኛ ዜና 33:8 (ዝ.ከ. 2ኛ ሳሙ 7:10)፡፡
በተደጋጋሚ ጊዜ በነቢያት የእግዚአብሔር ሕዝቦች ወደ "ራሳቸው ምድር" ይመለሳሉ የሚለው ትኩረት ተሰጥቶታል(ዝ.ከ. ኢሳ 14:1-2፤ ኤር 16:15፤ ሕዝ 11:17፤ 34:13፤17፤ 36:24፤ 37:12፤14፤21፤ አሞፅ 9:15)፡፡

## አሞፅ: : 9:13-15

**[13] እነሆ፥ አራሹ አጫጁን፥ ወይን ጠማቂውም ዘሪውን የሚያገኝበት ወራት ይመጣል፥ ይላል እግዚአብሔር ተራሮችም በተሀውን የወይን ጠጅ ያንጠባጥባሉ፥ ኮረብቶችም ሁሉ ይቀልጣሉ።**
**[14]የሕዝቤን የእስራኤልን ምርኮ እመልሳለሁ፥ የፈረሱትንም ከተሞች ሠርተው ይቀመጡባቸዋል ወይኑንም ይተክላሉ፥ የወይን ጠጁንም ይጠጣሉ አታክልትንም ያባጃሉ፥ ፍሬውንም ይበላሉ።**
**[15]በምድራቸውም እተክላቸዋለሁ፥ ከእንግዲህም ወዲህ ከሰጠኋቸው ከምድራቸው አይነቀሉም፥ ይላል አምላክህ እግዚአብሔር**

**9:13-15** እስራኤል በተደጋጋሚ ጊዜ የታሪክ ዋና ትኩረት በመሆኗ የዚህ ጥቅስ የጊዜ ትኩረት የመጨሻው ዘመን መሆን አለበት፡፡ ይህ የተስፋ ቃል (ፖለቲካዊ ሰላም እና የግብርና ብዛት፤ ዝ.ከ. ዘዳ 27-29፤ ሌላ የመጨረሻ ዘመን ጽሑፍ በኢዩኤል 3:18 ውስጥም አለ) አሁንም ቢሆን በቃል ኪዳኑ መገዛት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይህ በቀጥታ የተገለጸ ባይሆንም በእርግጠኝነት በተዘዋዋሪ ተመላክቷል፡፡

**9:13 "የወይን ጠጅ ያንጠባጥባሉ"** በ6:6 ላይ መጽሐፍ ቅዱስ በአልኮል (አልኮል መጥመቅ) እና ጠጪነት (ሱስ) ላይ ያለው ዝንባሌ የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

▣

**NASB** **"ኮረብቶችም ሁሉ ይቀልጣሉ"**

**NKJVNRSV፤**
**TEV፤ NJB** **"ኮረብቶችም ሁሉ አብረውት ይሄዳሉ"**

ግሱ (BDB 556፤ KB 555፣ Hithpolel IMPERFECT) *"መቅለጥ"* ማለት ነው (ማለትም፤ የእግዚአብሐር ፍርድ፤ ዝ.ከ. ሚክያስ 1:4፤ ናሆም 1:5)፤ ነገር ግን እዚህ ላይ በተጋነነ ቃል በንግድ ምክንያት ወይን እየተዘዋወረ መሆኑን የሚገልጽ ሲሆን ይህም የግብርናው መበልጸግ ምልክት ነው!

**9:14** ይህ መታደስ የዘዳ 28:38-40፤ አሞፅ 5:11፤ ሚክያስ 6:15፤ ሰፎ 1:13 ተቃራኒ ነው፡፡የእግዚአብሔር ሕዝቦች በምድሩ ላይ የወይን ተክል ይተክላሉ ፤ በፍሬው ይደሰታሉ (ማለትም፤ በምድሩ ላይ ስላለው ደህንነት እና ቆይታ ዘይቢያዊ አገላለጽ ነው ኤር 31:5፤ ሕዝ 28:26)፡፡

**9:15** ይህ ምንም እንኳን ቅድመ ሁኔታ የሌለው ቢመስልም የተስፋ ቃሉ በአይሁዳዊያን ሕዝቦች ታሪክ መሰረት መገምገም ይኖርበታል፡፡ያልተለመደው ቃል ኪዳን በአይሁድ ሕዝቦች ታሪክ አንጻር ነው፡፡ በግልጽ እንደሚታየው ይህ የሁለቱንም ዘላለማዊ (ዝ.ከ. 2ኛ ሳሙ 7:10፤ ኤር 24:6፤ 32:41፤ 42:10) እና ታሪካዊ ሃሳቦች አሉት፡፡

▣ **"አምላክህ እግዚአብሔር"** የሚያስገርም የሁኔታ ምልልስ (ቃል ኪዳን - ፍረድ - ቃል ኪዳን)፤ እንደገና የቃል ኪዳን ሕዝብ ናቸው(ዝ.ከ. ሆሴ 2:21-23)፡፡

# ወደ ሆሴዕ መግቢያ

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. መጽሐፉ ስሙን ያገኘው ከዋናው ተናጋሪው ከሆሴዕ ነው፡፡

ለ. የስሙ ትርጉም "ነጻነት" (BDB 448) ማለት ነው ፡፡ በመጀመሪያ ይህ የኢያሱ ስም ነበር (ዝከ. ዘኍ. 13:16)፡፡ ይህ ሆሴዕ ከሚባለው ስም ጋር ተመሳሳይ ነው (2ኛነገ.17:1)

II. ቅዱስ አጻጻፉ

ሀ. ይህ መጽሐፍ "የቀደምት ነብያት" አካል ነው (Ecclesiasticus 49:10).

ለ. ይህ በደቂቅ ነብያት ምደባ (*Baba Bathra* 14ለ) ከአስራ ሁለቱ የመጀመሪያው ነው፡፡

1. ልክ እንደ ኢሳያስ ፣ ኤርምያስ እና ሕዝቁኤል መጽሐፎች እነዚህም አስራ ሁለት ትናንሽ መጽሐፎች በአንድ ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡
2. አደራደራቸው የእያንዳንዱን መጽሐፍ የተለመደ የጊዜን ቅደም ተከተል የሚያንጸባርቅ ነው፡፡

ሐ. የ "አስራ ሁለቱ" ወይም የደቂቅ ነብያት አደራደር በተለያዩ ምሁራን የጊዜ ቅደም ተከተል ሲሰጣቸው ቆይቷል፡፡ ሆኖም ን በዚህ እይታ ችግሮች አሉ፤

1. የመጀመሪያዎቹ ስድስት መጽሐፎች በ ማሶሬቲኩ (እብራዊያን ጽሑፍ) እና በ የሰባ ሊቃናት ትርጉም(ግሪክ ጽሑፍ) መካከል የተለያዩ
ናቸው፡፡

| ማሶሬቲኩ | LXX |
|---|---|
| ሆሴዕ | ሆሴዕ |
| ኢዮኤል | አሞፅ |
| አሞፅ | ሚክያስ |
| አብድዩ | ኢዮኤል |
| ዮናስ | አብድዩ |
| ሚክያስ | ዮናስ |

2. ውስጣዊ መረጃ አሞፅን ከሆሴዕ በፊት የዘመን ቅደም ተከተል እንዳለው ያሳያል፡፡
3. ምናልባትም ሆሴዕ በጊዜ እርዝመቱ እና በስምንተኛው ክፍለ ዘመን መቼት ምክንያት በመጀመሪያ ደረጃ የተቀመጠ ሊሆን ይችላል፡፡

መ. ምናልባትም የሆሴዕ ጽሑፍ ከማንኛውም የብሉ ኪዳን መጽሐፍ በጣም ከባዱ ነው (ዝከ. IX)፡፡

1. ለዚህም አንዱ ምክንያት የመጽሐፉ ግጥማዊ እና ስሜታዊ አቀራረቡ ነው፡፡
2. ሌላኛው ምክንያት የጽሑፍ አገለባበጥ ነው፡፡ ማሶሬቲኩ እና የሰባ ሊቃናት ትርጉም የተለያዩ ናቸው፡፡
3. ሌላው ምክንያት በእስራኤል እና በይሁዳ መካከል ያለው የእብራዊያን አነጋገር መለያየት ነው፡፡

III. ዘውጉ

ሀ. መጽሐፉ የስድ ንባብ እና የቅኔ ውህድ ነው (ባብዛኛው ቅኔያዊ)፡፡

ለ. ምዕራፍ 1 እና 3 የሆሴን ሕይወት እና ጊዜ ታሪካዊ ትረካዎች ሲሆኑ ምዕራፍ 2 ደግሞ ግጥም ነው፡፡

ሐ. የሆሴዕ ሕይወት እና ጋብቻ በተመሳሳይ ሁኔታ የእስራኤልን ያልተገራ ባህሪ እና የያህዌን የማይናወጥ ልባዊ ፍቅሩን ለማስረዳት አገልግለዋል፡፡

1. ያህዌ እንደ ታማኝ ወጣት አፍቃሪ (ከምዕራፍ 1-3)
2. ያህዌ እንደ ወላጅ አፍቃሪ (ምዕራፍ 11)
3. እነዚህ ዘይቤዎች እስራኤላዊያን ከያህዌ ይልቅ ባዖልን እንደ "ባል" እና "ጌታ" በመውሰድ ከፈጠሩት ግራ መጋባት ጋር መሰረት ያበጁ ናቸው፡፡

መ. የተጻፈው በሚያምር ፣ ኃይለኛ እና ስሜታዊ በሆነ ቅኔ ሲሆን ምዕራፎቹ ግን ተያያዥ አይደሉም (ከምዕራፍ 4-14)፡፡ የሆሴዕ ጽሑፎች እና ትንቢቶች ምናልባትም እሱ ከሞተ በኋላ ተሰብብበው ሳይስተካከሉ አልቀረም፡፡

ሠ. ዴቪድ ኤ.ሁባርድ፤ ሆሴዕ (ቲንዳል ብሉ ኪዳን ሃተታዎች)፤ የዘውጉን ሁኔታ በሚከተለው መንገድ ገልጾታል፤ "በጣም ከባድ ሐዘን የሚቀሰቅሰው ፤ ወደ እስራኤል ከቁጥጥር ወጪ ሆኖ የቀረበው በንግግር ላይ ሌላ ንግግር ፣ በምጸት ላይ ምጸት በዘይቤ ላይ ሌላ ዘይቤ ፣ በጥያቄ ላይ ሌላ ጥያቄ ፤ የሆነ አገላለጽ ለመጽሐፉም ኃይለኝነቱን አላብሰውታል" (ገፅ. 20).

ረ. የነብዩን ጋብቻ በተመለከተ የተለያዩ ዕይታዎች አሉ፡፡

1. መላምታዊ (አሊጎሪ)
2. መንፈሳዊ ታማኝነት የጎደለው (ከእስራኤል ጣዖት አምላኪነት ጋር የሚመደብ)
3. ድንግል ካልሆነች ጋር የተደረገ ትክክለኛ ጋብቻ (የልምላሜ አምልኮ ስርዓት)
4. በኋላ ላይ በርቢ አምልኮ ስርዓት ውስጥ ተሳታፊ ከሆነች ሚስት ጋር የተደረገ ትክክለኛ ጋብቻ (ቀጥተኛ)

IV. ደራሲው

ሀ. ስለሱ የምናውቀው ጥቂት ቢሆንም ቁም ነገሩ ሁልጊዜ ሆሴዕ ራሱ ነበር፡፡

ለ. ሰውዬው

1. የብኤሪ ልጅ ነው (1:1)

2. የእስራኤል ዜግነት አለው (7:5)፤ የየትኛው ከተማ ሰው እንደሆነ አይታወቅም
3. አሞፅ ለህብረተሰብ የፍትህን አስፈላጊነት እንደተናገረ ሁሉ ሆሴዕ ደግሞ ስለ ቃል ኪዳን ታማኝነት እና አስፈላጊነት ተናግሯል፡፡
4. ሲጠራ የነበረውም
   ሀ. "የእስራኤል ኤርምያስ"
   ለ. "የብሉ ኪዳኑ ሐዋሪያ ዮሐንስ"
5. "የእስራኤል የመጀመሪያው ወንጌላዊ"

ሐ. *ባባ ባዝራ* 15ሀ የታላቁ የአይሁድ ቤተመቅደስ ሰዎች "አስራ ሁለተኛው" ብለው ጽፈዋል ሲል ተናግሯል፡፡ ይህ በአንድ ላይ በተቀመጠ እና በተስተካከለ ሁኔታ መሆን አለበት፡፡
መ. አንዳንዶች በእሱ ጸሃፊነት ላይ ጥያቄ አላቸው ፤ ምክንያቱም፤
1. በይሁዳ ማጣቀሻዎች ፤ 1:1፤7፤11፤ 4:15፤ 5:5፤10፤12-14፤ 6:4፤11፤ 8:14፤ 10:11፤ 11:12፤ 12:2
2. በወደፊቱ ብልጽግና እና ነጻ መውጣት ላይ በሚናገሩት ምንባቦች
3. የሆሴዕ ጋብቻ በምዕራፍ አንድ እና ሁለት ላይ የተገጸው በሦስተኛ ሰው ወገን ሲሆን በምዕራፍ ሶስት ግን በሁለተኛ ሰው ወገን የተገለጸ በመሆኑ

ሠ. ለተቃውሞዎች ምላሾች
1. ሁሉም ነብያት በእስራኤል እና ይሁዳ መካካል ያለውን መነጣጠል ትክክል እንዳልሆነ ያስባሉ፡፡ ይሁዳ ሁል ጊዜ ለአብራሃም እና ለዳዊት የተደረገው የቃል ኪዳን ተስፋ ዋና ህጋዊ አካል እንደሆነ ይታያል፡፡
2. ነብዩ በተደጋጋሚ ጊዜ ፍርድ እና ተስፋ ቃልን ያዘሉ ትንቢቶችን ያከታትላል፡፡ እነዚህም እንደ አንድ መለኮታዊ መልዕክት በአንድ ላይ ይገለጻሉ፡፡
3. ምንልባትም ስብከቱ እና ቅኔዎቹ በአጠቃላይ የሆሴዕ መገለጫዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

V. ጊዜው

ሀ. ሆሴዕ ከክ.ል.በ የስምንተኛው ክፍለ ዘመን ነብይ ነው
1. ኢሳያስ እና ሚክያስ በይሁዳ ውስጥ ተናግረዋል
2. ዮናስ፤ አሞፅ፤ እና ሆሴዕ በእስራኤል ውስጥ ተናግረዋል

ለ. ሆሴዕ የአሞጽን አገልግሎት የሸፈነ እና የተከተለ ነበር

ሐ. የሆሴዕ ስብከቶች ጊዜ (ስለ ተከፋፈሉት ንጉሳዊ አገዛዝ የሚያሳየውን የንጉሶች ቻርት በተጨማሪ መግለጫው ውስጥ ይመልከቱ) የነበረው በ1፡1 ላይ በተጠቀሱት የንጉሶች ቀናት ውስጥ ሳይሆን አይቀርም፡፡
1. *ዖዝያን* (በይሁዳ)
2. ኢዮአታም (በይሁዳ)
3. አካዝ (በይሁዳ)
4. ሕዝቅያስ (በይሁዳ)
5. ኢዮርብዓም 2ኛ (በይሁዳ)
   በአዋቂዎች የተሰጡ ብዙ አስተያየቶች አሉ (ልዩነቱ የመጣው በፋቁሔ የ30 አመታት ንግስና ምክንያት ነው፡፡ ዝከ. 2ኛነገ. 15:27፡፡ (ጥሩ ለሆነ የተብራራ ምላሽ Gleason Archer, Encyclopedia of Bible Difficulties, ገፅ 209-211 ያለውን ይመልከቱ)፡፡
   1. ኬይል፤ 790-725 ከክ.ል.በ
      ሀ. 1:4፤ ከኢዩ ሥርወ መንግስት ውድቀት በፊት ጀመረ
      ለ. 10:14፤ ሻልምናሶር 5ኛ ወረራ ጊዜ የነበረ
   2. ፍራንሲስኮ ፤ 750-735 ከክ.ል.በ
      ሀ. ከአሞፅ ትንሽ ቀደም ብሎ
      ለ. የኢዮርብአም 2ኛ የመጨረሻ ቀናት
      ሐ. ከ735 ከክ.ል.በኋላ አልነበረም ምክንያቱም አሶራዊያን የገልአድን አከባቢ ይዘው ነበር፡፡
   3. ሃሪሰን 753 ከ 722 ከክ.ል.በ በፊት
      ሀ. ኢዮርብአም 2ኛ በ753 ከክ.ል.በ ውስጥ ሞተ
      ለ. ቴጌል ተልፈለሶር III በምናሄም የተከፈለ ግብር (8:9) ወደ 739 ከክ.ል.በ አካባቢ
      ሐ. በ5:8-6:6 (በተጨማሪም ኢሳ. 7-14) ውስጥ የተጠቆመው ከ735-734 ከክ.ል.በ የነበረው የሶርያ ኤፍሬማዊ ጦርነት ክስተቶች
      መ. የሆሴዕ ቀናት በ7:11፤ 9:6፤ እና 12:2 ወስጥ የተጠቆሙትን ግብፅ
         9:6፤ and 12:2.
   4. ላሶር/La Sor፣ ሁባርድ/Hubbard፣ እና ቡሽ/ Bush፣ 753 - እስከ 722 ከክ.ል.በ
      ሀ. ከኢዮርብአም 2ኛ ሞት በፊት የተጀመረ፤ ከክ.ል.በ በ753
      ለ. ወደ ህዝቅያስ ንግስና የሚቀጥል
      ሐ. ተባባሪ ገዢ ከ728 ከክ.ል.በ በኋላ
      መ. ከክ.ል.በ በከ715 በኋላ የነበረ ንጉስ
      ሠ. የተጌልተልገልፈልሶር III' ንግስና ወቅት የሰበከ፤ 745-727 ከክ.ል.በ

VI. ታሪካዊውን መቼት - የአሞፅ መግቢያ VI የሚለውን ይመልከቱ፡፡

VII. ሥነ-ጽሑፋዊ ምድቦች (አውደ ምንባብ)

ሀ. (በሲልይድ ፍራንሲስኮ/Clyde Francisco ከተጻፈው የብሉ ኪዳን መግቢያ ከገፅ. 150-163 የተወሰደ፤)

1. መግቢያ፤ 1:1
2. የሆሴዕ የሃገር ውስጥ ቀውሶች፤ 1:2-3:5
3. የእግዚአብሔር ክርክር ከእስራኤላዊያን ጋር፤ 4:1-10:15
4. አባትና አስቸጋሪ ልጁ 11:1-12
5. በስም ውስጥ ምን አለ (ያዕቆብ ከ እስራኤል ጋር) 12:1-15
6. የሕዝብ መሞት፤ 13:1-16
7. የፍርድ አማራጮች 14:1-9

ለ. (በኢ.ጄ.ያንግ/E. J. Young ከተጻፈው የብሉ ኪዳን መግቢያ ከገፅ. 252-254 የተወሰደ)

1. እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ያለው ዝምድና (ግንኙነት)፤ 1:1-3:5
2. የተለያዩ የነብዩ ሰፊ ንግግሮች፤ 4:1-14:9
   ሀ. የሰሜኑ ነገዶች ጥፋተኝነት፤ 4-8
   ለ. የሰሜኑ ነገዶች ቅጣት፤ 9:1-11:11
   ሐ. ንስሃ ለሚገቡ ሕዝቦች የወደፊቱ ባርኮቶች፤ 11:12-14:9

VIII. ዋነኞቹ ሐቆች

ሀ. ይህዌ የግል አምላክ ነው፡፡ ኃጥያት ፍቅር ከሆነው እግዚአብሔር ጋር የሚቃረን ነው (ሆሴዕ)፤ የቃል ኪዳኑን ህጎች መተላለፍ ብቻ አይደለም (አሞፅ)፡፡

ለ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ብዙ ሰዎች ባሉበት ቤተሰብ ውስጥ በሚገኙ ዘይቤዎች የበለጠ ሊገለጽ ይችላል፡፡

1. ባል (እግዚአብሔር) - ሚስት (እስራኤል)
2. ወላጅ (እግዚአብሔር) - ልጅ (እስራኤል)

ሐ. ይህዌ በተስፋ ቃል ፣ በመስዋዕት እና በቃል ኪዳን ከወደቀው የሰው ዘር ጋር ለመታረቅ መርጧል፡፡ በሰው ዘንድ ደግሞ እነዚህ የግል እምነት እና የቃል ኪዳን መታዘዝን ያካትታሉ፡፡

መ. የቃል ኪዳን መተላለፍ ውጤቱ ፍርድ ነው፡፡ ፍርድ ሁል ጊዜ አላማው መታደስ ነው (ዝከ. 1:10-2:1፤ 2:14-23፤ 3:1-5፤ 11:8-11፤ 14:1-7)፡፡ ቅጣት የአባታዊ ፍቅር ተግባር ነው (Heb. 12:5ff)፡፡ የእስራኤል የወደፊት ባርኮቶች አሁን ባላት መታዘዝ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

IX. የእብራይስጡ የሆሴዕ ጽሑፍ

በብሉ ኪዳን ውስጥ የሆሴዕ ጽሑፍ ከፍተኛው አጨቃጫቂ ነው፡፡ እኔ በእርግጠኝነት የእብራዊያን ምሁር አይደለሁም፤ ነገር ግን በአተረጓገም ሂደቱ ውስጥ ሌላ ጥንካሬ (አመለካከት) አምጥቻለሁ፡፡ የእብራዊያኑ ጽሑፍ ሁኔታ በአንድ ጎኑ በሆሴዕ የአጻጻፍ ስሜት ላይ እንዲሁም በሌላ ጎኑ በቅኔያዊ አቀራረቡ (ዘውጉ) ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

የእሱ ዘይቤዎች አዳዲስ እና የተለያዩ ናቸው፡፡ ይህ ለሁለቱም ለድሮ እና ለዘመናዊ እንባቢያን/ጸሓፊዎች ችግሮችን ፈጥሯል፡፡ ቅኔያዊ የአጻጻፍ ተፈጥሮው ፣ የቃላት ችግር ቢኖረውም፤ የአጻጻፉ የተፈጥሮ ተያያዥነት ምንም እንኳን ዋነው ጽሑፍ ወይም የቃሉ መልክ ቢጠፋም የቅኔው መስመሮች ላይ የሚገኘውን ግንዛቤ የሚገልጽ መንገድ ይፈጥራል፡፡ የትኛውም ዋና እውነት ሊጠገን በማይችል ሁኔታ የጠፋ የለም ምክንያቱም የእውነቶቹ ተያያዥነት እና እንደገና የሚጠቀሱበት ሁኔታ ስላለ ነው፡፡

ጽሑፋዊ እርማት ጠቃሚ (እንዲሁም አስፈላጊ) ነው፤ ነገር ግን ሁልጊዜ በግምት ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡ እዚህ ላይ ነው የተለያዩ የጥንት እትሞች የሚጠቅሙት፤ እነዚህን የሚያጨቃጭቁ የቅኔ መስመሮች ሌሎች የጥንት ተርጓሚዎች እንዴት እንደሚያዩዋቸው ለመገንዘብ ይጠቅማሉ፡፡

# ሆሴዕ 1
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|
| 1:1 | ከበላይ የሚጻፍ<br>1:1 | 1:1 | ርዕስ<br>1:1 |
| የሆሴዕ ቤተሰብ | ሆሴዕ ጋለሞታ ሴት ጎሜርን አግብቶ ሦስት ልጆችን ወለደችለት በትንቢታዊ መልኩ አድፈላጊ ስሞች ናቸው | የሆሴዕ ሚስትና ልጆቹ | የሆሴዕ ጋብቻ፡-ሦስት ልጆቹ |
| 1:2-3 | 1:2-3 | 1:2 | 1:2 ሀ |
| | | 1:3-5 | 1:3-5 |
| 1:4-5 | 1:4-5 | | |
| 1:6-7 | 1:6-7 | 1:6-7 | 1:6-7 |
| 1:8-9 | 1:8-9 | 1:8-9 | 1:8-9 |
| የእስራኤል መታደስ | የእስራኤል ቅጣት የመጨረሻ አይደለም | የእስራኤል መታደስ አለባት | የወደፊት ተስፋ |
| 1:10-2:1 | 1:10-2:1 | 1:10-2:1 | 1:10-2:1 |
| | | | 2:1-3 |

### የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ vii ተመልከት)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

*ተመስጧዊ ባይሆኑም፣ የአንቀጽ ምድቦች የሚከተለውን የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ ለመረዳት ቁልፍ ናቸው። እያንዳንዱ ዘመናዊ ትርጉም አንቀጾቹን መድቦ ማጠቃለያውን እንዲያቀርብ ተደርጓል። እያንዳንዱ ቅጂ ያንን ርዕስ በራሱ የተለየ መንገድ አጽዕሮቱን አስፍሯል። ጽሑፉን ስታነበው፣ የትኛው ትርጉም በርዕስ ጉዳይም ሆነ በቁጥር ምድቦች ከአንተ መረዳት ጋር እንደሚስማማ ራስህን ጠይቅ።

በእያንዳንዱ ምዕራፍ በቅድሚያ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ይኖርብናል፣ እንዲሁም ርዕሰ ጉዳዮቹን መለየት (አንቀጾቹን) ። ከዚያም የእኛን መረዳት ከአዲሶቹ ትርጉሞች ጋር ማወዳደር አለብን። መጽሐፍ ቅዱስን ልንረዳ የምንችለው የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ ምን እንደሆነ የሱን አመክኖአዊ (ሎጂክ) እና አቀራረቡን ስንረዳ ነው። ዋነኛው ጸሐፊ ብቻ ነው ተመስጧዊው— አንባብያን መልዕክቱን ለመቀየርም ሆነ ለማሻሻል መብት የላቸውም። የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢዎች ተመስጧዊውን እውነት በየዕለቱና በሕይወታቸው ሁሉ ተግባራዊ ለማድረግ ኋላፊነት አለባቸው።

**ማስታወሻ፡- ሁሉም ሙያዊ ቃላትና አጽሕሮተ ቃላት በሙሉ በቅጥያ አንድ፣ ሁለት፣ እና ሦስት ላይ ተብራርተዋል።**

---

5. የመጀመሪያው አንቀጽ

6. ሁለተኛው አንቀጽ

7. ሦስተኛ አንቀጽ

8. ወዘተርፈ

## አውዳዊ እይታ

ሀ ከምዕራፍ 1-3 ያለው የመጀመሪያው ቀጥተኛ ክፍል የሚገልጻቸው
1. ሆሴዕ በእግዚአብሔር ምሪት ጎሜርን ማግባቱን ምዕራፍ 1 (በሦስተኛ ሰው የተነገረ) ፣የሕይወት ታርክ
2. የእስራኤል ለያህዌ (YHWH) አለመታመን ግጥማዊ አገላለጽ፣ምዕራፍ 2
3. ሆሴዕ በእግዚአብሔር ምሪት ዋጋ በመክፈል ጎሜርን ዳግመኛ አገባት፣ ምዕራፍ 3 (በአንደኛ ሰው የተነገረ፣የግል ሕይወት ታርክ)

ለ የእያንዳንዱ ሦስቱ ንዑስ ክፍሎች ማጠቃለያ የታሐድሶ ቃል ኪዳን ነው፡፡

1 1:10-2:1

2 2:16-23

3 3:5

ሐ የእስራኤል ጣዖትን ማምለክ ሕግን መጣስ ብቻ ሳይሆን ፍቅርንም ጭምር፣ ቃል ኪዳን እንደ.ጋብቻ ቃልኪዳን መሆኑን የሚገልጽ ጥሩ ምሳሌ ነው!

## የቃላት እና ሐረግ ጥናት

**ሆሴዕ: 1:1**

**1 በይሁዳ ነገሥታት በዖዝያንና በኢዮአታም በአካዝና በሕዝቅያስም ዘመን በእስራኤልም ንጉሥ በዮአስ ልጅ በኢዮርብዓም ዘመን ወደ ብኤሪ ልጅ ወደ ሆሴዕ የመጣ የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነው::**

1:1 **"የእግዚአብሔር ቃል"** ይህ ለነቢያት የተለመደ የመክፈቻ ሐረግ ነው (ከ250 ጊዜ በላይ በብሉይ ኪዳን ጥቅም ላይ ውሏል) (ማለትም፣ሆሴዕ፣ኢዮኤል፣ሚክያስ፣ሶፎንያስ፣ሐጌ፣ዘካርያስ፣እና ሚልኪያስ):: ነቢያት ከራሳቸው መረዳት እንደማይናገሩ ያሳያል፣ ግን ከሚያነሳሳቸው ከእግዚአብሔር መገለጥ ነው:: "ቃል" የሚለው አገላለጽ (BDB 182) የተነገረው ቃል ብቻውን ኃይል አለው ከሚለው ከእብራይስጥ አመለካከት ጋር ይመሳሰላል (ዝ.ከ. ዘፍጥ 1፤እሳ 55:11፤ዮሀ 1:1፣14፤ራዕ፤ 19:13)::

"ጌታ" ለሚለው አሞጽ 1:2 ላይ ያለውን የመለኮት ስሞች የሚለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት::

▣ **"ሆሴዕ"** ትርጉሙ "መዳን" ማለት ነው (BDB 448):: አንድ ሰው የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ስም የሆነውን ያህዌን ("YHWH፣") ፣"ቃሉ" በሚለው ላይ ከጨመረ "እያሱን" (ዝ.ከ. ማቴ፡ 1:21) ላይ ያገኛል::

"የብኤርልጅ" የስሙ ትርጉም "ምንጩ" (BDB 92) ስለ እርሱ የሚናውቀው ምንም ነገር የለም ስሙ በሌላ ክፍል ኬጢያዊው የዔሳው አማች እንደ ሆነ በ (ዝ.ከ. ዘፍጥ 26:34) ላይ ብቻ ይገኛል።

▣ **"በይሁዳ ነገሥታት በዖዝያንና በኢዮአታም በአካዝና በሕዝቅያስም ዘመን"** ከደቡብ መንግሥት የሆነው ነቢይ በእንዲህ ሁኔታ የይሁዳን መንግስታት በጥልቀት ስገልጽ ያልተለመደ ይመስላል::

የመንግስታቱ ዝርዝር ብዙ ዘመናትን የሚያጠቃልል ነው (ተጨማሪ መግለጫን ተመልከት፣ " የነገሥታት መከፋፈል ዘመነ መንግሥት") ።

ይህ የይሁዳ ነገስታት ዝርዝር ከኢሳይያስ መግቢያ ጋር ይመሳሰላል፣ ስለዚህ፣ ሆሴዕ የሰሜኑ ዘመነኛ ነቢይ መሆኑን ለማሳየት እየሞከረ እንደሆነ ያረጋግጣሉ:: እንደዚያውም ምናልባት የሚያሳየው።

(1) ሆሴዕ የመንግሰቱን መከፋፈል የሚቃወም እና ይሁዳ ብቻኛዋ የቃል ኪዳን ተስፋ እንደሆነች ያያት ነበር ወይም

(2) ይህ ቁጥር በኋለኞቹ የይሁዳ ጸሐፊዎች የተጨመረ ነው:: እንደ ብዙ መላምቶች በዘመነኛው እንደ ማይታወቅ ግልጽ ነው!

▣ **"በእስራኤልም ንጉሥ በዮአስ ልጅ በኢዮርብዓም ዘመን"** ሌሎች የእስራኤል ነገስታት አለመጠቀሳቸው የሚስደንቅ ነው (ማለትም፤ዘካርያስ፣ ሻሉም፣ ምናሔ፣ ጳካህያ፣ ጳቁሔ፣ ሆሴዕ):: ይህንን በማስመለከት ብዙ መላምቶች ነበሩ:- (1) ለጥቂት ጊዜ ነግሶ ከነበረው ከኢዮርብአም 2ኛ በኋላ የፓለቲካ አለመረጋጋት ነበር (ተጨማሪ መግለጫን ፣ የነገሥታት መከፋፈል ዘመነ መንግሥት"ተመልከት) ።) ፤ (2) ነቢዩ ለሁለቱም ነገስታት እየተናገረ ነው፤ ወይም (3) ይሁዳ ህጋዊ ዳዊታዊ መስመር ናት (ዝ.ከ. አሞጽ 9:11-15):: ለኢዮርብአም 2ኛ ታሪካዊ ዘመን መቸት አሞጽን መግቢያ ተመልከት፣ VI::

**ሆሴ: 1:2-5**

***2እግዚአብሔር መጀመሪያ በሆሴዕ በተናገረ ጊዜ፥ እግዚአብሔር ሆሴዕን፦ ምድሪቱ ከእግዚአብሔር ርቃ ታላቅ ግልሙትና ታደርጋለችና ሂድ ጋለሞታን ሴትና የግልሙትናን ልጆች ለአንተ ውሰድ አለው። " 3እርሱም ሄዶ የዴቤላይምን ልጅ ጎሜርን አገባ እርስዋም ፀነሰች ወንድ ልጅንም ወለደችለት። 4እግዚአብሔርም፦ ከጥቂት ዘመን በኋላ የኢይዝራኤልን ደም በኢዩ ቤት ላይ እበቀላለሁና፥ ከእስራኤልም ቤት መንግሥት እሽራለሁና ስሙን ኢይዝራኤል ብለህ ጥራው:: 5በዚያም ቀን በኢይዝራኤል ሸለቆ ውስጥ የእስራኤልን ቀስት እሰብራለሁ አለው።"***

1:2

NASB፣ NRSV፣

TEV "እግዚአብሔር ለመጀመሪያ ጊዜ በሆሴዕ በኩል ሲናገር

NKJV "እግዚአብሔር በሆሴዕ መናገር ሲጀምር"

NJB "ያህዌ በሆሴዕ ከተናገራቸው የመጀመሪያው"

G Campbell Morgan፣*ሆሴዕ*፣ገጽ 9-11፣ asserts that the ASV፣

"ያህዌ ለመጀመሪያ ለሆሴዕ ሲናገር፣"የጊዜ ቁልፍ ነው ሆሴዕን ለማየት፣ ሕይወቱን ወደ ኋላ ለመመልከት፣ቁ 2 ን የጻፈው ከምልከታ ጥቅም ነው:: ስለዚህ፣እርሱ ሲያገባት ጎሜር ታማኝ እንደ ነበረች ይናገራል፣ግን ታማኝ ሳትሆን ቀረች:: ስለዚህ፣ከእግዚአብሔር ቅድመ እውቅና፣ ምን እንደሚሆን ያውቅ ነበር እንደዚሁም ከሆሴዕ የኃለኞቹ ዓመታት እንደምንረዳው ስለ.ጋብቻው አሳዛኝነት ያውቅ ነበር (በተጨማሪ Gleason Archer፣*Encyclopedia of Bible Difficulties*፣ ገፅ 294- 295 እና *Hard Sayings of the Bible*፣ ገፅ 322-324 እይ)::

▣ **"ሂድ፣የጋለሞታን ሴት ውሰድ"** ያህዌ (YHWH) ለመጀመሪያ ወደ ሆሴዕ የላከው መልዕክት ሁለት ትዕዛዞች እና የሦስተኛው እንድምታ::

1. "ሂድ" (BDB 229፣ KB 246፣ትዛዛዊ ቃአል (*Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)* )
2. "ውሰድ" (BDB 542፣ KB 534፣ትዛዛዊታ አል (*Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)* )

3. "ልጆች ይኑርህ፣" ከአውዱ ይረዳል፡፡
እነዚህ ከጋብቻ እና ከልጆች ጋር የተገናኙ ትዕዛዞች፣ እግዚአብሔር ሆሴዕን የጠራው ወጣት በነበረበት ጊዜ እንደ ነበር ያሳያል፣ኮረዳ በነበረበት ጊዜ ሊሆን ይችላል (13-14 ባለው ዕድሜ)፡፡
"ጋለሞታ" የሚለው ቃል (BDB 276፣ KB 275) ብዙ ቁጥርን ያሳያል፣ ይህም በዕብራይስጥ (ውስጥ የሚገልጸው (1) ብዛቱን ወይም (2) ድግግሞሽ ሊሆን ይችላል።
የሚመስለው ወይ ከጣዖት አምልኮ ጋር የተያያዘ ግልሙትና (ዝ.ከ. 4:14፤ NET Bible) ወይም ደግሞ ከበዓል ባህላዊ ሁኔታ የተነሳ በእርሱ ዘመን በግልሙትና ድርጊት ውስጥ የሚትሳተፍ የታወቀች ሴት ሊትሆን ትችላለች (ቢያንስ ድንግልናን ለማረጋገጥ ከካህናት ጋር ግብረ-ሥጋ ግንኙነትት ማድረግ) እና ስለዚህ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ እንደጋለሞታ ትወሰዳለች፡፡
ይህ በብዙ ተንታኞች ዘንድ ክርክሮችን ኣስከትሏል፡፡

1. እንደ ኦሪገን አባባል ምንም እግዚአብሔርን የማይመለከት ነገር በቀጥታ መወሰድ የለበትም፣ ግን ይመናፈሳል /allegorized (followed Philo)፡፡
2. ጀርም እና ኢቢን እዝራ (ብዙ መምህራን) ይህንን እንደ ራኣይ ይተረጎሙታል
3. ካልቪን እና ኢ ጄ፡ ያንግ እንደ አልጎሪ ይተረጎሙታል
4. ማርቲንሉተር ጎሜር ታማኝ ሴት እንደሆነች እና መልዕክቱን ለማስተላለፍ ሆን ብሎ ድራማውን እንደሠሩት ይተረጉማል፡፡
5. ዊልሐውሰን (Wellhausen) ከጋብቻ በኋላ ግልሙትናን እንደ ጀመረች ይናገራል (KB ወደ ግልሙትና ወዳዘነበለች አንድ ትርጉም ይጠቅሳል")፡፡

*znh የሚለው ቃል* (BDB 275፣276) በሁለት መልኩ የሚገኘው (ግስ፣ስም) በቁጥር 2 ላይ አረት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል እንደዚሁም በተለያየ መልኩ ተተርጉሟል፡፡

1. NASB፣ NKJV - *ጋለሞታ*
2. NRSV - *ዝሙት አዳሪ*
3. TEV - *የማይታመን*
4. NJB - *ህገ ወጥ ወሲብን የምትፈጽም ሴት*

*የተረጋገጠ ያልተወሰነ ቃአል Qal* INFINITIVE ABSOLUTE እና *Qal* IMPERFECT*ያልተፈፀመ ቃአል አንድ ላይ የሚያረጋግጡት ትርጉም፡-*

1. *በተለመደ መልክ ዝሙትን መፈፀም (ተከታታይ)*
2. *ከዝሙት የተነሳ የአእምሮ ክስ ወይም ታላቅ ዝሙት (የኃጢአት ዓይነት)*

*መጣስ፣ታማኝ ፍቅር፣ ሕግን መተላለፍ ኣይደለም፣ የነቢዩ ማዕከላዊ መልዕክት ይሆናል፡፡*
ግሱ በ1:2 ውስጥ (ሁለትጊዜ) ፤ 2:5፤ 3:3፤ 4:10፣12፣13፣14፣15፣18 (ሁለትጊዜ) ፤ 5:3፤ 9:1 በ1:2 ውስጥ ያለው ስም (ሁለትጊዜ) ፤2:2፣4፤ 4:12፤ 5:4 እስራኤል አስደሳች ካልሆነው ፍርድ በፊት ሐጥኃተኝነት አይሰማትም ነበር፣ ግን ከተሰበረ ልብ ፍቅረኛ በፊት!
የጋብቻው ምሳሌ በያህዌ (YHWH) እና በእስራኤል መካከል ያለውን ጥልቅ የሆነ ግንኙነትት የሚገልጹ ሌሎች ቦታዎች በትንቢቶቹ ውስጥ አሉ (ዝ.ከ. ኤርም፤ሕዝ16፣እንደዚሁም ኤፌ 5:23-33)፡፡

▣ **"የግልሙትና ልጆች ይኑሪይ"** ለሦስቱ ልጆች ትንቢታዊ ስም ተሰጣቸው። ከጎሜር ግልሙትና የተነሳ ሁለቱ የመጨረሻ ልጆች የሆሴዕ ትክክለኛ ልጆች መሆናቸው እርግጠኛ ኣይደለም፡፡

▣ **"ምድሪቱ ከእግዚአብሔር ርቃ ታላቅ ግልሙትና ታደርጋለች"** እግዚአብሔር የነቢዩን አለመታመን ልምምድ እና እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ያለውን አለመታመን ምሳሌን እየተጠቀመ እንደሆነ ግልጽ ነው! ይሁን እንጂ፣ ትክክለኛ ዓላማው የያህዌን የተሰበረ ልብ እና ይቅር ባይነቱን ለመግለጽ ነው፡፡ የሆሴዕ ትልቁ እውነታ ያልተቆጠበ፣ ታማኝ እና ዘላ ቂ የእግዚአብሔር ፍቅር ነው!

በጎሜር እና በሆሴዕ የተገለጸው የእስራኤል እና የያህዌ ተመሳሳይነትን ስናስብ የሚመጣው ጥያቄ ጎሜር ከጋብቻ በፊት ታማኝ አልነበረችም ወይ? እንደዚያ ከሆነ ተመሳሳይነቱን እንዴት እናብራራለን?

1. አብርሃም እግዚአብሔር ሳይገለጥለት በፊት ሁር በነበረበት ጊዜ ከቤተሰቡ ጋር የብዛአ-አምላክ አምላኪ ነበረ (ዝ.ከ. ዘፍጥ 11)፡፡
2. እስራኤል ከዘፀዓት በፊት በጣዖት አምላኪነት ውስጥ ትሳታፍ ነበረች (ዝ.ከ. ዘፀ32 ወይም አሞ 5:25-27)፡፡

እስራኤል በተደጋጋም ጣዖት ያመለከችው ድርጊት በሙሴ ሲገለጽ "ከጣዖታቸው ጋር ዝሙት ይፈጽማሉ" (ለምሳሌ፣ 34:15፣16፤ዘዳግ 17:7፤ 20:5፣6፤ዘኁል 15:39፤ 25:1፤ዘዳግ 31:16) ይህ ሐረግ የለምለም አምልኮን በሚያመለክትበት ጊዜ ቀጥተኛ ዘይቤያዊም ነው፡፡
የተላዋጭ ዘይቤያዊ ዳራ ያህዌ (YHWH) እንደ ባል ሲሆን እስራኤል ደግሞ እንደ ሚስት ነበረች (ለምሳሌ፣ኢሳ 54:5፤ 62:4-5፤ኤርም2:2፤ 3:1፣6-9፣14፤ 31:32፤ሕዝ 16፤ 23፤ሆሴ 2:19)፡፡

1:3 "**ጎሜር**" በቢሉይ ኪዳን ውስጥ በዚህ ስም የተሰየሙ ሁለት ሰዎች ኣሉ፡፡ የኣያት ልጅ፣ የያፌት ልጅ (ዝ.ከ. ዘፍጥ 10:2፣3፤ I ዜና 1:5፣6)
የሆሴዕ ሚስት ስም ትርጉሙ እርግጠኛ ኣይደለም፣ ግን አንድ ዓይነት ተነባቢዎች ማለት"መጨረሻ፣" "ወደ መጨረሻ የደረሰ" (BDB 170)፡፡ የልጆቹ ስሞች እና የአባቷ ስም ዴቤላይም ምሳሌያዊ እንደሆነ ሁሉ ይህም ምሳሌያዊ ትርጉም ከሆነ ሊያስደንቅ ይችላል (ሩት ውስጥ ካለው ስም ጋር የሚመሳሰል)፡፡

▣ **"ዴቤላይም"** ይህቃል 3:1 ላይ ካለው"የዘቢቢ ጥፍጥፍ" BDB 84) ጋር ይመሳሰላል፡፡ "የበለስ አንኳር" ወይም "ዘቢቢ ጥፍጥፍ"" (BDB 179) ማለት ይቻላል፡፡ ዘቢቢ ጥፍጥፍ የከናዓኖች የወሊድ አምልኮ ሥርዓት አካል ነው (ዝ.ከ. ኤር 44:19)

▣ **"እርሷም ፀነሰች ወንድ ልጅም ወለደችለት"** ሆሴዕ የመጀመሪያው ልጅ አባት እንደሆነ በግልጽ ተቀምጧል፣ ዳሩ ግን ሌሎቹ ሁለቱ አይደሉም፡፡

**1:4 "ብለህ ጥራ"** ይህ ግስ (BDB 894፣ KB 1128) ትዕዛዛዊ ቃአል (*Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)* ) ነው፡፡ ከእስራኤል ጋር የተገናኘ ትንቢታዊ ዓላማ በእነዚህ ልጆች ስሞች ውስጥ ይታያል፡፡

**"ሕዝራኤል" "ኢይዝራኤል"** ማለት "እግዚአብሔር ይበትናል፣"ማለት ነው "እግዚአብሔር ይዘራል፣" ወይም "እግዚአብሔር ምርታማ ያደርጋል፡፡" ስለዚህ ይህ ቃል ሊያሳይ የሚችለው (1) ፍርድ (ዝ.ከ. ቁ 4-5) ወይም (2) ብልጽግና (ዝ.ከ. 2:22-23)፡፡ እንደ አውዱ፣ #1 የታወቀው ትርጉም ነው፡፡

ከተማይቱንና የገሊላን ተፋሰስ ያሳያል (የአርማጌዶን ተፋሰስ)፡፡ ይህ የደቡቡ ከተማ (የኦሚሪህ ሁለተኛዋና ከተማ) የአሃብ ቤተሰብ በኢዩ (ዝ.ከ. II ነገስ 9:7-10:28) የታረዱበትን ቦታ ያመለክታል (ሚስቱ የወሊድ ጣዖት አምልኮን በእስራኤል ውስጥ ያስተዋዋቀች) ፣ እናም ለፍርድ ምሳሌ ወይም ፈሊጣዊ አነጋገር ነው፡፡

የታዘዘውን ስለፈፀመ ኢዩ ተቀጥቶ ነበር? ይህንን *Hard Sayings of the Bible*፣ IVP (ገጽ 235-236) ኢዩ እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ እና የአከአብን ቤተሰብ ጨረሳቸው፣ ዳሩ ግን የእግዚአብሔርን ቁጣ ሊያመጣ በሚችል መጠንና ልክ አደረገ፡፡

▣ **"ከጥቂት ዘመን በኋላ"** ይህንን ጊዜ የሚያመለክት ሐረግ (ሁለቱ ተዉላጠ ስሞች BDB 728 እና 589) ሰባት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፣ስድስቱ ፍርድን በሚያመለክቱ ምንባቦች ውስጥ (ዝ.ከ. (ዝ.ከ. II ነገሥ 9:7-10:28) ፣ 37:10፤ ኢሳ 10:25፤ኤርም 51:33፤ሆሴ 1:4፤ሃጌ 2:6)፡፡ አንደኛው አዎናታዊ አጠቃቀም ደግሞ ኢሳ 29:17፡፡

**1:5 "የእስራኤ ን ቀስት ይሰብራለሁ"** ቀስት ወታደራዊ ኃይልንና ጥንካሬን ያሳያል፡፡ ይህ የተፈፀመው በሻልማንሳር ፭ (ShalmanesarV) የሦርያ መንግሥት ግዛት ነበር፣ከክርስቶስ ልደት በፊት በ724 እስራኤልን ድል ያደረገው፣ ዳሩ ግን ከመጀመያው ተጠናክራ ያለችው የሰማርያ ዋና ከተማ ከክርስቶስ ልደት በፊት እስከ 722 ፣በሳርኬን ሁለተኛ (Sargon II) (ዘመነ መንግሥት ድረስ አልወደቀችም፡፡

## ሆሴዕ: 1:6-7

**6ደግሞ ፀነሰች ሴት ልጅንም ወለደች። እግዚአብሔርም፦ ይቅር እላቸው ዘንድ የእስራኤልን ቤት ከእንግዲህ ወዲህ አልምርምና ስምዋን ሎሩሃማ ብለህጥራት፡፡**
**7ነገር ግን የይሁዳን ቤት እምራለሁ በአምላካቸውም በእግዚአብሔር አድናቸዋለሁ እንጂ በቀስት ወይም በሰይፍ ወይም በሰልፍ ወይም በፈረሶች ወይም በፈረሰኞች አላድናቸውም አለው።"**

**1:6"ሎሩሃማ ብለህ ጥራት"** አሁንም ግሱ ትዕዛዛዊ ቃአል ነው?*Qa*ትዕዛዝ አንቀፅ የስሙ ትርጉም "ምህረትን ያላገኘች" ማለት ነው (BDB 520፣ዝ.ከ. 2:4፣23) "ሪህራሔ" (ወይም "መህረት" አስተውልNKJV ፤ "ርህራሔ" BDB ) ለእግዚአብሔር ጥልቅና ውስጣዊ ስሜት ጥቅም ላይ ውሏል (ዝ.ከ. መዝ 103:13) በ2:19፣23 ላይ በአዎንታዊ መልኩ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ የእግዚአብሔር ፍርድ የፍቅር መጓደልን አያሳይም፣ ተቃራኒው ነው (ዝ.ከ. 11:8-9፤ ዕብ 12:6-13)፡፡

▣ **"ይቅር ይላቸው ዘንድ"** ምን የሚያስደንቅ ዓላማዊ፣መጨረሻ የሌለው የእግዚአብሔር ፍርድ ነው፡፡ (ዝ.ከ. አሞ 8:7፤ 9:4)፡፡ አሁንም ይህ የመጨረሻ መልዕክት ብዙ ጊዜ በነቢያት ውስጥ ከመዳን እውነታ ጋር እኩል ነው (ዝ.ከ. ቁ 10-11)፡፡ ይህ በሰዋሰው ፊጹም ያለተወሰነ ቃአል (*Qal* INFINITIVE ABSOLUTE) (BDB 669) ባልተፈፀመ ቃአል ይከተላል (*Qal* IMPERFECT) (BDB 669) ፣ቁ 2ሐ ላይ ካለው ጋር ተመሳሳይ ቅርፅ አለው፡፡ ይህ ቅርፅ ግሱን ያጠነክራል (ለምሳሌ፣"ይቅር ይላቸው ዘንድ" )፡፡

**1:7 "የይሁዳን ቤት"** ሆሴዕ እንደ አሞጽ ለሁለቱም መንግሥታት ይናገራል (ዝ.ከ. 1:7፣ 11፤ 4:15፤ 5:5፣ 8-15፤ 6:4፣ 11፤ 8:14፤ 10:11፤ 11:12፤ 12:2)። እግዚአብሔር ይሁዳን ከአሦራውያን ወረራ ለማስመለጥ ቃል ገባ። በተለያየ አያሌ ጊዜያት ይህንን አደረገ፡፡ በዚህ ጊዜ አሦራውያን በፍልስጥኤም ላይ ምን ያህል ጊዜ ወረራ እንዳካሄዱ በትክክል አይታወቅም። ከዚህ የተነሣ ለእስራኤል ወሳኝ ነው፣ እንደ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች የይሁዳ ጸሐፊዎች በኋላኛው ዘመን የጨመሩበት ነው ዳሩ ግን፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ922 መከፋፈል የተነሣ እየተፈጠረ ያለውን የሰሜኑን ጎሣ እያወገዘ ነው። ሁሉም ነቢያት የሰሜኑን መንግሥት አውግዘዋል፣ በተለይ የዳንና የቤትኤልን የአምልኮ ሥፍራዎችን (ከወርቅ የተሠራ የጥጃ ምስል) በመቃወም፤ እንደዚሁም ይሁዳ የእስራኤልን መንገድ እንዳትከተል ማስጠንቀቅ ነው፣ ግን እነርሱ ተከተሉት (ዝ.ከ. ኤር 3:6-10)፡፡

▣ **"በአምላካቸውም በእግዚአብሔር አድናቸዋለሁ እንጂ በቀስት ወይም በሰይፍ ወይም በሰልፍ ወይም በፈረሶች ወይም በፈረሰኞች አላድናቸውም አለው"** እግዚአብሔር (BDB 446፣ KB 448፣የተፈፀመ ሂፊል (*Hiphil* PERFECT) እስራእል ከምትሸነፍባት ከወታደራዊ ኃይል ይሁዳን ይታደጋታል፣ ዳሩ ግን በተለመደ መንገድ ሳይሆን፣ ከተፈጥሮ ሕግ ውጭ በሆነው መንገድ (ዝ.ከ. II ነገስ 18:13-19:37፤ II ዜና 32:1-23፤ኢሳ 36-37)፡፡

## ሆሴ: 1:8-9

**8 ሎሩሃማም ጡት ባስጣለች ጊዜ፥ ደግሞ ፀነሰች ወንድ ልጅንም ወለደች። 9እግዚአብሔርም፦ሕዝቤ አይደላችሁምና፥ እኔም አምላክ አልሆናችሁምና ስሙን ሎዓሚ ብለህጥራው አለው።"**

**1:8"ጡት ባስጣለች ጊዜ...ደግሞ ፀነሰች"** ጎሜር እነዚህን ሦስቱን ልጆች በፍጥነት መፀነሷ መፍጠኗን፣ ተከታታይነት ያለው የግብረ-ሥጋ ግንኙነትትን ያንፀባርቃል፡፡

**1:9 "ሎዓሚ ብለህ ጥራው"** አሁንም ግሱ ትዕዛዛዊ ቃአል (*Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)* )። ይህቃል ሕዝቤ አይደለም" ማለት ነው (BDB 520፣ዝ.ከ. 2:23)፡፡ የተሰበረውን ቃል ኪዳን ያሳያል (ዝ.ከ. ኢያሱ 24:19-28፤ኤርም 31:32)።

| | |
|---|---|
| NASB፣ NRSV | "እኔ አምላካችሁ አይደለውም" |
| NKJV | "እኔ አምላካችሁ አልሆንላችውም" |
| TEV | "እኔ አምላካቸው አይደለውም" |
| NJB | "እኔ ለእናንተ አልሆንም" |

በ ማሶሬቲኩ ውስጥ የእግዚአብሔር ስም የለበትም (ዝ.ከ. NJB)፡፡ ይህ ሐረግ ቃል ኪዳን መሰበሩን በኃይል ያሳያል፡፡

## ሆሴ: 1:10-11

**10ይሁን እንጂ እስራኤላውያን ሊሰፈርና ሊቆጠር እንደማይቻል እንደ ባህር አሸዋ ይሆናሉ፤**
**"ሕዝቤ አይደላችሁም" በተባሉበት ቦታ፣ "የሕያው አምላክ ልጆች" ተብሎ ይጠራሉ፡፡**
**11የይሁዳ ሕዝብና የእስራኤል ሕዝብ እንደገና አንድ ይሆናሉ አንድ መሪም ይሾማሉ፤**
**አንድ ሆነውም በምድርቱ ይገኛሉ፤ የኢዝራኤል ቀን ታላቅ ይሆናልና፡፡**

**1:10 "እስራኤላውያን እንደ ባህር አሸዋ ይሆናሉ"** ዕብራይስጡ መጽሐፍ ምዕራፍ ሁለትን ምዕራፍ 1 ቁ 10 ላይ ባለው ይጀምራል፡፡ ይህ ለአብርሃም የተሰጠውን የእግዚአብሔርን ተስፋ ያሳያል (ዝ.ከ. ዘፍጥ 15:5፤ 22:17፤ 26:4) ይህ ቁጥር በቁ 9 ብርሃንም ቢሆን አሁንም ተስፋ እንዳለ ያሳያል (ዝ.ከ. ኤርም 31:33፤አሞ 9:8-15)፡፡ የእግዚአብሔር ምህረት ወደ አህዛቦች መድረሱን ለመግለጽ ጳውሎስ ይህንን ቁጥር በሮሜ 9:26 ላይ ተጠቅሞበታል፡፡ ሆሴ 2:23 ንም በሮሜ 9:25 ላይ ተጠቅሞበታል፡፡ የማይቆጠረው የእግዚአብሔር ሕዝብ የአዳም ልጆችን ሁሉ ያጠቃልላል!

▣ **"የሕያው አምላክ ልጆች"** ይህ ያህዌ አባት እንደሆነ የብሉይ ኪዳንን ዳራ ያንፀባርቃል፡፡ ይህ የእግዚአብሔር አባትነት በዘፍጥ 1-2 ላይ የተመሠረተ አይደለም፣ ዳሩ ግን አብርሃምን እና ዘሮቹን በራሱ በመምረጡ ነው፡፡
የቃል ኪዳን ህብረት ነው፡፡ በሁለት መልኩ ይታያል:-

1. "አባት" የሚለው ስያመ ወይም ምሳሌው፣ዘዳግ 32:6፤መዝ 103:13፤እሳ63:16፤ 64:8፤ኤርም 3:4፣19፤ 31:9፣ሚልክ 1:6፤ 2:10፤ 3:17
2. የ "ልጅ" ወይም "ሕፃን፣"ጥቅም ዘፀ 4:22፤ዘዳግ 14:1፤ 32:5፣19፤ኢሳ 1:2፤ኤርም 3:22፤ 31:20፤ሆሴ 1:10፤11:1

"ሕያው እግዚአብሔር፣ "የሚለው ሐረግ የያህዌ ስም ትርጉም ሥር ነው፡፡ ያህዌ ሕያው ነው፤ ጣዖታት አይደሉም!
አህዛቦች ወደ ቃል ኪዳን ሕዝብ ሲጨመሩ በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንደተስፋ ተወስደዋል (ዝ.ከ. ሮማ9:24-26 እና1ጴጥ 2:10)፡፡ ጥሩ ጽሑፍ "የእስራኤል አምላክ ማን ነው?"የሚለው*Hard Sayings of theBible* ፣ገጽ 633-636 ውስጥ ይገኛል፡፡ ምክንያቱም የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ተመርተው ብሉይ ኪዳንን ክፍል በመውሰድ ለአማኞች ተጠቅመዋል፣ የእግዚአብሔር ሕዝቦች "እናታችሁ ማን ናት" (ማለትም፣ውድድር)! ከማለት ይበልጥ፣ በክርስቶስ ስላላቸው እምነት ብዙ ይጠበቅባቸዋል፡፡

**1:11 "የይሁዳ ሕዝብና የእስራኤል ሕዝብ እንደገና አንድ ይሆናሉ"** ግሱ (BDB 867፣ KB 1062፣*Niphal* PERFECT) የእግዚአብሔር ሕዝብ ዳግም መሰብሰብን ማሳየት ይጠቅማል (ለምሳሌ፣ዘዳግ 30:1-10፤ኢሳ54:7፤ 56:8፤ኤርም 31:10-14፤ሚክ 2:12፤ 4:6):: ይህ ቁጥር እንደገና ተመልሰው በዳዊታዊ መንግሥት ሥር ተመልሰው አንድ እንደሚሆኑ ይናገራል (3:5፤ሕዝ 34:23፤ 37:15-28፤አሞ 9:11) ፣ መስህያዊ የሚያደረገው፡፡ ብዙዎች ይህንን ቁጥር የቁጥር 4 ተገላቢጦሽ የሆነ ተስፋ እንደሆነ ያዩታል፡፡ ኢዝራኤል የሚለው ቃል በዚህ ቁጥር "ፍሬያማነት" የሚል ሐሳብ አለው!

▣ **"አንድ መሪም ይሾማሉ"** በቁ 10 እና 11ሀ ላይ ያለውን እውነታ አስተውል፣እንደዚውም:: 11ለ ላይ የሰው ልጅ ምላሽ፡፡ እነዚህቃል ኪዳናዊ ሐሳቦች አንድ ላይ መሆን አለባቸው (ለምሳሌ፣ዘዳግ 17:14 ቁ 15) ሁለቱም እውነት ነው፣ ግን ይህ እንዴት እንዲህ ሊሆን ቻለ የሚለው ግልጽ አይደለም! ይሄ ሁለት ገጽታ ያለው የተለለያ ሰዎች መሳሳብ ነው ኃብቻን ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ኪዳን ትክክለኛ የሰው ልጅ ምሳሌ ያደረገው፡፡
"አንድ መሪ" የሚለው ከኢዮርብአም II ሞት በኋላ በትክክል ከእስራኤል አመራር ታሪካዊ እውነታ ጋር የሚቃረን ነው፡፡ ተከታታይ የሆነ ንግስና እና የፖለቲካ ቀውስ ነበር!

# ሆሴዕ 2

# የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|
| የማይታመኑ የእግዚአብሔር ሕዝቦች | እስራኤል በአደባባይ መከራ ታፍራለች እነዲሁም እነደጋለሞታ ትቸገራለች | ያልታመነች ጎሜር- ያልታመነች እስራኤል | ያህዌ እና ያልታመነች ሚስቱ |
| 2:2-5 | 2:2-13 | 2:2-5 | 2:4-7 |
| 2:6-8 | | 2:6-7 | |
| | | 2:8-13 | 2:8-15 |
| 2:9-13 | | | |
| የእግዚአብሔር ምህረትና ተስፋው | ጌታ እስራኤልን በስሜት ይስባታል | የእግዚአብሔር ፍቅር ለህዝቡ | |
| 2:14-20 | 2:14-23 | 2:14-17 | እርቅ |
| | | | 2:16-17 |
| | | 2:18-23 | 2:18-19 |
| | | | 2:20-25 |
| 2:21-23 | | | |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ vii ተመልከት)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ

2. ሁለተኛው አንቀጽ

3. ሦስተኛ አንቀጽ

4. ወዘተርፈ

## አውዳዊ እይታ

ሀ. ከቁጥር 1-15 ያለው ጣዖትን ማምለኳን ካለማቆሟ የተነሳ እግዚአብሔር ከእስራኤል መፋታቱን የሚገልጽነው፡፡
ለ. ቀሪዎቹ ምዕራፎች የእግዚአብሔርን የወዲያውኑ ዕቅዶቹን እና የወደፊት ዕቅዶቹ ላይ ያርፋል (በተደጋጋሚ"ስለዚህ" የሚለውን በመጠቀም)፡፡

1. የወዲያውኑ ዕቅዶች
   ሀ. ከ6-8 ያሉት ቁጥሮች ፣እግዚአብሔር እስራኤልን ጣዖትን ከማምለክ እንደሚያሰቆማት ("መንገድን ይዘጋባታለሁ")
   ለ. ከ 9-13 ያሉ ቁጥሮች፣ እግዚአብሔር የእስራኤልን የተደባለቀ የጣዖት አምልኮን እንደሚያሰቆም (ማስወገድ)
2. የወደፊት ዕቅዶች
   ሀ. ከ 14-20፣እግዚአብሔር እስራኤልን ዳግመኛ እንደሚያጽናናት እና እንደሚያገባት
   ለ. ከ21-23፣እግዚአብሔር የበረከት ቃል ኪዳኑን በተስፋይቱ እስራኤል ምድር ላይ እንደሚያፈስ

## የቃላት እና የሐረግ ጥናት

**ሆሴዕ: 2:1-9**

**1የእስራኤልም ልጆች ቍጥር እንደማይሰፈርና እንደማይቈጠር እንደ ባሕር አሸዋ ይሆናል እንዲህም ይሆናል**
**እናንተ ሕዝቤ አይደላችሁም ተብሎ በተነገረበት በዚያ ስፍራ የሕያው አምላክ ልጆች ይባላሉ።”**
**2"የይሁዳ ልጆችና የእስራኤል ልጆች በአንድነት ይሰበሰባሉ፥ ለእነርሱም አንድ አለቃ ይሾማሉ፥**
**ከምድሪቱም ይወጣሉ የኢይዝራኤል ቀን ታላቅ ይሆናልና። 3ወንድሞቻችሁን፦ዓሚ፥ እኅቶቻችሁንም ሩሃማ በሉአቸው።**
**4እናታችሁ ሚስቴ አይደለችምና፥ እኔም ባልዋ አይደለሁምና ተምዋገቱ ከእናታችሁ ጋር ተምዋገቱ።**
**ግልሙትናዋን ከፊትዋ፥ ምንዝርናዋንም ከጡቶችዋ መካከል ታስወግድ፡፡**
**5ዕራቁትዋን እንዳልገፍፋት፥ እንደተወለደችበትም ቀን እንዳላደርጋት፥**
**እንደምድረበዳና እንደደረቅ ምድር እንዳላደርጋት፥ በጥማትም እንዳልገድላት፡፡**
**6የግልሙትናዋ ልጆች ናቸውና ልጆችዋን አልምርም።**
**7እናታቸው አመንዝራለች የፀነሰቻቸውም። እንጀራዬንና ውኃዬን፥ ጥጤንና የተልባ እግሬን፥**
**ዘይቴንና መጠጤን ከሚሰጡኝ ከውሽሞቼ በኋላ እሄዳለሁ ብላ አስነወረቻቸው።!'**

**2:1 “በሉአቸው”** ይህቃል (BDB 55፣ KB 65) ትዕዛዛዊ ቃአል (*Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)* ) ፣የወደፊት ታድሶ እና ውህደትን ድርጊት በዘይቤያዊ አባባል የሚገልጽ ነው፡፡ ይህ ቁጥር ቀጣይ ካለው የመዳን ራዕይ ጋር ይሄዳል (1:10-2:1)፡፡

▣ ***“ዓሚ”*** *ይህ ማለት “ሕዝቤ” ማለት ነው* (BDB 766)፡፡ *ይህ ለእግዚአብሔር ሕዝብ የቃል ኪዳን ቃል ነው* (*ለምሳሌ፣ዘፀዓ* 6:6-7፤ 19:5-6) *ይህ የ*1:9 *ተገላቢጦሽ ነው* (*ዝ.ከ. ቁ* 23)፡፡

▣ ***“ሩሃማ”*** *ይህ ቃል ማለት “ተጽናናች፣” “ሩህሩህ፣” ወይም “ርህራሄ”* (BDB 933)፡፡ *ይህ የአስደናቂ ፍቅር፣ርህራሄ፣እና የእግዚአብሔር ምህረት መገለጫ ነው፡፡ ይህ የ*1:6 *ተገላቢጦሽ ነው* (*ዝ.ከ. ቁ* 23) ።

**2:2**

| | |
|---|---|
| **NASB** | **“ተሟገቱ...ተሟገቱ”** |
| **NKJV** | **“ጥያቄ አቅርቡ...ጥያቄ አቅርቡ”** |
| **KRSV፣ TEV** | **“ተከራከሩ...ተከራከሩ”** |
| **NJB** | **“ፍረዱ...ፍረዱ”** |
| **JPSOA** | **“ተቆጡ...ተቆጡ”** |

*ይህ ሕጋዊ ቃል ነው* (BDB 936፣ KB 1224፣*Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)* ፣በዚህ ቁጥር ውስጥ ሁለት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል) ለክስ (ዝ.ከ. 4:1-3፤ 12:2፤ኤርም 2:5-9፣ሚክ 6:1-8) ይህ ቁጥር የሆሴዕ ከጎሜር መፋታት ምሳሌ ነው (ዝ.ከ. ዘዳግ 24:1-4) በአካዲያን ስነ-ጽሑፍ (Akkadian literature) ውስጥ ተመሳሳይ የፍቺ አካሄዶች ኣሉ፡፡ የሆሴዕ የጋብቻ ስምምነት አስፈላጊነት ጥቅም በእግዚአብሔር እና በእስራኤል መካከል ያለውን ተመሳሳይነት በኢሳ 50:1፤ 54:4-8፤ኤርም 3:1-20፤ሕዝ 16 እና 23፤ማቴ 9:15፤ዮሀ 3:29፤ኤፌ 5:22-33፤ራኣይ 19:7-9፤ 21:9፤ 22:17፡፡ ሆሴዕ ከእናታቸው ጋር እንዲከራከሩ ለልጆቹ ጥሪ ያቀርባል (የእስራኤል ብሔር) ወደ ፍቺ የሚወስዳትን ድርጊት (ለምሳሌ፣ጣዖትን ማምለክ) ለማቆም (lit *“መተው”* BDB 693፣KB 747፣*Hiphil* JUSSIVE)፡፡

ይህ የወላጅ እና የልጆች ምሳሌ በዘፀ20:5፤ዘዳግ5:9-10 ውስጥ ካለው ትውልድ አቀፍ ከሆነው ሐሳብ ጋር የሚያያዝ ከሆነ ሊያስደንቅ ይችላል፡፡ ክፋት እና አመፃ ቤተሰብን ይከተላል (ከሦስት እስከ አራት ትውልድ) ፣ደስ የሚል ግን ይቅርታ ማግኘት ይቻላል እሱም ብዙ ትውልድን ይከተላል (እስከ *መቶ* ትውልድ፣ዝ.ከ. ዘዳግ 7:9)!

▣ **“ከእናታችሁ ጋር”** ይህ ቁጥር ለእስራኤል ከተነገረው ከሕጋዊ ፍቺ ጋር ይመሳሰላል፡፡ ብዙ ጊዜ ኣገር አቀፋዊ ኣለመታመን ከአባት ሐጢኃት ጋር ይያያዛል፣ እዚህ እና በኢሳ 50:1፤ሕዝ 16 ውስጥ ግን ከእናት አለመታመን ጋር ይያያዛል! ቃል ኪዳኑ ሊሰበር የቻለው በተደጋጋም ካለመታመናቸው የተነሳ ነው!

▣ **“እናታችሁ ሚስቴ ኣይደለችም፣ እኔም ባሏ አይደለሁም”** ይህ ሕዝባዊ የሆነው ቀላል የአዋጅ ንግግር ምናልባት በጥንታዊቷ ቅርብ ምስራቅ ሕጋዊ የፍቺ ማስተዋዋቅ አካሄድ ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ፣ እዚህ አውዱ አጥብቆ የሚያቀርበው ፍቺ ብቸኛ ስጋት እንደሆነ ነው ምክንያቱም እሷ (እስራኤል) የምትመለስ ከሆነ ባሏ (YHWH) ጥሪ ሊያደርግላት ተገዷል (ዝ.ከ. ቁ 3)፡፡

▣ **“ታስወግድ”** ይህ ግስ (BDB 693፣ KB 747፣*Hiphil* JUSSIVE) “እንዲትመለስ፣” ይሆናል
በዘዳግ 7:4 ላይ እንዳለ አሞጽ ውስጥ እግዚአብሔር የእስራኤልን አምልኮ እንደ ናቀ ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል (ዝ.ከ. አሞ 5:23)፡፡ ሆሴዕ ግሱን በተደጋጋሚ ይጠቀምበታል (ዝ.ከ. :2፣17፤ 4:18፤ 7:14፤ 9:12) አውድ ሁሉም ነገር ነው!

▣ **“ምንዝርናዋ ከጡቶቿ መካከል ነው”** ይህ ሊያመለክት የሚችለው (1) የወርቅ አምባር እየለየ(ዝ.ከ. ኤር 4:30) ወይም
የጣዖት አመንዝሮች የሚያድርጉትን ያሳያል (ዝ.ከ. 2:13፤ቃል በቃል “ቅዱስ ነገር”) ወይም በቀጥታ በርሷ ላይ ሰልጥኖ ያለውን ወንድ ፍቅረኛዋን (ማለትም፣ “ከፊቷ ላይ”፤ “ከጡቶቿ መካከል”)፡፡

**2:3 “እዕራቁትዋን እንዳልገፍፋት፥** እዕራቁትነት በዘዳግ 28:48 (ዝ.ከ. ኤር 16:39፤ 23:29) ውስጥ የቃልኪዳንን አለመታዘዝ ውጤት ነው)፡፡ ይህ የፈታችውን ሴት በይፋ የማባረር እና እራቁትዋን የማድረግ ባህል(ዝ.ከ. ሕዝ 16:35-42) በሽክላ ላይ ተጽፎ ይገኛል፣ሁለቱም ከሀና እና ከኑዚ፣

ከክርስቶስ ልደት በፊት 1500 ይህ የሚያመለክተው (1) የተፈታች እና ወደ ባርነት የምትሄድ መሆኗን ወይም (2) የምድሩ ፍሬ አለመስጠት (በዘዳግ 27-29 ያሉ መርገሞች) እርሷ በተደጋጋም ዝሙት ከማድረጓ የተነሳ።

▣ **"እንደ ምድረ በዳ እንዳላደርጋት"** ቀሪው የቁ 3 ክፍል በእስራኤል ላይ ሊመጣ ካለው ኪቃል ኪዳን መርገሞች (ዝ.ከ. ዘዳግ 27-20) ስለአንዱ ይገልጻል። የለምነት ምንጭ ባዖል ሳይሆን ያህዌ (YHWH) ነው! እርሱ የበረከት ተስፋ እንደ ነበር ሕዝቡ ሁሉ እንዲያውቅ እና ወደ ራሱ ሊጠራቸው ከሚጠቀምበት ከእግዚአብሔር መንገዶች አንዱ ነው፡፡ የአብርሃም ዘሮች የቃል ኪዳን መታዘዝ ከማጣት የተነሳ ይህ እንዳይሆን እንቅፋት ሆኑ። ሰለዚህ፣ይህ የበረከት ተስፋ ለጊዜው ሳይሆን ቀረ፣ዳሩ ግን ለዳግም ምፃዓት ጊዜ ዳግመኛ ፀድቋል (ዝ.ከ. አሞ9:13-15፤ ኢዮኤ 3:18) ።

**2:4 "ልጆቿን አልምርም"** ይህ ተመሳሳይ ቃል ነው (BDB 933) በቃልደረጃ (KB 1216፣*Piel* IMPERFECT) በ1:6 ውስጥ ይገኛል፣ ይህም የጎሜር ሁለተኛ ልጅ ስም ነው፡፡ በ2:19፣23 ውስጥ በአሉታዊ ሳይሆን፣በአዎናታዊ መልኩ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡
በፍርድ እና በበረከት መካከል ያለው ማመንታት የእግዚአብሔር ልብ አመለካካት መቀያየሩን (anthropomorphic) የሚገልጽ ይመስላል፡፡
እርሱ ሊባርክ ይሻል፣በረከት ግን በግል መታመንና እርሱን ልመምሰል ፈቃዳኝነትን የሚጠይቅ ነው!
"የግልሙትናዋ ልጆች ናቸውና" የእናት ጣዖት አምላኪነት (ዝ.ከ. ቁ5) ልጆችንም ይመለክታል፡፡ ልጆች እያናዳንዱን የእስራኤልን ሕዝብ ሲወክሉ (ዝ.ከ. The Jewish Study Bible፣ ገጽ 1146) ፣ሚስት ደግሞ ያልታመነችውን የእስራኤልን ሀገር ትወክላለች።

**2:5** እዚህ የእስራኤልን ምሳሌ ነው፣ ሁሌ የሲና ተራራ ቃል ኪዳን አምላክ፣ የያህዌ ሆኖ እያለ፣ ባአል እና አሴራ ምግብ፣ አልባሳት፣ እና ውድ የሆኑ ነገሮችን እንደሚያቀርቡላት ታስባለች (ዝ.ከ. ቁ8፤የዘዳግ27-29መርገሞች፤ኤር14:22) ያህዌ (YHWH) ቀናተኛ (የፍቅር ቃል) አምላክ ነው (ለምሳሌ፣ዘፀዓ 20:5፤ 34:14፤ዘዳግ 6:24፤ 5:9፤ 6:15) ።የአብርሃም ዘሮች ሌሎች አማልክቶችን በመከተል ያህዌን (YHWH) ቀናተኛ አደረጉት (ለምሳሌ፣ዘዳግ 32:16፣21፤መዝ 78:58)፡፡ በኋላ ላይ የሰሜኑ አሥር ጎሳዎች (Israel) እርሱን አስቀኑት (ለምሳሌ፣ሆሴ 2:8) እናም ይሁዳ (ዝ.ከ. 1 ነገስ 14:22፤ዘካ 1:14፤ 8:2) ።
በብሉይ ኪዳን ከወሲብ ጋር በተያያዘ የከናዓናዊያን አምልኮን በተመለከተ በመጽሃፍ ቅዱስ አዋቂዎች መሃከል ክርክር አለ፡፡ በከናዓን ውስጥ ወሲብ ተኮር የሆነ የለምነት ጣዖትን በተመለከተ ጥቂት የጽሑፍ መረጃ አለ። በሆሴዕ እና በኤርያስ ውስጥ ያለ ብዙዎቹ አነጋገሮች ቀጥተኞች ሳይሆኑ፣ዘይቤአዊ ናቸው፡፡ ይህ ትክክል ከሆነ እስራኤል እና የኃለኛዋ ይሁዳም የከናዓናዊያንን አይማኖት ኣበላሽቷል!

▣ **"ብላ"** በዚህ በተጠቀሰው ውስጥ የበአልን (Ba'al ) የአምልኮ *ሥነ-ሥርዓት* የሚያንፀባርቅ ድግግሞሽ አለ።

**2:6 "*መንገዷን በእሾክ አጥርባታለሁ*"**አጥር (BDB 962) ያገለግሉ የነበሩት (1) እንስሳትን ወይም ሰዎችን ከማሳ ለመጠበቅ ወይም (2) እንስሳት አንድ ቦታ እንዲጠበቁ ለማድረግ። ዘኁ 2 ከዚህ አውድ ጋር በደንብ ይገጥማል፡፡
በዚህ ቁጥር ውስጥ ሦስት ዘይቤአዊ ድግግሞሽ አሉ

1. *መንገድሽን በእሾክ አጥራለሁ* (BDB 962፣ KB 1312፣*Qal* ACTIVE PARTICIPLE)
2. *ግንቧን* (BDB 154፣ KB 180፣*Qal* PERFECT) ይከልላለው (COGNATE ACCUSATIVE)
3. *አምነቷን ልታገኝ አትችልም* (BDB 592፣ KB 619፣*Qal* IMPERFECT)

የእስራኤል እውነተኛ ባል ታማኝ እንዳልሆነ ወድያውኑ አይጥላትም፣ዳሩ ግን ባአልን ለማምለክ ያላትን መንገድ በመዝጋት ወደ ንስሐ ይመራታል ("ፍቅረኞቿ" የከናዓን ለምልም አማልክቶች እንደሆኑ ታስባለች)፡፡
በሌላ በኩል"ፍቅረኞቿ"የውጭ ኃይሎች ከሆኑ (and by implication of treaty rituals their gods) ይህ ቁጥር 5:13ጋር ይቀራረባል ኣስታውል ያህዌ (YHWH) አሁንም ንስዐ እና ታድሶን ይመኛል (ዝ.ከ. 5:15)! የያህዌ (YHWH) ፍርዶች ዓላማ ሁል ጊዜ መዋጀት ነው (ዝ.ከ. 3:5፤ 6:1፤ 14:1) ከውሽሞቹ በኋላ እሄዳለሁ ብላ አስነወረቻቸው።

**2:7 "በኋላ እሄዳለሁ በመጓጓት ኣሰድዳለሁ"** ሁለቱም (*Piel* PERFECTS) ናቸው፡፡ በሆሴዕ ውስጥ "ፍቅረኞቿ" (ዝ.ከ. ቅጽ 5) የበአል አምልኮን (Ba'al worship) ያመለከታሉ ቢሆንም፣ የፖለቲካ አንድነትንም የሚያመለክቱ ሊሆኑ ይችላሉ (ዝ.ከ. 5:13፣ NIDOTTE፣ ቅጽ 4፣ ገጽ 422-426 እይ) እርስዋም ፡-ከዛሬ ይልቅ የዚያን ጊዜ ይሻለኝ ነበርና ተመልሼ ወደ ቀደመው ባሌ እሄዳለሁ ትላለች።

▣ **"እርሷም፣ ከዛሬ ይልቅ የዚያን ጊዜ ይሻለኝ ነበርና ተመልሼ ወደ ቀድመው ባሌ እሄዳለሁ ትላለች"** በወቅታዊ ፍርዶች (ዝ.ከ. ዘዳግ 27-29) ውስጥ የእግዚአብሔር ዓላማ እስራኤልን ወደ ራሱ ለመመለስ ነበር፡፡ ብልጽግናቸው (ዝ.ከ. ቁ 21-23) የዓለምን ትኩረት ለመሳብ መንገድ እንዲሆኑ ነበር፡፡

## ሆሴዕ: 2:8-13

**8"ስለዚህ፥ እነሆ፥ መንገድሽን በእሾህ እዘጋለሁ፥ መንገድዋንም እንዳታገኝ ቅጥርን እቀጥርባታለሁ።**
**9ውሽሞችዋንም ትከተላለች፥ ነገር ግን አትደርስባቸውም ትፈልጋቸውማለች፥ ነገር ግን አታገኛቸውም እርስዋም፡-**
**ከዛሬ ይልቅ የዚያን ጊዜ ይሻለኝ ነበርና ተመልሼ ወደ ቀደመው ባሌ እሄዳለሁ ትላለች።**
**10እርስዋም እህልንና ወይንን ጠጅ ዘይትንም የሰጠኋት፥ ለበኣልም የተሠራውን ብርና ወርቅ ያበዛሁላት እኔ እንደ ሆንሁ አላወቀችም።**
**11ስለዚህ እህሌን በጊዜዋ፥ ወይን ጠጄንም በወረትዋ እወስዳለሁ፥ ዕራቁትነትዋንም እንዳትሸፍን ጥጤንና የተልባ እግሬን እገፍፋታለሁ።12አሁንም ውሽሞችዋ እያዩ ነውርዋን እገልጣለሁ ከእጄም ማንም አያድናትም።**
**13ደስታዋንም ሁሉ፥ በዓላቶችዋንም፥ መባቻዎችዋንም፥ ሰንበቶችዋንም፥ የተቀደሱትንም ጉባኤዎችን ሁሉ አስቀራለሁ።**

**2:8 "የሰጠኋት እኔ እንደ ሆንኩ አላወቀችም"** እግዚአብሔር የእርሱ ሙሽራ (ከቃል ኪዳን ሕዝቡ የሆኑ) ፍቅሩንና አቅርቦቱን ሳታውቅ ስትቀር ልቡ ይሰበራል (emphatic "እኔ") (ዝ.ከ. ኤር 14:22) ስለዚህ፣በ ቁ 9፣ያህዌ (YHWH) በረከቱንና ሕዝቡን በመስቀል ሰወረ (ዝ.ከ. ዘዳግ 27-29)፡፡

▣ ***"እህልንና ወይንን ጠጅ ዘይትንም"*** እነዚህ ሦስቱ ነገሮች የሕይወት መሠረታዊ ነገሮችን ይወክላሉ (ዝ.ከ. ዘዳግ7:13፤ 11:14፤ Joel 2:19) "ወርቅና ብር"በጣም ጠቃሚ የሆኑ የእግዚአብሔር ኣሐሶችን (ወይ በዘጸአት ውስጥ ውይንም በግብርና ብልጥግና ውስጥ) ጣዖታትን (ለምሳሌ፣ዘዳግ 29:17፤ኢሳ 40:19፤ 46:5-7፤ኤር 10:3-10) እና ጌጣጌጦችን ለመሥራት ይጠቀሙበት ነበር (ዝ.ከ. ቁ 13) በአል ክብር!

▣ ***"ለበአልም ተጠቀመችበት"*** "በአል" ታዋቂ የTyrian ለምለም አምልኮ አማልክት በኤልዛቤል በኩል ወደ እስራኤል የተጋባ በአል ማለት"አለቃ፣" "ባል፣" "ጌታ" እና የከናዓኖች የንፋስ አማልክት ስም ነው (አንዳንድ ጊዜ የጦር ወይም የውጊያ አማልክት) በብሉይ ኪዳን ሚስቱ አሼራ ወይም አስታሮት ትባላለች (በኡገራይት አፈታሪክ እሱ አይጥ ነው)
2:9-13 ይህ ከምርኮ መመለስን የሚያሳይ ይመስላል (ዝ.ከ. ሕዝ 16:35-43)

**NASB፣ NRSV፣**
**TEV፣ NJB** **"መልሼ ይወስዳለሁ"**
**NKJV** **"ይመልሳለሁ እናም ይወስዳለሁ"**

NKJV እዚህ በጣም ቀጥተኛ ነው ሁለት ግሶች አሉ፣ "ይመልሳለሁ" (BDB 996፣ KB 1427፣*Qal*
IMPERFECT) and "ይወስዳለሁ" (BDB 542፣ KB 534፣*Qal* PERFECT)፡፡ የመጀመሪያው ዋና ግስ ነው ወይም ለ"ንስዐ" የሚጠቀሙበት የዕብራይስጡ ቃል ነው እነርሱ ወደ ያህዌ (YHWH) አይመለሱም ስለዚህ እርሱ ወደ እነርሱ ተመለሰ እናም ስጦታውን ወሰደባት
(እህል፣ወይን ጠጅ፣ዘይት፣ውድ ብረቶች) ፣እርሱ ለሚስቱ በነፃ ና በፍቅር የሰጣት፡፡
በተሰጣት ነገር በመሳሳት ለበአል ዕውቅና ከመስጠቷ የተነሣ ስጦታውን መልሶ ወሰደባት (ዝ.ከ. ቁ 8)፡፡

▣ ***"መልሼ ይወስዳለሁ"*** ይህ ቃል (BDB 664፣ KB 717፣*Hiphil* PERFECT) ከአጥቂው ተጠቂውን ነጥቆ ለማውጣት ይጠቅማል (ለምሳሌ፣ 1 ሳሙ 17:35፤መዝ 50:22፤ ሆሴ 2:9፤ 5:14፤አሞ 3:12፤ሚክ 5:8፤ሕዝ 34:10) ይህ ተመሳሳይ ኃይለኛ በድጋም ቃል ቁ 10 ጥቅም ላይ ውሏል፣እዛ ቦታ ላይ"ማዳን" በሚል ተተርጉሟል (NASB፣ NRSV) የሌሉ የከናዓን ጣዖታትም ሆኑ የፖሊቲካ ቡድን እስራኤልን ከያህዌ (YHWH) ፍርድ አያድኗትም (ዝ.ከ. ቁ 10፤ 5:14) !

2:10 የእስራኤል "ፍቅረኞች፣" (1) ሕይወት የሌላቸው ጣዖታትም ሆኑ (2) የውጭ ድርጅቶች፣ ሊረዷት አይችሉም

▣
**NASB፣ NKJV** **"ሀፍረተ-ብስነት"**
**NRSV** **"ሀፍረት"**
**TEV** ------
**NJB** **"ውርደት"**

የቃሉ ትርጉም አይታወቅም (BDB 615፣ KB 664) *ሥሩ ካለመታወቁ የተነሣ የመጽሃፍ ቅዱስ አዋቂዎች ገምቷል* (KB 664)

1. አስጠልታ
2. መዋረድ
3. ሞኝነት

**2:11** የእስራኤል የጣዖት አምልኮ ሕይወት ያቆማል! መደበኛ፣አስደሳች የአምልኮ ጊዜያት፣እርሱን ለማስተዋወቅ በእግዚአብሔር የተሰጣት፣ተበላሸ እናም እንዲያስቆም ምክንያት ሆኑለት

**2:12 "ወይንዋንና በለስዋን ኣጠፋለሁ"** ነቢያት ለዘፀዓት ቃል ኪዳን በጣም ይጠነቃቃሉ እናም ብዙዎቹ ትንቢቶቻቸው በ ሌዋ26 እና ዘዳግ27-29 ውስጥ ስለሚገኙት መርገሞችና በረከት ክፍል ያወራሉ

▣ **እርሷም፡- 'ውሽሞቼ የሰጡኝ ዋጋዬ ይህ ነው ያለችውን'** ይህ የእስራኤል የከናዓን የለምልም አማልከቶች አምልኮ ጋር የሚያያዝ ዘይቤአዊ ቋንቋ ነው እስራኤል የምድሯን ለምለምነት ከእነዚህ አማልክቶች ጋር ታያይዛለች (ዝ.ከ. ቁ 13፣በአል - ወንድ፤አሼራ ፣አስታሮት (Astarte) - female) ያህዌ (YHWH) እውነተኛ የእስራኤል ባል እስከሆን ድረስ፣እርሷ ከሌሎች አማልክቶች ጋር የሚታደርጋው ህብረት እንደ"መንፈሳዊ" (እናም ከለምለም አማልክቶች ጋር በተያያዘ እውነታ) ዝሙት ወይም ለትዳር እንደ አለመታመን ይወሰዳል፡፡ David A Hubbard፣ሆሴዕ በ (Tyndale Old Testament Commentaries፣ p 79) ውስጥ "በለስ ተክል" (BDB 1061) እና "ዋጋ" (BDB 1071፣ዝ.ከ. 9:1) መካከል የሚጫወት ቃል አንዳለ ይገምታል፡፡ ዱርም አደርገዋለሁ፥የምድረበዳም አራዊት ይበሉአታል።

▣ **"ዱርም አደርጋለሁ የምድረ በዳም አራዊት ይበሉታል"** በምድረ በዳ ውስጥ ያደጉት ደንን በጣም ይፈሩታል ይህ ሐረግ ማለት የተታረሱ የእስራኤል ምድር ወደ ቀድሞ ሁኔታቸው ይመለሳሉ በዚህ አካባቢ አንስሳት ይበዛሉ እናም ይጎዳሉ ይህ የሚያመለክተው (1) እህልን ይጎዳሉ ወይም (2) ሰውን ይጎዳሉ (ዝ.ከ. 13:7-8)፡፡ በ #1 አውድ ከ በአሊም ጋር ይጣጣማል ለበኣሊም ያጠነችበትን ወራት እበቀልባታለሁ፥ይላል እግዚአብሔር፡-

**2:13 "የበአል ወራት"** እነዚህ የወሲብ በዓላት አከባበር እና ማስመሰል (ዝ.ከ. 4:13-14)፡፡ በአል የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር ነው፣ሊያመለክት የሚችለው በአል ይመለክ የነበረው በእያንዳንዱ ከተማና መንደር ባለው ቤተ-መቅደስ ነው፡፡ ወሰባዊ የበአል አምልኮ የከናዓኖች የእምነት ባህል ነበር ወይስ እስራኤዊያን የጨመሩበት ነው በሚል አሁንም ቢሆን በመጽሃፍ ቅዱስ አዋቂዎች መካከል ክርክር አለ!

**NASB** **"መስዋይት ያቀርባሉ"**
**NKJV፣ NRSV፣**
**TEV፣ NJB** **"የሚቃጠል እጣን"**

የግሱ (BDB 882፣ KB 1094፣*Hiphil* PERFECT) ትርጉም "ማቃጠል" ስለዚህ ሊያመለክተው የሚችለው (1) እጣን (ዝ.ከ. ኤር 11:13) ወይም (2) መስዋይት (ዝ.ከ. ኤር 7:9) በ 11:2ውስጥም ተመሳሳይ አሻምነት ይፈጠራል በI ነገስ 11:8ውስጥ ይህ ተመሳሳይ ቃል በተመሳሳይ ቅርፅ (*Hiphil* PERFECT) "መሰዋይት ለማቅረብ" (BDB 256፣ KB 261) ከሚለው ግስ ጋር በመስተጻምር ጥቅም ላይ ውሏል፣ሁለት የተለያዩ ድርጊትን የሚያሳይ የሚመስል: (1) እጣን እና (2) መስዋይት እንደዚህ ከሆነ፣ይህ ክፍል እጣንን ማመልከት አለበት፡፡

▣ **"በጉትቾችዋና በጌጥዋም"** ጉትቾች በተወሰነ ያህል ከዝሙት ጋር ይያያዛል (ዝ.ከ. ዘፍጥ 35:4፤ዘፀዓ 32:2)
ይህ ለአምልኮ ለመልበስ የተለመደ ድርጊት ነው አንደንዶች እንደሚያስቡት ለሦርያዊያን ቃላት ጉትቾች (ወይም የአፍንጫ ቀለበት) ማለት "ቅዱስ ነገር" እናም ይህ ጣዖታዊ ዝሙትን ያመለክታል 1በኤር 4:30፤ሕዝ 23:40-43 ውስጥም በዚህ መልኩ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በጉትቾችዋና በጌጥዋም እያጌጠች።

▣ **"ለዚህ እርሷ እኔን ረስታለች"** ይህ ሐረግ የሚያተኩረው! ያህዌ (YHWH) የታየው (anthropomorphically) ፈቃደኛ እንዳልሆነና፣እንደ ቀናተኛ አፍቃሪ ነው፡፡ በሰውኛ አባባል የእግዚአብሔር ስሜት በሰው ምርጫና ግርጊት ይነካል!
ጉዳዩ የግል ግንኙነትት ነው፣እዚህ እንደ ጋብቻ ቃል ኪዳን ይታያል፡፡ ያህዌ (YHWH) በአምሳሉ ከተፈጠረው ሰው ጋር ህብረትን ማድረግ ይፈልጋል፡፡ ይህ የተፈጥሮ ግብ ነው፡፡

## *ሆሴዕ*: 2:14-20

**14"እርስዋም፡- ውሽሞቼ የሰጡኝ ዋጋዬ ይህ ነው ያለችውን ወይንዋንና በለስዋን አጠፋለሁ ዱርም አደርገዋለሁ፥ የምድረ በዳም አራዊት ይበሉታል።**
**15እኔን ረስታ ውሽሞችዋን እየተከተለች፥ በጉትቾችዋና በጌጥዋም እያጌጠች ለበኣሊም ያጠነችበትን ወራት እበቀልባታለሁ፥ ይላል እግዚአብሔር፡-**
**16ስለዚህ፥ እነሆ፥ አባብላታለሁ፥ ወደ ምድረ በዳም አመጣታለሁ፥ ለልብዋም እናገራለሁ።**
**17 ከዚያም የወይን ቦታዋን፥ የተስፋ በርም እንዲሆንላት የአኮርን ሸለቆ እሰጣታለሁ**
**በዚያም ከግብጽ ምድር እንደ ወጣችበት ቀን እንደ ሕፃንነትዋ ወራት ትዘምራለች።**
**18በዚያ ቀን ባሌ ብለሽ ትጠሪኛለሽ እንጂ ዳግመኛ በኣሌ ብለሽ አትጠሪኝም፥ ይላል እግዚአብሔር**
**19የበኣሊምን ስም ከአፍዋ አስወግደዋለሁና፥ በስማቸውም እንግዲህ አይታሰቡምና።**
**20በዚያም ቀን ከምድር አራዊትና ከሰማይ ወፎች ከመሬትም ተንቀሳቃሾች ጋር ቃል ኪዳን አደርግላቸዋለሁ**
**ቀስትንና ሰይፍን ሰልፍንም ከምድሩ እሰብራለሁ፥ ተከልለውም እንዲኖሩ አስተኛቸዋለሁ።**

**2:14-19** የሚያስገርም ለውጥ በቁ 14 ተፈጠረ! የፍርድ አምላክ ተመልሶ የታማኝ ፍቅር አምላክ ሆነ ምን የመሰለ የማይረሳ ሰውኛ ተምሳሌት ነው ለእግዚአብሔር
የእስራኤል ቅዱስ፣የዘላለም ፈጣሪ የሆነው አምላክ የሰው ልጅ ቤተሰባዊ ህብረት ላይ በሚያተኩር መልኩ በሰውኛ ምሳሌ ራሱን ለሰብዓዊው ሰው ገለጠ እነዚህ ቤተሰባዊ ህብረት የወደቀው የሰው ልጅ አምላኩን እንዲረደ ያግዛል፣ የእርሱ ፍላጎትም ሊያውቀን እና ከእኛ ጋር ህብረት ለመፍጠር ነው!

2:14 "አባብላታለሁ" ይህ ግስ (KB 984) ፔይል ፓርቲሲፒል (*Piel* PARTICIPLE) ነው የቃሉ ትርጉም እርግጠኛ አይደለም፣መሠረታዊ ሐሳቡ ግን "ለማሳመን መግፋፋት" ወይም "ማሳመን" እነዚህን ሐሳብ በመጠቀም (1) ወጣት ፍቅረኖች እና (2) ትዕግስት (KB 985) በርግጥ የፍቅር ቃል ነው!
አዲሱ የህብረት ቃል ኪዳንም የሚታወቀው "አደርጋለሁ" በሚል ነው (ዝ.ከ. ቁ 14፣ 15፣ 17፣ 18፣19[ሁለት ጊዜ]፣ 20፣ 21[ሁለት ጊዜ]፣ 22[ሦስት ጊዜ])

▣ **"ወደ ምድረ በዳም አመጣታለሁ"** ምድረ በዳ ሊያሳይ የሚችለው
1. ከእስራኤል ጣዖታት የመለያ ጊዜ (ለምሳሌ፣ Hos 3:3)
2. እስራኤል በምድረ በዳ ውስጥ ያለ ሥራ የሚዞርበት ዘመን (ዝ.ከ. ቁ 15) ፣ከያህዌ (YHWH) ጋር በቅርበት የሚገናኙበት ሆኖ ያታያል በኋላ ላይ ጸሃፍቶች (rabbis) የእስራኤልእና የያህዌ (YHWH) የጫጉላ ሽርሽር ጊዜ ነበር ይላሉ (ለምሳሌ፣ 11:1-2፤ 13:4-5፤ዘዳግ 32:10-14፤ኤር 2:2-3)

▣ **"ለልቧም እናገራለሁ"** በመሠረቱ ይህ ግስ (BDB 180፣ KB 210፣*Piel* PERFECT) ማለት "መናገር፣"ግን ይህ ቃል ሰፋ ያለ ስነ-ፍቺ አለሁ በዚህ አውድ ያሚያመለክተው "በቅርበት ከአንዱ ልብ ለሌላው ልብ መናገር" ነው፡፡

**2:15 "የአኮርን ሸለቆ" "አኮር"** (BDB 747) ማለት "ጭንቀት/ችግር" ይህ አካን ኃጢአት ከመሥራቱ የተነሳ የእስራኤል ወራዊት በአይ የተሸነፈበት ሸለቆ ነው (ዝ.ከ. ኢያሱ 7) ይሁን እንጂ፣ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመግባት የመጀመሪያው ጊዜ ነበር (ማለትም፣ "እንደ ተስፋ በር") እናም

እግዚአብሔርም እነርሱ ወደ እርሱ ከተመለሱ፣ በሁሉ ከእነርሱ ጋር እንደ አዲስ እንደሚጀምር ያረጋግጥላቸዋል (ሁለተኛ መውጣትና የጫጉላ ሽርሽር ጊዜ፣ዝ.ከ. 11:1-4፤ 13:4-5)

**2:16 "በዚያን ቀን"** ይህ ወደ ፊት ሊመጣ ስላለው የያህዌ ስብዕና መገለጥ (ማለትም፣ መሲሕ እና የቃል ኪዳን ልጆቹ መታዘዝ) የዳግም ምፅዓት ፈሊጣዊ አነጋገር ነው (ዝ.ከ. ቁ 17፣18፣21)

▣ **"አይሺ"("Ishi")** ይህ ማለት "ባል" (BDB 35፣ለምሳሌ፣ዘፍጥ 2:23፤ኤር 31:32) እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ በቤተሰብ ቃል ይገለጻል (ማለትም፣ባል፣አባት፣ Go'el) ምክንያቱም እርሱ ስብዕና ያለው አምላክ ነው እናም ከሕዝቡ ጋርም የጠበቀ ህብረት እንዲኖረው ይፈልጋል እግዚአብሔር እንደ ባልም የ"ቅናት"ምልክት ያሳያል (ዝ.ከ. ዘፀዓ 20:5፤ 34:14፤ዘዳግ 4:24፤ 5:9፤ 6:15)

▣ **"በኣሌ"** ይህ "አለቃዬ፣" "የእኔ ባለቤት፣" "የእኔ ጌታ፣" "ባለቤት" (BDB 127፣ዝ.ከ. ኢሳ 54:5)
ያህዌ (YHWHism) እና በአል (Ba'alism) በግልጽ የተደባለቁበት ሁኔታ ነበር (የከናዓን የለምለም ጣዖት) : (1) በአል የሚለውን ቃል ያለውን የዮናታንና የሳኦል ልጆች ስም አስታውል (ዝ.ከ. 1 ዜና 9:40) ፤ (2) በእዮርባም II ዘመን የተገኘው የሰማርያ ልዩ መጽሐፍ (Samaritan Ostraca) ከበአል ስም የተሰየሙ አሥር ስሞችና ከያህዌ ስም (ዝ.ከ. ቁ 17) የተሰየሙ የሌዋውያን ስሞች አሉት፡፡ የያህዌ (YHWH) የፍቅር መግባት በአል እንዳደረገ ተደርጎ ይቆጠር ነበር (ዝ.ከ. ቁ 8) ይህ መቆም አለበት (ዝ.ከ. ቁ 9-13) !

**2:18 "በዚያም ቀን"** እግዚአብሔር የእስራኤልን የወደፊት ታድሶን ተስፋ እየሰጠ ነው (ዝ.ከ. ቁ 18-23) በ ቁ 16ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት "ቃል ኪዳን አደርግላቸዋለሁ" ከመጀመሪያውም ወሳኝ የዘላለም ቃል ኪዳን ነበራቸው (ለምሳሌ፣ዘፍጥ 15:18፤ 17:2፣4፣7፣9፣10፣11፣13፣14፣19፣21፤ኢሳ 24:5፤ 55:3፤ 61:8) ለምን አዲሱ አስፈለጋቸው (ዝ.ከ. ኤር 31:31-34፤ሕዝ 36:22-38)?ምክንያቱም ያህዌ (YHWH) ጨርሶ ታማኝነት የሌላትን ሚስቱን ፈቷታል (ማለትም፣የመጀመሪያው ቃል ኪዳን ተሰበረ) ፣ምርኮ እየመጣ ነበር (እንደ አሞራውያን (Amorites) ፣ዝ.ከ. ዘፍጥ 15:16 ከተስፋይቱ ምድር መነሣት)፡፡

## ልዩ ርዕስ፡ ኪዳን

የብሉይ ኪዳን ቃል የሆነው ቤሪዝ (BDB 136) ኪዳን፣ ለመግለጽ ቀላል አይደለም። በዕብራይስጥ የሚገጥም ግሥ የለውም። ሥርወ ቃላዊ ፍች ለማምጣት የተደረጉት ሙከራዎች ሁሉ የማያሳምኑ ሆነዋል። ሆኖም፣ የጽንሰ ሐሳቡ ማዕከላዊነት የቃሉን አጠቃቀም ይመረምሩ ዘንድ ሊቃውንትን አስገድዷቸዋል፣ ተግባራዊ ፍችውን ለመወሰን።

ኪዳን አንዱ እውነተኛው አምላክ የእሱ ፍጡር ከሆነው ሰው ጋር የሚደረግ ውል ነው። የኪዳን ጽንሰ ሐሳብ፣ ውል፣ ወይም ስምምነት የመጽሐፍ ቅዱስን መገለጥ ለመረዳት ወሳኝነት አለው። በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት እና በሰው ልጆች ነጻ ፍቃድ መካከል ያለው ክርክር በኪዳን ጽንሰ ሐሳብ በግልጽ ይታያል። አንዳንድ ኪዳናት የተመሠረቱት ግላዊ በሆኑ በእግዚአብሔር ባሕርይ እና ድርጊት ላይ ነው።

1. ተፈጥሮ ራሱ (ዘፍ 1-2)
2. የአብርሃም መጠራት (ዘፍ 12)
3. ከአብርሃም ጋር ኪዳን (ዘፍ 15)
4. የኖህ መጠበቅና ተስፋ (ዘፍ 6-9)

ሆኖም፣ የኪዳን ዋነኛ ባሕርዩ ምላሽን መፈለጉ ነው

1. በእምነት አዳም እግዚአብሔርን መታዘዝ ነበረበት፣ በኤደን ገነት መሐል ከሚገኘው ዛፍ መብላት የለበትም
2. በእምነት አብርሃም ወገኖቹን ትቶ፣ እግዚአብሔርን መከተል፣ እንዲሁም ስለ መጪው ዝርዮቹ ማመን ነበረበት
3. በእምነት ኖህ ትልቅ መርከብ ገንብቶ፣ ከውሃ ራቅ ያለ፣ እንስሳትን ማሰባሰብ ነበረበት
4. በእምነት ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብፅ አውጥቶ የተወሰኑ መመሪያዎችን ፣ ለሃይማኖታዊና ለማህበራዊ ሕይወት የሚሆኑ፣ የበረከትና የርግማን ተስፋዎችን መቀበል ነበረበት (ዘዳ 27-29)።

ተመሳሳይ የሆነ ክርክር እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ስላለው ግንኙነት "በአዲስ ኪዳን" ተመልክቷል። ክርክሩ በግልጽ የሚታየው ሕዝ 18ን ከሕዝ 36፡27-37 ጋር በማወዳደር ነው የያህዌ ድርጊት። ኪዳኑ የተመሠረተው በእግዚአብሔር የጸጋ ድርጊት ነውን ወይስ ለሰው በተሰጠ የውክልና ሃላፊነት? ይህ አንገብጋቢ ጉዳይ ነው፣ በብሉይ ኪዳን፣ በአዲሱም ጭምር። የሁለቱም ግቦች ተመሳሳይ ናቸው፡ (1) የጠፋው ኅብረት መመለስ፣ ዘፍ 3 እና (2) የእግዚአብሔርን ባሕርይ የሚያንጸባርቅ ጻድቅ ሕዝብ መመሥረት።

የኤር 31፡31-34 አዲስ ኪዳን ክርክሩን ያቃልላል፣ የሰዎችን ድርጊት ተቀባይነት ለማግኘት የሚደረገውን በማስቀረት። የእግዚአብሔር ሕግ ውስጣዊ መሻት ሆነ፣ ውጫዊ የሕግ ቁጥር ቀርቶ። መልካም፣ ጻድቅ ሕዝብ የመሆን ግብ በተመሳሳይ መልኩ ነው የሚቀረው፣ ነገር ግን ዘዴው (አገባቡ) ነው የተቀየረው። የወደቀው የሰው ልጅ የእግዚአብሔር አምሳል ነጸብራቅ ከመሆን ብቃት እንደሌለው ተረጋግጧል። ችግሩ ኪዳኑ አልነበረም፣ ነገር ግን የሰው ሃጢአተኝነትና ድካም ነው (ሮሜ 7፤ ገላትያ 3)።

ተመሳሳይ ክርክር በብሉይ ኪዳን ሁኔታዊ ያልሆነና በሁኔታዊ ኪዳናት መካከል እንዳለ ይኖራል፣ በአኪ። ደኅንነት በፍጹም ነጻ ነው በኢየሱስ ክርስቶስ የተፈጸመ ሥራ፣ ነገር ግን ንስሐና እምነትን ይጠይቃል (ሁለቱንም በመነሻነትም ሆነ በቀጣይነት)። እሱም ሁለቱም፣ ሕጋዊ ሥልጣናዊ አዋጅና ክርስቶስን ወደ መምሰል መጠራት፣ አመላካች መግለጫ ለተቀባይነትና አስፈላጊ ቅድስና! አማኞች በራሳቸው ድርጊት የዳኑ አይደሉም፣ ነገር ግን በመታዘዝ (ኤፌ 2፡8-10)። እግዚአብሔርን በመምሰል መኖር የመዳን ማስረጃ ነው እንጂ የመዳን ምክንያት አይደለም። ሆኖም፣ የዘላለም ሕይወት ሊስተዋሉ የሚችሉ ባሕርያት አሉት! ይህ ክርክር በዕብራውያን መጽሐፍ ላይ በግልጽ ይታያል።

▣ ይህ አዲስ ቃል ኪዳን ከእንስሳት እና ከምድር ጋር በኢሳ 11:6-9 and Rom 8:16-25 ሆሴዕ ውስጥም
"ቃል ኪዳን" የሚለውን ቃል (BDB 136) ከማናቸውም ከ8ኛ ወይም ከ7ኛ ክ/ዘመን ትናንሽ ነቢያት ይበልጥ ይጠቅሳል (ዝ.ከ. ሆሴ 2:18፤ 6:7፤ 8:1)፡፡

▣ **"ቀስትንና ሰይፍን ሰልፍንም ከምድሩ እሰብራለሁ፥"** ጦርነትን ማስቆም ከእግዚአብሔር ብቻ ይመጣል፡፡

የወደቀው የሰው ልጅ ለግጭት እና ለቁጣ አዝማሚያን ያሳያል አለመኖሩ አዲሱን የቃል ኪዳን ቀንን ያመለክታል (ለምሳሌ፣መዝ 46:9፤ኢሳ 2:4፤ሚክ 4:3-4፤ዘካ 9:10)

▣ **"ተከልለውም እንዲኖሩ አስተኛቸዋለሁ"** "አስተኛቸዋለሁ" የሚለው ቃል አሻሚ ነው ሊያሳየው የሚችለው (1) እስራኤል (ዝ.ከ. ቁ 18a) ፤ (2) እንስሳትን (ቁ 18b-d) ፤ ወይም (3) በእንስሳትና በሰው ልጆች መካካል ያለውን ህብረት በኤደን እንደ ነበር (ዝ.ከ. ዘፍጥ2)፡፡
2:19-20 ሰባት አዲሱ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ባህርያት፡-

1. ቋሚ ነው
2. ጽድቅ ነው
3. ፍትህ ነው
4. ታማኝና እውነት ነው (ማለትም፣*hesed* ዝ.ከ. 4:1)
5. የሚራራ ነው
6. የሚታመን ነው (ዝ.ከ. 4:1)
7. ስብዕና ያለው ህብረት ነው (ማለትም፣ "ለ እኔ"[ሁለት ጊዜ] እና "ማወቅ")፡፡

እነዚህ ቁጥሮች እንደሠርግ ቃል ኪዳን ነው!

በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ያሉ ግሶች፣የመከናወኑን እርግጠኝነት የሚያጠነክሩ፣ትንቢታዊ ተፈፃሚዎች ናቸው፡፡
አሁንም"አጭሻለሁ"የሚለው በቁጥር 19 ውስጥ በተደጋጋም ጥቅም ላይ መዋሉን አስተውል (BDB 76፣ KB 91፣*Piel* PERFECTS) የራሱን *ሥራና* ብቃት (ማለተም፣መስሕ) መሠረት በማደረግ አዲሱን ቃል ኪዳን የጀመረና ሁኔታውን የሚያመቻች እግዚአብሔርነው!
ግቡ አሁንም ጻድቅ ሕዝብ ነው፣ ዳሩ ግን ለውጡ ከውስጥ ወደ ውጭ የሚሆን ነው፣ ውጫዊውን መስፈርት በመታዘዝ አይደለም፡፡ ምሳሌው ከሕጋዊ ስምምነት ወደ ኃብቻ ቃልኪዳን የሚለወጥ ነው!

**2:19 "ለእኔም እንድትሆኚ በመታመን አጭሻለሁ"** ግሱ (BDB 76፣ KB 91፣*Piel* PERFECT) በቁ 19-20 ውስጥ ሦስት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በ "ዋጋለመግዛት" የሚል እንድምታ አለው (ማለትም፣ጥሎሽ፣ዝ.ከ. ዘዳግ 28:30)፡፡ እዚህ የሚያሳየው ለሙሽራይቷ የሚሰጥ ስጦታን ነው (ማለትም፣የአዲስ ቃል ኪዳን ባህሪይ ነው)፡፡ የእግዝአበሔር ሕዝብ በራሱ (የቃልኪዳን መታዘዝ) ማግኘት የማይችለው ከውድ ባለቤቱ እንደስጦታ ቀረበለት!

▣ **"ለዘላለም"** በሆሴዕ ይህ ብቻኛ የኡላም (*'olam*) ጥቅም ነው። የሚቀጥለውን ልዩ ርዕስተ መልከት፡፡

## ልዩ ርዕስ፡ ኦላም (ዘላለም)

ይህ የተለመደ (ከ400 ጊዜ በላይ ጥቅም ላይ የዋለ) ቃል ነው 'ኦላም (BDB 761፣ KB 798)። ጥቅም ላይ የዋለውም የጊዜን ወሰን ለማሳየት ነው፣ በብዙ መልኩ፣ እሱም እያንዳንዱ የግድ መያያዝ ያለበት የነገሮችን አፈጣጠር የሚያመላክተውን ነው።

ሀ. ያለፈ ጊዜ (ምሳሌ ብቻ)

1) "የድሮ ኃያላን፣" ዘፍ 6፡4
2) "ተራሮችና ኮረብቶች፣" ዘፍ 49፡21
3) "የጥንት ትውልዶች፣" ዘዳ 32፡7
4) "አባቶች፣" ኢያሱ 24፡2
5) "የጥንት ጊዜያት፣" ኢሳ 51፡9

ለ. እስከ ሕይወት ዘመን የሚቀጥል (ምሳሌ ብቻ)

1) "ባንተ ለዘላለም እናምናለን" (ማለትም፣ ሙሴ) ዘጸ 19፡9
2) "የዘላለም ባሪያ፣" ዘዳ 15፡17፤ 1ኛ ሳሙ 27፡12
3) "በዘመንህ ሁሉ፣" ዘዳ 23፡6
4) ሳሙኤል "ለዘላለም እዚህ ቆይ፣" 1ኛ ሳሙ 1፡22
5) ንጉሥ "ለዘላለም ይኑር፣" I ነገሥ 1:21፤ ነህ 2:3፤ መዝ 21:4
6) "እግዚአብሔርን ለዘላለም አመስግኑ፣" መዝ 115:18፤ 145:1-2
7) "ለዘላለም ዘምሩ፣" መዝ 89:1፤ 115:18፤ 145:1-2
8) "ለዘላለም በማጎፀን" (ዘይቤ)፣ ኤር 20፡17
9) ሊሆን የሚችል ምሳ 10፡25

ሐ. ቀጣይነት ያለው ሕላዌ (ግን ግልጽ ወሰኖች ያሉት

1) ሰዎች ለዘላለም ይኖራሉ፣ ዘፍ 3፡22
2) መሬት፣ መዝ 78:69፤ 104:5፤ 148:6፤ መክ 1:4 (II ጴጥ 3:10)
3) አሮናዊ ክህነት፣ ዘጸ 29:9፤ 40:15 (1 ሳሙ 2:30)
4) ጸባኦት፣ 31:16-17
5) የበዓላቱ ቀናት ዘጸ 12:14፣17፣24፤ ሌዋ 16:29፣31፣24፤ 23:14፣21፣41
6) ግርዘት ዘፍ 17:13 (ሮሜ 2:28-29)

7) የተሰፋይቱ ምድር ዘፍ 13:15፤ 17:18፤ 48:4፤ ዘጸ 32:13 (ዝ.ከ. ስደቶች)
8) የፈረሱ ከተሞች ኢሳ 25:2፤ 32:14፤ 34:10

መ. ሁኔታዊ ኪዳናት
1. አብርሃም፣ ዘፍ 17:7፣8፣13፣19
2. እስራኤል፣ ዘዳ 5:29፤ 12:28
3. ዳዊት፣ II ሳሙ 7:13፣16፣25፣29፤ መዝ 89:2፣4
4. እስራኤከ፣ መሳ 2:1 (ገላ ገላትያ 3)

ሠ. ሁኔታዊ ያልሆኑ ኪዳናት
1. ኖህ፣ ዘፍ 9:12፣16
2. አዲስ ኪዳን፣ ኢሳ 55:3፤ ኤር 32:40፤ 50:5 (ኤር 31:31-34፤ ሕዝ 36:22-30)

ረ. እግዚአብሔር ራሱ
1. የሱ ሕላዌ፣ ዘፍ 21:33፤ ዘዳ 32:40፤ መዝ 90:2፤ 93:2፤ ኢሳ 40:28፤ ዳን 12:7
2. የእሱ ስም፣ ዘጸ 3:15፤ መዝ 135:13
3. የእሱ ግዛት፣ ዘጸ 15:18፤ መዝ 45:6፤ 66:7፤ ኤር 10:10፤ ሚክ 4:7
4. የእሱ ቃል፣ መዝ 119:89፣160፤ ኢሳ 40:8፤ 59:21
5. የእሱ ደግነት፣ መዝ 25:6፤ 89:2፤ 103:17፤ 118:1-4፣29፤ ኤር 33:1

ሰ. የእሱ መሲሕ
1. የእሱ ስም፣ መዝ 72:17፣19
2. ለዘላለም የተባረከ መዝ 45:2፣17፤ 89:52
3. የሚገዛ፣ መዝ 89:36፣37፤ ኢሳ 9:7
4. ካህን፣ መዝ 110:4
5. ቀድሞ የነበረ፣ ሚክያስ 5:2

ረ. የአዲሱ ዘመን ሕይወት
1. የዘላለም ሕይወት፣ ዳን 12፡2
2. የዘላለም እፍረት፣ ዳን 12፡2
3. ከዚያም እንባ አይሆንም፣ ኢሳ 65፡19 (ራዕ 21፡4)
4. ፀሐይም አይኖርም፣ ኢሳ 60፡19-20 (ራዕ 21-23)

ምን ያህል የተለያዩ የእንግሊዝኛ ቃላት ጥቅም ላይ እንደዋሉ ተገንዘብ፣ የዕብራይስጡን ቃል ለመተርጎም፣ በአዓአት (አዲሱ ዓለም አቀፍ ትርጉም)
1. ዘላለም
2. የድሮ ድሮ
3. የማያልቅ
4. ዘላለማዊ
5. ማለቂያ
6. ዘወትር
7. ለሕይወት
8. የማያቋርጥ
9. መደበኛ
10. ቋሚ
11. ሁል ጊዜ
12. የጥንት፣ የጥንት ጊዜያት
13. ፍጻሜ የሌለው
14. ዓለም ዘላለም
15. እስከ ወዲያኛው
16. ረጅም ጊዜ
17. በድሮ ጊዜ

▣ **"በጽድቅ"** የዚህ ቃል ሥር ማለት "የመለኪያ ሽምበቆ" በእግዚአብሔር ሁሉ ነገሮች የሚፋረዱበት መመዘኛ ነው፡፡ ልዩ ርዕስ ጽድቅን በአሞ 2:6 ላይ ተመልከት፡፡

▣ "በደግነት"

## ልዩ ርዕስ፡ ደግነት (ሄሰድ*HESED)*

ይህ ቃል ሰፊ የፍቺ መስክ አለው። BDB በዚህ መልኩ ይመድበዋል (338-339)፡
ሀ. ከሰው ልጆች ጋር በተያያዘ ጥቅም ላይ ሲውል
1. ለሰው ሁሉ ደግነት (ምሳ 1ኛ ሳሙ 20:14፤ II ዜና 24:22)
2. ለደሀና ለችግረኛ ደግነት (ምሳ ሚክ 6፡8)
3. ማዘን (ኤር 2፡2፤ ሆሴ 6፡4)
4. ገጽታ (ኢሳ 40፡6)

ለ. ከእግዚአብሔር ጋር በተያያዘ ጥቅም ላይ ሲውል
1. የኪዳን ታማኝነት እና ፍቅር
   ሀ. "ከጠላቶችና ከችግሮች በመዋጀት" (ምሳ ኤር 31:3፤ እዝራ 27:28፤ 9:9)
   ለ. "ከሞት ሕይወትን መመለስ" (ምሳ ኢዮብ 10:12፤ መዝ 86:13)
   ሐ. "መንፈሳዊ ሕይወትን ለማቀላጠፍ" (ምሳ መዝ 119:41፣76፣88፣124፣149፣150)
   መ. "ከኃጢአት ለመቤዠት" (መዝ 25:7፤ 51:3)
   ሠ. "ኪዳኖቹን ለመጠበቅ" (ምሳ 2ኛ ዜና 6:14፤ ነህ 1:5፤ 9:32)
2. መለኮታዊ አስተዋጽዖን ለመግለጽ (ምሳ ዘጸ 34፡6፤ ሚክ 7፡20
3. የእግዚአብሔር ደግነት
   ሀ. "የተትረፈረፈ" (ምሳ ነህ 9:17፤ መዝ 103:8)
   ለ. "መጠነ- ታላቅ (ምሳ ዘጸ 20:6፤ ዘዳ 5:10፤ 7:9)
   ሐ. "ዘላለማዊ" (ምሳ 1ኛ ዜና 16:34፣41፤ II ዜና 5:13፤ 7:3፣6፤ 20:21፤ ዕዝራ 3:11)
4 የደግነት ድርጊቶች (ምሳ 2ኛ ዜና 6:42፤ መዝ 89:2፤ ኢሳ 55:3፤ 63:7፤ ሰቆ 3:22)

**2:20 "እግዚአብሔርን ታውቂአለሽ።"** እግዚአብሔር እንደ ግውዝ ነገር (object or idol) ፣አድርገን እርሱን እንድናውቅ አይፈልግም (BDB 393፣ KB 390) ፣ዳሩ ግን በቅርበት፣ በግላዊ ህብረ እንጂ፡፡ ለዚህ ነው ነቢዩ የጋብቻን ስምምነት ምሳሌ የተጠቀመው፡፡ የኃጢአት ክብደት ታማኝ ፍቅርን አንደመጣስ ይታያል፡፡ እግዚአብሔር እንደ ውድና ታማኝ ባለቤት ይታያል፣ዳሩ ግን ሁለተኛ ላይ፣እንደተነቃቃ ቀናተኛፍቅረኛ፡፡ "ማወቅ" የሚለው ቃል በዕብራይስጥ (Hebrew) ምክንያታዊ ውነታዎች ላይ አያተኮርም፣ግን በህብረት ላይ (ለምሳሌ፣ዘፍጥ 4:1፤ 19:8፤ዘኁል 31:17፣35፤መሳፍ 11:39፤ 21:11፤ I ሳሙ 1:19፤ I ነገስ 1:4፤ኤር 1:5) እግዚአብሔር ቤተሰብን ይፈልጋል!

## ሆሴዕ: 2:21-23

**21"በዚያንም ቀን እመልሳለሁ፥ ይላል እግዚአብሔር ለሰማይ እመልሳለሁ፥ ሰማይም ለምድር ይመልሳል፤ 22ምድርም ለእህልና ለወይን ጠጅ ለዘይትም ትመልሳለች እነርሱም ለኢይዝራኤል ይመልሳሉ። 23በምድርም ላይ ለእኔ እዘራታለሁ ምሕረትም የሌላትን እምራለሁ፥ ሕዝቤም ያልሆነውን፦ አንተ ሕዝቤ ነህ እለዋለሁ እርሱም፦ አንተ አምላኬ ነህይለኛል።!"**

**2:21-22** The VERB "እመልሳለሁ" የሚለው (BDB 772፣ KB 851፣*Qal* IMPERFECT) ግስ በሁለት ቁጥሮች ውስጥ አምስት ጊዜጥ ቅም ላይ ውሏል፡፡

መልሱ ያልታሰበ እና ሁኔታዊ ያልሆነ ነው (ለምሳሌ፣ኢዮኤል2:19)፡፡ ለግብርና ብልጽግና ተስፋየ ተሰጠ (ዝ.ከ. ዘዳግ 27-29) ፣ለቃል ኪዳን በመታዘዝ የሚወሰን አዲስ ቀን፣እየመጣነ ው (ዝ.ከ. ዘዳግ 27-29) ፣ ዳሩ ግን የቃል ኪዳኑ ሁኔታዎች ተላሏል፡፡ የወደቀው የሰው ልጅ ልብና መንፈስ በ"አዲስ ልብ" እና በ"አዲስ መንፈስ" (ዝ.ከ. ኤር 31:31-34፤ሕዝ 36:22-38) ተተክቷል፡፡ አሁንም ግቡ መታዘዝ ነው!
የመጀመሪያው የተፈጥሮ ዓላማ በእግዚአብሔር አምሳል ከተፈጠረው ከሰው ልጅ ጋር ህብረት ለማድረግ መነሻ ነበር (ዝ.ከ. ዘፍጥ 1:26-27) ያዓላማ ከሰው ልጅ አመፅ የተነሳ ተሰናከለ፡፡ የዘአመፅ ውጤት ፕላነቱንም ጎድቷል (ዝ.ከ. ሮማ 8:18-25)፡፡ ክርስቶስ የሆነው አዲሱ የመዳን ቃልኪ ዳን የተበላሸውን ማንነት ያድሳል፣ ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ህብረት እና መታዘዝ እንዲኖር ያደርጋል፡፡
ብሉ ይኪዳን ኤደናዊ (agricultural) በሆኑቃሎችይህንን አዲስን ዘመን ያሳያል፣አዲስ ኪዳን ግን ይህንን ምሳሌ ወደ "አዲስ ሰማይ እና አዲስ ምድር "ሰፋ ያደርጋል (ዝ.ከ. ኢሳ 55-66፤ራእይ 21-22)፡፡ ወሰኑ ፓልስታይን መሆኑ ቀረ፣ግንፕላነት!

**2:21 "ሰማይም"** ይህ ዝናብ የሚሰጠውን እና በምድር ዙርያ ያለውን ከባቢ አየርን ይመለከታል፡፡

**2:22 "ኢይዝራኤል"** ፣ "ኢይዝራኤል" የሚለው ቃልትርጉሙ "እግዚአብሔር ይዘራል፣"ስለዚህ፣በቁ 22 እና 23፣መካካል የቃላቶች ጨወታ አለ፣በ 1:4 እና 11 መካካል እንደ ነበር፡፡ ይህም የሆሴዕ የመጀመሪያ ልጁ ስም ነው፣አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ሊሆን የሚችለው (ዝ.ከ. 1:4)፡፡

**2:23 "እምራለሁ"** ይህ ሩሃማ የሚል ስምነው፣ ከሆሴዕ ልጆች አንዷ የሆነች (ዝ.ከ. 1:6) በአውዱ ውስጥ ሶስት ጊዜ ተጥቅሷል፣ቁ 19 እና 23 (ሁለትጊዜ)፡፡ ሌለኛዋ የሆሴዕ ልጅ የሆነችው ሎአሚ (Lo-Ammi) ፣ 1:9፣እንደዛው በቁ 23 ላይ እንደተጠቀሰች አስተውል፡፡
"አንተሕዝቤነህ አንተ አምላኬ ነህ" ይህተስፋ በሮማ 9:25 እና I ጴጥ 2:10 ውስጥ ለይሁዳ ብቻ ሳይሆን (ዝ.ከ. ኢሳ 11:9) ፣ሰፋበማድረግ ለሁሉም ሰው እንዲሆን ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

*goi* (BDB 156) እና *'am* (BDB 766) የሚሉ ብዙ ጊዜ ልዩ በሆነ የቃል ኪዳን ሐሳብ ውስጥ ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡
*የመጀመሪያው የሚያመለክተው ማንኛውንም ትውልድ፣ሕዝብ፣ወይም ማህበረሰብ ከተናጋርው ተለይቶ ያለውን (ማለትም፣የዛ ትውልድ ያልሆኑ፣ከውጭ የሆኑ፣ቃል ኪዳን የሌለ ሰው)፡፡*
ጨወታ አስተውል:-

1. 1:9፣እስራኤል *'am ኢይደለችም፡፡*
2. 1:10፣በሮሜ 9:24-26 እና 1ጴጥ 2:10 ውስጥ አሕዛቦችን (*goi*) በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ሕዝብ ውስጥ እንደሚያጠቃልል ጽሁፍ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡
3. 2:23፣ *ሐጥታተኛዋ* እስራኤል ተተወች፣ አሁን ግን ከእግዚአብሔር ምህረት የተነሳ ድጋም ተጠቃለለች፣ የእነርሱ *መታዘዝ* ወይንም *ታማኝነት* አይደለም፣ ግን በእግዚአብሔር ምህረት (ዝ.ከ. "እኔ አደርጋለሁ" ቁ 14-23ድጋም ጥቅም ላይ የዋለ)፡፡

**የምዕራፍ 1 እና 2 የውይይት ጥያቄዎች**

*ይህ የጥናት* <u>*መመሪያ*</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. በትክክል ሆሴዕ አመንዝራ ሴትን አግብቶ ነበር?
2. ለምንጋብቻ ለቃል ኪዳን እንደምሳሌ አገለገለ?

# ሆሴዕ 3

## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|
| እስራኤል ወደ እግዚአብሔር ትመለሳለች | የጎሜር መመለስ | ሆሴዕ እና ያለታመነች ሚስት | የሆሴዕ ጋብቻ ሁለተኛው ዘገባ |
| 3:1-5 | 3:1-5 | 3:1-5 | 3:1-5 |
| | | 3:2-5 | ማብራሪያ |
| | | | 3:4-5 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ vii ተመልከት)**

*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. *የመጀመሪያው አንቀጽ*
2. *ሁለተኛው አንቀጽ*
3. *ሦስተኛ አንቀጽ*
4. *ወዘተርፈ*

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**ሆሴዕ: 3:1-5**

**1እግዚአብሔርም፡- የእስራኤል ልጆች ወደ ሌሎች አማልክት ቢመለሱና የዘቢብ ጥፍጥፍን ቢወድዱ እንኳ፥ እግዚአብሔር እንደሚወድዳቸው አንተም ውሽማዋን የምትወድደውን አመንዝራይትን ሴት ውደድ አለኝ።" 2እኔም በአሥራ አምስት ብርና በአንድ ቆሮስ መስፈሪያ ተኩል ገብስ ገዛኋት። 3ከእኔ ጋር ብዙ ወራት ተቀመጪ፥ አታመንዝሪም፥ ለሌላ ሰውም አትሁኚ እኔም እንዲሁ እሆንልሻለሁ አልኋት።" 4የእስራኤል ልጆች ያለ ንጉሥና ያለ አለቃ፥ ያለ መሥዋዕትና ያለ ዓምድ፥ ያለኤፉድና ያለተራፊም ብዙ ወራት ይቀመጣሉና። 5ከዚያም በኋላ የእስራኤል ልጆች ተመልሰው አምላካቸውን እግዚአብሔርንና ንጉሣቸውን ዳዊትን ይፈልጋሉ በኋለኛውም ዘመን ፈርተው ወደ እግዚአብሔርና ወደ በረከቱ ይመጣሉ።**

**3:1"አንተም ውሽማዋን የምትወድደውን አመንዝራይትን ሴት ውደድ አለኝ።"** አስተውል ተናጋሪው ያህዌ (YHWH) ነው! ይህ ቁጥር በሁለት ትዕዛዛዊ ቃአል (*Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)* S) ይጀምራል፡፡

1. 1ሂድ (BDB 229፣ KB 246)
2. ውደድ (BDB 12፣ KB 17 [ይህ ግስ በዚህ አንዱ ቁጥር ውስጥ አረት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል])

አሁንም ያልታመነች እና ባሏን የፈታችውን ሴት እንዲወዳት ሆሴዕን እያዘዜ ነው፡፡ ሁለተኛው የ"ውደድ" ጥቅም *Qal* PASSIVE PARTICIPLE CONSTRUCT፣ የባልዬውን (ማለትም፣ሆሴዕ እንደያህዌ (YHWH) ምሳሌ) ቀጣይ ፍቅር የሚያሳይ!

ስለዚህች ሴት ማንነት ብዙ ክርክሮች አሉ፡፡

አንዳንዶቹ ጎሜርን ያመለክታል ማለት እንደመይቻል ያምናሉ እናም፣ ስለዚህ፣ሌላ ጣዖታዊ አመንዝራ ወይም የማትታመን፣ የፈታች ሴት መሆን አለባት፡፡

ይሁን እንጂ፣ ለእኔ፣ ምሳልያዊየ ሆነው የእግዚአብሔር ታማኝ ፍቅር ለእስራኤል ይህ ጎሜር መሆኑን ያረጋግጣል እናም "አሁንም" የሚለው ቃል (BDB 728) ወደዚህትርጉምራሱን ይሰጣል፡፡ በ 2:2 ውስጥ ያለው ሕጋዊ ፊቺ ትክክለኝነት ያለው ይመስላል፡፡ እንደባሪያ እስከምትሸጥ ድረስ ጎሜር አለመታመኗን ቀጥላ ነበር፡፡

▣ **"አሁንም"** የሚለውቃል (BDB 728) ጌታ ሁለተኛ ጊዜ ስለ ጎሜር ለሆሴዕ እየተናገረ እንዳለ ሊያመለክት ይችላል፣የማሶሬቲኩ ጽሁፍ ግን ያህዌ (YHWH) ለሆሴዕ ከተናገራቸው ቃላቶች ክፍል እንደሆነ ያሳያል፡፡ የ ማሶሬቲኩ ተጨማሪዎች መንፈሳዊ ምሪት ባይኖራቸውም፣ ጥንታዊቷ ይሁዳ ስለሥርዓተ-ነጥብ እና የቃላት አነባብ ያላትን ባህል ይወክላሉ፡፡ ይህ ጉዳይ ክፍት ሆኖ መቅረትአለበት!

NASB **"በባሏ የምትወደድ ሴት ውደድ"**
NKJV **"በፍቅረኛዋ የምትወደድ ሴት ውደድ"** [footnote፣ **"የወንድ ጓደኛወይም ባል"**]
NRSV **"ፍቅረኛያላትን ሴት ውደድ"**
TEV **"ከፍቅረኛ ጋር ዝሙት እየፈፀመች ላለች ሴት ፍቅርህን አሳይ"**
NJB **"ሌላ ወንድ የምትወድ ሴትን ውደድ"**

ቃሉ (BDB 945) አያሌ አጣቃቀም አለው፡፡ የተወሰኑ ምሳሌዎች፡-

1. ጓደኛ፣መሳፍ 14:20፤ሚክ 7:5
2. ተባባሪ ወይም ረዳት፣ዘካ 3:8
3. ፍቅረኛ፣መኃልይ 5:16
4. ባል፣ኤር 3:1፣20
5. ባልደረባ፣ኢዮብ 30:29

ለአመንዝራ ነጠላ ቁጥር የተለመደ አይደለም፡፡ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች የራሷን የጣዖት ፍቅረኛን እንደሚያመለክት ያስባሉ፡፡ የራሷ የቀድሞ ባሏን እንደሚያመለክት አስባለሁ (ማለትም፣ሆሴዕ)

▣ **"እግዚአብሔር የእስራኤልን ልጆች እንደሚወድዳቸው"** ይህ መውደድ ለሚለው ግስ ሦስተኛጊዜ ነው በቁ 1 ውስጥ (*Qal* INFINITIVE CONSTRUCT)፡፡ ይህ ወሳኝ ምሳሌ ነው!

"ወደ ሌሎች አማልክት ቢመለሱም እንኳ" ይህ (BDB 815፣ KB 937፣ *Qal* PERFECT) የያዕቆብ ዘሮች የከናዓናዊያን ለምለም አምላኪዎች (ዝ.ከ. ዘዳግ 31:18፣20) እንደሚሆኑ ለመናገር የተጠቀመበት ቃል ነው፡፡ ያህዌ (YHWH) ራሱ ከእነርሱ ጋር ተናግሯል ወደዚህ ፈተና እንዳይገቡ (ዝ.ከ. ሌዋ 19:4፤ 20:6)፡፡

▣ **"እናም የዘቢብን ጥፍጥፍ ቢወድዱ"** ይህ መውደድ ለሚለው ግስ አረተኛ ጊዜ ነው (*Qal* PERFECT) ፣እንዴት እስራኤላዊያን የበአልን አምልኮ እንደተቀላቃሉ በመግለጽ፡፡ እነዚህ በጥንቃቄ የተሠሩ ከመስዋይት በኋላ ለአምላኪዎች ይሰጣል (ዝ.ከ. II ሳሙ 6:19) በኢሳ 16:7 እናኤር44:19 ውስጥም የለምለም አምልኮነገሮችን ያሳያሉ (also possibly ኤር 48:31)፡፡

**3:2 "ለራሴ ገዛኋት"** "ገዛኋት"የሚለው ግስ (BDB 500 II፣ KB 497፣ *Qal* IMPERFECT) ትርጉሙ "በቅያሪ ወይም በገንዘብ መግዛት" ነው (ዝ.ከ. ዘዳግ 2:6) ይሁን እንጂ፣ ሰባ ሊቃናት ፣ዓረብኛ አቻውን በማስከተል"ተቀጣሪ የሚል አለው"፡፡

በግለጽ ሆሴዕ ሚስቱን መልሶ ገዛኋት! የተከፈለው ዋጋ የአንድ ባሪያ ዋጋ ግማሽ ነው (ዝ.ከ. ዘፀ 21:32 እናሌዋ 27:4)፡፡ በግልጽ እርሱ የከፈለው ግማሹ ናዓስ ሲሆን ግማሹን ደግሞ ምርት ነበር፡፡ ይህ እኮኖሚያዊ ገቢውን ኣዳክሞታል፡፡

እሱ የከፈለው ለማን ነበር? እርግጠኛመሆን እንደማይቻል መጽሃፉ በጣም ግልጽ ነው፡፡

ለየት ባለ ሁኔታ ለሚወዳት ሰው ለእርሷ አስተዳዳሪ ለሁለተኛጊዜ ለእርሷ እንደሸርሸር ስጦታ

እኔ እስከማስበው ፍቅረኛዋን የሚገልጽ ሐረግ ሆሴዕን ያመለክታል፣ስለዚህ ቁጥር 3 ከአውዱ ጋር በደንብ ይገናኛል፣ዳሩግን በታርክ ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለሸርሸር ሁለተኛ ስጦታ ሌላ ምሳሌ የለም፡፡

"አምስት ብርአንድቆሮስ መስፈርያ" ልዩርዕስተመልከት: የጥንታዊቷ የቅርብ ምስራቅ መለኪያ እና መስፈርያ በአሞ 8:5፡፡

▣ **"አንድቆሮስ መስፈርያ እና ተኩል ገብስ"** "ቆሮስ " (BDB 330) ማለት "የአንድ አህያ ዳውላ" ይህ ከአምስት የእህል መስፈርያ ጋር እኩል ነው፡፡ ስለዚህ፣የግዢው ዋጋ ወደ 75 የእህል መስፈርያ ይሆናል፡፡

**3:3 "ከእኔ ጋር ብዙ ወራት ተቀመጪ"** በማያጠራጥር መልኩ ለዝሙተኞች የመንጻት ጊዜ ነበር፡፡ ለእግዚአብሔር ሕዝብ የምርኮ ጊዜ ምሳሌ ነበር፡፡

**3:4** ስለዚህ ቁጥር ትርጉም አያሌ ክርክር ይኖራል፡፡ ሦስት ዋና ዋና መላምቶች አሉ፡-

1. እነዚህ ሦስቱ ቁጥሮች ያህዌን በመከተል (YHWHism) እና በአልን በመከተል (Ba'alism) መካከል ያለውን ልዩነትይወክላል፡፡
2. እነዚህ ከዝሙት እውነታጋር ይቀራረባል፣ለእስራኤል የእምነት ልምምድ ልማድ ሆኖ የነበረው (ዝ.ከ. 8:4-5፤10:7-8፣15)፡፡
3. እነዚህ እስራኤል ከተስፋይቱ ምድር የተለየችበት የምርኮ ጊዜን ያሳያል፡፡

▣ "የተቀደ ሰዓምድ" የተቀደ ሰዓምድ ለመጀመሪያ ለመታሰቢያ የቆሙ ናበሩ፡-

1. በዘፀ 24:4 በሙሴ የሲና ተራራን ቃልኪዳን መመሥረቱን ለማስታወስ (ለምሳሌ፣ኢያሱ 4:3፣9፣20)
2. ለተወሰኑ ታላለቅ ዲርጊቶች ወይም ለእግዚአብሔር መታየት
   ሀ. ሴኬም (ዝ.ከ. ኢያሱ 24:26) ፤
   ለ. ቤትኤል (ዝ.ከ. ዘፍጥ 28:18)
   ሐ. ገለዓድ (ዝ.ከ. ዘፍጥ 31:45)
   መ. ጌልጌላ (ዝ.ከ. ኢያሱ 4:5)
   ሠ. ምጽጳ (ዝ.ከ. I ሳሙ 7:12)
   ረ. ገባዖን (ዝ.ከ. IIሳሙ 20:8)
   ሸ. ኤን-ሮጌል (ዝ.ከ. I ነገስ 9:9)

እነርሱ ከበአል አምልኮ ዝሙት ጣዖትጋር ተቆራኙ በዘፀ 34:13፤ዘዳግ 12:3፤ 16:22፤ሚክ 5:13

ይህ እንዴት አንድ ዓይነት የሆኑ ልምምድ ወይም ቦታ ወይም ዕቃ ከብሉይ ኪዳን አሮጌው ክፍል እንደ ተወሰዱ ያሳያል፣ ግን በሌላ ክፍል ተወቅሰዋል፡፡

▣ **"ኤፉድ"** ይህ መነሻው የካህናትን ልብስ ያሳያል (ለምሳሌ፣1 ሳሙ 2:18፤ 22:18) ለየት ያለው በሊቀ ካህናት ይለበሳል (ለምሳሌ፣ዘፀ 25:7፤ 28:6-35)፡፡ ኤፉድ እና ተራፍም ከደረት በኋላ ባለው ኪስ ውስጥ ይደረጋሉ፣በኤፉድ ፍት ለፊት ላይ የታሰረ (ዝ.ከ. ዘፀ 28:30)፡፡
ኤፉድ የያህዌ ካህናት ምልክት ነው፡፡ ሕገ ወጥ የሆኑ ሐውልቶችን፣ ቅዱስ ሥፍራዎችን እና ካህናትን ህጋዊ የማድረግ ጥረት ነው (ለምሳሌ፣መሳ 8:26-27፤ 17:5፤ 18:14፣17፣18፣20)፡፡ ምናልባት ለሕይወት ልክ የሚሆን ጣዖት በሚያንፀባርቅ ካባ ይሸፈን ነበር፡፡ እንግዲህ ይህ የሰማያዊ መገለጥ ሥፍራን ያሳያል (ሊመጣ ያለውን)፡፡

**"የቤት ውስጥ ጣዖታት"** በቀጥታይህተራፊም ነው (BDB 1076) ምንጩ እና ታርኩ ግልጽ አይደለም፡፡

## ልዩ ርዕስ፡ ተራፊም

ከብሉይ ኪዳን የተለያዩ ክፍሎች የተጠናቀረ መግለጫ መስጠት ያስቸግራል፡

1. ትንሽና ሊያንቀሳቅሱት የሚቻል የቤት ውስጥ ጣዖት፣ ዘፍ 31:19፣34፣35
2. ትልቅ ጣዖት እንደ ሰው ቅርፅ ያለው፣ 1ኛ ሳሙ 19:13፣16
3. በቤት ውስጥ የሚጠቅሙ ጣዖታት፣ ግን ደግሞ በማምለኪያ ስፍራዎችም፣ መሳ 17:5፤ 18:14፣17፣18
4. የወደፊቱን ለማወቅ የሚጠቅሙ ጣዖታት ወይም የጣዖታት/የጣዖትን ፍቃድ
   ሀ. የተወገዙና ከመናፍስት ጥሪ ተርታ ጋር የተመደቡ፣ 1ኛ ሳሙ 15፡23
   ለ. የተወገዙና ከመናፍስት ጥሪ፣ መናፍስት፣ እና ጣዖታት ተርታ ጋር የተመደቡ፣ 2ኛ ነገሥ 23፡24
   ሐ. የተወገዙና ከመናፍስት ጥሪ (ማናገር)፣ ፍላጻችን መወዝወዝ፣ እና የበግ ጉበት ማየት ተርታ የተመደቡ፣ ሕዝ 21፡21
   መ. የተወገዙና ከሟርተኞችና ከሐሰተኛ ነቢያት ተርታ የተመደቡ፣ ዝካ 10፡2

**3:5"ከዚያም በኋላ"** ይህ በብዙ መንገድ ጥቅም ላይ የዋለ የተለመደ ተውላጠ ስም (BDB 29) ነው፡፡ ይህ ከያህዌ የፍርድ ጊዜ በኋላ ያለውን ጊዜ የሚያመለክት ይመስላል፡፡ ተመሳሳይ ቃል (BDB 31) ፣ "በመጨረሻዎቹ ቀናት፣"በቁጥር 5 መጨረሻ ላይ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ እንደ ጸሐፊው አመለካከት የወደ ፊት ሁኔታን ያሳያል፡፡ ትክክለኛ ጊዜው አሻሚ ነው፡፡
ያህዌ (YHWH) ሕዝቡን ይቀጣል፣ከዛ በኋላ ግን፣የሚታደሱበት ዘመን፣ይቀጥልበታል!
እነዚህ የወደፊት እውቅና እና የጊዜ ማሳያዎች የያህዌን እውቅና እና ታርክን እንደሚቆጣጠር መጽሐፍ ቅድሳዊ ማሳያ ናቸው፡፡ የያህዌ ፍርዶች የፍፃሜው ትልቁ ራእይ እና የመጨረሻ ግቡ ከሆነው ከሰው ልጅ ጋር ህብረት ማድረግ ላይ መታየት አለበት! ፍርዶች በራሳቸው ቤተሰባዊ ፍቅር ናቸው (ዝ.ከ. ሆሴ 11)፡፡

▣ **"የእስራኤል ልጆች ተመልሰው አምላካቸውን እግዚአብሔርን ይፈልጋሉ"** ሁለቱ የመጽሐፍ ቅዱስ እምነት ዓምዶች፤አንዱ አሉታዊ ስሆን አንዱ አዎንታዊን ው (ለምሳሌ፣ማር 1:15፤ሐዋሥራ 3:16፣19፤ 20:21፤ 26:20)፡፡ እኛ "መመለስ" አለብን—እሱም ንስዐ ነው (ማለትም "ወደቀድሞ መመለስ" BDB 996፣ KB 1427፣*Qal* IMPERFECT፣ልዩ ርዕስ አሞ 1:3 ተመልከት) ፣ እና "ወደ-መመለስ"—እሱም እምነት ነው (ማለትም፣ "መፈለግ" BDB 134፣ KB 152፣*Piel* PERFECT፣ዝ.ከ. 5:6፣15፤ 7:10፤ኢሳ 45:19፤ 65:1፤ኤፌ 1:6፤ 2:3) ሌላው የእስራኤል ልብ መለወጥ ክፍል በቁ 5 ላይ ይገኛል፡፡

▣ **"ፈርተው ወደ እግዚአብሔርና ወደ በረከቱ ይመጣሉ።"** ይህቃል አዲስ "ማደነቅ" እና "ክብር" ለእግዚአብሔር መካታቱን ይመስላል።

▣ **"ንጉሣቸውን ዳዊትን"** ዳዊት የሚስማማ ንጉስ ነበር። ያህዌ (YHWH) በሳሙ11 7 ላይ ለእርሱና ለዘሩ የማያቋርጥ ተስፋ ሰጥቶት ነበር። የአሞጽ ጓደኛ ሆሴዕም፣ የዳግም ምጽዓት የዳዊት ዘር ንግስን ጠቅሶታል (ማለትም፣መሲሕው፣ዝ.ከ. 1:11፤አሞ 9:11-15፤ኤርም 33:15፣21-22፣25-26፤ሕዝ 34:23-24፤ 37:24-28)፡፡
በይሁዳና በእስራኤል መካከል የነበረው የፓሊትካ መከፋፈል እንደ ኃጢአት ና አለማዊነት ይታይነበር (ለምሳሌ፣ 3:4፤ 7:7፤ 10:15) ምክንያቱም እዮርባምነ በቤትኤል ና ዳን ከተሞች ለሞርያ ተራራ የጣዖት አምልኮ ማዕከል እንዲሆን የወርቅ ጥጃ ከማሰራቱ የተነሣ (ለምሳሌ፣ 8:5) ።

▣ **"ፈርተው ወደ እግዚአብሔር ይመጣሉ"** ይህ ግስ (BDB 808፣ KB 922፣*Qal* PERFECT) በተመሳሳይ መልኩ (እና ተመሳሳይ ቅርፅ) በ8ኛው ክፍለ ዘመን በይሁዳ ውስጥ የሆሴዕ ጓደኛ በነበረው ነቢይ ጥቅም ላይ ውሏል፣ሚክ (ዝ.ከ. 7:17)፡፡ በአያሌ ስሜት ጥቅም ላይ ውሏል:-

1. የታማኙ አዎንታዊ
   ሀ እግዚአብሔርን ቃል ማክበር፣መዝ 119:16
   ለ ታማኝን የሚያስፈራ የለም፣መዝ 78:53፤ምሳ 3:24፤ኢሳ 12:2፤ 44:8
   ሐ የሚያስደንቅ የደስታ ስሜት በያህዌ (YHWH) ማዳን፣ኢሳ 60:5፤ኤር 33:9፤ሆሴ:5
2. የሐጥኃተኞች አሉታዊ፣መዝ 119:120፤ኢሳ 33:14፤ 44:11

▣ **"እና ወደ በረከቱ"** "በረከት" የሚለው ስም (BDB 375) ከ "ያህዌ" ጋር ይመሳሰላል። ይህቃል በብዙ ስሜት ጥቅም ላይ ውሏል። የእስራኤልን አምላክ ሊያመለክት ይችላል። እስራኤልን ለመግለጽ ማለት ነው። የኃጢአት ፣
ክፋት፣ እና የጨለማ ተቃራኒ ነው (ዝ.ከ. አሞ 5:14-15) ! "ብልጽግና" ወይም "በረከት" በማለትም ሊተረጎም ይችላል (ለምሳሌ፣ኤር 31:12፣14)፡፡ እግዚአብሔር ለቃልኪዳንታማኝነት እንደሸልማት እስራኤልን በመባረክ ዓለምን ወደ ራሱ ለመሳብ ፈልጎ ነበር።

ይሁን እንጂ፣እስራኤል አልቻለችም (አልታዘዤችም) ። ይህ በፍርድ ውስጥ ይታያል (ዝ.ከ. ዘዳግ 27-29፤ 30፤15)፡፡
የዳግም ምጽዓት በረከት በሰው ልጅ ቃል ኪዳን አፈጻጸም አይደገፍም፣ ዳሩ ግን እግዝሐብሄረን ለመምሰል በአዲስ ፈቃድናችሎታ በተደገፈ በሰማያዊ አፈጻጸም ነው (ዝ.ከ. ኤር 31:31-34፤ሕዝ 36:22-38) ! ቁ5 ሌላ የእስራኤል ወቅታዊ ሁኔታ ተገላቢጦሽ ነው፣ ለየት ያለተስፋና መመለስ፣ሌላ ትንቢት ስለዳዊት ንግስ (መስይ) !

▣ **"በኋለኛውም ዘመን"** በሁሉም የሆሴዕ መጽሐፍ ውስጥ የዳግም ምጽዓት ክፍሎችን እናገኛለን። አይሁዶች ሁለት ዘመናትን ብቻ ያያሉ— ክፉ የሆነው የአሁኑ እና ሊመጣ ያለው የመሲይው ዘመን። ይሁንእንጂ፣በአዲስ ኪዳን ውስጥ በስፋት ከሚታየው መገለጥ በመነሳት ከአንድ የበለጡ ሁለት የመሲይው አመጣጦች አሉ። እኛ በመጨረሻዎቹ ዘመን ውስጥ እንኖራለን፣ ሁለቱ የአይሁድ ዘመናት አንድ ላይ ያለበት። የመጨረሻዎቹ ዘመናት ኢየሱስ በቤተሌም ከመወለዱ ጀምሮ እስከ ዳግም ምጽዓቱ ያለውን ጊዜ ነው።

## ልዩ ርዕስ: ይህ ዘመንና ሊመጣ ያለው ዘመን

የብሉይኪዳን ነብያቶች የወደፊቱን የሚያዩት እንደ የአሁን ጊዜ መስፋት ነው። ለእነርሱ የወደፊቱ የእስራኤል መልካምድራዊ መታደስ ነው። ይሁንእንጂ፣እንድያውም እንደአዲስ ቀን ያዩት ነበር (ዝ.ከ. ኢሳ 65:17፤ 66:22) ። ያህዌ በቀጣይነት የአብርሃምን ዘሮች (ከምርኮ በኋላም ቢሆን) ከመናቁ የተነሣ በአይሁድ ውስጥ የወደፊቱን የሚያበላሽ ሥነ-ጽሑፍ አስተሳሰብ አደገ (ማለትም፣ሔኖክI ፣ዕዝራIV፣ ባሩክ II)፡፡ ጽሑፉ የሚጀምረው በሁለቱ ዘመን መካከል ልዩነትን በማስቀመጥ ነው፡፡
የአሁኑ ክፉ ዘመን በሴጠን ይሸነፋል፣ ሊመጣ ያለው የጽድቅ ዘመን ደግሞ በመንፈስ ይቆጣጠር እና በመሲይው ይከፈታል (ብዙ ጊዜ አስደናቂ ተዋጊ)፡፡
በዚህመጽሐፍ ቅዱሳዊ (ዳግም ምጽዓት) ዙርያ የታወቀ ዕድገት አለ።
የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ይህንን "የሚያድግ መገለጥ" ይሉታል። አዲስ ኪዳን የዚህን ሁለት አዲስ ዘመናት ዉነታን ያጠነክራል (ማለትም፣ጊዜያዊ ሁለትዮሽ) :

| **ኢየሱስ** | **ጳውሎስ** | **እብራውያን** |
|---|---|---|
| ማቴ 12:32 | ሮማ 12:2 | 1:2 |
| ማቴ13:22 እና 29 | ቆሮI 1:20፤ 2:6፣8፤ 3:18 | 6:5 |
| ማር 10:30 | ቆሮII 4:4 | 11:3 |
| ሉቃ 16:8 | ገለ 1:4 | |
| ሉቃ 18:30 | ኤፌ 1:21፤ 2:1፣7፤ 6:12 | |
| ሉቃ 20:34-35 | I ጥሞ 6:17 | |
| | II ጥሞ 4:10 | |
| | ቲቶ 2:12 | |

በአዲስ ኪዳን መጽሀፍ ቅዱስ ትምህርት እነዚህ ሁለቱ የአይሁድ ዘመናት ተደርቧል፡፡ ምክንያቱም ካልታሰበና ከተዘናጋ ሁለቱ የመሲሁ መምጫ። የኢየሱስ ተስጉት ሥጋዌ የብሉይ ኪዳን የአዲስ ዘመን መከበር ትንቢቶችን ይፈጽማል (ዳን 2:44-45) ። ይሁንኢንጂ፣ብሉይ ኪዳን መምጫውን እንደ ፈራጅእና አሸናፊ ያይ ነበር፣ቢሆንም እርሱ መጀመሪያ የመጣው መከራን እንደወሰደ ባሪያ (ዝ.ከ. ኢሳ 53) ፣ራሱን ዝቅ ያደረገ እና ትሁት ሆኖ ነው (ዝ.ከ. ዘካ 9:9) ። ብሉይ ኪዳን እንደተናገረ በኃል ተመልሶ ይመጣል (ዝ.ከ. Rev 19) ። የዚህ ሁለት ደረጃ ፍጻሜ መንግስቱ እንዲከበር ያደርጋል፣ ግን ወደፊት (በሙሉ አልተፈፀመም) ። ይህ የአዲስ ኪዳን የአሁኑ አስተሳሰብ፣ግን ገና ያላለቀ!

# ሆሴዕ 4
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|
| በእስራኤል ላይ የእግዚአብሔር ክስ | ቀዋሚ ስለሁነው የእስራኤል አመፃ ምክንያት የተነሳ የእግዚአብሔር ፍርድ በእስራኤል ላይ ነው | በእስራኤል ላይ የእግዚአብሔር ወቀሳ | አጠቃላይ የሞራል ውድቀት |
| 4:1-10 | 4:1-3 | 4:1-3 | 4:1-4 |
| | | ጌታ ካህናትን ይወቅሳል | ካህናትን ይቃወማል |
| | 4:4-6 | 4:4-6 | 4:4-6 |
| | 4:7-14 | 4:7-10 | 4:7-11ሀ |
| የእስራኤል ጣኦት አምልኮ | | ጌታ የአህዛብን አምልኮ ይከስሳል | በእስራኤል አምልኮ ጣዖት አምልኮና ወራዳነት ነው |
| 4:11-14 | | 4:11-13ሀ | 4:11b-14 |
| 4:15-19 | 4:15-19 | 4:13b-14 | ማስጠንቀቂያ ለእስራኤልና ለይሁዳ 4:15-19 |
| | | 4:15-19 | |

### የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ vii ተመልከት)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ

2. ሁለተኛው አንቀጽ

3. ሦስተኛ አንቀጽ

4. ወዘተርፈ

## የምዕራፍ 4-11 መሠረታዊ መውጫዎች

ሀ. ምዕራፍ 4-5 የኤሴራኤልን ታማኝነት የሚገልጽ ሥነ-ጽሑፍ ክፍል ያጠቃልላል።

ለ. ምዕራፍ 6-10 የኤሴራኤልን ቅጣት የሚገልጹ ሥነ-ጽሑፍ ክፍል ናቸው።

## የቃላት እና የሐረግ ጥናት

**ሆሴዕ: 4:1-3**

**1እናንተ የእስራኤል ልጆች ሆይ፥ እውነትና ምሕረት እግዚአብሔርንም ማወቅ በምድር ስለሌለ**
**እግዚአብሔር በምድሩ ላይ ከሚኖሩ ጋር ክርክር አለውና የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ።**
**2እርግማንና ሐሰት ገዳይና ስርቆት ምንዝርናም ወጥተዋል ደምም ወደ ደም ደርሶአል።**
**3ስለዚህ ምድሪቱ ታለቅሳለች ፥በእርስዋም የሚቀመጡ ሁሉ**
**ከምድር አራዊትና ከሰማይ ወፎች ጋር ይደክማሉ የባሕሩም ዓሦች ያልቃሉ።**

**4:1**
**NASB** “የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ”

| | |
|---|---|
| NKJV፣ NRSV | "የእግዚአብሔርን ቃል አድምጡ" |
| TEV | "እርሱ የሚላችሁን ስሙ" |
| NJB | "ያህዌ የሚለውን አድምጡ" |

ግሱ (BDB 1033፣ KB 1570፣*Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)* ) የሚለው ለመፈጸም መስማት ማለት ነው፡፡ በሆሴዕ ውስጥ አያሌ ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል (ዝ.ከ. 4:1፤ 5:1፤ 9:17) ፣ዳሩ ግን በሌሎች የ8ኛ ክፍለ ዘመን ነቢያት ብዙ ጊዜ ነበር፡፡

1. አሞ፣ 3:1፣13፤ 4:1፤ 5:1፤ 7:16፤ 8:4፣11
2. ሚክ፣ 1:2፤ 3:1፣9፤ 5:15፤ 6:1[ሁለት ጊዜ]፣2፣9፤ 7:7

የአሞ 3:1 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት፡፡

▣ **"እግዚአብሔር ክርክር አለው"** ይህቃል (BDB 936) ሁለት ዋና ሐሳብ አለው፡፡

1. ህጋዊ ክስ፣ኢሳ 1:23፤ 41:21፤ኤር 2:9፤ 25:31፤ 50:34፤ Hos 4:1፤ 12:3፣ሚክ 6:2፤ 7:9
2. ክርክር ወይም ተቃውሞ፣ኢሳ 41:11፤ 58:4፤ኤር 15:10፤ሆሴ 2:2

ያሄዌ (YHWH) ተጎጂ፣ህጋዊ ጠበቃ፣እና ዳኛ! ነብያቶች ከሚጠቀሙበት ሦስት ሥነ-ጽሑፋዊ ዘዴዎች የፍርድ ቤት ክስ አንዱ ነው።

1. ህጋዊ ክስ (ማለትም፣የፍቺ ክስ)
2. የቀብርመዝሙር (የፍርድ ጥላ)
3. የመዳን ተስፋ (የማስመለጥ ጥላ)

▣ **"በምድሩ ላይ ከሚኖሩ ጋር"** የፍልስጤም ምድር (ከናዓን ለየት ያለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንድምታ አለው። ይህ ለአብረሃም ዘር፣ስም፣እና ምድር ሊሰጠው እግዚአብሔር ከሰጠው ተስፋ ይጀምራል (ዝ.ከ. ዘፍጥ12:1-1)፡፡ ይህ ተስፋ ልዩ በሆነው በ"ራአይ ቃል ኪዳን" ዘፍጥ 15:12-21 ውስጥ በድጋም ተረጋግጧል። የከናዓን የለምለም ጣዖት አምልኮ ምድርቱን ይጠረጋል (ዝ.ከ. ቁ 16) ። የእግዚአብሔር ሕዝብም ተመሳሳይ መጥፎ ነገር ውስጥ በገቡ ጊዜ፣እንደዛው ከያህዌ ምድር ይጠረጋሉ!

| | |
|---|---|
| NASB፣ NRSV፣ | |
| TEV | "ታማኝነት" |
| NKJV | "እውነታ" |
| NJB | "ቅንነት" |

በዮናስ 3:5 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት

| | |
|---|---|
| NASB | "ርህራሄ" |
| NKJV | "ምህረት" |
| NRSV | "ቅንነት" |
| TEV | "ፍቅር" |
| NJB | "እምነት" |

ይህ ሄሴድ (*hesed*) የሚል የእብራይስጥ ቃል ነው (BDB 338፣ዝ.ከ. 6:4) ደግነት የሚለውን ልዩ ርዕስ 2:19 ላይ ተመልከት (*Hesed*)

**"ማወቅ"** ይህ የመጽሐፉ ርዕስ ነው (ለምሳሌ፣ 2:20፤ 4:6፤ 5:4፤ 6:6፣6) —እግዚአብሔርን እንደ ሌላ ነገር ማዬት የለብንም ("እሱ፣"ጣዖት) ፣ግላዊ በሆነ፣የጠበቀ ህብረት (a person) "ማወቅ" (BDB 395) የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከግላዊ፣የጠበቀ ህብረትጋር ይገናኛል (ዝ.ከ. ዘፍጥ 2:20፤ 4:1፤ኤር፡፡ 1:5) የዚህ መጽሐፍ አስገራሚ ውነታ ሐጥያተኛው የሰው ልጅ እግዚአብሔርን ማወቁ ብቻ ሳይሆን፣ እነርሱ በእግዚአብሔር መታወቃቸው ነው (ዝ.ከ. ኤር 31:34፤ Heb 8:1ff) እርሱ ይፈልገናል!

**4:2** እስራኤል ከታመኝነት፣ርህራሄ፣እና እውቀት ይልቅ፣በቁ 2 ላይ በተጠቀሱት ቃለቶች ትታወቃለች (all INFINITIVE ABSOLUTES) ፣ አሥርቱ ትዕዛዛት መሰበራቸውን የሚያሳዩ ናቸው (ማለትም፣በተለይ 2ኛው፣ 6ኛው፣ 7ኛው፣እና 8ኛው) አሥርቱ ትዕዛዛት ለሰው ዘር የእግዚአብሔር ፈቃድ ናቸው። የሰው ዘርን ነፃነት ለመገደብ አልተሰጡም፣ ዳሩ ግን የጋራ ደስታውን ለማጠናከር ነው! እስራኤል ግን እያወቀች የሥነ-ምግባር ድንበሮችን ሰብራለች (BDB 829፣ KB 971፣*Qal* PERFECT)!

**4:3 "በእርስዋም የሚቀመጡ ሁሉ ይደከማሉ።"** የቃሉ (BDB 51፣ KB 63፣*pulal* PERFECT) ትርጉም በድርቅ መድከም በሚለው እንድምታ መድከም ማለት ነው (ለምሳሌ፣ኢዮኤ 1:10፤ኢሳ 16:8፤ 24:4፤ 33:9፤ኤር 12:4) ዘዳግም የእግዚአብሔር እሳት (ማለትም፣ድርቅ) ፍርዶች (ዝ.ከ. ዘዳግ 27-20 እና ሌዋ 26) መጥቷል (ዝ.ከ. አሞ 7:4)

1. ምድር ታዝናለች
2. ሕዝቡ ይደከማል
3. እንስሳት ይጠፋሉ

የሚታዩ ፍጥራታት (በተለይ የያህዌ የተስፋ ምድር) ከሰው ዘር ኃጢአት ተየተነሳ ተጎዳ (ዝ.ከ. ዘፍጥ 3:17-19፤ሮማ 8:18-25)፡፡ ይህ ክፍል ከውሃ ጥፋት (ዝ.ከ. ዘፍጥ 6-9) ይልቅ ከባድ ነው ምክንያቱም ዓሳዎችም ይጎዳሉ (ዝ.ከ. ኤፌ 1:2-3)፡፡ እንግዳ በሆነ ሁኔታ የውሃ ብዛት ፍርድ አሁን ደግሞየ ውሃ ማጣት ፍርድ ነው (ማለትም፣ድርቅ)! ስቃይ ወይም ውዥምብር ዳግም መጣ!

## ሆሴዕ: 4:4-6

**4ነገር ግን ሕዝብህ ከካህን ጋር እንደሚከራከሩ ናቸውና ማንም አይከራከር፥ ማንም አይዝለፍ።**
**5በቀንም ትሰናከላለህ፥ ነቢዩም ከአንተ ጋር በሌሊት ይሰናከላል እናትህንም አጠፋታለሁ።**
**6ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቷል አንተም እውቀትን ጠልተሃልና እኔ ካህን እንዳትሆነኝ እጠላሃለሁ የአምላክህንም ሕግ ረስተሃልና እኔ ደግሞ ልጆችህን እረሳለሁ።**

4:4-5:7 *ይህ ሥነ-ጽሑፍ* ክፍል ስለካህናት ይናገራል!
4:4 *የመጀመሪያዎቹ ሁለት ግሶች* JUSSIVES ናቸው:
1. *ማንም አይዝለፍ፣Qal* JUSSIVE
2. *ማንም አይከራከር፣Hiphil* JUSSIVE

እነዚህሁለቱም ህጋዊ እንድምታ አላቸው (ለምሳሌ፣ #1 መሳ 6:31-32፤ #2 አሞ 5:10) ግን በ4ሀ ተናጋሪው ማን ነው?
1. በስም ያልተጠቀሰ አካል (ዝ.ከ. አሞ 5:10)
2. የካህናት ተወካይ የሆነ (ማለትም፣ሊቀ-ካህን)
3. የእስራኤል ሕዝብ (ካህንና ነቢይ የሆነ)
4. ያህዌ ራሱ ነው (ተናጋሪው ፈራጅ፣ዝ.ከ. ቁ 5ሐ)

| | |
|---|---|
| **NASB፣ NKJV** | **"ሕዝብህ ከካህንጋር እንደሚከራከሩ ናቸው"** |
| **NRSV** | **"ካህን ሆይ፣ከአንተጋር ይከራከራሉሁ"** |
| **TEV** | **"እናንተ ካህናት ይቃወማቸዋለሁ"** |
| **NJB** | **"የማወዝዘው አንተን ነው፣ካህን"** |
| **JOA** | **"ካህን ሆይ፣ሕዝብህ በአንተ ላይ ቅሬታውን ያቀርባል [አንተ]"** |
| **NASB** | |

ከአውዱ ጋር በደንብ አይገናኝም። ልዩ የአገላለጽ እና አንድን ተናባቢ እጥፍ ማድረግ "ካህን ሆይ፣ ከአንተ ጋር ይከራከራለሁ" የሚል እንዲፈጠር ያደረጋል እናም በተሻለ ከአውዱጋር የሚስማማ (ዝ.ከ. ቁ 6)።

**4:5 "መሳሳት"** የሚለው ግስ (BDB 505፣ KB 502፣*Qal* PERFECT) ሁለት ጊዜ ተደግሟል። መሳሳት የ"ታማኝነት" ተቃራኒ ምሳሌ ነው፡፡

| | |
|---|---|
| **NASB፣ NKJV፣** | |
| **NRSV** | **"እናታችሁን አጠፋታለሁ"** |
| **TEV** | **"እናም እናታችሁ እስራኤልን፣ላጠፋት ነው"** |
| **NJB** | **"እናም እናታችሁ እንዲትጠፋ አደረጋለሁ"** |
| **JPSMOA** | **"እናም ዘመድህን አጠፋለሁ"** |

NETመጽሐፍ ቅዱስ (ገጽ 1562) የማስተካከያ ሐሳብ ያቀርባል (ሁለት ተነባቢ ይለወጣል) ። "ሕዝብህን አጥፍተሃል" ይህ እንግዲህ ከያህዌ የተሰጠ አይደለም፣ ግን የመጀመሪያው በደንብ ካህናትን ለመውቀስ ነው፡፡ ካህናት ተወቀሰዋል (1) የእግዝአብሄርን ቃል ኪዳን ባለማስተማራቸው እና (2) የተበላሸ የተትረፍረፈ የሕይወት ልምምድ በመኖራቸው፡፡

**4:6 "ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል አንተም እውቀትን ጠልተሃልና"** "መጥፋት" (BDB 198፣ KB 225፣*Niphal* PERFECT) ማለት "ከመለየት" እና እዛ መኖርን ማቆም ነው። ሕዝቡ ጥፋተኛ ነው፣ ካለመረዳት ሳይሆን፣ዳሩ ግን እያወቁ እግዚአብሔርን መታዘዝ እምቢ በማለታቸው እና በመተዋቸው (BDB 549፣ KB 540፣*Qal* PERFECT) ። ይህ በተለይ ለአይማኖት እና ለፖለትካ መሪዎች እውነት ነው።

▣ **"እኔ ካህን እንዳትሆነኝ እጠላሃለሁ"** የእስራኤል ሕዝብ ለዓለም ሁሉ ካህናት ነበሩ (ዝ.ከ. ዘፀ 19:4-6) ይሁን እንጂ፣ እዚህ ሕዝቡን በእግዚአብሔር ቃል የሚመሩትን ካህናትን ይመለከታል (ዝ.ከ. ሌዋ 10:11፤ዘዳግ 17:10-11፤ 33:10ሌር 18:18፤ሚል 2:6-7) ፣እነርሱ ያላደረጉትን!
"የአምላክህንም ሕግ ረስተሃልና" እውቀት ሁለት መልክ አለው:- (1) ግላዊ የሆነ ህብረት፤እና (2) የቃል ኪዳን ኋላፍነቶች። ያህዌንና ቃል ኪዳኑን ረሱ (BDB 1013፣ KB 1489፣*Qal* IMPERFECT) እርሱም ዘራቸውን ይረሳል (*Qal* IMPERFECT) ። ይህየ ዘፀ 20:6 እና ዘዳግ 5:10፤ 7:9 የቃል ኪዳን ተስፋዎች ተገላቢጦሽ ነው! ካህናት (እና ሌዋዊያን) የእስራኤል አስተማሪዎች እንዲሆኑ ነበር፣ ዳሩ ግን እስራኤልን የሚያበላሹ ሆኑ! እንደ መስዋይት አቅራቢዋች ቀጥሎ ማገለገል አይችሉም!

## ሆሴዕ: 4:7-10

**7እንደ ብዛታቸው መጠን ኃጢአት ሠሩብኝ እኔም ክብራቸውን ወደ ነውር እለውጣለሁ።**
**8የሕዝቤም ሐጢያት መብል ሆኖላቸዋል፥ ልባቸውንም ወደ በደላቸው አድርገዋል። 9እንደ ሕዝቡም እንዲሁ ካህኑ ይሆናል በመንገዳቸውም እበቀላቸዋለሁ፥ሥራቸውንም እመልስባቸዋለሁ።**
**10እግዚአብሔርንም መጠበቅ ትተዋልና ሲበሉ አይጠግቡም፥ሲያመነዝሩም አይበዙም።**

**4:7 "እንደ ብዛታቸው መጠን ሐጢዖት ሠሩብኝ"** *"ሠሩብኝ"* የሚለው የጣዖታት ድርጊቶችን ወደ ሚፈፅሙ ካህናቶች መስዋይትን የሚያመጡትን ሕዝብ የሚያሳይ ይመስላል (ዝ.ከ. ቁ 8-10)፡፡ እግዝአብሄር ሕዝብ በሰጣቸው መጠን እነርሱ ደግሞ እርሱን ተውት (በ 11:2 ውስጥ ያሉትን ነቢያት በመጠቀም ተመሳሳይ ምሳሌን ተመልከት)፡፡

| | |
|---|---|
| **NASB፣ NKJV** | **"ክብራችሁን ወደ ውርደት ይለውጣለሁ"** |
| **NRSV** | **"ክብራቸውን ወደ ሀፍረት ለወጡ"** |
| **TEV** | **"ክብራችሁን ወደ ውርደት ይመልሳለሁ"** |
| **NJB** | **"ክብራቸውን በሀፍረት ቀየሩ"** |

ከትርጉሞቹ እንደሚታዩት የአውዱ ጉዳይ ባለቤቱ ማን ነው ከሚል በላይ ነው፣ያህዌ (NASB፣ TEV)
ወይስ እስራኤል (NRSV፣ NJB)፡፡ ማሶሬቲኩ እንደ ባለቤት ያህዌ የሚለውን አለው (BDB 558፣ KB 560፣ያልተፈፀመ ሂፍል (*Hiphil* IMPERFECT) ይሁን እንጂ፣ የአይሁድ ባህል ግሱን ወደተፈፀሜ ሂፍል ይቀይራል (*Hiphil* PERFECT) ።
ይህ ማስተካከያ በአይሁድ ታርጉም (Targums) (የአሮማይክ ትርጉም እና ማብራሪያ) እና ፔሽታ (Peshitta) የአሮማይክ የክርስቲያን ትርጉም ይከተላል።

▣ ***"ሀፍረት"*** የሚለው ቃል (BDB 885) የ"ክብር" ተቃራኒ ነው (ዝ.ከ. መዝ 83:16፤ምሳ 3:35፤ 13:18) ። በዚህ አውድ ዝሙትን ያሳያል (ዝ.ከ. ቁ 18) ። እንደ ቃል ኪዳን ሕዝብ የእግዝአብሄር ክብር ይካፈላሉ፣ ዳሩ ግን ይህንን ለራሳቸው ወሲባዊ ለምለም አምልኮ ቀየሩት (የበአል ክብር) ።

**4:8 "የሕዝቤምሐጢዓት ሙብል ሆኖላቸዋል፥ ልባቸውንም ወደ በደላቸው አድርገዋል"** ይህ ካህኑ ለኃጢአት ለሚቃርበው *ሥጋ* ካለው ምኞት ጋር ይመሳሰላል (ዝ.ከ. ሌዋ 6 : 26) ፣ ግን በለምለም አምልኮ *ሥርዓቶች* ውስጥ መሳተፋቸውን በምሳሌያዊ መልኩ የሚያሳይ ነው።

▣ **"ልባቸውንም ወደ በደላቸው አድርገዋል"** የሚል ሐረግ በቀጥታ "የአንድን ሰው ነፍስ ወደ አንድ አቅጣጫ"። በዚህ መልኩ ስድስት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል (ዝ.ከ. ዘዳግ 24:15፤መዝ 24:4፤ምሳ 19:18፤ኤርም 22:27፤ 44:14፣እና በዚህ ክፍል ውስጥ)፡፡

**4:9 "እንደ ሕዝቡም እንዲሁ ካህኑ ይሆናል"** ይህ ካህናት ለሐጥ*ዖ*ታቸው እንደሚፈረድባቸው፣ የሕዝቡም እንደዛ እንደሆነ የሚያንፀባርቅ የተለመደ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው።

▣ **"በመንገዳቸውም እበቀላቸዋለሁ፥"** በመሠረቱ የግሱ ትርጉም (BDB 823፣ KB 955፣*Qal* PERFECT)

▣ ***"ለመንብኛት"*** ወይም *"መገኛት"* የሕዝቡ ለቃል ኪዳን መታመን ለይ ተመሰርቶ ያህዌ ለፍርድ ወይንም ለበረከት ሊጎበኝ ይችላል (ዝ.ከ. ዘዳግ 27-29፤ሌዋ 26) ።

**4:10** የፍሬያማነት ጣዖታትን ቢፈልጉም እንኳ፣በቂ ምግብም ሆነ ልጆችን አላገኙም (ለምሳሌ፣ ሐጌ 1:6)! በቁ 7ሀ ውስጥ የሚታየው የሕዝብ ብዛት ወደ መጨረሻ ነው!

## ሆሴዕ: 4:11-14

**11ግልሙትናና የወይን ጠጅ ስካርም አእምሮን ያጠፋል። 12 የግልሙትና መንፈስ ሕዝቤን አስቶአቸዋልና፥ እነርሱም ከአምላካቸው ርቀው አመንዝረዋልና በትራቸውን ይጠይቃሉ ፥ ዘንጋቸውም ይመልስላቸዋል። 13በተራሮችም ራስ ላይ ይሠዋሉ ጥላውም መልካም ነውና ከኮምበልና ከልብን ከአሆማም ዛፍ በታች በኮረብቶች ላይ ያጥናሉ ስለዚህ ሴቶች ልጆቻችሁ ይገለሙታሉ ፥ ሙሽሮቻችሁም ያመነዝራሉ። 14ወንዶችም ደግሞ ከጋለሞቶች ጋር ይጫወታሉና፥ ከጋለሞቶችም ጋር ይሠዋሉና ሴቶች ልጆቻችሁ በገለሞቱ ጊዜ፥ ሙሽሮቻችሁም ባመነዘሩ ጊዜ አልቀጣቸውም የማያስተውልም ሕዝብ ይገለበጣል።**

**4:11** ይህ በግልጽ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው፡፡ ኃጢአት የሰውን ትክክለኛ እይታን ይሰርቃል እናም እንደ ሰካራምና ዕውር በዳበሳ ይሄዳሉ" (ዝ.ከ. ኢሳ 28:1-4) ልዩ ርዕስ ተመልከት: ስለ አልኮል እና የአልኮል ሱሰኛ መሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከቶች በአሞ6:6፡፡

**4:12** እስራኤል የወደ ፊቱን ለማወቅ እና ትክክል ባልሆነ መንገድ ለመቆጣጠር እየፈለገ ነው (ዝ.ከ. ዘዳግ 18:9-13)፡፡

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"ከእንጨት የተሠራ ጣዖት"** |
| **NKJV** | **"ከእንጨት የተሠሩ ጣዖታት"** |
| **NRSV፣ TEV** | **"የእንጨት ስብርባሪ"** |
| **NJB** | **"የእንጨት ጣውላ"** |

ይህ ቃል (BDB 781) "ዛፍ" ወይም "እንጨት"ማለት ነው፡፡ ትንሽ ለየት ባለ መልኩ በ 4:17፤ 8:4፤ 13:2፤ 14:8ጥቅም ላይ ውሏል እናም "ጣዖታት"ማለት ነው፡፡ይህ ከእንጨት ወይም ዘንግ ወይም በትር ጋር የሚቀራረብ ከሆነ የአሼራን እንጨት ሊያመለክት ይችላል (በሰው አምሳል ከእንጨት የተሠራ ጣዖት ሳይሆን ሹል እንጨት)፡፡

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"ሰማያዊያን መታጠቂያ (ማሰርያ) "** |
| **NKJV** | **"መቋሚያ"** |
| **NRSV** | **"ትንባያ ዱላ"** |

TEV፣ NJB "ዱላ"
ይህ ቃል (BDB 596) ማለት "ዛፍ፣" መቋሚያ፣" ወይም "ዱላ" የተወሰኑ ጥቅሞቹ:

1. የእንጨት ጦር (ዝ.ከ. 1 ሳሙ 17:40፣43፤ሕዝ 29:9)
2. *መቋሚያ* (ዝ.ከ. ዘፍጥ 32:20፤ዘፀ 12:11)
3. የእንስሳት መከላከያ ዱላ (ዝ.ከ. ዘኍል 22:27)
4. ለጋ ዛፍ (ለምሳሌ፣ዘፍጥ 30:37-39፣ 41፤ኤርም 1:1)
5. የእረኛ በትር (ዝ.ከ. ዘካ 11:7፣10፣14፣ NIDOTTE፣ ቅጽ 2፣ ገጽ 1088 እይ)

▣ ***"የግልሙትናመንፈስ"*** "መንፈስ" የሚላው ቃል በዚህ ውስጥ በአጋንንት ከመያዝ ጋር አይገናኝም፣ዳሩ ግንበብሉይ ኪዳን ለ "አስተሳሰብ ሁኔታ፣" "ማንነት"ወይም "ማጠናከርያ ማዕከል" የሰውን ባህርያት ወይም ስሜት ለመግለጽ ቃሉ እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋለ:

1. የመንፈስ መራራነት፣ዘፍጥ 26:35
2. የመንፈስ ስብራት፣ዘፀ 6:9
3. የተጎዳ መንፈስ፣ 1 ሳሙ 1:15
4. ደስተኛ ያልሆነ መንፈስ፣ 1 ነገስ 21:5
5. መንፈስ መረበሽ፣ኢዮ 21:4፤ምሳ 14:29
6. የመንፈስ ትዕቢት በመንፈስ ትሑት ጋር ፣ምሳ 16:18-19፤ኢሳ 66:2
7. ታማኝ መንፈስ፣ምሳ 11:13
8. በመንፈስ መስከር፣ኢሳ 19:14
9. የመንፈስ ሀዘን፣ኢሳ 54:6

ይህ እስራኤላውያን በምኞታቸው የከናዓን ለምለም ጣዖትን እንደሚፈልጉ ይገልጻል (ዝ.ከ. 5:4)፡፡ የትርጉሙ ጉዳይም በቡድን ስለ ተደራጀ የወሲብ ድርጊት ነው (ዝ.ከ. ቁ 3-14) ወይም ደግሞ ያለመታመን ምሳሌ ሊሆን ይችላል (ለምሳሌ፣ዘፀ 34:15-16፤ሌዋ 20:5፤መሳ 2:17፤ 8:27፣33፤ 1 ዜና 5:25፤መዝ 73:27፤ 106:39)፡፡

▣ ***"ከአምላካቸው በመለየት"*** በቀጥታ ይህ "ከእግዝአብሄር በታች አለመሆን" (BDB 1065) ፣ከእግዚአብሔር ስልጣን መለየትን ያሳያል፡፡

**4:13 "*ይሠዋሉ ያጥናሉ*"** እነዚህ ሁለት የተለያዩ ቡድን ድርጊትን ያሳያሉ ወይም እጣን ማጠን፡፡ ካካባቢው በኣል አምልኮ ጋር ግንኙነት ያለው መሰዊያ የሉም፡፡

▣ **"በተራሮችምራስላይ በኮረብቶችላይ"** ይህ ሁለት ነገሮችን ያሳያል: (1) ከከፍታዎቹ የተሸለ ከፍታ ያለው የሠፈሩ በአል መሰወያ ቦታ ነበር ወይም (2) የበአል መስወያ ቦታ ዘዳግ (12:2፤ኤርም 2:20፤ 3:6፤ሕዝ6:13)

▣ **"ከኮምበል፣ከልብን፣እና ከአሆማም"** ዛፎቹ ቅዱስ *ሥፍራዎችን* ያሳያሉ፣ ምክንያቱም የከርሰ ምድር ውሃ መኖሩን ያሳያሉ፣ለበረሃ ሰዎች በጣም አስፈላጊ የሆነ፡፡እንደ ቅዱስ ስፍራዎች ቢወስዷቸውም እንኳ፣እስራኤል ዛፎችን እንደሚያመልክ የተጻፈ ነገር የለም (ለምሳሌ፣ዘፍጥ 13:18፤ Jdgs 4:5)፡፡በዚህ አውድ ዛፎቹ ለበአል ለምለም ልምምድ እንደ ጥላ ያገለግሉ ነበር፡፡

**4:14** እነዚህ ዐረፍተ ነገሮች በርግጥ የ "አዎን" መልስ የሚጠብቁ ጥያቄዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡በከእግዚአብሔር ዘንድ ሁለት ደረጃ የለም፡፡ሁለቱም ወንዶች እና ሴቶች ስለ ዝሙት ለምለም በኣላቸው ይፈረድባቸዋል (ዝ.ከ. ዘዳግ 23:17-18)፡፡ ሦስት ዓይነት ሴቶች ተሳትፏል: (1) አዲስ ሙሽሮች፤ (2) ሴተኛ አዳሪ ቡድን፤እና (3) ሴሎች የሠፈር ወይም የአከባቢ ሴቶች፡፡

እንደዚሁም በሰዋሰውም ሆነ በአውዱ መሠረት ካህናቱ ቁ 14 ላይ ያለውን ቡድን ድርጊት ተቀባዮች እንደ ሆኑ ማየት ይቻላል፡፡ የተሻለ እውቀት ያለቸው ካህናትም፣በወሲባዊው ድረጊት ውስጥ ይሳተፋሉእናም ለማህበረሰቡ መጥፎ ምሳሌ አስቀመጡ! ይህ ትክክል ከሆነ፣በቁ 13 ላይ የተጠቃሱ ሴቶች የካህናት ቤተሰብ ሳይሆኑ አይቀሩም!

## *ሆሴዕ* 4:15-19

**15እስራኤልሆይ፥አንተብታመነዝርይሁዳአይበድልእናንተምወደጌልገላአትግቡ፥**
**ወደቤትአዌንምአትውጡ፥ወይምሕያውእግዚአብሔርን! ብላችሁአትማሉ!"**
**16እስራኤል እንደ እልከኛ ጊደር እንቢ ብሎአል እግዚአብሔርስ በሰፊው ቦታ እንደጠቦት ያሰማራዋልን?**
**17ኤፍሬም ከጣዖታት ጋር ተጋጠመ ተወው።**
**18ስካርን ፈጽመዋል፥ግልሙትናንም አብዝተዋል አለቆችዋም ነውርን እጅግ ወደዱ።**
**19ነፋስ በክንፍዋ አስሮአታል ከመሥዋዕታቸውም የተነሣ ያፍራሉ።**

4:15 ይህ ቁጥር የጁሲቭስ (JUSSIVES) ቀደም ተከተልአለው:

1. "ይሁዳ አይበድል" (BDB 79፣ KB 95፣*Qal* JUSSIVE)
2. "ወደጌልገላ አትግቡ" (BDB 97፣ KB 112፣*Qal* JUSSIVE)
3. "ወደ ቤትአዌንም አትውጡ" (BDB 748፣ KB 828፣*Qal* JUSSIVE)
4. "መሃላ ተቀበሉ" (BDB 989፣ KB 1396፣*Niphal* JUSSIVE)

▣ **"እስራኤል ሆይ፥ አንተ ብታመነዝር ይሁዳ አይበድል"** ይህ ሊመና ከሕዝ 23 ጋር ተመሳሳይ ነው (ዝ.ከ. ኤር 3:6-18)፡፡ ይሁዳ መረዳትና መፍራት ነበረባት፣እርሷ ግን አላደረገችም! እንዳሁም ይበልጥ እርሷ ተጠያቂ ነች!

▣ **"ወደ ጌልገላ አትግቡ"** ይህ ለመጀመሪያው ለኢያሱ ሠፈር፣ እስራኤላውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር በገቡ ጊዜ ጥሩ ማሳያ ነው፡፡ አሁን የጣዖት አምልኮ ሥፍራ ሆኗል (see notes at አሞ 4:4፤ 5:5 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት)፡፡
ሌላው የደቡቡን ግልገላ ያሳያል፣የነቢያት ትምህርት ቤት ቦታ የነበረው (ዝ.ከ. II ነገስ 2:1፤ 4:38) ፣በኋላ ላይ የበአል የአምልኮ ማዕከል የሆነው (ዝ.ከ. 9:15፣ 12:11፤አሞ 5:5፣ see *HardSayings of the Bible*፣ p 330)

▣ **"ቤትአዌን"** ይህ ቤትኤልን ያሳያል (ዝ.ከ. 4:15፤ 5:8፤ 10:5፤አሞ 5:5) ፣ "የእግዚአብሔር ቤት፣" በሚያሳዝን ሁኔታ ወደ "አመጸኞች ቤት" የተለወጠው (BDB 110)፡፡ ይህ በእዮርባም ከተሠሩት ሁለት "ከወርቅ የተሠራ ጥጃ" አምልኮ ቦታ አንዱ ነበር (ዝ.ከ. I ነገስ 12:28-29)፡፡ ሲጀመር ጥጃው ያህዌን ይወክል ነበር (ዝ.ከ. ዘፀ32) ፣ ግን በፍጥነት ወደ ለምለም ምልክት ተቀየረ፡፡

▣ **"እናም መሃላ ተቀበሉ :ሕያው እግዚአብሔርን"** ይህ መሃላ የያህዌ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ስምን ያንፀባርቃል (ዝ.ከ. ዘፀዓ 3:14) ልዩ ርዕስ ተመልከት: የአምላክ ስሞች አሞ 1:2 የ ቁ 15ሐ አሉታዊ ቅርፅ በ 15መ-ረ ተንጸባርቋል፡፡

**4:16 "እስራኤል እንደ እልከኛ ጊደር እንቢ ብሎአል"፣** "እንቢ" የሚለው ቃል (BDB 710፣ KB 770) ኤስራኤልን ከእልከኛ የእርሻ እንስሳ ጋር በማነፃፀር ሁለት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል (ማለትም፣ ለጌታው አለመታዘዝ) ። ይህ ብዙ ጊዜ ለአመፅ መንፈስ ያገለግላል:
1 የልጅ፣ዘዳግ 21:18-21
2 ገገር፣ኢሳ 1:23 (ዝ.ከ. ሆሴ 9:15)
3 የሕፃናት፣ኢሳ 30:1
4 ሕዝብ፣ኢሳ 65:1-7
5 የእግዝሐበሄር ሕዝብ፣ኤርም 6:28

▣ **"እንብተኛ" እና "አመፀኛ"** ብዙ ጊዜ አንድ ላይ ይመጣሉ (ዝ.ከ. ዘዳግ 2:18፣20፤መዝ 78:8፤ኤርም 5:23)
"እግዚአብሔር ያሰማራዋልን?" ይህ ዐረፍተ ነገር ወይም እንከን የሌለ የሥነ-ቋንቋ ጥያቄ ሊሆን ይችላል።
አውዱ የፍርድ ከስተት እንደ ሆነ ያሳያል እንጂ (ማለትም፣ምርኮ) ፣የተወዳጅ እረኛ ጥንቃቄ አይደለም።

▣ **"በሰፊው ቦታ እንደጠቦት"** ጠቦት ጠበብ እንጂ፣ ሰፊ ቦታን አትወድም።

**4:17 "ኤፍሬም ከጣዖታት ጋርተ ጋጠመ።"** ኤፍሬም ከኤሴራኤል ትልቁ ጎሳ ነበር፣ስለዚህ የደቡብን አሥር ጎሳዎችን ይወክላል። የመጀመሪያው ንጉሳቸው ከኤፍሬም ጎሳ የሆነው፣ እዮርባም ነነበር። "ተጋጠመ" የሚለው ቃል በተባበሩት የፖለቲካ (እናም የእምነት እንድምታ) ህብረት መካከል ትልቅ ቃል ነው (BDB 287፣ KB 287፣*Qal* PASSIVEPARTICIPLE፣ዝ.ከ. ዘፍጥ 14:3)፡፡
David A Hubbard፣ ሆሴዕ (The Tyndale OT Commentaries) ፣የሚያቀርበው ሐሳብ "ተጋጠመ" የሚል ቃል በጥንቆላዊ ጽሑፍ ውስጥ እንደ አጠቃቀሙ መተርጎም እንዳለበት (ዝ.ከ. ዘዳግ 18:11፤መዝ 58:5) ። እንዲህ ከሆነ፣ኤሴራኤል ሞገስ አገኝታለች ወይም "በጥንቆላ ሥር ናት" ከ 4:12፤ 5:4 ጋር ሊያያዝ ይችላል (ገጽ 110) ። እዚህ ላይ ያለኝ ችግር ሥነ-ጽሑፋዊው ሳይሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊው ነው።
ለወደቀው የሰው ልጅ ኃጢአት ክፉን እንደ ሰው አድርጎ ማቅረብ እንደ ይቅርታ አይጠቅምም። እነዚህ ሰዎች ኃጢአት ሠሩ "የተከፈተ ዓይን" የቃል ኪዳን አምላካቸውን ተቃወሙ። ክፉ ቢሆንም፣ሁለቱም ተፈጥሮና ግል፣የወደቀው የዓለማችን ክፍል ነው፣አሁንም ቢሆን የሰው ልጅ ለድርጊቶቻቸው ተጠያቂ ናቸው (ዝ.ከ. ቁ 18ሐ)፡፡

▣ ***"ተወው"*** *ምን* ዓይነት የሚከብድ ፍርድ ነው (BDB 628፣ KB 679፣*Hiphil* ትዕዛዝ አንቀፅ) ። ከመንፈሳዊ እውርነታቸው የተነሳ (ዝ.ከ. 5:4፤ሮማ 1:24፣ 26፣ 28) ። እግዚአብሔር ሕዝቡ የራሱን ምኞት እና ምርጫ እንዲያገኝ እናም የሚያስከትለውንም) ይፈቅዳል።
4:18 የደስታ ጊዜ አልቋል! "ገዢዎች"ቃሉ በቀጥታ "ጋሻ" ማለት ነው (BDB 171) ። ብዙ ጊዜ የፖለቲካ መሪዎችን ያመለክታል፣ዳሩ ግን እዚህ ካህናትንና ነቢያትን ያጠቃልላል (ዝ.ከ. ቁ 5) ።

**4:19 "ነፋስ በክንፍዋ አስሮአታል"** የ "ነፋስ ክንፎች" ምሳሌያዊ ነው
1 የውጭ ድርጅቶች (ዝ.ከ. 12:1)
2 ሊመጣ ያለውን የያህዌን ፍርድ (ዝ.ከ. 13:15፣ማለትም፣ሕዝቡ በምርኮ እንዲወሰዱ ያህዌ የሜስፖታምያን ኃይል ተጠቀመ፣ዝ.ከ. ኤርም 22:22)
3 የክፉ መንፈስ ተፅእኖ (ማለትም፣ "ነፋስ" ስተረጎም "መንፈስ፣" ዝ.ከ. 4:12፤ 5:4)
ያህዌ በነፋስ ክንፎች እንደሚሄድ ይታያል (ዝ.ከ. IIሳሙ 22:11፤መዝ 18:10፤ 104:3) ። የያህዌ መገኘት የቃል ኪዳን ደህንነትን እና ጥበቃን ፣የቃል ኪዳን ፍትህነትን እና የቃል ኪዳን መፍረስ ውጤቶችን ያሳያል!

**ለምዕራፍ 3 እና 4 የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1 በምዕራፍ 3 ውስጥ ለምን ዳዊት በደቡብ ኤስራኤል አውድ ተጠቀሰ?
2 በ 3:5ውስጥ የተጠቀሰውን የመጽሐፍ ቅዱስ እምነት አመለካከትን አብራራ።
3 ታማኝነትን፣ ትሑትነትን፣ እና እውቀትን በራስህ ቃላቶች ተርጉም።
4 እንዴት አድርጎ የዘመኑ ሰው ዝሙት ውስጥ መሳተፍ ይችላል?

# ሆሴዕ 5

## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
| --- | --- | --- | --- |
| በእስራኤል እና በይሁዳ ላይ ሊሆን ያለ ፍርድ | ቀዋሚ ስለሁነው የእስራኤል አመፃ ምክንያት የተነሳ የእግዚአብሔር ፍርድ በእስራኤል ላይ ነው (4፡1-14፡9) | የእግዚአብሔር የአረማዊያንን አምልኮን ይወቅሳል (4:11-5:3) | በካህናትና በነገሥታት ቤት ላይ |
| | | | 5:1-2 |
| 5:1-7 | | | የእልከኝነት ተፅእኖ |
| | 5:1-2 | | |
| | | ሆሴዕ አመንዝራነትን ያስጠነቅቃል | 5:3-7 |
| | 5:3-4 | | |
| | | 5:4-7 | |
| | | በእስራኤል እና በይሁዳ መሃከል ጦርነት | ወንደማማቾች መሀከል ጦርነት |
| | 5:5-7 | | |
| 5:8-15 | | 5:8-9 | |
| | | | 5:8-12 |
| | 5:8-14 | | |
| | | 5:10-12 | የውጭዎች ስምምነት ስንፍና |
| | | 5:13-14 | 5:13-15 |
| | | 5:15 | |
| | 5:15-6:3 | | |

### የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ vii ተመልከት)

*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**ሆሴዕ: 5:1-7**

**1ካህናት ሆይ፥ ይህን ስሙ የእስራኤል ቤት ሆይ፥ አድምጡ የንጉሥ ቤት ሆይ፥ ልብ አድርጉ በምጽጳ ላይ ወጥመድ፥ በታቦርም ላይ የተዘረጋ**
**አሽክላ ሆናችኋልና ፍርድ በእናንተ ላይ ነው። 2 ዓመፀኞችም እርድ አብዝተዋል እኔ ግን እነዚያን ሁሉ እዘልፋለሁ።ኤፍሬምን አውቀዋለሁ፥**
**እስራኤልም ከእኔ አልተሰወረም ኤፍሬም ሆይ፥ ዛሬ አመንዝረሃል፥ እስራኤልም ረከሶአል።4 ወደ አምላካቸው ይመለሱ ዘንድ ሥራቸውን**
**አላቀኑም የግልሙትና መንፈስ በውስጣቸው አለና እግዚአብሔርንም አላውቁምና።5የእስራኤልም ትዕቢት በፊቱ ይመሰክራል ስለዚህ እስራኤልና**
**ኤፍሬም በኃጢአታቸው ይሰናከላሉ ይሁዳም ደግሞ ከእነሱ ጋር ይሰናከላል።6 እግዚአብሔርንም ለመሻት በጎቻቸውንና ላሞቻቸውን ነድተው**
**ይሄዳሉ ነገር ግን እርሱ ከእነርሱም ተመልሶአልና አያገኙትም።7 ዲቃሎችን ልጆች ወልደዋልና እግዚአብሔርን ወንጅለዋል አሁንም አንድ ወር**
**እነርሱንና ርስታቸውን ይበላቸዋል።**

**5፡1፣ 2** "ስሙ" በ4፡1 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት፡፡ ይህ ምዕራፍ ከእግዚአብሔር መልዕክት ጋር በተገናኘ በሦስት ትዕዛዞች( ትዕዛዝ አንቀፅS) ይጀምራል፡፡

1. ስሙ፣ BDB 1033፣ KB 1570፣ *Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)* ፣ "ስሙ እና ታዘዙ፣" ምሳሌ፣ ዘዳግ 6:4
2. ማተኮር፣ BDB 904፣ KB 1151፣ ትዕዛዛዊ ሂፍል(*Hiphil* ትዕዛዝ አንቀፅ)፣ "በትኩረት አድምጥ" ምሳሌ ፣ እሳ 10:30፤ 28:23፤ 34:1፤ 49:1፤ ሚክ 1:2
3. Listen፣ BDB 24፣ KB 27፣ ትዕዛዛዊ ሂፍል(*Hiphil* ትዕዛዝ አንቀፅ)፣ "ጆሮ ስጡ" ምሳሌ ፣ ዘፍጥ 4:23፤ ዘኁል 23:18፤ እሳ 32:9

እነዚህ ሦስት የተላያዩ ግሶች ሦስት የተለያዩ ቡድኖችን ያሳያሉ፡-

1. ካህናት ሆይ
2. የእስራኤል ቤት ሆይ
3. የነጉስ ቤት ሆይ

▣ ***"ምጽጳ ታቦር የተዘረጋ አሽክላ ሆናችኋልና"*** እዚህ ሦስት የተላያዩ መልካዓ ምድራዊ መቼቶች ተመቅሰዋል(ሦስቱን ትዕዛዞች እና ሦስቱን ቡድኖች ያአምዳል)፡፡ "**የተዘረጋ አሽክላ ሆናችኋልና**" ሽቲም በሚለው የቦታ ስም መተርጎም አለበት (BHS ማተካከያ ያስቀምጣል፣ ዝ.ከ. ዘኁል 25:1ff)

▣ ***"ምጽጳ"*** ይህ ማለት (BDB 859) "ግዛት" ወይም "መጠበቂያ ግንብ"፡፡ ትክክለኛ ቦታቸው ግልጽ ያልሆነ በተስፋይቱ ምድር ውስጥ ተበትነው የነበሩ እና በዚህ ስም የሚጠሩ ብዙ ከተሞች አሉ፡፡ ዳኑ ግን፣የወንዱ ፍሬያማ ጣዖት፣በአል ምሳሌ ቅዱስ ዓምዶች ስፍራ እንደ ሆነ እናውቃለን፡፡

▣ ***"ታቦር"*** ይህ (BDB 1061) የዘዳግ 33:18-19 መጣቀሻ ሊሆን የሚችል ነው፡፡ እንደ ማንኛውም የጥንቱ ስፍራ ለያህዌ የተሰጠ ነበር፤አሁን ግን ከጢሮስ የበአል አምልኮ ጋር ተደባልቋል፡፡

▣ ***"መረብ"*** ቃሉ(BDB 440) የዓሳ መጥመጃ መረብን ያመለክታል፣ ግን ለወፎች ከሚሆን ወጥመድ ጋር ከመቀራረቡ የተነሳ እሱ ሊሆን ይችላል(መሳሌ፣ 7:12፤ ምሳሌ 1:17)፡፡ ካህናት ታማኝነት ያህዌን የሚያመልኩትን ያህዌ በሚመለክበት ሥፍራ በተደባለቀ ፍሬያማ ጣዖት አምልኮ እንዲጠመዱ መከራ ያድርጉ ነበር፡፡

**5:2**

| | |
|---|---|
| **NASB፣ NKJV** | **"አመፀኞቹ"** |
| **NRSV፣ NJB** | **"ሽጢም"** |
| **TEV** | **"በአካኪያ ከተማ"** |

ይህ (BDB 962) could mean "የሽፈቱ" ወይም "ያመፁ" ሊሆን ይችላል፣ግን ብዙ ተንታኖች እንደሚሉት ይህ ግጥም መስመር ማለት " እናም በጥልቀት ያዘጋጁት የሽጢም ገድጓድ ነው" (ማለትም፣ ሦስቱን ትዕዛዞች እና ሦስቱን የሰዎቹን ቡድን ለማዛመድ ሌላ ከተማ ይሆናል)፡፡

ማሶሬቲኩ "ጥልቅ ማድረግ" የሚል ግስ አለው(BDB 770፣ KB 847፣ የተፈፀመ ሂፍል(*Niphil* PERFECT)፣የሰው ልጅን እሴት የሚያሳይ የእስራኤል ሕግ በሚል መልኩ ጥቅም ላይ ውሏል(ዝ.ከ. 4:2፤ 6:9)፡፡ በ 9:9 ውስጥም በጋባኦን የሆነውን ኃጢአት እና ሞትን ለማሳየት ተመሳሳይ ቃል ጥቅም ላይ ውሏል(ዝ.ከ. መሳ 19)፡፡ ይህንን መስመር ግጥም "ዓመፀኞችም እርድ አብዝተዋል" (BDB 1006) በሚል ልወሰድም ይቻላል፡፡ ይህ ትክክል ከሆነ የሕፃናትን መስዋይት የሚያሳይ ሊሆን ይችላል(ዝ.ከ. እሳ 57:5 እና ሕዝ 23:39)፡፡

**5:3 "ኤፍሬም እና እስራኤል"** ከክርስቶስ ልደት በፊት በ922 የይሁዳ መንግስት ከተከፋፈለ በኃላ የደቡቡ ጎሳ ቀጥለው ባሉት ስሞች ይታወቁ ነበር: (1) በዋና ከተማቸው፣ ሰማርያ፤ (2) በትልቁ ጎሳቸው፣ኤፍሬም(ለምሳሌ፣ እሳ 7:9፣17)፤ እና (3) ቀዳሚያቸው ለሆነው ለያዕቆብ የአጠቃላይ ስም፣በእሰራኤል፡፡

▣ ***"አውቃለሁ ከእኔ አልተሰወረም"*** እነዚህ ሁለት ግሶች(#1 BDB 393፣ KB 390፣ *Qal* PERFECT፣ #2 BDB 470፣ KB 469፣ የተፈፀመ ኒፍል(*Niphal* PERFECT) የእግዚሐብሄርን ሁሉን ቻይነት የሚጋሩ ናቸው(በግለሰብ ደረጃ መዝ 69:5፤ 139:15 ተመልከት)፡፡ ጣዖት አምላኪነታቸውን ያውቃል(ዝ.ከ. ቁ 3ለ እና ሐ)፣ የቃል ኪዳን ሕዝቡ ከመሆናቸው የተነሳ መጥፎውን ሁሉ ያመጣ(ዝ.ከ. አሞ 3:2፣ "የማውቀውን ብቻ አለህ" NRSV)፡፡

▣ ***"እስራኤልም ረክሶአል"*** የግሱ (BDB 379፣ KB 375፣ *Niphal* PERFECT) ትርጉም የሙሴ ሕግ የሚከለክለውን በመጣስ "በአምልኮ ስነ-ስርዓት ቅድስና ማጣት" (ዝ.ከ. 6:10፤ 9:3-4፤
ሚክ 2:10)፡፡ የ"ንፁሕ" እና "እርኩስ" መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ በሌዋ 10:10፤ ዘዳግ 12:15፣22፤ 15:22፤ ሕዝ 22:26፤ 44:23) በግልጽ ተቀምጧል፡፡

**5:4 *"ወደ አምላካቸው ይመለሱ ዘንድ ሥራቸውን አላቀኑም"*** ይህ ቁጥር የእስራኤልን ጣዖት አምላኪነት በግልጽ ያስቀምጣል(ዝ.ከ. ቁ 5)፡፡ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ከ4:12፣19 ጋር በማያያዝ እንደ ግል ከፋት ጫና ያዩታል፡፡
የእስራኤል ሕዝብ የመመለስ ወሰን በማለፍ በመጥፎ ድርጊታቸው ውስጥ በረቱ(ማለትም፣ "የዝሙት መንፈስ") (ዝ.ከ. 4:17፤ መዝ 81:12፤ ሮማ 1:24፣26)፡፡

▣ ***"እግዚአብሔርንም አላወቁምና"*** "አላወቁም" የሚለው የእብራይስጡ ቃል የጠበቀ ህብረትን ያሳያል(ዝ.ከ. ዘፍጥ 4:1)፡፡
በቅርበት በአምልኮ ስነ-ሥርዓት ውስጥ የሚሳተፉ ቢሆኑም እንኳ ከእግዚአብሔር ጋር ለያት ያለ ህብረት አልነበራቸውም(ዝ.ከ. እሳ 29:13)፡፡ እውቀት ማጣት፣ቃል ኪዳናዊም ሆነ የግል፣ የማይቋረጥ የሆሴዕ ዋና ርዕስ ነው(ዝ.ከ. 2:20፤ 4:1፣6፤ 6:3፣6)፡፡

**5:5**

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"የእስራኤልም ትዕቢት በእርሱ ይመሰክራል"** |
| **NKJV** | **"የእስራኤልም ትዕቢት በፊቱ ይመሰክራል"** |
| **NRSV** | **"የእስራኤል ትዕቢት በፊቱ ይመሰክራል"** |

TEV "የእስራኤል ሕዝብ እብሪተኝነት በእነርሱ ይጨአል"
NJB "የእስራኤል እብሪተኝነት ይከሰዋል"

ከአሞ 8:7 የተነሳ አንዳንዶቹ ይህንን ያህዌን የሚያሳይ አድርጎ ያዩታል፣ በዚህ አውድ ግን የእስራኤልን ምን ያህል ቃል ኪዳን እንደሚተማመን ያሳያል፡፡ እሷ በጣም አይማኖተኛና በጣዖት አምልኮ ንቁ ነበረች፡፡ በሁለት እንድትፋረጅ ያደረጋት ይህ የቅርፅ፣የቤተ-መቅደስ ሥርዓት እና የአምልኮ ሥርዓት ትዕቢት ነው፡- (1) ያለ እውነተኛ እምነት የሆነ ቅርፅ እና (2) ትክክል ባልሆነ አምልክ መታመን፡፡ "ብዙ ከተሰጠው፣ ብዙ ይፈከግበታል" (ሉቃ 12:48)፡፡ ይህ የኪዳን እውቀት አስተሳሰባቸው እና ድርጊታቸው የበለጠ ክፉ እንዲሆን አድጓል!

▣ **"መሰናከል ተሰናከሉ"** ግሱ(BDB 505፣ KB 502) በ ቁ 5 ውስጥ ሁለት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በብሉ ኪዳን የእግዚአብሔር ፈቃድ ለሕዝቡ እንደ መንገድ ይወሰድ ነበር፡፡ መንገዱን መልቀቅ እና በመንገዱ ላይ መሰናከል የኃጢአት እና የአመፅ ተምሳሌት ነበርn (ዝ.ከ. 14:1)፡፡ "መሰናከል" እምብዛም ከ" ውድቀት" ጋር ይያያዛል (ዝ.ከ. ምሳሌ 24:17፤ እሳ 3:8፤ 31:3፤ ኤርም 6:15፤ 8:12፤ 46:6፣16)፣ ግን እንደዚሁም በተምሳሌታዊ ስሜት ያገለግላል፡፡

**5:6 "በጎቻቸውንና ላሞቻቸውን ነድተው ይሄዳሉ"** እስራኤል በመሰዋይት ብዛት ያህዌን ለመቅረብ ትፈልጋለች፣እርሱም ሆነ(ዝ.ከ. አሞ 5:21-23፤ እሳ 1:10-15፤ ኤርም 14:12፤ ቃሉ አየገኙም፣ አሞ 8:12)!
ወደ ቅዱሱ እግዚአብሔር ለመቅረብ መንገድ የሆነው፣ የመስዋይት ሥርዓት፣ ፈረሰ! ኪዳኑም ተሰበረ!
**5:7 " እግዚአብሔርን ወንጅለዋል "** ግሱ(BDB 93፣ KB 108፣ *Qal* PERFECT) በመደበኛነት ለጋብቻ ቃል ኪዳን ያገለግላል (ለምሳሌ፣ ሚል 2:14-16)፡፡ እዚህ እስራኤል ለያህዌ እምነት የለሽ መሆኗን ለመግለጽ ያገለግላል(ዝ.ከ. ኤርም 3:20)፡፡

▣ "ዲቃሎችን ልጆች" ይህ ሊወሰድ የሚችለው
1. በቀጥታ፣ካህናት እና ሕዝብ በንቃት ፍሬያማ የጣዖት አምልኮ ውስጥ ተሳትፈዋል
2. በተምሳሌታዊ፣ እስራኤል ራሷን ከወረራ ለመከላከል ያህዌን ከመፈለግ ይልቅ የውጭን አካል ትፈልጋለች

▣ **"አንድ ወር እነርሱንና ርስታቸውን ይበላቸዋል"** አሁንም ግል ጉዳይ የማድረግ ቀትታ ዘዴን አስተውል፡፡ ያህዌ ሁሉንም የእስራኤል በኣላትን ናቀ(ዝ.ከ. 2:11)፡፡

## ሆሴዕ: 5:8-15

**[8] በጊብዓ መለከትን፥ በራማ እንቢልታን ንፉና። ብንያም ሆይ፥**
**ከአንተ በኋላ እያላችሁ በቤትአዌን ላይ እሪ በሉ።**
**[9] ኤፍሬም በዘለፋ ቀን የፈረሰ ይሆናል። በእስራኤል ነገዶች ዘንድ በእርግጥ የሚሆነውን ነገር ገልጫለሁ።**
**[10]የይሁዳ አለቆች ድምበርን እንደሚነቅሉ ሆነዋል እኔም መዓቴን እንደ ውኃ አፈስስባቸዋለሁ።**
**[11] ኤፍሬም ከትእዛዝ በኋላ መሄድን ወድዶአልና የተገፋና በፍርድ የተጐዳ ሆኖአል።**
**[12] እኔም ለኤፍሬም እንደ ብል፥ ለይሁዳም ቤት እንደ ነቀዝ ሆኜአለሁ።**
**[13] ኤፍሬምም ደዌውን፥ ይሁዳም ቍስሉን ባየ ጊዜ ኤፍሬም ወደ**
**አሦር ሄደ ወደ ንጉሡም ወደ ኢያሪም መልእክተኛን ላከ**
**እርሱ ግን ይፈውሳችሁ ዘንድ፥ ከቍስላችሁም ያድናችሁ ዘንድ አልቻለም።**
**14እኔም ለኤፍሬም እንደ አንበሳ፥ ለይሁዳም ቤት እንደ አንበሳ ደቦል እሆናለሁና**
**እኔም ነጥቄ እሄዳለሁ እወስድማለሁ፥ የሚያድንም አይገኝም።**
**[15] በደላቸውንም እስኪያውቁ ድረስ፥ ፊቴንም እስኪሹ ድረስ ሄጄ ወደ**
**ስፍራዬ እመለሳለሁ በመከራቸው ጊዜ እጅግ አድርገው ፊቴን ይፈልጋሉ።**

**5:8-15** ይህ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ735-732፣ ያለውን የእስራኤል- ሲርያ ውጊያ ያሳያል፡፡ እስራኤል እና ሲርያ ሶርያን ተቃወሙ እናም ይሁዳ ተቃዉሞውን ለመቀላቀል አሰባ ነበር፡፡ ይሁዳ አላደረገችም፣ስለዚህ እንዲትቀላቀል ለማድረግ አጠቋት (ዝ.ከ. 11 ነገስ 16:1ff እና እሳ 7:1ff )፡፡ የእነዚህ ወረራ ግትም መነሻ(ዳራ) ሳይሮ ኤፍሬማቲክ ወረራ ነው ብሎ ለማሰብ ችግሩ በቀ 13 ላይ የተጠቀሰችው ሦርያ ነእስራኤል ተከትላለች፡፡ ይህ የአስራኤልንና የሥርያን ተቃውሞ መሠረት በማድረግ ሦርያ ካደረገችው ጥቃት ጋር አይገጥምም፡፡

**5:8** ይህ ቁጥር የእስራኤል ወረራን ይናገራል፡፡ የእግዚአብሔር ፍርድ ምድርቱን ለመጥረግ የእርሱ መሳር ሆኖ በውጭ የአሕዛብ ሕዝብ(ሦርያ) መጣ!
የ ቁ 8 ሦስቱ ከተሞች(ጊብዓ፣ ራማ፣ እና ቤትአዌን) ከይሁዳ ጋር ሊያያዙ ነው(ማለትም፣ ብንያም)፡፡
ይህ ምናልባት ቁ 10 ላይ "ድምበርን የነቀሉ" ለሚል ማሳያ ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህ ከተሞች የእስራኤል ንጉስ በሆነው በኢዮአስ ከይሁዳ ተወስደዋል (ዝ.ከ. 11 ነገስ 14:8-14፤ 11 ዜና 25:17-24)፡፡

**5:8 "መለከትን እሪ በሉ"** ይህ ግስ(BDB 1075፣ KB 1785፣ *Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)* ) ሾፋርን( shophar) (የወደቀ የኮርማ ቀንድ፣ BDB 1051) ያመለክታል፡፡ ከሌሎች የሙዝቃ መሣርያዎች ጋር በተያያዘ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ አልነበረም፡፡ ይጠቅም የነበረው
1. ለአምልኮ ድርጊቶች
   ሀ. ታቦቱ ሲንቀሳቀስ
   ለ. የበዓል ቀናት
   ሐ. የመጨረሻው ዘመን ድርጊት

2. ወታደራዊ ድርጊቶች
ሀ. የአጥቂ መቅረብ
ለ. ወታደርን ለመትራት
ሐ. ከጥቃት ለመመለስ
በዚህ አውድ #2 በደንብ ይገጥማል(ለምሳሌ፣ ኤርም 4:5፤ 6:1፤ ኢዮኤል 2:1፣15)፡፡

▣ **"ጥሩምባ"** ይህ (BDB 348) በቀጥታ ከነሀስ የተሰራ ጥሩምባ ነው፡፡ እርሱም የነበረው
1. ለአምልኮ ከሌሎች መሳርያዎች ጋር ያገለግላል
2. ስብሰባን ለመጥራት ያገለግላል
3. በንጉስ ንግስ ጊዜ ይጠቅማል
4. በዓላትን ለማስጀመር ይጠቅማል
5. ለወታደራዊ ፈይዳ ይጠቅማል

አውዱከ #5 ጋር በደንብ ይገጥማል፡፡

▣ **"በቤትአዌን ላይ እሪ በሉ"** ግሱ (BDB 929፣ KB 1206፣ *Hiphil* ትዕዛዝ አንቀፅ) ለጦር ጩኸት፣ የድል ድምፅ፣እና የቀንድ ጥሩምባ፡፡ እዚህ የማስጠንቀቂያ ድምፅ በጣም ይገጥማል፡፡
ቤትአዌን ማለት "የአመፀኞች ቤት" (ዝ.ከ. 4:15፤ 5:8፤ 10:5)፡፡ እዮርባም 1 የወርቃማ ጥጃ አቁሞ በያህዌ ፋንታ እንዲመለክ(ዝ.ከ. አሞ 5:5)፣ቤትኤል("የእግዚአብሔር ቤት")፣ ያቆመውን ያመለክታል፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"ብንያም ሆይ፣ ከአንተ በኋላ "** |
| **NKJV፣ NRSV** | **"ብንያም ሆይ፣ከኃላይ ተመልከት"** |
| **TEV** | **"የብንያም ሰው፣በውጊ ውስጥ"** |
| **NJB** | **"ብንያም ሆይ፣ ከአንተ በኋላ ነን"** |

ይህ ከአውዱ ጋር አይገጥምም በጣም ብዙ ተርጓሚዎች የሰብቶአጀንቱን(Septuagint) ይከተላሉ፣ልዩ የእብራስጥ ባህልን የሚያንፀባርቅ፣ "ብንያም ፣በፍርሀት ንቀጠቀጠ፡፡"

**5:9**

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"በእስራኤል ነገዶች ዘንድ በእርግጥ የሚሆነውን ነገር ገልጫለሁ"** |
| **NKJV፣ NRSV** | **"በእስራኤል ነገዶች መካከል በእርግጥ የሚሆነውን ነገር አሳውቀሃለሁ"** |
| **TEV** | **"የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፣ይህ በእርግጥ ይሆናል"** |
| **NJB** | **"በእስራኤል ጎሳዎች ለይ እውነተኛ የሆነ ጥፋት ተናግረሃለሁ"** |

ይህ ሊመጣ ያለው የእግዚአብሔርን ፍርድ ውነታነትን ያንፀባርቃል(ለምሳሌ፣ እሳ 14:24 ፣ 20-27፤ 25:1፤ 46:10)፡፡

**5:10 "የይሁዳ አለቆች ድምበርን እንደሚነቅሉ ሆነዋል"** ይሁዳ እስራኤል ውስጥ ያለውን የድካም ጊዜን በመጠቀም አንዳንድ ከሰሜኑ እስራኤል ጊዛት ጋር ተያያዘች፡፡ ድምበርን መንቀል የጥንት ጭካኔ ነው(ዝ.ከ. ዘዳግ 19:14፤ 27:17፤ ምሳ 22:28፤ 23:10፤ ኢዮ 24:2)፡፡

**5:11 "የተገፋና ... የተጐዳ"** These are both *Qal* PASSIVE PARTICIPLES (#1 BDB 1075፣ KB 1785፤ #2 BDB 929፣ KB 1206)፡፡ እዚህ የውጭን ወራሪዎች ተጠቅሟል (ዝ.ከ. እሳ 52:4፤ ኤርም 50:33)፡፡ እነዚህ ተመሳሳይ ሁለት ቃሎች እኮኖሚያዊ ሀብትን ያለአግባብ መጠቀሚን ያሳያሉ(ምሳሌ፣ 12:7፤ ዘዳግ 24:14፤ ኤርም 7:6፤ አሞ 4:1)፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"ከሰው ትእዛዝ በኋላ መሄድን ወድዶአልና"** |
| **NKJV** | **"ወዶ በሰው ትዕዛዝ ይሄዳል"** |
| **NRSV** | **"ራሱን ብቻ መከተልን ወድዶአል"** |
| **TEV** | **"ምንም ወደማይሰጧት መሄድን አላቆም አለች"** |
| **NJB** | **"በዓላማ ውሸትን ትከተላለች"** |

ችግር የሆነው ቃል "ትዕዛዝ" የሚለው ነው(BDB 846)፣ እዚህ እና በእሳ 28:10 (ዝ.ከ. ቁ 13) ውስጥ ብቻ ጥቅም ላይ የዋለ፡፡ አድሱ መደበኛ ትርጉም(NIV) ከሌላ እብራይስ ሥር ይወስድና "ጣዖታት" (TEV፣NJB) ብሎ ይተረጉመዋል፣ ይህም ታርጉም(Targums)፣ ሰባ ሊቃናት ትርጉም(Septuagint)፣ እና የሦርያን ትርጉሞች የሚከተል ነው፡፡
አያሌ የዘመናችን አይማኖተኝነት ዝም ብሎ ባህል ነው እንጂ የእግዚአብሔር ቃል አይደለም(ዝ.ከ. እሳ 29:13፤ ቆላ 2:16-23)፡፡

**5:12**

| | |
|---|---|
| **NASB፣ NKJV** | **"ነቀዝ"** |
| **NRSV** | **"የሥጋ ትል"** |
| **TEV** | **"ጥፋት"** |
| **NJB** | **"ላሸ"** |

ይህ በቀጥታ “ነቀዝ” (BDB 799፣ ዝ.ከ. መዝ 39:11፤ ኢሳ 50:9፤ 51:8) ነው፡፡ የጥፋት ተምሳሌት ነበር(ዝ.ከ. TEV)፡፡ እግዚአብሔር በትል እና በመበስበስ እስራኤልን እና ይሁዳን ይቀጣቸዋል(BDB 955)፡፡
“ነቀዝ” (51 BDB 799) ለሚለው ቃሉ ከሌላ ሥር ልንሆን ይችላል (55፣ BDB 799)
ማለትም “የማይጠቅም፣” እዚህ ግን የሚያቃጥል እንደ ማለት ነው፡፡

▣
NASB፣ NKJV፣
NRSV “መበስበስ”
TEV “ፍርስራሽ”
NJB *“ጋንግሪን”*
NAB “የስጋ ትል”

ቃሉ (BDB 955) “በትል የተበላ” ማለት ነው፡፡ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂች “ነቀዝ” የሚለው “ትል መልታ” እንደሚጋራ ይገምታሉ፡፡ ይሁን እንጂ፣ይህ ቃል ከሚታይባቸው ሌሎች ሥፍራዎች የአጥንት ውስጡ መበስበስን ያሳያል (ዝ.ከ. ኢዮብ 13:28፤ ምሳሌ 12:4፤ 14:30፤ እንባቆ 3:16)፡፡

**5:13 ሁለቱ እስራኤል እና ይሁዳ ከውጭው የአሕዛብ ግዛቶች ፖለትካ ድርጅት እርዳታ በመፈለግ ለእግዚአብሔር ፍርድ መልስ ለመስጠት ነበር፣** እንጂ ወደ ኪዳን አምላካቸው በንስዐ እና እምነት አልነበረም፡፡

▣ ***“እመም” ቃሉ*** (BDB 318) “በሽታ” ወይም “መታመም” ማለት ነው፡፡ የሐጥኃተኝነት ተምሳሌት ነው(ለምሳሌ፣ እሳ 1:5-6 እና 53:4 ተመልከት፣ለተመሳሳይ አመለካከት)፡፡ ይህ “በሽታ” ሕጉን ካልታዘዙ የመጣባቸዋል ብሎ ሙሴ ካስጠነቀቃቸው ውስጥ አንዱ ነው(ምሳሌ፣ ዘዳግ 7:15፤ 28:59፣61)፡፡

▣ ***“ቁስል ቁስል” ይህ ቃል***(BDB 267) “ወደ ውጭ መግፋት” ማለት ነው (ማለትም፣ ቆሻሻ እና በቁስል ውስጥ ያሉ አለስፈላጊ ነገሮች፣ለማጽዳት)፡፡ በኤርም 30:13 ውስጥ አጠቃቀሙን ተመልከት፡፡ ቁስሉ ካልጸዳ እና ካልተሸፈነ ቁስሉ እውነተኛና ለሞት የሚዳርግ ነው፡፡ እስራኤል ታማለች፣ይሁዳም ቆሸሻለች ስለዚህ ያ ሞት (ምሳሌ፣ የእግዚአብሔር ፍርድ) እና ምርኮው እርግጥ ነው፡፡ ሊያድን እና ሊያነፃ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ያንን የሚያደርገው እርሱን ከፈለጉና ንስዐ ከገቡ ብቻ ነው(ዝ.ከ. ቁ 5)፡፡

▣ ***“ንጉስ ኢያርም”*** ይህ የሦርያ ንጉስ ለነበረው ለቴጌል ፕላሶር III ቅፅል ስም ሊሆን ይችላል፡፡ ቃሉ “ንጉስ ጥላቻን መረጠ” ወይም “ንጉስ ከአውራ ዶሮ ጋር ተጋጠመ” (BDB 937፣ “፣”አርበኛ ዝ.ከ. 10:6) ማለት ነው፡፡ “ታላቅ ንጉስ” ወደሚለው መቀየር ይቻላል (ዝ.ከ. NRSV፣ TEV፣ NJB)፡፡ ግልጽ የሆነ የዛን ዘመን ነገስታት ዝርዝር: ቴጌል ፕላሶር III፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ745-727፤ ሰለምናሶር V፣ 7ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ27-722፤ሳረጎን II፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ722-704 ፤ እና ሴናክሬብ፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ704- 681፡፡

**5:14** እግዚአብሔር ራሱን ገለጸ (ማለትም፣ “እኔ፣ እኔ”) በፍርዱ ቁጣ እንደ አንበሳና እንደ አንበሳ ደቦል (ዝ.ከ. 13:6-8፤ መዝ 50:22፤ አሞ 1:2)፡፡ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለምርኮ የሚዳርጋቸው የአአዛብ ሕዝብ ኃይልም፣ የእግዚአብሔር ኃይል መጣትም አይደለም፣ ዳሩ ግን የተደጋገመ ሐጥኃታቸው እና አመፃቸው ነው፡፡ እግዚአብሔር እነዚህን ሕዝብ(ሦርያ፣ ባብሎን፣ ፔርሽያ) ለዓላማው ተጠቀመባቸው፡፡

## ልዩ ርዕስ: አናብስት በብሉይ ኪዳን

ብዙ ጊዜ የግለሰብ ወይም የሕዝብ ኃይል እንደ አንበሳ ይገለጻል፣ አድኖ ለሚበሉት እንስሳት ንጉስ፡፡

1. ይሁዳ፣ ዘፍጥ 49:9፤ ሚከ 5:8
2. ያህዌ በእስራኤል ፋንታ፣ ዘኍል 24:9፤ እሳ 31:4፤ 35:9፤ ሆሴ 11:10
3. እስራኤል እንደ ተሸነፈ አንበሳ፣ ሕዝ 19
4. የዳን ጎሳ፣ ዘዳግ 33:22
5. የዳዊት ጉልበት በአናብስት ላይ፣ I ሳሙ 17:34-37
6. ሳሙኤል እና ዮናታን፣ II ሳሙ 1:23
7. የሰሎሞን ዘፈን ጠባቂዎች ተምሳሌት፣ I ነገስ 10:19-20
8. እግዚአብሔር አንበሳን እንደ ቅጣት ይጠቀምበታል፣ I ነገስ 13፣20፤ II ነገስ 17:25-26፤ እሳ 15:9፤በኢዮብ 4:10 ውስጥ ተምሳሌት፤ ኤርም 2:30፤ 49:19፣44፤ Lam 3:10፤ አሞ 3:4፣8፣12፤ 5:19፤ ሆሴ 5:14፤ 13:7-8፤ ነህም 2:11-12
9. እግዚአብሔር ከሚያድነው የዳዊት ጠላቶችን ይገልጻል፣ መዝ 7:2፤ 10:9፤ 17:12፤ 22:13፣21
10. ለማይታወቅ ክፉ ተምሳሌት ነው፣ ምሳሌ 22:13፤ 26:13፤ 28:15
11. የባቢሎንን ወታደር ለመግለጽ ተጠቅሞበታል፣ ኤር 4:7፤ 49:19-22፤ 51:38
12. የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚቃወሙ የነገስታት ወታደር፣ ኤርም 5:6፤ 25:32-38፤ 50:17፤ኢዮኤል 1:6
13. የእግዚአብሔር ሕዝብ አምላካአቸውን እንዴት ማየት እንዳለባቸው፣ ኤር 12:8
14. የእግዚአብሔር መሪዎች ሕዝባቸውን እንዴት ማየት እንዳለባቸው፣ ሕዝ 22:25፤ ሶፎ 3:3
15. የተቆጣ ንጉስ ተምሳሌት፣ ምሳሌ 19:12፤ 20:2
16. የጻድቅ ተምሳሌት፣ ምሳሌ 28:1፤
17. የመሲይው ተምሳሌት፣ ዘፍጥ 49:9፤ ረአይ 5:5

በኤርምያስ ውስጥ በ #11 እና #12 ላይ፣ዳንኤል ለባብሎን ወታደር እንደ ፈጣን አንበሳ ተምሳሌት የወሰደው የታወቀ ነው፡፡ ለም ግዛቶች የሆኑ (Empires of the Fertile Crescent) ብዙ ጊዜ አንበሳን ለሕዝብ ለማስመሰል ይጠቀሙበታል፡፡

**5:15** ይህ ቁጥር ለተአድሶ እና ለንስዐ የተስፋ ብልጭታ አለው፣ ግን ሁነታዊ ነው(ዝ.ከ. 2:7)፡፡ የዘዳግ 4:25-31 መልካም ዜናን ወይንም መጥፎ ዜናን ያንፀበርቃል

▣ ***"በደላቸውንም እስኪያውቁ ድረስ"*** *ግሱ* (BDB 79፣ KB 95፣ *Qal* IMPERFECT) "በበደልኝነት መያዝ" ማለት ነው(ማለትም፣ ኪዳንን በመጣስ ሆነ በደል፣ ይህም ፍርድ የሚያስከትለው፣ ዝ.ከ. 5:15፤ 10:2፤ 13:16፤ መዝ 34:21-22፤እሳ 24:6፤ ኤርም 2:3፤ ሕዝ 6:6፤ Joel 1:18፤ ዘካ 11:5)፡፡

▣ ***"ፊቴን እስኪሹ ድረስ እጅግ አድርገው ፊቴን ይፈልጋሉ።"*** See note atበ 3:5 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተልከት፡፡ ሁለት የተለያዩ የእብራይስጥ ሥሮች አሉ፡፡

1. BDB 134፣ KB 152፣ የተፈፀመ ፒይል(*Piel* perfect)፣ ለምሳሌ፣ ዘፀ 33:7፤ ዘዳግ 4:29፤ I ዜና 16:11፤ II ዜና 7:14፤ ሆሴዕ 3:5፤ 5:6፤ 7:10፤ አሞ 8:12፤ ሶፎ 1:6፤ 2:3
2. BDB 1007፣ KB 1465፣ ያልተፈፀመ ፒይል(*Piel* IMPERFECT)፣ ለምሳሌ፣ ምሳሌ 8:17፤ እሳ 26:9፤ ሆሴ 5:15

# ሆሴዕ 6

## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|
| ለንስሐ ጥሪ | ቀዋሚ ስለሁነው የእስራኤል አመፃ ምክንያት የተነሳ የእግዚአብሔር ፍርድ በእስራኤል ላይ ነው (4:1-14:9) | የህዝቡ የውሸት ንስሐ (6:1-7:2) | የእስራኤላዊየን መላሽ |
| 6:1-3 | (5:15-6:3) | 6:1-3 | 6:1-6 |
| እስራኤልና ይሁዳ አለመጸጸት (6:4-7:10) | | | የእልከኝነት ተፅእኖ |
| 6:4-11 | 6:4-6 | 6:4-6 | በእስራኤል ውስጥ ስርአት መዛባት |
| | 6:7-11 | 6:7-10 | 6:7-7:2 |
| | | 6:11-7:2 | |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ vii ተመልከት)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ

2. ሁለተኛው አንቀጽ

3. ሦስተኛ አንቀጽ

4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

| |
|---|
| **ሆሴዕ: 6:1-3** |
| **1 ኑ፥ ወደ እግዚአብሔር እንመለስ እርሱ ሰብሮናልና፥ እርሱም ይፈውሰናል እርሱ መትቶናል፥** |
| **እርሱም ይጠግነናል። 2 ከሁለት ቀን በኋላ ያድነናል በሦስተኛውም ቀን ያስነሣናል፥ በፊቱም በሕይወት እንኖራለን።** |
| **3 እንወቅ እናውቀውም ዘንድ እግዚአብሔርን እንከተል እንደ ወገግታም ተዘጋጅቶ እናገኘዋለን እንደ ዝናብም ምድርንም እንደሚያጠጣ እንደ መጨረሻ ዝናብ ይመጣል።** |

**6:1 "ኑ"** ይህ ትእዛዛዊ ቃአል ነው(*Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)* ) (BDB 229፣ KB 246)፡፡ It seems thath 6:1-3 ያለው 5:14-15 ውስጥ የሚገኘውን እውነተኛ ንስዐን ይገልጻል፣ ግን አንድ ሰው 6:4-6 ያለውን ሲያነብ ቀጠይነት ያለው የባሕርይ ለውጥ ወይም የግል ህብረት መጀመሩ ሳሆን መሰረት የሌለው ንስዐ መሆኑ የታወቀ ነው፡፡

▣ **"እንመለስ"** ይህ ትዕዛዛዊ ቃአል ነው(*Qal* COHORTATIVE) (BDB 996፣ KB 1427)፡፡ ስለ ንስዐ ብሉይ ኪዳን ውስጥ አሞ 1:3 ላይ ተመልከት፡፡
ከቁጥር 1-3 የካህነት ቃል ሊሆን ይችላል፡፡ የዚህ ሀለነተናዊ አውድ ለእነርሱ እየተናገረ ነው፡፡ ይህ ምናልባት በ5:15 ላይ ለተደረገው የንስዐ ጥሪ በአምልኮ ስርኣታቸው ጊዜ ለያህዌ የሚሰጡት ምላሽ ሊሆን ይችላል፡፡

▣ **"እርሱ ሰብሮናል"** ይህ ቃል (BDB 382፣ KB 380፣ *Qal* PERFECT) የ5:14 ማጣቀሻ ሊሆን ይችላል፡፡ ያህዌ በፍርድ እንደ ተቆጣ አንበሳ ነው(ዝ.ከ. ኢዮብ 16:9)፡፡ ይሄው ተመሳሳይ ቃል በአሞ 1:11 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል፣ ዳሩ ግን የያህዌን ወይም የኤዶምን ቁጣ እንደሚገልጽ

እርግጠኛ አይደለም፡፡ "ሰብሮናል" የሚለው ሐረግ "አቆስናል" የሚለውን ሐረግ ይጋራል (BDB 645፣ KB 697፣ *Hiphil* JUSSIVE ይህ ቃል በአውዱ፣ "ሊገል በማይችል መሳርያ መቀጥቀጥ" ማል ሊሆን ይችላል (ለምሳሌ፣ ዘፀ 21:15፣19) ወይም "በተደጋጋም መቀጥቀጥ" (ለምሳሌ፣ ዘፀ 2:11፣13፤ 5:16)፡፡

▣ **"እርሱም ይፈውሰናል"** "ፈውስ" የሚለው ቃል(BDB 950፣ KB 1272፣ ያልተፈፀመ ቃአል(*Qal* IMPERFECT) "ቁስል ማሰር" የሚውን ይጋራል(BDB 289፣ KB 289፣ ያልተፈፀመ ቃአል(*Qal* IMPERFECT)፡፡እስራኤል የቅጣቷ ምንጭ ያህዌ መሆኑን አውቃለች እናም ንስዐ ከገቡ ይቅር ይላቸውና ያድናቸዋል፡፡

**6:2 "በሕይወት ያኖረናል ያስነሳናል"** የመጀመርያው ቃል(BDB 310፣ KB 309፣ *Piel* IMPERFECT) "መኖር" ወይም "በሕይወት መኖር" ከሚለው ሥር ነው (ለምሳሌ፣ መዝ 119:50፣93)፡፡ በሚቀጥለው ግጥማዊ መስመር ውስጥ "መነሳት" የሚለውን ጋራል፡፡
ይህ ምናልባት የሰሙት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ሊሆን ይችላል፡፡ በሕይወት ለማኖር፣ ለማዳን፣ እና አርነት ለማውጣት የማይለወጠውን የእግዚአብሔርን መሐርነት እየቆጠሩ ነው! ኪዳናዊ የእምነት እና የመታዘዝ አስፈላጊነት በመዘንጋት ረስተው ነበር፣ ግን ጥቅሙን ይፈልጉ ነበር!

▣ **"ከሁለት ቀን በኃላ"** ይህ ምናልባት የአጭር ጊዜ የእብራይስጥ አባባል ሊሆን ይችላል (ለምሳሌ፣ መሳ 11:4)፡፡

▣ **"በሦስተኛውም ቀን"** ይህ የሚያመለክተው (1) ስምምነት ለመፈጸም የተለመደ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው(ዝ.ከ. ኢያሱ 9:16-17፤ II ሳሙ 20:4፤ ሕዝራ 10:8-9) ወይም (2) በቀላሉ በቀጥታ(ማለትም፣ ሁለት ሦስት) የጊዜ ክፍፍልን ያሳያል፡፡
እስራኤል እግዚአብሔር በፍጥነት ይቅር እንደሚላትና እንደሚያድናት ተስፋ ታደርግ ነበር! ይሁን እንጂ፣ አንዳንድ ተንታኞች (በተሳሳተ መንገዱ አስባለሁ) ይህንን ቁጥር ኢየሱስ በመቃብር ውስጥ ሦስት ቀን መሆኑን ለማሳየት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ መረጋገጫ አድርገው ይወስዱታል(ዝ.ከ. I ቆሮ 15:4)፡፡
**6:3 "እንወቅ እናውቀውም ዘንድ እግዚአብሔርን እንከተል"** እነዚህ ሁለቱ ግሶች ተደጋጋፊ ቃአል(*Qal* COHORTATIVES) ናቸው፡፡ ከያህዌ ጋር ሊፈጥሩ ስላሰቡት ህብረት እና ቅርበት ፍላጎታቸው የሚናገር ነው፡፡ ይህ የሆሴዕ ዋና ርዕስ ነው(ዝ.ከ. 2:8፣20፤ 4:1፣6፤ 5:4፤ 6:3፣6)፡፡

▣ **"ወገግታም ዝናብም መጨረሻ ዝናብ"** እነዚህ የተፈጥሮን ብዛሐነትን ይገልጻል፣ የያህዌ ባህሪይም እንደዚሁ ነው፡፡ መሠረታዊ ፍላጎቱ በራሱ አምሳል ከተፈጠረው ከሰው ልጅ ጋር ነው፡፡ ይህ የተፈጥሮ ዓላማ ነው/ነበር! ፍቅሩ ለሺ ትውልድ ነው(ዝ.ከ. ዘዳግ 7:9) ቁጣው ከሦስት እስከ አረት ትውልድ ብቻ ነው (ዝ.ከ. ዘዳግ 5:9)፡፡ የእግዚብሔር ቸር ባሕሪይ የሰው ልጅ ተስፋ ነው!
ከሚወዳቸው ጸሐፊዎች አንዱ ኤፍ ኤፍ ብሩስ ነው፡፡ ለጥያቄዎች መልስ ውስጥ ስለፍልስጤም ዝናብ ጥሩ ጽሑፍ አለው፣ ገጽ 13፡፡ ይህ መጽሐፍ ለእኔ በጣም ጠቃሚ ነገር አለው ስለዚህ እንድታነቡ አበረታታቸዋለሁ፡፡

## ሆሴዕ: 6:4-11

**4 ምሕረታችሁ እንደ ማለዳ ደመና፥ በማለዳም እንደሚያልፍ ጠል ነውና**
**ኤፍሬም ሆይ፥ ምን ላድርግልህ? ይሁዳ ሆይ፥ ምን ላድርግልህ?**
**5 ስለዚህ በነቢያት እጅ ቈረጥኋቸው፥ በአፌም ቃል ገደልኋቸው ፍርዴም እንደ ብርሃን ይወጣል።**
**6 ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን፥ ከሚቃጠልም መሥዋዕት ይልቅ እግዚአብሔርን ማወቅ እወድዳለሁና።**
**7 እነርሱ ግን እንደ አዳም ቃል ኪዳንን ተላልፈዋል በዚያም ላይ ወንጅለውኛል።**
**8 ገለዓድ ኃጢአትን የሚሠሩ ሰዎች ከተማ፥ በደምም የተቀባ ነው።**
**9 ለሰውም እንደሚያደቡ ወንበዴዎች፥ እንዲሁ**
**የካህናት ወገኖች በሴኬም መንገድ ላይ ይገድላሉ ሴሰኝነትንም ያደርጋሉ።**
**10 በእስራኤል ቤት የሚያስፈራን ነገር አይቻለሁ በዚያ በኤፍሬም ውስጥ ግልሙትና ተገኘ፥ እስራኤልም ረክሶአል።**
**11 ይሁዳ ሆይ፥ የሕዝቤን ምርኮ በምመልስበት ጊዜ ለአንተ ደግሞ መከር ተወስኖልሃል።**

**6:4 "ምን ላድርግልህ"** ይህ በቀጥታ "ምን ላድርግልህ" ወይም "አንተን ምን ላድርግህ " የህዌ በቀጥታ በሆሴዕ በኩል እየተናገረ ነው፡፡ እግዚአብሔር በሕዝቡ እምነት ባዶነት እና እስፋርነት ተደነቀ፣ አሁንም እርሱ ግን በሚጠብቃቸው ፍርድ የተሰበረ ልብ አለው (ዝ.ከ. 11:8-9)፡፡

▣ **"ምሕረታችሁ እንደ ማለዳ ደመና"** ንስዓቸው የማስመሰል እና ታማኝነታቸው የንቀት(ማለትም፣የኪዳን ታማኝነት) ሆነ፡፡ "ታማኝነት" የሚል ቃል (ሔጽድ(*hesed)*፣ BDB 338) በ 4:2 ውስጥ "ትሁት" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት: Lovingkindness at 2:19፡፡

▣ **"በማለዳም እንደሚያልፍ ጠል ነው"** "ጤዛ" (BDB 378) በብሉይ ኪዳን ውስጥ በሁለት መልኩ ጥቅም ላይ ውሏል:-

1. በበጋ ጊዜ እህል እርጥበትን የሚያገኝበት መንገድ ነው (አዎንታዊ)
2. የመፍጠን ምሳሌ(አሉታዊ)

በሆሴዕ 6:4 ውስጥ የእስራኤል ንስዐ አለመግባቷ በ 13:3 ውስጥ ካለው የፍርዷ መፍጠን ጋር ይዛመዳል፡፡
**6:5** የዚህ ቁጥር ተመሳሳይነት የነብዩ መልዕክት በመንፍስ(አሞጽ በኤልሳዕ በኩል) መሆኑን ያሳያል፡፡ ሁለተኛው መስመር የ ራእይ 1:12፣16 መነሻ ምሳሌ መሆኑ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃሎች ኃይለኛ ጉልበት ናቸው!
▣

| | |
|---|---|
| NASB፣ NKJV | "በእናንተ ላይ ያለው ፍርድ እንደ ብርሃን ይወጣል" |
| NRSV | "ፍርዴም እንደ ብርሃን ይወጣል" |
| TEV | --------------- |
| NJB | "ፍርዴ እንደ ማለዳ ፀሐይ ያቃጥላል" |

የእብራይስጠን ተናባቢ በተለያዩ መልክ መከፋፈል ይቻላል እና “ፍርዴም እንደ ብርሃን ይወጣል” (ዝ.ከ. LXX፣ፔሺታ እና ታርጉም/
“ብርሃን” የሚለው ቃል (BDB 21) “ማለዳ” የሚለውን ያሳያል (BDB 1007) በቁ 3ለ ውስጥ። ማለዳ በእርግጠኝነት እንደሚመጣ ሁሉ፣ በነብያት በኩል የሚመጣውም የእግዚአብሔር የፍርድ መልዕክት እንደዛው ነው።

**6:6 “ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን፥”** እግዚአብሔር ለብን ያያል! ከውስጥ የሚያነሳሳ ደግሞ ቁልፉ ነው (ዝ.ከ. ኤርም 9:24)!
ይህ የመጽሐፉ አንዱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቁልፍ ነው (ዝ.ከ. 8:7፤ 11:12) *“ታማኝነት”* ከቁ 4 ጋር አንድ ነው፣ እዚህ ግን እውነተኛ የኪዳን ፍቅር ወይም ታማኝነት ነው። ኢየሱስ በማቴዎስ ውስጥ ከፈሪሳዊያን ጋር ስነጋገር ይህንን ሐሳብ ተጠቅሞበታል።
9:13፤ 12:7 ይህ ማለት እግዚአብሔር መስዋይት እንዳየቀርቡ ለማስቆም ፈልጎ ነበር ማለት አይደለም፣ ዳሩ ግን ጥሩ ልብ እንዲኖራቸው እንዲጠነቀቁ ነው(ዝ.ከ. 1 ሳሙ 15:22፤ እሳ 1:11-13፤ ኤርም 7:21-23፤ አሞ 5:21-24፤ ሚክ 6:6-8)። ለጥሩ ውይይት ከባድ የመጽሐፍ ቅዱስ አባባሎች (For a good discussion see *Hard Sayings of the Bible) የሚለው፦ ገጽ* 207-208፣ 294-295) ተመልከት። የመስዋይት አካሄድ የኃጢአት ብዛትን እና እግዚአብሔር ከሐጥኃተኞች ጋር ህብረት ለማድረግ ፈቃደኛ መሆኑን የሚያሰይ መንገድ ነበር። ይሁን እንጂ፣ያለ ንስዐ እና እምነት ወደ አምልኮ ሥርዓት ሲቀየር፣ ትርጉም የለለ ይሆናል፣ ከእግዚአብሔር ጋር ለሚደርግ እውነተኛ ግኑኝነትም እንቅፋት ነው።

**6:7**

| | |
|---|---|
| **NASB** | **“እነርሱ ግን እንደ አዳም ቃል ኪዳንን ተላልፈዋል”** |
| **NKJV** | **“እነርሱ ግን እንደ ሰዎቹ ቃል ኪዳንን ተላልፈዋል”** |
| **NRSV** | **“እነርሱ ግን የአዳምን ምድር እንደ ረገጡ፣ኪዳኑን ሰበሩ”** |
| **NJB** | **“እነርሱ ግን በአዳም ኪዳኑን ሰበሩ”** |

በመጀመርያ ደረጃ፣ ይህ የመጀመርያ የሆነው የእኛ መነሻ፣አዳሚን የሚያመለክት ይመስላል፣ buእዚህ ግን አውዱን በጥልቀት ሲናጠና ኪዳን ከመስበር ጋር በተገኛኘ ሁት ከተሞችን(በጊልዓድ ውስጥ ያለው አዳማ እና ሴከም/Adam in Gilead and Shechem/) የሚመስል። ሆሴዕ ብዙ ከተሞችንና ታርካዊ ማሳያዎችን ይጠቅሳል። እንዳንዱ የጥንት ድርጊቶች፣እንዳንዱ የማናውቃቸው ዘመናዊ ድርጊቶች እና እንዳንዱ ደግሞ የወደፊቱን መዳንና ተስፋን ነው። ወደ ሴኬም በሚወስደው መንገድ ላይ በጊልዓድ የሆነው ድርጊት ምስጢር ነው።ዳሩ ግን፣ ካህናተን ያሚያካትት ስለሆነ ፖለትካዊ ወይም አይማኖታዊ ሊሆን ይችላል። ሼኬም “መጠለያ ከተማ” እስከ ሆነች ድርስ የጥገኝነትን ጉዳይ የሚያሰይ ይሆናል።
ሁለቱ የአሁኑና የጥንቱ ትርጉም፣ በዚህ ቁጥር ላይ እንዳላቸው መረዳት በስፋት ይለያያል። ይሁን እንጂ፣በአውዱ ላይ በመሞርኮዝ፣ I think “አዳም” ኢያ 3:16 ላይ የተጠቀሰው ከተማ መሆን እንዳለበት አስባለሁ። በቁ 7ለ ውስጥ “እዛ” የሚለው(BDB 1027) ይህንን ትርጉም የሚደግፍ ይመስለኛል።

ግሱ (BDB 716፣ KB 778፣ *Qal* PERFECT) ማለት “መውጣት፣” “ውስጥ ማለፍ፣” ወይም “አጠገብ ማለፍ”።
በዚህ አውድ የታወቀ ድንበርን መተላለፍ፣መጣስ ማለት ነው (ማለትም ፣ 8:1፤ ዘኁል 14:41፤ ዘዳግ 17:2፤ 26:13፤ መዝ 17:3፤ እሳ 24:5) ። ልዩ ርዕስ ተመልከት: በ 2:18 ላይ ያለውን ኪዳን።

| | |
|---|---|
| **NASB** | **“በዚያም ላይ ወንጅለውኛል”** |
| **NKJV** | **“በዚያም ላይ እኔን ወንጅለውኛል”** |
| **NRSV** | **“በዚያም ላይ እምነት በማጣት ወንጅለውኛል”** |
| **TEV** | --------------- |
| **NJB** | **“በዚያም ላይ ከደውኛል”** |

ግሱ (BDB 93፣ KB 108፣ *Qal* PERFECT) “ለኪዳን አለመታመን” ማለት ነው(ማለትም ፣ጋብቻን እንደ ያህዌ ምሳሌ፣ ማለትም፣ እሳ 24:16፤ ኤርም 3:20፤ 5:11፤ ሚል 2:15)። ቃሉ በእሳ 33:1 ውስጥ ብዚ ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል።
ይህንን የመጀመርያ የማንነት ታመኝነት ድርጊትን አስተውል(ማለትም፣ “በእኔ ላይ”)። ይህ ተመሳሳይ ቃል ከጋብቻ ቃል ኪዳን ጋር በተገናኜ በ5:7 ውስጥ ጥቅም ላይ ውሏል!

**6:9 “ለሰውም እንደሚያደቡ ወንበዴዎች፥ እንዲሁ የካህናት ወገኖች በሴኬም መንገድ ላይ ይገድላሉ ”** ሴኬም ለያህዌ ታመኝ መሆንና ሌሎች ካህናት ደግሞ በቤትኤልና በጌልጌላ ብዙ አምላኪዎች እንዲኖራቸው ወደ ሴኬም የሚሄዱትን አምላኪዎችን እንደሚገድሉ ያስታውሰናል ወይም ደግሞ፣ የሴኬም ካህናት በጣም ስለሚቀኑ በከተማቸው ውስጥ በማለፍ ሌሎች አማልክቶችን ለማምለክ የሚሄዱትን መንገደኞችን ለማስቆም ነበር። ማንም ሰው አሰቦ የሚያደርግ ቢሆንም(ለዚህ የእብራይስጥ ቃል ጥሩ ውይይት እና ከአስርቱ ትዕዛዛት ጋር ላለው ግኑኝነት የመርሀፍ ቅዱስ ከባድ አባባሎች(*Hard Sayings of the Bible)*፣የሚለውን መጽሐፍ ገጽ 114-116 እና 148-149 ያለውን ተመልከት)፣ ካህናቶቹ ከመጀመርያው ጥሪቻው ርቀው እንዳሉ ግልጽ ነው።

**6:10 “የሚያሰፈራ ነገር”** ይህ ቃል በኤርምያስ ውስጥ ለተለየ ሐሳቦች ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል:-

1. *መሠረታዊ ትርጉሙ* the basic meaning is rottenness (ዝ.ከ. ኤርም 29:17)
2. የአይማኖት መሪዎች መበላሸት (ዝ.ከ. ኤርም 5:30-31፤ 23:14)
3. የትውልዱ በአጠቃለይ መበላሸት (ዝ.ከ. ኤርም 18:13)

▣ **“እስራኤልም ረክሶአል”** ይህ ግስ (BDB 379፣ KB 375፣ *Niphal* PERFECT) የፍሬያማ ጣዖት አምልኮን ለማሳየት ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል (ለምሳሌ፣ 5:3)።

**6:11**

| | |
|---|---|
| **NASB** | **“ ይሁዳ ሆይ፥ የሕዝቤን ንብረት በምመልስበት ጊዜ ለአንተ ደግሞ መከር ተወስኖልሃል”** |
| **NKJV** | **“ይሁዳ ሆይ፥ የሕዝቤን ምርኮ በምመልስበት ጊዜ ለአንተ ደግሞ መከር ተወስኖልሃልAlso”** |
| **NRSV** | **“ይሁዳ ሆይ፥ የሕዝቤን ንብረት በምመልስበት ጊዜ ለአንተም ደግሞ መከር ተወስኖልሃል”** |

TEV " ይሁዳ ሕዝብ፣ እያደረግክ ላለው የቅጣት ጊዜን ለአንተ አስቀምጨሃለሁ"

NJB "For you too፣ ይሁዳ፣ የሕዝቤን ንብረት በምመልስበት ጊዜ ፣ለአንተም የመከር ጊዜ ተቀምጦልሃል"

ይህ ቁጥር አሻሚ ነው፡፡ ጣዖትን ከማምለኳ የተነሳ በይሁዳ ላይም (ማለትም፣ መከር፣ ዝ.ከ. ኤርም 51:33፤ ኢዩኤ 3:13) ሊመጣ ያለውን ፍርድ የሚያሳይ ይመስላል(ዝ.ከ. 8:14፤ 12:2)፣ አሁንም ቀጥሎ ያው መስመር የመመለስን ተስፋ ያሳያል፡፡ 6:11ለ ከ 7:1ሀ ጋር ለሄድ ይችላል፡፡

**ለምዕራፍ 5 እና 6 የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. በ5:8-15 ውስጥ የተጠቀሰው ጦርነት ታሪካዊ መቼቱን ግለጽ፡፡
2. ለምንድ ነው 6:1-4 ያለው እውነተኛ ስላልሆነው ንስዐ ብቻ የሚያስተምረው?
3. "ለማወቅ" የሚለውን የእብርይስጥን ቃል ተርጉም
4. ቁ 11 ለመተርጎም ከባድ የሆነው ለምንድ ነው?

# ሆሴዕ 7
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|
| የእስራኤል እና የይሁዳ እመቢ፣ተኝነት | ቀዋሚ ስለሁነው የእስራኤል አመፃ ምክንያት የተነሳ የእግዚአብሔር ፍርድ በእስራኤል ላይ ነው (4፡1-14፡9) | የህዝቡ የውሸት ንስሐ (6፡1-7፡2) | ብጥብጥ በእስራኤል ውስጥ |
| 7፡1-3 | 7፡1-3 | ሴራ በቤተ-መንግስት ውስጥ | ሴራ የቀን ቅደም ተከተል በእስራኤል ውስጥ |
| | | 7፡3-6 | 7፡3-7 |
| | | 7፡7 | እስራኤል በውጭ መንግስታት ላይ በመታመኗ ተደመሰሰች |
| | | እስራኤል እና ህዝቦች | |
| 7፡8-10 | 7፡8-10 | 7፡8-10 | 7፡8-10 |
| በህዝቦች ላይ ከንቱ ሆነ መታመን | 7፡11-13 | | የእስራኤል ምስጋናቢስነትና ቅጣት |
| 7፡11-12 | | 7፡13-16 | |
| | 7፡14-16 | | 7፡13-16 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ vii ተመልከት)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**ሆሴዕ: 7፡1-7**

**1 በሐሰት አድርገዋልና፥ ሌባም ገብቶአልና፥ በውጭም ወንበዴዎች ቀምተዋልና እስራኤልን እፈውስ ዘንድ በወደድሁ ጊዜ የኤፍሬም ኃጢአትና የሰማርያ ክፋት ተገለጠ።2እኔም ክፋታቸውን ሁሉ እንዳሰብሁ በልባቸው አያስቡም አሁንም ሥራቸው ከብባቸዋለች፥ በፊቴም አለች። 3 ንጉሡን በክፋታቸው፥ አለቆቹንም በሐሰታቸው ደስ አሰኝተዋል። 4 ሁሉም አመንዝራዎች ናቸው ጋጋሪ እንደሚያነድድበት እንደ ምድጃ ናቸው ሁሉ እስኪቦካ ድረስ እሳትን መቈስቈስና እርሾን መለወስ ይቀያል። 5 በንጉሣችን ቀን አለቆች ከወይን ጠጅ ሙቀት የተነሣ ታመሙ እርሱም ከዋዘኞች ጋር እጁን ዘረጋ። 6 እያደቡ ልባቸውን እንደ ምድጃ አዘጋጅተዋል አበዛቸውም ሌሊቱን ሁሉ አንቀላፋ በጠባም ጊዜ እንደ እሳት ነበልባል ይነድዳል። 7 ሁሉም እንደ ምድጃ ግለዋል፥ ፈራጆቻቸውንም በሉ ነገሥታቶቻቸውም ሁሉ ወደቁ ከእነርሱም ወደ እኔ የሚጮኽ የለም።**

**7፡1 "እስራኤልን እፈውስ ዘንድ በወደድሁ ጊዜ "** የዚህ መስመር ግጥም ይዘት ምዕራፍ 6 መጨረሻ መስመር ላይ ካለው ጋር በደንብ ተጋጥሞ የሚሄድ ይመስላል (LXX፣ Peshitta፣ ቮልጌት፣ NKJV፣ NASB)፡፡

▣ ***"ፈውስ"*** *"ፈውስ"* የሚለው ቃል(BDB 950፣ KB 1272፣ *Qal* INFINITIVE CONSTRUCT) እግዚአብሔር ከአመጽ በሽታ ለሕዝቡ መንፈሳዊ ተሀድሶን እንደሚያመጣላቸው ለመግለጽ ብዙ ጊዜ በሆሴዕ ውስጥ ጥቅም ላይ ውሏል(ለምሳሌ፣ 5:13፤ 6:1፤ 7:1፤ 11:3፤ 14:4) በብሉይ ኪዳን ውስጥ ኃጢአት እንደ በሽታ ይታይ ነበር (ለምሳሌ፣ መዝ 103:3፤ እሳ 1:5-6)፡፡

▣ **"ከፋት"** የእስራኤል ኃጢአት እንደ ከፋት ተገልጾአል **"ከፋት"** (ማለትም፣ መበላሸት፣ 4:8፤ 5:5፤ 8:13፤ 9:7፣9፤ 10:10፤ 12:8፤ 13:12፤ 14:1-2፣ BDB 730) እና "ከፉ ሥራቸው" (BDB 949፣ ዝ.ከ. 7:2፣3፤ 9:15፤ 10:15[ሁለት ጊዜ])፡፡

▣ ***"ተገለጠ"*** ይህ ግስ (BDB 162፣ KB 191፣ *Niphal* PERFECT) በመግለጥ ማሳየት ማለት ነው(ምሳሌ፣2:10፤ 1 ሳሙ 2:27፤ 14:8፤ እሳ 53:1)፡፡ በእሳ 57:8 ውስጥ የፆታዊ ግኑኝነት አመለካከት አለው፣ እዚህ ውስጥ እንደሚሆን ሁሉ (ማለትም፣ የፍሬያማ የጣዖት አምልኮ)

▣

**NASB፣ NRSV** ***"ሐሰት ይናገራሉ"***
**NKJV** ***"በሐሰት አድርገዋልና"***
**TEV** ***"ያታልሉ"***
**NJB** ***"ማታላል የባህሪያቸው ሕግ ነው"***

ግሱ (BDB 821፣ KB 950፣ *Qal* PERFECT) የእስራኤልን "ማጨበርበር" እና "ውሸት" የሚያሳይ ነው (ዝ.ከ. ኤርም 6:13፤8:8፣10)

▣ ***"ሌባም ገብቶአልና፥ በውጭም ወንበዴዎች ቀምተዋልና"*** "ገብቶአል" እና "በውጭም" የሚለው የሚያሳየው (1) የሕዝቡ ኃጢአት በሙሉወይም (2) መወረር (ለምሳሌ፣ ኤርም 18:22) እና ምርኮ፡፡
"ሌባ" የሚለው (በቀጥታ "ወንበዴ" BDB 151 I) ቀደም ብሎ በ 6:9 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል(ዝ.ከ. II ዜና 25:9፣10፣13)፡፡

▣ ***"እስራኤል ኤፍሬም ሰማርያ"*** ከክርስቶስ ልደት በፊት በ922 በኢዮርባም 1፣ከኢፍሬም ነሳ የሆነው ኃይለኛ መሪ፣ እና ሬሆብያም፣ የሰለሞን ልጅ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከተከፋፈለ በኃላ እነዚህ ሦስት ቃላቶች የደቡብን አስር ነሳዎች ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋሉ ናቸው፡፡

**7:2 "እኔም ክፋታቸውን ሁሉ እንዳሰብሁ በፊቴም አለች"** ይህ እግዚአብሔር የኪዳን ሕዝቡን ኃጢአት እንዴት እንዳስቀመጠ ያሳያል፡፡ ይቅር ማለት መርሳት ማለት ነው(ለምሳሌ፣ እሳ 1:18፤ 38:17፤ 43:25፤ 44:22፤ ኤርም 31:34፤ ሕዝ 18:22፤ 33:16)፣ ዳሩ ግን ማስታወስ (ዝ.ከ. 8:13፤ 9:9) ንስዐ ያለ መግባት ("በልባቸው አያስታውሱትም") እና የሚያስከትለውን ፍርድ ምልክት ነው (ምሳሌ፣ ኤርም 14:10፤ 44:12)፡፡

▣ ***"ሥራቸው ሁሉ ከብባቸዋለች"*** ይህ ግስ (BDB 685፣ KB 738፣ *Qal* PERFECT) በጠላት ወይም በወታደር መከበብን ለማሳየት ይጠቅማል (ለምሳሌ፣ ኢዮብ 16:13፤ መዝ 17:11፤ 88:11)፡፡ ይህ ተመሳሳይ ቃል በ11:12 ውስጥ፣ ኤፍሬም በውሸት እግዚአብሔርን በሚከብበት ጊዜ ለማሳየት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

**7:3 "እነርሱ"** ከቁ 3-6 ያለው "እነርሱ" የሚለው ቃል ማንን እንደሚያመለክት ብዙ ክርክር አለው፡፡ ሁለት መላ ምቶች አሉ፡፡ በስውር የሚሰሩ የፖሊትካ ቡድኖች ያሳያል(ዝ.ከ. ቁ 7 እና NET Bible) ፣ ቁ 1 ላይ ከተገለጹት ወንበዴዎችና ሌቦች ጋር በተወሰነ መልኩ የሚቀራረብ፡፡ በፊት ለፊት ለንጉሱ ታማንኝ ሲሆኑ፣ በግላቸው ግን ሞቱን ያስባሉ (ዝ.ከ. 8:4)፡፡ ከእዮርባም II ሞት በኃላ ፤በፊጥነት ስድስት ነገስታት መተካካት ሆነ(ዝ.ከ. ቁ 7): Zechariah፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ746-745 ዘካርያስ፣ የተገደለው፤ ሻሎም ከክርስቶስ ልደት በፊት በ745፣የተገደለ፤ ምናሴ ከክርስቶስ ልደት በፊት፣ከ 745- 738 ፤የሶርያ ቃለ-ቀባይ የነበረ (ዝ.ከ. II ነገስ 15:19)፤ ፔከህያ(Pekahiah) ከክርስቶስ ልደት በፊት፣ ከ738-737፣ የተገደለ፤ ፔኪያ(Pekah) ከክርስቶስ ልደት በፊት፣ 737-732 ፣ የተገደለ፤ ሆሴዕ፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ732-724፣በሶርያ የታሰረ (ዝ.ከ. II ነገስ 17:4)፡፡

ይህ ከ 4:4-6፣7-10፣11-14፤ 5:1-7 የሆሴዕ ማሾፍያ የነበሩ ካህናቶች ያሳያል፡፡ እናም አሁን በፖለትካ ግጭት ውስጥ ተሳትፏል፡፡ እነዚህንን ሁለቱን ማደባለቅ ይቻላል፡፡ እንደ ፖለትከኞች ስራ አስፈጻም ከገዣዎች ጋር የሚሠሩ ካህናት ናው፡፡

**7:4 *"ሁሉም አመንዝራዎች ናቸው"*** ይህ ወይ (1) የፍሬያማ ጣዖት አምልኮ ሌላ መግለጫ ሊሆን ይችላል (በጥሬው) ወይም (2) ለኪዳን ታማኝነታቸው መግለጫ (ዘይቤያዊ፣ ዝ.ከ. ኤርም 9:2)፡፡

▣ ***"ጋጋሪ እንደሚያነድድበት እንደ ምድጃ ናቸው"*** ለእነዚህ የፖለትካ ሥራ አስፈጻሚዎች ግልጽ ያልሆነ አለ ወይም ካህናት እንደ ጋጋር እና ምድጃ ሆነዋል፡፡
ምሳሌው ሊሆን የሚችለው (1) ኪህደታቸውን ለማቀድ ማልደው ይነሳሉ (ዝ.ከ. ቁ
6፣7፣8ለ) ወይም (2) ለሥራቸው ትኩረት የመይሰጡ እና ዳቦውን የሚያበላሹ ናቸው፡፡

**7:5 "በንጉሣችን ቀን"** ይህ ዓመታዊ ንግስ በዓል፣ የልደት በዓል፣ ወታደራዊ ድልን የሚያከብሩበት ልዩ ቀን፡፡

▣ **"አለቆች"** ይህ የንጉስን ቤተሰብ ወይም ሀገሪን ያሳያል፡፡ ብዙ ጊዜ በሆሴዕ ውስጥ ተጠቅሰዋል(ዝ.ከ. 7:5፣16፤ 8:4፣10፤ 9:15፤ 13:10)፡፡

▣ ***"ከወይን ጠጅ ሙቀት የተነሣ ታመሙ"*** የፖለትካ መሪዎቹ ውሸታሞች ናበሩ(ቁ 3)፣ ሰካራሞች (ቁ 5)፣ እና ዘዴኞች (ቁ 5-7)፡፡ ስካር አቢይ የወደቀው የሰው ልጅ ችግር ነው (ዝ.ከ. ምሳሌ 20:1፤ 23:29-35፤ እሳ 28:1፣ 7)፡፡ ብዙ ጊዜ ለእግዚአብሔር ፍርድ እንደ ምሳሌ ያገለግላል፡፡
▣

**NASB፣ NKJV** ***"ተሳላቂዎች"***

NRSV "ዋዘኞች"
TEV -------
NJB "በእርሱ የሚስቁ ሕዝብ"
ይህ ቃል እዚህ ብቻ ይገኛል፡፡ "አመጽ" ማለት ይቻላል (ማለትም፣ በአመጽ ማጥቃት ያስባሉ) ወይም ከሌላ ሥር፣ "መሳለቅ" (ማለትም፣ ከሰካራም ዳኛ ምክርን እንደ መቀበል)፡፡

**7:6 "እያደቡ"** ይህ ቃል (BDB 70) በስውር ማጥቃትን ያሳያል (ዝ.ከ. ኤርም 9:8፣ ግሱ በኤርም 51:12 ላይ ተቀረፃ)፡፡ ይህ በዘፀ 20:13 እና ዘዳግ 5:17 ላይ የተከለከለው የታቀደ ነፍስ ገዳይነት ነው!

**7:7 "ነገሥታቶቻቸውም ሁሉ ወደቁ"** በ7:3 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት፡፡

## ሆሴዕ: 7:8-16

**8 ኤፍሬም ከአሕዛብ ጋር ተደባለቀ ኤፍሬም እንዳልተገላበጠ ቂጣ ነው።**
**9 እንግዶች ጕልበቱን በሉት፥ እርሱም አላወቀም ሽበትም ወጣበት፥ እርሱም አላወቀም።**
**10 የእስራኤልም ትዕቢቱ በፊቱ መሰከረ ወደ አምላካቸው ወደ እግዚአብሔር ግን አልተመለሱም፥**
**በዚህም ሁሉ አልፈለጉትም።11ኤፍሬምም አእምሮ እንደሌላት እንደ ሰነፍ ርግብ ነው ግብጽን ጠሩ፥**
**ወደ አሦርም ሄዱ። 12ሲሄዱ አሽከላዬን አዘረጋባቸዋለሁ እንደ ሰማይ ወፎች አወርዳቸዋለሁ**
**መከራቸውን ሲሰሙ እገሥጻቸዋለሁ። 13 ከእኔ ፈቀቅ ብለዋልና ወዮላቸው!**
**በእኔም ላይ ዐመፀዋልና ጥፋት ይምጣባቸው! እኔ ልታደጋቸው ወደድሁ፥**
**እነርሱ ግን በሐሰት ተናገሩብኝ።14 በመኝታቸው ላይ ሆነው ያለቅሱ ነበር እንጂ በልባቸው**
**ወደ እኔ አልጮኹም ስለ እህልና ስለ ወይን ጠጅ ይሰበሰቡ ነበር በእኔም ላይ ዐመፁ።**
**15 እኔም ከንዳቸውን አስተማርሁና አጸናሁ እነርሱ ግን ክፉ ነገርን መከሩብኝ።1**
**6 ወደ ከንቱ ነገር ተመለሱ እንደ ተንኰለኛ ቀስት ሆኑ አለቆቻቸው ከምላሳቸው ቍጣ የተነሣ**
**በሰይፍ ይወድቃሉ ይህ በግብጽ ምድር ውስጥ መሳለቂያ ይሆንባቸዋል።**

**7:8 "ኤፍሬም ከአሕዛብ ጋር ተደባለቀ"** ይህ እስራኤል የውጭ የፖለትካ ቡድን ከሆኑት ከሦርያ እና ከግብጽ ጋር መተባበሯን ያሳያል(ዝ.ከ. ቁ 11፣16)፡፡ "ተደበላቀ" የሚለው ቃል የመስዋይትነት ሐሳብ አለው(BDB 117፣ KB 134፣ *Hithpolel*፡ ለምሳሌ፣ ዘፀ 29:2፣ 40፤ ሌዋ 2:4፤ 7:10)፡፡ የውጭ ቡድኖች ለዕርዳታ የጣዖታቸውን ስም ይጠራሉ፡፡ እስራኤልም ለዕርዳታ ያህዌን ከመጥራት ይልቅ ወደ ውጭው ጣዖታት ተመለሰች(ዝ.ከ. ቁ 13-15)፡፡

▣ **"ኤፍሬም እንዳልተገላበጠ ቂጣ ነው"** ይህ የጋጋራ ምሳሌ ሆኖ (ዝ.ከ. vv 4፣6፣7) በአንድ በኩል ተቃጥሎ በሌላ ጎኑ ደግሞ ሊጥ የሆነውን ቂጣን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ የኪዳን ሕዝብ የሆነው የእግዚአብሔር ሕዝብ ጥቅም የሌለው መሆኑን የሚያሳይ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለ ጥንቱ ጋጋራ እና ምድጃ በደንብ ለማወቅ ስለመጽሐፍ ቅዱስ ታርካዊ ዳራ የሚናገረውን ማብራርያ(*Bible Background Commentary*)፣ ብሉይ ኪዳኙ ገጽ 756 ጳመልከጽ ወይ ደግሞ ማንኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃለት ወይም እንሳይኮሎፒድያ(Bible dictionary or encyclopedia)፡፡ እኔ ዞንደርፈን ፒክቶሪያል የመጽሐፍ ቅዱስ እንሳይኮሎፒድያን ይጠቁማለሁ(Zondervan *Pictorial Encyclopedia of the Bible* 5 ቅጽs ) አምስተኛ ቅፅ፡፡

**7:9** ይህ አሦር ትልቅ ከበረታን መፈለጓን የሚያሳይ ነው፡፡ አሁንም የእስራኤል ችላ ባይነት ተተኩሯል ("አውቃለሁ" BDB 393፣ KB 390፣ *Qal* PERFECT፣ ሁለቴ፣ ዝ.ከ. 4:1)፡፡

▣
**NASB፣ NRSV** **" ሽበት ፀጉር ከእርሱ ይታያል"**
**NKJV** **"ሽበት ፀጉር እዚህ እና እዚያ እርሱ ላይ አለ"**
**TEV** **"ቀኖቻቸው የተቆጠረ ነው"**
**NJB** **"ፀጉራቸው ወደ ሽበት እየተለወጠ ነው"**
ይህ ለኃይል መቀነስ እና የሞት መቅረብ ምሳሌ ነው!

**7:10 "የእስራኤልም ትዕቢቱ በፊቱ መሰከረ"** ይህ የሚያመለከተው እስራኤል በመጽሐፍትና(ማለትም፣ ሙሴ) በነብያት በኩል ያህዌን ከማወቃቸው የተነሣ፣ ጣዖታትን በመከተላቸውና ኪዳንን በመቃወማቸው እሊናቸው በጣም ይከሳቸዋል፡፡

እስራኤል ወታደራዊ ኃይሏ ያረጋጋኛል ብላ ወደ አሰበችሁ ቦታ ማጥታለች(ዝ.ከ. 5:5)፣ዳሩ ግን ዝሙቷ መንፈሳዊ ክህደትን እና ድክመትን፡፡

▣ **"ወደ አምላካቸው ወደ እግዚአብሔር ግን አልተመለሱም"** የራሱ ሕዝብ ወደ እርሱ አለመምጣቱ ለያህዌ የልብ ስብራት ነው (ዝ.ከ. ቁ 7መ)፡፡ ልዩ ርዕስ: በብሉይ ኪዳን አሞ 1:3 ላይ ያለውን ንስዐ ተመልከት፡፡
ሁለቱ ግሶች (#1 "መመለስ" BDB 996፣ KB 1427፣ *Qal* PERFECT እና "መፈለግ" BDB 134፣ KB 152፣*Qal* PERFECT) መመለስ(ንስዐ) እና መከተልን (እምነት፣ ዝ.ከ. Mark 1:15፤ Acts 3:16፣19፤ 20:21) ያሳያል፡፡

**7:11** ይህ ቁጥር ከያህዌ ይልቅ የፖለትከ ቡድንን ተስፋ የማድረግ ሞኝነትን ያሚያሳይ ነው(ዝ.ከ. v 16፤ 8:9-10፣ 13፤ 9:3፣ 6፤ 11:11፤ 12:1)፡፡ አድሱ መደበኛ ትርጉም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጥሩ ማስታወሻ አለው፣ "Menahem turned to Assyria (II ነገስ 15:19- 20) and Pekah to Egypt ሆሴ ea alternated in alliance to both (II ነገስ 17:4)" (ቁ 1330)፡፡

**7:12 "ሲሄዱ አሽከላዬን እዘረጋባቸዋለሁ"** ይህ የሚያመለክተው ያህዌ የውጭውን ግዛት እንደሚቆጣጠር ነው፡፡ የእስራኤልን መጨረሻ የሚቆጣጠር እርሱ እንጂ፣ ሦርያም ግብጽም አይደለም፡፡

▣ "እንደ ሰማይ ወፎች አወርዳቸዋለሁ መከራቸውን ሲሰሙ እገሥጻቸዋለሁ" ይህ ሊያመለክት የሚችለው

1. የጥጆችን ጣዖት ከወርቅ አሰርቶ ያቆመው የእዮርባም I አዋጅ ነበር
2. እርሱን ያልታዘዙ የእስራኤል ተከታታይ ነገስታት
3. በዚህ የተስማሙ የእነዚህ ነገስታት ምክር ቤቶች (የእስራኤል መሪዎች ሞኝነት)

**7:13-15 "በእኔም ላይ ዐመፁ በሐሰት ተናገሩብኝ በልባቸው ወደ እኔ አልጮኹም ከእኔ ፈቀቅ ብለዋልና ክፉ ነገርን መከሩብኝ"** ሕዝቡ በእግዚአብሔር ላይ ማመፁን የሚያሳይ የማንነት መገለጫ የሆኑን ነገሮች("እኔ" ስድስት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል) አስተውል፡፡
የመጀመርያዎቹ ሦስት የተፈፀሙ ቃአል ግሶች፣ የተረጋጋ ሁነታን የሚያሳዩ ሲሆኑ፤ የመጨረሻዎቹ ሁለት ደግሞ ያልተፈፀሙ፣ ድግግሞሽን የሚያሳዩ፣ሂደታዊ አመፅን ያሳያሉ፡፡

**7:13 "መታደግ"** ይህ ግስ (BDB 804፣ KB 911፣ *Qal* IMPERFECT) ማለት "መልሶ መግዛት" ወይም "መግዛት" ነው፡፡ በብሊይ ኪዳን ውስጥ ሰፋ ያለ ጥቅም አለው: (1) ጎኤል( *go'el)* ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው ፣ ግን የዘር ሐረግ ትኩረት ይጎላል፤ (2) በመጀመርያ ከእስራት ነፃ መውጣትን ለማሳየት ያገለግላል፣በመንፈስም ሆነ በአካል፤ (3) ምሳሌዎች: ዘፀ 13:13፣ 15፤ 20:30፤ 21:8፤ መዝ 34:22፤ 49:7፣ 8፣ 15፤ 130:7፣ 8፤ እሳ 1:27፤ and 29:22፡፡

## ልዩ ርዕስ: መዋጀት/መቤዠት

I. ብሉይ ኪዳን
  ሀ. በቀዳሚነት ሁለት የዕብራይስጥ የሕግ ቃላት አሉ፣ ይሄንን ጽንሰ-ሐሳብ የሚገልጹ።
    1. ጋል *Gaal*፣እሱም በመሠረቱ "ነጻ ማውጣት" የሚል ፍቺ አለው፣ ዋጋ በመክፈል። ጎል የሚለው ቃል በቅርጹ ጽንሰ-ሐሳቡ ላይ ግላዊ ጣልቃ ገብነትን ይጨምራል፣ ዘወትር የቤተሰብ አባል (ማለትም፣ ተቤዣ ዘመድ)። ይህ ባህላዊ ገጽታ፣ ማለትም ዕቃዎችን፣ እንስሳትን፣ መሬትን መልሶ የመግዛት መብት (ሌዋውያን 25፡27)፣ ወይም ዘመዶችን (ሩት 4፡15፤ ኢሳ 29፡22) ከሥነ መለኮት አኳያ የተሸጋገረው፣ የያህዌ እስራኤልን ከግብፅ መቤዠት ለማሳየት ነው (ዘጸ 6:6፤ 15:13፤ መዝ 74:2፤ 77፤15፤ ኤር 31:11)። እሱም "ተቤዣ" ሆኗል (ኢዮብ 19:25፤ መዝ 19:14፤ 78:35፤ ምሳ 23:11፤ ኢሳ 41:14፤ 43:14፤ 44:6፣24፤ 47:4፤ 48:17፤ 49:7፣26፤ 54:5፣8፤ 59:20፤ 60:16፤ 63:16፤ ኤር 50:34)።
    2. ፓዳህ *Padah*፣፣ እሱም በመሠረቱ ፍችው "መታደግ" ወይም "ማዳን" ነው
      ሀ የበኩር ልጅ መቤዠት፣ ዘጸ 13:13፣14 እና ዘኍ 18:15-17
      ለ ሥጋዊ መዋጀት ከመንፈሳዊ መዋጀት በተቃርኖ ነው፣ መዝ 49፡7፣8፣15
      ሐ ያህዌ እስራኤልን ከኃጢአታቸውና ከዐመጻቸው ይዋጃቸዋል፣ መዝ 130፡7-8
  ለ. ሥነ-መለኮታዊ ጽንሰ-ሐሳቡ ሦስት ተያያዥ ነገሮችን ያካትታል።
    1. ችግረኝነት፣ ባርነት፣ ኪሳራ፣ እስር ይኖራል።
      ሀ አካላዊ
      ለ ማኅበራዊ
      ሐ መንፈሳዊ (መዝ 130፡8
    2. ለነጻነት፣ ለመለቀቅ፣ እና ለመመለስ ዋጋ መከፈል ይኖርበታል።
      ሀ ለሕዝብ፣ እስራኤል (ዘዳ 7፡8)
      ለ ለግለሰብ (ኢዮብ 19:25-27፤ 33:28)
    3. አንዱ እንደ ጣልቃ ገቢ እና ረድኤት መሥራት አለበት። በጋል ይህ ዘወትር የሚሆነው በቤተሰብ አባል ወይም በቅርብ ዘመድ ነው (ማለትም ጎል)።
    4. ያህዌ ዘወትር ራሱን የሚገልጸው በቤተሰባዊ ቃላት ነው።
      ሀ አባት
      ለ ባል
      ሐ የቅርብ ዘመድ ተቤዣ/ተበቃይ
      መቤዠት የሚጸናው በያህዌ አካላዊ ወኪልነት በኩል ነው፤ ዋጋ ይከፈላል፣ እናም መቤዠቱ ይቀዳጃል!
II. አዲስ ኪዳን
  ሀ. ሥነ መለኮታዊውን ፅንሰ ሐሳብ ለመግለጽ በርካታ ቃላት ጥቅም ላይ ውለዋል።
    1. አጎራዞ *Agorazō* (1ኛ ቆሮ 6:20፤ 7:23፤ II ጴጥ 2:1፤ ራዕ 5:9፤ 14:3-4) ይህ የንግድ ቃል ነው፣ እሱም ለአንድ ነገር የተመለከተውን ዋጋ የሚያንጸባርቅ። እኛ በደም የተገዛን ሕዝቦች ነን፣ የገዛ ራሳችንን ሕይወት መቆጣጠር የማንችል። የክርስቶስ ነን።
    2. አክሳጎራዞ *Exagorazō* (ገላ 3:13፤ 4:5፤ ኤፌ 5:16፤ ቆላ 4:5)። ይህም ደግሞ የንግድ ቃል ነው። እሱም የሚያንጸባርቀው

    3. የኢየሱስን የምትክ ሞት ነው፣ በእኛ ፈንታ። ኢየሱስ እርግማንን ተሸክሟል፣ በሕግ ተግባር ላይ የተመሠረተውን (ማለትም፣ የሙሴ ሕግ፣ ኤፌ 2:14-16፤ ቆላ 2:14)፣ እሱንም ኃጢአተኞቹ የሰው ልጆች መፈጸም የማይችሉት። እሱ እርግማንን ተሸከመ (ዘዳ 21፡23)

ለሁላችንም (ማርቆስ 10:45፤ II ቆሮ 5:21)! በኢየሱስ፣ የእግዚአብሔር ፍትሕና ፍቅር ወደ ሙሉ ምሕረት፣ ተቀባይነት፣ እና ቀረቤታ ይወጣል!

4. ሉ፣ *Luō* "ነጻ ማውጣት"

*ሀ* ሉትሮን፣ *Lutron* "የተከፈለ ዋጋ" (ማቴ 20:28፤ ማርቆስ 10:45)። እነዚህ ጠንካራ ቃላት ናቸው፣ ከኢየሱስ ከራሱ አንደበት የወጡ፣ የመምጣቱን ዓላማ በተመለከተ፣ የዓለም አዳኝ ለመሆን፣ የእሱ ያልሆነውን የኃጢአት ዕዳ ለመክፈል (ዮሐንስ 1:29)።

*ለ* ሉትሮ፣ *Lutroō* "መልቀቅ"

   i. እስራኤልን መዋጀት፣ ሉቃስ 24:21
   ii. ሕዝቡን ለመዋጀትና ለማጥራት ራሱን ሰጠ፣ ቲቶ 2:14
   iii. ኃጢአት-የለሽ ምትክ መሆን፣ 1ኛ ጴጥ 1:18-19

*ሐ* ሉትሮሲስ፣ *Lutr ōsis* "መቤዠት፣ ማዳን፣ ወይም ነጻ ማውጣት"

   (1) የዘካርያስ ትንቢት፣ ስለ ኢየሱስ፣ ሉቃስ፣ 1:68
   (2) የሐና ለእግዚአብሔር ምስጋና፣ ስለ ኢየሱስ፣ ሉቃስ 2:38
   (3) የኢየሱስ የተሻለ፣ አንድ ጊዜ የቀረበ መሥዋዕት፣ ዕብ 9:12

5. አፖሊትሮሲስ *Apolytrōsis*

*ሀ* መዋጀት በዳግም ምጽአቱ (ሐዋ 3:19-21)

   (1) ሉቃስ 21:28
   (2) ሮሜ 8:23
   (3) ኤፌሶን 1:14፤ 4:30
   (4) ዕብራውያን 9:15

ለ በክርስቶስ ሞት መቤዠት

   (1) ሮሜ 3:24
   (2) 1ኛ ቆሮንቶስ 1:30
   (3) ኤፌሶን 1:7
   (4) ቆላስይስ 1:14

6. አንቲሊትሮን *Antilytron* (1ኛ ጢሞ 2:6)። ይህ ወሳኝ የሆነ ጽሑፍ ነው (ቲቶ 2:14 እንደሆነው)፣ መለቀቅን ከኢየሱስ የመስቀል ላይ ምትክ ሞት ጋር የሚያያይዘው። እሱ አንዱና ብቸኛ ተቀባይነት ያለው መሥዋዕት ነው፤ ብቸኛው ስለ "ሁሉ" የሞተ (ዮሐንስ 1:29፤ 3:16-17፤ 4:42፤ I ጢሞ 2:4፤ 4:10፤ ቲቶ 2:11፤ II ጴጥ 3:9፤ I ዮሐንስ 2:2፤ 4:14)።

ለ. *ሥነ-መለኮታዊ ጽንሰ-ሐሳቡ በአኪ የሚያመለክተው*

1. የሰው ልጅ በኃጢአት ባርነት ተይዟል (ዮሐንስ 8:34፤ ሮሜ 3:10-18፤ 6:23)።
2. የሰው ልጅ የኃጢአት ባርነት በብኪ የሙሴ ሕግ ተገልጧል (ገላትያ 3) እና በኢየሱስ የተራራው ስብከት (ማቴዎስ 5-7)። የሰዎች ድርጊት የሞት ፍርድ ሆነ (ቆላ 2:14)።
3. ኢየሱስ፣ ነውር የሌለው የእግዚአብሔር በግ፣ መጥቶ በእኛ ምትክ ሞተ (ዮሐንስ 1:29፤ 2ኛ ቆሮ 5:21)። ከኃጢአት የተገዛነው እግዚአብሔርን እንድናገለግል ነው (ሮሜ 6)።
4. በአንድምታ ያህዌም ሆነ ኢየሱስ "የቅርብ ዘመዶች" ናቸው፣ ለእኛ ብለው የሚሠሩ። ይህም ቤተሰባዊውን ዘይቤ ቀጣይ ያደርገዋል (ማለትም፣ አባት፣ ባል፣ ልጅ፣ ወንድም፣ የቅርብ ዘመድ)።
5. መቤዠት ለሰይጣን የተከፈለ ዋጋ አይደለም (ማለትም፣ መካከለኛው ሥነ-መለኮት)፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል እና የእግዚአብሔር ፍትሕ ከእግዚአብሔር ፍቅርና ሙሉ ሰጭነት ጋር በክርስቶስ የታረቁበት ነው። በመስቀል ሰላም ተመልሷል፣ የሰዎች ዐመጸኝነት ይቅር ተብሏል፣ የእግዚአብሔር አምሳል በሰው ልጆች አሁን በመሥራት ላይ ይገኛል፣ በወዳጃዊ ኅብረት!
6. ወደፊትም ቢሆን የመቤዠት ገጽታ ይኖራል (ሮሜ 8:23፤ ኤፌ 1:14፤ 4:30)፣ እሱም የእኛን የሥጋ ትንሣኤና አካላዊ ወዳጅነትን ከሥላሴ (አምላክ) ጋር ያካትታል።

▣ **"በሐሰት ተናገሩብኝ"** ይህ ምናልባት የሚያመለክተው (1) የያህዌን ጥቅም ለባአል መድረግ፤ (2) እንድም ያህዌን እንዳይፈልግና እንዳያውቅ የባአልን አምልኮ ከያህዌ ጋር ማደባለቅ፤ (3) ስለ እግዚአብሔር ባህሪይ እውነት ያልሆነ፣ (ለምሳሌ፣ 6:1-3) ግምት፤ ወይም(4) ነፃነትን እና ብልጽግናን ተስፋ መስጠት፡፡

**7:14** የቁ 14 የመጀመርያው መስመር በቁ 7 ላይ ያለውን የያህዌን ሐዘን ይጋራል፡፡ ቀጣይ የሆኑ ብዙዎቹ ቃላቶች እና ሐረጎች የባአል አምልኮ ታርካዊ ዳራን ያስረዳሉ:

1. "መልቀስ፣" ለባአል ሞት መንፈሳዊ ሐዘን
2. "አልጋዎች፣" በባአል ቅዱስ ቦታዎች የሚደረጉ ወሲባዊ ድርጊትን ያሳያል (ዝ.ከ. እሳ 57:7)
3. "ወይን ጠጅ፣" ከፍሬያማ ጣዖት በስጦታ እንደ ተሰጠ ይታያል(ባአል እና አሼር)
4. "ስብሰባ" (*grr* BDB 657)፣ የሰባ ሊቃናትን ትርጉም ተከትሎ (ዝ.ከ. REV፣ NEB፣ JB) ምናልባት "ቆረጠ" (*gdd*

BDB 151)፣ አይማኖታዊ ድርጊትን የሚያሳይ (ዝ.ከ. I ነገስ 18:28፤ ኤርም 16:6) of Ba'al worship
See David Allan Hubbard፣ ሆሴ ea (Tyndale OT Commentaries)፣ ቁ 141፡፡

▣ **"ስብሰባ"** እዚህ የእብራይስጡ ግስ(BDB 157፣ KB 184፣ *Kithpolel* IMPERFECT) ግልጽ አይደለም፡፡ አያሌ ትርጉሞች ለክፉ ዓላማ እንደተሰበሰበ ስብሰባ ያዩታል(ዝ.ከ. ASV፣ NASB፣ RSV፣ እና KJV፣ የBDB 151 አማራጭ ትርጉም ፣ "በውንብድና እንድ መሆን")፡፡ ይሁን እንጂ፣ቃሉን ማስተካከል ላይ መሠረት ባደረገ መልኩ ሌላው አማራጭ ትርጉም (BDB 151) "መጉዳት" ወይም "መጥቃት" የሚለው ነው፡፡ ይህ በሰፕቱአጀንት ውስጥ ይገኛል፣ የእዬሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ፣ እናም አዲሱ የእንግሊዘኛ መጽሐፍ ቅዱስ፡፡ ለባአል አምልኮ ጊዜ ለሚጠቀሙት

መገለጫ ነው(ዝ.ከ. 1 ነገስ 18:28፤ ኤርም 16:6፤ 41:5፤ 42:5፤ 48:37) እናም በሙሴ ሕግ የተከለከለ ነው(ዝ.ከ. ዘዳግ 14:1 and ሌዋ 19:28፤ 21:5)፡፡

▣

**NASB** "**ከእኔ ፈቀቅ ብለዋል**"
**NKJV፣ NRSV** "**በእኔም ላይ ዐመፁ**"
**TEV** "**ምን ዓይነት አመፃኞች ናቸው**"
**NJB** "**በእኔ ላይ እያመፁ ናው**"

**7:15** "**ወታደሮቻቸውን አሰልጥኜ አበረታውአቸው**"

እዚህ እግዚአብሔርን እያመሰለ ነው እንደ (1) የሚወዱ ቤተሰብ (ዝ.ከ. 11:1- 4) ወይም (2) እስራኤልን በእረሱ እንዲታመኑ በማስተማር ለጦርነት እንደሚያዘጋጅ ሰው (ማለትም፣ ቅዱስ ጦርነት)፡፡

▣ **"እንደ ተንኰለኛ ቀስት ሆኑ**" ይህ አንዱ የኃጢአት መገለጫ የሆነውን "ምልክቱን መሳት፣" የሚለውን ሐሳብ ያመለክታል፡፡ " እዚህ የጦርነት ጦር የሚታመንበት አይደለም፡፡

# ሆሴዕ 8
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|
| የእስራኤል ክህደት | ቀዋሚ ስለሁነው የእስራኤል አመፃ ምክንያት የተነሳ የእግዚአብሔር ፍርድ በእስራኤል ላይ ነው (4:1-14፡9) | ለጣዖት አምልኮ ምክንያት እግዚአብሔር እስራኤልን ይከሳል | ምልክት |
| 8:1-10 | 8:1-6 | 8:1-3 | 8:1-7 |
| | 8፡7-10 | 8፡4-10 | እስራኤል በውጭ ኃይላት ላይ በመታመኗ ጠፋች |
| | | | 8፡8-10 በውጪያዊ አምልኮ ላይ |
| 8:11-14 | 8:11-14 | 8:11-13 | 8:11-14 |
| | | 8፡14 | |

### የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ vii ተመልከት)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ

2. ሁለተኛው አንቀጽ

3. ሦስተኛ አንቀጽ

4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**ሆሴዕ: 8:1-7**

[1] መለከትን ወደ አፍህ አቅርብ ቃል ኪዳኔን ተላልፈዋልና፥ በሕጌም ላይ
ዐምፀዋልና በእግዚአብሔር ቤት ላይ እንደ ንስር ይመጣል።
[2] እርሱም፡- አምላክ ሆይ፥ እኛ እስራኤል አወቅንህ ብለው ወደ እኔ ይጮኻሉ።
[3] እስራኤል ደግነትን ጥሎአል ጠላትም ያሳድዱታል።
[4] ለራሳቸው ነገሥታትን አነገሡ፥ ከእኔም ዘንድ አይደለም አለቆችንም አደረጉ፥
እኔም አላወቅሁም ለጥፋታቸውም ከብራቸውና ከወርቃቸው ጣዖታትን ለራሳቸው አደረጉ።
[5] ሰማርያ ሆይ፥ እምቦሳህን ጥሎአል ቍጣዬ በላያቸው ነድዶአል እስከ መቼ ድረስ ንጹሕ ሊሆኑ አይችሉም?
[6] ይህ ደግሞ ከእስራኤል ዘንድ ነው ሠራተኛ ሠራው፥ እርሱም አምላክ አይደለም የሰማርያም እምቦሳ ይቈራረጣል።
7 ነፋስን ዘርተዋል፥ ዐውሎ ነፋስንም ያጭዳሉ አገዳ የለውም፥ ከፍሬውም ዱቄት አይገኝም ቢገኝም እንግዶች ይበሉታል።

**8፡1 “መለከትን”**ይህ ለሃይማኖታዊ አላማ እና በጦር ሃይል ውስጥ መረጃን ለመለዋወጥ ያገለግል የነበረውን “የበግ ቀንድ” (BDB 1051) ያመለክታል፡፡ በ5፡8 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት፡፡ እግዚአብሔር እስራኤል እንድትቀጣ አሦርያን እየጠራ ነው (ዝ.ከ. ቁ 3ለ፣ዘዳ 28:49፣ ኢሳ 10:5)፡፡

▣ **“ንስር”** ይህ ጥንብ አንሳን (BDB 676) ይገልጻል፡፡ የሚያመለክተውም በእግዚአብሔር የተላከ ንጹህ ያልሆነን አዳኝ ወፍ ሲሆን ይህም አብሮ ከሚመጣው ሞት እና ጥፋት ጋር የተያያዘውን የአሦሪያን ወራሪ ጦር እንደሚወክል ግልጽ ነው (Targums)፡፡

▣ **“በእግዚአብሔር ቤት”** ይህ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚያመለክት ሲሆን እዚህ ላይ ግን የተጠቀሱት የእስራኤል ሰሜን ነገዶች ናቸው (ዝ.ከ. 9:3-4፣15፣አአት)፡፡ ሆኖም ግን የአኢት መጽሐፍ ቅዱስ “የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ” ብሎ ተርጉሞታል፡፡

▣ **“ቃልኪዳኔን ተላልፈዋልና”** ይህ “ሕግን ማፍረስ” (BDB 716፣ KB 778፣ *Qal*PERFECT፣ዝ.ከ. 6:7፣ዘዳ 17:2፣ኢያ 7:11፣15፣መሳ 2:20፣2ኛነገ 18:12፣ ኤር 34:18) ማለት ነው፡፡ ሆሴዕ የቃል ኪዳኑን ሃሳብ ብዙ ጊዜ ይጠቀምበታል (ዝ.ከ. 2:18፣6:7፣8:1)፡፡ ሆሴዕ ከእግዚአብሔር የተቀበለው ልዩ መልዕክት ሃጥያት ሕግ መተላለፍን ጨምሮ ቃል ኪዳንን መተላለፍ እየሆነ መምጣቱን (ማለትም፤ የቃል ኪዳኑ ጋብቻ) የሚያሳይ ነው፡፡

▣ **“በሕጌም ላይ ዐምፀዋልና”** ይህ “ህጋዊ ስልጣንን መቃወም” (BDB 833፣ KB 981፣ *Qal*PERFECT) ማለት ነው፡፡ በዚህ ቁጥር ውስጥ ያሉት ሁለቱ ሃረጎች (“ጥሰዋል” እና “አምፀዋል”) በእብራዊያን ውስጥ ትይዩ ዝምድና አላቸው (ሁለቱም*Qal*PERFECT፤ “የእኔ ቃል ኪዳን” እና “የእኔ ሕግ”)፡፡ ኒዶት ፤ በጥራዝ 4 ፤ ገፅ 712 ውስጥ እስራኤል በያህዌ ላይ የፈጸመቻቸው ሃጥያቶች ዝርዝር በማራኪ ሁኔታ አቅርቦታል፤

1. “ከውሽማ በኃላ መሔድ፤” 2:5፣13
2. “እኔን ረስተዋል፤” 2:13፣ 4:6፣ 8:14፣ 13:6
3. “እልከኛ” 4:16፣ 9:15
4. “እግዚአብሔርን መወንጀል” 5:7፣ 6:7182
5. “በሐሰት ማድረግ” 7:1፣ 10:2
6. “ሐሰታቸው፤” 7:3፣ 10:13፣ 11:12
7. “ከእኔ ፈቀቅ ብለዋል እና፤” 7:13
8. “በእኔም ላይ አምጸዋልና፤” 7:13፣ 8:1
9. “በሐሰት ተናገሩብኝ” 7:13
10. “በልባቸው ወደ እኔ አልጮኹም፤” 7:14
11. “በእኔም ላይ ዐመፁ” 7:14

**8:2 “‘አምላክ ሆይ ፤ እኛ እስራኤል አወቅንህ’፤ ብለው ወደ እኔ ይጮኻሉ’”** በልማዳዊ እና በአምልኮ ሥነሰርዓቶች ላይ እግዚአብሔርን ያውቁት ነበር (ማለትም፤ “ይጮኻሉ” BDB 277፣ KB 277፣ *Qal*IMPERFECT )፤ ነገር ግን እግዚአብሔርን በግል ግንኙነት እና እምነት አያውቁትም (BDB 393፣ KB 390፣ *Qal*PERFECT)፡፡ የአምላክነት መልኩን ብቻ ይዞ እግዚአብሔርን አለማወቅ አሳዛኝ ነገር ነው (ዝ.ከ. 7:14፣ ኢሳ 29:13፣ 2ኛጢሞ 3:5)፡፡

**8:3 “እስራል ደግነትን ጥሎአል”** ይህ ግስ (BDB 276፣ KB 276፣ *Qal*PERFECT) በቁ 5 ውስጥ ተደግሟል፡፡ እስራኤል የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ጥላለች፡፡ እግዚአብሔር የ“ጥጃ” አምልኳቸውን አልተቀበለውም! ይህ ጤናማ ፣ የሚወደድ እና የተባረከ ማህበረሰብ የሚወክለውን የያህዌን የቃል ኪዳን ታማኝነት የሚያሳይ ይመስላል (ዝ.ከ. አሞፅ 5:14፣ 15፣ ሚክያስ 6:8)፡፡

**8:4 “ለእራሳቸው ነገስታትን አነገሱ ከእኔም ዘንድ አይደለም”** በመጀመሪያዎቹ ሁለት መስመሮች መካከል ያለውን ትይዩነት ያስተውሉ፡፡ቀጣዮቹ ሁለት መስመሮች ከቁ 5 የመጀመሪያ ሁለት ጽሑፎች ጋር እና ከቁ 6 ሁለት የመጨረሻ ጽሑፎች ጋር ትይዩ ናቸው፡፡እነዚህ ሁሉም ወርቃማዎቹን ጥጆች ያመለክታሉ፡፡ ምስሎች ያህዌን እንደሚወክሉ ነበር የሚታሰበው (ዝ.ከ. ዘጸ 32) ፤ ነገር ግን ይህ ሃሳብ ወደ ርቢ ጣዖታት ተለውጦ ነበር!
“እነሱ” የሚለው የእስራኤልን መሪዎች (ካህናት እና ልዕላን) ያመለክታል፡፡ ከዳዊት ዘር ንጉሶች (በይሁዳ ውስጥ) ፊታቸውን በማዞር የራሳቸውን መሪዎች ሾመዋል፤ እንዲሁም የራሳቸውን የማምለኪያ ቦታዎችን ሰርተው ነበር (በቤቴል እና በዳን ኢዮርብአም የሰራቸው ሁለቱ “ጥጃዎች”)፡፡ ለዚህ የጊዜው ምሳሌ ከኢዮርብአም 2ኛ ቀጥሎ የነበሩት ተከታታይ ንጉሶች ናቸው (በ7:3 ላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ)፡፡ በምድር ላይ የራሱን ተወካዮች መሾም የሚችለው እና እውነተኛ ንጉሳቸው ያህዌ ብቻ ነበር፡፡

**8:5 “ጥጃ”** የሰሜኑ ነገድ (ከክርስቶስ ልደት በፊት በ922 ውስጥ) አዲሱ መሪ ኢዮርብአም 1ኛ ሕዝቦቹ በእየሩሳሌም ውስጥ ማምለክ እንዲቀጥሉ ስላልፈለገ ሕዝቡ ባለበት እንዲቆይ ለማድረግ ያህዌን የሚወክሉ ሁለት ወርቃማ ጥጃዎችን፤ እንዱን በሰሜን ዳን ውስጥ ሁለተኛውን ደግሞ በደቡብ ቤቴል ውስጥ መስርቶ ነበር፡፡ ይህም ሙሉ በሙሉ የተወገዘ ነበር (ለምሳሌ፤ ዘጸ 32:4-5፣ 1ኛነገ 12:28-29፣ ሆሴ 13:2)፡፡

▣ **“ጥሎአል ቁጣዬ በላያቸው ነድዶአል”** እነዚህን አማራጭ የአምልኮ ቦታዎችን በተመለከተ የእግዚአብሔር ስሜት በግልጽ ተገልጽዋል፤:
“ጥሎአል” (BDB 276፣ KB 276፣ *Qal*PERFECT) ጠንካራ ቃል ነው ፤ ተመሳሳይ መነሻ ያለው በ*ሂፊል ውስጥ* “ክርፋት” ማለት ነው! አአት “አውጥቶ መጣል” ብሎ ይተረጉመዋል፡፡
“ቁጣዬም ነድዷል” (BDB 354፣ KB 351፣ *Qal*PERFECT) በቃል ኪዳኑ አለመገዛት የተነሳ የእግዚአብሔርን ምላሽ ለመግለጽ ያገለግላል (ለምሳሌ፤ ባብዛኛው በሙሴ ውስጥ ዘዳ 6:15፣ 7:4፣ 11:17፣ 29:26፣ 31:17፣ አልፎ አልፎ በነብያት ውስጥ ኢሳ 5:24-25)

▣

**NASB፣ NRSV** **“እስከ መቼ ድረስ ንጹህ ሊሆኑ አይችሉም”**

NKJV "እስከመቼ ድረስ ንጹህነት ይኖራቸዋል"
TEV "እስከ መቼ ድረስ ጣዖት አምላኪነታቸውን ያቆማሉ"
NJB "እስከ መቼ ንጹሕነታቸውን ሊመልሱ ይችላሉ"
ይህ አሉታዊ ምላሽ የሚፈልግ የሽንገላ ጥያቄ ነው፡፡ እስራኤል በቋሚነት ንጹህ እና የጠራ መሆን ሳይችል ቀርቷል!

**8:6** ይህ ለእስራኤል (የየትኛውም ሕዝብ) ጣዖት አምላኪነት የተሰጠ አሽሙራዊ ምላሽ ሊሆን ይችላል፡፡ ምንም ዓይነት እግዚአብሔርን የሚወክል ምስል (ዝ.ከ. ዘጽ 20፣ዘዳ 5) እንዳይኖራቸው ማስጠንንቀቂያ የተሰጣቸው ሕዝቦች ፤ ጥጆች ነበሯቸው—ሁለቱንም!

**8:7 *"ነፋስን ዘርተዋል ዐውሎ ነፋስን ያጭዳሉ"*** የመጀመሪያ ሁለት ጽሑፎች በህብረት እና በግል ለእግዚአብሔር ማድረግ ያለብንን ተግባሮች የሚናገሩ ምሳሌያዊ ጽሑፎች ናቸው (ማለትም፤ የመዝራት እና የማጨድ መንፈሳዊው መርህ፤ ዝ.ከ. 10:12-13፣ 12:2፣ ኢዮ 4:8፣ 2ኛቆሮ 9:6፣ ገላ 6:7)፡፡

▣ ***"እንግዶች ይበሉታል"*** ይህ የእስራኤልን በአሦርያ መገዛት የሚያሳይ ነው (ዝ.ከ. ኢሳ 1:7)፡፡ እስራኤል ባዖልን ያመሰገነችበት ሰብል (ምናልባት አንድ ከተገኘ ዝ.ከ. ቁ 7፣መስመሮች ሐ፣መ) እራሳቸው የሚበሉት አይሆንም (ማለትም፤ አሦራዊያን)፡፡

## *ሆሴዕ*: 8:8-10

**[8] እስራኤል ተውጦአል፥ በአሕዛብም መካከል ዛሬ እንደ ረከሰ ዕቃ ሆኖአል።**
**[9] ለብቻውም እንደሚቀመጥ እንደ ምድረ በዳ አህያ ወደ አሦር ወጥተዋል ኤፍሬምም ወዳጆቹን በእጅ መንሻ ገዛ።**
**[10] ነገር ግን ለአሕዛብ እጅ መንሻ ቢሰጡ እኔ አሁን እሰበስባቸዋለሁ ከንጉሥና ከአለቆችም ሸክም የተነሣ ይደክማሉ።**

**8:8 *"እስራኤል ተውጦአል"*** ይህ ግስ በመሞት (*ሲኦል*፣ ዝ.ከ. ምሳ 1:12) እና በጥፋት ላይ የለውን ሓዘን የሚገልጽ ዘይቤ ነው፡፡ እዚህ ላይ እስራኤል ለግዞት እንደተወሰደች ለመግለጽ ያገለግላል (ለምሳሳሌ፤ መዝ 124:3፣ ኤር 51:34፣ ሰቆ 2:16)፡፡

▣ ***"ዛሬ እንደ ረከሰ ዕቃ"*** ይህ *"ዕቃ"* (BDB 479) የሚለው ቃል ሰፊ የትርጉም ዘርፎች አሉት፤
1. ወድ ከሆነ ቁሳቁስ በሰው የተሰራ ነግር(ማለትም ፤ ወርቃማ ጥጃዎች)
2. የሆነ ዓይነት ውድ ዕቃ ማስቀመጫ (ለምሳሌ ኤር 25:34መ)
3. በምርኮ የተወሰደ ዕቃ (ማለትም፤ "ጓዝ" ለምሳሌ ኤር 46:19፣ ሕዝ 13:3፣4፣7)
4. የተሸነፈ ሕዝብ ዘይቤ (ለምሳሌ ኤር 48:38)

በቁጥር 4 እና በቁጥር 1 መካከል አለም አቀፍ ብኾርታ ሊኖር ይችላል! የእስራኤል ተወላጆች "ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ ርስት" ፤ "የካህናት መንግስታት" (ዝ.ከ. ዘጽ 19:5-6) እንዲሆኑ ነበር የታሰበው ፤ ነገር ግን አሁን ልክ እንደ ማንኛውም ህዝብ ናቸው፡፡እግዚአብሔር በእነሱ በኩል ለአለም እራሱን የመግለጽ አላማው (ዝ.ከ. ዘጽ 19:5ሐ፤ አሞፅ 3:2) ተጨናፍኋል!

**8:9 *"ወደ አሦር ወጥተዋል"*** ይህ ግስ (BDB 748፣ KB 828፣ *Qal*PERFECT) በአቅጣጫ ጠቋሚ ኮምፓስ ስሜት የተገለጸ ነው፡፡ ምንም እንኳን አሦሪያ በሰሜንምስራቅ ያለች ቢሆንም ወደ እሷ ለመሄድ ብቸኛው መንገድ ሰሜኑን በመያዝ ነው፡፡ ሰሜን የርኩሰት እና የአመፅ ዘይቤ እየሆነች ሄዳለች፡፡ይህ ቀጥር እስራኤል ከለላን ለማግኘት ስትል የአሦሪያን ኢጋርነት እየፈለገች መሆኗን የሚገልጽ ነው፡፡

▣ ***"ለብቻውም እንደሚቀመጥ እንደ ምድረ በዳ አህያ"*** የዱር አህዮች አንዱ ባህሪያቸው (BDB 825) በግንኙነት ጊዜ (የተራክቦ አምልኮ መግለጫ) ከቁጥጥር ወጪ መሆናቸው ነው (ዝ.ከ. ኤር 2:23-24) ፡፡ እስራኤል በዚህ መንገድ ነበር ወደ ጣዖት አምልኮ ያዘነበለችው፡፡

▣ ***"ኤፍሬምም ወዳጆቹን በእጅ መንሻ ገዛ"*** ግሱ (BDB 1071፣ KB 1759፣ *ሂፊል* PERFECT) የውሽማ አምልኮ የመቀበል ቅዱሳዊ አጻጻፍ አለው (ዝ.ከ. 2:12)፡፡ይህ የውጪ አገር ኢጋሮችን ያመለክታል(ለምሳሌ፤ ቁ 10፣ ሕዝ 16:36-37)፡፡ እነዚህ የፖለቲካ ኢጋርነት የሕዝቡንም አማልክት በማካተት ሁልጊዜ ይካሄድ ነበር፡፡ ምፀቱ ውሽማዎቿ አሁን ጠላቶች ናቸው የሚለው ነው (ዝ.ከ. ቁ 3)! በዚህ ዓውድ ውስጥ የርቢ አምልኮ የመንፈሳዊ ህይወት ብልሹነት ለመግለጽ እንደሚያገለግል ግልጽ ነው፡፡ይህ (1) ቀጥተኛ (2) ዘይቤያዊ ወይም (3) ሁለቱንም እንደሆነ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው፡፡ ከከነዓናዊው ባዖል አምልኮ ጋር የተያያ የተራክቦ ክፍል እንደነበር ጥቂት ማስረጃዎች አሉ፡፡እስራኤል ጥፋታቸውን የበለጠ መራራ የሚያደርገውን ይህን አምልኮ አድርጋ ሊሆን ይችላል!

**8:10 *"ነገር ግን ለአሕዛብ እጅ መንሻ ቢሰጡ ከንጉስ እና ከአለቆችም ሸክም የተነሳ ይደክማሉ"*** ይህ በአሦሪያ (ንጉሳቸው "የነገስታት ንጉስ" ይባል ነበር ይህም ከባቢሎናዊያን መጠሪያ "የንጉሶች ንጉስ" ከሚለው ጋር ተያያዥነት አለው) ይጠየቅ የነበረውን ከፍተኛ ግብር የሚያመለክት ነው፡፡

▣ ***"እኔ አሁን እሰበስባቸዋለሁ"*** ግሱ (BDB 867፣ KB 1062፣*peil* IMPERFECT) በተለምዶው እግዚአብሔር ከፍርዱ በኃላ የተበተነ ሕዝቡን እንደሚሰበስብ ለማሳየት የሚጠቅም ሲሆን እዚህ ላይ ግን ለፍርድ እንደሚሰበሰቡ የሚያስረዳ ትርጉም አለው (ማለትም፤ ለግዞት)፡፡

## *ሆሴዕ*: 8:11-14

**11 ኤፍሬም ኃጢአትን ለመሥራት መሠዊያ አብዝቶአልና መሠዊያ ለኃጢአት ይሆንለታል።**
**12 የሕጌን ብዛት ጽፌለታለሁ እነርሱ ግን እንደ እንግዳ ነገር ቈጥረውታል።**
**13 መሥዋዕቴን ያቀርባሉ፥ ሥጋንም ያርዳሉ፥ ይበላሉም እግዚአብሔር ግን አይቀበላቸውም በደላቸውንም ያስባል፥**
**ኃጢአታቸውንም ይቀጣል እነርሱም ወደ ግብጽ ይመለሳሉ።**

**14 እስራኤል ፈጣሪውን ረስቶአል፥ መስገጃዎችንም ሠርቶአል ይሁዳም የተመሸጉትን ከተሞች አብዝቶአል**
**እኔ ግን በከተሞች ላይ እሳትን እሰድዳለሁ፥ አዳራሾችንም ትበላለች።**

**8:11 "ኤፍሬም *ኃጥያትን ለመሥራት መሠዊያ* አብዝቶአልና"** ይህ (1) በቤቴል እና በዳን የሚመለውን ወርቃማ ጥጃ ወይም (2) በሃገሩ ውስጥ በሁሉም ኮረብታ እና በእያንዳንዱ መንደር ውስጥ ባዖል የሚመለከበት ቦታን ያመለክታል፡፡ ምፀቱ የእስራኤል ሃይማኖተኝነቷ የሚረዳት አልሆነም ፤ እንዲያውም ጥፋትን ያመጣባት ነበር! "ኃጥያትን ለመስራት መሰዊያ" የሚለው ሃረግ ትኩረት እንዲያገኝ ሁለት ጊዜ ተደግሟል፡፡

**8:12 "የሕጌን ብዛት ጽፌለታለሁ"** እግዚአብሔር በግልጽ እና በተደጋጋሚ እራሱን ገልጾላቸዋል (ማለትም፤ "አስር ሺህ ህጎች"፣ ለምሳሌ፤ 11:2 እና 2ኛነገ 17:13-15 ለይሁዳ)፡፡ የእነሱ ችግር የመረጃ እጥረት አልነበረም ነገር ግን እጥረት የነበረባቸው (1) የእውነት (2) የቃል ኪዳኑ ታማኝነት እና (3)የግል እምነት ነበር (ዝ.ከ. 4:1)! በእግዚአብሔር ብርሃን እና እውነት ላይ አመጹ፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB፣ NRSV | **"እንርሱ ግን እንደ እንግዳ ነገር ቆጥረውታል"** |
| NKJV | **"ነገር ግን እነርሱ እንግዳን ነገር ተመልክተዋል"** |
| TEV | **"ነገር ግን እነርሱ እነደ እንግዳ እና እንደ ባዕድ ጥለዋቸዋል"** |
| NJB | **"ኤፍሬም እንደማይታወቅ ነገር ቆጥሮታል"** |

"እንግዳ ነገር" (ዲቢዲ266፣ KB 267፣ *Qal*ሙሉ ቦዝ አንቀጽ) የሚለው መጠሪያ በብዙ ስሜቶች ቀርቧል፤

1. የቤተሰብ አባላት ያልሆኑ (ለምሳሌ፤ ዘዳ 25:5፣ ሆሴ 5:7)
2. ለትክክለኛ ደንቦች አለመገዛት
   *ሀ* መበሳጨት ዘጸ 30:9
   *ለ* እሳት ዘሌ 10:1
3. *አመንዝራዎች* ለምሳሌ፤ ምሳ 2:16፣ 5:3፣20፣ 7:5፣ 22:14
4. የውጭ ሃገር ሰዎች (ጠላቶች ፣ ወራሪዎች)፣ ለምሳሌ 7:9፣ 8:7፣ ኢሳ 1:7፣ 25:2፣5፣ 29:5፣ 61:5፣ ኤር 51:51፣ ሕዝ 28:7፣10 ለነሱ የእግዚአብሔር ህግ ቤተሰባዊ ያልሆነ የወጭ አካል ሆኖባቸው ነበር!

**8:13 "*መሥዋዕቴን ያቀርባሉ ፤ ሥጋንም ያርዳሉ ፤ ይበላሉም*"** ስሙ (BDB 257) እና ግሱ (BDB 256) ትኩረት ለመስጠት ያላቸውን አጠቃቀም አስተውል፡፡ ይህ በራስ ወዳድነት የመነጨ ፍላጎት ሃይማኖታዊ *ሥነ ሥርዓትን* ፤ በዋናነት የጋራ ምግብ ማከናወንን የሚያመለክት ይመስላል (ዝ.ከ. ዘሌ 7:15-18)፡፡

▣ **"እግዚአብሔር ግን አይቀበላቸውም "** "ደስታ" (BDB 953፣ KB 1280፣ *Qal*PERFECT) "*መቀበል*" (ሰዎች፤ ዝ.ከ. ኤር 14:10፣ ሕዝ 20:40 እና መስዋዕቶች ዝ.ከ. ኤር 14:12፣ ሕዝ 20:41) ማለት ነው፡፡ይህ ቁጥር እና ሃሳቡ በ 5:6 ይዛመዳሉ፡፡ እግዚአብሔር በአምልኮ ስነስርዓቶች የሚደሰተው ከልብ የመነጨ እምነት እና መታዘዝ ሲታከልበት ነው (ዝ.ከ. አሞፅ 5:21- 28: ሚክ 6:6-8)፡፡

▣ **"በደላቸውንም ያስባል"** በ 7:2 ላይ ያውን ማሰታወሻ ተመልከት

▣ **"እነርሱም ወደ ግብፅ ይመለሳሉ"** ይህ የዘጽዓት ዳግም መምጣት ወይም የባርነትን መንገድ የሚያመለክት ዘይቤ ይመስላል (ዝ.ከ. 7:16፣ 9:3)፡፡ይህን እና 11:5ን ሲያነጻጽሩ የሚጣረኑ ይመስላል፡፡ሆኖም ግን እኔ ግብፅን እንደ ባርነት ምልክት አድርጎ እየተጠቀመ እንደሆነ አስባለሁ፡፡እስራኤል ወደ ባርነት ትመለሳለች ፤ ነገር ግን አሁን በአሦሪያ መንግስት ይሆናል (ማለትም ግዞት)፡፡
እስራኤል "የምትመለስ"(ማለትም ግዞት፣ ተመሳሳይ ግስ) ሆና "አትዘርም" (ማለትም፤ንስሃ መግባት BDB 996፣ KB 1427)፡፡

**8:14 "እስራኤል ረስቶአል"** እስራኤል እግዚአብሔርን እና ቃል ኪዳኑን (ዝ.ከ. 2:13፣ 4:6፣ 13:6) "ረስታለች" ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር በደሏን "ያስባል"(ዝ.ከ. ቁ 13መ)!

▣ **"*ፈጣሪውን*"** ይህ የ"መርሳት" ቀጥተኛ ተሳቢ እና የ"መስራት"(BDB 793፣ KB 889) ግስ *Qal*ሙሉቦዝ አንቀጽ ነው፡፡እስራኤል ለራሳቸው (ዝ.ከ. ቁ 6) ጣዖታን (ማለትም፤ ወርቃማ ጥጆች) ሰሩ በሚለው እና እስራኤል የፈጠራቸውን (ዝ.ከ ዘፍ 1:26፣ ኢሳ 17:7) ረሱ በሚለት መካከል ምፀት አለ፡፡
"ፈጣሪ" የሚለው ቃል ዘፍጥረትን ሳይሆን ሕዝብን (ማለትም የአብርሃም መጠራት ፣ ዘፀአት የሲና ህግ መስጠት)፣ለማበጀት የእግዚአብሔርን መነሳሳት የሚያመለክት ሊሆን ይችላል፡፡

▣ **"*መስገጃዎችንም ሰርቶአል* የተመሸጉትን ከተሞች"** እስራኤል በሃብቷ እየተማመነች ነበር (ዝ.ከ. ቁ 14ሐ)፡፡ ይሁዳ በጦር ኃይሏ ጥንካሬ እየተማመነች፡፡ሰሪው በሰው ልጁ ስራቶች የሚገረም አይደለም፡፡ ይጠፋሉ! በ 2ኛነገ 18:13 ውስጥ ሰናክሬም ሁሉን የይሁዳ ምሽግ ከተሞች እንደተቆጣጠራቸው ተነግሯል፡፡

▣ **"እሳትን እሰድዳለሁ"** ኒዶት፣ ጥራዝ 1፣ ገፅ 533፣ "ለእስራኤል ጠላቶች የተተነበየው ቅጣት የከተማዎች መቃጠልን ያካተተ ነበር (ኤር 43:12-13፣ 49:27)፡፡ ይህም ልዩ በሆነ ለውጥ በአሞፅ 1:4፣7፣10፣12፣14፣ 2:2፣5፣ በሆሴዕ 8:14 ውስጥ የተቀመጠ ሲሆን "እሳትን እሰድዳለሁ '" ተብሎ የተቀመጠው ይህ ሃሳብ ምናልባትም ከቅዱስ ጦርነቱ ሃሳብ በተቃራኒው የተቀመጠ ሊሆን ይችላል፡፡
እንደዚህ ከሆነ እግዚአብሔር ለእስራኤል የሚከላከል እና የሚዋጋ ሳይሆን እግዚአብሔር እራሱ ዋናው የእስራኤል ጠላት ሆነ ማለት ነው! እንደ ነብያት መልክቶች ሁሉ ይህ የሚያስደነግጥ ተገላቢጦሽ ነው!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. በ 8:4 ወስጥ "እነሱ" የሚለው የሚያመለክተው ማንን ነው?
2. ለምንድን ነው "የወርቅ ጥጃዎችን" ማምለክ ያህዌን እንደ መጥላት የሚታየው?
3. 8:13 ከ11:5 ጋር የሚጣረን ነው?

# ሆሴዕ 9
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|
| ለእስራኤል ኃጢአት ፍርድ | ቀዋሚ ስለሁነው የእስራኤል አመፃ ምክንያት የተነሳ የእግዚአብሔር ፍርድ በእስራኤል ላይ ነው (4:1-14:9) | ሆሴዕ ለእስራኤል ኃጢአት ቅጣትን ያውጃል | የምርኮ ሀዘን |
| 9:1-2 | 9:1-17 | 9:1-6 | 9:1-6 |
| 9:3-6 | | | ቅጣት እነደሚመጣ አስቀድሞ በመናገሩ የነብዩ መከራ |
| | | 9:7-9 | 9:7-9<br>ቅጣት በበኣል ፒኦር ወንጀል |
| | | የእስራኤል ኃጢአት እና መዘዙ | |
| 9:10-16 | | 9:10-12 | 9:10-14 |
| | | 9:13-14 | |
| | | በእስራኤል ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ | ገልጌላ |
| | | 9:15-16 | 9:15-17 |
| 9:17 | | ነብዩ ስለ እስራኤል ይናገራል<br>9:17-10:8 | |

### የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ vii ተመልከት)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ

2. ሁለተኛው አንቀጽ

3. ሦስተኛ አንቀጽ

4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

### ሆሴዕ: 9:1-6

[1] እስራኤል ሆይ፥ ከአምላክህ ተለይተህ አመንዝረሃልና እንደ አሕዛብ ደስ አይበልህ፥
ሐሴትንም አታድርግ በእህሉ አውድማ ሁሉ ላይ የግልሙትናን ዋጋ ወድደሃል።
[2] አውድማውና መጥመቂያው አይመግባቸውም፥ ጉሽ ጠጅም ይጐድልባታል።
[3] በእግዚአብሔር ምድር ላይ አይቀመጡም ኤፍሬምም ወደ ግብጽ ይመለሳል፥
በአሦርም ርኩስን ነገር ይበላሉ። [4] ለእግዚአብሔርም የወይን ጠጅን ቁርባን አያፈስሱም፥ መሥዋዕታቸውም
ደስ አያሰኘውም የሐዘንም እንጀራ ይሆንላቸዋል፥ የሚበላውም ሁሉ ይረክሳል እንጀራቸውም
ለሰውነታቸው ይሆናል እንጂ ወደ እግዚአብሔር ቤት አይገባም። [5] በዓመት በዓል ቀንና በእግዚአብሔር በዓል ቀን ምን ታደርጋላችሁ?
[6] እነሆ፥ ከጥፋት ሸሽተው ሄዱ፥ ግብጽም ትሰበስባቸዋለች፥
ሜምፎስም ትቀብራቸዋለች ሳማም የብራቸውን ጌጥ ይወርሳል፥ እሾህም በድንኳኖቻቸው ውስጥ ይበቅላል።

**9:1 "ደስ አይበልህ"**ይህ ቁጥር የአዝመራ ጊዜ ክብረ በዓልን ያመለክታል (ዝ.ከ. ቁ 5)፡፡ እነዚ ጊዜዎች ባዖል የሚከበርበት እና የሚመለክበት በዓላት ነበሩ (ምትሐት የተጀመረበት)፡፡ይህዌ የነሱን የማይረባ ክብረ በዓል ወደ ቀብር ሙሾ ይለውጠዋል!
ይህ ግስ (ዲቢዲ 970፣ KB 1333፣ *Qal* JUSSIVE በቅርጽ ሳይሆን በትርጉም፤ ዝ.ከ. ኒዶት ፣ ጥራዝ 1 ገጽ 856) "መደሰት" ወይም "ደስታ" (ዝ.ከ. 7:3) ማለት ነው፡፡እስራኤል እንደ ሌላ አገር "ሕዝብ"(BDB 766) እየሆነች ነው፡፡ይህ ከብዙዎቹ የአምልኮ ቃላት አንዱ ነው፤

1. መደሰት፤ ቁ 1
2. ሐሴት፤ቁ 1
3. የመጠጥ መስዋዕት፤ ቁ 4
4. መስዋዕት፤ ቁ 4
5. በዓመት በዓል ቀን፤ ቁ 5

ነገር ግን ዋናው ቁም ነገር ቁ 1ለ "ከአምላክህ ተለይተህ አመንዝረሃልና" የሚለው ነበር ፤ መደሰት ሳይሆን ለቅሶ (ዝ.ከ. ኢሳ 22:12-14) የሚገባ ነበር! አምልኮን በተመለከተ ከአይሁዶች ትምህርት መውሰድ አለብን፡፡ የአምልኮ ጊዜያቸው በእግዚአብሔር መልካምነት እና አፈጣጠሩ ምክንያት ታላቅ ደስታ የሚከሰትባቸው ነበሩ፡፡ በዚህ ዓውድ ውስጥ ሆነን ስናየው ግን እግዚአብሔር በጣዖት አምልኳቸው ምክንያት ፍርድ እየጠበቃቸው ስለሆነ ሐሴት ማድረጋቸው አግባብ እንዳልሆነ አሳውቋቸዋል፡፡ብልጽግና በብሉ ኪዳን ውስጥ (በይበልጥ ዘዳግም) የእግዚአብሔር የበረከቱ ምልክት ነበር ፤ ነገርግን በዚህ ታሪካዊ ቅንብር ውስጥ አሳሳች ሁኔታን የሚጠቁም አጭር ቃል ነው፡፡ እስራኤል በልማዳዊ እና በጣዖት አምልኮ ወጥመድ ውስጥ ገብታለች ፤ ያህዌ ግን ይህን ስህተቷን ስርዓት ያሲዘዋል (ለተመሳሳይ ተግባራት ይሁዳ ላይ ያደርገዋል ለምሳሌ፤ ኤር 2፣ ሕዝ 23)፡፡

▣ **"እንደ አሕዛብ!"** ይህ አስቸጋሪ ሁኔታ ነበር! ለያህዌ ይገባ የነበረውን አምልኮ ለከነዓኒያኑ ባዖል አድርገውታል፡፡

▣ **"አመንዝረሃልና"** የከነዓናዊያንን የርቢጣዖታት አምልኮ እየተለማመዱ ነበር፡፡ በያህዌ ስም ስጋዊ እና መንፈሳዊ እርኩሰትን (ለምሳሌ፤ 1:2፣ 4:10፣13፣14፣15፣18[ሁለት ጊዜ]፣ 5:3፣ 9:1) እያደረጉ ነበር!

▣ **"የጉልምትናን ዋጋ ወደሃልና"** የእስራኤል ፍቅር (BDB 12፣ KB 17፣ *Qal* PERFECT) ወደ "የግልሙትና ዋጋ" (BDB 1071፣ ዝ.ከ. 2:5፣12) ያዘነበለ ነው፡፡በ 8:10 ውስጥ የውጪ አገር ህብረትን ለመግለጽ ይህ ተመሳሳይ ቃል ተገልጧል፡፡ ይህ ቀጥተኛ ይሁን ምሳሌያዊ ለመለየት በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡

▣ **"በእህሉ አውድማ ሁሉ ላይ"** ይህ (BDB 175) ጥራጥሬውን ከገለባው የመለያ ቦታ ነበር፡፡ ቦታው ከፍታ ላይ ያለ ሲሆን ጥራጥሬው ወደ አየር ላይ በሚወረወርበት ጊዜ ክብደት የሌው ገለባ አየር ላይ ይበተናል፤ ክብደት ያለው ጥራጥሬ ግን መሬት ላይ ባለው ክምር ላይ ይወርዳል፡፡ የርቢ አምልኮ ምትሃት የማስጀመሪያ መልክ ስላለው ይህ የፍትወት ተግባር የተደረገበት የመጀመሪያ ቦታ ነበር (ለምሳሌ፤ 4:11-14)፡፡ ሆኖም ግን የያህዌን ምላሽ በ ቁ 2፣11፣14፣16 ውስጥ ያስተውሉ!

**9:2** የርቢ ምንጩ ያህዌ እንጂ ባዖል አልነበረም(ዝ.ከ. 2:16)፡፡

**9:3 "በእግዚአብሔር ምድር ላይ አይቀመጡም"** የተስፋይቷ ምድር (ለምሳሌ፤ ዘሌ 25:23፣ኤር 2:7፣16:18፣ሕዝ 36:5፣38:16፣ኢዩ 1:6) እንዲሁም ሁሉም መሬት የያህዌ ነው (ለምሳሌ፤ ዘጸ 9:29፣ 19:5)፡፡ይህዌ በዘፍ 15:16 ውስጥ መሬቱን ከአሞራዊያን እንደሚያጸዳ ቀደም ብሎ ተናግሯል፡፡ የያህዌ ህዝብም እንደ አሞራዊያን ተመሳሳይ ርኩሰትን ካደረጉ እነሱንም እነደዚሁ ያሶግዳቸዋል (ዝ.ከ. ዘሌ 18:24-28)፡፡ እነሱም አደረጉት እሱም አደረገባቸው!

▣ **"ኤፍሬምም ወደ ግብጽ ይመለሳል፥"** በ7:8፣11፣16፣ 8:13 ያለውን እና ይህን ምንባብ ከ11:5 ጋር ቢያነጻጽሩ በመካከላቸው ግጭት የሚመስል ነገር ይመለከታሉ፡፡ ግብፅ የባርነት ምልክት ልትሆን ትችላለች (ማለትም፤በአሦሪያ ውስጥ ግዞት)፡፡ሆኖም ግን የተወሰኑ ምሑራን ይህን የፖለቲካ ህብረት አድርገው ያዩታል፡፡ ሆሼ፣ የመጨረሻው የእስራኤል ንጉስ በአሦሪያ ላይ የግብፅን እርዳታ ጠይቆ ነበር፡፡

▣ **"በአሦርም"**ይህ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ722 ውስጥ ከሰማሪያ መውደቅ ጋር ተያይዞ በሰሜኑ አስር ነገዶች ላይ የደረሰውን ምርኮ የሚያመለክት ነው (ዝ.ከ. 8:9-10)፡፡

▣ **"ርኩስን ነገር ይበላሉ"** ምርኮ ልማዳዊ አምልኮአቸው እንዲቆም ያደርጋል፡፡ የአይሁድ ቤተ መቅደስ መቋቋሙ ባህሎቻቸው ተጠብቆ እንዲቆይ ያደርጋል ፤ ነገር ግን አብዛኞቹን የዘለዋዊያን ትዕዛዞች በስራ ላይ ባለ ቤተ መቅደስ ካልሆነ በስተቀር አንዳቸወውንም ለመተግበር አስቸጋሪ ነው (ዝ.ከ. ኩቁ 4-5)፡፡ሕዝቅኤል 4:13 እንደሚያመለክተው በባዕድ አገር ላይ የተበላ እንጀራ ንጹህ አይደለም!

**9:4 "ለእግዚአብሔርም የወይን ጠጅን ቁርባን አያፈስሱም፥"** የፈላ ወይን የመስዋዕት ስርዓት አንዱ አካል ስለሆነ እንደ ተበላሽ ወይን እንደማይቆጠር መታወስ አለበት (ዝ.ከ. ዘጸ 29:40፤ ዘኁ 15:1-10፤ መዝ 104:14-15)፡፡ ኩቁ 3-4 ያሉት መስዋዕቶች ንጹህ ያልሆኑበት ምክንያት በባዕድ መሬት ላይ ስላሉ ነው፡፡ በአሞፅ 6:6 መጽሐፍ ቅዱስ በአልኮል (የተብላላ) እና በአልኮል ጠጪነት (መጥፎ ልማዱ እና አለአግባብ መጠቀም) ላይ ያለው አመለካከት የሚለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

▣ **"የሐዘንም እንጀራ"** ይህ (BDB 536 CONSTRUCT 19) የመሻገት ዘይቤ ነው፡፡ ከሞት ጋር ተያይዞ ስለቀረበ የተበከለ ነገር ነበር፡፡ ባብዛኛው ድሆች የሚመገቡት ከትንሽ ነገር የሚሰራ ምግብ ነበር፡፡ በተጨማሪም የሚሰራው እና የሚበላው በአሦሪያ ውስጥ ስለነበር ንጽሁ አይደልም፡፡

**9:5 "በዓመት በዓል ቀንና በእግዚአብሔር በዓል ቀን ምን ታደርጋላችሁ?"** ይህ እነሱን ወደ እውነታው ለመመለስ የተጠየቀ ጥያቄ ነበር፡፡ አምልኮዋቸው ባጠቃላይ ሊቋረጥ እና ሕዝባቸውም ሊባረር ነበር!

**9:6 "ግብጽም ትሰበስባቸዋለች፥ ሜምፎስም ትቀብራቸዋለች"** ሜምፎስ (BDB 592) የታችኛው ግብፅ ዋና ከተማ እና ከስነ ምድር ጥናት ግኝት እንደተማርው ቀብር ይካሄድበት የነበረ በጣም ትልቅ ቦታ ነበር (ግስ BDB 868፣ KB 1064፣ ፒል IMPERFECT)፡፡ ትርጉሙ (1) ከምርኮ የተረፉት በብዛት በግዞት እና በባርነት ይሞታሉ (ማለትም፤ እንደ ግብፁ) ወይም (2) ወደ ግብፅ የሸሹት ተራፊዎች እዚያው ግብፅ ውስጥ ይሞታሉ!

▣ **"ሳማም የብራቸውን ጌጥ ይወርሳል"** "የብራቸውን ጌጥ" ስለሚለው ሃረግ ሁለት ዋና ሃሳቦች አሉ ፤ (1) ጣዖታትን እና በዚሁ ምክንያት ደግሞ ቅዱስ ቦታዎችን በአግባቡ አለመጠቀም (2) ቅጥ ባጣ ወጪ የተሰሩ ቤቶቻቸውን እና እጅግ ሐብታም የሆነው ህብረተሰብ መጥፋትን ያመለክታል (ዝ.ከ. 8:14) ወይም (3) በቁ 2 እና በ ኢሳ 7:23 ምክንያት የወይን ማሳዎቻቸውን የሚገልጽ ዘይቤ ሊሆን ይችላል፡፡

▣ **"እሾህም በድንኳኖቻቸው ውስጥ ይበቅላል"** ይህ ለባዶ ቤታቸው ዘይቤያዊ አገላለጽ ወይም ደግሞ ለማምለኪያ ቦታዎቻቸው ሌላ ማጣቀሻ ሊሆን ይችላል (ዝ.ከ. 10:8)፡፡

## ሆሴዕ: 9:7-9

**7 የበቀል ወራት መጥቶአል፥ የፍዳም ወራት ደርሶአል፥ እስራኤልም ያውቃል**
**ከኃጢአትህና ከጠላትነትህ ብዛት የተነሣ ነቢዩ ሰንፎአል፥ መንፈስም ያለበት ሰው አብዶአል።**
**8 ኤፍሬም ከአምላኬ ጋር ተመልካች ነበረ አሁን ግን ነቢዩ በመንገዱ**
**ሁሉ ላይ የወፍ ወጥመድ ሆነ፥ በአምላኩም ቤት ጠላትነት አለ።**
**9 በጊብዓ ዘመን እንደ ነበረ እጅግ ረከሱ እርሱም በደላቸውን ያስባል፥ ኃጢአታቸውንም ይበቀላል።**

**9:7 "የፍዳም ወራት"** ይህ "ጉብኝት" (BDB 824 CONSTRUCT 398) ማለት ነው፡፡ ይህ ገለልተኛ ቃል ነው፤ ነገር ግን በዚህ ዓውድ መሰረተት (ከ ጽሑፍ 2 ያለው ዝምድና) ለፍርድ አላማ የሚደረግ ጉብኝት የሚል ትርጉም ሲኖረው ፍርዱም ደግሞ አሁን ነው (ማለትም ፤ "መጥቷል" ተደግሟል)፡፡

▣ **"የበቀል ወራት መጥቶአል፥"** ነብያቶች እውነትን ለማስተጋባት የፍርድ ቤት ዘይቤን ይጠቀማሉ፡፡ ይህ ህጋዊ ውሳኔን ያመለክታል (BDB 1024 CONSTRUCT 398)፡፡ ጥፋተኛ ወይም ጥፋተኛ አለመሆን ማለት ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ዓውድ ምክንያት ስንሄድ የእግዚአብሔርን የማይቀር ፍርድ ያመለክታል

▣ **"እስራኤልም ያውቃል"** ይህ ግስ (BDB 393፣ KB 390፣ *Qal* IMPERFECT) በ JUSSIVE (ትዕዛዝ) ስሜት ቀርቧል፡፡ በ 8፡2 ውስጥ እስራኤል አውቃለሁ ብላለች፤ ነገር ግን በግልጽ እንደሚታየው እግዚአብሔርን ወይም ነብያቶቹን አያውቋቸውም ነበር!

▣ **"ነቢዩ ሰንፎአል፥ መንፈስም ያለበት ሰው አብዶአል"** እንዚህን ትይዩ ሁለት ግጥማዊ ጽሑፎች ለመተርጎም አስቸጋሪ ነው፡፡ ይህ ሕዝቡ ለሆሴዕ መልዕክት (በኤር 29:36 ውስጥ የተጠቀሰው ተመሳሳይ ቃል) የሰጠው ምላሽ ይመስላል፡፡ ሆሴዕን ከቀደምት አስደሳች የነብያት ቡድኖች (ዝ.ከ. 1ኛሳሙ 10:6ረረ) ጋር ለማያያዝ እየሞከሩ እንደ ነበር እና በዚሁ ምክንያት ደግሞ በመልዕክቱ ላይ እየተሳለቁ እንደሆነ የሚገልጽ ይመስላል፡፡ በኃጥያታቸው ጥልቀት ምክንያት የእግዚአብሔር ቃል እንግዳ ሆኖባቸው ነበር (ዝ.ከ. 8:12)፡፡
ዳቪድ ኤ ሁባርድ ፤ ሆሴዕ (ቲንዳል ብሉይ ኪዳን ሃተታዎች) ገፅ 159 ላይ ስለ "መንፈሱ የተነቃቃ ሰው" ማለትም ስለ "መንፈስ ያለበት ሰው" ማራኪ ሃተታ አስቀምጧል፡፡ ሆሴዕ "መንፈስ" የሚለውን በአሉታዊ መልክ ስለገለጸው እሱም ይህን በአሉታዊ ስሜት እንደቀረበ ይናገራል (ዝ.ከ. 4:12፣19፤ 5:4)፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB | "ከኃጢአትህ ብዛት የተነሣ" |
| NKJV | "ከኃጥያትህ ብዛት የተነሳ" |
| NRSV | "በብዙ ኃጥያትህ ምክንያት" |
| TEV | "ኃጥያትህ በጣም ብዙ ነው" |
| NJB | "በደልህ የበዛ ነው" |

የመጨረሻዎቹ ሁለት የ ቁ 7 ግጥማዊ ጽሑፎች መጪውን የእስራኤል ምርኮ ምክንያቶች ማጠቃለያ የሚሰጡ ናቸው፡፡እግዚአብሔርን ወይም የእግዚአብሔርን ህግ አያውቁም!
"ብዛት" (BDB 913) ማለት "ብዙ ሰው" ወይም "መትረፍረፍ" ማለት ነው፡፡ በ8፡12 ወስጥ የእግዚአብሔርን ህግጋት ለመግለጽ ተጠቅሷል ፤ ነገር ግን እዚህ ላይ የእስራኤልን የኃጥያት ብዛት ለመግለጽ የተቀመጠ ነው፡፡

▣

| | |
|---|---|
| NASB | "ከጠላትነትህ ብዛት የተነሳ" |
| NKJV | "እና ብዙ ጠላትነትህ" |
| NRSV | "ጠላትነትህ ብዙ ነው" |
| TEV | "እናንተ ሕዝቦች ኃጥያታችሁ ብዙ ስለሆነ እኔን ጠላችሁ" |
| NJB | "ከኃጥያታችሁ ሁሉ አልፎ ጠላትነታችሁም በዛ" |

"ጠላት"(BDB 966) የሚለው ስም በእግዚአብሔር እና ለእግዚአብሔር አገልጋዮች የነበረውን ጠላትነት እና ቂመኝነትን ይገልጻል፡፡ ቃሉ የተገለጸው በሆሴዕ 9፡7 እና 8 ውስጥ ብቻ ነው፡፡

**9:8**

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"ኤፍሬም ከአምላኬ ጋር ተመልካች ነበረ አሁን ግን ነቢዩ"** |
| **NKJV፣ NJB** | **"የአፍሬም ተመልካች ከአምላኬ ጋር ነው"** |
| **NRSV** | **"ነብዩ በኤፍሬም በኩል ከአምላኬ ጋር ተመልካች ነበር"** |
| **TEV** | **"እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዳስጠነቅቅ ነብይ አድርጎ ልኮኛል"** |

የእብራዊያኑ ቃሉ በጣም አሻሚ ነው፡፡ ሦስት ሃሳቦች አሉ፤ (1) ኤፍሬም የእግዚአብሔር ተወካይ (ዝ.ከ. ዘጽ 19:5-6) እንዲሆን ነበር የታሰበው ፤ (2) ኤፍሬም የእግዚአብሔርን ነብይ እያሰቃየ ነበር፤ ወይም (3) አፍሬም ሐሰተኛ ነብያትን እየተከተለ እንደነበር የሚያሳዩ አማራጭ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ሆሴዕ አራሱን እንዴት አንደሚያይ ሲገልጽ ነብይ ፣ ተመልካች ፣ እውነተኛ እና ታዛዥ የቃል ኪዳን ሰው እያለ ነው፡፡

▣ **"በመንገዱ ሁሉ ላይ የወፍ ወጥመድ ሆነ"** ቀጣዮቹ ሁለት ግጥማዊ ጽሑፎች እስራኤል መልከተኞቹን እያጠቃች የእግዚአብሔርን መልክት እየተቃወመች እንደሆነ የሚገልጹ ይመስላል፡፡
የእግዚአብሔር መልዕክት የሚያስፈልጋቸው እና በደስታ መቀበል የነበረባቸው የእግዚአብሔር ሕዝቦች በተቃራኒ ጥላቻ ተሞልተዋል!

▣ **"በአምላኩም ቤት ጠላትነት አለ"** ይህ የተወሰኑ የያህዌ የሆነ የማምለኪያ ቦታን (ማለትም፤ ቤቴል እና ዳን) ሊያመለክት ይችላል፤ ሆኖም ግን አጠቃላይ መሬቱም ሊሆን ይችላል (ዝ.ከ. 8:1፤ 9:4፣15)፡፡

**9:9**

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"እጅግ ረከሱ"** |
| **NKJV** | **"ራሳቸውን እጅግ ያረከሱ ናቸው"** |
| **NRSV** | **"ራሳቸውን እጅግ አርክሰዋል"** |
| **TEV** | **"ተስፋ የሌለው መጥፎዎች ናቸው"** |
| **NJB** | **"ረሳቸውን እጅግ ያረከሱ ሆነዋል"** |

የዚህ ግጥማዊ ጽሑፍ ሁለቱ ግሶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. እጅግ - BDB 770፣ KB 847፣ ሂፊል PERFECT
2. ረከሱ ፣ ተበላሹ - BDB 1007፣ KB 1469፣ ፒል PERFECT

ሁለተኛው ግስ ዋናው ሃሳብ እንዲሁም የመጀመሪያው ግስ ደግሞ ተውሳከ ግስ ሆነው እንደ አንድ ግስ ያገለግላሉ፡፡
ይህ መበላሻት የሚለው ቃል በሚከተሉት ቦታዎች ላይ ያመልኩ የነበሩትን ሰዎች መንፈሳዊ ሁኔታ ለመግለጽ ያገለግላል፡፡

(1) በ ዘጸ 32:7፣ ዘዳ 9:12፣ 32:5 ውስጥ አሮን ባሰራው ወርቃማ ጥጃ
(2) በኢዮርብኣም 1ኛ የወርቅ ጥጆች ያሉ እስራኤላዊያን ሆሴዕ 9:9
(3) በ ኢሳ 1:4፣ ኤር 6:28፣ ሕዝ 20:44፣ 23:11፣ ሰፎ 3:7 ውስጥ ያለው ይሁዳ
(4) በ መዝ 14:1፣ 53:1 ውስጥ ያሉት አጠቃላይ የሰው ዘር

▣ **"በጊብዓ ዘመን"** ከቀ 9 ጀምሮ እስከ ምዕራፍ 10 ላሉት ታሪካዊ ዝርዝር ፍንጮች አሉ፡፡ እንዚህ ከሚታወቁ ከተሞች እና በነሱ ውስጥ ከተገኙት ጣዖት አምልኮ ጋር የሚያያዙ ናቸው፡፡ጊቢዓ በ 10፡9 ውስጥ ተገልጧል፡፡ ለዚህም ብዙ አማራጮች አሉ (1) ይህ የሳኦል ቤት ነበር ፣ (2) ይህ ሳኦል መጀመሪያ ኃጥያት የሰራበት ቦታ (ዝ.ከ. 1ኛሳሙ 13:8-14) ፣ (3) ይህ መሳፍንት 19-20 ውስጥ ያሉትን ክስተቶች ያመለክታል ወይም (4) በዘመናዊ ተርጓሚዎች ትክክለኛው ታሪካዊ ማጣቀሻ የተረጋገጠ አይደለም፡፡

▣ **"እርሱም በደላቸውን ያስባል"** እግዚአብሔር "ሲያስብ" ሲል ፍርድን ያመለክታል፡፡ ሰው እግዚአብሔርን መጥራት ረስቷል! እግዚአብሔር ሰው ቃል ኪዳኑን እንዲያብ ይጠራል (ዝ.ከ. 7:2፣ 8:13፣ 13:12)፡፡

## ሆሴዕ: 9:10-14

**10 እስራኤልን በምድረ በዳ እንዳለ ወይን ሆኖ አገኘሁት አባቶቻችሁንም ከመጀመሪያዋ ዓመት እንደ በለስ በኵራት ሆነው አየኋቸው እነርሱ ግን ወደ ብዔልፌጎር መጡ፥ ለነውርም ተለዩ፥ እንደ ወደዱትም ርኩስ ሆኑ፥ 11 የኤፍሬምም ክብር እንደ ወፍ በርሮ ይጠፋል መውለድና መፅነስ ማርገዝም አይሆንላቸውም። 12 ልጆቻቸውንም ቢያሳድጉ ሰው እንዳይቀርላቸው ልጅ አልባ አደረጋቸዋለሁ ከእነርሱም በራቅሁ ጊዜ ወዮላቸው! 13 እኔ እንዳየሁ የኤፍሬም ልጆች ለምርኮ ተሰጥተዋል ኤፍሬምም ልጆቹን ወደ ገዳዩች ያወጣል። 14 አቤቱ፥ ስጣቸው ምን ትሰጣቸዋለህ? የሚጨነግፍን ማኅፀን የደረቀውንም ጡት ስጣቸው።**

**9:10 "እስራኤልን በምድረ በዳ እንዳለ ወይን ሆኖ አገኘሁት እንደ በለስ በኵራት ሆነው"** ያህዌ በአብርሃም ተወላጆች ላይ ፍሬያማነትን እና አቅምን አይቷል፡፡ ይህ የምድረበዳው መንከራተት ጊዜ እግዚአብሐር ከአይሁዳዊያን ጋር ያደረገው የትዳር ስምምነት እና የጫጉላ ጊዜ ነው ለሚለው ሃሳባዊ ትንታኔ ሌላ ምሳሌ ነው (ዝ.ከ. 2:14-19፣ ዘዳ 32:10)፡፡ ይህ እግዚአብሐር ከአብርሃም ወይም ከፓትሪያርኮች ጋር ሳይሆን ከዘጸዓት (ከሙሴ) ጀምሮ እስራኤልን መምረጡን የሚያስረዳ ትንታኔ ነው፡፡

▣ **"ብዔልፌጎር"** ይህ እስራኤል በርቢአምልኮ ውስጥ ከሞዓባዊት ሴት ጋር አመንዝራ ያደረገችበት በሞአብ መሬት (BDB 128) ላይ የሚገኝ ሰጢም የሚባል ቦታን ያመለክታል፡፡ ይህ የሞአቡ ንጉስ እስራኤልን እንዴት ማሸነፍ እንዳለበት ባላም (Balaam's) የመከረው ምክር ነው (ዝ.ከ. ዘኀ 25:1-9)፡፡ ይህ ምናልባትም በ 5፡2 ውስጥ የተጠቀሰ ሲሆን ተመሳሳዩ ቃል በቁ 9ሀ ውስጥ ተጠቅሷል፡፡ ይህ ቦታ የአመጽ እና የጣዖት አምልኮ መታወቂያ ቦታ ሆኖ ነበር (ለምሳሌ፤ ዘዳ 4:3-4፣ ኢያሱ 22:17፣ መዝ 106:28፣ እና እዚህ)፡፡

▣ **"ለነውርም ተለዩ"** ይህ ግስ (BDB 634፣ KB 684፣ ኒፋል IMPERFECT) "መሓላ" ወይም "ቃል መግባት" ማለት ነው፡፡ እስራኤል በሲና (Sinai) (ዝ.ከ. ዘጸ 19-20) ለእግዚአብሔር እንዳደረገችው መለየት ሁሉ በሰጢም ላይ ለባዖል ለመለየትም ጊዜ አልፈጀባትም ነበር፡፡
"ነውር" ጣዖት አምልኮን የሚወክል የተለመደ ቃል ነው (BDB 103)፡፡ ነብያት ቃሉን እንደ ባዖል ሌላ ስም አድርገው ይጠቀሙበት ነበር፡፡እስራኤል ለያህዌ መለየት አቁማ (ዝ.ከ. ዘጸ 19-20) ባዖልን ተከትላ ነበር! የጫጉላው ጊዜ አብቅቷል! ቃሉ እንደገና ጣዖት አምልኮን ከሚያመለክተው "ርኩሰት" (BDB 1055) ጋር ትይዩ ነው (ዝ.ከ. ዘዳ 29:17፣ 2ኛነገ 23:13፣24፣ኢሳ 66:3፣ ኤር 4:1፣ 7:30፣ 32:34፣ ሕዝ 5:11፣ 7:20፣ 11:18፣21፣ 20:7፣8፣30፣ 32:23)፡፡

**9:11 "የኤፍሬምም"** ይህ ስም "ፍሬያማ" ማለት ነው፡፡ የሰሜኑ አስር ነገዶች በእስራኤል ውስጥ ትልቁ ነገድ ስለነበሩ ይህን ስም ይጠቀሙ ነበር፡፡ "ፍሬያማ" የነበረው ፍሬ አልባ ይሆናል! ቃል ኪዳኑን ባለመጠበቅ የተነሳ የእግዚአብሔር በረከት ቀርቷል (ዝ.ከ. ዘዳ 27-29)፡፡

▣ **"ክብር እንደ ወፍ በርሮ ይጠፋል"** ክብራቸው ከያህዌ ጋር የነበራቸውን የቃል ኪዳን ዝምድና ያመለክታል (ዝ.ከ. ዘጸ 19:5-6፣ አሞፅ 3:2)፡፡ ሆሴዕ ርግብን በተለያ ስሜት ይጠቀምበታል፡፡

1. እስራኤል ሰነፍ ርግብ ትመስላለች (የፖለቲካ ዝምድና) - 7:11
2. እስራኤል የሚንቀጠቀጥ ርግብ ትመስላለች(ደንጋጭ ተመላሾች) - 11:11
3. የፍርድ ጥንብ አንሳ/ንስር - 8:1
4. የወፍ መንጋ (ፍርድ) - 5:1፣ 7:12
5. የጠፋ ወፍ - 9:11

▣ ***"መውለድና መፅነስ ማርገዝም አይሆንላቸውም"*** በምጸት ሲገለጽ ፤ባዖል የመራባት ምንጭ ነው ብለው ያስቡ ነበር ፤ ነገር ግን እውነታው መራባት የመጣው ከያህዌ ነበር፤ ስለዚህ ሁሉም መራባት እግዚአብሔር የሚያቆመው ይሆናል (ዝ.ከ. vቁ 14 16)፡፡

**9:12 "ከእነርሱም በራቅሁ ጊዜ ወዮላቸው"** እግዚአብሔር በሕዝቄል 10፡18ረረ ላይ ይሁዳን እንደተወው ሁሉ እነሱንም የሚተዋቸው ይሆናል፡፡ በጣም አስፈሪ ፤ ታላቅ ፍርድ ነው (ዝ.ከ. 4:17፣ እና ሮሜ 1:23፣26፣28)፡፡ ይህ በነብያቶች የተገለጸ ሌላ የዘይቤ እና የግጥም ምት ባህሪ ያለው የቀብር ለቅሶ(ዋይታ) ምሳሌ ነው፡፡

**9:13 "ለምርኮ ተሰጥተዋል"** ይህን ምንባብ በተመለከተ ብዙ ሃሳቦች አሉ (ሁባርድ ፤ ሆሴዕ ገፅ 166 ላይ ይመልከቱ)፤ (1) የጢሮስ ርቢ ጣዖት ማጣቀሻ ነው (ዝ.ከ. ሕዝ 27:28)፣ (2) ጢሮስ የባዖል አምልኮ ምንጭ መሆኑ ተመልክቷል (ዝ.ከ. 1ኛነገ 18:31)፣ ወይም (3) ኤፍሬም ልክ እንደ ጢሮስ በምድር ላይ ተሰራጭቷል፡፡

▣ ***"ኤፍሬምም ልጆቹን ወደ ገዳዩች ያወጣል"*** ይህ (1) ለሞሎክ የሚደረግ የልጆች መስዋዕት (ዝ.ከ. ዘሌ 18:21፣ 20:2-5፣ 2ኛነገ 23:10፣ ኤር 32:35) ወይም (2) ለባዖል የሚደረግ የሐሰት እምነት ውጤቱ በሰው ዘር ርቢ ላይ የያህዌ ፍርድ ይሆናል (ዝ.ከ. ቁ 11፣12፣14፣16) የሚሉትን የሚያመለክት ይመስላል፡፡

**9:14** "ማውጣት" (BDB 678፣ KB 733) የሚለው ግስ በዚህ ቁጥር ውስጥ በአሽሙራዊ መልኩ ሦስት ጊዜ ተጠቅሷል፡፡
*Qal*IMPERFECT - ሰጣቸው!
*Qal*IMPERFECT- ምን ትሰጣቸዋለህ?
*Qal*IMPERFECT - ሰጣቸው !
ይህ ነብዩ ሆሴዕ እስራኤል የሚገባትን እንዲሰጣት ወደ ያህዌ እየጸለየ ይመስላል (ማለትም፤ ርቢ አይኖርም ፤
ቅጣቱ ከኃጥያቱ ጋር የሚሄድ ነው፣ የርቢ ጣዖት አምልኮ)፡፡
ኒዶት ፤ ጥራዝ 4፣ ገፅ 47 ላይ ይህን ጽሑፍ በተመለከተ ማራኪ አስተያየት አለው፡፡፤ ጸሓፊው ሮበርት ቢ ቺሾልም ከያዕቆብ ወደ ዮሴፍ የሄደው በረከት ላይ ርቢን ወክሎ የነበረው "ጡት እና ጽንስ" የሚለው ሃረግ እዚህ ውስጥ የርቢ ጣኦታትን ለምትፈልገው እስራኤል ቅጣት ይሆን ዘንድ አለመራባት እንዲሆን ታስቦበት እንደቀረበ ይናገራል!

## ሆሴዕ: 9:15-17

**[15] ክፋታቸው ሁሉ በጌልገላ አለ በዚያ ጠልቻቸዋለሁ ስለ ሥራት ክፋት ከቤቴ አሳድዳቸዋለሁ**
**ከእንግዲህ ወዲያ አልወድዳቸውም አለቆቻቸው ሁሉ ዓመፀኞች ናቸው።**
**[16] ኤፍሬም ተመታ፥ ሥሩም ደረቀ፥ ፍሬም አያፈራም ደግሞም ቢወልዱ የማኅፀናቸውን ፍሬ እገድላለሁ።**
**[17] አልሰሙትምና አምላኬ ይጥላቸዋል በአሕዛብም መካከል ተቅበዝባዦች ይሆናሉ።**

**9:15 "ክፋታቸው ሁሉ በጌልገላ አለ"** ጌልገላ "የድንጋዮች ክብ" ማለት ነው፡፡ ይህ (1) ከጆርዳን ወንዝ በተወሰዱ ድንጋዮች ለእያሱ መታወሻ የተሰራበት ቦታ፣ (2) እንዲሁም ሳኦል የተቀባበት ቦታ (ዝ.ከ. 1ኛ ሳሙ 11:14-15) ፤ ሆሴዕ ንጉሳዊ አገዛዝን እያወገዘ ይመስላል (ዝ.ከ. 7:3-7፣ 8:4፣ 10፣ 13፣ 13:9-11)፣ (3) ሳኦል ኃጥያት የሰራበት ቦታ (ዝ.ከ. 1ኛሳሙ 13:1-14)፣ እና (4) በሰሜን የርቢ አማልክት አምልኮ ይደረግበት የነበረበትን ቦታ ሊያመለክት ይችላል፡፡

▣ ***"በዚያ ጠልቻቸዋለሁ"*** *ይህ* (*"መጥላት"* BDB 971፣ KB 1338፣ *Qal* PERFECT) *ያህዌ ለኃጥያት የሰጠውን ምላሽ የሚገልጽ ጠንካራ ቋንቋ ነው* (ለምሳሌ፤ ዘዳ 12:31፣ ኢሳ 63:3-6፣ ኤር 12:8፣ አሞፅ 5:21፣ 6:8)።

▣ **"ከቤቴ አሳድዳቸዋለሁ ከእንግዲህ ወዲያ አልወድዳቸውም"** በጣም አሳዛኝ ፍርድ! ቃል ኪዳኑ ተሰብሯል። እስራኤል ባለመታመኗ እግዚአብሔር ጋብቻውን አፍርሷል። ከእግዚአብሔር ቤት ተባረረች (ማለትም፤ከተስፋይቷ ምድር)።
ይህ "ከእንግዲህ ወዲያ አልወድዳቸውም" የሚለው የመጨረሻ ሃረግ የሚከተኩት ሁለት ሃረጎች ህብር ነው።

1. "እንደገና አለመስራት" ወይም "የበለጠ ማድረግ" (BDB 414፣ KB 418፣ በቅርጽ *ሂፊል* JUSSIVE)
2. *"መውድ"*(BDB 12፣KB 17፣*Qal መጨረሻ የሌለው* CONSTRUCT)

ያህዌ ከእስራኤል ጋር ያለውን ጉዳይ ጨርሷል!

▣ ***"አለቆቻቸው ሁሉ ዓመፀኞች ናቸው"*** *መሪዎቻቸው የእግዚአብሔር ተወካዮች እንዲሆኑ ነበር የታሰበው ነገር ግን እነሱ አመጸኞች ነበሩ።*

**9:17 "አምላኬ ይጥላቸዋል**" *ሆሴዕ ያህዌን "አምላኬ" እያለ እየጠራ እንደሆነ አስተውል ፤ ይህም* እግዚአብሔር ከዚህ በኋላ የእስራኤል የቃል ኪዳን አምላክ እንዳልሆነ አመላካች ነው (ዝ.ከ. ዘዳ 31:16-18)። የግሱ (BDB 549፣ KB 540፣ *Qal* IMPERFECT) ትርጉም *"መጣል"* ፣ *"መናቅ"* ወይም *"ማጥፋት"* ሊሆን ይችላል። በሆሴዕ ውስጥ በ4:6 (ሁለቴ) እና እዚህ ላይ ተጠቅሷል። የእግዚአብሔርን ሕግ "ጥለዋል" (ዝ.ከ. 8:12፣ ኢሳ 5:24፣ 30:9፣12፣ ኤር 6:19፣ 8:9፣ሕዝ 5:6፣ 20:16፣ አሞፅ 2:4)፤ እሱም ጥሏቸዋል (ዝ.ከ. ኤር 33:24)።

▣ **"አልሰሙትምና"** ስደቱን *ያመጣው የአሦራዊያን እና የባቢሎናዊያን ጥንካሬ ሳይሆን የእስራኤል ኃጥያት ነበር። የሜሶፖታሚያ ጣዖታት* ከያህዌ የበለጡ ብርቱዎች አይደሉም።ይህዌ ሕዝቡን ለመዳኘት ተጠቀመባቸው (ለምሳሌ፤ ኢሳ 10:5፣ 44:28-45:7)።

▣ **"በአሕዛብም መካከል ተቅበዝባዦች ይሆናሉ"** *ይህ* በዘዳግም 27-29 ያለው የቃል ኪዳኑ እርግማኖች የተፈጸመበት ነው (ዝ.ከ. ዘዳ 28:58-68)!

# ሆሴዕ 10
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|
| የእስራኤል ኃጢአት እና ምርኮ | ቀዋሚ ስለሁነው የእስራኤል አመፃ ምክንያት የተነሳ የእግዚአብሔር ፍርድ በእስራኤል ላይ ነው (4:1-14፡9) | ነብዩ ስለ እስራኤል ይናገራል (9:17-10:2) | የእስራኤል የአምልኮ ቁቁሶች መወገድ |
| 10:1-2 | 10:1-2 | | 10:1-10 |
| 10:3-8 | 10:3-10 | 10:3-4 | |
| | | 10:5-8 | |
| | | ጌታ በእስራኤል ላይ ፍርድን አወጀ | |
| 10:9-11 | | 10:9-10 | እስራኤል የያህዌን ተስፋ ቅር ተሰኘች |
| | | 10:11-13ሀ | 10:11-15 |
| | 10:11-12 | | |
| 10:12-15 | | 10:13-15 | |
| | 10:13-15 | | |

### የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ vii ተመልከት)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**ሆሴዕ: 10:1-2**

**1እስራኤል ፍሬው የበዛለት የለመለመ ወይን ነው እንደ ፍሬው ብዛት መሠዊያውን አብዝቶአል እንደ ምድሩም ማማር መጠን ሐውልቶችን እያሳመሩ ሠርተዋል።**
**2 ልባቸው ተከፈለ አሁንም በደላቸውን ይሸከማሉ እርሱ መሠዊያቸውን ያፈርሳል፥ ሐውልቶቻቸውን ያጠፋል።**

**10:1**

| | |
|---|---|
| NASB፣ NRSV፣ | |
| NJB | "እስራኤል ፍሬው የበዛለት የለመለመ ወይን ነው" |
| NKJV | "እስራኤል ወይኑን ባዶ ያደርጋል" |
| TEV | "የእስራኤል ሕዝብ በፍሬው የበዛለት ወይን ይመስል ነበር" |

"የለመለመ" (BDB 132 I፣ *Qal* ACTIVE PARTICIPLE) እዚህ ውስጥ ብቻ ይገኛል፡፡ ሰፕቱአጀንቱ መጽሐፍ ቅዱስ " ቅርንጫፉ የሚያስደስት ወይን" የሚል አለው፡፡ ይህ የ 9:10 (መዝ 80:8-13) ማሳያ ይመስላል፡፡ እግዝአብሄር እስራኤልን ፍሬያማ አድርጓታል(ይህ ከ *bqq ትርጉሞች ለንዱ ሊሆን ይችላል*)፡፡ ይሁን እንጂ፣ያህዌ በባረካቸው መጠን እነርሱም ደግሞ በአልን ይከተላሉ(11:1)፡፡ እንዴት የሚገርም ነው! ወይን ብዙ ጊዜ

የእስራኤል ምሳሌ ነው(ለምሳሌ፣ ዘዳግ 32:32፤ መዝ 80:8-19፤ እሳ 5:1-7፤ ኤርም 2:21፤ ሕዝቂ 15:1-8)፡፡ ግሱን "ባዶ" በሚል መውሰድ ይቻላል፡፡ (BDB 132 I) እናም እስራኤል እግዝአብሄር የሚፈልገውን እንደማታፈራ ወይን ናት (9:10-17)፡፡

▣ **"ፍሬው የበዛለት ነው"** ቀሪው የዚህ ቁጥር ክፍል የ8:11 ማሳያ ነው(BDB 915) ወይም የ12:11 (ኤርም 2:28፤ 11:13)፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"ሐውልቶችን እያሳመሩ ሠርተዋል"** |
| **NKJV** | **"የተቀደሱ ሐውልቶቹን ያወድሳል"** |
| **NRSV** | **"ሐውልቶቹን አሻሻለ"** |
| **TEV** | **"የሚያመልኩትን ሐውልቶች አሳምረው ሰሩ"** |
| **NJB** | **"የተሻለ የተቀደሰ ሐውልቶችን ሠራ"** |
| **NET Bible** | **"ፍሬያማ ሐውልቶችን አሸበረቁ"** |

ብልጽጋና ልባቸውን ወደ እግዝአብሄር አልመለሰም(ታስቦ እንደ ነበር፣ ዘዳግ 27-29)፤ዳሩ ግን አምልኮአቸውን እና ምስጋናቸውን ለበአል ጨመሩ፡፡ የአምልኮ ቦታውን በማስተካካል የያህዌን ቤተ-መቅደስ ናቁ!

**10:2 "ልብ"** እብራይስጡ አመላካከት የፋቃድ እና የአህምሮ ማዕከል የሆነው ልብ ነው እንጂ ስሜት አይደለም፡፡

**ልዩ ርዕስ፡- ልብ 197**

"ካርዲያ"*Kardia* የሚለው የግሪኩ ቃል leb ልብ የሚለው የእብራይስጡን ቃል (BDB 523) ለማንጸባረቅ በሰብትዋጅንት እና በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተጠቅሷል፡፡ ይህ ቃል በተለያዩ መንገዶች ጥቅም ላይ ውሏል (Bauer፣ Arndt፣ Gingrich and Danker፣ A Greek-English Lexicon፣ ገፅ 403-404)::

1. የተፈጥሮአዊ ሕይወት ማእከል፤ ለሰው የሚደረግ ተለዋዋጭ ዘይቤ (የሐዋ.14:17፤ 2ኛ ቆሮ.3:2-3፤ ያዕ. 5:5)
2. የመንፈሳዊ ሕይወት ማዕከል (ማለትም ሞራላዊ)
   ሀ. እግዚአብሔር ልብን ያውቃል (ሉቃ.16:15፤ሮሜ 8:27፤ 1ኛ ቆሮ. 14:25፤ 1ኛ ተሰሎ.2:4፤ ራዕ.2:23)
   ለ. የሰውን ልጅ መንፈሳዊ ሕይወት የሚያመለክት (ማቴ.15:18-19፤ ሮሜ. 6:17፤ 1ኛ ጢሞ. 1:5፤ 2ኛ ጢሞ. 2:22፤ 1ኛ ጴጥ. 1:22)
3. የአስተሳሰብ ሕይወት ማዕከል (እውቀት ማቴ.13:15፤24:48፤ የሐዋ.7:23፤16:14፤28:27፤ሮሜ.1:21፤10:6፤2ኛ ቆሮ.4:6፤ኤፌ. 1:18፤4:18፤ ያዕ.1:26፤ 2ኛ ጴጥ.1:19፤ራእ.18:7፤ ልብ ከአእምሮ ገር ተመሳሳይ ነው በ2ኛ ቆሮ.3:14-15 እና ፊልጵ 4:7)
4. የፈቃድ ማዕከል (ማለትም ፈቃድ የሐዋ.5:4፤11:23፤1ኛ ቆሮ. 4:5፤5:37፤2ኛ ቆሮ.9:7)፡፡
5. የስሜቶቻችን ማዕከል (ማቴ.5:28፤ የሐዋ. 2:26፡37፤7:54፤21:13፤ሮሜ 1:24፤ 2ኛ ቆሮ. 2:4፤7:3፤ኤፌ.6:22፤ ፊልጵ.1:7)፡፡
6. የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ልዩ ሥፍራ (ሮሜ 5:5፤ 2ኛ ቆሮ. 1:22፤ገላ.4:6/ክርስቶስ በልባችን፡-ኤፌ. 3:17/)
7. ልብ የአንድን ሰው ሁለንተና የሚያመለክት ተለዋዋጭ ዘይቤ ነው (ዘይቤያዊ ቋንቋ) ነው (ማቴ.22:37 ከዘዳ. 6:5 የተወሰደ)፡፡ ሃሳቦች፣ዓላማዎች፣ ድርጊቶች አንድ ላይ ተቀናጅተው የግለሰቡን ማንነት ያሳያሉ፡፡ ብሉይ ኪዳን ጎላ ያለ የቃሉ አጠቃቀም አለው፡፡
   ሀ. ዘፍ. 6:6፤8:21 "እግዚአብሔር በልቡ ተጸጸተ" ሆሴ. 11:8-9ንም አስታውል
   ለ. ዘዳ.4:29፤ 6:5 "በፍጹም ልብህና በፍጹም ነፍስህ"
   ሐ. ዘዳ. 10:16 "ያልተገረዘ ልብ" እና ሮሜ 2:29፡፡
   መ. ሕዝ.12:31-32 "አዲስ ልብ"
   ሠ. ሕዝ 36:26 "አዲስ ልብ" እና "የድንጋይ ልብ"

▣

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"እምነት አልባ"** |
| **NKJV፣ NJB** | **"ተከፈለ"** |
| **NRSV** | **"ወሸት"** |
| **TEV** | **"እታላይ"** |

የእብራይስጡ ቃል(BDB 325 II፣ KB 322፣ *Qal* PERFECT) "የሚሟልጭ፡፡" አስተማማኝ ላልሆነ እርምጃ ምሳሌ ነው፣ስለዚህ፣ የማይታመን በሚል ይተረጎማል(አድሱ የባርከላይ ትርጉም( New Berkeley version) "ልባቸው የሚንሸራተት ነበር")፡፡ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ይህ ግስ ልብ የሚለውን የሚጠቀም እዚህ ብቻ ነው፡፡" ብዙ ጊዜ ምላስን ያመለክታል፡፡ ይህ እምነት አልበኝነት ሊያመለክተው የሚችለው(1) በአል ወይም እግዚአብሔር ወይም ደግሞ (2) በእስራኤል አምላክ መታመን ወይም ደግሞ ከግብጽ/ከአሦር ጋር ያላቸውን የፖለትካ ቡድን፡፡ የእርግጠኝነት አቋም ተቃራኒ ምሳሌ ለብሉይ ኪዳን የእምነት ቃል ምንጭ ነው(BDB 52-54)፡፡

ግሱን "ተከፈለ" (BDB 324) በሚል መውሰድ ይቻላል ማለትም ጽሞናቸው(ማለትም፣ ልብ) በያህዌና በበአል መካከል ተከፍሎ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ ይህ ቃል በብዛት ጥቅም ላይ የዋለው በዜና መዋይል ውስጥ ነው እንጂ ነብያቶች አይደሉም፡፡

▣ **"በደላቸውን ይሸከማሉ"** 4:15፤ 5:15፤ 13:1፣16፤ ሚክያስ 5:10-15 ተመልከት)፡፡

▣ ***"መሠዊያቸውን......ሐውልታቸውን"*** የዚህ አምልኮ ዓላማ ብዙ ጊዜ ከበአል የዝሙት ልምምድ ጋር ይያያዛል (የድንጋይ ሐውልት አቆሙ፣ ማለትም፣ phallic symbol፣ 3:4፤ 1 ነገስ 14:23-24) እናም አሼራ(raised፣ cut stone altar with a place for a carved stake or live tree)፡፡

**ሆሴዕ: 10:3-10**

[3]አሁንም። ንጉሥ የለንም፥ እግዚአብሔርን አልፈራንምና ንጉሥስ ምን ያደርግልናል ይላሉ?"
[4] የማይረባውን ቃል ይናገራሉ ቃል ኪዳን በገቡ ጊዜ በሐሰት ይምላሉ ስለዚህ መርዛም
ሣር በእርሻ ትልም ላይ እንደሚበቅል መቅሠፍት ይበቅልባቸዋል፡፡
[5] የሰማርያ ሰዎች ስለ ቤትአዌን እምቦሳ ይፈራሉ ክብሩም ከእርሱ ዘንድ ወጥቶአልና
ሕዝቡ ያለቅሱለታል፥ የጣዖቱ ካህናትም በሐዘን ይንተባተባሉ፡፡
[6] ለንጉሡ ለኢያሪም እጅ መንሻ ይሆን ዘንድ ወደ አሦር ይማረካል ኤፍሬምን እፍረት ይይዘዋል፥ እስራኤልም በምክሩ ያፍራል፡፡
[7] ሰማርያ ከንጉሥዋ ጋር በውኃ ላይ እንዳለ አረፋ ጠፍታለች፡፡
[8] የእስራኤል ኃጢአት የሆኑት የአዌን የኮረብታው መስገጃዎች ይፈርሳሉ እሾህና አሜከላ
በመሠዊያዎቻቸው ላይ ይበቅላል ተራሮችንም ከደኑን፥ ኮረብቶችንም ውደቁብን ይሉአቸዋል!"
[9] እስራኤል ሆይ፥ ከጊብዓ ዘመን ጀምረህ ኃጢአትን ሠርተሃል በዚያ ጸንተዋል በጊብዓ ላይ ሰልፍ አይደርስባቸውምን?
[10] በፈቀድሁም ጊዜ እገሥጻቸዋለሁ ስለ ሁለቱም ኃጢአታቸው በታሰሩ ጊዜ አሕዛብ ይሰበሰቡባቸዋል፡፡

**10:3 "ንጉስ የለንም"** ይህ ምናልባት 1 ሳሙ 8:4-9 ሊያንፀባርቅ ይችላል፡፡ ብዙ ጊዜ ሆሴዕ ለሰሜኑ ነገስታት ይናገር ነበር(7:3-7፤ 8:4፣ 10፣ 13፤ 13:9-11)፡፡ የመጀመርያው መንግስት(እዮርባም 1) ሊዘልቅ አልቻለም፡፡ በመሪነት ላይ አያሌ ለውጦች ነበሩ(ማለትም፣ነገስታት)፡፡

**10:4 "የማይረባውን ቃል ይናገራሉ ቃል ኪዳን በገቡ ጊዜ በሐሰት ይምላሉ"** This is a COGNATE ACCUSATIVE፣ትርጉም የሌለውን የሰው ልጅን ወሬ እንደሚያወሩ ያሳያል (BDB 150፣ KB 210፣ *Piel* PERFECT) (እሳ 58:13)፡፡ ይህ ለያህዌ ያላቸውን ቃል ኪዳን (ዘፀአ 19-20) ለውጭ ኃይል ካላቸው ቃል ኪዳን ጋር ያነፃፅራል፡፡ የእስራኤል መሀላ አይታመንም፡፡ በሙሉ በግል ፍላጎት ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡
የግጥሙ ሁለተኛ መስመር ሁለት የመጀመርያ የሆነ ፍጹምነት አለው፡፡ የዚህ አወቃቀር ወደ መጀመርያው መስመር ግስ ሳይሆን ወደ ሁለተኛው መስመር ትኩረት ይስባል፡፡

▣ **"መርዛም ሣር በእርሻ ትልም ላይ እንደሚበቅል መቅሠፍት ይበቅልባቸዋል"** ይህ ምናልባት የመሳፍንቶችን ኢ-ፍታዊነትን የሚያሳይ ሊሆን ይችላል(አሞ 2:6፤ 5:12፤ 6:12)፡፡

**10:5 "ሰማርያ"** ሰማርያ፣የተራራ ጫፍ ኮረብታ፣ በሳምር ተገነባ(1 ነገስ 16:24) እናም የእስራኤል ዋና ከተማ ሆነች፡፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ922 በኃላ፣ መንግስቱ በሁለት ስከፈል፣ የደቡቡ አሥር ነገዶች እስራኤል፣ኤፍሬም፣ወይም ሰማርያ በእዮርባም 1 የሚመራ፣ እናም የሰሎሞን ልጅ በሆነው በሬሆብያም የሚመሩ ሁለት ነገዶች ይሁዳ ይባላሉ፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"ይፈራሉ"** |
| **NKJV** | **"ፍርሃት"** |
| **NRSV፣ NJB** | **"ይንቀጠቀጣሉ"** |
| **TEV** | **"ፈሪ ይሆናሉ"** |
| **NET Bible** | **"ያለቅሳሉ"** |

የእብራይስጡ ግስ(BDB 158፣ KB 185፣ *Qal* IMPERFECT) "መደንገጥ" ማለት ነው፡፡ ይህ ግስ " ለየት ያለ ክብርም" ሊሆን ይችላል(ማለትም፣ አምልኮ) ወይም "ፍርሃት" (ማለትም፣ መወሰድ፣ ቁ 5-6)፡፡ ብዙ የመጽሀፍ ቅዱስ አዋቂዎች "መልቀስ" (BDB 626) የሚለውን ተመሳሳይነት መሠረት በማድረግ ለማስተካከል ያስባሉ፡፡

▣ **"ስለ ቤትአዌን እምቦሳ"** ይህ እዮርባም 1 በቤተኤል ያስቆመውን የወርቅ ጥጃ ጣዖትን ያሳያል(4:15፤ 5:8፤ 1ነገስ 16:2829)፡፡ የወርቅ ጥጃዎቹ(ቤትአል እና ዳን) ጣዖታት ማለት አይደለም፣ዳሩ ግን ያህዌን ይወክላሉ (ዘፀአ 32:4-5)፡፡ ቤት-አዌን የሚለው ቃል(BDB 110)፣ የ"መለኮት ቤት፣" በሚለው የተተረጎመ በቤተኤል የሚጠቀሙት ነው("የእግዚአብሔር ቤት")፡፡ ከጣዖታት አምልኮ ጋር በተገናኘ ሁነታ አይሁዶች ስሙን የማበለሻታቸው ምሳሌ ነው( የጣዖት አምላክ ወይም ቦታ)፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **NASB፣ NRSV** | **"የጣዖታት ካህናት"** |
| **NKJV** | **"ካህናቶቹ"** |
| **TEV** | **" ጣዖትን የሚያገለግሉ ካህናት"** |
| **NJB** | **"የጣዖቱ ካህናት"** |

ይህ በዳን እና ቤትኤል ታዋቅ ሥፍራዎች የባአል ካህናት የተባሉትን የሚያመለክት ነው(11ነገስ 23:5፤ ሶፎ 1:4)፡፡
እነዚህ የእብራይስጥ ተነባቢዎች *kmr* አያሌ ትርጉሞች አሉ፡፡

1. መቃጠል(ጥቁር መሆን) BDB I
2. ጥቁር መሆን (from Syriac) BDB II
3. በሆድ መተኛት፣ BDB III
4. ወጥመድ ወይም መረብ

እነዚህ ተነባቢዎች በከናዓን እና አካዲያን ውስጥ ለሚገኙት ካህናት የተለመደ ቃላት ነው፡፡ እነዚህ የደቡቡ ካህናት በሆሴዕ እንደ እንግዶች ካህናት ይታዩ ነበር!

▣

| | |
|---|---|
| NASB | **"በርሱ ላይ ያለቅሳሉ"** |
| NKJV | **"ይጮሁለታል"** |
| NRSV | **"ያዝኑበታል"** |
| NRSV (footnote) | **"ያወድሳሉ" (እብራይስጥ)** |
| TEV | **"በርሱ ላይ ያነባሉ"** |
| NJB | **"በክብሩ ያወድሱታል"** |

ማሶሬቲኩ (ማሶሬቲኩ) "ደስ ይላቸዋል" የሚል አለው (BDB 162፣ KB 189፣ *Qal* IMPERFECT) ዳሩ ግን ለአሽሙር ጥቅም ላይ የዋለ ይሆናል፡፡

▣ **"ክብሩ" ይህ ቃል**(BDB 458 II)ብዙ ጊዜ ለያህዌ ጥቅም ላይ ውሏል(1 ሳሙ 4:21-22)፣እዚህ ግን ያህዌን ይወክላል ለተባለው የጥጃ ጣዖት በአሽሙር ስሜት ጥቅም ላይ ውሏል፣ዳሩ ግን በኣልን መወከል ከጀመረ ቆይቷል፡፡

**10:6 "ንጉስ ኢያርም"** ይህ ቴልጌል-ተል-ፋለሶር III የሚያሳይ ይሆናል፡፡በቃጥታ"ታላቁ ንጉስ፣" ለሚለው ምሳሌ ነው በቀጥታ"የሚቋቃም ንጉስ" ማለት ነው(BDB 937፣ 5:13)፡፡

▣ **"እስራኤልም በምክሩ ያፍራል" ግሱ**(BDB 202፣ KB 116፣ *Qal* IMPERFECT) በ2:5 እና 4:19 ውስጥም ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ጣዖት ማምላካቸው ያሳፍራቸዋል፡፡"
የውሸት ምክራቸው(BDB 420) ቀደም ብሎ በ7:12 ውስጥ ተጠቅሶ ነበር (ኤርም 7:24)፡፡ ለ"ምክር" ብዙ የታሰቡ አማራጮች አሉ፡፡

1. አለመታዘዙ
2. የእንጨት ጣዖቱ (10:5)

NASB፣ NKJV፣ NRSV፣ TEV፣ እና NJB "የእንጨት ጣዖት" የሚል አላቸው፡፡

**10:7 "ሰማርያ ከንጉሱዋ ጋር ጠፍታለች" ግሱ**(BDB 198፣ KB 225፣ *Niphal* PERFECT) ማስወገድ፣ ማፍረስ ማለት ነው(ቁ 8)፡፡ ከእዮርባም ትዕብት የተነሳ ያህዌ የሰሜኑን ንጉስ ለቆታል፣ ዳሩ ግን የወርቅ ጥጃን በማቆም በፊቱ ክፋትን ሠርቶ ነበር፡፡ አሁን በመዓቱ ያስወግደዋል( 13:11)፡፡

| | |
|---|---|
| NASB | **"በውሃ ላይ እንዳለ በትር"** |
| NKJV | **"በውሃ ላይ እንዳለ የዛፍ ቅርንጫፍ"** |
| NRSV፣ TEV | **"በውሃ ላይ እንዳለ የእንጨት ፍቅፋቂ"** |
| NJB | **"በውሃ ላይ እንደሚነዳ ገለባ"** |

እብራይስጡ በጣም ከባድ ነው፡፡ የእንጨት ፍቅፋቂን ሊያመለክት ይችላል(BDB 893 II፣ ኢዩ 1:7) ወይም "አረፋ" (ቮልጌት)፡፡

**10:8 "የአዌን የኮረብታው"** ይህ ማለት "ባዶነት" ወይም "ምንም" (BDB 19)፡፡ይህ ቃል ብዙጊዜ በአይሁዳዊያን ዘንድከጣዖት አምልኮ ጋር ንክክ ያለቸውን የሰው ስም ወይም የቦታን ስም ለማበላሸት ይጠቀሙበታል፡፡
"ኮረብታማ ቦታዎች" ሊያመለክቱት የሚችሉት (1) የተራራ ጫፍ (ማለትም፣ አውድማ) ወይም (2) ለባአል መታሰብያ ተቀርፆ የቆመ የሐውልት መሰዊያ(4:13)፡፡

▣ **"እሾህና አሜከላ በመሠዊያዎቻቸው ላይ ይበቅላል"** ይህ ምናልባት የመርገም ማሳያ ሊሆን ይችላል(ዘፍጥ 3:18) ወይም ጥቅም አልባ የመሆን ምልክት(9:6)፡፡

▣ **"ተራሮችንም ከደኑን፥ ኮረብቶችንም ውደቁብን ይሉአቸዋል።"** የመጀመርያው ግስ(BDB 491፣ KB 487) ትዕዛዛዊ ፒይል/*Piel* ትዕዛዝ አንቀፅ/ ነው፡፡
ሁለተኛው ግስ(BDB 656፣ KB 709) ትዕዛዛዊ ቃአል ነው/*Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)* /፡፡ ይህ የእግዚአብሔርን ፍርድ ለማሳየት በሉቃ 23:30 እና ዩሀ ራእይ 6:16 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ምናልባት በበአል አምልኮና "በተራሮች" እና"በኮረብታዎች" መካከል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኑኝነት ሊኖር ይችላል፡፡

**10:9 " ከጊብዓ ዘመን ጀምረህ ኃጢአትን ሠርተሃል"** ይህ ነገስታትን የሚቃወም ዐረፍተነገር ሊሆን ይችላል ምክንያቱም የሳኦል ከተማ እና ለመጀመርያ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት የሠራበት ቦታ ነው(1 ሳሙ 13:8-14)፡፡ በመሳ 19-21 ላይ ለተጸፈም ኃጢአት ማብራሪያ ነው፡፡

▣ **"በፈቀድሁም ጊዜ"** ይህ ሐረግ ግስ የለውም(BDB 16)፡፡የእግዚአብሔርን ፈቃድ መግለጫ መንገድ ይመስላል(ማለትም፣ ፍርድ)፡፡
በሁለተኛ ላይ የተጻፈው ሆሴዕ፣ ስሜታዊ በሆነው ምሳሌ እግዚአብሔርን ይገልጻል (አንትሮፖሞርፊክ)፡፡

1. የዱር አራዊት፣ 5:14፤ 13:7፣8
2. ጥላቻ፣ 9:15
3. ለመፍረድ ኃይለኛ መሻት፣ 10:10
4. ቁጣ፣ 11:9፤ 13:11

እግዚአብሔርን ለመግለጽ የሰው ልጅ ቋንቋ ሁል ጊዜ ዘይቤያዊ እና ምሳሌያዊ ነው፡፡ የሰው ልጅ ኃጢአተኛ ነውጊዜያው ነው፣ ፣ በዚህ ምድር ይወሰናል፡፡ የእኛ ሰዋሰው እና የአህምሮአችን ችሎታ ዘላለማዊውን፣ ቅዱሱን፣ እና ማንነት ያለውን ለመግለጽ አይችልም!

▣ **"እገሥጻቸዋለሁ"** ግሱ በአጠቃለይ(BDB 415፣ KB 418፣ *Qal* IMPERFECT) በመግራት"አስተምራሉ" "አድሳለሁ" (በስነምግባር)ማለት ነው፡፡ ኪዳንን ከመጣስ የተነሳ መግራትን ያሳያል(ማለትም፣ፍርድ)፡፡

▣ **"አሕዛብ ይሰበሰቡባቸዋል" እግዚአብሔር ይሰበስባል**(BDB 62፣ KB 74፣ *Pual* PERFECT) አሕዛብን(BDB 766)በሕዝቡ ላይ እንዲፈርዱ፡፡

▣ **"ስለ ሁለቱም ኃጢአታቸው" ይህ በጥሬው** "ሁለቱን ሐጥኃታቸውን ነው፡፡" "ሁለቱም ሐጥኃታቸው " የሚለው ሐረግ የመጣው ከሰባ ሊቃናት ትርጉም(Septuagint)፣ ፔሺታ(Peshitta)፣እና ከቩልጌት(ቮልጌት) ነው፡፡ ሊያመለክት የሚችለው(1) በኤፍሬም ስም ዙርያ ያጠነጥናል("እጥፍ ፍሬያማ")፤ (2)በአልን የመከተል እና ያህዌን የመርሳት ሁለቱ ሐጥኃቶች ናቸው(ኤርም 2:13)፤ ወይም(3) በቤትኤል እና በዳን የቆሙት የወርቅ ጥጃ ነው፡፡

## ሆሴዕ: 10:11-15

**11 ኤፍሬም ማበራየት እንደ ለመደች ጊደር ነው፥ እኔ ግን በአንገቱ ውበት እጫንበታለሁ**
**በኤፍሬም ላይ እጠምድበታለሁ፥ ይሁዳም ያርሳል፥ ያዕቆብም አፈሩን ያለሰልሳል።**
**12 እግዚአብሔር መጥቶ ጽድቅን እስኪያዘንብላችሁ ድረስ እርሱን**
**የምትሹበት ዘመን ነውና ለእናንተ በጽድቅ ዝሩ፥ እንደ ምሕረቱም መጠን እጨዱ፥ ጥጋታችሁንም እረሱ።**
**13 ክፋትን አርሳችኋል፥ ኃጢአትንም አጭዳችኋል፥ የሐሰትንም ፍሬ በልታችኋል በኃያላንህ ብዛት፥ በመንገድህም ላይ ታምነሃልና ፤**
**14 በሕዝብህም መካከል ሽብር ይነሣል እናትም ከልጆችዋ ጋር በተፈጠፈጠች ጊዜ**
**ሰልማን ቤትአርብኤልን በሰልፍ ቀን እንዳፈረሰ፥ አምባዎችህ ሁሉ ይፈርሳሉ።**
**15 ከኃጢአታችሁም ክፋት የተነሣ ቤቴል እንዲሁ ያደርግባችኋል በነጋ ጊዜ የእስራኤል ንጉሥ ፈጽሞ ይጠፋል።**

**10:11 "ኤፍሬም ማበራየት እንደ ለመደች ጊደር ነው፥"** ይህ ግጥማዊ መስመር እህል ማበራይት ቃላል ሥራ መሆኑን ይገልጻል፡፡ ቀጣዮቹ መስመሮች ከባድ ለሆነው ለማረስ እንደተሠራች ይታነብያሉ(ማለትም፣ ቀንበር በጫንቃዋ ላይ)፡፡

▣ **"ይሁዳ ያርሳል"** ይህ የወደፍት የባብሎን ምርኮ ከባድ መሆን ያሳያል(ማለትም፣ 605፣ 597፣ 586፣ 582 B፡፡C፡፡)፡፡

▣ **"ያቆብ አፈሩን ያለሰልሳል" ግሱ** (BDB 961፣ KB 1306፣ *Piel* IMPERFECT) ከማረስ ጋር ይመሳሰላል፡፡" በኢዮብ 39:10 እና እሳ 28:24 ላይም ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ያዕቆብ የሚያመለክተው:

1. የእስራኤል ሌለኛው ስም
2. ሁሉም ነገዶች የሚገለጹበት መንገድ(ማለትም፣ እስራኤል እና ይሁዳ)፡፡

**10:12 "በጽድቅ ዝሩ፥ እንደ ምሕረቱም መጠን እጨዱ፥ ጥጋታችሁንም እረሱ"** በዚህ የፍርድ አውድ ውስጥ ምን ዓይነት የሚየስገርም ቁጥር ነው፡፡ ሦስት ትዕዛዛዊ ቃአሎች አሉ(*Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)* S)፣ (ዝሩ፣ እጨዱ፣ እርሱ)፡፡ ይህ ግስ ሕዝቡ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ በነብዩ ወይም(በእግዚአብሔር ራሱ) ለሕዝቡ የቀረበ ሊሆን ይችላል(ምሳ 11:18)፡፡ እነዚህ ሦስቱ የግጥም መስመሮች አጠቃላይ ውነታን ይናገራሉ፣ "ሰው የዘራውን ያጨዳል" (8:7፤ 12:2፤ ኢዮ 4:8፤ መዝ 126:6፤ ምሳ 11:18፤ 22:8፤ ኤርም 4:3፤ II 9:6 ገላቲ 6:7)፡፡

"ምህረት"የሚለው ቃል (BDB 338) የእብራይስጥ ቃል ሔጼድ(*hesed)* ነው፣ ማለትም "የኪዳን ታማኝነት፣" ለእግዚአብሔርም ሆነ ለኪዳን ተካፋዮች(4:1፤ 6:4-6፤ 12:7፤ ሚክያ 6:8)፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት: : ሔጼድ(*Hesed)* በ2:19፡፡

▣ **"የእርሻ ቦታችው ይታረስ"** ይህ የንስዐ ማሳያ ምልክት ነው(ኤርም 4:3)፡፡

▣ **"እግዚአብሔርን ለመፈለግ ጊዜው ነው"** ግሱ (BDB 205፣ KB 233) is a *Qal* INFINITIVE CONSTRUCT፡፡
የኪዳን እንድምታ አለው(ለምሳሌ ፣ ዘዳግ 4:29)፡፡ በእውነት ከተፈለገ ያህዌ ይገኛል(ለምሳሌ ፣ ኤርም 29:13)፡፡ ጥፋትን ለማስወገድ የእስራኤል ብቻኛው ተስፋ ያህዌን መፈለግ ነው(10:12፤ እሳ 55:6-7፤ አሞ 5:4፣6)፡፡ እግዚአብሔርን ለመፈለግ ትክክለኛ ጊዜው አሁን ነው!

▣ **"መጥቶ ጽድቅን እስኪያዘንብላችሁ ድረስ"** ለእውነተኛ መንፈሳዊነት ይህ የሚያስደንቅ የግብርና ዘይቤያዊ አነጋገር ነው(ማለትም ፣ ዓመታዊ እና መደበኛ ዝናብ) (ማለትም፣ ጽድቅ)፡፡ ይህ በነብያት ውስጥ የሚደጋገም ርዕስ ነው (ለምሳሌ ፣ 2:19-20፤ 6:3፤ 14:5፤ መዝ 72:6-7፤ እሳ 44:3-4፤ 45:8፤ ኢዮኤ 2:23፤ 3:18)፡፡

**10:13 " ክፋትን አርሳችኋል፥ ኃጢአትንም አጭዳችኋል"** የእግዚአብሔር መሻት"ለጽድቅ" እና"ለታማኝ" ሕዝብ ነው(ቁ 12)፣ የግብርና ምሳሌን በመጠቀም("የእርሻ ቦታችው እታረስ")፣ ሳይታሰብ ታቃራኒ ፍሬ ሰጠ—ክፋት እና ኢ-ፍታዊነት፡፡
ከያህዌ ይልቅ በራሳቸው ኃይል ተማመኑ(BDB 105፣ KB 120፣ *Qal* PERFECT፡፡ ውጤቱ(ቁ 14-15) ከባድ ጥፋት ሆነ!

▣ **"በኃያላንህ ብዛት፥ በመንገድህም ላይ ታምነሃልና"** ታርካው መቼቱ ታላቅ የብልጽግና እና የወታደራዊ ድል ጊዜ ነበር(መግብያ ተመልከት)፡፡ እስራኤል(እንደ ይሁዳ፣ 8:14) በወታደራዊ ኃይሏ ትተማመን ነበር(ኤርም 9:23-24)፡፡
"መንገድህ" (BDB 202) የሚለው ሐረግ በሰባ ሊቃናት ትርጉም (Septuagint) ውስጥ"ጋሪ" በሚል ተተርጉሟል (14:3)፣ ለማመሳሰል ጥሩ የሚያደርግ፣ ዳሩ ግን ማስተካከያ ይፈልጋል፡፡ ከዩጋርትክ ሥር (Ugaritic root) ተነባቢዎቹን እንደ ኃይል ማንበቡ ይሻላል፡፡

**10:14 "ሰልማን ቤትአርብኤልን በሰልፍ ቀን እንዳፈረሰ፥"** ይህ ከክርስቶስ ልደት በፊት 858-824 ድረስ ለነገሰው ለሰልማን‌III እንደ ማብራርያ ነው፡፡ ከመጽሀፍ ቅዱስ እርሱ እያመለከተ ያለው በ II ነገስ 17:3 እና 18:9 ውስጥ ተጠቅሷል፡፡ የሞአብ ንጉስ የሆነውን ሰልማንንም ሊገልጽ ይችላል፣ ከቴልጌልፋሦር III ጋር በአንድ ዘመን የሆ፡፡ ቤትአርብኤል የማይታወቅ ቦታ እና ታርካዊ ማብራርያው የሚታወቅ አይደለም፡፡

▣ **"እናትም ከልጆችዋ ጋር በተፈጠፈጠች"** ይህ የአሦር ምርኮ ሁነታ አስደንጋጭ መሆኑን ያሳያል፡፡
ሰራዊቱ በምርኮ ጊዜ በደንብ ሊሄዱ የማይችሉትን ያረጁ እና ሕፃናትን ገደሏቸው፡፡ይህ በርግጥ፣ እርጉዝ ሴቶችን ያጠቃልላል፡፡ ይህ ሕዝቡን ለመጉዳት እና ለማስደንገጥ የተደረገ ነበር(13:16)፡፡

## ለምዕራፍ 9 እና 10 የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. በሆሴዕ 9 እና 10 ውስጥ ለፍሬያማ አምልኮ መጣቀሻ የሚሆኑትን ዘርዝር፡፡
2. በ 9:9-10:15 ውስጥ የሚገኙትን ከተሞች ዘርዝር፡፡
3. እስራኤል በግብጽ ወይም በአሦር ተማርካለች? 11:5ን ከ7:10፤ 8:13፤ 9:3 ጋር በማነፃፀር አብራራ፡፡
4. የእብራይስጥን የ "ነውር"አጠቃቀም አብራራ፡፡

# ሆሴዕ 11

## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|
| ለእስራኤል ዘላቂ የእግዚአብሔር ፍቅር | ቀዋሚ ስለሁነው የእስራኤል አመፃ ምክንያት የተነሳ የእግዚአብሔር ፍርድ በእስራኤል ላይ ነው (4:1-14፡9) | የእግዚአብሔር ፍቅር አመፀኛ ለሆነ ህዝቡ | የእግዚአብሔር ፍቅር ተናቀ፡ በቀል |
| | 11:1-7 | | |
| 11:1-4 | | 11:1-4 | 11:1-6 |
| | | | የእግዚአብሔር ፍቅር ከበቀሉ በላይ ይበረታል |
| 11:5-7 | | 11:5-9 | |
| | 11:8-9 | | 11:7-9 |
| 11:8-11 | | | ከምርኮ መመለስ |
| | 11:10-12 | 11:10-12 | 11:10-11 |
| የእግዚአብሔር ቁጣ በይሁዳ ኃጢአት ላይ | | እስራኤልና ይሁዳ ተከሰሱ | |
| 11:12-12:14 | | 11:12-12:6 | 11:12 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ vii ተመልከት)**

*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

### ሆሴዕ: 11:1-4

**1 እስራኤል ሕፃን በነበረ ጊዜ ወደድሁት፥ ልጄንም ከግብጽ ጠራሁት፡፡ 2 አብዝቼ ብጠራቸው አጥብቀው ከፊቴ ራቁ ለበኣሊምም ይሠዉ ነበር፥ ለተቀረጹ ምስሎችም ያጥኑ ነበር፡፡ 3እኔም እፈውሳቸው እንደ ነበርሁ አላወቁም፡፡ 4 በሰው ገመድ በፍቅርም እስራት ሳብኋቸው ለእነርሱም ቀምበርን ከጫንቃቸው ላይ እንደሚያነሣ ሆንሁ፥ ድርቆሽም ጣልሁላቸው፡፡**

**11:1-4** ሆሴዕ እግዚአብሔርን እና ድርጊቱን ለመግለጽ አዳድስ እና የተለያዩ ዘይቤዎችን በመጠቀም ይታወቃል፡፡ በጣም ኃይለኛ እና ግላዊ የሆኑ ሁለቱ ዘይቤዎቹ(1) እግዚአብሔር እንደ ታማኝ ፍቅረኛ፣ ምዕራፍ 1-3 እና (2) እግዚአብሔር እንደሚዋደዱ ቤተሰብ(ሴት እና ወንድ)፣ ምዕራፍ 11፡፡ እግዚአብሔር ሰዎች የለመዱትን በመምረጥ ለወደቀው ሰው ራሱን ገለጸ—በጥልቀት ግላዊ እና በኃይል መንቀሳቀስ የሚችሉትን ነገሮች —

እናም፣ "እኔ ለእናንተ እንደዛው ነኝ" ብሏል፡፡ ለዚህ ነው ብዙ ጊዜ የቤተሰብ ዘይቤእና ምሳሌ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር በተገናኘ ጥቅም ላይ የዋለው፡፡ ሁሉም ሰው የሰውን የፍቅር ስሜት ተለማምዷል እናም ቤተሰባዊነትንም ተለማምዷል፡፡ እንግዲህ በእነዚህ ልምምዶች ናቸው እግዚአብሔር ራሱን፣ የፍቅሩን ጥልቀት እና ታማኝነቱን የገለጸው(11:8-9)፡፡

**11:1 " እስራኤል ሕፃን በነበረ ጊዜ ወደድሁት"** ይህ 9:10 እና 10:1 በማተኮር ውስጥ በጣም ተመሳሳይ ነው፡፡ የያህዌን ፍቅር እና የተለዩ ሕዝቡ እንዲሆኑ የአብርሃም ዘር ምርጫ ላይ ያተኩራል(ዘዳግ 4:32-40) (አሞ 3:2፣ ዘፀአ 19:5-6ን የሚያንፀባርቅ)፣ የዘፍጥ 15:12-21 ትንቢታዊ ፍጻሜ የነበረው፡፡
እግዚአብሔር በምድር ላይ እርሱን የሚወክሉትን ሕዝብ ከቤተሰብ ለመምረጥ አንድን ሰው መረጠ (ዘፍጥ 12:3፤
ዘፀአ 19:5-6)፡፡ መስሕዉ የሚመጣው ከዚህ ቤተሰብ ነው(ማለትም፣ በኢየሱስ ሕይወት ውስጥ በማቴ 2:15 ላይ ይንን ክፍል እንደ ምሳሌ ተጠቅሟል)፡፡

▣ **"ልጄንም ከግብጽ ጠራሁት"** ልጄ የሚለው ቃል በነጠላ መልኩ በብሉይ ኪዳን ሊያመለክት የሚችለው(1) የእስራኤል ሕዝብ(ለምሳሌ ፣ 1:10፤ ዘፀአ 4:22)፤ (2) የእስራኤል ንጉስ (ለምሳሌ ፣ II ሳሙ 7:14፤ መዝ 2:7)፤ ወይም(3) መስሕውን(ለምሳሌ ፣ መዝ 2:7፣ በሐዋ ሥራ 13:33፤ እብ 1:5፤ 5:5 ተጠቅሷል)፡፡ ይህ ጥቅስ ኢዬሱስ በልጅነቱ ከሔሮድስ ለመሻሽ ወደ ግብጽ በተወሰደ ጊዜ በማቴ 2:15 ላይ ለእርሱ ጥቅም ላይ ውሏል ፣ ይሁን እንጂ፣ በዚህ አውድ ውስጥ የእስራኤልን ሕዝብ ያመለክታል፡፡ በምርጫ ላይ ያለውን ትኩረት አስተውል፣ "ጠራውት" (BDB 894፣ KB 1128፣ *Qal* PERFECT)፡፡ በብሉይ ኪዳን ምርጫ ቅድሚያ ለአገልግሎት ሲሆን(በያህዌ የመዋጀት ዕቅድ የእስራኤል ቦታ)፣ በአድስ ኪዳን ደግሞ ለደህንነት ነው(ኤፌ 1:3-14)፡፡

**11:2 " አብዝቼ ብጠራቸው"** ይህ ነብያትን ያመለክታል(የሰባ ሊቃናት ትርጉምትርጉም እና II ነገስ 17:13-18፤ እሳ 6:10፤
ኤርም 7:25-26)፡፡ ይሁን እንጂ፣ እስራኤል እንደ ሰው ሕፃናት ያደርግ ነበር፡፡ እግዚአብሔር በጠራቸው መጠን (the Septuagint and the Syriac have "እነርሱ" በሚል ፋንታ "እግዚአብሔር" ይላል)፣አብዝተው ተቃራኒውን ሠሩ(ቁ 7ለ)፡፡
David A Hubbard፣ ሆሴዕ (Tyndale OT Commentaries)፣ ሁለተኛውን መስመር ገና በሁለት ይከፍልና እነርሱ የሚለው እንደ የፍሬያማ ጹሆር ባአል-25 ቁጥር ሴቶችን ማምለክ አሳሳሶችን ያመለክታል ብሎ ያስባል፡፡ መስመሩ የሚሆነው "አብዝቶ በጠረአቸው፣ አብዝተው ከእኔ ርቀው ሄዱ" (ገ 187)፡፡ እንደ ጀሮም የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራርያ(Jerome Biblical Commentary) "እነርሱ" የሚለው በአከባቢው ያሉትን የበአል መስዊያዎችን እንደሚያመለክት ይናገራል(ገ 262)፡፡ ወደ ራሱ እና ወደ ኃጢአት ለዘነበለው እና ላፈነገጠው ልጅ፣ የጣዖት ጥሪ ከሚወድ ቤተሰብ ጥሪ ይልቅ ይሰማል ይጠነክራል (ማለትም፣ የጠፋው ልጅ ሉቃ 15)፡፡የትኛውም አመለካከት ትክክል ቢሆን የእምብተኝነት ባሕሪይ ይተኮራል! ያለፈው መሰጠቷ በአሁኑ ምኞቷ ጠፋ፡፡

▣ **"በአል"** የከናዓን ወንድ ፍሬያማ ጣዖትን ያመለክታል፡፡ ለሙሉ የከናዓን ፓንተሑሆን (Canaanite pantheon) አርክኦሎጂና የእስራኤልን እምነት ተመልከት(*Archaeology and the Religion of Israel)*፣ by William Foxwell Albright፡፡

▣ **"አጥብቀው ከፊቴ ራቁ ለበኣሊምም ይሠዉ ነበር፥ ለተቀረጹ ምስሎችም ያጥኑ ነበር"** እነዚህ ሁለቱ የግጥም መስመሮች ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ ለበአል የቀረበው መስዊይት እንስሳ ይሁን የሚታወቅ ነገር የለም፣ስለዚህ፣መስዋይቱ(BDB 256፣ KB 261፣ *Piel* IMPERFECT) የሚታጠን ሊሆን ይችላል(BDB 882፣ KB 1094፣ *Piel* IMPERFECT)፡፡
ለፍሬያማ እሳት ጣዖት፣ ሞሌክ ለተባለው የሕፃናት መስዋይት ይቀርብለት ነበር፡፡ ይህ ምናልባት በአንዳንድ የሆሴዕ መጽሐፍ ውስጥ የሕፃናት መታረድን ሊያመለክት ይችላል፡፡

**11:3 "እኔም ኤፍሬምን ክንዱን ይዤ በእግሩ እንዲሄድ መራሁት"** ይውህ ለዋና ቃሉ ያልተለመደ ትርጉም የሚሰጥ ውስን ግስ ነው (BDB 920፣ KB 1183፣ *Tiphel*)፡፡ ቁጥር 3 እና 4 ያህዌ እንደሚወዱ ቤተሰብ፣ ሁለቱ አባት እና እናት በማድርግ የእግዚአብሔርን ፍቅር በምሳሌ ይገልፃል(የቁ 4ለ፣ሐ ማስተካከያ)፡፡ አባት ወይ (1) ለጉዞ ከልጁ በፊት ሄዶ ይሆናል ወይም (2) ምሳሌ ለመሆን ወይም ለጥበቃ ከልጁ በፊት ሄዶ ነበር፡፡

▣ **"እኔም እፈውሳቸው እንደ ነበርሁ አላወቁም"** በዚህ ሐረግ ውስጥ የያህዌ እምም ይሰማሃል? ከግብጽ ያዳናቸው እና ራሱን የገለጠላቸው፣ የራሱ ሕዝብ የፍቅር ስጦታውን ለከናዓን የፍሬያማ ጣዖት አደረጉት! የተበላሸ/የተጎዳ ፍቅር!
"ፈውስ" የሚለው ግስ(BDB 950፣ KB 1272፣ *Qal* PERFECT) እግዚአብሔር ኃጢአት ን ይቅር ስል ጥቅም ላይ ውሏል፣ በሆሴዕ 5:13፣ 6:1፤ 7:1፤ ዘፀአ 15:26፤ እንደሚታየው የ መዝ 163:3፤ እና እሳ 1:5-6፣ ተመሳሳይ ፣ እንደ አካላዊ በሽታ የተገለጸ ሕዝባዊ ኃጢአት (እንደዚሁም እሳ 53:5 እና I ጴጥ 2:24-25 አስተውል)፡፡

**11:4 "በሰው ገመድ በፍቅርም እስራት ሳብኋቸው"** ይህ የሕፃናት ማስልጠኛ ገመድን ያሳያል፡፡" የእግዚአብሔር ቅጣት እንደ ማንኛውም ምህረቱ የፍቅር ምልክት ነው(እብ 12:5-13 የእግዚአብሔርን ድርጊት እና ለሐጥኃተኛው ሰው፣በነፃነት እና መልካም እና ክፉ መለያ ዛፍን በማወቅ ራሳቸውን ለማጥፋት መንገድ ላይ ለሉት የሚሰጠውን ምሪት ለመረዳት የፍቅር ቤተሰብ ቅጣት ቁልፍ ነው፡፡ ያለ ፈተና እንድንሄድ አያደርገንም! ራሳችንን እንድናጠፋ አያደርግም፡፡

▣ **"ቀምበር"** "ቀምበር" የሚለው የእብራይስጡ ቃል (BDB 760) ከዚህ ዘውድ የወጣ ይመስላል (ይሁን እንጂ፣ 10:11ሊያሳይ ይችላል)፡፡ አሁንም ቢሆን አናባቢውን በመቀየር እና የመጨረሻ ተነባቢውን እጥፍ በማድረግ፣ የቤተሰብን እንክብካቤ አውድ ሊያሳይ የሚችለውን(፣ NIDOTTE፣ ቅጽ 3፣ ገጽ 401) "ጨቅላ ሕፃን"የሚለውን የእብራይስጥ ቃል ማስገባት ይቻላል (BDB 760፣ 14:1)፡፡ ሊሆን የሚችለው ትርጉም እንደ አድሱ የአሜርካ መጽሐፍ ቅዱስ እና የእዬሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ"ጨቅላ ሕፃንን ወደ ጉንጩ እንደሚወስድ ሰው፡፡" ይህ ያህዌ እንደ አሳዳግ እናት መሆኑን የሚያሳይ አማራጭ መግለጫ ነው፡፡
እግዚአብሔር ወንድ ወይም ሴት አይደለ፡፡ እርሱ ዘላለማዊ፣ ማንነት ያለው፣ ሁል ጊዜ፣ ሁሉ ቦታ፣ እና በውነታ ውሉ ውስጥ የሚገኝ መንፈስ ነው፡፡ በዚህ ምድር ውስጥ የመራብያ መሠርያ እንዲሆኑ ወንድ እና ሴትን ፈጠራቸው፡፡ ለሁለቱም የሚሆን መልካም ነገር በራሱ ውስጥ አስቀመጠ፡፡

ይህ አነስታይነት ለየት ብሎ የሚታየው ብዙ ቦታዎች አሉ፡፡

1. ዘፍጥ 1:2፤ "በውሃ ላይ ይንሳፈፍ ነበር" - ይህ የሴት ወፍ ቃል ነው
2. ሆሴዕ 1:4፤ ኢሳ 49:15፤ 66:9-13 - እግዚአብሔር እንደ አሳዳግ እናት

## ሆሴዕ፡ 11:5-7

**[5] ወደ እኔ ይመለሱ ዘንድ አልወደዱምና ወደ ግብጽ ምድር ይመለሳሉ፥ አሦርም ንጉሣቸው ይሆናል፡፡**
**[6] ከመከሩትም ምክር የተነሣ ሰይፍ በከተሞቻቸው ላይ ይወድቃል፥ ከበርቴዎችንም ያጠፋል፡፡**
**[7] ሕዝቤም ከእኔ ይመለሱ ዘንድ ወደዱ ወደ ላይም ቢጠሩአቸው ማንም ከፍ ከፍ ያደርጋቸው ዘንድ አይችልም፡፡**

**11:5 "*ወደ እኔ ይመለሱ ዘንድ አልወደዱምና ወደ ግብጽ ምድር ይመለሳሉ፥*"** ይህ የ7:16፤ 8:13፤ 9:3 ተቃርኖ ማንፀባረቅያ ነው፡፡ ሊሆኑ የሚችሉ ሁለት የአተረጓጎም መላምቶች አሉ: (1) ግብጽ የባርነት ምሳሌ ናት ወይም (2) ግብጽ ሌላ የፖለትካ ቡድን ምሳሌ ናት፡፡ ሁለተኛው መላምት ለምዕራፍ 11:5 አውድ የሚሆን ይመስላል፤ይሁን እንጂ አንደኛው መላምት ለሌላው መጣቀሻ አውድ የሚሆን ይመስላል፡፡
It is possible to translate "አይደለም" የሚለውን "በርግጥ፣" ወደሚለው መተርጎም ይቻላል፣ ይህ የሚንፀባረቀውን ታቃርኖ ሊያቃልል ይችላል፡፡

▣ **"*አሦርም ንጉሣቸው ይሆናል*"** ይህ ግልጽ ያለ ትንቢታዊ የአሦር ምርኮ ነው(7:11፤ 8:9-10፤ 9:3፤ 10:6)፡፡ የእስራኤል ታማኝነት በፖለቲካ ጥገኝነት ቡለቱም ግብጽ እና አሦር ዘንድ ተቀባይነት እንደለሌ ቁጥሩ ያሳያል፡፡ አሦርን እንደ ንጉስ 10:3 ሊያንፀባርቅ ይችላል፡፡ እንደ አሕዛቦች እስራኤል ንጉስ ፈለገች(1 ሳሙ 8:5 አንድ ነበራቸው!

▣ **"*ወደ እኔ ይመለሱ ዘንድ አልወደዱም*"** "መመለስ" የሚለው ቃል(BDB 996፣ KB 1427፣ *Qal* INFINITIVE CONSTRUCT) የብሉይ ኪዳን የንስዐ ቃል ነው፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት: : የብሉይ ኪዳን ንስዐን አሞ 1:3 ላይ ተመልከት፡፡ የእግዚአብሔር ልብ እመም "**አልወደዱም**" (BDB 549፣ KB 540፣ *Piel* PERFECT) በሚል ግስ ውስጥ ይታያል፡፡ በእስራኤል በኩል ጥፋተኝነታቸውን አለመቀበል አልነበረም፣ ግን በያህዌ እና ሥርዓቱ ላይ ዓይን ያወጣ ተቃውሞ ነበር(7:13-15፤ 8:1፣12)፡፡

**11:6 "ሰይፍ በከተሞቻቸው ላይ ይወድቃል"** ግሱ(BDB 296፣ KB 297፣ *Qal* PERFECT) ለዳንስ፣ ለአውሎ ንፋስ ሁከት፣ ወይም በሚጥ ጊዜ መወራጨትን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የእስራኤልን ከተማ የሚያጠፋው ሰይፍ የሚበላበል እና የሚያንፀባርቅ መሆኑ ነው፡፡

▣ **"*የበሮቻቸው መወርወያ*" ይህ ቃል**(BDB 94) የሚያሳየው (1) ሌሊት የከተማን ደህንነት ለመጠበቅ የሚያገለግል የእንጨት ተሸካሚ(እስራኤል በጦር መከላከያዎቿ ትተማመን ነበረች፣ 8:14፤ 10:14) ወይም (2) ትምቢታዊነት(እሳ 44:25፤ ኤርም 50:36) እና "ምክርን" በሚመስል መልኩ፡፡

▣ **"*ከመከሩትም ምክር የተነሣ*"** ይህ ሊያሳይ የሚችለው (1) የወርቅ ጥጃን ያሠራው፣ እዮርባም 1 ሕግ፤ (2) ከርሱ ቀጥሎ ያሉት የስርወ-መንግስታት ሕግ፤ ወይነ (3) የፖለትካ አማካሪዎች ውሳኔ፡፡ ይህ በሆሴእ ውስት ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል(ለምሳሌ ፣ 7:12)፡፡

**11:7 "ሕዝቤም ከእኔ ይመለሱ ዘንድ ወደዱ" ግሱ** (BDB 1067፣ KB 1736፣ *Qal* PASSIVE PARTICIPLE)፣ which is used literally inበ ዘዳግ 28:66፣ በቀጥታ ጥቅም ላይ የዋለ ነው"አንድን ነገር በአንድ ሰው ፊት መስቀል፣" እዚህ ወደ አንድ ሰው የማዘንበል አዝማምያ ነው(ግን ወደ ያህዌ አይደለም)፡፡
"ከ... *መመለስ*" (BDB 1000) ማለት "ወደ ኃላ መመለስ" ወይም"አለመከተል/መካድ" (14:5፤ in ኤርም 3:6 የእስራኤል በኤርም 2:18፤ 3:22፤ 5:6፤ 8:5፤ 14:7 የይሁዳ፣ ብዙ ጊዜ የተተረጎመው "እምነት የለሽ" በሚል ነው)፡፡ በንስዐ ወደ እግዚሐብሔር ከመመለስ ይልቅ እርሱን በመካድ ከእርሱ ራቁ!
"ሕዝቤ የሚለው" መክፈቻ የ1:9 መጥቀሻ ነው (ማለትም፣ "ሎሩሃማ")፣ ዳሩ ግን ከወደፊት ተስፋ የ2:23 ሙሉ ተስፋ ጋር(ማለትም፣ ሩሃማ፣ 1:6 እና ሎዓሚ)!

▣ **"*ማንም ከፍ ከፍ ያደርጋቸው ዘንድ አይችልም* "** ይህ የወደቀው የሰው ዘር ችግር ነው፣ በተለይ የኪዳን ሕዝብ(ለምሳሌ ፣ እሳ 53:6 ሀ፣ለ፣በ 1 ጴጥ 2:25 ውስጥ ተወስዶ ጥቅም ላይ ውሏል)፡፡

## ሆሴዕ፡ 11:8-11

**8 ኤፍሬም ሆይ፥ እንዴት እጥልሃለሁ? እስራኤል ሆይ፥ እንዴትስ አሳልፌ እሰጥሃለሁ?**
**እንዴትስ እንደ አዳማ እጥልሃለሁ? እንዴትስ እንደ ሲባዮ አደርግሃለሁ?**
**ልቤ በውስጤ ተናውጣለች፥ ምሕረቴም ተነሣሥታለች፡፡**
**9 እኔ አምላክ ነኝ እንጂ ሰው አይደለሁምና፥ በመካከልህም ቅዱሱ ነኝና የቁጣዬን መቅሠፍት**
**አላደርግም፥ ኤፍሬምንም አጠፋ ዘንድ አልመለስም በመዓትም አልመጣም።**
**10እግዚአብሔርን ይከተላሉ፥ እርሱም እንደ አንበሳ ያገሣል ባገሣም ጊዜ ልጆች እየተንቀጠቀጡ ከምዕራብ ይመጣሉ።**
**11 እንደ ወፍም ከግብጽ፥ እንደ ርግብም ከአሦር ምድር እየተንቀጠቀጡ ይመጣሉ በቤታቸውም አኖራቸዋለሁ፥ ይላል እግዚአብሔር፡፡**

**11:8 "እንዴት እጥልሃለሁ?"** የያህዌ ልብ እየተሰበረ ነው (በዚህ ቁጥር ውስጥ ሶስተኛ የተመሳሳይነት ጥርቅም፣ 6:4) እምብተኛ ልጅ ከሚወዱት ታማኝ ቤተሰብ እንደተለየ፡፡ በብሉይ ኪዳን ውስጥ በድንጋይ ተወግሮ ይሞታል (ዘዳግ 21:18-21)፡፡ ፍትህ ወይም ፍቅር የት ይገናኛሉ?

▣ **"እንዴትስ አሳልፌ እሰጥሃለሁ?"** ይህ ግስ ማለት(BDB 171፣ KB 545፣ *Piel* IMPERFECT) "ማዳን" ወይም "ማስቆም፡፡" ይህ ቃል በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሦስት ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ ውሏል እንደዚሁም በዘፍጥ 14:20 ላይ በተመሳሳይ ትርጉም፡፡

▣ **"አዳማ… ሲባዮ"** እነዚህ ከከፋታቸው የተነሣ ከሰዶም እና ጎሞራ ጋር የጠፉ ከተሞች ናቸው (ዘፍጥ 10:19፤ 19:24-25፤ ዘዳግ 29:23)፡፡ ከዛ በኃላ አለተገኙም፤ እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ይፈርዳል፣ ግን ሊያጠፋቸው አይደለም፡፡

▣ **"ልቤ በውስጤ ተናውጣለች"** ይህ ግስ(BDB 245፣ KB 253፣ *Niphal* PERFECT) "ከ…መመለስ" ወይም "ለመተው" ለሚለው ማጠቃለያ ቃል ነው፡፡ እግዚአብሔር እነዚያን ከተሞች እንደሚያጠፋቸው ለመግለጽ ያገለግላል(በ ቁ 8 ላይ ያሉ ወደ ሁለቱ ተመሳሳይ መስመሮች ያሳያል) በ ዘፍጥ 19:21፣25፣29፤ ዘዳግ 29:22 ውስጥ፡፡ የእስራኤልን ኃጢአት እና አመጽን በተመለከተ እግዚአብሔር ቁጣውን አልተወም፣ ዳሩ ግን ፍቅሩ እና ምህረቱ የወደፊት መዳንን ያመጣል፡፡ ይህ የአድሱ ኪዳን መንፈስ በኤርም 31:31-34፤ ሕዝቄ 36:22-38፣ ይህም የሰው ውጫዊ አፈጻጸም ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ማንነት፣ በመስሕው ሥራ፣ እና በመንፈስ ዕርዳታ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ እግዚአብሔር ከወደቀው የሰው ዘር ጋር የሚነጋገርበትን መንገድ ቀየረ (የግሱ ሁለተኛ አማራጭ ትርጉም፣ TEV፣ NIV፣ NET Bible)፡፡

▣ ***"ምሕረቴም ተነሣሥታለች"*** ይህ ቃል ለ "ምህረት" (BDB 637) በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሦስት ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ ውሏል፣ እሳ 57:18፤ ዘካ 1:13፤ እና እዚህ ውስጥ፡፡ "ተቃጥላለች" የሚለው ግስ(BDB 485፣ KB 481፣ *Niphal* PERFECT) ትርጉሙ "በፍቅር ለማደግ፣" መጀመርያው ፍሬ እንዲበስል ለማድረግ አፈር ውስጥ ለመቅበር ያገለግል ነበር(ለምሳሌ ፣ ዘፍጥ 43:30፤ I ነገስ 3:26፤ እና እዚህ)፡፡

**11:9 "በመዓትም አልመጣም"** The CONSTRUCT "መዓት" የሚል አወቃቀር (BDB 354 እና 60) 8:5 ውስጥም ይገኛል (ለምሳሌ ፣ ዘፀአ 32:12 በሐሮን የወርቅ ጥጃ ጊዜ፤ ዘኁ 25:4 የእስራኤል ጣዖት አምልኮ በሰጢም፤ ዘኁ 32:13-15 ወደ ተስፋይቷ ምድር ለመግባት እስራኤል እምነት ባታ ጊዜ፤ ኢያ 7:26 በአካን ኃጢአት  በአይ፤ ዘዳግ 13:17 በከተማው ጣዖት አምልኮ እና ሌሎች)፡፡

▣ **"ኤፍሬምንም አጠፋ ዘንድ አልመለስም"** እግዚአብሔር ምህረት ማድረግን ይመርጣል(ኤርም 26:3)፡፡ ይህ ማለት ግን አልተቀጡም ማለት አይደለም(ቁ 10ሀ፤ ኤርም 30:11)፡፡

▣ **"እኔ አምላክ ነኝ"** ይህ የ *El* ስም ነው (BDB 42 II)፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡፡ የመለኮት ስም በአሞ 1:2፡፡

▣ **"እኔ አምላክ ነኝ"** ይህ ያለ ምንም አባባል መሆን አለበት (ዘኁ 23:19፤ I ሳሙ 15:29፤ ኢዮ 9:32)፣ በእኛ ዘመን ግን የእግዚአብሔር የሚታይ አካል በ"በመልክ እና በምሳሌ" በ ዘፍጥ 1:26-27 ውስጥ ይገለጻል፡፡ እግዚአብሔር መንፈስ ነው! እግዚአብሔር ( በሆሴዕ ውስጥ ይህ ባሕሪ ለያህዌ የተሰጠበት ብቻኛ አውድ ነው 11:12)፡፡

▣ **"በመካከልህም ቅዱሱ ነኝና"** ይህ (BDB 899፣ 872) "አማኑኤል" ከሚለው ትርጉም ጋር ተመሳሳይ ነው፣ ማለትም"እግዝአብሄር ከእኛ ጋር ነው" (BDB 769፣  እሳ 6:12፤ እሳ 7:14)፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እግዝአብሄር እና ሰው ልጅ በጋራ በገነት ውስጥ በሚል ይጀምር(ዘፍጥ 1-2) እና እግዝአብሄር እና ሰው ልጅ በጋራ በገነት ውስጥ ብሎ ይጨርሳል(ዮሐ ራእይ 21-22)፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ የእምነት መንፈስ እግዝአብሄር እና ፍጥረቱ በህብረት የሚል ነው፣ በመንፈስ ብቻ ሳይሆን በአካል፡፡

የሰው ልጆች የተፈጠሩት ከእግዝአብሄር ጋር ህብረት እንዲያደርጉ ነው(ዘፍጥ 1:26-27)፡፡ ትንሽ እና ትልቅ ልዩነት በመካከላቸው ነበር ማለት አይደለም፡፡ የሰው ኃጢአት  ብቻ ነው እጥረቱን ያመጣው!

▣

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"በመዓትም አልመጣም"** |
| **NKJV** | **"በማስፈራራት አልመጣም"** |
| **NRSV (footnote)** | **"ከተማይቷን አልገባም"** |
| **TEV፣ NJB** | **"በቁጣዬ አልመጣብህም"** |

በእብራይስጡ ግንድ ላይ በመመርኮዝ አሻሚ የሆነውን ይህንን የእብራይስጥ ሐረግ በብዙ መልኩ መረዳት ይቻላል:

1. "ለማቃጠል" ወይም "ለማጥፋት" (BDB 128)
2. "ለማስወገድ"ወይም "ለማፍረስ" (BDB 128)
3. "ጋር" እና "ጭንቅ" ወይም "መዓት" (BDB 786)
4. ማሶሬቱ፣ ""እና ከተማይቷን አልገባም" (VERB BDB 97፣ OBJECT BDB 746 II)፣ 8:14፤ 10:14 ጋር የሚያገናኘው፣ የያህዌ መገኘት ፍርድን ያመጣል፡፡

**11:10 "እርሱም እንደ አንበሳ ያገሣል"** ***"ያገሣል"*** እዚህ የዱር እንስሳትን ተቃውሞ አያሳይም፣ ዳሩ ግን የእናት ትንሳ ልጁን መጥራት ነው፡፡

▣ **"ልጆች እየተንቀጠቀጡ ከምዕራብ ይመጣሉ"** ምናልባት በያህዌ ቁጣ እና እየተንቀጠቀጡ ይመጣል በሚል መካከል የሚሰማ ነው (BDB 354)፣ (BDB 353፣ KB 350፣ *Qal* IMPERFECT፣ሁለት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፣ 10:11)፡፡ ይህ ቃል የሚያገለግለው(1) በዘፍጥ 42:28 ውስጥ በእግዚአብሔር ድርጊት ላይ ባለው ፍርሃቻ፤ (2) በ ሳሙ I 10:4 ውስጥ ለእግዚአብሔር ነብይ በፍርሃት የተሞላ አክብሮት፤ እና (3) በ ሳሙ I 21:1 ውስጥ በንጉስ ዳዊት መገኘት ፍርሃት፡፡ ቅፅሉ በእሳ 66:2፤ ሕዝራ 9:4፤ 10:3 ውስጥ ላለው የእግዚአብሔር ቃል ክብር እና ታላቅ አክብሮት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

አሦር በምዕራብ ከመሆኗ የተነሣ የአመጣጡ አቅጣጫ"ምዕራብ" (በቀጥታ "ባሕር") የሚያስደንቅ ነው፡፡ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዋች ቁ 10 እና 11 በሦስት አቅጣጫ ተመልሶ እንደመሚጣት(ማለትም፣ከሁሉም አቅጣጫ፣ እሳ 11:11-12)፡፡

1. በፍሊስጥያ ደሴቶች እና የበህር ዳር ቦታዎች፣ ቁ 10
2. ግብጽ፣ ቁ 11
3. አሦር፣ ቁ 11

**11:11 " ይመጣሉ ...... ከግብጽ...... ከአሶር ምድር"** ብዙ አይሁዳዊያን በባብሎን ወረራ እና ምርኮ ጊዜ ወደ ግብጻዊያን ኮብልለው ነበር፡፡ እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ቤት ይመልሳል!

▣ **"በቤታቸውም አኖራቸዋለሁ"** ይህ በዘዳግ 27 እና 28 ላይ ላለው የመርገም እና በረከት ተስፋ ማጣቀሻ ናው፡፡

## ሆሴዕ: 11:12

**12 ኤፍሬም በሐሰት፥ የእስራኤልም ቤት በተንኰል ከበበኝ ይሁዳም ከታመነው ቅዱሱ ከእግዚአብሔር ጋር አይጸናም።**

**11:12 ማሶሬቲክ መጽሐፍ ቅዱስ** (Massoretic Text) ቁ 12 ን ከምዕራፍ 12 ጋር ያስቀምጣል፡፡ አውዱ ይህንን ያረጋግጣል! የቁ 12 የመጨረሻ ሐረግ ከሙሉ መጽሐፉ ማዕከላዊ ሐሳብ አንዱ ነው (6:6፤ 8:7)፡፡ የእግዚአብሔርን ታማኝነት እና የእስራኤልን እምነት አልባነትን ያተኩራል፡፡ ይህ ሁኔታዊ ባልሆነው(የእግዚአብሔር ባህሪይ) እና ሁነታዊ በሆነው(የሰው መታዘዝ) መካከል ያለው ውጥረት ነው፡፡

▣ **"ኤፍሬም በሐሰት፥ ከበበኝ" ግሱ** (BDB 685፣ KB 738፣ *Qal* PERFECT) በ7:2 ውስጥ ጥቅም ላይ ውሏል፣ የእስራኤል ክፉ ድርጊት እነርሱን ስከባቸው፡፡
የእስራኤል ሐሰት ሊሆን የሚችለው (7:13)

1. ኪዳንን መቃወም (የተሻሩ ተስፋዎች)
2. ፖለቲካዊ ምክር (የውጭ ቡድን፣ 7:3)
3. የእምነት መለኮታዊነት(የጣዖት ካህነት)
4. የሐሰት ነብያት(ብልጽግና እና ደህንነት)
5. ስለ ያህዌ የሐሰት ዘገባ

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"ይሁዳም ከእግዚአብሔር ጋር አይጸናም"** |
| **NKJV፣ NRSV** | **"ይሁዳ አሁንም ከእግዚአብሔር ጋር እየሄደ ነው"** |
| **TEV** | **"የይሁዳ ሕዝብ አሁንም እግዚአብሔርን እየተቃወመ ነው"** |
| **NJB** | **"(ይሁዳ ግን አሁንም የእግዚአብሔር ወገን ነው)"** |

እብራይስጡ አሻሚ ነው፡፡ ጥያቄ የሚሆነው፣ " ሁለቱ የመጨረሻ የግጥም መስመሮች ተመሳሳይ ናቸው ወይስ ተቃራኒ?" ይሁዳ ከሐጥኃተኛዋ እስራአል ጋር ተፃራሪ ናት ወይስ ይሁዳ እና እስራኤል ከቅዱስ እግዚአብሔር ጋር ተፃራሪ ናቻው? አንዳንድ የመጽህፍ ቅዱስ አዋቂዎች ግሱን"መንከራተት" ወይም "መዞር" (BDB 923፣ ለምሳሌ ፣ *Hiphil*፡ ዘፍጥ 27:40፤ *Qal*፡ ኤርም 2:31)፤ ሌሎች የሚያዩት (BDB 921፣ *Qal*፡ እሳ 14:2፤ ሕዝቁ 34:4፤ *Hiphil*፡ እሳ 41:2)፡፡

### የውይይት ጥያዌዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. የብሉይ ኪዳን ምርጫዎችን ተርጉም እና አንራራ፡፡
2. እግዚአብሔር ለምን እንደ ባል እና ቤተሰብ ተገለጸ?
3. ለምን በብሉይ ኪዳን ሁሉ ውስጥ የፖለትካ ቡድኖች ተኮነኑ?

# ሆሴዕ 12
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|
| የእግዚአብሔር ቁጣ በይሁዳ ኃጢአት ላይ | | እስራኤልና ይሁዳ ተከሰሱ | የእስራኤል ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ እልከኝነት |
| | | 11:12-12:6 | |
| 11:12-12:8 | አመፅ እና ተሀድሶ | | |
| | (12:1-14:9) | | |
| | | | 12:1-2 |
| | 12:1 | | |
| | 12:2-6 | | |
| | | | በያዕቆብና በኤፍሬም ላይ |
| | | ተጨማሪ የፍርድ ቃላት | 12፡3-9 |
| | | 12፡7-9 | |
| | 12፡7-9 | | |
| 12:9-14 | | | እርቅ |
| | | 12:10-11 | 12:10-11 |
| | 12:10-14 | | |
| | | | አዲስ ማስፈራራት |
| | | | 12:10-14 |
| | | 12:10-14 | |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ vii ተመልከት)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**ሆሴዕ: 12:1-11**

**1 ኤፍሬም ነፋስን ይበላል፥ የምሥራቅንም ነፋስ ይከተላል ሁልጊዜም ሐሰትንና ተንኰልን ያበዛል**
**ከአሦር ጋር ቃል ኪዳን ያደርጋሉ፥ ወደ ግብጽም ዘይት ይወስዳሉ።**
**2 እግዚአብሔርም ደግሞ ከይሁዳ ጋር ክርክር አለው፥**
**ያዕቆብንም እንደ መንገዱ ይቀጣል እንደ ሥራውም ይመልስለታል።**
**በማኅፀን ውስጥ ወንድሙን በተረከዙ ያዘው፥ በጒልማስነቱም ጊዜ ከአምላክ ጋር ታገለ፡**
**ከመልአኩም ጋር ታግሎ አሸነፈ አልቅሶም ለመነው። በቤቴልም አገኘው፥ በዚያም ከእኛ ጋር ተነጋገረ።**

**እርሱም የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር ነው የመታሰቢያው ስም እግዚአብሔር ነው።**
**6 ስለዚህ ወደ አምላክህ ተመለስ ምሕረትንና ፍርድን ጠብቅ፥ ዘወትርም በአምላክህ ታመን።**
**7 ከከነዓን ወገን ነው በእጁ የተንኰል ሚዛን አለ፥ ሽንገላንም ይወድዳል።**
**8 ኤፍሬምም። ባለ ጠጋ ሆኜአለሁ፥ ሀብትንም አግኝቻለሁ፥ በድካሜም ሁሉ ኃጢአት የሚሆን በደል አይገኝብኝም አለ።**
**9 እኔም ከግብጽ ጀምሬ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ እንደ ዓመት በዓል ቀን እንደ ገና በድንኳን እንድትኖር አደርግሃለሁ።**
**10 ለነቢያትም ተናግሬአለሁ፥ ራእይንም አብዝቻለሁ በነቢያትም እጅ ምሳሌዎችን አውጥቻለሁ።**
**11 ኃጢአት በገለዓድ አለ ፈጽመው ከንቱ ናቸው ወይፈኖች በጌልገላ ይሠዋሉ፥**
**መሠዊያዎቻቸውም በእርሻ ትልም ላይ የድንጋይ ክምር ይሆናሉ።**

**12:1 "ይበላል… ይከተላል"** እነዚህ ሁከቱም ግሶች፣ ቀጣይነት ያለውን ድርጊት የሚናገሩ VERBS are Qal ACTIVE PARTICIPLES ናቸው፡፡

▣ **"ነፋስ"** "ነፋስ" (BDB 924) በግርከም ሆነ በእብራይስጥ "ባዶነትን" ወይም "ከንቱነትን" ቃል ነው(ለምሳሌ ፣ ኢዮ 7:7፤ Eccl፡፡ 1:14፣17፤ እሳ 41:29) እንደዚሁም "መንፈስ፣" "ንፋስ፣" ወይም "እስትንፋስ፡፡" እስራኤል በውጭ ኃይሎች ራሷን ለመከላከል የሚታደርገውን ሙከራን ያሳያል(ግብጽ በ II ነገስ 17:4)፡፡

▣ **"የምስራቅ ነፋስ"** ይህ ምናልባት እስራኤል ከአሦር ጋር ያላትን ቀጣይ የፖለትካ ጥገኝነትን የሚያሳይ ምሳሌ ነው(5:13፤ 7:11፤ 8:9፤ 13:15፤ II ነገስ 17:3)፡፡ ይሁን እንጂ፣ በጥሬው እፁአትን የሚያጠፋ የሲራኮ በረሃ ንፋስን( sirocco desert winds) የሚያመለክት እና፣ ስለዚህ፣ የወረራ ምሳሌ ነው (እሳ 27:8)፡፡ በ ኤርም 18:17 እና ሕዝቄ 17:10፤ 19:12፤ 27:26 የባብሎዊያን ወረራን ያመለክታል፡፡

▣ **"ሐሰትንና ተንኰልን ያበዛል"** የእስራኤል ሐሰት የተለመደ ጉዳይ ነው (12:12)፡፡ በ 7:13 ላይ ያለውን ማስጣወሻ ተመልከት፡፡ **"ያበዛል፣"** የሚለው ቃል በሆሴዕ ውስጥ በሂፊል ቅርፅ( *Hiphil* form) ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

1. ወርቅ እና አልማዝን ያበዛል፣ 2:8
2. ለኃጢአት መስዊያን ያበዛል፣ 8:11
3. አዳድስ ከተማዎችን ያበዛል፣ 8:14
4. ብዙ መስዊያ፣ 10:1
5. የበዛ ሐሰት እና ተንኮል፣ 12:1
6. የበዛ ራእይ፣ 12:10

የበዛ የእግዚአብሔር ስጦታዎች(#1፣ #6) ከበዛ የእስራኤል ኃጢአት ጋር ኣቻ ነው!

▣ **"ቃል ኪዳን ያደርጋሉ"** The VERB "ያደርጋል" የሚለው ግስ "ለማቁረጥ" ነው(BDB 503፣ KB 500፣ *Qal* IMPERFECT)፡፡ በመጀመርያ ቃል ኪዳን የሚደረገው እንስሳትን በሁለት ቦታ በቁረጥ እና ቃል የሚገቡ ሰዎች ደግሞ በመካከሉ ያልፋሉ(ዘፍጥ 15:17)፡፡ ምናልባት "ቃል ኪዳን" የሚለው የእብራይስጡ ቃል የመጀመርያ ትርጉሙ ሆኖ የነበረው(BDB 136) "መቁረጥ" ነው፡፡

▣ **"ከአሦር ጋር"** እስራኤል መጀመርያ ላይ አሦርን ለመቃወም ሞክራ ነበር፣ በኃላ ለይ ግን ከእርሷ ጋር የፖለትካ ስሚምነት ለማድረግ አሰበች(II ነገስ 17:3-6)፡፡

▣ **"ወደ ግብጽም ዘይት ይወስዳሉ"** እስራኤል አሦርን ለመቃወም(II ነገስ 17:4) ስትል ከግብጽ የፖለትካ ጥገኛ ለመሆን ወደ ግብጽ የዘይት( በእስራኤል ውስጥ የተለመደ ነው፣ ዘዳግ 8:8፣ በግብጽ ውስጥ ግን አይደለም) ስጦታን ትልካለች፡፡

**12:2 "ክርክር"** የሚለው ቃል (BDB 936) ሕጋዊ አቤቱታ ማለት ነው(2:2፤ 4:14፤ ዘዳግ 25:1፤ II ሳሙ 15:2፣4፤ ሚክያ 6:2፤ 7:9)፡፡ ሁለቱም ይሁዳ እና ያእቆብ ደስተኞች አይደሉም(4:9b)፡፡ አትታለሉ፣ እግዚአብሔር የሚዘበትበት አይደለም፤ ሰው የዘራውን ሁሉ፣ ያንኑ ያጨዳልና(8:7፤ 10:12-13፤ ኢዮ 4:8፤ መዝ 126:5፤ ምሳ 11:18፤ 22:8-9፤ II ቆሮ 9:6፤ ገላቲ 6:7)፡፡ ይህ ለይዳ እየተባለ ያለው አሉታዊ ሐሳብ አውዱ በ11:12ሐ ውስጥ ከተገለጸው "አሉታዊ" (?) ጋር ይገናኛል፡፡

**12:3-4** ይህ በእስራኤል እና በያዕቆብ ስሞች ላይ ያለው ጨወታ ነው፡፡ "ያዕቆብ" በዘፍጥ 25:26 ውስጥ፣ "ወንድሙን በተረከዙ የያዘው ተብሎ" ተገልጾአል፡፡ ቃሉ "የሚተካ፣" " የሚቆጣጠር" ወይም "አታላይ" (BDB 784) ሊሆንም ይችላል፡፡
"እስራኤል" የሚለው ቃል በዘፍጥ 32:28 ውስጥ "ከእግዚአብሔር ጋር የሚታገል" ተብሎ ተገልጾአል፡፡
ቤት-ኤል ያዕቆብ ወይም እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር የተገባኘበት ልዩ ቅዱስ ሥፍራ ነው፡፡ አሁን ግን እስራኤል በተለይ ክፉ ወደ ሆነው ወደ ጣዖት ሥፍራ ተመልሷል፡፡

▣ **"ከእግዚአብሔር ጋር ታገለ......... ከመላአክ ጋር የታገለ እነዚህ ይመሳሰላሉ"** የእግዚአብሔር መላአክ እንደ እግዚአብሔር ማንነት እና አካል ይታያል(ዘፍጥ 16:7-13፤ 22:11-15፤ 24:7፣40፣31:11፣13፤ 48:15-16፤ ዘፀአ 3:2፣4፤ 13:21፤ 14:19፤ መሳ 2:1፤ 6:22-23፤ 13:3-32፤ ዘካ 3:1-2)፡፡

**12:5 "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር"** ይህ ቁጥር ለእስራኤል አምላክ ሦስት ስሞች አሉት፡፡ ይህ ለሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር መግለጫ ነው ማለትም (1) "የሰማይ ሠራዊት መሪ/አዛዢ"፤ (2) the "የሳማያዊ ጉባኤ ሰብሳቢ/ ዋና" (BDB 838፣ ለምሳሌ ፣ II ሳሙ 5:10)፤ ወይም (3) በባብሎናዊያን የኳክብት አምልኮ አውድ በሕይወታቸው ላይ ተጽዕኖ ሊያመጣ የሚችለው የበላይ የሆነ ኃይል፣ የሰማ ኳክብቶችን ያመለክታል፡፡ ይህ ድህረ-ምርኮ ላሉት መጽሐፍቶች የተለመደ ስም ነው (አሞ 3:13፤ 6:14፤ and 9:5)፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት: : በአሞ 1:2 ላይ ያለውን የመለኮት ስሞች፡፡

▣ **"የመታሰብያው ስም እግዚአብሔር ነው"** ይህ በቀጥታ/ በትሬው"መታሰብያው" (BDB 271) ማለት ነው፡፡ ስሞች የባሕርይን ማንነት የሚያሳዩ እና የሚገለጹ ናቸው(ለምሳሌ ፣ መዝ 135:13)፡፡ ይህ በዘፀአ 3:14 ውስጥ ለሙሴ የተገለጠውን የያህዌን ስም ይገልጻል፡፡ ከዚህ ጊዜ በፊት የነበሩ አባቶች እግዚአብሔርን ኤል-ሻዳይ(*El Shaddai)* (ዘፀአ 6:2-3) ብሎ ይጠሩታል፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት: :በአሞ 1:2 ላይ ያለውን የመለኮት ስም፡፡

**12:6 አሁንም ለንስዐ የሚደረግ ጥሪ**("ተመለሱ" BDB 996፣ KB 1427፣ *Qal* IMPERFECT፣ but functioning as a JUSSIVE)፡፡ አሁንም እነዚህ ልዩ የሆኑ ቃሎች ዳግም ይታያሉ(2:19፤ 4:1፤ 6:6፤ 10:12፤ አሞ 5:24፤ ሚክያ 6:8)፡፡
እግዚአብሔርን ማወቅ ባህሪይውን የሚያንፀባርቅ የሕይወት ለውጥ ማምጣት አለበት!

▣ "ፈልግ......... ጠብቅ" እነዚህ ሁለቱ ትዕዛዛዊ ናቸው፡

1. ፈልግ/ተመልከት፣ BDB 1036፣ KB 1501፣ ትዕዛዛዊ ቃአል (*Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)* )
2. ጠብቅ፣ BDB 875፣ KB 1082፣ትዕዛዛዊ ፔይል(*Piel* ትዕዛዝ አንቀፅ) (ሰቆ 3:25፤ ሚኪያ 7:7)፡፡

**12:7 "ነጋዴ" ይህ ከናዓንን ሰው የሚያመለክት ቃል ነው** (BDB 488 II፣ እሳ 23:8፤ ሕዝቁ 16:29፤ 17:4)፡፡ ይህ የሰርካዝም(sarcasm) ማንራርያ የሚሆን ይመስላል፡፡ ቃሉ ሊሆን የሚችለው ወይ አንድ የጎሣ ቡድን ወይንም አንድ ነጋዴ ነው፡፡ እስራኤላዊያን እንደ ከነዓናዊያን ያደርጋሉ(ማለትም፣ "የውሸት ሚዛን፣" ምሳ 11:1፤ 20:23፤ አሞ 8:5)፡፡

▣ **"ሽንገላንም ይወዳል" ይህ ግስ** (BDB 798፣ KB 897፣ *Qal* INFINITIVE CONSTRUCT)በዘዳግ 24:14 ውስጥ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ድህውን መጨቆን/መሽንገል አልተፈቀደም (ምሳ 14:31፤ 22:16፤ አሞ 4:1፤ ኤርም 7:6፤ ሕዝቁ 22:29፤ ዘካ 7:10)፡፡ ይህ የቁ 6 ተቃራኒ ነው! ይህ ቃል እስራኤል የተሳሳተውን ነገር ተወዳለች በሚል በአሉታዊ መልኩ ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል (4:17-18፤ 10:11፤ 12:7፤ አሞ 4:4-5፤ ሚኪያ 3:1-2)፡፡

**12:8 እስራኤል ታማኝነት በጎደለው መልኩ ያገኘችው ሀብት እንደሚያድናት ታስባለች** (8:14)፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"በደል አይገኝብኝም፣ ኃጢአት ሊሆንብን የሚችል"** |
| **NKJV** | **"ኃጢአት የሚሆንብኝን በደል በእኔ ውስጥ አያገኙም"** |
| **NRSV** | **"ኃጢአት ሊሆንብኝ የሚችል ተቃውሞ አይገኝብኝም"** |
| **TEV** | **"ታማኝነት በጎደለው መንገድ ሃብታም በመሆን ማንም ሊከሰን አይችልም"** |
| **NJB** | **"ዳሩ ግን ከበደሉ የመጣበት ኃጢአት የተነሣ ካገኛቸው በሙሉ ምንም አይቀርለትም"** |

የሰባ ሊቃናት ትርጉም( Septuagint) መጽሐፍ ቅዱስ የእብራይስጥ MSS በመከተል ደግሞ ይተረጉመዋል፣ "ከፈጸመው ኃጢአት የተነሣ ማናቸውም ሥራዎቹ ቀርቶ ሊገኙ አይችሉም፣" የነብዩ ወይንም የሕግ ጠበቃ ክስ ሊሆን ይችላል፡፡
እስራኤል ተመልሳ በደል እንደማይገኝባት ቃል መግባቷን ማሶሬቲኩ ላይ የሚገኝ ከሆነ፡፡

**12:9 "እኔም ከግብጽ ጀምሬ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ"** ይህ ሙሉ የእስራኤል አምላክ የቃል ኪዳን ስም ነው(ቁ 5፤ ዘፀአ 20:2)፡፡

▣ **"እንደ ዓመት በዓል ቀን እንደ ገና በድንኳን እንድትኖር አደርግሃለሁ"** ይህ ሁለት የሚቃረኑ ትርጉሞችን ያመለክታል: (1) የምድረ በዳ ጊዜ በእስራኤል እና በእግዚአብሔር መከከል እንደ ፍጹም ጊዜ ይታይ ነበር፣ (2:14፤ 9:10፤ 11:1-4፤ ኤርም 2:2፤ አሞ 2:10 ) ወይም (2) በአሉታዊ መልኩ በቦዝ በዓል(Feast of Booths) አይሁድ ቋሚ ባልሆነ ቤት ውስጥ ሲኖር ( ሌዋ 23:42-44)፣ እግዚአብሔር በራሱ ውሳኔ ቋሚ ባልሆነ ቤት ውስጥ በቋሚነት እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል(የ 8:14 ተቃራኒ)፡፡ የሚቀርበው አውድ ሁለተኛው አማራጭ ነው(ማለትም፣ ቁ 8)፡፡

**12:10 "ተናግራሀለው" ይህ ቁጥር ያህዌ በትክክል በነብያት በኩል ራሱን እና ፈቃዱን ለእስራኤል እንደ ገለጸ ይናገራል** (6:5)፡፡ ይህንን ያደረገው በራእይ እና በምሳሌ ነው፡፡ ቀደም ብሎ በሙሴ ሕጎች በኩል ራሱን ገልጦ ነበር(ማለትም፣ የሙሴ መጽሐፍቶች፣ 4:6፤ 8:1፣11)፡፡

ነብያት የቃል ኪዳን መካከለኛ ነበሩ፡፡ ተጨማሪ መስፈርቶችን አያመጡም፣ ዳሩ ግን የሕዝቡን አስተሳሰብ ወደ ጥንቱ ኪዳን ይመልሱታል(ማለትም፣ አንርሃም፣ የእምነት አባቶች፣ ሙሴ፣ ዳዊት)፡፡ የቃል ኪዳኑን የአፈጻጸም ሁኔታዎች እና ስሜቱን ይከታተላሉ፡፡ ቀደም ብሎ ከእግዚአብሔር የተሰጡ መንገዶችንና የአሁኑን አተገባበር እና አስፈለግነተን ያያሉ፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **NASB፣ NJB** | **"ምሳሌዎች"** |
| **NKJV** | **"ምልክቶች"** |
| **NRSV** | **"ጥፋት"** |
| **TEV** | **"ማስጠንቀቅያ"** |

ምናልባት ይህ ለእዩሱስ ምሳሌዎች የብሉይ ኪዳን ዳራ ነው(BDB 197 I)፡፡ አውዱ እና ትኩረቱ በእስራኤል ሕይወት ውስጥ የእግዚአብሔር ወቅታዊ ራእይ ላይ ነው፣ ዳሩ ግን አይሰሙም ነበር(እሳ 6:9-13)፡፡ ምሳሌ እምነትን በማብራት አለማመንን ደግሞ ግራ ያጋባል(Mark 4:10-12)፡፡ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች የሚያስቡት የእብራይስጡ "የሞት አባባሎች" ማለት (BDB 198 II፣ 4:5፣6፤ 10:7፣15[ሁለት ጊዜ]፤ NRSV፣ TEV)፡፡

**12:11**
NASB፣ NRSV፣
NJB **"በደል"**
NKJV፣ TEV ***"ጣዖታት"***

*ይህ awen የሚለው ቃል ነው ፣ ሊሆን የሚችለው "አስቸጋር፣" "ሐዘን፣" "ክፋት፣" ወይም "ጣዖት አምልኮ፡፡"* በቀጣይ መስመር ላይ የሚገኘው ተመሳሳይ፣ "የማይጠቅም" (BDB 996)፣ የሚለው ሁለቱም ጣዖት አምልኮ እንደሆነ ያሳያል(የከነዓናዊያን ፍሬያማ የጣዖት አምልኮ)፡፡

▣ **"ጌልገላ"** እንደዚሁም 6:8-9፡፡

▣
NASB፣ NKJV፣
NRSV፣ TEV **"ኮርማዎችን ይሰዋሉ"**
NJB **"ለኮርማዎች ይሰዋሉ"**

ምናልባት ጥሩ መረዳት የሚሆነው "ለኮርማዎች" (ማለትም፣ የወርቅ ጥጃ ምሳሌዎች)፡፡

▣ **"ጌልገላ... የድንጋዮች ክምር"** ይህ "ጌልገላ፣" በሚለው ቃል የሚዞር ነው ማለትም "የድንጋዮች ክምር" (BDB 166)፡፡ በእነዚህ ቃላቶች መካከል ታስቦ የሚዞር "ገለዓድ፣" "ጌልገላ፣" እና "የድንጋይ ክምሮች"።

ከእስራኤል አመፅ የተነሣ፣ እነዚህ ቅዱስ ሥፍራዎች እግዚአብሔርን የሚያስታውስ መሆኑ ቀርቶ ወደ ድንጋዮች ክምር እና (ማለትም፣ የበአል ምሶሶዎች) ወደ ታረሰ መሬት ተለወጠ!

## *ሆሴዕ*: 12:12-14

[12] **ያዕቆብ ወደ ሶርያ አገር ሸሸ፥ እስራኤልም ስለ ሚስት አገለገለ፥ ስለ ሚስትም ጠባቂ ነበረ።**
[13] **እግዚአብሔርም በነቢይ እጅ እስራኤልን ከግብጽ አወጣ፥ በነቢይም እጅ ጠበቀው።**
[14] **ኤፍሬም አስመርሮ አስቈጣው ስለዚህ ደሙ በላዩ ላይ ነው ጌታውም ስድቡን በራሱ ላይ ይመልሳል።**

**12:12 "ያዕቆብ"** ይህ ከቁ 4-6 ጋር የሚያይዝ ይመስላል፣ ከያዕቆብ ታርካዊ ሕይወት ጋር የሚያይዝ(ማለትም፣ እስራኤል፣ ዘፍጥ 28-30)፡፡

**12:13 "እግዚአብሔርም በነቢይ እጅ እስራኤልን ከግብጽ አወጣ፥"** ይህ ሙሴን የሚያመለክት ነው(ዘዳግ 18:15፤ 34:10)፡፡

**12:14 የእስራኤል ሕዝብ እንደ እስራኤል እየሰራ አይደለም፣** ዳሩ ግን እንደ ያዕቆብ የሐጥኃቷን ውጤት ታገኛለች፡፡ የኃጢአት በደል ምናልባት የሕፃናት መስዋይት ወይንም ግድያን ያመለክታል (ማለትም፣ ለሞሌክ)፡፡

# ሆሴዕ 13

## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|
| የማይቋረጥ ፍርድ በእስራኤል ላይ | አመፅ እና ተሀድሶ<br>(12:1-14:9) | እስራኤል ላይ የመጨረሻ ፍርድ | የጣዖት አምልኮ ተቀጣ |
| 13:1-3 | 13:1-3 | 13:1-3 | 13:1-3 |
| | | | ቅጣት ስለውለታ ቢሲነት |
| 13:4-8 | 13:4-13 | 13:4-8 | 13:4-8 |
| | | | የንጉሳዊ አገዛዝ ፍጻሜ |
| 13:9-11 | | 13:9-11 | 13:9-11 |
| | | | የጥፋት አይቀሬነት |
| 13:12-14 | | 13:12-16 | 13:12-14:1 |
| | 13:14-16 | | |
| 13:15-16 | | | |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ vii ተመልከት)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. *የመጀመሪያው አንቀጽ*
2. *ሁለተኛው አንቀጽ*
3. *ሦስተኛ አንቀጽ*
4. *ወዘተርፈ*

## የቃልና የሐረግ ጥናት

### ሆሴዕ: 13:1-3

**1 ኤፍሬም በተናገረ ጊዜ ፍርሃት ነበረ፥ በእስራኤልም ዘንድ ታበየ ነገር ግን በኣልን በማምለክ በበደለ ጊዜ ሞተ፡፡**
**2 አሁንም ኃጢአትን ይሠሩ ዘንድ ጨመሩ በብራቸውም ለራሳቸው ቀልጠ የተሠራ ምስልን፥ እንደ ጥበባቸውም ጣዖታትን ሠርተዋል ሁሉም የሠራተኛ ሥራ ናቸው። ስለ እርሱም፡- የሚሠዉ ሰዎች እምቦሳውን ይሳሙ ይላሉ!" 3 ስለዚህም እንደ ማለዳ ደመና፥ በጥዋትም እንደሚያልፍ ጠል፥ በዐውሎ ነፍስም ከአውድማ እንደሚበተን እብቅ፥ ከመስኮትም እንደሚወጣ ጢስ ይሆናሉ፡፡**

**13:1 "ኤፍሬም በተናገረ ጊዜ ፍርሃት ነበረ፥"** ሁለት ዓይነት የዚህ ቁጥር አረዳድ አለ፡፡

ይህ"ለኤፍሬም" ያልተለመደ አጠቃቀም ነው ምክንያቱም አጠቃለይ የደቡቡን ጎሣ የሚያመለክት አይደለም፣ ዳሩ ግን ("ራሱን ከፍ ከፍ አደረገ፣" BDB 669፣ KB 724፣ *Qal* PERFECT) የዛኛ ብቻኛ ጎሳ እብሪዕተኝነት ነው(ለምሳሌ ፣ መሳ 8:1፤ 12:1)፡፡ የዚህ ጎሳ ፍርሃት የመታየው እርሱ ሲናገር፣ ሌሎች ጎሣዎች "ይፈራሉ" (BDB 958)፡፡ የዮሴፍ ልጆች ከመሆናቸው የተነሣ ኤፍሬም እና ሚናሴ ግማሽ ጎሣ መሆናቸውን አትርሳ(ዘፍጥ 48)፣ ዳሩ ግን ትልቁን ጎሰ ይወክላሉ፣ በመልካዓ ምድራውም ሆነ በቁጥር፡፡
ሁለተኛው አማራጭ ለሰማርያ ዋና ከተማ መሪዎች እና ነገስታት የሚቆም ነው፡፡ የኢዩሩሳሌም ቤተ መቅደስ ተቀናቃኝ እንዲሆን የመጀመርያውን የወርቅ ጥጃዎችን ያቆመው እርሱ ነበር (1 ነገስ 16:31)፡፡ የበአልን አምልኮ ወደ እስራኤል ያመጡ አሃብ እና ኤልዛቤል ነበሩ(1 ነገስ 16:31)፡፡

▣ **"በአል"** ይህ የከነዓናዊያን ተባታይ የጣዖት አምልኮን ያሳያል፡፡ ለእጅግ በጣም ጥሩ ማብራርያ William Foxwell Albright's book፣ *Archaeology and the Religion of Israel*፣ ገጽ 72ff ተመልከት፡፡

▣ **"በበደለ ጊዜ ሞተ"** ይህ እያለቀ ያለውን የጎሳ ኃይል እና የበላይነትን ያሳያል ("ሞተ" BDB 559፣ KB 562፣ *Qal* IMPERFECT፣ የእግዚአብሔር ፍርድ ምሳሌ ሆኖ ያገለግላል፣ ለምሳሌ ፣ የሞአብን በአሞ 2:2 ውስጥ፤ የእስራኤለን በሕዝቁ 18:31 ውስጥ)፡፡

**13:2 "ቀልጦ የተሠራ ምስልን፥ ......... ጣዖታትን"** ይህ ምናልባት የቤትኤልን እና የዳን የወርቅ ጥጃን ያመለክታል(መስመር 5)፡፡ እሁን እንጂ፣ እነዚህ ማብራርያዎች በትክክል አይመትኗቸውም፡፡ ከእንጨት የተሠሩ እና በወርቅ የተቀቡ ናቸው፡፡ ስለዚህ፣ ይህ በበአል መታሰብያ ሥፍራዎች ያሉትን ምስሎችን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል(2:8፤ እሳ 46:6፤ ኤርም 10:4)፡፡

▣ **"የሚሠዉ ሰዎች እምቦሳውን ይሳሙ ይላሉ"** ጣዖትን መሳም የበአል አምልኮ አካል እንደሆነ ከ1 ነገስ 19:18 እና ኢዮ 31:27 እንማራለን(ግሱ ያልተፈጸመ ሊሆን ይችላል ወይም a JUSSIVE፣ NASB)፡፡ ይህ ለያህዌ የታሰበ አምልኮ እንዴት የበአል አምልኮ በሆነው የወርቅ ጥጃ እንደተበላሸ ምሳሌ ነው፡፡ የማያይ፣ የማይሰማ፣ እና የማይሰራ በራሳቸው የሠሩትን አመለኩ!

**13:3 እስራኤልን በመተላለፏ እና በአመጹዋ ውስጥ የሚጹገልጹአት፣ በቶሎ ሊፈራጁ እና ሊጠፉ የሚገባቸው አረት ጉዳዮች አሉ**: የማለዳ ዳመና፣ ጠል፣ እብቅ፣ እና ጢስ፡፡

▣ **"ቀዳዳ"** ይህ በጥሬው"መስኮት" (BDB 70) ነው፡፡ መስኮት በጥንቱ ዓለም አልነበረም፡፡ ሕንፃዎቹ በጣራው ሥር ለጢስ ማውጫ አላማ ትንንሽ መስኮቶች/ቀዳዳዎች ነበሯቸው፡፡ ብዙ ቤቶች እሳትን መሃል በማድረግ ጢሱ በሚመቼው ቃዳዳ እንዲወጣ ያረጉታል፡፡

## ሆሴዕ: 13:4-8

**4 እኔ ግን ከግብጽ ምድር ጀምሬ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ አታውቅም፥ ከእኔም በቀር ሌላ መድኃኒት የለም። 5 በምድረ በዳ፥ እጅግ በደረቀ ምድር አውቄህ ነበር። 6 ከተሰማሩ በኋላ ጠገቡ፥ በጠገቡም ጊዜ ልባቸው ታበየ ስለዚህ ረሱኝ።**
**7 ስለዚህም እኔ እንደ አንበሳ ሆንሁባቸው፥ እንደ ነብርም በመንገድ አጠገብ አደባባቸዋለሁ፡፡**
**8 ልጅዋ እንደ ተነጠቀባት ድብ እገጥማቸዋለሁ፥ የልባቸውንም ስብ እቀድዳለሁ በዚያም እንደ አንበሳ እበላቸዋለሁ፥ የምድረ በዳም አውሬ ይነጣጠቃቸዋል።**

**13:4 "እኔ ግን ከግብጽ ምድር ጀምሬ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ"** ይህ እንዴት ያህዌ አሥርቱ ትእዛዞቹን እንዳስታወቀ ነው ዘፀአ 20:2፤ ዘዳግ 5:6)፡፡ ይህ አሁንም በእግዚአብሔር እና በእስራኤል መካከል ለዘዳግም እንደ ስምምነት እና የጋብቻ ጊዜ ነው (ቁ 5፤ 2:14፤ 9:10፤ 12:9)፡፡

▣ **"ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ አታውቅም፥"** ይህ ሐረግ ከአሥርቱ ትዕዛዛት ነው(ዘፀአ 20:3፤ ዘዳግ 5:7)፡፡ ግሱ (BDB 393፣ KB 390፣ *Qal* IMPERFECT) ቅርበትን፣ ግል ግኑኝነትን ያሳያል (BDB 446፣ KB 448፣ *Hiphil* PARTICIPLES፣ ለምሳሌ ፣ እሳ 43:3፤ 11:14፤ 45:15፣21-22፤ 63:8)፡፡

▣ **"ከእኔም በቀር ሌላ መድኃኒት የለም"** ያህዌ አንዱ እና ብቻኛው አዳኝ ነው (BDB 446፣ KB 448፣ *Hiphil* PARTICIPLE፣ ለምሳሌ ፣ እሳ 43:3፣11፣14፤ 45:15፣21-22፤ 63:8)፡፡

**13:5 " በምድረ በዳ፥ አውቄህ ነበር"** ግሱ (BDB 393፣ KB 390፣ *Qal* PERFECT) በጥሬው "ማወቅ" (ማለትም፣ ለያህዌ እውቅና ተመረጠ እና የተሰጠ ትርጉም)፡፡ ለእስራኤል የተደረገ ለየት ያለ የእግዚአብሔር ጥንቃቄ ፍቅሩን ያሳያል (ዘዳግ 32:10)፡፡
የጥንቱ የግርክ እና የሦርያ ትርጉም "መመገብ" (BDB 944) "ጥንቃቄ" ከሚለው ይልቅ፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **NASB፣ NRSV** | **"በደረቅ ምድር"** |
| **NKJV** | **"በከባድ ደረቅ ምድር"** |
| **TEV** | **"የበረሃ ምድር"** |
| **NJB** | **"በአሳቃቅ ደረቅ ምድር"** |

ይህ አወቃቀር ማለት "ኃይለኛ ሙቀት እና ድርቅ" በምድረ በዳው መንከራተት ጊዜ የያህዌን መለኮታዊ ውሃ አቅርቦት መግለጫ ነው (ለምሳሌ ፣ ዘፀአ 15:22-26፤ 17:1-7፤ ዘኁ 20:2-13፤21:16)፡፡

**13:6** ምን ዓይነት የሚያሳዝን ነው! የእግዚአብሔር በረከቶች ("ጠገቡ" [ሁለት ጊዜ] BDB 959፣ KB 1302፣ የመጀመርያው ያልተፈጸመ ቃአል ሲሆን/*Qal* IMPERFECT/ እና ሁለተኛው የተፈጸመ ቃአል/*Qal* PERFECT/ ነው) ወደ ግላዊ መመኪያ እና መንፈሳዊ ውፍረት ተቀየሩ (ዘዳግ 6:10-12፤ 8:11- 20፤ 32:13-15)።

▣ **"ስለዚህ ረሱኝ"** የሚያሳዝን ነው። ውጫዊውን በመውሰድ፣ ዋጋ ያለውን ግን አጡ—ብቻኛ ከሆነው ፈጣሪ እና አዳኝ አምላክ ጋር ግላዊ የሆነ ግንኙነት(2:13፤ 4:6፤ ፤8:14፤ ዘዳግ 8:14፤ 31:16፣20፤ 32:15፣18፤ Jdgs። 10:6)።

**13:7-8** እነዚህ ዱር አራዊት ለእግዚአብሔር ፍርድ እንደ ምሳሌ ናቸው: አንበሳ፣ ነብር፣ ድብ፣ እና አናብስት(ለምሳሌ ፣ ኤርም 2:15፤ 4:7፤ 5:6፤ መዝ 7:2፤ 50:22)። ይህ የእንስሳት ጥቃት ቁ 6 ላይ ያለውን የእረኝነት መግለጫን ይፃረራል።

## *ሆሴዕ*: 13:9-11

**9 እስራኤል ሆይ፥ በእኔ በረዳትህ ላይ በመነሣትህ ጥፋትህ ነው። 10 በየከተማህ ሁሉ ያድንህ ዘንድ ንጉሥህ ወዴት አለ? ስለ እርሱም፡- ንጉሥንና አለቆችን ስጠኝ ብለህ የተናገርኸው መሳፍንቶችህ ወዴት አሉ? 11 በቍጣዬ ንጉሥን ሰጠሁህ፥ በመዓቴም ሻርሁት።**

**13:9 "በእኔ በረዳትህ ላይ በመነሣትህ"** ምን የሚያሳዝን ነው! እስራኤል ብቻኛ ረዳቷን ረሳች(ለምሳሌ ፣ ኤርም 2:17፣19)። የግርክ እና የሦርያ ትርጉሞች፣ "እንግዲህ ማን ይረዳሻል?" የሚል አለው።

**13:10-11** ይህ ሆሴዕ ስለ ንጉስ ነገስታት ለነበረው አሉታዊ አመለካከት ጋር የሚመሳሰል ሌላው መግለጫ ይመስላል (7:3-7፤ 8:4፣10፣13፤ 10:3)፣ ዳሩ ግን ዘዳግ 28ንም ያንፀባርቃል( ቁ 36፣52)። 11ሀ መስመር፣ "በቁጣዬ ንጉስን ሰጥቼሽ ነበር፣" II ሳሙ 8:4-9ን ያንፀባርቃል። ቀጣይ መስመር፣ 11ለ፣ በአሦር መማረክን ይወክላል (II ነገስ 17:1-6)።

**13:10 "መሳፍንቶችህ ወዴት አሉ"** ማሶሬቲኩ "ንጉስህ ለመሆን ይፈልጋለሁ፣" የጥንቱ ትርጉሞች ግን (ግርክ፣ የሦርያ፣ እና ቨልጌት) እንደ NASB እንዲነበብ ያስተካክላል።

## *ሆሴዕ*: 13:12-14

**12 የኤፍሬም በደል ታስሮአል፥ ኃጢአቱም ተከማችቶአል።**
**13 ምጥ እንደ ያዛት ሴት ጭንቅ ይመጣበታል በሚወለድበት ጊዜ በማኅፀን አፍ ቀጥ ብሎ አይወጣምና አእምሮ የሌለው ልጅ ነው።**
**14 ከሲኦል እጅ እታደጋቸዋለሁ፥ ከሞትም እቤዣቸዋለሁ ሞት ሆይ፥ ቸነፈርህ ወዴት አለ?**
**ሲኦል ሆይ፥ ማጥፋትህ ወዴት አለ? ርኅራኄ ከዓይኔ ተሰወረች።**

**13:12 "ታስሮአል" ግሱ** (BDB 864፣ KB 1058፣ *Qal* PASSIVE PARTICIPLE) የበደል መኖሩን ያሳያል።

▣ **"ኃጢአቱም ተከማችቶአል"** ግሱ(BDB 860፣ KB 1049፣ *Qal* PASSIVE PARTICIPLE) "ላለመረሳቱ" ወይም"ለመከፋፈሉ" ምሳሌ ነው(7:2፤ 8:13፤ 9:9)።

**13:13 ይህ ምሳሌ** ("የወሊድ ጊዜ ሚጥ" BDB 408፣ KB 411፣ *Qal PARTICIPLE (በዝ አንቀፅ)* ) የሚያሳየው (1) ከማዕፃን ለመውጣት ፈቃደኛ እንዳልሆነ እንዳልተወለደ ልጅ እና፣ ስለዚህ፣መንፈስ የሞተች(II ነገስ 19:3፤ እሳ 37:3) ወይም (2) የሥራ ድካም የእግዚአብሔር ፍርድ ምሳሌ(ሚክያ 4:9-10)። እስራኤል እመሙን አውቃ ንስዐ መግባት አለባት(እሳ 21:3፤ 26:17)።

**13:14 "እቤዣቸዋለሁ......... እታደጋቸዋለሁ"** እነዚህ ሁለት ተመሳሳይ ሐረጎች እንደ ጥያቄ(questions፣ NASB) ወይም እንደ አመልካች (statements፣ NIV) ሊተረጎሙ ይችላሉ። ሰፕቱአጀንቱ( Septuagint) እንደ አመልካች ይተረጉማል እናም ጳውሎስ በI ቆሮ 15:55 ውስጥ ተጠቅሞበታል። ይሁን እንጂ፣ የማዞራይትኩ መጽሐፍ(Masoretic Text)፣ በአውድ ጥያቄዎች እንደ ሆኑ(NASB) በመጠቆም ፍርድን ያሳያሉ (ቁጥ 14ሠ NET Bible)።
የመጀመርያው ግስ(BDB 804፣ KB 911) ያልተፈጸመ ቃአል(*Qal* IMPERFECT) ሲሆን ሁለተኛው ግስ ደግሞ(BDB 145፣ KB 169) ያልተፈጸመ ቃአል(*Qal* IMPERFECT) ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት: : መቤዠት/መዋጀትን በ7:13 ላይ ተመልከት።

▣ "ሰኦል" ልዩ ርዕስ ተመልከት: : ማጥፋት የት አለ? በ አሞ 9:2።

▣ **"ቸነፈር...... ጉዳት"** እነዚህ የሞት ፍርሃት እና መንገዶች ናቸው(ማለትም፣ "መቅሰፍት" BDB 184 እና"ጥፋት" BDB 881)።

▣ **"ርኅራኄ ከዓይኔ ተሰወረች"** አድሱ የዓለም አቀፍ መጽሐፍ ቅዱስ( NIV) ይህንን ከቁ 15-16 ካለው ጋር ይመድባል።

## *ሆሴዕ*: 13:15-16

**15 በወንድሞቹ መካከል ፍሬያማ ቢሆን የምሥራቅ ነፋስ ይመጣል፥ የእግዚአብሔር ነፋስ ከምድረ በዳ ይመጣል**
**ምንጩንም ያደርቃል፥ ፈሳሹንም ያጠፋል፥ የተከበሩ ዕቃዎች ሁሉ ያሉበትን መዝገብ ይበዘብዛል።**

16 ሰማርያ በአምላክዋ ላይ ዐምፃለችና በደልዋን ትሸከማለች በሰይፍ ይወድቃሉ፥ ሕፃኖቻቸውም ይፈጠፈጣሉ፥ እርጉዞቻቸውም ይቀደዳሉ፡፡

13:15
NASB "በሸምበቆ መካከል ቢያድግም"
NKJV "በወንድሞቹ መካከል ፍሬያማ ቢሆን"
NRSV "በፈጣኖች መካከል የሚያድግ ቢሆንም"
TEV "እስራኤል እንደ አረም ቢያድግም"
NJB "ኤፍሬም ከወንድሞቹ የበለጠ ፍሬ ብያፈራም"
ማሶሬቲኩ "የወንድሞች ልጅ ፍሬ የሚያፈራ ቢሆንም" የሚል አለው፡፡ የጥንቱ ትርጉሞች(Greek፣ Syriac፣ Latin) "በወንድሞች መካከል መከፋፈልን አመጣ" የሚል አለው፡፡ ዘመናዊ ትርጉሞች እንደ NASB "አረም" የሚለውን "ወንድሞች" በሚል ማስተካከያ ያስባሉ፡፡

▣ **"ፍሬ አፈራ"** የሚለው ግስ(BDB 826፣ KB 903፣ያልተፈጸመ ሂፍል/*Hiphil* IMPERFECT/) በ"ኤፍሬም" አከባቢ የሚዞር ቃል ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ የእግዚአብሔር የምስራቅ ነፋስ እየመጣ ነው(Assyria) እናም ከዚህ በኃላ ፍሬያማ አይሆንም (ማለትም፣ ውሃ ይደርቃል)፡፡ ጦርነት በጣም ተጎጂ የሆኑትን ሕዝቡን ያጠፋል(ቁ.16)!

▣ **"የእግዚአብሔር ነፋስ"** ይህ ሐረግ እስራኤል ሕዝቡን ለመቅጣት እግዚአብሔር አሦርን እንደ መሳርያ እንደ መረጠ ያሳያል(12:1፤ ኢሳ 10:5)፡፡

**13:16 "በሰይፍ ይወድቃሉ፥"** ይህ ከክርስቶስ ልደት በፍት በ722 ዋና ከተማው ሰማርያ በአሦር እንደሚጥወድቅ ያሳያል፡፡ ይህ ቁጥር የጥንቱ ጦርነት እስከፊ እንደሆነ ይገልጻል(10:14 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት)፡፡ ሕዝቡ እንዳለ ይሰቃያል(ኢሳ 10:24-27)፡፡

# ሆሴዕ 14

## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|
| በሰተመጨረሻ እስራኤል ትታደሰሳለች | አመፅ እና ተሀድሶ (12:1-14:9) | ሆሴዕ ለእስራኤል ለመነ ላይ | የጥፋት አይቀሬነት (13:12-14:1) |
| 14:1-3 | 14:1-3 | 14:1-3 | |
| | | | የእስራኤል ወደ ያህዌ እውነተኛ መመለስ |
| | | ጌታ ለእስራኤል አዲስ ህይወትን ተስፋ ገባ | 14፡2-9 |
| 14:4-7 | 14:4-7 | 14:4-8 | |
| 14:8 | 14:8-9 | ማጠቃለያ | |
| | | | በማስጠንቀቂያ ማጠቃለል |
| | | 14፡9 | 14፡10 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ vii ተመልከት)**
2:1 **"ውዩ"** የዚህ ቃላኢጋኖ "አሃ"፤ "ሃ" ማለትም "ወይኔ" ማለት ነው (BDB 222፣ ለምሳሌ ኢሳ 1:4፣24፤ 10:5፤ 17:12፤ 28:1፤ 55:1፤ ኤር 22:18፤ 34:5፤ አምጽ 5:16፤ 6:1)፡፡ ይህ ቀብር ሥርአት ላይ የሚፈፀመው ሙሾ በቀጥታ ያመለክታል (ለምሳሌ ከ3-2 ምት )፡፡ ምዕራፍ አንድ የስቆቃውን የሀዘንን ቃል እንደሚደግም ሁሉ (ቁ. 8፣10፣11፣16) ምዕራፍ ሁለትም በዚሁ ፈውስ ይቀጥላል (ቁ 4)፡፡

▣ ***"በመኝታቸው ላይ በደልን ለሚያስቡ ክፍትንም ለሚያደርጉ"*** እነዚህ ጎን ለጎን የሚሄዱ ናቸው፡፡ የመጀመሪያውን ግስ "ማሰብ" (BDB 362፣ KB 359) እና ሁለተኛው ለሚያደርጉ (BDB 821፣ KB 950) የሚሉት ሁለቱም በመድረግ ላይ ያለን ድርጊት ግላጭ ናቸው Qal ACTIVE PARTICIPLES፡፡ ይህ የሚያመላከተው የእስራኤላውያን ክፉውን የማውጣጥን እቅድ ነው (መዝ 36 1-4፤ ምሳ 23፡7፤ ኢሳ 32፡7)፡፡ ዐውዱ የሚያሳየው ከድሆች የገጠር ገበሬዎችን መሬትን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ የሚያደርጉትን እቅድ ነው፡፡

▣ ***"ሲነጋ ይፈጽሙታል"*** ሁለተኛው መስመር ላይ ያለው ግስ ተደግሟል፡፡ ነገር ግን ቃሉ ያለፈውን የአሁኑን የሚያሳይ ሳይሆን ቀጣይነት ያለውን ድርጊት ግላጭ ነው፡፡ ኃጢአት የሚጀምረው በሀሳብ ላይ ነው (ሆሴ 7:6)፡፡ አስተማሪዎች አዕምሮችን ለዘር የተዘጋጀ መሬት የሚሉት አይናችን የሚያየውን ጀሮአችን የሰማዋል እና በውሳጣችን የሚያድረው ሐሳብ ነው ድረጊት የሚሆነው፡፡

▣ ***"ኃይል በእጃቸው ነውና"*** ይህ ከብሉይ ኪዳን ኃይል ትክክል ያደርጋል ከሚለው ጋር ተዛማችነት ያለው ነው፡፡ ምክንያቱም መቻላችን መሆናችን አይደለም እግዚአብሔር ሥነ ምግባራዊ አምላክ ነው፡፡ እርሱም ስነ ምግባራዊውን ዓለም ሁሉም ሰው የተሰጠውን ህይወት ባለ አደራ ሆኖ እንዲጠበቅ ተደርጎ ተፈጥሯል፡፡

**2:2 "በእርሻው ላይ ይመኛሉ፥ በግዴታም ይይዙታል ... ሰውንና ቤቱን፥ ሰውንና ርስቱንም ይነጥቃሉ"**
እነዚህ አራት ከሁለት ጠንካራ ግሶች ጋር ጎን ለጎን የሚሄዱ መስመሮች ናቸው)፡፡

1. *መመኘት* BDB 326፣ KB 325፣ Qal PERFECT
2. *መያዝ* BDB 159፣ KB 186፣ Qal PERFECT
3. ይነጠቃል BDB 669፣ KB 724፣ Qal PERFECT
4. *መጨቆን* BDB 798፣ KB 897፣ Qal PERFECT

የርስትን እጅግ በጣም አስፈላጊነት የአይሁዶችን በተስፋይቱ ምድር ውስጥ ያላቸውን የመሬት እርስት ይዞታ ማስታወስ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው ሌዋ. 25:23፤ ዘኁ. 33:54፤ 36:1-12፤ ኢያ 12-21)፡፡ የእግዚአብሔር ስጦታ ለአብርሃም ዘሮች በሙሉ አሁን ያለው በክፉና በሃብታም ጨቋኞች እጅ ነበር፡፡ ሚኪያስ ያደገውና ይኖረው በትንሽ የገጠር መንደር በየጊዜው በተደጋጋሚ ያየው ነገር ነው፡፡

"ቤት" የሚለው ቃል የአንድን ቤተሰብ የመኖሪያ ቤት ቦታ ወይም ቤተሰበ (ርስት እንደሚለው ቃል) የሚያመለክት ነው፡፡ እነዚያ በዝባዦች የሚፈልጉት ሁሉንም ነገር መሬት ህፃናትን ወጣቶችንና ያላቸውን ንብረት በሙሉ ነው፡፡

**2:3 "ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እነሆ፥ ... አስባለሁ"** *"እነሆ"* የሚለው *ቃልኢጋኖ* ቃል (hh፣BDB 243 II) የሚያስደንቅ ውጤትን የሚያሳይ አረፍተ ነገር ነው፡፡ ሚክያስን ለሚያጠኑ የሚረደው ዩ.ቢ.እስ (*UBS Helps For Translators) እንደሚለው* "ይህ አዲስና ያልተጠቀሰ ነገር ለማሳየት የሚጠቀሙበትን መንገድ ገላጭ ነው፡፡ ይህ ምፃታዊ አነጋገር ነው፡፡ ክፉ ሰዎች እንደሚያቅዱ በቁጥር 1ላይ እንደተጠቀሰው ግስ እንደዚያው ነው፡፡ እግዚአብሔር ያቅዳል (ለምሳሌ የምንዘራውን እንደምናጭድ ገላ 16:7)

▣ ***"በዚህ ወገን ቤተሰብ ላይ"*** ቤተሰብ የሚለው ቃል ጎሳ (BDB 1046) ማለት ነው፡፡ ያንዳንድ ክፉ ኃጢአቶች ውጤቶች በብዙሀኑ (ጤናማ በሆነው) እና አጠቃላይ በሐገሩ ላይ ያመጣውን ፍርድ አስታውስ (አሞፅ 3:2)፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"በህይወት ላይ የሚመጣ ጥፋት"** |
| **NKJV፣ TEV፣** | |
| **NJB** | **"በህይወት ላይ የሚመጣ ጥፋት"** |
| **NRSV** | **"ክፉ"** |

ይህ የዕብራይስጡ ቃል (BDB 949) "ክፉ"፣ "መጨነቅ" ወይም "አመፀኝነት" ማለት ነው፡፡ በዘፀ 32፡12 14 የሚያሳየው እነዲዚሁ እግዚአብሔር ፍርድን ነው ዘዳ. 29:112፤ አሞ 9:4)፡፡ በቁጥር 3ላይ ሁለት ጊዜ እና እንደገናም በምዕ 3፣2፣11 ውስጥ ተጠቅሷል፡፡

▣ ***"አንገታችሁን አታነሡም"*** ይህ ግስ (BDB 559፣ KB 561) Hiphil IMPERFECT ነው፡፡ ይህ የማሸነፍ ወይንም በሀይል መያዝ በሰቆቃ እርምየስ 1:14፣ 5:5 ላይ ጥቅም ላይ ዉሏል፡፡ የሚያመልከተው በሬዎች ስራዎችን እንዲሰሩ የሚመራቸውን በአንገታቸውን ላይ የሚደረገውን ቀንበር ነው፡፡

▣ **"ቀጥ ብላችሁ አትሄዱም"** እስራኤል ኩሩና ደንቆሮ ሆነ ነበር፡፡ (ማለትም በስምንተኛው ምእተ አመት ታሪካዊ ስሪት ስንመለከት) እግዚአብሔር አካሄዳቸውንና አመለካከታቸውን ይቀየራል፡፡

**2፡4 "በዚያ ቀን"** ይህ የሚያሳየው የእግዚአብሔር ህጋዊ የአደራረግ ጊዜ አንዳንዴ እዚህ ጊዜያዊ በሌላ ጊዜ ደግሞ (የሚመጣ የያህዌ ቀን መሆኑ ነው)፡፡

▣ **"ያለቅሱላቸዋል"** የሚለው መዝሙርን ወይም ምሳሌን (ማለትም *mashal*፣ BDB 605 II) ያመለክታል፡፡ ሌሎች ደግሞ የሚያመለክቱት የአሁኑ የሰዎችን የቡድን ሁኔታ ነው ይላሉ፡፡ እንደተለመደው እንደያደርጉ ሌሎችን ለማስጠንቀቂያ የተሰተ የማስተማሪያ መሳሪያ ነው፡፡

▣ **"ጽኑ ልቅሶ"** የሚለው የሚያመለክተው ቀብር ላይ የሚቀርብን መሾ ነው (BDB 624፣ KB 675፣ Qal PERFECT)፡፡ ስላቁ በቁጥር4ሐ-መ ላይ ነው (አራት የግጥም መስመሮች)፡፡

ይህ ቃል (BDB 624፣ KB 675) በማሶሬቲኩ የእብራይስጥ ስነ-ፅሁፍ ላይ ሶስት ጊዜ በተደጋጋሚ ተጠቅሷል፡፡

1 ግሱ (Qal PERFECT)
2 ስሙ (ተበእታዊ ነጠላ ቁጥር)
3 ስሙ (እንስታዊ ነጠላ ቁጥር)

ይህ ድግግሞሽ የሚጠቀመው በጣም ከባድ አሳዛኝ ስቆቃን ነው፡፡

▣ **"ፈጽመን ጠፍተናል"** ይህም ትኩረት ለመስተት የገባ ተመሳሳይነት አግባብ ያለው ነው፡፡

1 ፍጽም የሆነ ገደብ BDB 994፣ KB 1418፣ a Qal INFINITIVE ABSOLUTE
2 BDB 994፣ KB 1418፣ a Niphal IMPERFECT

**2፡4 "የህዝቤን እድል ፈንታ ይሰፍራል"** "ይሰፍራል" የሚለው ቃል (BDB 558፣ KB 560፣ Hiphil IMPERFECT)ያለፈ ግን ያላለቀ ህጋዊ የሆነ የመሬትን ይዞታ ለማስተላለፍ የሚጠቅም ቃል ነው፡፡ ቁጥር 4እና 5 የኃያላን፣ የባለጠጎች፣ ተጽእኖ አምጭ የሆኑ እስራኤላዊያን (ከድሆች በመስረቅ) ለሚመጣው ምርኮኝነት ውስጥ የሚጨኹትን ጩኸት ነው፡፡ ነገር ግን ልብ በሉ በድርጊታቸው በማዘን አይደለም ነገር ግን በድርጊታቸው ለመጣባቸው ቅጣት እንጂ የዘሩትን አጨዱት (በየአይነት)፡፡

▣ **"እርሻችንን ለዓመፀኞች ይከፍላል"** ይህ ሊያመለክት የሚችለው (1) ለከሃዲዎች (ወደ ኋላ ለሚመለሱ) BDB 1000፣ NKJV) ወይም (2) JPSOA "ከጥፋት" ተቃውሞ የሚል አለው የአሶራውያን ወራሪዎችን ያስታውሳል (ከዕብራይስጥ የቃል ስርወ-ቃል BDB 1000፣ NRSV፣ TEV፣ NJB)፡፡ ምጽታዊ አባባሉ እነዚያ ሀብታሞች እና ሃያላን መሬት ዘራፊዎች ሌሎችን ስለመጥራታቸው ነው (ወራሪዎች የመሬት ቀማኞችን)፡፡

**2፡5 "በእጣገመድ የሚጥል አይኖርህም"** የሰባው ለቃውንት ትርጉም (LXX) "ይሰፈራል" የሚለው ግስ የመጀመሪያውን ቃል ማለትም "ይጥላል/ ይላካል" በሚል ቃል በትክክል በማስገባት ይህን የግጥም መስመር ቤት አስመትቷል፡፡

▣ **"በእግዚአብሔር ጉባኤ መካከል በዕጣ"** ይህ የሚያመለክተው የተቀደለችዋን የተስፋይቱን ምድር ክፍፍልን ነው (ኢያሱ 12-21)፡፡ ይህ አረፈተ ነገር ለኃያላኖች ለባለጠጎች ለተጽእኖ አመጭዎች ከተስፋይቱ ምድር ከተስፋይቱ ምድር ለተወገዱ በጊዜያዊነት እና በዘላቂነት ነው(ቁ 10)፡፡ ይህ ምንባብ በወራሪዎ ላይ የሚያመጣውን የእግዚአብሔር ፍርድ በዘፀ 20፡5 ዘዳ 5፡9 ከተገለፀው የበለጠ አስከፊ የሆነ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ ከሚለው ጋር ተዛማጅ ነው፡፡ ይህ የመከላከል ሁኔታ ቋሚና ከትውልድ ወደ ትውልድ ተሸጋጋሪ ነው፡፡

▣ **"በዕጣ"** የሚለው ቃል (BDB 174) ''ዕጣ" የሚያመለክተው ኡሪምና ቱሚም ማለትም በካህን ደረት ላይ የሚሆኑትን አስራ ሁለቱን ድንጋዮች ጎን ያሉትን ነው፡፡

በዚህ መንገድ ይሰራል ብለን እርግጠኛ ባንሆንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ የምንጠቀመው

1. የተለያዩ ቀለም ያሏቸው ድንጋዮች
2. "አዎን" ወይም "አይደለም" የሚል ቅብ ቀለም ያላቸው ድንጋዮች
3. ፊደል ያላቸው ድንጋዮች
4. ሌሎች ያልታወቁ መንገዶች

የአዲስ ኪዳኑ ቃል "ካህን" የሚለው የመጣው ከዚሁ ከዕብራይስጡ ሀሳብ በመነሳት ነው፡፡ በእግዚአብሔር ጉባኤ የሚለው ቃል ኪዳናዊ ሐረግ ነው የሳባ ሊቃናቱ ትርጉም ቃሉን *qahal* የሚለው ኤክሌሽያ (*ecclesia*) (መሰባሰብ ወይም ሰብሰብ፣ በኃላ በአዲስ ኪዳን አማኞች ለራሳቸው መጠሪያነት የተጠቀሙት (ማለትም ቤተ-ክርስቲያን)፡፡

## ሚኪያስ 2፡6-11

**6 ትንቢት አትናገሩ ብለው ይናገራሉ በእነዚህ ላይ ትንቢት አይናገሩም፥ ስድብም አይርቅም።**
**የያዕቆብ ቤት የተባልህ ሆይ፥ በውኑ የእግዚአብሔር መንፈስ የማይታገሥ ነውን?**
**ወይስ ሥራው እንደዚች ናትን? ቃሌስ በቅን ለሚሄድ በጎነት አያደርግምን?**
**8 ነገር ግን ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ሕዝቤ እንደ ጠላት ሆኖ ተነሥቶአል ቀሚስንና መጐናጸፊያን ገፈፋችሁ ሳይፈሩም የሚያልፉትን ከሰልፍ እንደሚመለሱ አደረጋችኋቸው።**
**የሕዝቤንም ሴቶች ከተሸለሙ ቤቶቻቸው አሳደዳችኋቸው ከሕፃናቶቻቸውም ክብሬን ለዘላለም ወሰዳችሁ።**

**10 በዚህ ዕረፍት የላችሁምና ተነሥታችሁ ሂዱ በርኵሰት ምክንያት ክፉ ጥፋት ታጠፋችኋለች።**
**11 ነፋስንም ተከትሎ። ስለ ወይን ጠጅና ስለ ስካር ት**
**ንቢት እናገርልሃለሁ ብሎ ሐሰትን የሚናገር ሰው ቢኖር እርሱ ለዚህ ሕዝብ ነቢይ ይሆናል።**

**2፡6-7** ቁጥር 6-7 ክርክሮች ናቸው፡፡ ሚክያስ ይናገራል፡፡ ለመረዳት አዳጋች የሆነው ነገር ሚክያስ ከየት ጀምሮ የት እንደጨረሰ እና ሀብታሞች መቼ በቡድን መናገር ጀምረው እንደጨረሱ እርግጠኛ መሆን ላይ ነው፡፡

ለስልዬ አልን Leslie Allen (New International Commentary on the Old Testament)፣ ገፅ 292፣ እና 7 ላይ ጥሩ የሆነ ማብራሪያ ሰጥቷል፡፡ ስብከታችሁን አቁሙ ብለው ይሰብካሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ሰብከታቸውን ማቆም አላባቸው፡፡ ዝቅተኝነት እኛን ለሚያስማ አይገባም የያቆብ ቤት ክፍል ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ የማይታገስ ነውን? ወይስ ስራው እንደዚች ናትን? ተስፋዎች መልካም እድልን አያሳዩምን? ቃሌስ በቅን ለሚሄድ በጎነት አያደርግምን? ቁጥር 6 እና 7 ስንመለከት የሀብተሞችን ቃል ኪዳናዊ ልማድና ስነ መለኮታዊ ባህርይ የሚያንፀባርቁ ይመስላል፡፡ ነገር ግን ቃል ኪዳኑ የሚጠይቀውን መስፈርት አያሟሉም፡፡ ወይም ይጉድላቸዋል፡፡

**2፡6 ትንቢት አትናገሩ ብለው ይናገራሉ በእነዚህ ላይ ትንቢት** አይናገሩም ይናገራሉ ጨዋታው (ግሱ ሶስት ጊዜ ተደጋግሟል) እንዲህ በሚለው ቃል ይናገራሉ፡፡ ወይም "ትንቢት"(BDB 642፣ KB 694፣ Hiphil IMPERFECT ያለፈ ነገር ግን ያላለቀ ድርጊትን የሚያሳይ ሲሆን የተጠቀሰው ስርዓትን በማስያዝ መንፈስ ስሜት ነው፡፡ "መልዕክቶችን ለአንድ ሰው መተውን" ፣ "ማስቀመጠን" ቁ6 [ሶስቱንም ጊዜ ሁሉም Hiphil IMPERFECTS]፤ ነገር ግን ያላለቀ ጉዳይን የሚያመለክቱት [ቁ 11 ሁለት ጊዜ እንደገና በአምጽ 7፡16]፡፡ "ተናገር" የሚለው ቃል በቁሙ ስንተረጉመው "ማንጠባጠብ" ማለት ነው (ዘዳ32፡2፣2፣ሕዝ 20፡46 ተመልከቱ)፡፡

▣

**NASB** **"የያዕቆብ ቤት የተባልህ ሆይ"**
**NKJV** **"የያእቆብ ቤት ተብለህ የተጠራህ አንተ"**
**NRSV** **"ይህ የያቆብ ቤት ይባል ዘንድ"**
**TEV** **"የእስራኤል ቤት በእርግማን በታች ናቸው ብለህ ታስባለህ"**
**NJB** **"የያቆብ ቤት የተረገመን ማለት ይቻላል"**

የትርጉሞች መለያየት መንስኤው *hapox legommenon* እንዲህ ሊባል ይገባል (BDB 55፣ KB 65፣ Qal PASSIVE PARTICIPLE) NET መጽሐፍ ቅዱስ ግን አስተካክሎ ፍጽም ይሆን ቀጣይነት ያለው ሆኖ አንድ መነሻ ያላቸው የያእቆብ ቤት እንዲህ ይላል የሚለውን የሚያመለክት አድርጎ አቅርቦታል፡፡ "የተረገመ" የሚለው ቃል (NJB) ወይም "ተረግሟል" (TEV) የሚለው ብሏል ይናረጋል የሚለው የማስተካከያ ውጤት ሆኖ እናገኛዋለን፡፡

▣ ***"የእግዚአብሔር መንፈስ"*** በአውዱ መሠረት የሚያመለክተው መንፈስ ቅዱስ አይደለም ነገር ግን የያህዌን ማንነት ነው (ማለትም የያህዌን መንፈስ 3:8):: እዚህ በዚህ ግስ (BDB 894፣ KB 1126፣ Qal PERFECT) የተጠናቀቀ ድርጊት አመልካች ሆኖ የእግዚአብሔር ትዕግስት ወይም አለመቆጣት ይመለከታል (NRSV፣ TEV፣ NJB)::

**2፡8 "ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ህዝቤ እንደ ጠላት ሆኖ ተነስቷል"** ግሱ (BDB 877፣ KB 1086) Polel IMPERFECT (ያለፈ ሆኖ ያላለቀ ድርጊት አመልካች) ነው፡፡ የቃል ኪዳን ህዝብ በተደጋጋሚ የሙሴን ቃል ኪዳን ተላልፈዋል ወይንም ጥሰዋል፡፡ ይህም ወራሪዎችን እውቅና በመሰጠት የመቃወሚያ መንገድ ሆኗል፡፡ የእግዚአብሔር ህዝብ በቃል ኪዳኑ ወንድና ሴት ልጆች ላይ እንደወራሪ ጠላት ሆኖ ተነሳበት ሁኔታ ነበር፡፡ ይህን ሐረግ ለመተርጎም ችግሩ የማሶሬቲኩ ትርጉም (ማሶሬቲኩ) የተጠቀመው ህዝቤ እንደ ጠላት (አጥቂና /ወራሪ የሚለው ነው፡፡ መቼም በሚቀጥሉት ቁጥሮች መስመሮች ላይ ስናየው ወራሪዎች ይላልና ነው ብዙ ትርጉሞች የማሶሬቲኩ ትርጉም (ማሶሬቲኩ) በማስተካከል ነገር ግን በህዝቤ ላይ እንደጠላት ተነሳስቷል ተብሏል NRSV፣ TEV፣ NJB፣ NET Bible)፡፡

▣ ***"ቀሚስንና መጐናጸፊያን ገፈፋችሁ"*** ግሱ (BDB 832፣ KB 980) Hiphil IMPERFECT ነው፡፡ የሚያመለክተውም ሃብታሞች በድሆች ላይ የሚያደርጉት የወራሪ ድርጊት ነው፡፡ የምንባቡ ክፍል የሚያመለክተው የሀብታሞችን ጭካኔና ልበቢስነት ተፅእኖ የእስራኤላውያን መሬትና የድሆች ቤቶች ልብሶቻቸውን (ልጆቻቸውን) ሳይቀር ለተበደራቸው ገንዘብ መያዣነት እንደሚበዘብዙአቸው ነው (ዘጸ. 22:26፣27).)

በበዝባዦች ተፅእኖ የሚደረግባቸውን አስተውሉ

1) በቃል ኪዳን ወንድቻቸው ቁ 8ለ-ሐ
2) ከጦርሜዳ የተመለሱ ወታደሮች ቁ 8መ
3) የቃል ኪዳን ሴቶች ቁ9ሀ-ለ
4) የቃል ከዲን ልጆች ቁ 9ሐ

▣

**NASB** **"ካልተጠበቁ መንገድ አላፊዎች"**
**NKJV** **"ከጦርነት ከተመለሱት"**
**NRSV** **"ሲያልፉ አንተን ከሚታመኑ፣**
**TEV** **"ከጦርነት የሚመለሱትን ወንዶች በሰላም በቤታቸው እንዳሉ የሚያስቡት ነገር እናንተ ሰረቃችሁአቸው፡፡**
**NJB** **"ሰላም የሚሰማቸውን መንገዶች አበላሻችሁ"**

ከእነዚህ የተለያዩ ትርጉሞች የእብራይስጡ አደናጋሪ መሆኑ ነው፡፡ ከአውድ እንምንረዳው መጎናፀፊያ ካልተጠረሩ እንግዶች ነው የሚፈለገው፡፡ መፋለስን ያመጣው ከጦርነት የተመለሱ የሚለው ሀገር ነው፡፡

በጣም ምርጥ የሆነው አተረጋጎም ለዚህ አደናጋሪ ለሆነው ሐረግ የአይሁድ ወታደሮች ከውጭ ጠላቶቻቸው ሲዋጉ ቆይተው ሲመለሱ (ወራሪዎች የመሬት ዘራፊዎች) ሰላም ይሰማቸው እንደነበር ነገር ግን እንማይሰማቸው የራሳቸው የሆኑ የቃል ኪዳን ወንድቻቸው ግን ባልጠበቁት ሁኔታ አጠቋቸው እና መሬታቸውን ንብታቸውን ወሰዱባቸው፡፡

**2፡9 "የሕዝቤንም ሴቶች ከተሸለሙ ቤቶቻቸው አሳደዳችኋቸው"** ግሱ (BDB 176፣ KB 204፣ Piel IMPERFECT) ማለትም ወደ "ውጭ ማሳደድ" (ሆሴ 9፡15)፡፡ ይህ በግልፅ የሚያሳየው ባሎች ከኮንትራት መልክ ለባርነት እንደሰጡ ነው፡፡

▣ **"ከሕፃናቶቻቸውም ክብሬን ለዘላለም ወሰዳችሁ"** እነዚህ ህጻናት ባሪያዎችና መጥፎዎች ሆነው ነበር (አባቶታቸው እንዳደረጉ) እንደ ቃል ኪዳኑ ህዝብ የተስፋይቱን ምድር የመውረስ መብታቸው በወራሪዎችና በጨካኞች ተነጥቀዋል፡፡ በተጨማሪም በአንድ ላይ በእግዚብሔር ፍርድ ተጠቂ ሆነዋል (ተማርከዋል)፡፡ በእስራኤል ላይ የደረሰው ሁሉ ወደ ይሁዳም ይመጣል፡፡ ነገር ግን ወደፊት እንደገና ርስታቸውን ይቀበላሉ (ቁ 5)፡፡ ስለዚህ "ለዘላለም" የሚለው የሚያመለክተው በዚህ ላይ ጊዜን ሳይሆን ከፍተኛ ግለትን ነው፡፡

ይህ የሚያንፀባርቀው የእስረኤላዊያን ወታደሮች የግድያ መማሪያ የሆነውን ወጣቶችን (አዛውንቶችን) በማርኳቸው ፊት የመግደልን ለዕላዊ መግለጫ ነው፡፡

**2፡10 "ተንስታችሁ ሂዱ"** እነዚህ ሁለት ግሶች (BDB 877፣ KB 1086) "ተነሱ" እና "ሂዱ" (BDB 229፣ KB 246) ሂዱ ሁለቱም Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ) S ትዕዛዝ አንቀፅ ናቸው ወይንም የሚከትሉትን ይጠቁማል፡፡ (1) ለጥቂት ታማኞች ማስጠንቀቂያ (ለትሩፋን) ወይም (2) ምናልባትም በሀገሪቱ ላይ ሊማጣ ያለውን የእግዚአብሔርን ፍርድ (ምርኮኝነት)፡፡

▣ **"በዚህ ዕረፍት የላችሁምና"** ይህ ቃል ለተስፋይቱ ምድር በዘዳ 12፡9 መዝ 95፡11 ውስጥ ተጠቅሷል፡፡ ይህም ለወራሪዎችና ለምርኮኞች በግጥም መልክ የቀረበ ነው፡፡

▣ **"በርኩሰት ምክንያት ክፉ ጥፋት ታጠፋችኋለች"** ይህ ቃል ወይም አገባብ (BDB 380) በብሉይ ኪዳን የከነአናውያንን ተቃዋሚነት ለመግለፅ ተጠቅሟል፡፡ ሚክያስም ይህን ተመሳሳይ ቃል እግዚአብሔር ከነዓናውያን ለማስወገድ ምክንያት የሆነበትን (ዘፍ 15፡6) በመጠቀም የእግዚአብሔር ህዝብ ይኮንናል (ዘሌ 18፡24)፡፡ አሁን ደግሞ እስራኤላዊያንን ያባርራል፡፡

ሌላ ደግሞ ተመሳሳይ አገባብ ይታያል፡፡

1. ግሱ BDB 287 II፣ KB 285፣ *Piel* IMPERFECT (ውድቀትን ማምጣት)
2. ስም BDB 287፣ KB 285 (ህመም የሞላበት ውድቀት)

▣

| | |
|---|---|
| **NASB** | ***ህመም የሞላበት ወድቀት*** |
| **NKJV** | ***ውድቀትን መናገር*** |
| **NRSV** | ***ሀዘን የሞላበት ውድቀት*** |
| **TEV** | ***ይህ ቦታ እንዲፈርስ መፍረድ*** |
| **NJB** | ***ከሚፈለገው በላይ ቃል ኪዳን መግባት*** |

ይህ *Niphal* PARTICIPLE (BDB 599፣ KB 637) ቃል በቃል ሲተረጎም "ህመምን መፍጠር" ማለት (ለምሳሌ ኤር 14፣17) አካላዊ ህመም የአጢያት እና የአመድ ምሳሌያዊ አገላለፅ ነው (ምሳሌ ኢሳ 1፣5-6)፡፡

**2፡11 "ነፋስንም ተከትሎ"** ይህ የሚያሳየውል እውነተኛ ነቢያት ተገልለው እያሉ የሐሰተኛ ነቢያትን በቀላሉ መያዛቸውን ነው (ቁ 6)፡፡ እነዚህ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ዘዳ 27-29 ላይ ያለውን ቃል መሰረት በማድረግ ሁልጊዜ ጤንኝነትን፣ ሀብትና ብልፅግናን ይሰብካሉ (3፡5)፡፡
እነዚህ ሐሰተኛ ነቢያቶች ሁልጊዜ የኃላፊነትን (ተጠያቂነት) ቃልኪዳን ይዘነጋሉ The Disease of the Health፣ Wealth Gospels by Gordon Fee)፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የብሉይ ኪዳን ተስፋዎች በምክንያት ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ በዚህ ሐረግ ላይ "መንፈስ" እና "ንፋስ" በሚሉ ቃላቶች ላይ የቃላት ጨዋታ አለ BDB 924 ሆሴ 8:7፣ 12:1)፡፡

▣ **"ስለ ወይን ጠጅና ስለ ስካር ትንቢት እናገርልሃለሁ"** ይህ በዘዳ 28 ላይ የተገባውን የእግዚአብሔር በግብርና ስራ ላይ ብልፅግና መስጠት ተስፋ የሚያመለክት ይሆናል፡፡ ይህ ምናልባትም የመንፈሳዊ ብልጽግናን ውጤቶችንም ሊያመለክት ይችላል (ኢሳ 5፣11 12፣22፣28፣7) ሰካራምነትም በብሉ ኪዳን አብዛኛውን ጊዜ የፍርድ ምሳሌያዊ አገላለጽ ነው፡፡

በአሞፅ 6፡ 6 ላይ ያለውን "መጽሐፍ ቅዱሳዊ አዝማሚያ በአልኮል እና በአልኮለኝነት" ሚለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት፡
በሚል ልዩ ርዕስ አምፅ ላይ ይመልከቱ፡፡

▣ **"እርሱ ለዚህ ህዝብ ነቢይ ይሆናል"** ለቃል ኪዳን ህዝብ የተገባው የብልጥግና መልዕክት ዘዳ 28 ማለትም በዘዳ 27 እና 29 ላይ ካለው የኃላፊነት ቃልኪዳን ጋር የተለያየ ነው (ልክ እንደዛሬው ጊዜ) በጣም ተወዳጅ ነበር፣ እነዚህ ሐሰተኛ አስተማሪዎች የሚሰጡት የሚናገሩት ተስፋ የሰላም (3፡5) እና የብልጽግና ነው፡፤ ነገር ግን እየተገለጠ ያለው የእግዚአብሔር ፍርድ እንጂ በረከት አይደለም፡፡

## ሚኪያስ 2፡12-13

[12] *ያዕቆብ ሆይ፥ ሁለንተናህን ፈጽሞ እሰበስባለሁ፥ የእስራኤልንም ቅሬታ ፈጽሞ አከማቻለሁ*

**እንደ ባሶራ በጎችና እንደ መንጋ በማሰማርያቸው ውስጥ በአንድነት አኖራቸዋለሁ ከሰው ብዛት የተነሣ ድምፃቸውን ያሰማሉ።**
**[13] ሰባሪው በፊታቸው ወጥቶአል እነርሱም ሰብረው ወደ በሩ አልፈዋል፥ በእርሱም በኩል ወጥተዋል ንጉሣቸውም በፊታቸው አልፎአል፥ እግዚአብሔርም በራሳቸው ላይ ነው።**

**2፡12-13** እነዚህ ጥቅሶች ቅፅበታዊ የፍርድን ወደ ተስፋ መለወጥ ያመለክታሉ፡፡ ደግሞ የመጽሐፍ አጠቃላይ ባህርይ ያሳያል፡፡ ይህንን ቅፅበታዊ ለውጥ በተመለከተ የተለያየ ጥቂት የማይባሉ ጥቂት የማይባሉ አስተምህሮቶች አሉ፡፡ 1ኛ ጆን ካልቪን እና ኪሚቺ በቁጥር 12 እና 13 ላይ ያለው ክፍል በምርኮ ስለመወሰድን ያመለክታል ይላሉ፡፡ (2ኛ) ምናልባትም ከሐሰተኛ አስተማሪዎች ትምህርት ተቀንጭቦ የተወሰደ ከቁጥር የተሰጠ ምላሽ ሊሆን ይችላል፡፡ (3ኛ) ምናልባት ይህ የሚክያስ የራሱ ነእግዚአብሔር (ያህዌ) ጥበቃ ስር ስለመሆን ተስፋ ሊሆን ይችላል፡፡ ወይም (4ኛ) የኋለኛውን ዘመን ጣልቃ መግባት ያመለክታል፡፡ እኔ የምመርጠው ድንገተኛውን የስነፅሁፍ ለውጥ ማለትም ወደ ግጥማዊ አይነት እሱም antithetical parallelism ተቃርኖአዊ የሆነ ነው፡፡ ስለዚህ በእብራዊያን ስነፅሁፍና ትንቢታዊ ግጥም የተለመደ ነው፡፡

**2፡12 *"ያዕቆብ ሆይ፥ ሁለንተናህን ፈጽሞ እሰበስባለሁ"*** ይህ በያህዌ የተሰጠ የወደፊት ተሀድሶ የተስፋይቱን ምድር ቃል ኪዳን ነው (ዘዳ. 30፡4፤ ኤር. 23፡3፤ 31፡8)፡፡ ምንም ያህል እስራኤል ስለ ኃጢአት ብትቀጣም፡፡ሁሉም ህዝቦቹ የምርኮ የቅጣት ዋጋ ከፍለዋል፡፡ እግዚአብሔር በእውነት በርሱ በሚታመኑት ደግሞም ለሚታዘዙትና እንዲሁም ለዘር ዘሮቻቸው ቃል ኪዳኑን ይጠብቃል፡፡ በቁጥር 12 የተጠቀሰው "እኔ" በሚል ነጠላ ቁጥር ነው፡፡ ነገር ግን ቁጥር 13 የሶስተኛው መደብ ቁጥር ነው፡፡ይህ አገባብ በእብራዊያን አገባብ ውስጥ የተለመደ ነው፡፡ ቢሆንም ግን ቁ.12 ሊሆን የሚችለው ያህዌ ራሱ እየተናገረ እንዳለ እና ራሱ ቁ.13 ደግሞ የሚክያስ አስተያየትና ማብራሪያ ነው፡፡

▣ ***"የእስራኤልንም ቅሬታ"*** ይህንን ስነመለኮታዊ ፅንሰ ሀሳብ ነቢያት በተደጋጋሚ የሚከሰት ተስፋ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ይህ የሚያመለክተው በቁጥር ጥቂት ግን ታማኝ አማኝና ታዛዥ እንዲሁም የቃልኪዳን ህዝብ የሆኑ እስራኤላዊያን ሲሆን እግዚአብሔር የሚመሰርትበት ህዝብ ናቸው (4፡6-7)፡፡ አብዛኛው የቃል ኪዳን ህዝብ ወይም (የአብርሃም ዘሮች) አማኞች አይደሉም ፣ ታዛዥ አይደሉም፡፡ እንዲሁም ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ አካሄድ የላቸውም፡፡ እነዚህ ሰዎች ጊዚያዊም ሆነ የመጨረሻ ፍርድ ይገባቸዋል፡፡

## ልዩ ርዕስ፡ ቅሬታ፣ ሦስት መልኮች

የብሉይ ኪዳን ጽንሰ-ሐሳብ *"ታማኝ ቅሬታ"* የነቢያት ተደጋጋሚ ጭብጥ ነው (ባመዛኙም በስምንተኛው ክፍለ ዘመን ነቢያትና ኤርምያስ)። እሱም ጥቅም ላይ የዋለው በሦስት መልኮች ነው፡

1. ከምርኮ የተረፉት (ምሳ. ኢሳ. 10፡20-23፤ 17፡4-6፤ 37፡31-32፤ ኤር. 42፡15፣19፤ 44፡12፣14፤ 28፤ አሞጽ 1፡8)
2. ለያህዌ ታማኝ ሆነው የቀሩ (ምሳሌ፣ ኢሳ. 4፡1-5፤ 11፡11፣16፤ 28፡5፤ አዮኤል 2፡32፤ አሞጽ 5፡14-15፤ ሚክያስ 2፡12-13፤ 4፡6-7፤ 5፡7-9፤ 7፡18-20)
3. እነሱ የመጨረሻው ጊዜ መታደስ እና ዳግም መፈጠር አካል የሆኑ (ምሳሌ፣ አሞጽ 9፡11-15)

በግዞት ዐውዶች እግዚአብሔር ጥቂቶችን ብቻ ነው የመረጠው (ቅናታዊ ታማኝነት ያላቸውን) ከቅሬታዎቹ (የግዞት ቅሬታዎች) ወደ ይሁዳ ለመመለስ። ቀደም ሲል በዚህ ምዕራፍ እንዳየነው፣ ጭብጡ ካለፈው እስራኤል ይደገማል (ቁ. 6)።እግዚአብሔር ቁጥሩን ይቀንሳል፣ ኃይሉን፣ ሰጪነቱን፣ እና ጥበቃውን ለማሳየት እንዲችል (ምሳሌ፣ ጌዲዮን፣ መሳፍንት 6-7)።

▣ ***"እንደ ባሶራ በጎችና እንደ መንጋ በማሰማርያቸው ውስጥ"*** ይህ ምናልባት (1) የቦታ ስም Bozrah (ማሶሬቲኩ፣ JPSOA) የተባለ በመልካም በጎች የሚታወቅ ወይም (2) ከበጎች ማሰማሪያ ትይዩ እና የተጣበቀ ግን ወይም (እርሱም፣ የበጎች መንጋ የተራራውን ጉዳይ አያካትትም)፡፡ የበጎችና የእረኝነት ምሳሌያዊ አገላለፅ የያህዌነው የጠባቂነትና የመጋቢነት ቃል ኪዳን ያሳያል (መዝ 23)፡፡ በጎች ጥበቃና እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው እንስሳት ናቸው፡፡ የቁ 12 መጨረሻ የሚያመለክተው (1ኛ) ሀሴት የተሞላ ህዝብ (2ኛ) NKJV እና NIV ላይ እነዳለው ቁጥራቸው ብዙ የሆነ ህዝቦችን ነው፡፡

**2፡13 እዚህ ጋ ሚክያስ በድጋሜ የሚናገር ይመስላል (እርሱም ያህዌን እንደ ሶስተኛ መደብ** third person **አድርጎ ጠቅሷል)፡፡ ይህ ጥቅስ ስለ መሲሁ የተነገረለት ክፍል ነው፡፡ ይህ ደግሞ የዳዊት ቤት ንግስና እንደሚታደስ ነው (2ሳሙ 7)፡፡**

**እዚህ ላይ የቃላት ጫወታ አለ "ሰባሪው"** (13ሀ፣ BDB 829፣ KB 971፣ *Qal PARTICIPLE (ቦዝ አንቀፅ)* ) **እና "በሰብሮ መወጣት"** (13ለ፣ BDB 829፣ KB 971፣ Qal PERFECT) መካከል ነው፡፡ ንጉሱም ህዝቡን ከምረኮ አጥር አውጥቶ ወደ ሰፊና ለምለም መስክ ይወስዳቸዋል፡፡ እነርሱም በደስታ እየዘለሉ ይፈነጥዛሉ፡፡ እዚህ ልብ ሊባል የሚገባው ነገር "አጥር" የሚለው በሁለት አቅጣጫዎች መታየት መቻሉ ነው፡፡ በቁ 12 እንደ መጠለያ አጥር ሲሆን በቁ 13 ላይ ደግሞ እንደ ማገጃ አጥር ነው፡፡

የዳዊትን ቤት ንግስና (በቁ 13ሀ) ከያህዌ (በቁ 13መ) ጋር እንዴት ትይዩ እነደሆነ ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡ ይህ የሚያሳየው መለኮታዊ ንጉስ (5፡2-4) ነው፡፡ ነገር ግን ይህ አውድ ሊታይ የሚገባው ያህዌ ምርኮው እንዲከሰት የደረገነ ደግሞ ከምርኮ መመለስንም ያደረገው እርሱ ነው፡፡ ንጉስ የሚለው ቃል እግዚአብሔርን ለማመላከት ሊሆን ይችላል (4፡7፤ 1 ሳሙ. 8፡7)፡፡

▣ "በሩ" ይህ ቃል በብሉይ ኪዳን ያንድን ከተማ ሀይል ወይንም ያንድን ሀገር ሀይለኝነት መግለጫ ምሳሌያዊ አገላለፅ ነው፡፡ እዚህም ጋር የቃላት ጨዋታ አለ፡፡ እርሱም "የበጎች መንጋ በር" እና "ያገሪቷ ሀይል" ነው(የአሶርን)፡፡ እርሱም የሰሜኑን አስር ነገድ በ722አከልበ በፊት ማረኩ ናቸው፡፡

# ሚክያስ 3
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|
| ለክፉ ገገርዎችና ነቢያት | በሰማሪያና በኢየሩሳሌም ላይ ያነጣጠረ ዛቻ (1:2-3:12) | ሚክያስ የእስራኤል መሪዎችን አወዘ | ህዝቡን በሚጨቁኑት ገዢዎች ላይ |
| 3:1-3 | 3:1-3 | 3:1-4 | 3:1-4 |
| | | 2:3-4 | |
| 3:4 | 3:4 | | 3:5-8 |
| 3:5-7 | 3:5-8 | 3:5-7 | |
| | | 3:8-11 | ለገገርዎች፡ የጽዮን መውደቅ ትንቢት |
| | 3:9-12 | | 3:9-12 |
| | | 3:12 | |

### የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ vii ተመልከት)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ

2. ሁለተኛው አንቀጽ

3. ሦስተኛ አንቀጽ

4. ወዘተርፈ

## ዓውዳዊ እይታ

**ግልፅ የምዕራፍ ማውጫ** -እግዚአብሔር የይሁዳ አለቆች እንዲገነዘቡ ይጠራቸዋል

ሀ. የፖለቲካ መሪዎች 3፣1-4

ለ. ነብያት 3፣5-8

1. ሀሰተኛ ቁ 5-7
2. እውነተኛ ቁ 8

ሐ. አለቆች ካህናት እና ነብያት 3፣-12

መ. በሀ እና ሐ መካከል በቀላሉ የሚታይ መመሳሰል አለ ( ይህም፣ ስሙ*shema*፣ Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ) )

## የቃል እና የሐረግ ጥናት

### ሚክያስ 3፡1-4

**እንዲህም አልሁ። የያዕቆብ አለቆችና የእስራኤል ቤት ገዦች ሆይ፥ እባካችሁ ስሙኝ ፍርድን ታውቁ ዘንድ አይገባችሁምን?**
**2 መልካሙን ጠልታችኋል፥ ክፉውንም ወድዳችኋል ቁርበታቸውን ገፍፋችኋቸዋል፥ *ሥጋቸውንም* ከአጥንታቸው ለያይታችኋል**
**3 የሕዝቤን *ሥጋ* በልታችኋል፥ ቁርበታቸውንም ገፍፋችኋቸዋል፥ አጥንታቸውንም ሰብራችኋል ለአፍላል እንደሚሆን *ሥጋ* ለድስትም እንደሚሆን ሙዳ ቈራረጣችኋቸው።**
**4 የዚያን ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ይጮኻሉ፥ እርሱም አይሰማቸውም**
***ሥራቸውንም* ክፉ አድርገዋልና በዚያን ጊዜ ፊቱን ከእነርሱ ይሰውራል።**

**3፡1** ይህ ስም 2፤12-13 ጋር የተደረገ ከፍተና ንፅፅር ነው፡፡ ድንገተኛ የሆነ ከፍርድ መመለስ የዚህ መጽሀፍ መገለጫ ነው፡፡ የዚህ አይነት የመሰረታዊ ትምህርት ምንአልባት ከዕብራውያን (antithetical parallelism) ግጥም ጋር ባልታወቀ ሁኔታ ተያያዥነት ሊኖረው ይችላል፡፡ ምዕራፍ 3 በተጨማሪ መሰረታዊ ፍርድን ያመለከታል፡፡

▣ ***"ስማ"*** ይህ በእብረይስጥ ሽማ Shema (BDB 1033፣ KB 1570፣ Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ) ) ይህም ማለት ለማድረግ ወይም ለመፈጸም መስማት ነው 1:2፤ 3:1፤ 6:1)፡፡ ይህ ቃል የመጽሐፉን ፍሬ ሀሳብ ያዘለ ይመስላል፡፡ በ1:2 ላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ፡፡

▣ ***የያዕቆብ አለቆችና የእስራኤል ቤት ገዦች ሆይ፥ …ፍርድን ታውቁ ዘንድ አይገባችሁምን?*** ሶስቱም የግጥው መስመሮ የሚናገሩት ለይሁዳ የፖለቲካ መሪዎች ነው (ቁ 9-10)፡፡ አነርሱም በሙሴ ህግ ይመላለሱ ዘንድ ይገባቸው ነበር ዘዳ. 12:17) ፡፡ ነገር ግን በራስ ወዳድነትና በስግብግብነት መርህ ተጓዙአሞፅ 5:15፤ ኢሳ. 1:16፣17)፡፡ ይሁዳንና እስራኤልን መጥራት ምናልባት የሚያሳየው (1) ይህ የተናገረው በ 722 ዓ ዓ አስሩ የአሲሪያ ሰሜናዊ ጎሳዎች ውድቀት በኋላ ወይም (2) ማውገዝ ማሳያ መንገድ ነው (ለምሳሌ ህዝ 23)፡፡

▣ **"ፍትህ"** የእብራይስጡ አጠራር (BDB 1048) ሰፋ ያለ ከቃሉ ጋር የሚያያዝበት መንገድ አለ

1. መዳኘት (ለምሳሌ ኢሳ 41፣1፣59፣11 ሆሴ 5፣1፣11 ሚክ 7፡9)
2. ፍትህ
   ሀ. የእግዚ/ር ድርሻ (ምሳሌ ሆሴዕ 2፤19
   ለ. የሰው ድርሻ (ምሳሌ ሚክ 3፣1፣6፣8፣ ኢሳ 1፣17
3. ደንብ (ድንጋጌ)
   ሀ. የእግዚአብሔር (ምሳሌ ኤር 8፣7)
   ለ. የንጉስ (ምሳሌ 1ኛ ሳሙ 8፡9‌11)
4. የዳኞች ውሳኔ (ምሳሌ ዘፀ 21፤1፣31፣24፣3
5. የአንድ ሰው ህጋዊ መብት ምሳሌ ኢሳ 10፣2፣49፣4፣ ኤር 5፣8
6. ልማድ (ምሳሌ 1ኛ ነገ 18፣28፣2ኛ ነገ 11፣14

   ይህ ቃል በሚክያስ ውስጥ በተደጋጋሚ ይገኛል (3:1፣8፣9፤ 6:8፤ 7:9) እንዲሁም በስምንተኛ ክፍለ ዘመን ትንቢቶች ውስጥ በብዛት ይገኛል

1. ኢሳያስ 41 ጊዜ
2. አሞፅ 4 ጊዜ
3. ሆሴዕ 6 ጊዜ

**3፡2-3** እንደእረኛ ለመሆን ይልቅ እነዚህ የፖለቲካ መሪዎች (ሕዝ 34) ጨካኝና ነፈሰ ገዳይ ሆኑ (ይህም "ገፎአችኋል" "ሰብሮአችኋል" "ቀራረጣችኋል") የህዝቤን ስጋ "በልታችኋል" የሚለው ሀረግ በምሳሌያዊ አገላለፅ በመዝ 14፣4፣27 እና ምሳሌ 30፣14 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

**3፡2** "***መልካሙን ጠልታችኋል፥ ከፉውንም ወድዳችኋል***" እነዚህ ሁለት ቃላት (BDB 12፣ KB 17) Qal ACTIVE PARTICIPLES ናቸው፡፡ ሁለቱም ግሶች የተቃፅላነት ባህሪያ አላቸው፡፡ መሪዎች ምላሽ ፈፅሞ ለእግዚአብሔር ሀሳብ ጋር የተለያየ ነበር ኢሳ. 1:16-17፣21-23፣26፤ 5:7፣8፣20፤ አሞፅ 5:15)፡፡

**3፡4** "***የዚያን ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ይጮኻሉ፥ እርሱም አይሰማቸውም***" "ይጮኸሉ" የሚለው ቃል በህግ ፊት አቤቱታ እንደማቅረብ ነው፡፡ እነዚህ መጥፎ ዳኞች የድሆችን የወላጅ አልባዎችና የመበለቶን ለቅሶ እንዳልሰው እግዚአብሔር የእነርሱን ልቅሶ አይሰማም፡፡ (ሪታ ዘዳግም 31፣17፣18 31፣20፣ ምሳሌ 21፣13፣ ኢሳያስ 1፣15 59፣2፣64፣7፣ ኤር 33፣5 ያዕ 2፣13

▣ **በዚያን ጊዜ ፊቱን ከእነርሱ ይሰውራል** ይህ አረፍተ ነገር (BDB 711፣ KB 771) በአይነቱ (JUSSIVE) ትኩረት የሚሻ ትዕዛዝ ነው፡፡ ነገር ግን ትርገሙ ይለያል፡ "እነርሱ" የሚለው ቃል ለአመፀኞች መሪዎች የተናገረ እንደሆነ ይመለከታል፡፡ ይህ የእግዚአብሔር የመጨረሻ ተቃውሞም የተገለው "እርሱም አይሰማቸውም" እና "ፊቱንም ከእነርሱ ይሰውራል" በሚል ነው፡፡

▣ ***"ሥራቸውንም ከፉ አድርገዋልና"*** እዚህ ጋር ነው ችግሩ፡፡ የእግዚአብሔር ህዝብ በተደጋጋሚ በግልፅ የኪዳናቸውን ግዴታ ሲፃፁና ሲቃውሙ እንመለከታለን፡፡ አሁን የዘሩትን እያጨዱ ነው 7:13፤ ኢሳ. 3:10፣11፤ ገላ. 6:7)፡፡

## ሚክያስ 3:5-12

**5 እግዚአብሔር ሕዝቤን ስለሚያስቱ ነቢያት እንዲህ ይላል በጥርሳቸው ሲነክሱ በሰላም ይሰብካሉ በአፋቸው ግን አንዳች በማይሰጥ ሰው ላይ ሰልፍን ያስቡበታል።**
**6 ስለዚህ ሌሊት ይሆንባችኋል እንጂ ራእይ አይሆንላችሁም ጨለማም ይሆንባችኋል እንጂ አታምዋርቱም ፀሐይም በነቢያት ላይ ትገባለች፥ ቀኑም ይጠቍርባቸዋል።**
**7 ከእግዚአብሔርም ዘንድ መልስ የለምና ባለ ራእዩቹ ያፍራሉ፥ ምዋርተኞችም ይዋረዳሉ ሁሉም ከንፈራቸውን ይሸፍናሉ።**
**8 እኔ ግን በደሉን ለያዕቆብ፥ ኃጢአቱንም ለእስራኤል እነግር ዘንድ በእግዚአብሔር መንፈስ ኃይልንና ፍርድን ብርታትንም ተሞልቻለሁ።**
**9 ፍርድን የምትጠሉ ቅን ነገርንም ሁሉ የምታጣምሙ እናንተ የያዕቆብ ቤት አለቆችና የእስራኤል ቤት ገዦች ሆይ፥ እባካችሁ ይህን ስሙ።**
**10 ጽዮንን በደም፥ ኢየሩሳሌምንም በኃጢአት ይሠራሉ።**
**አለቆችዋ በጉቦ ይፈርዳሉ፥ ካህናቶችዋም በዋጋ ያስተምራሉ፥ ነቢያቶችዋም በገንዘብ ያምዋርታሉ ከዚህም ጋር። እግዚአብሔር በመካከላችን**

አይደለምን? ክፉ ነገር ምንም አይመጣብንም እያሉ በእግዚአብሔር ይታመናሉ።
[12]ስለዚህ በእናንተ ምክንያት ጽዮን እንደ እርሻ ትታረሳለች፥ ኢየሩሳሌምም የድንጋይ ክምር ትሆናለች፥ የቤቱም ተራራ እንደ ዱር ከፍታ ይሆናል።

**3፡5 "እግዚአብሔር ሕዝቤን ስለሚያስቱ ነቢያት እንዲህ ይላል"** ነብያቶች የያህዌን ሀሳብ ለማወቅ አማራጭ መንገዶች ነበሩ፡፡ እግዚአብሔር ለህዝቡ ሲገልጽ የሚገባቸው እነርሱ አስቀድመውም አላወቁትም (ሆሴ 4፣1) 1ኛሳሙ 28፣6፣ ሳኦል ስለ ያህዌ ሶስት ጥያቄዎች ይጠይቃል፡፡

1. ህልሞች
2. ኡሪምና ቱሚም (ማለትም ሊቀ ካህን)
3. ነብይ (ይህም ሳሙኤል)

▣ **"ህዝቤን ስለሚያስቱ"** ይህ ግስ (BDB 1073፣ KB 1766፣ Hiphil PARTICIPLE) ማለትም "እንድስት ማድረግ" ማለት ነው አሞ 2:4፤ ሆሴ 4:12፤ II ነገ. 21:9፤ ኢሳ. 3:12፤ 9:16፤ ኤር. 50:6) ፡፡ ይህ በ ምዕራፍ 2:6-7፤ 3:10-11 ውስጥ የተጠቀሱትን ሀሰተኞች ነብያት የሚመለከት ነው፡፡

▣ **"በጥርሳቸው ሲነክሱ በሰላም ይሰብካሉ በአፋቸው ግን አንዳች በማይሰጥ ሰው ላይ ሰልፍን ያስቡበታል"** ይህ ምግብን ስለመብላት ያመለክታል፡፡ ማለትም ከህዝቡ ለሚወጣ ስጦታ የሚተነብዩት ነው 3:5 አራተኛውና አምስተኛ መስመሮች)፡፡ ለእግዚአብሔር ሳይሆን ለራሳቸው ጥቅም ይተነብያሉ ኢሳ. 59:9-11)፡፡ ለሚሰጧቸው ሁሉ የመስማት የሚፈልጉት ይነግራቸዋል (እርሱም ሰላምና ብልጽግና) ለድሆች ደግሞ መከራና ችግር ይነግሯቸዋል፡፡

"መንከስ" የሚለው ቃል (BDB 675፣ KB 729፣ Qal PARTICIPLE (ቦዝ አንቀፅ) ) በተለምዶ የእባብ መንደፍን ያሰሳያል፡፡

▣ **"በሰላም ይሰብካሉ"** ሻሎም *(shalom)* የሚለው (BDB 1022) የእብራይስ ጥሬ ቃል ትርጉም "ሙሉነት" ማለት ነው፡፡ ግልፅ በሆነ ሁኔታ ነብያቶች ላጎርሱአቸው ይህም ማለት ምግብ ለሚሰጣቸው መልካምን ይናገራሉ (1 ሳሙ. 9:7-8) መልካም ዜናን ያበስራሉ (ለምሳሌ ኤር 5፣12፣6፣12-14፣8፣10-11፣13፣14፣23፣17 ህዝ 13፣10)፡፡ ነገር ግን በደንብ ላልመገቡአቸው ሰልፍን ይወጁበታል (BDB 536)፡፡ መልክታቸው መሰረት ያደረገው የራስ ወዳድነት ፍላጎት ላይ እንጂ በያህዌ ፍቃድ ላይ አልነበረም፡፡ እነዚህ ነብያት የሚገኙት ለግለቦች እንዲሁም ለንጉስ አማካሪነት ነበር፡፡ ነገር ግን የነብያት ፀጋ መስጠት የተለመደ ነበር፡፡ ለምሳሌ I ነገ. 14:3፤ II ነገ. 4:42፤ 8:8-9) ችግሩን ግን ያለው መልዕክቱን በማምታታት ላይ ነው፡፡

▣ **"ቅዱስ ሰልፍን** ያስቡበታል" "ቅዱስ" የሚል ቃል በ ማሶሬቲኩ (ማሶሬቲኩ) የለም ነገር ግን ቃሉ (BDB 872፣ KB 1073፣ Piel PERFECT) የመጣው ከዕብያስጥ ቃል ነው፡፡ ቃሉ የሚያመለክተው ሰዎችን ለጦርን ለመለየት ነው (ኤር 51፣27፣ ኢዮ 3፣9) እና በዚህ ላይም እንዲዘሁ (Robert Girdlestone፣ Synonyms of the Old Testament፣ ገጽ. 177)። ይህ የሚያመለክተው እውነተኛ ነብያት ይህም ማለት እግዚአብሔር መልዕክቶቸችን የማይታዘዙትን ከፉ ነገሮ ቸግር ጦርነት ይልክባቸዋል፡፡ እንደእኔ ሀሳብ ይህ ዓይነት ዘዴ ዛሬም በአሜሪካ የአስራት ሥርዓት ጋር ይመሳሰላል፡፡

**3፡6 ለሊት … ጨለማ …… ፀሐይማ … ትገባለች ቀኑም ይጠቁርባቸዋል"** እነዚህ አራቱ አስደንጋጭ ተለዋዋጭ ዘይቤዎች ናቸው(በኢሳያስ የፀሐይ ብርሃን አልተጠቀሰም) ስለ እግዚአብሔር መንፈስና እይታ ከመሪዎችና ከነብያት መውሰድ ያሳያሉ፡፡ ጨላማ እንደ ራዕይ እጥረት ሊወስድ ይችላል ይህም ማለት ብርሃን ለምሳሌ መዝ 82፣5 ምሳሌ 2፣13 4፣19 ኢሳ 59፣9 2ኛ ጴጥ 1፣19 ለና 1፣16-2፣11 ጨለማ ፈርድን ይመለከታል በሌላ አገላለፅ የእግዚአሔር ቃል ረሀብ ይለዋል፡፡ እግዚአብሔር ለፀሎታቸው ለነብያቶች አይመልስም፡፡

▣ **"ራዕይ"** ራዕይ (BDB 302) እና ህልም (BDB 321) እዮብ 33፣15 ኢሳ 29፣7 ዳን 7፣1 ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔር መልእክት መቀበያ መንገድ ተደርገው በመገለፅ ይመሳሰላሉ፡፤ ብዙ ጊዜ ሁሉንም ያጠቃለለ ባይሆንም ራዕይ የሚከሰተው በቀን ሲሆን ህልም ደግሞ በለሊት ነው፡፡

▣ **"መለኮታዊ"** ይህ (BDB 890፣ KB 1115) ጥንታዊ የእግዚአብሔር ፈቃድ በሚታይና ሜካንካል መንገድ የሚታወቅበት ነው፡፡ (ምሳሌ አሉታዊ ዘዳ 18፣9-22 አዎንታዊ 1ኛ ሳሙ 28፣6 እና ዘፍ 44፣5-15)፡፡

**3፡7 "ባለራእዮች"** ይህ የነብያቶች የቀድሞ መጠሪያቸው ነው፡፡ (BDB 302 ለምሰሌ ሳሙ 9፣9 2ና ሳሙ 24-11 1ኛ ቆሮ 9፣22 25፣5 ኢሳ 30፣10 አምፅ 7-12)፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **NASB፣ NKJV** | ***"ዕረፍት የተሰማው"*** |
| **NRSV፣ TEV** | ***"ማዋረድ"*** |
| **NJB** | ***"በፍረሀት መሞላት"*** |

ይህ አባባል (BDB 101፣ KB 116፣ Qal PERFECT) ትርጉም መዋረድ ሲሆን (ለምሳሌ 7፣16፣ ሆሴ 4፣19፣10፣9፣13፣15 በተጨማሪም በኢሳያስ መጽሐፍ ውስጥ ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ ተጠቅሶአል)፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **NASB** | ***"ማፈር"*** |
| **NKJV** | ***"ግራ መጋባት"*** |
| **NRSV** | ***"ሀፍረት መላበስ"*** |
| **TEV** | ***"መዋረድ"*** |
| **NJB** | ***"በግራ መጋባ መዋጥ"*** |

ይህ ግስ (BDB 344፣ KB 340፣ Qal PERFECT) "ሀፍረት" የሚለው "ማዋረድ" ከሚለው ጋር ጎን ለጎን የሚሄድ ነው፡፡ በኢሳ 24፣23 ላይ በአንድ ላይ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

1. በኢሳ 1፣29 ጣዖት አምላኪዎች
2. በዚህ ቦታ ላይ ምዋርተኞ
3. በኤር 50፣12 ውስጥ ባቢሎን

▣ **"ከንፈራቸውን"** ቀጥተኛ ትርጉሙ የላይኛው ከንፈር ላይ የሚቀበል "ፂም" (BDB 974) ነው፡፡ በፂም መሸፈን የሚለው ምሳሌ ማለት(1) በትልቅ ሀዘን ውስጥ መዋጥ ሕዝ. 24:17፣22) ለማለት ነው ወይም (2) ሐፍረት (በዘሌ 13፣45፣ የለምፅ ደዌ ያለበት ተብሎአል)፡፡

▣ **"በእግዚአብሔር ዘንድ ምላሽ የለምና"** እነዚህ መሪዎች በቁ 4 ላይ እንደተገለጸው ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት ችግር ነበረበት (1ኛ ሳሙ 258፣6)፡፡ ሰማያት ዝም ብለዋል፡፡

**3፡8** ቁጥር 5-7 ስለሀሰተኛ ነብያት እነደሚናገረው ቁ 8 ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ስላላቸው ስለ እውነተኛ ነብያት ይናገራል፡፡ (መዝ 89 13-14 እነዚህ ነብያት የእግዚአብሔር ባህሪያት የሚያካፍሉ ወይንም በተሻለ መንገድ የሚያንፀባርቁ ናቸው)፡፡
አስተዋሉ እውነተኛ ነብይ የተሞላው (BDB 569፣ KB 583፣ Qal PERFECT) (1) በሀይል (BDB 470)፤ (2) በየህዌ መንፈስ (ኢሳ. 11:2፤ ሕዝ. 2:2)፤ (2) በፍትህ (BDB 1048 "በፍርድ") እና (4) ማፅናናት (BDB 150 "ኀይል") ኃጥአት ለማጋለጥ በድፍረት ኢሳ. 58:1)፡፡ በመሪዎች ጋር ሲነፃፀር ሐፍረት ጥልቅ ሀዘንና አቅም ማጣት፡፡

ምንም እንኳ የሶስተኛው የሰላሴ አካል የመንፈስ ቅዱስ በሰው ውስጥ ማደር፣ በብሉይ ኪዳን ትምህርት ውስጥ በግልፅ ባይኖርም የእግዚአብሔር በግል ከሰዎች ውስጥ እና አብሮ መገኘቱ ተገልጦአል፡፡

1. ባሰልኤል ዘፀ. 31:3፤ 35:31
2. ኢያሱ ዘዳ. 34:9
3. ሳኦል 1 ሳሙ. 19:23-24
4. ኤልያስ 1 ነገ. 18:46
5. ሕዝቅኤል ሕዝ. 1:3፤ 37:1፤ 40:1
6. ሚኪያስ ሚክ 3:8
7. መሲህ ኢሳ 11:2፤ 48:16፤ 61:1 (ሉቃ 4:18-19)

በተጨማሪ በነብያትና በመንፈስ መካከል ያለውን ግንኙነት በሆሴዕ 9፣7 ይመልከቱ

▣

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"በሌላ በኩል"** |
| **NKJV** | **"በእውነት ግን"** |
| **NRSV፣ TEV** | **"ለእኔ ግን"** |
| **NJB** | **"እኔጋ እንደዚያ አይደለም"** |

ማሶሬቲኩ ማሶሬቲኩ "ግን በእርግጥ እኔ" የሚል ቃል በቃል አለው፡፡ ግን እብራይስጡ ተውሳከ ግስ (BDB 19) ጠንካራ የተገላቢጦሽ ነው(በኢዮ፣ 1:11፤ 11:5፤ 12:7፤ 13:4፤ 14:18፤ 17:10፤ 33:1 ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል)፡፡

▣ **"ያዕቆብ እራኤል"** የቁ 8 ሁለት መስመሮች እንደሚያመለክቱት ሚከያስ የሚናገረው ስለይሁዳ ስለ እስራኤል ኃጥአት ነው፡፡ ቁ 9 የመጀመሪያው መስመርና ሁለተኛ መስመርም እንደዚሁ

**3:9**

| | |
|---|---|
| **NASB፣ NKJV** | **"አሁን ይህንን ስሙ"** |
| **NRSV** | **"ይህን ስሙ"** |
| **TEV** | **"እኔን ስሙኝ"** |
| **NJB** | **"ይህ ቃል በቀጥታ ስሙ"** |

ይህ ሀረግ ቃል በቃል "ስማ ይህን እፀልያለሁ" የሚል ነው፡፡ ግሱ VERB (BDB 1033፣ KB 1570) Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ) ፣ ሲሆን ለልመና (אָנָּ) ጥቅም ላይ የዋለ ሀረጋዊ ግስ (PARTICLE) ተከተሎ ነው እና ከዚያም በኋላ ገላጭ የሆነውን "ይህን"፡፡

▣ **"ፍርድን የምትጠሉ"** ይህ ግስ (BDB 1073፣ KB 1765፣ Piel PARTICIPLE) ትርጉሙ ጥላቻን እንደሳደር የሚቀጠር ነው፡፡ ለምሳሌ አምጽ 5፣10፣6፣8፣ ኢሳ 14፣19፣49፣7፡፡ እነዚህ መሪዎች በቀጥታ መሳሳት ሳይሆን ለትክክለኛ መልካምና ለእግዚአብሔር ነገር ጥላቻ ነበረባቸው ኢሳ. 5:20፤ አሞ 6:12)፡፡ "ፈትህ" የሚለው ቃል (BDB 1048) በቁ 8 እና 9 ላይ ተደጋግመዋል፡፡

▣ **"ቅን ነገርም ሁሉ የምታጣምሙ"** "ማጠመም" የሚለው ግስ (BDB 786፣ KB 875፣ Piel IMPERFECT) ትርጉሙ አንድን ነገር በቀጥታ እንዳይሰራ ማድረግ ወይም መቆልመም (ምሳ. 10:9፤ 28:18፤ ኢሳ. 59:8)፡፡

"ቅን" የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን የፍትህ ወይም ጽድቅ ከተገኘበት ስርወ ቃል አመጣጥ (etymological root) ያለው ነው ይህም ማለት ቀጥታ ጠርዝ ወይንም የመለኪያ ገመድ (ኢሳ 5፡20) ማለት ነው፡፡ ስለጥያት የተነገሩ አብዛኞቹ የእብራይስጥ ቃላት የሚገልጸው ከዚህ መለኮታዊ የተለየ መሆኑን ነው፡፡ ጽድቅ የሚለውን ልዩ ርዕስ በሆሴ 2፤19 ይመልከቱ

**3፡10** "**ፅዮን ኢየሩሳሌም**" ፅዮን ከሰባት ተራራዎች መሀከል ኢየሩሳሌም የተገነባችበት ተራራ ነበር፡፡ ብዙጊዜ ለህዝብና ለከተማይቱ መጠሪያ ሆኖ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

▣ **"በደም ...በኃጥአት"** እነዚህ ሁለት ስሞች ጎን ለጎን ናቸው ኤር. 22:13፣17፤ ዕን.2:12)፡፡

**3፡11** በዚህ ቁጥር ውስጥ የተጠቀሱ ሶስቱም የመሪዎች ቡድን ስለስግብግብነታቸው ስለጥቅም ብቻ ፈላጊነታቸው የተወገዙበት ቁጥር ነው (7:3፤ ኢሳ. 56:9-12፤ ኤር. 5:30-31፤ 6:13-14፤ 8:8-12፤ 14:13-18፣22-23፤ 26:10-15፣16፤ ሕዝ. 13፤ 22:23-31)፡፡

▣ **"በጉቦ ይፈርዳሉ"** ይህ የዳኞችን የአለቆችን ሙስና ይመለከታል (7:3፤ II ዜና. 19:7፤ ኢሳ.1:23፤ 5:23)፡፡ ሁብት በአይሁዳውን ህይወት ትልቅ ስፋራ አለው፡፡

▣ **"ካህናቶቹዋም በዋጋ ያስተምራሉ"** በሙሴ ትዕዛዝ መሰረት ለካህናት ወይም ስሌዋውያን ድርሻ አንዱ ለህዝብ አስምህሮት መስጠት ነው ዘዳ. 33:10፤ II ዜና. 15:3፤ 17:9)፡፡ ለሙሴ ህግ የካህናዊ መረዳት እና ትምህርት (እና ኑሮ) ለጤናማ መንፈሳዊ እስራኤል ወሳኝ ነበር (ሆሴዕ 4፣6)፡፡

▣ **"በእግዚአብሔር ይታመናሉ"** "መታመን" ምርኩዝን መደገፍ ማለት ነው (BDB 1043፣ KB 1612፣ Niphal IMPERFECT፣ መዝ. 23:4)፡፡ እነዚህ መሪዎች ክፉ ስራዎችንና ህዝባቸውን በሃይማኖታዊ ካባ ለመጠቅለል እየሞከሩ ነው፡፡ ስራቸው ሌላ በአፋቸው የሚናገሩትን ሌላ ነው ኢሳ. 29:13)! የያህዌን ጥበቃ ተስፋ ያደርጋሉ (የኪዳኑ ጥቅም) ከርሱ ጋር ባላቸው ከኪዳናዊ ግንኙነት ምክንያት፣ ግን በኪዳኑ መሰረት የሚጠበቅባቸውን ፈፅመው ትተውት ነበር (ዘዳግም 27፡29 ዘሌ 26 ኢሳ 6፣9፣10፣29፣13)፡፡

▣ **"ክፉ ነገር ምንም አይመጣብንም"** ይህ በተደጋጋሚ ሀሰተኛ ነብያት የሚሉት የታወቀ ባህላዊ አባባል የሆነ ነው (ኤር. 5:12፤ 23:17፤ አሞፅ 9:10)፣ ነገር ግን ትክክል አይለደለም፡፡

**3፡12** ይህ ለይሁዳ ህዝቦች ከበድ ያለ አስደንጋጭ ንግግር ሳይሆን አያቀርም፡፡ እየሩሳሌምና የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ እንማይጠፉ በእግዚአብሔር ቃልኪዳን ታመኑ (ይህም ማለት ለህዝቅኤል የኢሳያስ ተስፋዎች ምናልባት መሰረቱ በ2ና ሳሙ 7) ቢሆንም ለኪዳኑ ስላቸው ቸልተኝን የተነሳ የእግዚአብሔር ለግዞት አሳልፎ ይሰጣቸዋል ኤር. 26:18)፡፡ እየሩሳሌም እንደማርያ ትሆናለች (cf. 1:6)!፡፡ ይህ ስለ እስራኤል ውድቀት የሚያወራ የመጀመሪያ ትንቢት ነው (እንደ እርሻ ትታረሳለች) መቅደስዋም (ይህም ማለት ሳይተከል የሚበቅል ወይም በቀጥተኛ ትርጉሙ "ዱር") ይህ በስነመለኮት በኢሳ 5 ጋር ያገናኛል፡፡ ሚክያስ በ701 ዓ ዓ ይህ ባልተፈፀመበት ጊዜ እነደቀለዱበት አኔ እርግጠኛ ነኝ (ይህም ማለት የሰናክሬብ ጦር በእግዚብሔር ተደመሰሰ II ነገ. 19:35-37)፣ ነገር ግን ነብዩ ልክ መሆኑ የተረጋገጠው በ586 ዓ ዓ ነበር ይህ ትንቢት ቃል በቃል የባቢሎን ንጉስ ዳግመዊ ናቡከደነፆር ይሁዳን በከበባት ጊዜ በተፈፀመበት ወቅት፡፡ F. F. Bruce፣ *Answers to Questions* ንጉሱ ህዝቅያስ (1:1) እና የይሁዳ ህዝብ ለሚክያስ መልእክት ምላሽ መስጠታቸውን እና እግዚአብሔር ከመፍረድ እንደራራ ያረጋግጣል፡፡

▣ **"በእናንተ ምክንያት"** እነርሱ (የፖለቲካና የሀይማኖታ መሪዎች) የሚገጥማቸው የእግዚአብሔር ፍርድ ብቻ ሳይሆን (እንደዘራፊዎች) ድርጊታቸው ለእግዚኢብሔር ፍርድ በእነርሱ ላይ መሁን ምክንያት ነበር፡፡

## ለሚክያስ 2-3 የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. በ2፣6 -11 ውስጥ የሀሳተኛ ነብያት መልእክት መገለጫዎች ምንድን ነበሩ?
2. 2፤12-13 ለምንድ ነው ከአውዱ ሀሳብ ወጣ ያለው?
3. አንድ ሰው በእውነተኛ ነብያት እና በሀሰተኛ ነብይ መሀከል ያለውን ልዩነት እንዴት ሊገልጸው ይችላል?
4. እግዚአብሔር እንዴት በዳዊት ዙፋን ላይ የሚቀመጥ ሰው እነደማይታጣ ተስፋ ገብቶ (2ሳሙ 7) አሁን ደግሞ እነዴት ነው ስለየሩሳሌም ሙሉ በሙሉ መጥፋትና ስርወ መንግስት መቋረት የሚያመለከተው?

# ሚክያስ 4

## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|
| በጽዮን ውስጥ የጌታ መንገስ | የኢየሩሳሌም የወደፊት ክብር እና የዳዊት መንግስት መታደስ | የጌታ አለምአቀፋዊ ንግስት | ለወደፊት የያህዌ በጽዮን ውስጥ መንገስ |
| | (4:1-5:15) | | |
| 4:1-3 | 4:1-4 | 4:1-2 | 4:1-4 |
| | | 4:3-4 | |
| 4:4-5 | | | |
| | 4:5 | 4:5 | 4:5 |
| የጽዮን የወደፊት አሸናፊነት | | እስራኤል ከምርኮ ትመለሳለች | የተበታተኑ መንጋዎች ወደ ጽዮን ይሰባሰባሉ |
| 4:6-8 | 4:6-7 | 4:6-7 | 4:6-7 |
| | 4:8 | 4:8-12 | 4:8 |
| | | | የጽዮን መከበብ፣ምርኮ፣ እና ነፃ መውጣት |
| 4:9-10 | 4:9-10 | | 4:9-10 |
| | | | ጠላት በአውድማው ላይ ይቀጠቀጣል |
| 4:11-12 | 4:11-13 | | 4:11-13 |
| 4:13 | | | የዳዊት ስረወ መንግስት መጨነቅ |
| | | 4:13-5:1 | 4:13-5:1 |
| 4:14 | | | |

### የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ vii ተመልከት)

*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ

2. ሁለተኛው አንቀጽ

3. ሦስተኛ አንቀጽ

4. ወዘተርፈ

## የታሪካዊ ዳራ ጥናት

ሚክያስ 4፡1-3 ኢሳያስ 2-፡2- 4 ጋር በተጣም ተመሳሳይነት አለው፡፡ የስነ ጽሑፍ መወራረስ በግልፅ ይታወቃል፡፡ ይህም ሚክያስ እና ኢሳያሳስ አንደኛው ከሌላኛው ተወራርሷል፡፡ ወይም ከሌላ ከሶስተኛ ምንጭ ወርሰው ሊሆን ይችላል፡፡
የሚኪያስ መጽሐፍ ሁለት ታሪካዊ ጊዜያትን የሚያንጸባርቅ ይመስላል፡፡ በተጨማሪም የመጨረሻውን ዘመን ምልከታም ያሳያል፡፡ አጠቃላይ መጽሐፍ (1ኛ) የሶሪያና ኤፍሬማዊ ጦርነት Syro-Ephramatic (735 አከልበ) ታሪካዊ ዳራ ወይም (2ኛ) የይሁዳን በአሶራዊው ስናክሬም (በ701 አከልበ) መማረክ ታሪካዊ ዳራ ያሳያል፡፡ ነገር ግን በምዕራፍ አራት መጀመሪያ ላይ እነዚህ ሀለቱ ታሪካዊ ወደፊት ሊሆኑ ይሉትን (1ኛ)

የባቢሎናውንን ወረራ (ቁ 10) እና (2ኛ) የታሪክን ዝቅጠት እንዲሁም መጪውን የእግዚአብሔርን መንግስት እንደሚያመለክቱ እንረዳለን፡፤ ይህንንም በተመለከተ መልስ ያላገኙ ጥቂት የማይባሉ ጥያቄዎች አሉ?

1. ከብሉይ ኪዳን ነብያቶች ሁለቱንም የመሲሁን ምፃቶች ያየ አለ ወይ
2. ይህ የሚያመለክተው አይሁድ ተኮር ሺህ አመታትን ነው ወይስ ቤተክርስቲያን ተኮር ዘላለማዊነትን ነው?
3. መንግስተትና ህዝቦች ያህዌን ወይም መሲሁን የሚያምንና የሚከተሉ ይሆናሉ ወይስ እሰከመጨረሻው ያመረሩ ጠላቶቹ ይሆናሉ?

## የቃላትና የሐረግ ጥናት

### ሚኪያስ 4፡1-5

**[1]በመጨረሻውም ዘመን የእግዚአብሔር ቤት ተራራ በተራሮች ራስ ላይ ጸንቶ ይቆማል፥ ከኮረብቶችም በላይ ከፍ ከፍ ይላል አሕዛብም ወደ እርሱ ይጐርፋሉ።**
**ከጽዮን ሕግ፥ ከኢየሩሳሌምም የእግዚአብሔር ቃል ይወጣልና ብዙዎች አሕዛብ ሄደው። ኑ፥ ወደ እግዚአብሔር ተራራ፥ ወደ ያዕቆብ አምላክ ቤት እንውጣ እርሱም መንገዱን ያስተምረናል፥ በፍለጋውም እንሄዳለን ይላሉ።**
**[3]በብዙዎችም አሕዛብ መካከል ይፈርዳል፥ በሩቅም ባሉ በብርቱዎች አሕዛብ ላይ ይበይናል ሰይፋቸውንም ማረሻ፥ ጦራቸውንም ማጭድ ለማድረግ ይቀጠቅጣሉ ሕዝብም በሕዝብ ላይ ሰይፍ አያነሣም ከእንግዲህም ወዲህ ሰልፍ አይማሩም።**
**[4] የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር አፍም ተናግሮአልና ሰው እያንዳንዱ ከወይኑና ከበለሱ በታች ይቀመጣል፥ የሚያስፈራውም የለም።[5] ሕዝብም ሁሉ እያንዳንዱ በየአምላኩ ስም ይሄዳል፥ እኛም በአምላካችን በእግዚአብሔር ስም ለዘላለም እንሄዳለን።**

4፡1፤3-5 እነዚህም የሚክያስ ቃላቶች ናቸው፡፡ እንደ ቁጥር 9-13 በቁጥር 2 ላይ የመንግስታት ወይም ህዝቦች ንግግር ሲሆን በቁጥር 6-8 ደግሞ የያህዌ ንግግር ነው፡፡ ይህ ክፍል እንግዲህ ከኢሳያስ 2፡2-4 ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

**4፡1 "በመጨረሻው ዘመን"** ይህ ሀረግ (BDB 31 CONSTRUCT with BDB 398) በብሉይ ኪዳን በተደጋጋሚ ተጠቅሷል፡፡ (ዘፍ 49፣1 ዘቁ 24፤14 ዘዳ 4፤30 እና 31፤29 ኢሳ 2፤2 ኤር 23፤20 እና 3 ፤24 48፣47፣49፣39፣ ህዝ 38፤16 ዳን 10፡14፤ ሆሴ 3፡5 ሚክ 4፡1) BDB (p. 31) በዚህ መልኩ ያብራራዋል፡፡ "እንደ ተናገሪው አስተሳብና እይታ የታሪካ መጨረሻው የሚያደርስበት ከአውዱ ጋር ልዩነት አለው፡፡ ግን አብዛኛውን ከመጪው የመሲሁ ነገር ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡"

ሐረጉ የተወሰነ ልዩነት አለው

1. ዳን 2፡28 BDB 1079 CONSTRUCT ከ BDB 1095 ጋር (የዘመን ፍፃሜ)
2. ህዝ 38፡8 BDB 31 CONSTRUCT ከ BDB 1040 ጋር (የኋለኛው ዘመን)

በህዝ 38 ላይ ያለው ሐረግ ከታዋቂ የነቢያቶች ሐረግ ማለትም "ያ ቀን" ወይም "በዚያን ቀን" ጋር ትይዩንት አለው (ህዝ 30፡2-3፤ 38፡10፣ 14፣ 18፤ 39፡ 11 እንዲሁም ኢሳ 2፤12 10፣3፣13፣6፣ እና 9፤34፣2 እና 8፣61፣2 ኤር 30 7 እና 8 ኢዩኤል 1፡15 2፤11፣31 ኢምድ 5፡18 ሶፍ 1፤14፣15፣16 እና 18)፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ የልውውጥ ወቅት የነበሩት አይሁዳውያን የሁለት ትውልዶችን ጽንስ ሀሳብ (1)የአሁኑ ክፉ ትውልድ (በዘፍ 3) የተጀመረ እና (2) የመጨረሻው ዘመን ፃድቃን ትውልድ "በመሲሁ ዘመን የተጀመረ" በማለት አርቅቀዋል (ሚክ 3፡12-13፤ 5፡1-5ሀ) ነግ ግን ከቀጣዩ የአዲስ ኪዳን መለገጥ አንፃር (በሂደት እየጨመረ የሚሄድ መገለጥ) የምንረዳው መሲሁ ሁለት ጊዜ እንጂ አንድ ጊዜ ብቻ እንዳልሆነ ነው፡፡
ከኢየሱስ በቤተልሄም መወለድ ጀምሮ እስከ ደግሞ ምጻት ደረስ ያለው ጊዜ "የመጨረሻ ዘመን" ተብሎ ይታወቃል፡፡ (ማብራሪያ) ትርጉም ሊሰጠው የሚገባው ሀሳብ የመሲሁ ደግሞ መፃት መቼ ይሆን? የሚለው ነው፡፡ (1) መቼ እንደሆነ የማይታወቅ የወደፊት ጊዜ? (2) ከምድራዊ የሺ ዓመታት ግዛት በፊት? (3) ከዘላለማዊነት ጅማሬ በፊት? የዚህ ጥያቄ ክፍለ ስለ ወደፊት ዘመ'ናት ያሉንን አይታዎች ይዳስሳል፡፡ ይህ ማለትስ ምድር መሰል (የታደሰው ኤደን ገነት ነውን?) ወይስ ጨርሶ የተለየ ነገር (1ቆሮ 15፣35-49) ? መጽሐፍ ቅዱስን ቃል በቃል እንየውን? (ቅድመ ሺ አመት ጊዜ) ወይም ስነ ጽሁፍዊ አተረጋጎም D. Brent Sandy፣ Plowshares and Pruninghooks)? እና ልዩ ረዕስ ሁለቱ ትውልዶች በሆሴህ 3፡5 ላይ ተመልከት፡፡

▣ **"የእግዚአብሔር ቤት ተራራ"** እየሩሳሌም በሰባት ተራሮች ላይ ነው የተገነባቸው፡፡ ከእነዚህም ሁለቱ ዋና ዋናዎች የሞሪያ ተራራ (ቤተመቅዱሰ የቆመበት) እና የፅዮን ተራራ (የኢያቡሳውያን ጥንታዊ ግንብ እና የንጉስ ዳዊት ቤተመንግስት መገኛ ማለትም ኋላ ላይ የታላቁ ከተማ ተምሳሌት የሆነው ናቸው (ቁ 2)

የተራራ የእግዚአብሔር ማደሪያነት ነፀብራቅ በሜስፖታሚያውያን ከከነአናውያን በዕብራውያን (መዝ 48፡ 2 87 ኢሳ 14፤13፣ህዝ 28፣14) እና በግሪኮ ሮማዊያን ስነ ፅሁፍ ላይ በተደጋጋሚ ታይተዋል፡፡ ይህንን በተመለከተ ማራኪ ጽሁፍ "Divine Assembly፣" in Dictionary of Biblical Imagery፣ ገፅ 50-53 እና በተጨማሪም "ተራራ" (ገፅ. 572-574) ይመልከቱ፡፡

1. ለመሴፓታማዊያንውን ዘኍራትስ (ሰው ሰራሽ ተራራዎች)
2. ለአነአናውያን (የዛፎን ተራራ)
3. ለዕብራውያን የፅዮን ተራራ /የሞሪያ ተራራ/ ወይም ሰሜናዊው ተራራ
4. ለግሪካውያን የኦሊምፐስ ተራራ ናቸው፡፡

ሚኪያስ የኢየሩሳሌምን እና የቤተመቅደሱን (3፡12) ሙሉ በሙሉ መፍረስ ተንብዮአል፡፡ አሁን ግን የእግዚአብሔርን ሁሉን አቀፍ መንግስት መምጣትና ለኢየሩሳሌም ፍሬ መስጠት መቻል በአፅንኦት ይገልፃል፡፡ እግዚአብሔርም በአዲስቷ የጽዮን ተራራ ("አዲስቷን ኢየሩሳሌም ራዕይ 21) ላይ ይነግሣል፡፡ የተናቀ ተራራ በምድር ላይ እጅግ ተፈላጊ ተራራ ይሆናል፡፡ (መስመር 2፡3 እና 4 ትይዩነት አስተውል) ለብሉይ ኪዳን እና ለአዲስ ኪዳን የወደፊት ጊዜያት ትንቢቶች ልዩነት የ4፡7ን ማስታወሻ ተመልከቱ፡፡

▣ **"ከኮብራቶችም በላይ ከፍ ከፍ ይላል"** ይህ ስእላዊ ቋንቋ የቤተመቅደስን በኢየሩሳሌም መግነን ይመለክታል፡፡ አይሁዳውያ እንዲህ ይላሉ "ወደ ኢየሩሳሌም እንሂድ" ይህ ፅንስ ሀሳብ ሁሉን አቀፍ ወደ ሆነ ሀሳብ ይሄዳል፡፡ የሞሪያ ተራራ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ቦታ ትልቅ እና ካሉት ንፍቀ ክበቦች ሁሉ ከፍ ያለ እንዲሁም በጣም ጠቃሚ የሆነ ተራራ ነው፡፡

▣ **"አህዛብም ወደ እርሱ ይጎርፋል"** ይህንን ሁሉን አቀፍ እንኳር አስተውሉ፡፡ 4:1-3 ይህም በብሉይ ኪዳን በተደጋጋሚ የተጠቀሰ ርዕስ ነው፡፡ (መዝ 22፣27፣66፣4፣86፣9፣ ኢሳ 19፣21፣23፣27፣13፣45፣20፣25፣50፣6፣8፣66፣23 ኤር 3፣17፣4፣2፣12፣14-16 ዘካ 2፣11፣8፣20፣23፣14፣16 በብሉይ ኪዳን እንዴት ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ተራራ መቅደስ እንደሚመጡ አስተውሉ፡፡ በአዲስ ኪዳን ህዝቡ ከመቅደስ ወደ ውጪ ሲላኩ እንመለከታል፡፡ (ማቴ 28፣18-20 ሉቃ 24 47 የሐዋ 1-8)፡፡ በኢየሱስ በማመን የእግዚአብሔር ቤተመቅደሶች የሚሆኑ አዲስ ህዝቦች አሉ፡፡

በኢየሩሳሌም ወዳለው ቤተመቅደስ ከመምጣት የአዲስ ኪዳን መቅደሶች ወደ አለም (ህዝቦች) ይሄዳሉ፡፡

"የእግዚአብሔር ሁሉን አቀፍ ዘላለማዊ እና ነጻ የማወጣት አላማ እነሆ በስራ ላይ ነው" በብሉይ ኪዳን እና በአዲስ ኪዳን መካከል ያለውን የወደፊት መንግስት ትንቢቶች ልዩነት ሙሉ ማስታወሻ በልዩ ርዕስ 4-7 ላይ ይመልከቱ፡፡

በ3:12 (ሞርኮ) እና 4:1 (ተሀድሶና ክብር ከፍታ) መካከል ያለውን ንፅፅር አስተውሉ እንዲሁም የመጪውን መሰህ ንግስና ሁሉን አቀፋዊ ባህርይም አስተውሉ (2፣13፤ 5፣2-5ሀ)፡፡ ይህ ሁሉን አቀፋዊነት የኢሳያስ እና የሚኪያስ ተመሳሳይ ባህርይ ያሳያል፡፤ (ዳን 7፤9-10 13-14)፡፡ ህዝቡ እንደ አመታዊ ክብረበአል በየአመቱ የሚመጡ ቢሆን ወይም እንዴ መጥተው ወደቤታቸው የሚመለሱ ቢሆን ነገሩ ግልፅ አይሆንም ነበር፡፡ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው በባቢሎናዊያን የምርኮ አውድ (ቁ10) "ይጎርፋሉ" የሚለው ግሥ (BDB 625፣ KB 676፣ Qal PERFECT) በምርኮ ሥር የነበሩ ህዝቦች ከባቢሎናዊያን እጅ ወጥተው መጉረፋቸው ነው ከሚያሳ ይ ግስ ከ (*Qal* IMPERFECT) ጋር ተመሳሳይ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ ነው ማለትም (ኤር 51፣44) የእግዚአብሔር ምርጥ እቃ የሆነው ቂሮስ (ኢሳ 445:28) በምርከ የነበሩ ህዝቦችን ከምርኮ ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ አስችሏቸዋል፡፡

**4:2 "ብዙዎች አሕዛብ ሄደው...ይላሉ"** ቁጥር 2 አህዛብ ሊሉ የተገባቸውን ነገር ይጠቅሳሉ ሁሉም አህዛብ ሊመጡ ይችላሉ (ኢሳ. 11:10፤ 49:22) አንድ አምላክ ካለ (1 ነገ. 8:43፣60) ሁሉም በእርሱ አምሳል ተፈጥረዋል (ዘፍ. 1:26-27) እና ሁሉንም ነጻ ሊያወጣቸው ቃል ኪዳን ገብቷል (ዘፍ 3:15) ከዚያም "አንድ ህዝብ" የሚለው የመጨረሻ ግቡ ነው(ዘፍ 3:23-29፤ ኤፍ. 2:11-3:13):: ያህዌ እስራኤል በምትባል ህዝብ በኩል ራሱን ሊገልጥ ወደደ፡፡ እርሱም መጨረሻ ላይ ለየት ባለው እስራኤላዊ በኩል ነው፡፡ እርሱም በአገልጋዮ (ኢሳ 52:13-53:12)) እና በልጁ በኩል (መዝ. 2: 11 ሳሙ. 7) ነው፡፡

ቁጥር ሁለት ጥቂት የማይባሉ ትዕዛዛዊ አንቀፆች አሉት

1. "ኑ"BDB 229፣ KB 246፣ *Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)*
2. "ሂዱ"BDB 748፣ KB 828፣ *Qal* IMPERFECT
3. "አስተምሩ"BDB 434፣ KB 436፣ *Hiphil* IMPERFECT ግን ያንባቢውን ትኩረት በሚሻ መልኩ
4. " ተራመዱ" BDB 229፣ KB 246፣ *Qal* COHORTATIVE

▣ **"እርሱም መንገዱን ያስተምረናል በፍላጋውም እንዴዳለን"** በመጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ሦስት ከአቅጣጫዎች አሉ፡፡ የመጀመሪያው እግዚአብሔር በግል ማወቅ ሁለተኛው የእግዚአብሔር ፈቃድ ማወቅ (ቅዱሳት መጽሐፍትን መዝ. 19:7-14፤ 119:1-176) እና ሶስተኛው እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ መኖር (ቅዱሳት መጽሐፍትን መታዘዝ ኢሳ. 51:4-8) እግዚአብሔር የእርሱን ባህርይ የሚያንጸባርቅ ህዝብ ይፈልጋል፡፡ የእግዚአብሔር ግብ ሁልጊዜ አለምን መደረስ ነው፡፡ (6ኛ እና 7ኛ መስመሮች ተመልከት) የሰው ልጅ የተፈጠረው ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት እንዲያደርግ ነው፡፡

**4:3 "በብዙዎችም ከህዝባ መካከል ይፈርዳል"** ይህ በይሁዳ የፍርድ ሂደት እና በያሕዌ የፍርድ ሂደት መካከል ያለ የተለጠጠ ማነፃፀሪያ ነው፡፡ 3:1፣ 9፣ 11)፡፡ የያህዌ ፍርድ (የመሲሁ ፍርድ እንደ ዕዝራ ኢሳ 11 3-5 ሚኪ 5-4) ለህዝብ ሰላም ይሰጣል እንጅ አይበዘብዝም (ኢሳ 2:2-4)፡፡

▣ **"ሰይፋቸውንም ማረሻ ጠራቸውንም ማጭድ ለማድረግ ይቀጠቅጣሉ"** ይህ የመሲሁን ጊዜያት ሰላም የሚገልጽ መልካም ሰዕላዊ አገላለጽ ነው (መዝ. 46:9፣ 76:3፤ ሆሴ 2:18፤ ተቃራኒው በኢዩ 3:10 ላይ ተገልጧል)፡፡

የእነዚህ የእርሻ መሳሪያዎች የተፈጥሮ ተግባር ግልጽ አልሆነም (BDB 88 III)፡፡ ክብረት የተሰሩ ነገር ግን ከእንጨት እንደተሰራ የመሬት መቆፈሪያ ሳይሆን እንደ ማስንጠቂያ የሚያገለግሉ ነበር፡፡ እነዚህ ደግሞ በእንጨት ጫፍ ላይ የተሰኩ የብረት መሳሪያዎች ናቸው፡፡

▣ **"ከአንግዲህ ወዲህ ሰልፍ አይሰለጥኑም"** መሰልጠን የሚለው ግሥ (BDB 540፣ KB 531፣ Qal IMPERFECT) መማር ወይም መለማመድ ማለት ነው፡፡ (ለምሳሌ ዘዳ. 4:10፤ 17:19፤ መዝ. 119:73) ይህ ጦርነትን ሊያመለክት ይችላል፡፡ ማለትም የሚመጣውን ሁሉን አቀፍ ተሃድሶ ብቻ ሳይሆን በዘላቂ የሚቀጥል ነገር ነው መስመር ቁ 7 4ኛ መስመር)፡፡

**4:4 "ሰው እያንዳንዱ ከወይኑና ከበለሱ በታች ይቀመጣል"** እስራኤልና ይሁዳ በግብርና የታወቁ ማህበረሰብ ነበሩ፡፡ ምሳሌዊ አገላለጽ ስላማዊና ደስታ የሞላበትን የግብርና ኑሮ ያሳያል፡፡ እነዚህ ሐረጎች የሁሉንም የአብርሃም ዘሮች በተሃድሶ ወደ ተስፋይቱ ምድር መመለስን ያንፀባርቃል፡፡ ይህም የሁሉንም ቤተሰብ ርስት መታደስ ነው (1ነገ. 4:25፤ ኢሳ. 36:16፤ ዘካ. 3:10)፡፡

▣ **"የሚያስፈራውም የለም"** በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ በተገለገለት ተስፋና ቃል ኪዳን መሰረት ቢኖር፤ እግዚብሔር ከለላ ይሆናቸውል (ሌዋ 23:3-6) በሚከስ ያለው ክፍል የሚያንፀባርቅ የመጨረሻውን ዘመን ማለትም የመሲሁን መገኘትና መግዛት ነው፡፡

▣ **"የሰራዊት ጌታ የእግዚአብሔር አፍም ተናግአልና"** ይህ የሚናገረው የእግዚብሔርን ቃል ኃይለኝነትና የሚታመን መሆኑንን ነው (ኢሳ 40:5፣8፤ 45:23፤ 55:11)፡፡ የእግዚኢብሔር የተስፋ ቃሎችና ታማኝነቱ ለሰው ልጅ እምነት መሰረት ናቸው (1ነግ 8:56)፡፡

የእግዘኢብሔር የተሰጠው የማዕረግ ስም "የሰራዊት ጌታ" እስራኤልን ይሁዳን በተመለከተ አውዱ እግዚአብሔር የጦር አዛዥና የመላዕክት ሰራዊቶች መሪ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በአንዳንድ አውዶች ለምሳሌ (የሜሰፓታሚያውያን የኮከቦች አምልኮት ደግሞ እንደ ጣኦት አምላኪዎች

አስምህሮች ከሰማይ ብርሃን ጀርባ ስላሉት አማልክት ወይም መላእክቶች ነው፡፡ እነዚህም ንፍቀ ክበባት ከከቦች ከዋክብቶችና ሌሎችም) በአሞጽ 1፡2 ላይ የመለኮት ስሞች በሚል ልዩ ላይ ተመልከቱ)፡፡

**4፡5** ይህ ጥቅስ ከአውዱ ውጭ የሆነ ይመስላል፡፡ ስለ ዘላቂውና ሁሉን አቀፋዊ ስለሆነው አንድ እውነተኛ አምላክ በሚናገረው አውድ መካከል ይህ ጥቅስ እንደ እንግዳ ሀሳብ ተጠቅሷል፡፡ የእስራኤልን ያህዌ አንዳንዶች እንዲህ ያዩታል

1. ይህ ክብር የሞላበት የወደፊት ጊዜ ገና አልተገጠም ምክንያቱም ሁሉም ሀገሮች (ህዝቦች) የየራሳቸው አማላልከት አላቸው (2ነገ 17፤29)
2. ሁሉም የዓለም ህዝቦች ያህዌ ማን እንደሆነ ወደፊትም ቢሆን በዚያን በተለየው ጊዜ እንኳን ሊያውቁት አይችሉም (ለምሳሌ ራዕይ 22፤15)
3. ይህ ወደ ኢየሩሳሌም የመጡ ህዝቦች ያህዌ ልዑልና ዘላለማዊ አምላካቸው እንደሆነ የሚያረጋግጡበት ማረጋገጫ ነው፡፡ (ቁ 1ሠ፤ 2ሀ፤ 3ሀ እና ለ)፡፡

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ "በሚያምኑ ህዝቦች" እና "በየማያምኑ ህዝቦች" መካከል የለውን የማነፃፀሪያ ሀሳብ ታይቷል (ቁ 1-4 እ4ና ቁ 5)

## ሚኪያስ 4፡6-8

**[6] በዚያ ቀን አንካሳይቱን እሰበስባለሁ፥ ይላል እግዚአብሔር፥ የባከነችውንና ያስጨነቅኋትንም አከማቻለሁ [7] አንካሳይቱንም ለቅሬታ፥ ወደ ሩቅም የተጣለችውን ለብርቱ ሕዝብ አደርጋታለሁ ከዚያም ወዲያ እስከ ዘላለም ድረስ እግዚአብሔር በጽዮን ተራራ በእነርሱ ላይ ይነግሣል። [8]አንተም የመንጋ ግንብ ሆይ፥ የጽዮን ሴት ልጅ አምባ፥ ወደ አንተ ትመጣለች የቀደመችው ግዛት፥ የኢየሩሳሌም ሴት ልጅ መንግሥት ትደርሳለች።**

**4፡6-8** ይህ ክፍል የቀድሞዎቹን የሚኪያስ መጽሐፍ ምዕራፎች ርዕስ በቀጣይነት ያሳያል፡፡ ማለትም እግዚአብሔርን እንደ እረኛ (2፤12-13፤መዝ 23 ኢሳ 40፤11 ህዝ 34) ለተገለሉት የሚያስብ ያለ እርሱ አንዳችም የሌለ መሆኑን (ኢሳ 35፤5-6፤61፤1-2 ኤር 31፤8 ሶፍ 3፤19)፡፡

**4፡6** "**በዚያ ቀን**" በ4 ፡1 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከቱ፡፡

▣ **"አንካሳ"** ይህ መ ለት የቆሰሉ የበግ መንጋዎች ማለት ነው፡፡ (BDB 854 II፤ ሰፎ. 3:19)፡፡

▣ **"መሰብሰብ"** አንካሳና ጉለልተኛ እንደሚነፃፀሩ የዚህ ቃል ግሶችም እንደዚያው ነው፡፡

1. "መሰብሰብ" (BDB 62፤ KB 74፤ Qal COHORTATIVE)
2. "አንድ ላይ መሆን" BDB 867፤ KB 1062፤ Piel COHORTATIVE

▣ **"የተገለሉ"** ይህ ቃል በቃል ከመንጋ የወጡትን በጎች ይመለከታሉ (የተጣለችውን BDB 621፤ cf. ሰፎ. 3:14)

▣ **"ያስጨቅኃትንም"** እግዚአብሔር እራሱ በህዝቡ ላይ ፍርድ አምጥቷል፡፡ በዚህ ሥፍራ አንከሳይቱን እና የተጣለችውን ምክንያቱም ህዝቡን ወደ እግዚአብሔር እምነት መመለስ ስለፈለገ፡፡ እግኢአብሔር የቤተሰቡን አባላት ይቀጣቸዋል (ዕብ 12፡5)፡፡

**4፡7 "ለቅሬታ...ለብርቱ ሕዝብ"** እግዚአብሔር ሁልጊዜ በጥቂት ሰዎች ነገሮችን ይጀምራል የምሳሌ አዳምና ሔዋን ኖህ አብርሃም ሙሴ ሌሎችም ይህም ማለት እነዚህ ጥቂት እማኞች ከሰማይ ከዋክብት በላይ ከባህር ዳር አሸዋ በላይ ከምድር አፈርም በላይ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡ በዘፍጥረት ላይ ለእምነት አባቶችና የተሰጠ ተስፋ ነው፡፡ በያህዌ የሚያምኑ ምድርን ሊሞሏት ይችላሉ ማለት ነው፡፡

እግዚአብሔር እራሱ ወይም መሲሁ (1ኛ በቁጥር 1 ቃልኪዳን መሰረት እና 2ኛ በራስህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እይታ world view ንፅረተ አለም አንድ ላይ ይህንን ታላቁን ስራ (ሁሉአቀፍ) መፈጸም ይቻላል፡፡ (ህዝ 36፡22-38) የእግዚአብሔር አላማ ሁልጊዜ ሁሉንም የሰው ልጆች ያጠቃልላል (ዘፍ 1፡26-27 3፡15 13፤3፤ ዘፀ 19፤5-6)፡፡ በዘፍትረት ላይ የኤደን ገነት ልዩ ቦታ ነው፡፡ በዘፀአት ኢያሱ የተስፋይቱ ምድ ልዩ ቦታ ነበረች፡፡ በነቢያት ዘመን ኢየሩሳሌም ልዩ ቦታ ነበረች፡፡ በአዲስ ኪዳን ደግሞ ከሰማይ የምትወርደ አዲሲቷ እየሩሳሌም ናቸው፡፡ ለስመነለኮታዊ አተረጋጎም ቅሬታ የሚለው ቃል የሚኪያስ 2፡12 ላይ የለውን ልዩ ርዕስ ተመልት፡፡

**NASB፤ NKJV፤**

| | |
|---|---|
| **REB** | **"የተጣለችው"** |
| **NRSV** | **"የተገለለችውን"** |
| **TEV** | **"የተተወችውን"** |
| **NJB** | **"ሩቅም የተጣለቸውን"** |
| **JPSOA** | **"የተባረረችውን"** |
| **NIV** | **"የተባረረችውን"** |
| **NAB** | **"በርቀት የተጣለቸውን"** |

የዕብራውያኑ ጽሑፍ ግልጽ አይደለም፡፡ በዚህ ላይ ጥቂት የማይበሉ ማስተካከያዎች ተሰጥተዋል፡፡

1. "መራቅ" -BDB 229፤ KB 245
2. "የደከመቸውን"
3. "የታመመችውን"
4. "የደከመቸውን" (JB)

▣ **"እግዚአብሔር በጽዮን ተራራ በእነርሱ ላይ ይነግሳል"** በብሉይ ኪዳን በመግዛት እና በእረኝነት መካከል የስነ ጽሁፍ ንፅፅር አለ (ለምሳሌ እረኛ 5፡4 እና 6 መግዛት 4፡7፤ 5-12)

▣ **"ከዚያም ወዲያ እስከ ዘላለም ድረስ"** ይህ ስቁ መስማማትም ጋር ይነፃፀራል፡፡ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል እውነተኛ አላማውም ፅኑ ነው፡፡ ነገር ግን በሂደት እየጨመረ የሚሄድ መገለጥ አለ፡፡ የብሉይ ኪዳን ወደ አዲስ ኪዳን ተሸጋግሯል፡፡ እግዚአብሔር እራሱን በተለያየ ሁኔታ ገልጧል ዋናው ግብ ግን ከእርሱ ጋር መኖር ነው (በሆሴዕ 2፡19 ልዩ ርዕስ (*'Olam* ዘላለምን )ተመልከቱ፡፡

## ልዩ ርዕስ ፡ የብሉይ ኪዳን ስለወደፊት ትንቢቶች እና የአዲስ ኪዳን ትንቢቶች

(በራዕይ ከተሰራው የኔ ሃተታ ላይ አስፈላጊ መግቢያ ፅሁፍ ላይ የተወሰደ)

**የመጀመሪያው ውጥረት** (ብሉይ ኪዳን የዘር፣የሃገራዊ እና የስነ ምድራዊ ምድቦች ከዓለም ላይ ከሚገኙ አማኞች ሁሉ ጋር)

ሁሉም ብሉይ ኪዳን ነብያት በፍልስጤም ወስጥ ኢየሩሳሌምን ማዕከል ያደረገ የአይሁዳዊ አገዛዝ እንደገና እንደሚመለስ እና የምድር ሕዝቦች የዳዊታዊ ስርዓት ገዢን ለማወደስ እና ለማገልገል ወደዚህ እንደሚሰበሰቡ ተንበየዋል፤ ነገር ግን ኢየሱስም ሆነ የአዲስ ኪዳን ሐዋሪያት በጭራሽ በዚህ ጉዳይ ላይ አላተኮሩም፡፡ ብሉይ ኪዳን አገላለጽ በመንፈስ አልተመራም (ዝ.ከ. ማቴ 5፡17-19) ማለት ነው? ወይስ የአዲስ ኪዳን ጸሐፍቱ የፍጻሜውን ዋንኛ እውነቶች ዘሏቸዋል?

ስለ አለም ፍጻሜ የሚያወሱ አያሌ ምንጮች አሉ ፤

7. ብሉይ ኪዳን ነብያት (ኢሳያስ፣ሚክያስ፣ሚልክያስ)
8. ብሉይ ኪዳን የምጽአት ቀን ጸሓፍት (ዝ.ከ. ሕዝቄል 37-39፤ ዳንኤል 7-12፤ ዘካሪያስ)
9. የማጣቀሻዎች ፣ ቅዱሳዊ አጻጻፍ ያልሆኑ የአይሁድ የምጽዓት ቀን ጸሓፍት (እንደ 1ኛ ኢኖች ስለ አይሁድ የጻፈው)
10. ኢየሱስ ራሱ (ዝ.ከ. ማቴዎስ 24፤ ማርቆስ 13፤ ሉቃ 21)
11. የጳውሎስ ጽሑፎች (ዝ.ከ. 1ኛ ቆሮንጦስ 15፤ 2ኛ ቆሮንጦስ 5፤ 1ኛተሰሎንቄ 4-5፤ 2ኛተሰሎንቄ 2)
12. የዮሐንስ ጽሑፎች (1 ዮሐ እና ራዕይ) ፡፡

እነዚህ በሙሉ ስለ ፍጻሜ ሃሳብ በግልጽ ያስተምራሉ(ክስተቶች፣ቅደም ተከተል ሰዎች)? ካልሆነ ለምን? በመንፈስ የተመሩ አይደሉም (ከአይሁዳዊያን ዘመን ኪዳን ጽሑፎች በስተቀር)?

በቃላት እና በምድብ ይረዱት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እውነቱን ለብሉ ኪዳን ጸሓፍት ገልጾላቸዋል፡፡ ሆኖም መንፈስ ቅዱስ እነዚህን ብሉይ ኪዳን መገለጦች የአለም መጨረሻ ሃሳብን እስኪያጠቃልል ድረስ አስፍቶታል ("የክርስቶስ ሚስጥር" ዝ.ከ. ኤፌ 2፡11-3፡13)፡፡

የሚከተሉት ተጨባጭ ምሳሌዎች ፣ መረጃዎች እንመልከት፤

5. በብሉ ኪዳን ውስጥ የኢየሩሳሌም ከተማ የእግዚአብሔርን ሕዝቦች (ፅዮን) የሚያመለክት ዘይቤ ሆና ተጠቅሳለች፤ ነገር ግን በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔርን አምኖ ንስሃ የሚገቡትን ሰዎች ሁሉ እንደሚተቀበል የሚያሳይ አቀራረብ አለው(የራዕይ አዲስቷ ኢየሩሳሌም)፡፡ የስነ መለኮታዊ አስተምዕሮት ጽሑፋዊ እና አካላዊ የነበረችው ከተማ ወደ አዲሷ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከተማ መስፋት (የአይሁድ እና የፈሪሳዊያን አማኞች) ምንም አይሁዳዊያን እና የአይሁድ ከተማ ሳይኖር በፊት እግዚአብሔር የወደቀውን የሰው ዘር ለመቤዥት የገባው የተስፋ ቃል መሆኑ በዘፍ 3፡15 ውስጥ ተገልጾ ይገኛል፡፡ የአብርሃም መጠራት እንኳን (ዝ.ከ. ዘፍ 12፡1-3) ፈሪሳዊያንን አሳትፎ ነበር (ዝ.ከ. ዘፍ 12፡3፤ ዘጸ 19፡5)፡፡
6. በብሉ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች የነበሩት የአካባቢው ጥንታዊ የቅርብ ምስራቅ አገሮች ነበሩ ፤ ነገር ግን በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች የማያምኑ ፣ በሰይጣናዊ መንፈስ የሚመሩ እና ጸረ እግዚአብሔር ወደ ሆኑ ሰዎች እየሰፋ መጥቷል፡፡፡፡ጦርነቱ ከአካባቢው ፣ክልላዊ ግጭት ወደ አለም አቀፋዊ እና ፈላካዊ ግጭት ተሸጋግሯል (ዝ.ከ. ቆላሲያስ)፡፡
7. በብሉ ኪዳን ተመጥኖ የነበረው የምድሪቱ ተስፋ ቃል (የዘፍጥረት ፓትሪያርካዊ ቃል ኪዳኖች ዝ.ከ. ዘፍ 12፡7፤ 13፡15፤ 15፡7-15፤ 17፡8) አሁን ወደ መላዋ ምድር ሰፍቷል፡፡ አሁን አዲሲቷ ኢየሩሳሌም የቅርብ ምስራቋ ብቻ ወይም የተወሰነች ሳትሆን አዲስ እንደገና የተፈጠረች ምድር ሆናለች (ዝ.ከ. ራዕ 21-22)፡፡
8. እየሰፉ ከመጡ የብሉይ ኪዳን ትንቢታዊ ሃሳቦች መካከል የተወሰኑ ምሳሌዎች የሚሆኑት፡- (1) አሁን የአብርሃም ዘር መንፈሳዊሳዊ ነገሩ ተገርዟል (ዝ.ከ. ሮሜ 2፡28-29) ፣ (2) አሁን የቃል ኪዳኑ ሕዝብ አሕዛብንም አካቷል (ዝ.ከ. ሆሴ 1፡10፤ 2፡23፤ በሮሜ 9፡24-26 ተጠቅሷል በተጨማሪም ዘሌ 26፡12፤ ዘጸ 29፡45፤ በ2ኛ ቆሮ 6፡16- 18 ተጠቅሷል እንዲሁም ዘጸ 19፡5፤ ዘዳ 14፡2፤ በቲቶ 2፡14 ተጠቅሷል) (3) አሁን መቅደሱ ኢየሱስ ነው ፤ እናም በእርሱ በኩል የአካባቢው ቤተክርስቲያን (ዝ.ከ. 1ኛ ቆሮ 3፡16) ወይም አማኙ ግለሰብ (ዝ.ከ. 1ኛ ቆሮ 6፡19) ፤ እና (4) አሁን በብሉ ኪዳን ሃረጋት የተገለጸችው እስራኤል እና የእርሷ ባህሪያት በአጠቃላይ የሚያመለክቱት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ነው ናቸው (ማለትም፤ "እስራኤል" ዝ.ከ. ሮሜ 9፡6፤ ገላ 6፡16 ፤ "የካህናት መንግሥት" ዝ.ከ. 1ጴጥ 2፡5፤ 9-10፤ ራዕ 1፡6)

የትንቢታዊ አርዓያ ተፈጽሟል፣ተስፋፍቷል፣ እንዲሁም አሁን የበለጠ ሁሉንም የሚያካትት ሆኗል፡፡ ኢየሱስ እና የሓዋሪያት ጸሓፍት ስለ መጨረሻው ዘመን እንደ ብሉ ኪዳን ነብያት አስመስለው አላቀረቡም (ዝ.ከ. ማርቲን ዋይንጋርደን፤ *የወደፊቱ መንግስት ትንቢት እና አፈጻጸም*)፡፡

በብሉ ኪዳን ያለውን ስነ ጽሑፋዊ አረዓያ ወይም ቅርጽ የሚወስዱ ዘመናዊው ተርጓሚዎች ራዕይን የበለጠ የአይሁዳዊያንን መጽሐፍ የሚገልጽ እና የኢየሱስን እንዲሁም የጳውሎስን ሃረጋት አቶማይዝድ ፣ ግራ የሚያጋባ እንዲሆኑ በማድረግ ጠምዝዘውታል!

የአዲስ ኪዳን ጸሓፍት የብሉ ኪዳንን ነብያት ሃሳብ ታላቅ እና አለማቀፋዊ ክስቶችን አመላካች እንደሆኑ ያገልጻሉ እንጂ የሚቃረኑ አይደሉም፡፡የኢየሱስ ወይም የጳውሎስ የመጨረሻው ዘመን ሃተታዎች ምንም የተቀናጀ እና ሊሆኑ የሚችል ስርዓት አያስፈልጋቸውም፡፡ ዋነኛ አላማቸው መቤዠት እና ወይም መንፈሳዊ ትምህርት ነው፡፡

ሆኖም ግን በአዲስ ኪዳንም ውስጥም ቢሆን ውጥረት አለ፡፡ ስለ መጨረሻው ዘመን ሁኔታዎች ምንም አይነት የቅድመ ሁኔታወች ስርዓት የለም፡፡ ራዕይ በብዙ መንገድ ኢየሱስ ስለ መጨረሻው ዘመን ሲገልጽ ካስተማራቸው ትምህርት ይልቅ የብሉ ኪዳንን ተምሳሌቶች መጠቀሙ የሚያስገርም (ዝ.ከ. ማቴዎስ 24፤ ማርቆስ 13)! በሕዝቄል፣ ዳንኤል እና በዘካሪያስ የተጀመረውን የስነ ጽሑፍ

ዘውግ ይከተላል፤ ነገር ግን በኪዳናዊ ዘመን ወቅት እያደገ መጥቷል (የአይሁድ የዘመን ፍጻሜ ስነ ጽሑፍ)፡፡
ይህ ምናልባትም ዮሐንስ አሮጌውን እና አዲሱን ቃል ኪዳኖች አንድ ያደረገበት መንገድ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ረጅም እድሜ ያለውን የሰው አመጻን እና የእግዚአብሔርን የማዳን ቁርጠኝነት ያሳያል! ምንም እንኳን አዲስ ኪዳን የብሉ ኪዳንን ቋንቋ ፣ ሰዎች እና ክስተቶች ቢጠቀምም ሁኔታዎቹን መልሶ የሚገልጸው ግን በሮም የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን እይታ ነው፡፡

**ሁለተኛው ውጥረት** (አንድ አምላክ ማመን ከ ተመረጡ ሕዝቦች ጋር)

የመጽሐፍ ቅዱሳዊው ትኩረት አንድ ማንነት ፣ መንፈሳዊነት ፣ ፈጣሪነት-ተቤዢነት ባለው እግዚአብሔር ላይ ነው (ዝ.ከ. ዘጸ 8:10፤ ኢሳ 44:24፤ 45:5-7፤14፤18፤21-22፤ 46:9፤ ኤር 10:6-7)፡፡ ብሉ ኪዳንን ልዩ የሚያደርገው በዘመኑ ስለ አንድ አምላክ መግለጹ ነው፡፡ በአካባቢው የነበሩት መንግስታት በሙሉ በብዙ አምላከት የሚያምኑ ነበሩ፡፡ ብሉይ ኪዳን መገለጥ የሚያሳየው እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ ነው((ዝ.ከ. ዘዳ 6:4)፡፡

ፍጥረት በእግዚአብሔር እና በራሱ መልክ እና ምሳሌ (ዝ.ከ. ዘፍ 1:26-27) በተፈጠረው ሰው መካከል ለታለመው ህብረት አንዱ ደረጃ ነው፡፡ ሆኖም ግን ሰው በእግዚአብሔር ፍቅር ፣ አመራር እና እቅድ ላይ ኃጥያት በመስራት አመጸ (ዝ.ከ. ዘፍ 3)፡፡ የእግዚአብሔር ፍቅር እና እቅድ በጣም ጠንካራ እና እውነት ከመሆኖ የተነሳ እግዚአብሔር የወደቀውን የሰው ዘር እንደሚቤዥ ቃል ገብቷል(ዝ.ከ. ዘፍ 3:15)!

ውጥረቱ የተባባሰው እግዚአብሔር የተቀረውን የሰው ዘር ለመድረስ አንድ ሰው ፣ አንድ ቤተሰብ ፣ አንድ ሕዝብን በመረጠበት ጊዜ ነው፡፡ የእግዚአብሔር አብርሃምን እና አይሁዶችን እንደ ካህናት መንግሥት(ዝ.ከ. ዘጸ 19:4-6) መምረጥ ከአገልግሎት ይልቅ ክብርን ፣ ከማካተት ይልቅ አለማካተትን አስከትሏል፡፡ እግዚአብሔር ለአብርሃም ያደረገው ጥሪ ሁሉንም የሰው ዘር ለመባረክ አቅዶ ነው (ዝ.ከ. ዘፍ 12:3)፡፡ ብሉይ ኪዳን ኪዳን ምርጫ የነበረው ለአገልግሎት እንጂ ለነጻነት እንዳልሆነ መታወስ እን ትኩረት የሚሰጠው መሆን አለበት፡፡ አጠቃላይ እስራኤላዊያን በግል እምነታቸው እና መታዘዛቸወው (ዝ.ከ. ዘፍ 15:6፤ በሮሜ 4 ውስጥ ተጠቅሷል) እንጂ ከእግዚአብሔር ጋር ስለ ሚስተካከሉ ፣ ዝም ብሎ በመወለድ ሙብታቸው ብቻ ፈጽሞ ለዘላለም የሚድኑ አይደሉም (ዝ.ከ. ዮሐ 8:31-59፤ ማቴ 3:9)፡፡ እስራኤል ተልዕኮዋን ስታለች፤ ኃላፊነቷን ወደ ጥቅም ፣ አገልግሎቷን ወደ ልዩ አቋም ለውጣለች! እግዚአብሔር ሁሉኑም ለመምረጥ አንድ መርጧል!

**ሦስተኛው ውጥረት** ( በሁኔታዎች የሚወሰን ቃል ኪዳኖች conditional በሁኔታዎች ከማይወሰኑ unconditional ቃል ኪዳኖች ጋር)

በቅድመ ሁኔታ ባላቸው እና በሌላቸው ቃል ኪዳኖች መካከል በመንፈሳዊ ትምህርት ውጥረት ወይም የሚጋጭ አባባል አለ፡፡ የእግዚአብሔር የመቤዠት እቅድ/አላማ ቅድመ ሁኔታ የሌለው እንደሆነ እርግጥ ነው (ዝ.ከ. ዘፍ 15:12-21)፡፡ ሆኖም ግን ሰው ለተሰጠው ኃላፊነት ምላሹ ሁል ጊዜ ቅድመ ሁኔታ ያለው ነው!

በሁለቱም ብሉ ኪዳን እና አዲስ ኪዳን ውስጥ "እንዲህ ከሆነ…እንዲህ ይሆናል" አይነት አጻጻፍ ይታያል፡፡እግዚአብሔር ታማኝ ነው ፤ የሰው ዘር ግን ታማኝ አይደለም፡፡ ይህ ውጥረት ብዙ ግራ መጋባቶችን አምጥቷል፡፡ተርጓሚዎች ከ "ከግራ መጋባቱ እምብርት" ወደ አንዱ ላይ ብቻ ትኩረት በማድረግ አዘንብለዋል ፤ የእግዚአብሔር ታማኝነት ወይም የሰው ጥረት ፣ የእግዚአብሔር የበላይነት ወይም የሰው ነጻ መሻት፡፡ ሁለቱም መጽሐፍ ቅዱሳዊ እና አስፈላጊ ናቸው፡፡

ይህ እስከ መጨረሻው ዘመን እግዚአብሔር በብሉ ኪዳን ውስጥ ለእስራኤል ከሰጠው የተስፋ ቃል ጋር ይዛመዳል፡፡ እግዚአብሔር ይህን ተስፋ ቃል ከሰጠ ፤ እንዲፈጸም ያደርጋል ትክክል ነው? እግዚአብሔር ከተስፋ ቃሎቹ ጋር የተቆራኘ ነው ፤ ዝናውም አብሮት ይሄዳል (ዝ.ከ. ሕዝ 36:22-38)፡፡ ቅድመ ሁኔታ ላቸው እና የሌላቸው ቃል ኪዳኖች በክርስቶስ አንድ ይሆናሉ(ዝ.ከ. ኢሳ 53) እንጂ በእስራኤል አይደለም! የእግዚአብሔር ታላቅ ታማኝነት ንስሃ በሚገቡት እና በሚያምኑ ሁሉ ላይ የሚያደርገው ተቤዥነት ነው እንጂ አባቱ/እናቱ ማነው በሚለው አይደለም! ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን እና የተስፋ ቃሎች ቁልፍ ክርስቶስ እንጂ እስራኤል አይደለችም፡፡ በመንፈሳዊ ትምህርት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከዋናው ሃሳብ ተነጥሎ የሚታ ነገር ካለ ይህ ቤተክርስቲያን ሳይሆን እስራኤል ነው (ዝ.ከ. የሐዋ 7 እና ገላ 3)፡፡

የአለም ወንጌል እወጃ ተልዕኮ ወደ ቤተክርስቲያን ተላልፏል(ዝ.ከ. ማቴ 28:19-20፤ ሉቃ 24:47 ፤ የሐዋ 1:8)፡፡ ይህ እስከ አሁን ቅድመ ሁኔታ ያለው ቃል ኪዳን ነው! ይህ ማለት እግዚአብሔር ሙሉ ለሙሉ አይሁዶችን ትቷቸዋል ማለት አይደለም (ዝ.ከ. ሮሜ 9-11)፡፡ በመጨረሻው-ጊዜ እስራኤልን ማመን ቦታ እና አላማ ሊኖረው ይችላል የሚችል (ዝ.ከ. ዘካ 12:10)፡፡

**አራተኛው ወጥረት**(የቅርብ ምስረቅ የስነ ጽሑፍ ቅርጾች ከ ምዕራባዊያን ቅርጾች ጋር)

መጽሐፍ ቅዱስን በትክክል ለመተርጎም ስነ ጽሑፋዊ ስልቱ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ ቤተክርስቲያን እድገቷ በምዕራባዊያን (ግሪክ) ባህል መሰረት ነበር፡፡የምስራቅ ስነ ጽሑፍ ከምዕራባዊያን ዘመናዊ የስነ ጽሑፍ ቅርጾች አጻጻፍ የበለጠ በጣም ገላጭ ፣ ዘይቤያዊ እና ምልክታዊ ነው፡፡ ከማህበረሰባዊ ታሳቢ እውነታዎች የበለጠ በሰዎች ፣ በገጠመኞች እና በክስተቶች ላይ ያተኩራል፡፡ ክርስቲያኖች የራሳቸውን ታሪክ እና የስነ ጽሑፍ ቅርጽ በመውሰድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢቶችን (በሁለቱም ብሉ ኪዳን እና አዲስኪዳን) ለመተርጎም መጠቀማቸው ጥፋተኛ ሲያደርጋቸው ቆይተዋል፡፡እያንዳንዱ ትውልድ እና የስነ ምድር አካል ራእይን ለመተርጎም የራሱን ባህል ፣ ታሪክ እና አንኳር ነገር ተጠቅመዋል፡፡ ከእነሱ መሃል አንዱም ትክክል አልነበረም! መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢት በምዕራባዊያን ዘመነዊ ባህል ላይ ያተኮረ ነው ብሎ ማሰብ ስህተት ነው! ዋናው ፤ በመንፈስ የተመራው ጸሐፊ ለመጻፍ የመረጠው ስነ ጽሑፋዊ ስልት ከአንባቢው ሁኔታ ጋር በሚስማማ መልኩ ነው፡፡

የራዕይ መጽሐፍ ታሪካዊ ትረካ አይደለም፡፡ መጽሐፉ የመልዕክት (ከምዕራፍ 1-3) ፣ የትንቢት እና በዋናነት ደግሞ የምጽዓት ቀን ስነ ጽሑፍ ቅልቅል ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን በዋናው ጸሐፊ ከታቀደው በላይ እንዲናገር ማድረግም ሆነ ጸሐፊ ካስቀመጠው በታችም እንዲሆን ማድረግ ስህተት ነው! የተርጓሚዎች እብሪት እና ቀኖናዊነት እንደ ራዕይ ባሉ መጽሐፎች ላይ የበለጠ አግባብነት ይኅለዋል፡፡ ቤተክርስቲያን በትክክለኛ አተረጓጎም ተስማምታ አታውቅም፡፡ የእኔ ዋና ነጥብ መጽሐፍ ቅዱስን በከፊል ሳይሆን በሙሉ መስማት እና ማጥናት ላይ ነው፡፡ በምስራቃዊያን አስተሳሰብ መጽሐፍ ቅዱስ እውነትን ከውጥረት ጋር አጣምሮ ይዟል፡፡ እኛ ምዕራባዊያን በታሳቢ እውነት ላይ ያለን ልምድ ዋጋ ቢስ አይደለም፤ ነገር ግን የተመጣጠነ አይደለም! የእኔ አስተሳሰብ ራዕይ ሲተረጎም ለሚቀጥለው አማኝ ትውልድ ቢያንስ አስቻሪ ነገሮቹ የሚለወጡበትን አላማ ማስታወሻ በመስጠት ማስወገድ ይቻላል፡፡ ለአብዛኞቹ ተርጓሚዎች ራዕይ በራሱ የጊዜ አቀራረብ እና በራሱ የስነ ጽሑፍ ስልት መተርጎም እንዳለበት ግልጽ ነው፡፡ በራዕይ ላይ ታሪካዊ አቀራራብ ሲጻፍ የመጀመሪያ አንባቢዎች ምን ያውቁ እንደነበር ፣ ምን እንደሚያውቁ እና ምን እንደሚረዱ የሚያገናዝብ መሆን አለበት፡፡ በብዙ መንገዶች ዘመናዊ ተርጓሚዎች የመጽሐፉ ብዙ ምልክቶች ትርጉም ጠፍቷቸዋል፡፡ የራዕይ ዋና መነሻ ሃሳብ በስቃይ ላይ ያሉትን አማኞች ለማበረታታት ነበር፡፡ መጽሐፉ እግዚአብሔር ታሪክን እንደሚቆጣጠር

አሳይቷል (ብሉይ ኪዳን ነብያት እንዳደረጉት)፤ ታሪክ ወደ ታለመለት የፍጻሜ ስፍራ እየሄደ እንደሆነ አረጋግጧል፤ ወደ ፍርድ ወይም ወደ በረከት(ብሉይ ኪዳን ነብያት እንዳደረጉት)፡፡ መጽሐፉ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን በአይሁዶች የምጽዓት ቀን ቃላት የእግዚአብሔርን ፍቅር ፣ ክብር ፣ ኃይል እና የበላይነት አረጋግጧል!

መጽሐፉ በእነዚ ተመሳሳይ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ዘዴዎች ለሁሉም አማኝ ትውልዶች ማገልገል አለበት፡፡የበጎነትን እና የክፋትን ፈለካዊ ትግል ያስረዳል፡፡ የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ዝርዝር ሁኔታ ጠፍቶን ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ኃይለኞቹ እና ነጻ አውጪዎቹ እውነታዎች አይጠፉንም፡፡ የምዕራባዊያኑ ዘመናዊ ተርጓሚዎች የራዕይን ዝርዝር ወደ ራሳቸው ታሪካዊ ሁኔታ ሲመሩት የአተረጓገሙ የተሳሳተ መልክ እየቀጠለ ይሄዳል!

የመጨረሻዎቹ አማኝ ትውልዶች የእግዚአብሔር ጠላት በሆነው መሪ (ዝ.ኪ. 2ኛተሰሎንቄ 2) እና ባህል ምክንያት ስለሚሸበሩ የመጽሐፉን ዝርዝር ሁኔታ ስሜት በሚሰጥ መልኩ እንደገና ቀጥተኛ እንዲሆን ማድረግ ያቻላል (ልክ ብሉ ኪዳን ከክርስቶስ መወለድ፣ሕይወት፣ እና ሞት ጋር በተያያዘ እንዳደረገው)፡፡ የኢየሱስ ቃላት ታሪካዊ መረጃ እስከሆኑ ድረስ (ዝ.ኪ. ማቴዎስ 24፤ ማርቆስ 13፤ እና ሉቃ 21) ስለ ራዕይ ጽሑፎች አፈጻጸም ማንም ሊያውቅ አይችልም፡፡ ግምታዊ መሆን ፣ በመረጃ አለመደገፍ እና ቀና አለመሆን ሁሉም አግባብ አይደሉም፡፡ የምጽዓት ቀን ስነ ጽሑፍ ይህን ነጻነት ይፈቅዳል፡፡ ታሪካዊ ትረካዎችን ለሚልቁ ምስሎች እና ምልክቶች እግዚአብሔር ይመስገን! እግዚአብሔር ሁሉንም ተቆጣጥሯል ፣ ይነግሳል ፣ ይመጣልም!

አብዛኞቹ ዘመናዊ ሃተታ አቅራቢዎች ይህን የስነ ጽሑፉን ስልት ነጥብ ይስታሉ! ዘመናዊ የምዕራባዊያን ተርጓሚዎች የሚያሻማውን ፣ በምልክት የቀረበውን የአይሁዶች የምጽዓት ቀን ስነ ጽሑፋዊ ስልትን በአግባቡ ከመተንተን ይልቅ ግልጽ ፣ የሚቀል የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ስርዓትን ይፈልጋሉ፡፡

በኤል ሆዋርድ ማርሻል በተስተካከለው የራልፍ ፒ ማርቲን *የአዲስ ኪዳን አተረጓገም* በሚለው መጽሐፍ ውስጥ "ለአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሃተታ አቀራረብ" በሚለው ጽሑፍ ላይ ይህ እውነት በደንብ ተገልጿል፤

> "የዚህን ጽሁፍ ማራኪ የአቀራረብ ብቃትን ካልተረዳን እና ሃይማኖታዊ እውነታን ለመግለጽ የተጠቀመበትን የቋንቋ አቀራረብ እንደ ዋና መንገድ አድርገን ካልወሰድን በስተቀር ስለ ምጽዓት ቀን የሚኖረን መረዳት በአሳዛኝ ስህተት የሚሞላ ይሆናል ፤ እንዲሁም በውስጡ ያሉትን ራዕዮች ለመተርጎም ስንሞክር ልክ እንደ ስድ ንባብ መጽሐፍ የመቁጠር እና ተግባራዊ የሆኑትን እንዲሁም ጊዜውን በሚገልጹ ታሪካዊ ክስተቶች ላይ ብቻ የማተኮር ስህተት እንሰራለን፡፡ ቀደም ብሎ የተጠቀሰውን ሁኔታ መሞከር በአተረጓገም ላይ ሁሉንም ሁኔታዎች ያካተተ ችግሮችን ያስከትላል፡፡የበለጠ በትኩረት ስናየው ይህ ስለ ምጽዓት ቀን የሚሰጠውን አስፈላጊ ትርጉም የሚያዛባ እና በአዲስ ኪዳን ክፍል በአስደናቂ ታሪካዊ ቋንቋ የተገለጸውን በክርስቶስ በኩል የሚመጣው የእግዚአብሔርን ዙፋን እንዲሁም በአገዛዙ ላይ ያሉትን የብርታት እና የፍቅር ሃሳቦች የሚያጋጭ ሁኔታ የሚፈጥር ይሆናል (ዝ.ኪ. 5:5፤6፤ አንበሳው በጉ ነው)"(ገፅ 235)፡፡

ደብሊው ራንዶልፍ ታት (W Randolph Tate) *መጽሐፍ ቅድሳዊ አተረጓገም* በሚለው መጽሐፉ ላይ እንደጠቀሰው፡ "በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳለው የምጽዓት ቀን ጽሑፍ ልብ የሚነካ እና ሃዘን የሚጭር ሌላ የስነ ጽሑፍ ስልት የለም ፤ በዋናነት የዳንኤል እና የራዕይ መጽሐፎች፡፡ ይህ ስነጽሑፋዊ ስልት የስነ ጽሑፋዊ መልኩን ፣ ይዘቱን እና አላማውን የያዙ አስፈላጊ ክፍሎች ባለመረዳት ምክንያት በታሪክ ውስጥ በጣም የሚያሳስቱ አጥፊ አተረጓገሞች ደርሰውበታል፡፡ የምጽዓት ጊዜ ስነ ጽሑፋዊ ስልት ከጊዜ በኋላ ምን እንደሚሆን የሚናገር በመሆኑ ምክንያት ስለ ወደፊቱ ሁኔታ እንደ መመሪያ እና ንድፍ ሆኖ ሲታይ ቆይቷል፡፡ በዚህ እይታ ውስጥ ያለው አሳዛኝ ችግር የመጽሐፉ መመዘኛዎች ከጸሐፊዊ ይልቅ በአንባቢው የዛሬው ሁኔታ ላይ መመስረታቸው ነው፡፡ ይህ የተሳሳተ አመለካከት (በዋናነት ራዕይ ላይ) ይህን ጽሑፍ ሚስጥራዊ ትርጉም እንዳለው በማሳብ የጽሑፉን ምልክቶች ለመተርጎም የዛሬውን ሁኔታዎች መጠቀም እንዲቻል መንገድ ይከፍታል፡፡

> " በመጀመሪያ ተርጓሚው የምጽዓት ቀን ስነጽሑፋዊ ስልት መልዕክቶቹን ለማስተላለፍ ምልክቶችን እንደሚጠቀም ማወቅ አለበት፡፡ ዘይቤያዊ ሆኖ ሳለ አንድ ምልክትን በቀጥታ መተርጎም በቀላሉ ወደ ተሳሳተ አተረጓገም የሚያመራ ነው፡፡ ጉዳዩ በምጽዓት ቀን ስነ ጽሑፋዊ ስልት ውስጥ ያሉ ክስተቶች ታሪካዊ መሆን አለመሆናቸው አይደለም፡፡ ክስተቶቹ ታሪካዊ ሊሆኑ ይችላሉ ፣ በትክክልም ተከስተው ሊሆን ይችላል ወይም የሚከሰቱ ይሆናል፤ ነገር ግን ጸሐፊው ክስተቶችን የሚያቀርበው እና ትርጉሙን የሚያስተላልፈው በምስሎች እና በታሪካዊ ቅርጾች በኩል ነው" (ገፅ 137)፡፡

በሪኬን ፣ ዊልሆስት እና በሎንድማን 3ኛ ከተስተካከለው የመጽሐፍ ቅዱሳዊ Dictionary of Biblical Imagery፣

> "የዛሬው አንባቢያን በዚህ ስነ ጽሑፋዊ ስልት ግራ ተጋብተዋል እንዲሁም ተስፋ ቆርጠዋል፡፡የማይጠበቀው አእምሮዋዊ ምስል እና ከዚህ አለም ወጣ ባለው የአገላለጽ ልምዳቸው ብዙዎቹን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች ግራ የሆኑ እና ያልተቀናጁ ያስመስላቸዋል፡፡ የዚህን ስነ ጽሑፍ በግልጽ የሚታውን ቁምነገር ብቻ መውሰድ ብዙዎቹን አንባቢያን በፍጥነት 'ቀጥሎ ምን ይሆናል' ወደ ሚለው ውሳኔ ያስኬዳቸዋል፤ይህ ደግሞ የምጽዓት ቀን መልዕክቱን ዋና ጭብጥ ያሰታቸዋል"(ገፅ 35)

**4፡8 አንተም የመንጋ ግብ ሆይ** ይህ ሊሆን የሚችለው 1ኛ ከቤተልሄም አቅራቢያ የሚገኝ የቦታ ስም ማለትም ለቀን መስዋዕት የሚሆኑ በጎች የሚስማሩት ቦታ ነው (እርሱም ጄሮም እና ምናልባትም በዘፍ 35 2፣1 ወይም ምግዳል ኤድር/*Migdal-eder)* ይህም በ5፡2 ውስጥ ያለው ትንቢት ትኩረት ይሆናል፡፡ እሱም ከመሲሁ (ኃጢአት ከሌለበት የእግዚአብሔር በግ ከሆነው) ጋር የተያያዘ ሐሳብ ነው (ዮሐ 1፣29) የትውልድ ቦታ (2) ህዝቡን በቀጣይነት ከሚመራ ለንጉስ ወይም እረኛ (አምላክ የሆነው መሲህ) ጋርም ተያያዥነት አለው፡፡

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ለመረዳት የስነ ግጥም ማነፃፀሮያ መጠቀም ይቻላል፡፡

1. በጽዮን ተራራ ውስጥ ቁ 7 መስመር 3
2. የመንጋ ግንብ ቁ 8 መስመር 1
3. የፅዮን ሴት ልጅ አምፅ ቁ 8 መስመር 2 (ቁ 10 እና 13)
4. የኢየሩሳሌም ሴት ልጅ ቁ 8 መስመር

የደቡቡን ክፍል ዋና ከተማ ለማመልከት ነው (ኢየሩሳሌም ኢሳ 24፣23)

▣ **"የፅዮን ሴት ልጅ አምባ"** ይህ ምናልባትም የሌላ ቦታ ስም ሊሆን ይችላል፣ ማለትም ኦፌል/Ophel (BDB 779 I)፡፡ ኦፌል የዳዊት መኖሪያ የሚገኝባት የኢየሩሳሌም ክፍል ከተማ ነበረች፡፡ በተጨማሪም የታደሰውን የዳዊት ሰርወ-መንግስት ሲያመለክት ይችላል (2ሳሙ 7)፡፡

▣ **"ወደ አንተ ትመጣለች የቀደመችው ግዛት"** ይህ ክፍል ምናልባት ኢሳ 1፡24 -26ን ሲያንፀባረቅ ይችላል፡፡ እስራኤል ከተፈረደባት በኋላ ወደ ቀድሞ ታላቅነቷ ትመለሳለች፡፡ በእርግጥም ይህ የተሃድሶ ምሳሌያዊ አገላለፅን ያሳያል ምክንያቱም የወደፊት ማንነቷ ከቀድሞ ማንነቷ በተሻለ ሁኔታ ማለትም ሁሉን አቀፍ ይሆናል፡፡ እርሱም ካሳለፈችው ጊዜያት (ማለትም ከዳዊት እና ከሰለሞን መንግስት ዘመን) የተሻለ ዘመን ይሆናል፡፡

## ሚኪያስ 4፡9-13

**[9]አሁንስ ለምን ትጮኺአለሽ? እንደምትወልድ ሴት ምጥ የደረሰብሽ፥ ንጉሥ ስለሌለሽ ነውን? ወይስ መካሪ ስለ ጠፋብሽ ነውን?**
**[10]የጽዮን ልጅ ሆይ፥ እንደምትወልድ ሴት አምጠሽ ውለጂ አሁን ከከተማ ትወጫለሽና፥ በሜዳም ትቀመጫለሽ፥ ወደ ባቢሎንም ትደርሻለሽ በዚያም ያድንሻል፥ በዚያም እግዚአብሔር ከጠላቶችሽ እጅ ይቤዥሻል።**
**[11]አሁንም። ርኵስ ትሁን፥ ዓይናችንም በጽዮን ላይ ይይ የሚሉ ብዙ አሕዛብ በአንቺ ላይ ተሰብስበዋል።**
**[12] ነገር ግን የእግዚአብሔርን አሳብ አያውቁም፥ ምክሩንም አያስተውሉም እንደ ነዶ ወደ አውድማ አከማችቶአቸዋልና።**
**[13] የጽዮን ልጅ ሆይ፥ ቀንድሽን ብረት፥ ጥፍርሽንም ናስ አደርጋለሁና ተነሺ አሂጂ ብዙ አሕዛብንም ታደቅቂአለሽ ትርፋቸውንም ለእግዚአብሔር፥ ሀብታቸውንም ለምድር ሁሉ ጌታ ትቀድሻለሽ።**

**4፡9-13** ታሪካዊ ሂደቱ አሁንም ግልጽ አይደለም፡፡ ግን ከቁ 10 ምክንያት የኢየሩሳሌም በ586 (አ.ከ.ል.በ) በአዲስ ባቢሎን ንጉስ ናቡከደነፆር ዳግማዊ መወደምን የሚያሳይ ይመስላል፡፡

**4፡9** "**አሁንስ ለምን ትጮኺአለሽ?"** ይህ የሞርኮን ጊዜ ያመለክታል ኤር 8፡19ን ተመልከቱ

▣ **"ንጉሥ ስለሌለሽ ነውን?"** ይህ በምዕራፍ 3 ላይ የተሰጠ የዘግናኝ ድርጊት ማብራሪያ ነው፡፡ ንጉስ የእግዘአብሔር አንደራሴ ሆኖ እያለ ክፋትን የሚያደርግ ከሆነ ህዝቡ ወደ ማን እቤት ይበል?

▣ **"ወይስ መካሪ ስለ ጠፋብሽ ነውን?"** ንጉስ እና አማካሪ ተነፃፃሪ ሆነው ሳሉ ሁለቱም የነገስታት ዘር ራስ ይመለከታሉ፡፡ በኢሳ 9፡6 የማእረግ ስም ሊመጣ ላለው መሲህና ንጉስ ከተሰጡት ሰሞች መካከል ናቸው ኢሳ 3፡1-3ንም ተመልከት፡፡

▣ **"እንደምትወልድ ሴት ምጥ የደረሰብሽ"** ምጥ (ቁ 10 መስመር 1-3) በብሉይ ኪዳን የርፍድ እና ስቃይ ምሳሌያዊ አገላለጽ ነው (ኢሳ 42፣14 ኤር 4፣31 እና 6፣24)፡፡ በማርቆስ 13፣8፣ እና በሮሜ 8፣22 ላይ እንደለ የአዲሱ ትውልድ ወሊድ ምጥ ተወስዷል (ለዘላለም)፡፡

**4:10**

| | |
|---|---|
| **NASB** | **እንደምትወልድ ሴት አምጣሽና ተንፈራፍረሽ ውለጂ** |
| **NKJV** | **አምጠሽ ወለጂ** |
| **NRSV** | **አያምጥሽ ጨኹ** |
| **TEV** | **በጭንቀት ጩኺ** |
| **NJB** | **እያማጥሽ ድምጽሽን ከፍ አድርሺ ጩኺ** |

ሁለቱን ግሦች ማለትም ("ተንፈራፍረሽ" BDB 296፣ KB 297 እና "አምጠሽ" BDB 161፣ KB 189) ትህዛዞች አንቀፅ ትዕዛዝ አንቀፅS ናቸው፡፡

▣ **"አሁን ከከተማ ትወጫለሽና"** በሜዳም ትቀመጫለሽ ይህ በተለይ የሚያመለክተው ከኢየሩሳሌም መያዝ በኋላ የተደረገውን አስገድዶ መማረክ ነው፡፡ እነዚህ ህዝቦች ከከተማ ውጪ ቢወጡም በመንገዳቸው ሁሉ ተገድደው በሜዳ እንዲቀመጡ ተደርገዋል፡፡

▣ **"ወደ ባቢሎንም ትደርሻለሽ"** ይህ በተለይ የሚያሳየው የኃያሏን የሜሶፖታሚያን መንግስት አሶርንና ለምለሚቷን ምድር መማረክ ነው፡፤ አሶር አሥሩን የሰሜን ነገዶች (እስራኤልን) በ722 ከ/ክ/ል/በፊት በምርኮ ወስዶ ነበር፡፡ ምዕራፍ 1 እና 2 ባቢሎን ደግሞ የደቡብን ሁለት ነገዶች (ይሁዳ) በ586 (ከ/ክ/በፊት) በምርኮ ወስዶ ነበር (ምዕራፍ 1-2)፡፡ ባቢሎን ደግሞ የደቡብን ሁለት ነገዶች (ይሁዳ) በ586 አ.ከ.ል.በ በምርኮ ወስዳለች (3፡12)፡፡ ብዙ የስነ መለኮት ፀሐፊዎች ስለ ባቢሎን ትኩረት መስጠቱ አስገርሞአቸዋል፡፡ እንደዚሁን የታሪክ ቅደም ተከተል ያልተከተለ ሂደት በኢሳ 13-14 ላይ ይታያል፡፡ ነገር ግን ባቢሎን የሚለው ሜስፖታሚያን ለማመለክት መጠቀስ አለበት፡፡ ምክንያቱም ከባቢሎናዊያን ግዛት ከአስራዊያን በፊት ስለነበረ (ዘፍ 10፡10) ከዘፍ 11፡4-9 ጋር ተያይዞ ደግሞ ፀረ እግዚአብሔር አለም ሀይሎችንም (እንደ ዳንኤል) ሊያመለክት ይችላል፡፡ ይህ ደግሞ የሐዋሪያውን የዩሐንስ ራእይ መጽሐፍ አጠቃቀም ይከተላል 14፡8፤ 16፡19፤ 17፡5፤ 18፡2፣10፣21)፡፡

▣ **"በዚያም ያድንሻል፥ በዚያም እግዚአብሔር ከጠላቶችሽ እጅ ይቤዥሻል"** እዚህ ላይ ሌላ የተስፋ ጨላንጭል ይታያል (መስመር 7-9) ማለትም ፍርዱ ጨላማ እያለ (ከቁጥር 10) በኋላ ሙሉ በሙሉ የርዕሱ ለውጥ ይታያል፡፡ ይህ አዲስ ርዕስ በቁ 11 -12 ላይ ተቀምጧል፡፡ ይህ ጽሁፍ ከነጻ መውጣት (ከባቢሎን ምርኮ መልስ) ወደ ሌላ የወደፊት ጥቃት ያመራል፡፡

**4፡11** "**አሁንም ብዙ አሕዛብ በአንቺ ላይ ተሰብስበዋል"** ይህ ሐረግ የአሶራውያንን (ለምሳሌ ሰናክሬም 701 ክ/ክ/ልበፊት) እና የባቢሎናውያንን (ለምሳሌ ናቡከደነፆር 586 ከ/ክ/ል/በፊት ቅጥረኛ ሰራዊቶች የሚመነለኮት ይመስላል፡፡ ነገር ግን የቅድመ ሺህ አመት አመለካት ላላቸው አንዳንድ ተንታኞች ይህ የትንቢት መጽሐፍ ከፍል አቋማቸው መታመኝነት እንደ መረጃ ይጠቀሙበታል፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **NASB** | ***“የተበከለች ትሁን”*** |
| **NKJV** | ***“ርኩስ ትሁን”*** |
| **NRSV** | ***“የተናቀች ትሁን”*** |
| **TEV** | ***“ፈፅሞ የጠፋች ትሁን”*** |
| **NJB** | ***“ውርደቷን ያሳየን”*** |

*የግሡ ትርጉም* (BDB 337፣ KB 335፣ Qal IMPERFECT) *በትርጉሙ ትኩረት የሚስብ* JUSSIVE *ነው፡፡ ማለትም “የተበከለች” ወይም “የተናቀች ትሁን” የሚል ነው መዝ.* 106:38፤ *ኤር.* 3:1፣9). *የዚሁ አይነት ሥርወ ቃል ኢሳ.* 9:16፤ 10:6 *ላይ ሥራ ላይ ውሏል፡፡*

▣

| | |
|---|---|
| **NASB፣ NJB** | ***“አይናችንም በፅዩን ጥፋት ላይ ይመልከት”*** |
| **NKJV** | ***“አይናችንም በእርሷ ላይ ይይ”*** |
| **NRSV** | ***“አይናችንም ሳያቋርጥ በእርሷ ላይ ይይ”*** |
| **TEV** | ***“እናያለን”*** |

*ግሱ ከላይ ከተጠቀሱት ከአንዱ ጋር ተነፃፃሪነት አለው፡፡* (BDB 302፣ 301፣ Qal JUSSIVE) *ይህም በአጠቃላይ “ማየት” የሚለውን ቃል ያሳያል፡፡* The USB Translator's Handbook *እንደሚለው ከሆነ እነዚህ ሁለት ግሶች ጾታዊ የሆነ ሀሳብን ይመለከታል፡፡ ምክንያቱም ሴት ልጅ የሚለው ቃል በቁጥር* 8 ፣10 *እና* 13 *ገፅ* 129 *መጠቀም) ያንን ስለሚያመለክት በሌላ በኩል ደግሞ የተስፋይቱ ምድር እንግዳ ሰልፎኞች ተግባር መርከስ ሊያመለክቱ ይችላሉ* (*ገጽ* 129)፡፡

**4፡12** *ያህዌን ቃሉን የማያውቁ ሰዎች ታሪክን የሚያዩት እግዚአብሔር በራሱ ህዝብ ላይ ፍርድን እንደፈረደ ብቻ ነው፡፡ እነዚህ የተለያዩ የቃል ኪዳን ህዝቦች በሌሎች ህዝቦች እግዚኢብሔር የማወቂያ መንገድ እንደሆኑላቸው ዘንግተዋል፡፡ የአብርሃም ዘሮች ቃል ኪዳኑን አልጠበቁም፡፡ እግዚአብሔርም ማን እነደሆነ ለሌሎች አልገለጡም ስለዚህ እግዚአብሔር ራሱን ሊገልጥ ወደደ* (*ህዝ* 36፤22-38)

*በዚህ ምዕራፍ ውስጥ* (1) *ሚያምኑ ሀገሮች እና* (2) *የማያምኑ አስጨናቂ ሀገሮች መካከል ያለ የቋንቋ ውጥረት ይታያል፡፡ ግጥማዊ አገላለጽ አንዳንዴ ግልጽ ነው አንዳዴም ደግሞ ግልጽ አይደለም፡፡ ሀሳቡን እንደፈለግን ለማስተካከል የሚከብድ* (*የማይቻል*) *ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ትላልቅ እውነታዎች ስለወደፊት ክስተቶች የሚያሳዩ የእውነት ነፀብራቆችና ምሳሌያዊ ስነ ጽሁፍ ናቸው፡፡*

1. *የአማኞች ተሃድሶ እውነተና የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፡፡*
2. *አንዳንዶች ባለማመን እግዚአብሔር ለመጉዳት የእግዚአብሔር ህዝብ ያጠቃሉ ፡፡*
3. *አንድ ወገን ከእግዚአብሔር ጋ ለዘላለም ይኖራል ሌላኛው ወገን ደግሞ ይጠፋል፡፡*

▣ ***“አከማችቶአቸዋልና”*** *ይሄ ደግሞ እግዚአብሔር እራሱ የአስራኤልን የይሁዳን ጠላቶች ሆነ ብሎ አንድ ላይ የሰበሰባቸው ይመስላል ምክንያቱም ጠላቶቹን በአንድ ላይ ለማጥፋት እንዲመቻት* (*ቁ* 13፤ *ኢሳ.* 13-14፤ *ህዝ.* 38-39፤ *ኢዮ* 4፤ *ዘካ.* 14)፡፡

**4፡13** *ቁጥር* 13-13 *አንድ ላይ መታየት ያለበት ክፍል ነው፡፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ሀሳብ በትክክል ለመረዳት ስለሚያስችል እግዚአብሔር ህዝቡን የቀጣበትን የማያምኑ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ይደመሰሱ ዘንድ የቃል ኪዳን ህዝቡን ይጠራቸዋል* (*ቁ.* 12፤ *ኢሳ.* 41:15-16፤ *ኤር.* 51:20-23፤ *እንባቆም*)፡፡

*ሁለቱም የመጀመሪያ ግሶች* (“*ተነሸ*”BDB 877፣ KB 1086 *እና “አሂጂ”* BDB 190፣ KB 218) *ወይም ትዕዛዞች /Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)* S/ *ናቸው፡፡*

*ግን በቁጥር* 13 *ላይ እግዚአብሔር እራሱ ለታደሰው የቃልኪዳን ህዝቦቹ ሲናገር ይታያል፡፡* (*አዲስ ቃልኪዳን ኤር* 31፣31-34)፡፡ *አንድ ቀን ህዝቡ ባለ ድል ይሆናል፡፡ እግዚአብሔር የአብርሃምን ዘር ሊጠቀም ወድዷል፡፡ በአብርሃም ዘር በኩል የአለም ህዝብ እግዚአብሔርን እንዲያውቁት ፈልጎ ነበር እነርሱ ግን ይህንን አላማ ማስፈፀም አልቻሉም አለምም ወደ እርሱ መምጣት አልቻለም፡፡*

▣ ***“ለምድር ሁሉ ጌታ”*** *በድጋሚ ይህንን ሁሉን አቀፋዊ ገለፃ አስተውሉ፡፡ በዚህ አውድ ይህ ምዕራፍ ከእግዚአብሔር የመጀመሪያ የቃል ኪዳን ህዝብ ጋር ነገር ግን በኢየሱስ በኩል ሊመጣ ስላለው በአዲስ የቃልኪን ህዝብ ነው የሚያመለክተው!*

### የውይይት ጥያቄዎች

*ይህ የጥናት* <u>*መመሪያ*</u> *ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡*

*እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።*

1. *የኢሳያስ እና ሚኪያስ መጽሐፍ ይህ ያህል ሊመሳሰል የቻለው ለምንድነው?*
2. *ለብሉ ኪዳን ትንቢቶች ሁሉን አቀፋዊ ይዘት መያዝ ያልተለመደ ነገር ነው ወይ?*
3. *ቁጥር* 5 *ከአውድ ውጪ መሆን ለምንድ ነው?*

# ሚክያስ 5

## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|
| | የኢየሩሳሌም የወደፊት ክብር እና የዳዊት መንግሥት መታደስ | የጌታ አለምአቀፋዊ ንግስት | የዳዊት ስረወ መንግስት መጨነቅ እና ክብር |
| | (4:1-5:15) | | (4:1-5:3) |
| የሚመጣው መሲህ | 5:1 | የእግዚአብሔር ገዥን ከቤተልሔም ተስፋ መስጠቱ | |
| 5:2 | 5:2-5ሀ | 5:2-5ሀ | |
| | | | አሶርን ለወደፊት አሸንፈው የሚገዙ |
| 5:2-5ሀ | | | 5:4-5 |
| በእስራኤል ጠላቶች ላይ ፍርድ | | ነጻ መውጣትና ቅጣት | የቅሬታዎች የወደፊት ሚና |
| 5:5ለ-6 | 5:5ለ-6 | 5:5ለ-6 | 5:6 |
| | | | 5:7 |
| 5:7-9 | 5:7-9 | 5:7-9 | ያህዌ ፈተናዎችን ሁሉ ያጠፋል |
| | | | 5:8-14 |
| 5:10-15 | 5:10-15 | 5:10-15 | |
| | | | 5:15 |

### የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ vii ተመልከት)

*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ

2. ሁለተኛው አንቀጽ

3. ሦስተኛ አንቀጽ

4. ወዘተርፈ

### የአውዳዊ ቅኝት

ሀ. ሚክያስ ብዙ ትንቢታዊ መረጃዎችን ይዟል፡፡ ለማብራሪያ ዘውግ መ መግቢያ III ን ተመልከቱ፡፡

ለ. አንዳንድ ትርጉሞች ምዕራፍ 5፡ 1ን ከምዕራፍ 4 ጋር ይቀላቅሉታል (ይህም እነደ 4፡14 በዕብራይስጥ መጽሀፍ (TEV)፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ሀሳቡ ምዕራፍ 4 ከቁጥ 9-10 ከሚገኘው ጋር ይመስላል፡፡ ስለ እየሩሳሌም መጠቃት እና ነፃ መውጣት ይናገራል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ትርጉሞች በተለየ መልኩ ምዕራፍ 5 ከቁጥር 1-5ሀ ጋር ያካትቱታል NASB፣ NJB፣ NIV)፡፡ ይህ ደግሞ በእየሩሳሌም እና እምነት አልባ በሆነው ንጉስ እንዲሁም ክፉ በሆኑ መሪዎች እና በክብር ስለሚመጣው የቤተልሔም ንጉስ እና በታዛዥ መሪዎቿ መካከል ልዩነትን ይፈጥራል፡፡

ሐ. ይህ ምዕራፍ ስለ መስሁ የትውልድ ቦታ በግልጽ ይናገራል፡፡ ሚክያስ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ8ተኛው ክፍለ ዘመን የተጻፈ ሲሆን በአጭሩ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ መንደር ተንብዩ ነበር፡፡ አንዳንዶች ሚክያስ የተጻፈበትን ዘመን አይቀበሉትም የ750ዎቹን ዓ ዓ.የማንቀበል ከሆነ ግን የሚክያስ መጽሀፍ በግሪክ ተተርጉሞ ነበር (የግሪክ ብሉይ ኪዳን ትርጉም ከ250-150 ዓ. ዓ) ይህ ከመወለዱ ከመቶ አመታት በፊት ቢሆንም እንኳ ጥሩ ነው፡፡

የትንበያው ይዘት ከመጽሀፍ ቅዱስ የሚለየው

1. የመጽሐፍ ቅዱስ መነሻ ሀሳብ
2. በዘመናት ሁሉን ቻይ የሆነው ያህዌ
3. የኢየሱስ እውነተኛ መሲህነት

መ. ከዚህ በተጨማሪ ይህ ምዕራፍ መሲሁ ቀድሞ የነበር ስለመሆኑ ከመተንበዩ ባሻገር (ቁ 2 መስመር 4 5) መሲሁ ሲመጣ ምን አይነት ግዛት ወይም መንግስት ሊኖረው እንደሚችል ተንብዩል (ቁጥር 4-5 መስመር 1) ይህ የሚደንቅ እና አስገራሚ የሆነ ግልጽ ትንቢት ነው፡፡ እንዴት የሚያስደንቅ እውነተኛ የሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ነው ከእግዚአብሔር የተቀበልነው!

## የቃል እና የሀገረግ ጥናት

### ሚልክያስ፡ 5፡1-5ሀ

**[1] የጭፍሮች ሴት ልጅ ሆይ፥ ጭፍሮችሽን አሁን ሰብስቢ ከብቦ አስጨንቆናል የእስራኤልን ፈራጅ ጕንጬን በበትር ይመታሉ።**
**[2] አንቺም ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ፥ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ፥ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል።**
**[3] ስለዚህ ወላጂቱ እስከምትወልድበት ጊዜ ድረስ አሳልፎ ይሰጣቸዋል የቀሩትም ወንድሞቹ ወደ እስራኤል ልጆች ይመለሳሉ።**
**እርሱም ይቆማል፥ በእግዚአብሔርም ኃይል በአምላኩ በእግዚአብሔር ስም ግርማ መንጋውን ይጠብቃል እነርሱም ይኖራሉ እርሱ አሁን እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ታላቅ ይሆናልና።**
**[5] ይህም ለሰላም ይሆናል አሦራዊውም ወደ አገራችን በገባ ጊዜ፥ ምድራችንንም በረገጠ ጊዜ ሰባት እረኞችና ስምንት አለቆች እናስነሣበታለን።**

**5፡1**

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"የጭፍሮች ሴት ልጅ ጭፍሮችን አሁን ሰብስቢ"** |
| **NKJV** | **"የጭፍሮች ሴት ልጅ ጭፍሮችን አሁን ሰብስቢ"** |
| **NRSV** | **"አሁን ዙሪያሽ በግንብ ታጥሯል"** |
| **TEV** | **"የእስራኤል ህዝብ ሆይ ጦርህን ሰብሰብ"** |
| **NJB** | **"አሁን ምሽግህን ስራ ሀይልህንም አበርታ"** |

ይህ ጥቅስ በዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፍ 4 ቁጥር 14 ጋር በመሆን ከዚህ ምዕራፍ ተካቶ ይገኛል፡፡ በዚህ ጥቅስ ላይ ብዙ የተለያዩ የትርጉም አማራጮች አሉ ከነዚህ መካከል፡-

1. NASB፤ NKJV፤ እና TEV የማሰሬቲኩን ትርጉም ይይዛሉ (BDB 151 I ኤር 5፡7፤ ግሱንም በዚህ ተመሳሳይ መልክ ይተረጉማል፡፡
2. የጥንቁ ግሪክ መደበኛ ትርጉም "አሁን ዙሪያሽ በግንብ ታጥሯል" (NRSV፣ REB) ዕብራይስጥ የተፃፈውን "ተሰብሰቡ" የሚለውን ግስ ገላጭ ቃል "ግድግዳ ለመስራት" በሚል ተመሳሳይ የዕብራይስጥ ቃል ይቀይረዋል ፡፡ በተከበበው ላይ ሀይልን አበርታ ሕዝ 13፡6 አዲሱ የዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ (BDB 151፣ KB 177፣ *Hithpoel* IMPERFECT)፡፡
3. ሌላው ሊሆን የሚችል ትርጉም ደግሞ ራስሽን አርደሻል አንቺ የአራጅ ልጅ (BDB 151) ነገር ግን ይህ በተለየ መልኩ መናገር ያስፈልጋል JPSOA፤ የሞፋት ትርጉም እና NET) ይህ የመጨረሻ ትርጉም ራስን ማረድ
   ሀ ጣዖትን ማምለክ (ዘሌ 19፡28 14፡1፤ 1 ነገ 18:28፤ ኤር 47፡5፤ ሆሴ 7፡14)
   ለ ሀዘን (ዘዳ 14፡1፤ ኤር 16፡6፤ 41፡5፤ 47፡5፤ 48፡37)፡፡

ቁጥር 1 በእየርሳሌም የሆነውን ነገር ሲገልጽ የእየሩሳሌምን መከበብ ከቁጥር 2-5 ያለው ደግሞ በመጨረሻው ዘመን ሊሆን ያለውን የሚናገር ነው፡፡ (የእየሩሳሌምን የታላቁ ንጉስ ቤት መሆን ይህ ጊዜያዊ የሀሳብ ሽግግር ደግሞ ከቁጥር 5-9 እንዲሀም ከ10-14 ካለው ሀሰብ ጋር ተጻራሪ ሆኖ ይገኛል፡፡ በዕብራይስጥ መጽሐፍ ላይ ምዕራፍ 4፡ከ ቁጥር 9-13 ያለው ስለ እየሩሳሌም ይናገራል፡፡ ስለዚህ 5፡1 (MT 4፡14) ስለ እየሩሳሌም መከበብ የሚያወራ አንድ አንቀጽ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ነገር ግን 5፡1 ከ 5፡2-5ሀ ካለው ሀሳብ ጋር ከተካተተ ደካማ እና ተስፋ ቢስ የሆነችውን እየሩሳሌም እና ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነው አዲሱ ከቤተልሔም (ዳዊት ያደገባት ከተማ) ስለሚወለደው መሪ በመናገር ሀሳቡ እርስ በርስ እንዲጋጭ ያደርገዋል፡፡ የይሁዳ መሪዎች እምነታቸው ጠፍቶ እና በሀጢያታቸው ተሰፋ ቢስ ሁነው ነበር (ከጥቂት እግዚአብሔር ከሚፈሩ ነገስታቶች ውጭ ለምሳሌ ህዝቅያስ እዮስያስ) እግዚአብሔርም ከዳዊት ዘር የሆነው ሌላ ታማኝ ንጉስ ያስነሳል እርሱም ያህዌን በሙሉ ማንነቱ ይከተላል (ዘፍ. 49፡9-10፤ II ሳሙ. 7)!

▣ **"እኛን ለማጥቃት ከበውናል"** (BDB 962፣ KB 1321) Qal PERFECT ነው፡፡ በዚህ ድርጊት ገላጭ ቃል ውስጥ የጊዜ ቅደም ተከተሉ ባይካተትም በአውዳዊ ትርጉም ውስጥ ግን መካተቱን ማስታዎስ እንችላለን፡፡ ይሄ ሀሳብ በግልፅ ስለ መከበብ ቢገልጽም ስለ የትኛው መከበብ እንደሚናገር ግን ማወቅ እንችልም፡፡

በዚህ ስር ብዙ አስተያየቶች አሉ፡-

1. የታሪኩን ቅደም ተከተል ስንመለከት በ701 ዓ. ዓ. የይሁዳ በስናክሬም መወረር እየሩሳሌምን ለመከበብ ግን እንዳተሳካለት መጠቀሱ II ነገ. 19፡35-36)፡፡
2. በ586 ዓ. ዓ. የእየሩሳሌም በናቡከደነፃር ሁለተኛ መከበብና መወረር መጠቀሱ (2ነገ 24-25)፡፡
3. ብዙ ሙሁራን እንደሚያምኑበት ይህ ምናልባት በ70 ዓ. ም. በእየሩሳሌም እና በቤተመቅደሱ ላይ በንጉስ ቲቶ ሊሆን ስላለው ወረራ እና ጥፋት የሚናገር ትንቢት ሊሆን ይችላል ይላሉ (ማቴ 24 ፣ማር 13፣ ሉቃ 21)

ከላይ ቁጥር 1 የጸሐፊውን ጊዜ በትክክል ሲገለጽ ቁጥር 3 ደግሞ ከመሲሁ ትክክለኛ ጊዜ ጋር ይገጣጠማል፡፡

**"በበትር"** ይህ በትር የሚለው ቃል (BDB 986) አጠር ያለ የዛፍ ቅርንጫፍ ቁራጭ ጥፋት የሰራ የሚቀጣበት ወይም የሚመታበት ነው፡፡

1. ለልጆች (ለምሳሌ10፡13፤ 13፡24፤ 22፡8፣15፤ 23፡13፣14፤ 26፡3፤ 29፡15)
2. ለእግዚአብሔር ፍርድ ነገስታት ለመቅጫ (መዝ. 2፡9 ( 110፡5-6 እይ)፤ ኢሳ. 9፡4፤ ራዕ. 2፡27፤ 19፡15)
3. በራሱ ህዝብ ላይ ሲፈርድ ኢሳ 10፡5፣24፤ 14፡29

በኢሳያስ ምዕራፍ 10 ቁጥር 5 እና 24 ላይ አሶር የእግዚአብሔር የቁጣ በትር ተብሎ ተጠርቶ ነበር፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር አሶርን ስለ ሀጢያቷ ይቀጣታል (ኢሳ 30፡ 31 ) "በትር" ማለት በዕብራይስጥ ፈሊጣዊ አነጋገር አንድ መሪ ንጉስ ማለት ነው (BDB 986፣ cf. 7:14፤ ራዕ. 2:27፤ 12:5፤ 19:15)፡፡

▣ **"የእስራኤልን ፈራጅ ጉንጩን በበትር ይመታሉ"** ፈራጅ የሚለው የእስራኤል ንጉስ መጠሪያ ስም ነው፡፡ አንድን ሰው ደግሞ ጉንጭ ላይ መምታት ከፍተኛ ስድብ እና ንቀት ነው ( 1 ነገ 22:24)፡፡
ይህም የአሶርን ንቀት እና የእስራኤልን ደካማነት ያሳያል፡፡ ጥፋቱንም ያህዌ በቃል ኪዳኑ ህዝብ ጠላቶች ላይ አድርጓል፡ አሁንም በእነርሱ ላይ እንዲሆን አድርጓል፡፡

የሮተርሐሞች (Rotherham's Emphasized Bible) ይህ ፍርድ በመሲሁ ላይ የሆነው ፍርድ ነው ብለው ተቀብለውታል (ገፅ 887)፡፡

▣ **5፡2-5ሀ** ይህ ሙሉ አንቀጽ ቀስ በቀስ (ከከበባ ወደ ነጻ መወጣት) እና ኢየሩሳሌም እና በይሁዳ ላይ ስለሆነው የእግዚአብሔር ፍርድ ይናገርና ስለ እግዚአብሔር አስደናቂ ታህድሶ ያተኩራል፡፡ (ሚክ 4፡6-8 እና 12-13) ይህ መወላወል በትንቢት ጽሁፎች ላይ መታየቱ የተለመደ ሲሆን ምናልባት (1) የቀድሞ የጽኁፍ አዘጋጆች የአሰራር ዘዴ (2) የዕብራይስጥ ነብያቶች የአስተሳሰብ ዘዬ ሊሆን ይችላል (ተፃራሪ ተመሳሳይ አስተሳሰብ)፡፡

▣ **5፡2 "ቤተልሔም ኤፍራታ"** (የይሁዳ የዘር ሀረግ 1ሳሙ 17፡12 ሩት 1፡2 4፡11 በተለይ 1ዜና 2፡19 24፡50) ኤፍራታ የሚለው ቃል የተጨመረበት ምክንያት በዛብሎን ሰሜናዊ የጎሳዎች መኖሪያ አካባቢ ሌላ የዳቦ ቤት (ቤተ-ልሄም) የምትባል መንደር ስላለች ነው ( ኢሳ 19-15) ቤተልሄም ኤፍራታ በመባል የምትታወቅ በጣም ትንሽ መንደር ነበረች (ዘፍ 38፡19፤ 48፡7)፡፡ ይህ ደግሞ የተጠቀሰው የንጉስ ዳዊት የትውልድ ስፍራ መሆኑን ለመግለጽ ብቻ ነው፡፡ በተጨማሪ (1 ሳሙ. 16:1 ll ሳሙ. 7፤ መዝ. 89 ከዳዊት ዘር ስለሚመጣው ንጉና መሲህ ለመጥቀስ ነው) ይህ ጥቅስ በማቴ 2፡6 ተጠቅሶ በሉቃ 2፡4 እና በዩሐ 7፡42ም ተወስቷል፡፡

▣ **"ታናሽ"** ይህ ቃል ስለ ትንሽነት አፅኖት ይሰጣል (BDB 859 I )
1. ነገዶች (1ሳሙ 9፡21)
2. ጎሳዎች (መዝ 68 27)
3. ቀንዶች (ዳን 8፡9)
4. ከተሞች (ሚክ5፡2)

(ከ NIDOTTE ቁጥር 3 ገጽ 830 ላይ የተወሰደ)

▣ **"ነገዶች"** የሚለው ቃል በዕብራይስጥ "ሺዎች" የሚል ነው (BDB 48 II)፡፡ ሺህ የሚለው ደግሞ በዕብራይስጥ እልፍ ማለት ሲሆን ይህን ደግሞ እንደሚከተለው ይጠቀሙበታል፡-
1. የቤተሰብ ወይም የነገድ አባል ዘኁ 10፡4 ኢያ 22-14 መሳ 6-15 1ሳሙ 10-19 23-23 ሚክ 5-2 ዘካ 9፡7
2. የጦር ሀይል አባል ዘፀ 18 21 (25) ዘዳ 1:15
3. እልፍ (ሺህ) መደበኛ መጠሪያ ዘፍ 20:16 ዘጸ 32-28
4. ምልክት ዘፍ 24-60 ዘፅ 20:6 (ዘዳ. 7:9)፤ 34:7፤ ኤር. 32:18

ቤተልሔም በጣም ትንሽ ከመሆኗ የተነሳ በኢያሱ 15 ለይሁዳ ጦር እንድ አጋዥ ሀይል ተደርጋ አልተጠቀሰችም ነበር፡፡ በነህምያም የእየሩሳሌም ቅጥር በድጋሜ ሲሰራ ቤተልሄም እንደ አጋዥ ሰራተኛ አልተጠቀሰችም ነበር፡፡

▣ **"የይሁዳ"** በሙሴ ትንበያ ምክንያት ከያዕቆብ ልጅ ዘር የሆነው ይሁዳ (BDB 397) በዘፍ 49፡8-12 በተለይ ቁጥር 10 ላይ መጠቀሱ ይህ ሀሳብ ተቀባይነት ያገኘ ትንቢት በመሆን መሲሁ ከይሁዳ የዘር ሀረግ ከእሴይ ወገን እንደሚወለድ ጠቋሚ ነው (2ሳሙ 7)፡፡

▣ **"ለእኔ"** የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ጥንታዊ ጽኁፍ (MT) አጽኖት ተሰጥቶል፡፡ መሲሁም በያህዌ ትዕዛዝ እንደመጣ ይናገራል፡፡ ከያህዌ የሆነ ሙሉ ፍጽም የሰው ልጅ እና እውነተኛ መሪ በትክክል እና ሙሉ በሙሉ የእስራኤልን አምላክ የሚያሳይ ብቸኛ መሲህ ነው፡፡ የብሉይ ኪዳን ተማሪዎች (ራቢስ) እግዚአብሔር ሰው ሆኖ ወይም ስጋ ለብሶ (ተሰግዎ/incarnation) ይመጣል ብለው አይጠብቁም ነበር፡፡ በስልጣን እና በሀይል ይመጣል ብለው ነበር የሚጠብቁ (እንደ ነገስት ዘመን) እግዚአብሔር ራሱ እውነተኛ ንጉስ ነበር (1ሳሙ 8፡7)፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"አመጣጡ ከጥንት ከቀድሞ ዘመን ከዘላለማዊ ቀኖች የሆነ"** |
| **NKJV** | **"አመጣጡ ከድሮ ከዘላለም ዘመን የነበር"** |
| **NRSV** | **"መነሻው ከድሮ ከጥንት ቀናቶች የሆነ"** |
| **TEV** | **"የዘር ሀገረጉ ወደኋላ ከጥንት ዘመን የሆነ"** |
| **NJB** | **"መነሻው ወደኃላ ከሩቅ ከጥንት ከድሮ ቀናቶች የሆነ"** |

እነዚህ ሁለት መስመሮች ቀጥተኛ ናቸው፡፡ አመጣጡ የሚለው ግስ (BDB 422፣ KB 425፣ Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ) ) የተለመደ የግስ አይት ነው፡፡ ይህ ግስ በሚክያስ 8 ጊዜ ተጠቅሷል (ለምሳሌ [1] ስለ ጌታ መምጣት በምዕራፍ 1፡3 ላይ [2] የእግዚአብሔር ህግ ይወጣል በምዕራፍ 4፡2 [3] ይቅርታን በማግኘት እስራኤል ከእንደገና ትታደሳለች (7፡15 አዲስ ነጻ መውጣት) ይህ ደግሞ ስለ መሲሁ አመጣጥ ወይም ስራዎች ይጠቅሳል (Genenius፣ NRSV፣ NJB) (ቁጥር 4 እና 5ሀ)

እነዚህ ሁለት መስመሮች ከዚህ በተጨማሪ (1) የመሲሁን ከዚህ በፊት አስቀድሞ የነበር መሆኑን ምሳ. 8:22-31፤ ዮሐ 1:1፣14-15፤8:56-59፤ 16:28፤ 17:5፤ I ቆሮ. 8:9፤ ፊል. 2:6-7፤ ቆላ. 1:17፤ ዕብ. 1:3፤ 10:5-8) ወይንም (2) ከዚህ በፊት ከነበሩት ታዋቂ የሰው ልጆችን ለመጥቀስ

(ምሳሌ አብርሃም ኖህ ወይም ምናልባት ዳዊት) ይህ ጥቅስ በአጠቃላይ ለንጉስ ዳዊት ከዳዊት የዘር ሀረግ፤ ከዳዊት የትወልድ መንደር መሆኑን ያስታውሳል፡፡ ዳዊት የተሰጠ እና ታዛዥ ንጉስ መሆኑ ይጠቀሳል፡፡

ዘላለማዊ ሕይወት የሚለው ቃል (BDB 761) ኦላም/ olam. ነው፡፡ ሆሴ 2፡19 ልዩ ርዕስን ለዘላለም ('Olam) የሚለው ተመልከት፡፡ (NIDOTTE ቁ 3 ገጽ 347 ኦላም የሚለውን ሀሳብ ሲያብራራ የሚቀጥለውን አስተያየት ሰጥቷል፡-

"ከዚህ ላይ እንደምንመለከተው የመሲሁን ዘላለማዊ እና አስቀድ የነበር መሆኑን ለመግለጽ ፈታኝ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ወይም ከመጽሐፍ ቅዱስ በኋላ በዕብራይስጥ የአፃፃፍ ስልት ውስጥ እንደዚህ አይት አስገራሚ ሀሳብ አናገኝም፡፡ ከሔኖክ ጋር ከመመሳሰሉ በቀር (ከ1ኛው ዓ ዓ በፊት እስከ 1ኛ ዓ ም በኃላ 1ሔኖክ 48፡2-6 ያለውን ተመልከት

እንደ እኔ ሀሳብ ምንም እንኳን በብሉይኪዳን ስለ ስጋ መልበስ የሚገልጽ ሀሳብ ቢኖርም ኢየሱስ በነበረበት ዘመን የነበሩ የአይሁድ መሪዎች ግን ከእግዚአብሔር ጋር ስላለው እኩልነት መናገሩ አስገርሟቸው ነበር፡፡ (ማር 2፡5-7 ዮሐ 1-14 8፡58 በተጨማሪ ጳውሎስ በ2ቆሮ 4፡4 ቆላ 1፡15 ፊሊ 2፡6 ቲቶ 2፡13) ያልተሟላው ዝርዝር የብሉይኪዳን ጽሑፍ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ቻይነት ይዘረዝራል፡፡

1. መዝ. 2:7፣ በዕብ 1፡5 ላይ ተጠቅሷል (ልዩ 1፡2-3ን ተመልከት)
2. መዝ. 45:6-7 ዕብ. 1:8-9 ላይ ተጠቅሷል
3. መዝ. 110:1 ዕብ. 1:13 ላይ ተጠቅሷል
4. ኢሳ. 9:6፤ Jer. 23:5-6፤ ሚክ 5:2 ጀምሮ እስከ ሉቃ 1:32 ተዘርዝሯል
5. ዳን. 7:13 ማቴ. 26:64፤ ማር 14:62 ላይ ተጠቅሷል
6. ዘካ. 13:7 ማቴ. 26:31፤ ማር 14:27 ላይ ተጠቅሷል
7. ሚልክያስ. 3:1 ማር 1:1-3፤ ሉቃ 2:26-27 ላይ ተጠቅሷል

## ልዩ ርዕስ፡ ሥላሴ

የሥላሴን ሦስት አካላት እንቅስቃሴ በአንድ ወጥ በሆነ አውደ ተመልከታቸው፡፡ «ስላሴ» የሚለው መጠሪያ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈጠረው በቱርቱስያን እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል አይደለም፡፡ ነገር ግን ሐሳቡ በጣም የተስፋፋ ነው፡፡

ሀ. ወንጌላት

1. ማቴ 3:16-17፤ 28:29 (እና ሌሎች ተመሳሳዮች)
2. ዮሐ 14:26

ለ. ሐዋርያት ሥራ - ሐዋ 2:32-33፤ 38-39

ሐ. ጳውሎስ

1. ሮሜ 1:4-5፤ 5፡1፡5፤ 8:1-4፡8-10
2. 1ቆሮ 2:8-10፤ 12:4-6
3. 2ቆሮ 1:21፡ 13:14
4. ገላ 4:4-6
5. ኤፌ 1:3-14፣ 17፤ 2:18፤3:14-17፤ 4:4-6
6. 1ተሰ 1:2-5
7. 2ተሰ 2:13
8. ቲቶ 3:4-6

መ. ጴጥሮስ 1ጴጥ 1:2

ሠ. ይሁዳ ቁ. 20-21

በእግዚብሔር ውስጥ የብዙ ቁጥር መኖሩ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ፍንጭ አለ፡፡

ሀ.የብዙ ቁጥር ለእግዚአብሔር መጠቀሱ

1. "ኤሎሂም" የሚለው ስም ብዙ ቁጥሮችን አመልካች ነው፡፡ ግን ምን ጊዜም በእግዚአብሔር ሲጠቀም ነጠላ ግስን አመልካች ነው፡፡
2. "እኛ" በዘፍጥረት 1፡26-27፣ 3፡22፣ 11፡7

ለ. የእግዚአብሔር መልአክ መለኮትን በሚታይ መልኩ የወከለ ነበር

1. ዘፍ. 16፡7-13፣ 22፡11-15፣ 31፡11፤13፣ 48፤15-16
2. ዘፀ. 3፡2፣4፤ 13፡21፤ 14፡19
3. መሳፍንት 2፡1፣ 6፡2-23፤ 13፡3-22
4. ዘካሪያስ 3:1-2

ሐ. እግዚአብሔር እና መንፈሱ የተለያዩ (ዘፍ1:1-2 መዝ 104:30፤ ኢሳ 63: 9-11፤ ሕዝ 37:13-14)

መ. እግዚአብሔር (ያህዌህ) እና መሲል (አዶናይ) የተለያዩ ናቸው መዝ 45:6-7፤ 110:1፤ ዘካ 2:8-11፤ 10:9-12

ሠ. መሲሑ እና መንፈስ የተያዩ ናቸው፤ ዘካ 12:10

ረ. ሦስቱም በኢሳ 48:16፤ 61:1 ላይ ተጠቅሰዋል፡፡

የኢየሱስ መለኮትነት እና የመንፈስ ስብእና አጥባቂ እና የአንድ አምላክ አምልኰ ተከታዮች ለነበሩት ለቀደሙት አማኞች ችግር የፈጠረባቸው ጉዳይ ነበር፡፡

1. ቱርቱስያን - ወልድ ከአብ እንደሚያንስ አሰረዳ
2. ኦሪገን - የወልድን እና የመንፈስ መለኰታዊ ማንነት ዝቅ አደረገ
3. አርዮስ - የወልድን እና የመንፈስ መለኰትነት ካደ
4. ምጥሮኪያኒዝም - አንድ አምላክ ተከታታይነት ባው ሁኔታ እንደ አባት፣ ልጅ፣ እና መንፈስ እንደ ተገለጠ የሚያምን

ስላሴ በታሪክ ሁሉ በቅዱሳት መፃህፍት አማካኝነት ሃሳቡ ሲገለፅ የኖረ ጉዳይ ነው፡፡

1. የኢየሱስ መለኰትነት፣ ከአብ ጋር እኩል መሆኑ በ325 ዓ.ም በኒቅያ ጉባኤ ፀደቀ
2. የመንፈስ ሙሉ ስብእና እና መለኰትነት ከአብ እና ከወልድ ጋር እኩል መሆኑ በኮንስታንቲኖፕል ጉባኤ (381 ዓ.ም) ፀድቋል፡፡
3. የስላሴ አስተምህሮ የአውግስቲን ሥራ በሆነው ውስጥ *Deir***itae** በሙላት ተገልጿል፡፡

እዚህ ላይ ግን እንቆቅል የሆነ ጉዳይ አለ፡፡ አዲስ ኪዳን ግን አንድ መለኰታዊ መንነት ያለው እና ሦስት ዘላለማዊ የስብእና መገለጦች እንዳሉት የሚያረጋግጥ ይመስላል፡፡

**5፡3 "እስከ ጊዜው ድረስ እርሱ አሳልፎ ይሰጣቸዋል"** በአውዱ ላይ ተዉላጠ ስም ሊያመለክተው የሚችለው(1) ያህዌ ወይም (2) የእርሱ መሲህ ማለት ሊሆን ይችላል፡፡ በቁጥ 3 መስመር 1 ላይ ያህዌን ሲጠቅስ በቁጥር 3 መስመር 3 ላይ ግን ስለ መሲሁ ይናገራል ይህ በአላማ የተፃፈ አከራካሪ ሀሳብ ነው፡፡

ይህ ግስ (BDB 678፣ KB 733፣ Qal IMPERFECT) በጣም የተለመደ ሌላ የግስ አይነት ነው፡፡ ይህ ማለት "ስጥ"፤ "አስቀምጥ"፤ "ተቀመጥ" የሚል ትርጉም አለው፡፡ ይህ ደግሞ መውለድ የሚልን ሀሳብ አብዛኛውን ጊዜ አውዳዊ የፍርድ ቃልን ያብራራል (ዘኁ 21፡3 መሳ 20፡13 1ሳሙ 11፡12 2ሳ 14፡7 1ነገ 14፡16 ሆሴ 11፡8)፡፡

▣ **"እሷ ወላድ የሆነችው ልጅ ወልዳለች"** ብዙ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱ የዘር ሀረጎች ሊኖሩ ይችላሉ፡-

1. ወደ ያህዌ የመጀመሪያው የምህረት ቃል ኪዳን ይመልሰናል፣ ይህ ደግሞ ከሴት በሆነ ወንድ ነጻ አውጭ ዘፍ 3፡15
2. ይህ ከሚክያስ ወቅታዊነት ጋር ይገናኛል፤ በኢሳይያስ ከብዙ ዓመታት በፊት ስለዚህ ልዩ ልደት ተጠቅሷል፡፡ (ኢሳ 7፡14 9፡6 11፡11-6)
3. ወደ 4፡9-10 ይመልሰንና ስለ እየሩሴም ተመሳሳይ ሰዋሰው ይጠቀማል፡፡
4. ይህ ከመሲሁ ማህበረሰብ ጋር ተያያዥነት አለው (ታማኝ ቅሬቶች ) እንደ ራዕይ 12 የመሲሁ መውለድ ጋር

የቁጥር 3 አጠቃላይ ሀሳብ እንደሚያሳየው እግዚአብሔር እምነት አልባ የሆኑትን የቃል ኪዳን ህዝቦች መጠነኛ ለሆነ ፍርድ (ቅጣት) አሳልፎ በመስጠት እንደገና በአስደናቂ ሲያድሳቸው ያሳየናል፡፡

▣ **"የቀሩትም ወንድሞቹ ወደ እስራኤል ልጆች ይመስላሉ"** ይህ ምናልባት ስለ አንዱ ወይም ሁለቱ ቡድኖች ሊናገር ይችላል (1) ታማኝ ቅሬቶች (2) የእስራኤል ልጆች (ኢሳ 10፡20-27 ) እንደ ታሪካዊ አመጣጠዩ ይህ ከባርነት ወደ ነጻ ስለ ተጓዙት አይሁዶች እና በተሰፋው ምድር ላይ ስለቀሩት አይሁዶች ይናገራል፤ ነገር ግን እንደ መጨረሻው ዘመን ጥናቶች eschatologically ከሆነ ሁሉንም እስራኤላዊያን ያጠቃልላል፡፡ (ሮሜ 9-11 በተለይ 9፡6) Expositor's Bible Commentary ቁጥር 7 ገጽ 428 እንደሚለው ከሆነ ይህ የሚናገረው በቀጠይ ገዥ ስለሚሆኑት ወንድች ነው (ቁጥር 2) እንደሚታወቀው ግጥማዊ ትንቢቶች አጭር አከራካሪ እና ለመተርጎም አስቸጋሪ ናቸው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የተጠቀሱትን ካልተጠቀምን ለመተርጎም በጣም አይቻልም (1) የታሪኩን ትክክለኛ ጊዜ እና ቦታ (2) የጽሁፉን አውዳዊ ትርጉም እና (3) የብሉይ ኪዳን ወይም የአዲስ ኪዳን የሚገኙ ተመሳሳይ ምንባቦችን ማየት ጠቃሚ ነው፡፡ D. Brent Sandy፣ Plowshares and Pruning Hooks: Rethinking the Language of Biblical Prophecy and Apocalyptic ይህ መጽሐፍ ትነቢት ለመተርጎም ለማብራራት የሚጠቅም ነው፡፡

▣ **"ተመለስ"** ሳብ (*shub*) በሚለው ቃል ላይ የቃላት ጨዋታ ይኖራል (BDB 996፣ KB 1427፣ *Qal* IMPERFECT) የሚያመለክተውም፡-

1. በቀጥተኛ ትርጉም በአካል ስለመመለስ (ከምርኮ)
2. መንፈሳዊ ተፅፅቶ የመመለስ (ከጣዖት አምልኮ እና ከአመፅ)

ይህ ደግሞ በ2፡12-13 እና በ4፡6-8 ባለው ተጠቅሷል

**5፡4** ይህ ስለ መሲሁ የንግስና ዘመን እና ባህሪ ማብራሪያ ነው (ኢሳ 9:6-7፤ 11:1-5፣6-9፣11-16):

1. እርሱ ይነሳል (ይጸናል ወይም ይቀራል ለምሳሌ መዝ. 102:26፤ 111:3፣10፤ 112:3፣9፤ መክ. 1:4፤ ኢሳ. 14:26፤ 66:22፤ ሐጌ. 2:5)
2. እርሱ ለህዝብ እረኛ ይሆናቸዋል (ዳዊት የበግ እረኛ ነበር ያህዌን ቢዚህ አባባል በመዝ 23 ገልፆታል)
3. እርሱ በጌታ ሀይል ይመጣል
4. እርሱ በግራማዊነት በጌታ ስም በእግዚአብሔር ይመጣል
5. እርሱ ከሀሉ የላቀ ይሆናል
6. እርሱ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ይነግሳል (ምሳሌ BDB 75 መዝ. 2:8፤ 22:27-28፤ 59:13፤ 72:8)
7. በቁጥር 5 መስመር 1 ላይ (ከቁጥር 4 ጋር አብሮ የሚሄደው) እሱ በሰላም ይነግሳል (ቁጥር 4 መስመር 4)

5፡4 የሚያብራራው የጊዜ ዘመን ከ 4፡1-4 ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

**5፡5ሀ "ይህ ሰላማችን ይሆናል"** ሰላም የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ሻሎም *shalom* (BDB 1022) ማለት ነው፡፡ ይህ ስለ መልካም ምኞት ያወራል፡፡ አይሁዶች ለሰላምታ እና ለስንብት ይጠቀሙበታል፡፡ እንደ መጨረሻው ዘመን ጥናቶች አመለካት ከሆነ ግን (3:5 እና 5:5፣ መስመር 2፣ ቁ 6). ስለ ሀሰተኛ ነቢያቶች የሰላም መልክዕት የሚናገረው ከነርሱ ሀሳብ ጋር ይቃረናል፡፡

ይህ ቁጥር የሚናገረው ሰላምን ይዞ ስለሚመጣው ገዥ ነው (ቁጥ 4 እርሱም ሰላም ተብሎ ይጠራል (ኢሳ 9፡6 ኤፌ 2፡14)

## ሚክ 5:5ለ-9

**ይህም ለሰላም ይሆናል አሦራዊውም ወደ አገራችን በገባ ጊዜ፥ ምድራችንንም በረገጠ ጊዜ ሰባት እረኞችና ስምንት አለቆች እናስነሣበታለን። 6 የአሦርንም አገር በሰይፍ፥ የናምሩድንም አገር በመግቢያው ውስጥ ያፈርሳሉ አሦራዊውም ወደ አገራችን በገባ ጊዜ፥ ዳርቻቻችንንም በረገጠ ጊዜ እርሱ ይታደገናል። 7 የያዕቆብም ቅሬታ በብዙ አሕዛብ መካከል ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሚወርድ ጠል፥ በሣር ላይ እንደሚወድ ካፊያ ሰውንም እንደማይጠብቅ፥ የሰውንም ልጆች ተስፋ እንደማያደርግ ይሆናል። 8 በዱር አራዊትም መካከል እንዳለ አንበሳ፥ በበጎች መንጋም መካከል አልፎ እንደሚረግጥ፥ የሚታደግም ሳይኖር እንደሚነጥቅ እንደ አንበሳ ደቦል፥ እንዲሁ የያዕቆብ ቅሬታ በአሕዛብና በብዙ ወገኖች መካከል ይሆናል። 9 እጅህ በጠላቶችህ ላይ ከፍ ከፍ ትበል፥ ጠላቶችህም ሁሉ ይጥፉ።**

**5፡5 ከ2ተኛው መስመር ቁጥር 9** ደረስ ያለው የሚናገረው አሶራዊያን እስራኤልን ለመቅጫ በእግዚአብሔር የተመረጡ ዕቃ መሆናቸውን ነው። (ኢሳ 10፡5)፡፡ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ህዝብ ያህዌን ማወቅ ትተው ባአልን እስከ ማምለክ ደርሰው ነበር (ሆሴ 11፡1-4)፡ በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር እንደገና ለመስራት ኪዳኑን ማፍረስ ነበረበት፡፡ የአሶር ፍርድ ግን ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነበር (ቁጥር 3)

የዚህ ምዕራፍ ትክክለኛ ወቅት እና ጊዜ በእርግጠኛነት መናገር አይቻልም፡፡ አሶራዊያን የሚላቸው ምናልባትም ሁሉንም ፀረ ያህዌ የሆኑ ህዝቦችን የሚገልጽበት መንገድ ሊሆን ይችላል (ዘካ 10-11) ልክ ባቢሎን እንደሚለው ስያሜ (በራዕይ መጽሐፍ እንደተጠቀሰው)፡፡

**5፡5 "ከዚያም በእርሱ ላይ ሰባት እረኞች እና ስምንት አለቆችን እናስነሳበታለን"** የቁጥር ቅደም ተከተል በኡጋሪቲክ እና በብሉይ ኪዳን የስነ -ጽኁፍ አፃፃፍ ስልት የተለመደ ነው (መዝ 6፤6 ፤3015፤18፤21 አሞ 1፤3 6፤9፤11፤13፤2፤4፤ 6 እና ሌላ ምሳሌ ደግሞ በመክ 11፤25 እናገኛለን) ይህ ሀሳብ አፅኖት የሚሰጠው የያህዌን ፈቃድ የሚፈጽሙ በቂ ቁጥር ያላቸው እና በሚፈልግበት ቀን በዚያ የሚገኙ እግዚአብሔር የሚፈሩ መሪዎች ላይ ነው፡፡ አሶሪያኖች ግን በመጨረሻ ቀን በያህዌ ፍርዳቸውን ይቀበላሉ (ኢሳ 10፤24-27)፡፡
በዚህ ሀሳብ ውስጥ አንድ ጥያቄ የሚፈጥር ሀረግ አለ "እናስነሳለን" (BDB 877፣ KB 1086፣ Hiphil PERFECT)፡፡ ይህ ምናልባት ተበታትነው የሚኖሩ እስራኤላዊያን እግዚአብሔር ነፃ-የማውጫ መጠቀሚያ ምንጭ መሆናቸውን ወይም የእግዚአብሔርን ስራ የሚገልጽ (ቁጥር 3 1ኛው መስመር) ወይም ስለ እርሱ መሲህ( ቁጥር 3 3 ተኛ መስመር ቁጥር 4-5 1ኛው መስመር) የሚናገር ይሆን? ቁጥር 5 4ተኛ መስመር ላይ "እናስነሳለን" የሚለው እና ቁጥ 6 1ኛ መስመር ላይ "መንጋውን ይጠብቃል" የሚለው ከ ቁጥር 6 3ተኛ መስመር ላይ "እርሱ ይታደገናል" (BDB 664፣ KB 717፣ Hiphil PERFECT) ከሚለው ጋር ስናነፃፅረው ይህን ተመሳሳይ አስተሳሰብ እናገኛዋለን፡፡
የዚህ አከራካሪ ጽሁፍ እና የአይሁድ ወታደሮች አሶራዊያንን ድል ማድረጋቸውን የሚገልጽ ታሪካዊ መሰረት አለመኖር ብዙዎች (እንዲሁም በትክክልል) ለ፡-

1. አሶር የሚል የሚወክለው ማንኛውም አይነት አለማዊ ሀይል የእግዚአብሔር ህዝብ ጠላት የሆነ ማለት ሲሆን
2. ድል አድራጊው "እነሱ" ሳይሆኑ "እርሱ" (የቁጥር 2-5ሀ ያለው ገዥ) የፍጻሜው ዘመን ተቃዋሚዎች ሁሉ ያንበረክካል (በተመሳሳይ መዝ. 2 ሕዝ. 38-39 ወይም ዳን. 11 36-45

**5፡6 "ናምሩድ"** ይህ ስም (BDB 650) ከባቤል ወይም ባቢሎን መስራት እና ነነዌ (በዘፍ 10፡8-12 ላይ አሶር) ናምሩድም ኃያል አዳኝ ተባለ እርሱም የመጀመሪያዋን ቅኝ ግዛት ሜሴፓታሚያን መሰረተ (በወንዞች የተከበበች ምድር የጢግሮስ እና የኤፍራጥስ) ስለዚህ እነዚህ ሁለት መጠሪያዎች አሶር እና ናምሮድ (1) ተመሳሳይ ስያሜዎች (2) በናባው ፓላሳር እና በናቡከደነጾር ስር ስላላቸው አዲሷ ባቢሎን ይናገራል፡፡

▣ **"አሶርም ምድራችን ሲያጠቃ እርሱ ይታደገናል"** በታሪክ ግን የተፈጠረው ክስተት ይህ አልነበረም፡፡ ስለዚህ ይህ

1. ስለ ወደፊቱ ቂሮስ ይናገራል (539 ዓ ዓ ስለ ባቢሎን ውድቀት ኢሳ 44-45)
2. ስለ ወደፊቱ የፍጥረት መጨረሻ የሚናገር (የመሲሁ ዘመን)
3. ስለ ሀሰተኛ ነቢያቶች የስህተት መልዕክት የሚናገር (ምንአልባት)

**5፡7-9** አብዛኛውን በሚክያስ መጽሀፍ (በሌሎችም ነቢያቶች) እግዚአብሔር የእርሱን ከጥፋት የተረፉ ህዝቦች (ልዩ ርዕስ 2፡12) ወደ እየሩሳሌም ይመልሳቸዋል፡፡ ለማብራሪያ የልዩ ርዕሱን 4፡7 የብሉይ ኪዳን የወደፊት ትንቢቶችን ከ አዲስ ኪዳን የወደፊት ትንቢቶች ጋር ማየት፡፡ ነገር ግን በአውዱ ላይ እግዚአብሔር የቀሩትን ታማኝ አማኞች በአለም ሁሉ ለበረከት ይሆኑ ዘንድ ይበትናቸዋል፡፡ (ከጌታ ዘንድ የሆነ ጠል) ቁጥር 7 እንዲሁም የፍትህ አሸናፊ እና የእግዚአብሔር ሰው ቁጥር 8 ይህ ትክክለኛ ከሆነ ያህዌ ከሀገር መውጣትን የእርሱን ህዝብ ለመበተኛነት ይጠቀምበታል (የዘፍጥረት አላማ ብዙ ተባዙ ሲል የወደቀው ሰው ግን ተቃወመው ዘፍ 10-11)፡፡ የእርሱ የተበተኑ ህዝቦች በህዝብ እና በአህዛብ መካከል ሁሉ የእርሱ ምስክሮች በመሆን የዘፍ 12፤2-3 22፤18፤26፤4 የሐዋ 3-25 ገላ 3-8!
ይህ በዚህ እንዳለ ሁለቱንም ሐረጎች ለመመልከት ይቻላል ብዩ አምናለሁ፡፡ (ቁጥር 7-8) ከፍርድ ጋር በማያያዝ (ቁጥር 9 2ኛ ሳሙ 17-12) ይህ ጥቅስ ስለ ማን እንደሚናገር ብዙ ክርክሮች አሉ፡፡ አንዳንዶች ከተበተኑት እስራኤላዊያን አንጻር ይመለከቱታል፤ አንዳንዶች ደግሞ ከመጨረሻው ዘመን የእግዚአብሔር ህዝቦች (ሮሜ 9-11፤2፡28-29 ገላ 3) በአጠቃይ ይህ ሁሉ አውድ (ከ5ለ-9 ያለው) የሚገልፀው ስለ ሀሰተኛ ነቢያቶች የሀሰት ተስፋዎች እና ትንቢቶች ነው (3፡5 ተመልከት)፡፡ ሚክያስ ቀስበቀስ ከፍርድ ወደ ምህረት መልዕክቱን ይቀይራል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ 5፡1-5ሀ የእውነተኛ ነብይ ትንበያ ነው፡፡ ነገር ግን 5፡5ለ-9 ያለው ደግሞ ስለ ሀሰተኛ ነቢያቶች የሀሰት ተስፋ ይናገራል፡፡

## ልዩ ርዕስ፡ የቦብ ወንጌላዊነት ቅድመ ዝንባሌዎች

ለአንባቢዬ የግድ መግለጽ የምሻው በዚህ ነጥብ ላይ ቅድመ ዝንባሌ አድሏዊነት እንዳለብኝ ነው። የእኔ ስልታዊ ሥነመለኮት ካልቫኒዝም አይደለም ወይም ሕጋዊ ፍቃዳዊነት፣ ነገር ግን የታላቁ ተልዕኮ ወንጌላዊነት ነው (ማለትም፣ ማቲ. 28፡18-20፤ ሉቃስ 24፡46-47፤ ሐዋ. 1፡8) ። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሁሉ የሚሆን ዘላለማዊ እቅድ እንዳለው አምናለሁ (ምሳ.ዘፍ. 3፡15፤ 12፡3፤ ዘጸ. 19፡5-6፤ ኤር. 31፡31-34፤ ሕዝ. 18፤ 36፡22-39፤ ሐዋ. 2፡23፤ 3፡18፤ 4፡28፤ 13፡29፤ ሮሜ. 3፡9-18፤19-20፤21-31)፣ በእሱ መልክና አምሳል የተፈጠሩት ሁሉ (ዘፍ. 1፡26-27)። ኪዳናቱ በክርስቶስ አንድ ሆነዋል (ገላ. 3፡28-29፤ ቆላ. 3፡11)። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ምሥጢር ነው፣ የተሸሸገ አሁን ግን የተገለጠ (ኤፌ. 2፡11-3፡13)!
ይህ ቅድመ-እውቅና ሁሉንም የቃሉ ትርጓሜዎቼን አቅልሟቸዋል ማለትም፣ (ዮናስ)። ሁሉንም ጽሑፎች የማነበው በእሱ በኩል ነው! ይህ በርግጥ አድሏዊነት ነው (ሁሉም ተርጓሚዎች አሉባቸው!)፣ ነገር ግን እሱ ከቃሉ የሆነ መረጃዊ ቅድመ ግምት ነው!

**5፡7 "ጠል"** ጠል የሚለው ቃል በብሉይ ኪዳን ብዙ ትርጉም አለው

1. የእግዚአብሔር በረከት ዘፍ 27፡ 28 ዘኍ 11፡9፤ ዳ 33 13 28 ምሳ 19፤12 ሆሴ 14፤5 ዘካ 8፤12
2. ጠል ከሌለ መለኮታዊ እርግማን ነበር 2ሳሙ 1፡21 1ነገ 17፡1 ሐጌ 1፡10
3. በጸሐይ ብርሃን በቀላሉ የሚተን ስለሆነ ዘይቤው (ሚስጥራዊ ትርጉም) ታይቶ ስለሚጠፋ ነገር ይናገራል ዘፀ 16፤13፤ ኢሳ 18፤4 ሆሴ 6፤4፤4፤13፤3 (ከጉም እንፋሎት እና ጭስ ጋር ይመሳሰላል)
4. ዘይቤው (ሚስጥራዊ ትርጉሙ) ህይወት ወይም ወጣትነት ኢሳ 26-19
5. ዘይቤው (ሚስጥራዊ ትርጉሙ) መስራጨት የሚልም ይሆናል 2ሳሙ 17፡12 ()

(Dictionary of Biblical Imagery ገፅ. 206-207 ላይ ተመልከት)

**NASB** **"ጠብቅ"**
**NKJV** **"ታገስ"**

**NRSV** **"ተደገፍ"**
**TEV** **...**
**NJB** **"እረፍ"**

ይህ ግስ (BDB 875 I፣ KB 1082፣ Piel IMPERFECT) በ *Piel* አቀማመጥ መሰረት 3 ትርጉሞች አሉት፡፡

1. አንድን ነገር በጉጉት መፈለግ ኢዮ 3:9፤ 6:19፤ ኢሳ. 5:2፣4፣7፤ 59:9፣11፤ ኤር. 8:15፤ 13:16፤ 14:19፣22፤ ሆሴ
2. ተጋድመህ ጠብቅ መዝ 56፡6፤ 119፡95
3. ጠብቅ (ቆይ) ሚክ 5፡7

የሰው ልጅ በትዕግስት ጠልን ይጠብቃሉ ምክንያቱም ጠልን ለማምጣት እነሱ ምንም ማድረግ የሚችሉት ነገር ስለሌለ ነው፡፡ "ከጌታ ዘንድ" ነው መምጣት ያለበት፡፡

**NASB** **"ጠብቅ"**
**NKJV፣NRSV** **ታገስ**
**TEV** **...**
**NJB** **....**

ይህ ግስ (BDB 403፣ KB 407፣ Piel IMPERFECT) በፓይል አቀማመጥ መስረት 2 ትርጉሞች አሉት፡-

1. ጠብቅ ሚክ 5፡7
2. ተስፋ አድርግ ሚክ 7፡7

የሰው ልጆች በህይወታቸው ማምረት መስራት እና በራሳቸው ማድረግ የማይቻላቸውን ነገሮች እንዳሉ ያውቃሉ (በመንፈሳዊ ሀይል ብቻ የሚሰራ)፡፡ ይህ ደግሞ ቁጥር 7 እና 8 ተያያዥነት ያላቸው መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የትርጉም ሀሳብ ግን አፅኖት መስጠቱስ ላይ ተያያዥነት አለው ወይ? ቁጥር 7 መልካም አጽኖት ሲኖረው ቁጥር 8 ግን አሉታዊ አፀኖት አለው (ቁጥር 9)፡፡

ምናልባት ሌላ ተያያዥነት ያለው ተቃራኒ ምሳሌ ሊኖር ይችላል (ለምሳሌ ምሳ 19፤12 "አንበሳ" እና "ጠል" የሚለውን ቃል ይጠቀማል)፡፡ የተበተኑት እስራኤላዊያን ለበረከት ወይም ለእርግማን ሲሆኑ ይችላሉ፡፡ እግዚአብሔር እውነትንም ሆነ ፍርድን በእነሱ አማካኝነት ወደ ህዝቡ ያመጣል፡፡ ብርሃን ሀላፊነትን ያመጣል (ሉቃ 12፤48)፡፡

▣ **"አንበሳ"** አንበሳ የሚለው ዘይቤ (ሚስጥራዊ ትርጉም) ጥንካሬን እና ሀይልን የሚገልጽ መሆኑን ጥንታዊ የቅርብ ምስራቅ ይጠቀሙበት ነበር፡፡ ልዩ ርዕስ አንበሳ የሚለውን በብሉይ ኪዳን ሆሴ 5፡14 መመልከት ይቻላል፡፡

▣ ***"ማንም የሚያስጥለን የለም"*** ይህ ፈሊጣዊ አነጋገር ሲሆን የአምላካዊ ሐይልን ለመግለጽ የተቀመጠ ነው (ዘዳ 32፡ 39 ኢዮ 10፤7 መዝ 50፤22 ሆሴ 5፤14 እንዲሁም ተቀራራቢ ቃላቶች ኢዮ 9፡12 23፡13 እና ኢሳ 42፡44 ናቸው፡፡)

**5፡9** ይህ ከ7-9 ያለው ሰንኝ በጣም አከራካሪ ነው፡፡ ስለዚህም የተለያዩ አስተምሮቶች በብዙ ተርጓሚዎች እና አስተያየት ሰጭዎች ተቀምጠው እናገኛለን፡፡ ቁጥር 9 ከቁጥር 7-8 ያለውን ሀሳብ የሚያጠቃልል ሀሳብ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም በቀጥታ ነፃ ስለሚወጡት የመጨረሻው ቅሬታዎች ይናገራል፡፡

"ማስወገድ" የሚለው ቃል (BDB 503፣ KB 500፣ Niphal IMPERFECT፣ ምናልባት JUSSIVE መልኩ) መሰረት የቁጥር 10፤ 11፤ 13፤ እና 14ን የሚዳስስ ሲሆን ስለ ከነዓን ህዝብ ላይ ስለሚሆነው ፍርድ የሚናገር አውድ ነው ፡ይህ ህዝብ ትምክት በ፡-

1. ጦር ሀይሉ ብዛት
2. በጠንካራ ምሽጎቹ
3. በሀይማኖታዊ ስርዓታቸው እና በጣዖታቸው ነበር

ይህ የሀሰት ተስፋ እና የሀሰት አምልኮም ከነዓንና እና በአከባቢ በሚኖሩ ህዝቦች እንዲሁም በእስራኤልና በይሁዳ ላይ ተጽእኖ አሳድሮ ነበር (ዘፍ 15፤16)፡፡

## ሚክያስ 5:10-15

**10 በዚያም ቀን ፈረሶችህን ከመካከልህ አጠፋለሁ፥ ሰረገሎችህንም እሰብራለሁ፥ ይላል እግዚአብሔር**
**11 የምድርህንም ከተሞች አጠፋለሁ፥ ምሽጎችህንም ሁሉ አፈርሳለሁ**
**12 መተትንም ከእጅህ አጠፋለሁ፥ ምዋርተኞችም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆኑልህም**
**13 የተቀረጹትን ምስሎችህንና ሐውልቶችህን ከመካከልህ አጠፋለሁ፥ ለእጅህም ሥራ ከእንግዲህ ወዲህ አትሰግድም**
**14 የማምለኪያ ዐፀዶችህንም ከመካከልህ እነቅላለሁ፥ ከተሞችህንም አፈርሳለሁ። 15 ባልሰሙም አሕዛብ ላይ በቍጣና በመዓት እበቀላለሁ።**

**5፡10-15** የእግዚአብሔር ህዝብ የተባሉት በእርሱ ላይ አይታመኑም ነበር ነገር ግን (1) በወታደራቸው ብዛት ቁጥረ 10 (2)በገነቡት ምሽጎቻቸው ቁጥር 11 (3) በአስማተኞቻቸው ቁጥር 12 እና በጣዖቶች ከቁጥር 12-13 ይመኩ ነበር ኢሳ 2፡8)፡፡ ያህዌ ለማቆም ሀይን እና ፈቃዱን መፈፀም ነበረበት፡፡ ይህ "እኔ" የሚለው የተደጋገመ ቃል በህዝ 36፡ 22-38 ላይ ያለውን ያስታውሰኛል (ስለ አዲሱ ኪዳን ያብራራል)፡፡

**5፡10** "***በዚያም ቀን***" የሚለው ቃል ስለ እግዚአብሔር የፍርድ ቀን የሚናገር ነው (4፡ 1፤6 ን ተመልት)

▣
**NASB፣ NKJV** **"መቁረጥ"**
**NRSV** **"ማጥፋት"**

**TEV** **"ማስወገድ"**
**NJB** **"ገንጥሎ ማስወገድ"**

ይህ ግስ (BDB 503፣ KB 500፣ Hiphil PERFECT) በ *Hiphil*አቀማመጥ ታዋቂ ዘይቤ ነው፡፡("ቆርጦ ማስወገድ") ስለ ሙሉ በሙሉ ማጥፋት እና ማስወገድ ያወራል (ምሳሌ ቁጥር 9፣10፣11፣12፣13፣ ኢሳ 9፣14፣10፣7፣14፣22 አሞፅ 1፤5 8 ዘካ 9-10)፡፡

▣ **"ፈረሶችህን"** የእግዚአብሔር ህዝብ (ነገስታቶች) ከእግዚብሔር ትዕዛዞች ጋር (ዘዳ 17፡16) ወታደራዊ ሀይላቸውን ለማብዛት ወደ ግብጽ መሄዳቸው (ሰረገሎች) ይህ ተራ አባባል ሳይሆን በየትኛውም ዘመን ወታደራዊ ሀይልን የሚገልጽ ነው፡፡

▣ **"ሰረገሎችህን"** ሰረገሎች የዚያን ዘመን ዋና የጦር መሳሪያ ነበሩ፡፡ በዚህ ጊዜ ነበር (በዋናነት ከግብጽ ሂክሶስ) በፎኒሺያን ወይም በፍሊስጤማዊያን የተዋወቁት እነሱም ከብረት በመስራት እንደ ጠንካራ የጦር መሳሪያ ያደረጉት ነበር፡፡

**5፡11** "**የሰራኸውን በሙሉ አጠፋለሁ"** ከአሶራዊያ መረጃ እንዳወቅነው በ701 ዓ. ዓ. ናቡከደነፆር የይሁዳን አርባ ስድስት በግንብ የተከበቡ ከተሞች ይዞ ነበር (ቁጥር 14ለን ተመልከት)፡፡

**5፡12 "መተተኞች… ጠንቋዮችን"** ከቁጥር 12-14 ያለው ከእግዚአብሔር ህዝብ መካከል የመተተኞችን ስራ የሚሰሩ እንዳሉ ይናገራል (BDB 506 የወደፊቱን ለማወቅ ስለሚያደርጉት ጥረት ይገልጻል)፡፡ ይህን ስራ እንዲሰሩ በዘሌዋ 19፤26 እና በዘዳ 18፡9-22 ተከልክለው ነበር፡፡ ብዙዎች በኤልዛቤል ወደ እስራኤል እንደመጡ በ2ነገ 9፡22 ላይ ተጠቅሷል፡፡

**5፡13** "**የተቀረ ምስሎች… ቅዱስ ሀውልቶች… የእጆችህም ስራዎች"** ይህ የእግዚአብሔር ህዝብ ሲያመልኳቸው ስለነበሯቸው ጣዖቶች ይናገራል (ዘፍ 28፡18 22 ዘዳ 16፡22)፡፡

**5፡14**

**NASB** **"አሼሪም"**
**NKJV** **"የእንጨት ምስሎች"**
**NRSV፣ NJB** **"ቅዱስ ሀወልቶች"**
**TEV** **"የአሼሪም አምላክ ምስሎ"**

ይህ የሚናገረው በትልልቅ (ረዣዥም) አለቶች ላይ ክፍ ብሎ ከተሰቀለው ከባአል ምስሎች ጎን ስለሚቀመጡ ከእንጨት የተሰሩ የጣዖት ሀወልቶች ነው፡፡ (BDB 81 የተረጠበ እንጨት ወይም ከለመለመ ዛፍ የተሰራ ጣዖት ሲሆን የሚወክለውም የህይወትን ዛፍ ነው)፡፡ ይህ የሚወክለው ልጅ የምትሰጠውን የከንዓንን አምላክ ሲሆን (ለምሳሌ ዘዳ 7፤5፤12፤3፤16፤21 መሳ 3፤7፤6፤ 25- 1ነገ 14፡23፤ 2ነገ 18፤8 2ዜና 31፡1) በቁጥር ላይ ያለው የተቀረፀ የጣዖት ምስል ደግሞ ልጅ የሚሰጥ አምላክን (ባአልን) ይወክላል፡፤ እነዚህ እንግዳ ልጅ የሚሰጡ አምላኮች እና አማልክቶችን በፎኒሺያ (ኤልዛቤል) አማካኝነት ሲተዋወቁ እነሱም በእግዚአብሔረ ህዝብ መካከል በጣም ታዋቂና ዝነና የሆኑ ጣዖቶች ነበሩ (1ነገ 18-19)፡፡

▣

**NASB፣ NKJV፣**
**TEV፣ NJB** **"ከተሞችህን"**
**NRSV** **"መንደሮችህን"**

አንዳንድ ሙህራን እንደሚገምቱት "ከተሞች" የሚለው ቃል ደግሞ ብሎ የተጠቀሰ በመሆኑ (በቁጥር 11 BDB 746) ይህ ተመሳሳይ ሀሳብ ደግሞ "አሼሪም" የሚለው በቁጥር 14 1ኛ መስመር ላይ መጠቀስ ነበረበት፡፡ ይህን ለማለት ደግሞ ከኡጋሪቲክ ሥር ምናልባት ከአረብ ሥር ሊሆን ይችላል ብለው ይገምታሉ (REB በደም የተሸፈኑ መስዊያዎች)፡፡

የአይሁዳ ማጥኛና መጽሀፍ ቅዱስ የግርጌ ማስታወሻ እና NET መጽሐፍ ቅዱስ ጣዖት በማለት ይጠቅሰዋል፡፡

**5፡15** "**በቁጣ እና በዓመት እበቀላለሁ"** "ቁጣ" የሚለው ("በ" የሚለው መስተዋድድ ሲደመር) እና "መዓት" (BDB 404) የሚሉት ቃል ትርጉሙን አፅዕኖት ይሰጡታል (ታላቅ መአት)፡፡

ሌላው አስተያየት ደግሞ ቁጥር 15ን በተለየ አስተያየት መመልከት ነው፡፡ ያሕዌ የእርሱን የተበተነ የኪዳን ህዝብ ያነጻቸዋል ከእንደገናም ያድሳቸዋል ነገር ግን ለእርሱ ምላሽ የማይሰጡትን አምንዝራዎች (ጣዖት አምላኪዎች ) ፈጽሞ ያጠፋቸዋል፡፡

▣ **"ስምተው በማይታዘዙ ህዝቦች ላይ"** የሚለው ግስ (BDB 1033፣ KB 1570፣Qal PERFECT) መስማት ማለት መታዘዝ ማለት ነው ይላል፡፡ (4፡1 ላዬያለውን ማስታወሻ ተመልከት) ተመሳሳይ የሆነ ቃል IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ) መልክ ሲቀመጥ በ6፡1 ላይ ተደጋግሟል፡፡ ከተበተኑት የኪዳን ህዝቦች መካከል ያህዌን በመስማት ነፃ የወጡት ግን ለሰሙት እውነት ምላሽ መስጠት አለባቸው (ቁጥር 7)፡፡ ይህ ግን ከዚህ በፊት ከነበረው አንቀጽ ጋር ሲነፃፀር ምናልባት ከአውዱ የወጣ ይመስላል ነገር ግን እግዚአብሔር በእስራኤል ወይም በይሁዳ ህዝቦች መካከል የማያዳላ የመሆኑ ሁኔታ ትኩረት በመስጠት ይናገራል፡፡

እርሱ የአለም ዳርቻ ሁሉ አምላክ ነው ነገር ግን የእርሱ የኪዳን ህዝቦች ብቻ የእርሱን እውነተኛ ቃል በእውነተኛ ነቢያቶች ይሰማል፡፡

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ከ750 አመት ከኢየሱስ ልደት በፊት ይኖር የነበረው ሚክያስ እንዴት ትክክለኛውን የኢየሱስ የትውልድ ቦት መተንበዩ በጣም ጠቃሚ ሊሆን ቻለ
2. ከቁጥር 7-9 ያሉት ሀሳቦች ከ8ተኛው ክፍለ ዘመን የነቢያቶች አውድ እንዴት ወጣ ያለ ሊሆን ቻለ
3. አገራችን ልክ እንደ እስራኤል ከቁጥር 10-14 ያለው ጋር እንዴት ሊያገናኛት ይችላል
4. የኢሳ 2፡6-8 የሚክ 5፡10-14 ያለውን ተመሳሳይነት አብራራ

# ሚክያስ 6

## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|
| ጌታ እስራኤልን ይለምናል | በኢየሩሳላዊያን የተለያዩ መደቦች ላይ ተከታታይ የሆነ ለቅሶ፣ ዛቻ፣ እና ተቃውሞ (6:1-7:7) | በእስራኤል ላይ የጌታ ጉዳይ | በእስራኤል ላይ የያህዌ ጉዳይ |
| 6:1-2 | 6:1-2 | 6:1 | 6:1-5 |
| | | 6:2 | |
| 6:3-5 | 6:3-5 | 6:3-5 | |
| | | እግዚአብሔር የሚፈልጋቸው | |
| 6:6-7 | 6:6-8 | 6:6-8 | 6:6-8 |
| | | | በከተማውስጥ ባሉ አታላዮች ላይ |
| ለተጓደለው ፍትህ የእስራኤል ቅጣት | | | |
| 6:9-12 | 6:9-16 | 6:9-16 | 6:9-15 |
| | | | የሰማርያ ምሳሌነት |
| 6:13-16 | | | |
| | | | 6፡16 |

### የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ vii ተመልከት)

*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኋላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የምዕራፍ ስድስት ዝርዝር አስተዋጽኦ

ሀ እግዚአብሔር (ያህዌ) በህዝቡ ላይ ይፍርዳል ቁ 5 እግዚብሔር ለህዝቡ ያለውን ታማኝነት የሚያስረዳበት ክፍል (ቁጥር 1-5 ነው በነብያቶች ዘንድ አይነቱ ንግረት የተለመደ ነው፡፡ ለምሳሌ ኢሳ 1 ኤር 2 ሆሴ 4

ለ ህዝቡ በእግዚአብሔር ለቀረበበት ክስ ምላሽ ይሰጣል (ቁ 6-7)

ሐ እግዚአብሔር (ያህዌ) በነብዩ በኩል ለህዝቡ ያለውን ፈቃድ ያስታውቃል፡ (ቁ 8)

መ እግዚአብሔር (ያህዌ) የእራኤልን ባለጠጎችና ተንኮለኞች ሃጢያት እንደሚቀጣ በነብዩ በኩል ይናገራል (ቁ 9-16) በዚህም ምክንያት በዘሌ 26 እና በዘዳ 28 የተነገረውን የቃል ኪዳኑን እርግማን ጠቅሶ ይፈርዳል (ለምሳሌ (ራዕ 26:26፤ ዘዳ 28:15፣18፣40፣51)፡፡

## የቃላትና የሐረግ ጥናት

### ሚክያስ 6፣1-5

**1 አሁን፦ ተነሣ፥ በተራሮችም ፊት ተፋረድ፥ ኮረብቶችም ቃልህን ይስሙ ብሎ እግዚአብሔር የሚለውን ስሙ።**
**2 ተራሮች ሆይ፥ ጠንካሮች የምድር መሠረቶችም ሆይ፥ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ክርክር አለውና፥ ከእስራኤልም ጋር ይፋረዳልና የእግዚአብሔርን ክርክር ስሙ።**

**3 ሕዝቤ ሆይ፥ ምን አድርጌሃለሁ? በምንስ አድክሜሃለሁ? መስክርብኝ።4 ከግብጽ ምድር አውጥቼሃለሁ፥ ከባርነት ቤትም ተቤዥቼሃለሁ በፊትህም ሙሴንና አሮንን ማርያምንም ልኬልህ ነበር። 5 ሕዝቤ ሆይ፥ የሞዓብ ንጉሥ ባላቅ የመከረውን፥ የቢዖርም ልጅ በለዓም የመለሰለትን አሁን አስብ የእግዚአብሔርንም የጽድቅ ሥራ ታውቅ ዘንድ ከሰጢም ጀምሮ እስከ ጌልገላ ድረስ አስብ።**

**6-1-2 "ስማ"** የሚለው የተለያዩ አገባብ ይዞ እንገኘዋለን ቁ 1-2

1. "ስሙ" … የፀሎን ጥያቄን ያመለክታል በጣም አስፈላጊና ትኩረት የሚሻ ነው፡፡
2. "ተነሳ" (BDB 877፣ KB 1086) - *Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)*
3. "ተፈረዳ" (DBD 936፣ KB 1224) - *Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)*
4. "ስማ"(BDB 1033፣ KB 1570) - *Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ) IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)* አስፈላጊ ትኩት የሚሻ
5. "አድምጥ"(BDB 1033፣ KB 1570) - *Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)*

"ስማ" የሚለው ለሚክያስ አዲስ ምዕራፍ ሲጀምር የሚጠቀምበት ቃል ነው (1:1፤ 3:1፤ 6:1)፡፡ ሁለተኛው ትኩረት የሚሻው "ተነሳ" የሚለው የወንድ ፆታ አመልካች ሆኑ ነጠላ ቁጥር ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተው ሚክያስ የሚለው የእግዚአብሔር አፈ ቀላጤ መሆኑን ወይም በአጠቃላይ ህዝቡን አመልካች ነው፡፡

ምርጫ #1 የበለጠ ትክክል ይገልጠዋል፡፡

ይህ ምዕራፍ እንደምዕራፍ እንደ ሁሉ የፍርድን ሁኔታ ያሳያል፡፡ ከዋናው ሀሳብ ጋር ተዛማች ያላቸውን የተለያዩ ቀላትን ልብ ማለት ይሻል፡

1. "ተነሳ" (መመስከር እና የሐሰት ምስክርነት ለምሳሌ ዘዳ 19፡15-16 እና የሀሰት ምስክርነት መዝ 27፡12፣ 35፡11) ቁ 1
2. "መፍረድ" (በፍርድ ቤት መከራከርን በመጥፎ ጎኑ ወይንም በአዎንታዊነት ለምሳሌ ኢሳ 1፣17 3:13፣ 97:16፣ በአውንታዊ መልኩ ኢሳ 7፣9 መዝ 103፣8፣14 በተለይ ቁ 9 ኤር 50፡34
3. "ስሙ" (ማለትም እንደ ፈራጅ ወይንም የተሰየሙ ዳኞች ለምሳሌ 1፣2)
4. "አድምጡ" ከቁጥር 3 ጋር አንድ አይነት ነው ቃል
5. "መካሰስ" ከቁ 2 ጋር ይመሳሰላል
6. " ጉዳይ ወይንም ክርክር" ከቁ 3 እና 5 ጋር ይመሳሰላል
7. "አለመስማማት"(BDB 406፣ KB 410፣ *Hithpael* IMPERFECT ወደ ሌላ ዳኛ ማሸጋገር ፍርድን ማሸጋገር ለምሰሌ ኢሳ 2፡4፤ ሚክ 4፡3

እግዚአብሔር (ያህዌ) በቃል ኪዳን ህዝቡ ተደጋጋሚ የሆነ አለመታመን (ሆሴዕ) እና ሀጢያት (የአመጽ) ምክንያት እየተፋታ ነው፡፡ ይህ ክርክር የፍርድ ጉዳይ እስከ ምዕራፍ 7 ሊቀጥል ይችላል፡፡

▣ ***"ተራሮች ሆይ፥ ጠንካሮች የምድር መሠረቶች"*** በብሉይ ኪዳን እውነትን ለማስረገጥ ለማረጋገጥ ሁለት ምስክሮች ያስፈልጋሉ (ዘኁ 35፡30፤ ዘዳ 17፡6፤ 19፡5)፡፡ያህዌ ሰማይና ምድርን ለምስክርነት እንደተጠቀመባቸው ሁሉ በእስራኤና በይሁዳ ላይ "ተራሮች ኮረብቶችን" ለምስክርነት ይጠራቸዋል (ዘዳ 4:26፤ 31:28፤ 32:l፤ መዝ 50:4 እና ኢሳ 1:2)፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ተራሮች በብሉይ ኪዳን በሰውኛ ተገልጠዋል (እንደ ሰው) ለምሳሌ 2 ሳሙ 1፣21 መዝ 15፣16 ኢሳ 35፣1 እነዚህ ዋነኛ ቦታዎች ናቸው ለምሳሌ ከፍተኛ ቦታዎች "በአልና አሰታሮት" የሚመለኩባቸው ናቸው፡፡

**6፡2** ይህ ጥቅስ ግልፅ የሆነ ዘይቢያዊ አነጋገር ነው፡፡ እግዚአብሔር በጅምላ ህዝቡን ከመውቀስ ይመለስና በይሁዳ ላይ ተራሮችንና ኮረብቶችን ቋሚ መሰረታዊ ሰውኛ የሆነ ምስክር አድርጎ ያቀርባል፡፡

▣ ***"ህዝቡ"*** እድለኛ (የቃል ኪዳን ህዝብ ቁ 3 ሮሜ 9፡4-5) ሀላፊነት ለመወጣት እድለኛ ነው!

▣ **"እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ክርክር አለውና"** ይሀ የሰሜኑን አስር ነገድ አያመለክትም (እስራኤልን ብቻ) ቁ 16 ብቻ፣ ነገር ግን ከሁሉም ወገኖች የያዕቆብን ዘሮች ወይም (እራኤልን)፡፡

**6፡3-5** እግዚአብሔር (ያህዌ) ህዝቡን ለምን ብሎ ይጠይቃል ይኸውም እርሱ ታማኝ ሆኖ ሳለ እነርሱ ግን በእልከኝነታቸው ስለቀጠሉ እግዚአብሔር (ያህዌ) አባታዊ ቃሉ እየተጠቀመ ነው፡፡ (ይህም የህታይት ሱዘርን የሁለተኛ ሺ ስምምነት በመግለጥ ዘዳግመንና የኢያሱን መጽሐፍ 24 አስተዋፅኦ በመጠቀም እርሱን የታማኝነት ስራ አድራጎት ወደ ኋላ ሄዶ ያስሰባቸዋል፡፡

**6፡3 "ምን አድርጌአለሁ"** እያለ ህዝቡን በመጠየቅ በእርሱ ላይ ያላቸውን ክስና ማንጎራጎርና ማጉረምረም ወደ እርሱ እቅርበው እንዲዋቀሉ ይጠይቃቸዋል ኤር 2፡5፡፡ እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ሃላፊነት የት መቼ እንዴት በታማኝነት እንዳልተወጣ ይጠይቃል፡፡

▣ ***"መስክርብኝ"*** ይህ ህጋዊ የሆነ ቃል ዘይቤ (BDB 772፣ KB 851፣*Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)* ) ይህም ማለት በእርሱ ላይ ህጋዊ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ነው፡፡ ዘፀ 20:16፤ ዘዳ 5:20፤ 11 ሳሙ 1:16)፡፡ እግዚአብሔር በፍቺ ለጉዳይ ላይ እንደሚንቀሳቀስ አንድ ግለሰብ ሆኖ እናየዋለን፡፡

**6፡4** "**ከግብጽ ምድር አውጥችሀለሁ"** ይህ የሚያመለክተው ለዘፍ 15፣6 እግዚአብሔር አብርሃም የገባውን ተስፋና በዘፅአት ከተፈፀመው ክስተት ጋር በማዛመድ ነው፡፡ ዘፀአት የሚለው በብሔራዊ እስራኤል ታሪክ ውስጥ መስታዊ የሆነ የእግዘአብሔር ድረጊት ነው ዘፀ 20:2፤ ዘዳ 5:6፤7:8፡፡ ይህ ድርጊት በግልጽ የሚያሳየው ለገባው ኪዳን ያለበትን ሀላፊነቶችና ታማኝ የሆነን መስጠቱን ነው፡፡ ለምሳሌ አሞ 2 ፡30፤ 3፡1፣ 9፡7) የእግዚአብሔር ፀጋ ከሙሴ ህግ በፊት ነበር ወይም መጥተዋል፡፡

▣ **"ተቤዥቼሃለሁ"** የሚለውን ቃል በቃል ስንተረጉመው መልስ መግዛት(BDB 804፣ KB 911፣ *Qal* PERFECT)፡፡ የቃሉ አገባቡ የሚያሳየው አንድን ባሪየ ወይም በጠላት ተማርኮ የታሰረ ምርኮኛ ወይም እስረኛ ሰው መልሶ መግዛትን ነው፡፡ በተለይም መቤዠት ወይም መዋጀት የሚለውን ርዕስ በሆሴዕ 7፡13 ተመልከት፡፡

▣ **"በፊትምህም ሙሴንና ኤሮንን ማርያምን ልኬልህ ነበር"** እግዚአብሔር የሚያስፈልገውን መገለጥና አመራር ሰጥቶ ነበር፡፡ ነገር ግን ህዝቡ ዓመፁ፤ በመወጣት ሰዓትም እንኳ እስጢአመፁ፡፡ የእግዚአብሔር ህዝብ የእልከኝነት ወይም የአንገተ ዳንዳናት መዝገብ እንደነበረው እስጢፋኖስ በሐዋ 7 ስብከቱ ገልጾታል፡፡ ልብ በሉ ማርያም እንደ ሙሴና አሮን ሁሉ በአንድነት ተጠቅሳለች፡፡

## ልዩ ርዕስ፡ ሴቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

I. ብሉይ ኪዳን

ሀ ከባህል አንጻር ሴቶች እንደ ንብረት ይታያሉ

1. በንብረት ዝርዝር ውስጥ ተካተዋል (ዘፀ 20÷17)
2. የባሪ ሴቶች አያያዝ (ዘፀ 21÷7-11)
3. የሴቶች መሃላዎች ወይም ቃል ኪዳኖች በማህበረሰቡ ኃላፊነት ባለባቸው ወንዶች ሊሻር ይችላል (ዘሑ 30)፡፡
4. ሴቶች በጦርነት ወቅት እንደ ዘረፋ ይቆጠሩ ነበር (ዘዳ 20÷10-14፤21÷10-14)

ለ በተግባር የጋራ የሆኑ ባህርያት

1. ወንድና ሴት በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጠሩ (ዘፍ 1÷26-27)
2. አባትና እናትን አክብር (ማክበር ዘፀ 20÷12 ዘዳ 5÷16)
3. እናትንና አባትን መፍራት (ዘሌ 19÷3፤20÷9)
4. ወንድና ሴት ናዝራውያን ሊሆኑ ይችላሉ ( ዘሑ 6÷1-2)
5. ሴት ልጆች የመውረስ መብት አላቸው (ዘሑ 27÷1-11)
6. የቃል ኪዳን ሕዝብ ክፍል ናቸው (ዘዳ 29፡10-12)
7. የአባትንና የእናትን ትምህርት (ቃል መከተል (ምሳ 1÷8፤6÷20)
8. የሔዋን ወንድና ሴት ልጆች ‹የሌዊ ብተሰብ) በቤተመቅደስ ውስጥ አምልኮን ይመሩ ነበር (1ኛ ዜና 25÷5-6)
9. በመጨረሻው ዘመን ወንድና ሴት ልጆች ይተነብያሉ (ኢዮዔ 2÷28-29)፡፡

ሐ ሴቶች በአመራር ቦታ/ሚና

1. ማርያም፣ የሙሴ እህት ነብይት ተብላ ነበር (ዘፀ 15÷20-21) እንዲሁም ሚክ 6÷4ን ይመልከቱ፡፡
2. ለማደሪው ድንኳን የሚያገለግሉ ነገሮችን ለመሸመን እግዚአብሔር ሥጦታን ሰጥቷቸው ነበር (ዘፀ 35÷25-26)፡፡
3. ሁሉንም የእሥራኤል ነገዶች የመራች ዲቦራ የተባለች ሴት ነብይት ነበረች (መሳ 4÷4-5፤ 5÷7)
4. ጠፍቶ የነበረውን እና በኋላም የተገኘውን የ"ሕጉን መጽሐፍ" ታነበው እና ትተረጉመው ዘንድ ንጉሥ ኢዮሲያስ የለመናት ህልዳና ነብይት ነበረች (2ኛ ነገ 22÷14፤2ኛ ዜና 34÷22-27)፡፡
5. የእግዚአብሔር ሰው ንግሥት አስቴር በፋርስ የነበሩትን አይሁድ ከሞት ታደገች፡፡

II. አዲስ ኪዳን

ሀ ከባህል አንጻር በአይሁድ እና በግሪኮ-ሮማን ዓለም ከተወሰኑ መብቶች ጋር እንደ ሁለተኛ ዜጎች ይቆጠሩ ነበር/ መቄዶንያ ግን በዚህ አትካከትም)/(ከመቄዶንያበስተቀር)

ለ ሴቶች በአመራር ሚና

1. ኤልሳቤጥና ማርያም፤ ለእግዚአብሔር የተገኙ የእግዚአብሔር ሰዎች (ሉቃ 1፡2)
2. የእግዚአብሔር ሰው ሃና በቤተመቅደስ ታገለግል ነበር (ሉቃ 2፡36)
3. ሊዲያ አማኝና የቤት ውስጥ ቤተክርስቲያን መሪ (የሐዋ 16፡14-40)
4. የፊልጶስ አራት ደናግለ ሴቶች ነብያት ነበሩ (የሐዋ 21፡8-9)
5. ፌቨን በ ክንክራኦስ ላለቸው ቤተክርስቲያን የሴት ዲያቆን ነበረች (ሮሜ 16÷1)፡፡
6. ጵርስቅላ ከውሎስ ጋር አብራ የምትሠራና የአጵሎስ አስተማሪ (የሐዋ 18፡26፤ ሮሜ 16፡3)
7. ማርያ፣ ዩሊያን፣ ብልያጦን፣ ስንጣክ፣ የኔረስ እህት፣ እና ከጳውሎስ ጋር ይሰሩ የነበሩ በርካታ ሴቶች ነበሩ (ሮሜ 16÷6-16)፡፡
8. ዩሊያ (KJV)፣ ምናልባትም የሴት የሴት ሐዋርያ ነበረች (ሮሜ 16÷7)።
9. ኢዮዲያና ሊንጢኬ ከጳውሎስ ጋር አብረው የሚሰሩ (ፊልጵ 4÷2-3)፡፡

III. የዘመናችን አማኝ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎችን ሚዛናቸውን እንዴት ይጠብቃል?

ሀ የመጀመሪያዎቹን የመልእክቱን ተቀባዮች ብቻ የሚመለከቱትን ታሪካዊና ባህላዊ እውነቶችን ከዘላለማዊእውነት አንፃር ለሁሉም ቤተክርስቲያናት በሁሉም ዘመንለሚገኙ ሁሉም አማኞች እውነቱን እንዴትማስተላለፍ ይቻላል?

1. በመንፈስ ቅዱስ መነዳት መልዕክቱን የጻፈውን የመጀመሪያውን ጸሐፊ ዋና ሃሳብ/ዓላማ በደንብ ማጤን አለብን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ በመሆኑም ለእምነትና ለተግባር ብቻኛው ምንጭ ነው፡፡
2. ታሪክ ቀመስ የሆኑ እና በእግዚአብሔር መንፈስ መሪት የተፃፉትን ጽሑፎች ማጤን አለብን፡፡

   ሀ የእስራኤል (የሐዋ 15፤ገላ 3፤ልማዶች (የቤተክርስቲያ ሥርዓት))
   ለ የመጀመሪያውን ክፍለ ዘመን የአይሁድ ኃይማኖት የሚያመለክት
   ሐ የ1ኛ ቆሮንጦስ ውስጥ የተጠቀሱትን ታሪክ ቀመስ የሆኑ የጳውሎስንጸሑፎች

   1) የአረማዊው የሮም መንግሥት የህግ ሥርዓት (1ኛ ቆሮ 6)
   2) ባሪ መሆን (1ኛ ቆሮ 7÷20-24)
   3) ጃንደረባነት (1ኛ ቆሮ 7÷1-35)
   4) ደናግል (1ኛ ቆሮ 7÷36-38)

5) ለጣኦት የሚሰዋ ምግብ (1ኛ ቆሮ 8፤ 10÷23-33)

6) በጌታ ራት ላይ የሚከናወኑ ያልተገቡ ነገሮች /ድርጊቶች (1ኛ ቆሮ 11)

3. በተወሰነ ወቅትና በተወሰነ ባህል ውስጥ እግዚአብሔር ራሱን ግልጽ በሆነ ሁኔታ ገልጧል፡፡ እኛ ግን በትኩረት መቀበል ያለብን መገለጡን እንጂ ማንኛውንም ከመገለቱ ጋር የተቆራኙትን ታሪካዊ ሁነቶችን አይደለም፡፡ የእግዚአብሔር ቃል የተጻፈው በተወሰነ ወቅት በተወሰነ ባህል ውስጥ በሰው ቃል የተጻፈ ነው፡፡

ለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አተረጓጎም የመጀመሪው ጽሐፊ ዓላማ/ሐሳብ መፈለግ አለበት፡፡ በጊዜው ለማለት የፈለገው ምን ነበር? ለትክክለኛ አተረጓጎም ይህ ወሣኝናመሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህንእውነት እኛ ለዘመናችን ሥራ ላይልናውለው ይገባል፡፡ አሁን በዚህ ክፍል ላይ በአመራር ላይ ሰላሉት ሴቶች ላይችግር አለ (እውነተኛው የአተረጓጎም ችግር የሚከሰተው ቃሉን መተርጎሙ ላይነው፡፡ እንደመሪዎች ከሚለዩት መጋቢዎች ይልቅ ብዙ አገልግሎቶች ነበሩ ማለትነው? ወይስ ሴት ዲያቆናትና ሴት ነብያት እንደጨዋዎች ይታዩ ይሆን? ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንጦስ 14፡34-35 እና 1ኛ ጢሞቲዎስ 2፡9-15 ላይ ሴቶች በጉባኤ አምልኮ ላይ መምራት እንዳሌለባቸው አስረግጦ መናገሩ በጣም የተገለጠ ነው! ይሁን እንጂ ያንን እውነትዛሬ እንዴት ነው ሥራ ላይ የማውለው? የጳውሎስም ሆነ የእኔ ባህል የእግዚአብሔርን ቃልና ፈቃዱን ዝም እንዲያሰኘው አልፈልግም፡፡ ምናልባት የጳውሎስ ዘመን ገደብ የበዛበት ሊሆን ይችላል፤ በአንፃሩም ደግሞ እኔ ያለሁበት ዘመን ደግሞ ገደብ የለበትም፡፡

የጳውሎስ ቃላትና አስተምሮዎች ሁኔታዊና የመጀመሪያው ክፍለዘመን እውነቶች ብቻ ናቸው ማለት ለእኔ አይመቸኝም፡፡ የእኔ አእምሮና የእኔ ባህል በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የጻፈን ጸሐፊ መቃወም አለበት ለማለት እኔ ማነኝና?

ይሁን እንጂ የሴተር መሪዎችን በሚመለከት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች ሲኖሩ ታዲያ ምንድ ነው የማደርገው? (በጳውሎስ ጽሑፎች በሮሜ 16 እንኳ)? ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንጦስ ምዕ 11-14 ላይ የሰጠው ትንታኔ ነው፡፡ በ11÷5 ላይ ሴቶች ራሳቸውን ሸፍነው በጉባኤ ላይ እንዲሰብኩና እንዲጸልዩ የሚፈቅድ ይመስላል፤ ይሁን እንጂ በ14÷34-35 ላይ ደግሞ ጸጥ እንዲሉ ይፈልጋል፡፡ ሴት ዲያቆናትና (ሮሜ 16) እና ሴት ነብያት ነበሩ (የሐዋ 21÷9)፡፡ ይህ ልዩነት ነው እንግዲህ ጳውሎስ የሰጠው ማብራሪያ (በሴቶች ላይ ከሚደረገው ማዕቀብ ሰለሚገናኝ) በመጀመሪያው ክፍለመን ለነበሩ የቆሮንጦስና የኤፌሶን ቤተክርስቲያን ብቻ የተወሰነ ነው እንድል ነፃነትን የሚሰጠኝ፡፡ በሁለቱም ቤተክርስቲያናት ውስጥ አዲስ የተመሰረተውን ነፃነት ሴቶች ለመጠቀም ችግሮች ነበሩ፤ ይህም በጊዜው የነበረችው ቤተክርስቲያን የጠፉትን በክርስቶሰ ወንጌል ለመድረስ ችግር በፈጠረ ነበር፤ ወንጌል ይስፋፋና ፍሬያማ ይሆን ዘንድ የነበራቸው ነፃነት መገደብ ነበረበት፡፡

እኔ ያለሁበት ዘመን ከጳውሎስ አንፃር ተቃራኒ ነው፡፡ እኔ ባለሁበት ዘመን ወንጌል ምናልባት ሊገደብ የሚችለው የሰለጠኑና የተማሩ ሴቶች ወንጌልን ካለሰሰበኩ እንጂ ካልመሩ አይደለም! የጉባኤ አምልኮ ዋነ ግብ ምንድ ነው? ወንጌልና ደቀመዝሙርነት አይደለም? እግዚአብሔር በሴት መሪዎች ሊከብርና ደስ ሊሰኝ ይችላል? መጽሐፍ ቅዱስ በጠቅላላው "አዎን" የሚል ይመስላል፡፡

ለጳውሎስ ሐሳብ ራሴን ማስገዛት እፈልጋለሁ፤ ምክንያቱም የእኔ ሥነ-መለኮት ከመጀመሪው የጳውሎስ ነውና፡፡ አሁን በሚታየው የሴቶች እንቅስቃሴ ተፅዕኖ እንዲደርስብኝ ወይም ማሰመሰል አልፈልግም! ይሁን እንጂ ቤተክርስቲያን በግል የሚታዩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን ለምሳሌ የባርነትን ተገቢ አለመሆን፣ ዘረኝነትን፣ ልቅ ወሲብን እና አክራሪነት ላይ ምላሽ ለመስጠት ለዘብተኛ ናት፡፡ እንዲሁም ባለንበት ዘመን በሴቶች ላይ በሚደረገው ጥቃት ላይ ተገቢውን መላሽ ለመስጠት ቸልተኛ ናት፡፡ እግዚአብሔር ባሪያንም ሆነ ሴትን በክርስቶስ ነፃ አውጥቷል፡፡ በቤተክርስቲያን የተሠራ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እንዲያሰራቸው አልፈቅድም፡፡

አንድ ሌላ ነጥብ ላንሳ፤ አንድ ተርጓሚ የቆሮንጦስ ቤተክርስቲያን በጣም የተበጠበጠች ቤክርስቲያን ነበረች፡፡ የካሪዝማቲክ ስጦታዎች (የጸጋ) ሽልማት ያሰጡና ያኮሩ ነበር፡፡ ምናልባትም ሴቶች በዚህ ሁኔታ ቴዘውም ሊሆን ይችላል፡፡ በኤፌሶን ባሉ የቤት ውስጥ ቤተክርስቲያናት ሴቶችን ለግል ጥቅማቸው መጠቀሚያ የሚያደርጉና ቅጥረኛ ሰባኪዎች አድርገው የሚጠቀሟቸው የሐሰት መምህራን በኤፌሶን ተጽእኖ እንደደረሰ ጭምር አምናለሁ፡፡

ሐ ለተጨማሪ ምንባብ አስተያየት

*How to Read the Bible for All Its Worth* በጎርደን ሊ እና ዳግላስ ሰቱዋርት (ገጽ 61-77)

*Gospel aℵd Spirit: Issues iℵℵew Testameℵt Hermeℵeutics*በጎርደን ፌ *Hard Sayiℵgs of the Bible* በ ዋልተር ሲ ኬይዘር፤ ፒተር ኤች ዳቢድስ፤ ኤፍ ኤፍ ብሩስ እና ማንፍሬድ ቲ ብራንች (ገጽ 613-616፤ 665-667)፡፡

**6፤5 "አስብ"** (BDB 269፣ KB 269) ይህ ቃል *Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ) IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)* ነው፡፡ ያህዌ የቃልኪዳን ህዝቡ የቀደመውን ዘመን መከራና መገለጥ እነዲያስብ ይፈልጋል ዘኊ 22፤5-6፡፡

▣ **"ባላቅ …በለአም"** ይህ በዝላ 22፤25 ባለው ምዕራፍ የተፃፈ ድርጊት ነው፡፡

▣ **ሲጢም** እስራኤል ልጆች ወደ ተስፋይቱ መድር ከመግባታቸው በፊት መጨረሻ ላይ ሰፈረውባት የነበረው ቦታ ነው በተጨማሪም ከምአባውያን ሴቶች ልጆች ጋር ያመነዘሩበትም ነው (ይህም የመራባት አምልኮ፤ ዘኊ 33፡ 49 እና ኢያሱ 3፤1

▣ **"ጌለጌላ"** ደግሞ እስራኤላውያን ዮርዳኖስ ከተሻገሩ በኋላ ወደ ተስፋይቱ ምድር ከገቡ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰፈሩበት ቦታ ነው፡ በሃጢያታቸው በልብ ዳኝነታቸው በስጢም እያሉ እግዚአብሔር ይቅር ብሎ ሞልቶ ከሚፈሰው የዮርዳኖስ ወንዝ ተሸከሞ አሻግሯቸዋል፡፡ ከላይ የተጠቀሱትን ሁለት ቦታዎች ብንወስድ የሚያመለክቱን የዮርዳስ ወንዝ በሚሞላበት ወይም በሞላበት ወቅት የተፈጠረውን ታምራዊ መሻገር ነው፡፡

## ሚክያስ 6፤6-8

**6 ምን ይዤ ወደ እግዚአብሔር ፊት ልምጣና በልዑል አምላክ ፊት ልስገድ?**
**የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የአንዱን ዓመት ጥጃ ይዤ በፊቱ ልምጣን?**
**7 እግዚአብሔርስ በሺህ አውራ በጎች ወይስ በእልፍ የዘይት ፈሳሾች ደስ ይለዋልን?**
**ወይስ የበኵር ልጄን ስለ በደሌ፥ የሆዴንም ፍሬ ስለ ነፍሴ ኃጢአት እሰጣለሁን?**
**8 ሰው ሆይ፥ መልካሙን ነግሮሃል እግዚአብሔርም ከአንተ ዘንድ የሚሻው ምንድር ነው?**
**ፍርድን ታደርግ ዘንድ፥ ምሕረትንም ትወድድ ዘንድ፥ ከአምላክህም ጋር በትሕትና ትሄድ ዘንድ አይደለምን?**

**6፡6-7** በዚህ ጥቅስ አገባብ መሰረት የሁለት ሺህ የሆነ ገሃዳዊ ገፅታ ነው የሚያሳየው የሀሳብ መልእክቱን የሚቀበለው ሰው ተጠቅሟል፡፡ ነብዩ የብዙ ቁጥር በሀሳብ ስሎ በይሁዳ ዘንድ የተለመደውን የሰዎች አመለካከት ድምጸት ጠቁሟል፡፡ እንዲህ ብለው ያስቡ ነበር እግዚአብሔር እኮ ለእኛ ሚዛናዊ እንዳልሆነና እንዲያውም ብዙ መስዋዕትን ብቻ የሚፈልግ መሆኑ፡፡
6፡6

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"በከፍታ ያህ አምላክ"** |
| **NKJV** | **"ከፍ ያልከው እግዚአብሔር"** |
| **NRSV** | **"እግዘኢብሔር ለከፍታ ላይ"** |
| **TEV** | **"የሰማይ አምላክ"** |
| **NJB** | **"ከሁሉ በላይ እግዚአብሔር"** |

ይህ (BDB 43፡ CONSTRUCT BDB 928) ከፍ ላለው ለልዑል እግዚአብሔር ለልዑል አምላክ ዘይቤያዊ አነጋገረ ነው፡፡

▣ ***"የአንዱን ዓመት አመት ጥጃ"*** ይህ ነውር የሌለበት ጥጃ ለመስዋእት የሚቀርበው ከስምንት ቀን እአስከ አንድ ዓመት ያለ ነው (ዘሌ 9፤3 እና 22፤27)

**6፤7 *"በሺህ አውራ በጎች"... የዘይት ፈሳሾች"*** ህዝብ 1ኛ እግዚአብሔር እንድናቀርብ የሚፈለገው ግብታዊ አይደለም የሆነው ሆኖ ግን እግዚአብሔር እንደሚሉት አልጠየቃችሁም የአህዛብን የአምልኮ ልምምድ ያንፀባረቁ ነበር፡፡ ወይም 2ኛ በአንድ ብሔራዊ በአል ብዙ መስዋዕቶች ይቀርባሉ (ሰለሞን ቤተ መቅደስ ለጌታ በሚያመርቁበት ጊዜ ለምሳ 1ነገ 8፤63 እነዚህ ተወካይ ተናጋሪዎች በብሔራዊ የንስሃ ቀን ስለሚደረገው ድርጊት ነው የሚናገሩት (የተለመደውን መስዋት)

▣ "***የበኩር ልጄን የሆዴንም ፍሬ"*** ለመሆኑ ይህ ነገር ሆን ብሎ (የተጋነነ) የዘፍጥረት 22 ወይም የዘፅ 13፤2-12 ያለው ሀሰብ የሚፃረር ነውን በሙሴ ህግ 20፤2-5 ዘዳ 12፤31 18፤10 መዝ 106፤37 ኤር 7፤31 የእግዚአብሔር ህዝብ በመንፈሳዊ ህይወቱ ግራ ሲጋባና እግዚአብሔርን (ያህዌን) ሞሎክ መልስ ለማምለክ መሞከር የአምላሜ አምላክ አምን ማምለክ አይቀሬ ነው (ሌዋ 18:21፤ 20:2-5፤ 1ነገ 11:7፤ II ነገ 3:27፤ 16:3፤ 17:17፤ 21:6፤ 23:10፤ ኤር 32:35፤ አሞፅ 5:26፤ ሐዋ 7:43) የእግዘኢብሔር ህዝብ ምድሪቱን ለመታደስ የሚሞክረው ምንም ነውር የሌለበትን ህጻን ሲያቀርብ ነው፡፡ አንድ በኩል የመስወዕቱን ይዘት ወደ አልሆነ አቅጣቻጫ ይሰጠዋል (ይሰፋዋል) የሆነው ሆኖ ግን ይህ አስተሳሰብ ነው በዘፍጥረት 22 እና በመስቀሉ (በጌታ)የታየው ማር 10 45፤ 2ቆሮ 5፤2፡፡

**6፡8 *"ነግሮሃል"*** የግሱ (BDB 616፤ KB 665) ሀሳብ የአሁንና የሀላፊ ጊዜ አመለካችና ምናልባትም ባህሪይና ፈቃድ ገልጧል፡፡ በተለይም ከመስዋእቱ ጋር በምናዘምድበት ጊዜ 1ሳሙ 15፤22 መዝ 51፤16-17 ኢሳ 1፤11-17 ሆሴ 6፤5-6 ይህ ጥቅስ የሚክያስ እርምት ሰጭነት የሚያሳይ ይመስላል፡፡

▣ ***"ሰው ሆይ"*** ይህ ሰማያዊ አጠራር የሚያመለክተው የአመንዝራዋን የቃል ኪዳን ህዝብ ይሁዳን ነው፡፡ ይህ ጥቅስ አህዛብ እንዴት እንደሚድኑ አይደለም የሚያመለክተው ነገር ግን የቃል ኪዳን ህዝቡ እንዴት ለእግዚብሔር ታላቅ ይቅርታ ምላሽ እየሰጡ መኖር እንደሚችሉ አመልካች ነው በብሉይ ኪዳን ተምሳሌትነት ምንም ነውር የሌለበት እንስሳ መስዋዕት መሆኑን ነው (የሐ 29 ቆሮ 5፤21) ለዚህ ርዕስ ግልፅ የሆነ ውይይት ካስፈለገ የመጽኸፍ ቅዱስን ጠንካራ አባባሎች የሚለውን ተመልከት (*Hard Sayings of the Bible*፤ pp 336-337)

▣ ***"መልካሙን"*** ይህጥቅስ ለሚክያስ በጣም ታዋቂ አባባሉ ነው፡፡ አባባሉ የሚያመለክተው የፍቅርን ቅድሚያ ስጭነት ርዕስ በርዕስ ግንኙነት ከፍተኛ ደረጃ የያዘውን እንክብካቤ ፍቅር ግላጭ ነው (መዝ 14:1፤3፤ 37:3፤ 51:17፤ 12:6 እና በመዝ 15:2-5 ላይ ተገልጧል፡፡ የእርግማን ማረጋገጫ አይደለም፡፡ መስዋት ብቻ ነው (ኢሳ 1:13፤ አሞፅ 5:21-23) ይህ ጥቅስ የእግዚአብሔር አይን መልካም ለሚለው ቃል በጣም ጥሩ ትርጉም የሚሰጥ ነው (BDB 373 II) (3:2፤ ኢሳ 1:17፤ 5:20፤ አሞፅ 5:14-15)፡፡

▣ ***"የሚሻው"*** ይህ ግስ (BDB 205፤ KB 233) ቀጣይነት ያለው ድርጊት (*Qal* ACTIVE PARTICIPLE) ገላጭ ነው፡፡ ቃሉ ሲተረጎም "የሚፈለገውን" ወይም "የሚጠይቀው" የሚል ነው (ለምሳሌ ዘዳ 18፤19፤23፤21)፡፡

▣ ***"ፍርድን"*** የሚለው በዚህ ዓውድ ፍትህ (ፍርድ) የሚያሳየው አውንታዊነት አድሎ የሌለበት ከቁ 9-11 ባለው ክፍል ላይ የሚያጤን ነው፡፡ ብሉይ ኪዳን የሚያውቀው በአለማውያንና በተቀደሱት መካከል ምንም ልዩነት እንደሌለ ነው፡፡ ሁሉም ህይወት ቅዱስ ነው በምዕራፍ 3 ስር ያለውን ማስታወሻ ተመልከት በተከታታይ የተገለፀ *Qal* INFINITIVE CONSTRUCTS ሦስት ቃላትን እናገኛለን፡፡

1) "ፍርድን" ታድርግ ዘንድ ፍርድን አድርገን (BDB 793፤ KB 889)
2) "ምህረትን" ትውድድ ዘንድ (BDB 12፤ KB 17)
3) "በትህትና" ትሄድ ዘንድ ምህረት (BDB 229፤ KB 246)

"ትህትና" የሚለው ቃል መጨረሻ የሌለው ፍፅምነት የሚያሳይ ነውINFINITIVE ABSOLUTE
መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት የየእለቱ የህይወት አቅጣጫ ላይ ተፅእኖ ያመጣል፡፡ እምነት የሕይወት ዘይቤ ነው ስነ መለኮት ወይም የእምነት አቋም መግለጫ አይደለም፡፡ የዘላለም ህይወት መለኮታዊ የቃል ኪዳን ስጦታ ነው፡፡ በውድቀት ጊዜ የጠፋውን መልክ /አምሳል/ እንደገና ማደስ የሚጠበቁ ባህሪዎች ከእግዚአብሔር ከሰውም ጋር ባለን ግንኙነት) ናቸው፡፡ ይህ ቃል በኪዳን ውስጥ እነዚያን ባህሪይዎች በዋናነት መግለጥ የሚችል ነው፡፡

▣ ***"ምህረትን መውደድ"*** የሚለውን በጣም ዋነኛ ሀይለኛ የሆነ የቃል ኪዳን ቃል ነው *hesed* (BDB 338)። ቃሉ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ን የቃል ኪዳን ታኻነት ነው የሚያንፀባርቅ ከምንም ጋር ያልተገኛው የእግዚብሔር መስዋዕታዊ ፍቅር ነው። እኔ ሳስበው ቀሉ በብዙ መንገድ ሲተረጎም በአዲስ ኪዳን ከምንም ጋር ያልተያያዘ ፍቅር እግዚአብሔራዊ ፍቅር ነው (ኢጋፔ)። በተለይም ልዩ ርዕስ በሆሴዕ 2፥19 ላይ ተመልከት።

▣ ***"በትህትና ተመላለስ"*** ይህ ለሰው ልጅ ፍላጎት እውቅና የሚሰጥ ነው። አማራጭ ትርጉም ለዚህ ቃል ትሁት BDB 557፣ ምሳ 11:2) እና እግዚአብሔር አቅርቦት የሙሴ ህግ የሚጠይቀውን ሁሉ ትክክለኛ የሆነ አመለካካት ሳይኖር የሚደረግ ስርዓት (ኢሳ 29:13 ቁ 57:15 and 66:2) የእግዚአብሔርን የሚያስቆጣ ነው። (1 ሳሙ 15:22፤ Matt 23:23)ተመላለስ በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ (1)የአንድ ሰው ማንነት የገባ ዘያቢያዊ ንግግር ለምሳሌ ዘፍ 5፣24፣6-9 ኢዮብ 34፣8፣ መዝ 1፣1 ሚል 2፣6 እና ወይም (2) ለእየለቱ አሎኣችን ዘይቢያዊ ንግግር ለምሳሌ ኢፌ 4፣1፣17፣5፣2፣18 መጽሀፍ ቅዱሳዊ እምነት ከእግዘኢብሔር እና ከሌሎች ሰዎች ጋር በየእለቱ የምንኖወው እንጂ በሳምንቱ ወይም በአመት የሚኖረን ግንኙነት አይለደም።

## ሚክያስ 6:9-16

**[9]የእግዚአብሔር ድምፅ ከተማይቱን ይጠራታል ስምህን መፍራት ጥበብ ነው የመቅሠፍትን በትር፥**
**እርሱንም ያዘጋጀ ማን እንደ ሆነ ስሙ።**
**[10] በውኑ በኃጢአተኛ ቤት የኃጢአት መዝገብ፥ የተጸየፈም ውሸተኛ መስፈሪያ ገና አለ ይሆን?**
**[11] በአባይ ሚዛንና በከረጢት ባለ በተንኰል መመዘኛ ንጹሕ እሆናለሁን?**
**[12] ባለ ጠጎችዋን ግፍ ሞልቶባቸዋል በእርስዋም የሚኖሩ በሐሰት ተናግረዋል፥**
**ምላሳቸውም በአፋቸው ውስጥ ተንኰለኛ ነው።**
**[13] ስለዚህ እኔ ደግሞ በክፉ ቍስል መታሁህ ስለ ኃጢአትህም አፈርስሁህ።**
**14 ትበላለህ፥ ነገር ግን አትጠግብም፥ ችጋርህም በመካከልህ ይሆናል ትወስዳለህ፥**
**ነገር ግን አታድንም የምታድነውንም ለሰይፍ እሰጣለሁ።**
**[15] ትዘራለህ፥ ነገር ግን አታጭድም ወይራውንም ትጨምቃለህ፥ ነገር ግን ዘይቱን አትቀባም**
**ወይኑንም ትጨምቃለህ፥ ነገር ግን የወይን ጠጁን አትጠጣም።**
**[16] አንተን ለጥፋት፥ በእርስዋም የሚኖሩትን ለማፍዋጫ እሰጥ ዘንድ**
**የዘንበሪን ሥርዓትና የአክዓብን ቤት ሥራ ሁሉ ጠብቃችኋል፥**
**በምክራቸውም ሄዳችኋል የሕዝቤንም ስድብ ትሸከማላችሁ።**

**6:9** የእግዚአብሔር ድምፅ መልእክት ሶስተኛው መስመር ላይ ይጀምርና እስከ ቁ 16 ድረስ ይቀጥላል። "ድምፅ"(BDB 876) አብዛኛውን ጊዜ የእግዚአብሔርን ንግግር ለመግለፅ ተጠቅመውበታል። (ዘጸ 19:19፤ 1 ነገ 19:13፤ ኢሳ 6:8፤ ህዝ 10:5) የ NJB ትርጉም "ከተማይቷን ያናውጣል" ዘጸ 19:13፣16።

▣ ***"ከተማይ"*** የሚለው እየሩሳሌም የያህዌ ስሙን ያኖረበትን ልዩ ከተማን ያመለክታል (ዘዳ 12:5፣11)፣ የመቅደሱን ቦታ አመልካች ነው።

***"ስምህን መፍራት ጥበብ ነው"*** ሀረጉ የሚክያስ መስተካከያ አመልካች ወይም በኋላ ሲተረጎም የተጨመረ (በ JB እና NJB የተዘለለ ነው)።እርሱ የጥበብ ንግግር ነበር። NRSV በቅንፍ ውስጥ ያስቀምጠዋል።

የእብራዊያን ቃል (BDB 444) ሲተረጉመው የጥበብ ድምፅ ይለዋል። ይህም በጥበብ መፅሀፍት ዘንድ የተክኒካዊ ቃል ነው ኢዮ 11:6፤ 12:16፤ 26:3፤ ምሳ 2:7፤ 3:21፤ 8:14፤ 18:1፤ ኢሳ 28:29)።

▣ ***"ፍርሃት"*** የሚለው ቃል "ማየት" ከሚለው የእብራዊያን ቃል እርማት የተደረገበት ነው (BDB 906፣ NKJV) ሰባ ሊቃናት ትርጉምን ተከትሎ (BDB 431)። ከአውድ ጋር ሊሄድ የሚችል የተሻለ እና በ NASB፣ RSV፣ NRSV፣ TEV፣ NEB፣ REB፣ NIV ውስጥ የሚገኝ ነው።
"ስም" የሚለው ቃል የእግዚአብሔር ስብእና ገላጭ ነው። (BDB 1027፣ ዘፍ 4:26፤ 12:8፤ 13:4፤ 21:33፤ ሐዋ 7:59፤ 9:14፣21፤ 22:16፤ ሮሜ 10:9-13፤ 1 ቆሮ 1:2፤ II ጢሞ 2:22)።

▣ ***"ስሙ" ይህ*** (BDB 1033፣ KB 1570) *Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ) IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)* አትኩሮት የሚሻ መሆኑን የሚያመለክት አዲሱ NKJV ወይንም "ብትሩን ስማ" ሲል NIV ደግሞ "ብትሩን አትኩር " ይላል።

▣ ***"ነገድ ሆይ"*** ይህ የሰባዎቹን ትርጉም (Septuagint )ተከትሎ ነው። የማሶሬቲኩ ጽሁፍ "ብትር" የሚለውን ይይዛል(BDB 641። ለምሳሌ፣ የእረኛ በትር" ዘዳ 4:17፤ ኢሳ 10:5)።ይህ የእብራዊያን ስርወ ቃል ሊሆን የሚችለው (1) ብትር፤ (2) ምርኩዝ፤ **(3)**ነገድ። እግዚአብሔር በቃል ኪዳኑ ወንድና ሴት ልጆቹ ችግርና ድሆች ማህበራዊ ህይወት መዛባት ትኩረት ይሰጣል (ቁ 12)።

▣

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"ግዜውን የወሰነ"** |
| **NKJV** | **"እርሱን የወሰነ"** |
| **NRSV** | **" የከተማይቱ ህዝብ"** |
| **TEV** | **"እናንተ በከተማይቱ የተሰበሰባችሁ ህዝቦች"** |

NJB " የተሰበሰባችሁ ዜጎች"

NASB እና NKJV ዕብራይስጡን ይከተላል ግን NRS፤ TEV፤ እና NJB የተስተካከለውን ይከተላል (የሰባ ሊቃናት ትርጉምውስጥ የለም)፡፡ የማሶሬቱ ትርጉም ይህንን ከተከተለ የሚናገረው ልዑል እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ምስረታ እና ሚፈርዱን ይናገራል፡፡

**6፡10**

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"እስካሁን በክፎዎች ቤት ሰው አለ"** |
| **NKJV** | **"እስካሁን እነርሱ የክፉዎች መዝገብ ናቸው"** |
| **NRSV** | **"የክፉዎች መዝገብ ልረሳ እችላለሁ"** |
| **TEV** | **"በኃጢአተኛ ቤት የኃጢአት መዝገብ፥ "** |
| **NJB** | **"ውሸተኛ መስፈሪያ ገና አለ ይሆን?"** |

በማሶሬቲኩ ውስጥ ያለው ቃል አይታወቅም:

1. አለ ይሆን (ማሶሬቲኩ፣ NKJV)
2. ሊረሰው እችላለሁ(NRSV)
3. ልሸከመው እችላለሁ(NJB)

የውሸት መስፈርያ አውድ (ማለትም፣ ቁ 10-11) ማሶሬቲክ ጽሑፍ በንግድ ምሳሌ መልሶ ማሰማትን (ተናባቢውን ሳይሆን አናባቢውን መቀየር) ይጠይቃል(ቁ 11)፡፡ ማሶሬቲኩ አዎን የሚል መልስ የሚፈልግ ጥያቄ ነው፡፡

**6፡10-11 "ውሸተኛ መስፈሪያ...... በአባይ ሚዛንና......በተንኰል መመዘኛ "** የማሶሬቲኩ ቁ 11 በጥያቄዎች መልክ ነው፣ ዳሩ ግን አይደለም መልስ ይጠብቃል፡፡ እነዚህ በንግድ ውስጥ ያሉ የማጭበርበር ምሳሌዎች ነው(ሆሴ 12:7፤ አሞ 8:5)፡፡ ለሙሉ የእብራይስጥ መለኪያ እና መመዘኛዎች ውይይት በአሞ 8:5 ውስጥ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት፡፡

**6፡12 "ባለ ጠጎች"** ሚክያስ ለዕድለኞች፣ ለኃይለኞች፣ ተጽዕኖ ለሚያመጡ፣ እና ለጤናማ የቃል ኪዳን ብሔሮች ያለው መልዕክት ከአሞጽ መልዕክት ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ መስመር 2 እና 3 እንጼት ተመሳሳይ እንደሆኑ አስተውል፡፡ ሁሉም ሦስቱ መስመሮች የቁ 9-10 ማጠቃለያ እና የቁ 8 ተቃራኒ ነው፡፡

**6፡13-15** እግዚአብሔር እዬሩሳሌምን በምርኮ እና መንዷን በመዝጋት ይፈርድባታል፡፡ በመልካም መንገድ ያገኙትን ሁሉ ሌሎች ይደሰቱበታል፡፡ ከውጭ ጣዖታት ሕዝቡን ለመጠበቅ የያህዌ ድከመት ሳይሆን ለዚህ ሁሉ ምክንያት ሐጥኃታቸው እንደ ሆነ አስተውሉ(ቁ 13b፣16)!

**6፡13**

| | |
|---|---|
| **NASB፣ NKJV** | **"በሽተኛ አደርገሃለሁ"** |
| **NRSV፣ TEV፣** | |
| **NJB** | **"ወደ ታች አደርግሃለሁ"** |

NASB እና NKJV ማሶሬቲኩን ይከተላሉ፤ ሌሎች ሰባ ሊቃናት ትርጉምን ፔሽታን(Peshitta)፣እና ቩልጌትን(ቮልጌት) ይከተላሉ፡፡

▣ **"ባዶ አድርግሃለሁ"** ይህ ቃል(BDB 1030፣ KB 1563፣ Hiphil INFINITIVE ABSOLUTE) በአካዲያን የሜድካል መጽሐፍቶች ውስጥ "ሸባ" "ደነዝ" እና "አንካሳ፡፡" በሚል ተተርጉሞ ይገኛል፡፡ ስለዚህ፣ የመጀመርያዎቹ በቁ 13 ሁለት የግጥም መስመሮች ውስጥ የቃል ኪዳን ሕዝብ ኃጢአት ከመሥራት ጋር በተገናኘ የህክምና ምሳሌነት አለው፡፡

**6፡14**

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"እጦት በመካከልህ ይሆናል"** |
| **NKJV** | **"ረሃብ በመካከልህ ይሆናል"** |
| **NRSV** | **"ኃይለኛ ረሃብ በመካከልህ ይገኛል"** |
| **TEV** | **"አሁንም ትርባለህ"** |
| **NJB** | -------- |

ችግሩ"እጦት" ወይም ባዶ የሚል ቃል ነው (ማለትም፣መራብ፣ BDB 445)፡፡ ትርጉሞ አይታወቅም፡፡ KB (446) "መቆሸሽ" የሚል አለው፡፡ ፔሽታ(Peshitta) "የበሰበሰ" በሚል ይተረጉማል(ማለትም፣ የአንጀት በሽታ)፡፡ እንደዚሁም እነዚህን የሚመለከት ከሆነ አይታወቅም(1) ግለሰብ ወይም (2) ሐጢአተኛ ማህበረሰብ፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"ለጥበቃ ለማስወገድ ትሞክር ይሆናል"** |
| **NKJV** | **"ትንሽ ትወስድ ይሆናል"** |
| **NRSV** | **"ታስቀምጣለህ"** |
| **TEV** | **"ትወስዳለህ"** |
| **NJB** | **"ትሰበስባለህ"** |

▣ **"ማንሳት"** የሚለው ግስ (BDB 690 I፣ KB 744፣ *Hiphil* [ይህ አይነት በብሉይ ኪዳን በብዙ ቦታ ጥቅም ላይ ዉሏል በአዲስ ኪዳንም የድንበር ምልክት ድንጋይን ማንሳት በሚል] JUSSIVE) ንብረትን ወይም ዋጋ ያለውን በተሸለ ሁነታ ለመደበቅ እንደሚደረግ ሙከራ ይታያል ፣ዳሩ ግን አዋጭ አይሆንም!

የግጥሙ ሁለተኛ መስመር“ማቆየት” ወይም “መቆጠብ” የሚለውን ግስ ይጠቀማል (BDB 812)፣ በእሳ 5:29 ውስጥ ለማቆየት ስትል ምግቧን ለሚትልስ አነስታይ አንበሳ ጥቅም ላይ የዋለ፡፡ NKJV እንደ NET መጽሐፍ ቅዱስ የሥጋ በልታ እንስሳትን ምሳሌ የሚከተል ይመስላል፡፡

**6:15 “ትዘራለህ ነገር ግን......... አታጭድም”** ይህ ቃለ ኪዳንን ከመስበር ከሚመጣ መርገም ውስጥ ነው(ዘዳግ 28:30 ff)፡፡

▣ **“ራስህን በዘይት አትቀባም”** በጥንቷ ቅርብ ምስራቅ ወይራ ብዙ ጥቅም ነበረው፡፡ አንዱ ለማህበራዊ ጉዳይ ለመዘጋጀት ቆዳን ለመታሸት ነበረ፡፡ የደስታ እና የእርካታ ምልክትም ነበረ፡፡ ዘይት ማጣት እንደ መለኮታዊ ፍርድ ይታይ ነበር (ዘዳ 28:40)፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **NASB፣ NRSV፣** | |
| **NJB** | ***“የወይን ፍሬ*** |
| **NKJV** | ***“ጣፋጭ ወይን”*** |
| **TEV** | ***“ወይን”*** |

ይህ የአብራይስጥ ቃል ነው “ለአድስ ወይን” (BDB 440)፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት በአሞ 6:6፡፡

**6:16 “የዘንበሪን”** ይህ በፖለቲካ ውጤታማ ንጉስ ነበር (1ነገ 16:21-28፣ ለነገስታት የአገዛዝ ዘመን ተጨማሪ Appendix ላይ ተመልከቱ፡፡ በአሦር መዝገብ ውስጥ ስሙ ለአሥሩ ነገድ የተለመደ ስም ሆኖ ነበር(ማለትም፣ የዘንበሪ ቤት)፡፡ ይህ ስም ለጣዖታቸውም ምልክት ሆኖ ነበር፡፡ ይሁዳን ይወክላል (ለምሳሌ II ነገስ 17:19፣22)!

▣ **“አክዓብ”** ይህ ኤልዛቤልን ያገባ የዘንበሪ ልጅ ነው፣ ወደ ሰማርያ ማህበረሰብ የበአልን እና የአሼራን ነብያት ያመጣ(1 ነገስ 16:29-34፤ 18፤ 21:25፣ for dates of reign see Appendix)፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **NASB** | ***“ወቀሳ”*** |
| **NKJV፣ NRSV** | ***“ቁጣ”*** |
| **TEV** | ***“ንቀት”*** |
| **NJB** | ***“መሳለቂያ”*** |

ይህ “ቁጣ” የእብራይስጥ ቃል ነው (BDB 1056)፣አለመክበርን እና አለመቀበልን ማሳያ ባህላዊ መንገድ ነበር(II ዜና 29:8፤ ኤርም 19:8፤ 25:9፣18፤ 29:18፤ 51:37)፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **NASB፣ NKJV** | ***“የሕዝቤን ወቀሳ ትሸከማለችው”*** |
| **NRSV** | ***“የሕዝቤን ወቀሳ ትሰከማለችው”*** |
| **TEV** | ***“በሁሉም ቦታ ያለ ሕዝብ በንቀት ያያሃል”*** |
| **NJB** | ***“ስለዚህ የሌሎች ሕዝቦችን ወቀሳ መቻል አለብህ”*** |

የአተረጓጎም ልዩነት አማራጮች የተመወረቱት:

1. በ ማሶሬቲኩ - NASB፣ NKJV፣ NRSV
2. በሰባ ሊቃናት ትርጉም- TEV፣ NJB

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ለምን እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ፍርድ አመጣቸው?
2. ለምን ቁ 6-7 እንደዚህ አሳዛኝ ሆኑ?
3. የራሳችን ጉዳይ እግዚአብሔርን ይገደዋል?

# ሚክያስ 7
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች*

| NKJV | NRSV | TEV | NJB |
|---|---|---|---|
| ለእሥራኤል ኃጢአት ሀዘን | በእስራኤል የተለያዩ ህብረተሰብ ክፍሎች ሁሉ ላይ የታሰበ ተከታታይ ሰቆቃ፣ ማስፈራራት፣ እና ወቀሳ (6:1-7:7) | የእሥራኤል የተለመደ ሙስና | ዓለምአቀፋዊ በደል |
| 1:17-2:9 | | | |
| 7:1-2 | 7:1-7 | 7:1-4ሀ | 7:1-6 |
| 7:3-4 | | 7:4ለ-6 | |
| 7:5-7 | | 7:7 | 7:7 |
| የእሥራኤል መናዘዝ እና መጽናናት | እግዚአብሔር ለእሥራኤል ምህረቱን ትዕግስቱን ፍቅሩነ ያሳያል እፈረት ደግሞ ጠላትን ይከድናል | ጌታ ደህንነትን ያመጣል | ጽዮን ስድብን ከጠላት |
| 7:8-10 | 7:8-10 | 7:8-10 | 7:8-10 |
| | | | የተሀድሶ ትንቢት |
| 7:11-13 | 7:11-13 | 7:11-13 | 7:11-13 |
| እግዚአብሔር እሥራኤልን ይምራል | | የእግዚአብሔር ርህራኄ በእሥራኤል ላይ | ጸሎት ለጽዮን ጠላት ግራ መጋባት |
| 7:14 | 7:14 | 7:14 | 7:14-17 |
| | | 7:15-17 | ለእግዚአብሔር ይቅርታ ልመና |
| 7:16-17 | | | 7:18-20 |
| 7:18 ሀ-ሐ<br>7:18 መ-19ለ<br>7:19ሐ-20 | 7:18-20 | 7:18-20 | |

**ዓውዳዊ እይታዎች**

ሀ ይህ ምዕራፍ ማን እንደሚናገር እና ለማ እንደሚነገር በማወቅ መመርመር ይቻላል፡፡

ለ NIV መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ተናጋሪው ማንነት ባጭሩ የሚያስቀምጠው

1. ሚክያስ፤ ከቁ 1-7፤11-13፤16-20
2. ጽዮን፤ቁ 8-10፤14
3. እግዚአብሔር፤ቁ 15

ሐ የሚከተሉትን ለማድረግ አስቸጋሪ ነው

1. የነብዩን ንግግር እና የእግዚአብሔርን ንግግር መነጣጠል
2. ምክንያቱም የእብራዊያን የግጥም ስንኝ የነገሩን ባለቤት በተደጋጋሚ ስለሚቀያየር ስነ ጽሑፉን ምቹ ማድረግ

## የቃላትና የሐረግ ጥናት

### ሚክያስ፡ 7:1-6

**1 የዛፍ ፍሬና የወይን ፍሬ ከተለቀሙ በኋላ እንደ ቀረው ቃርሚያ ሆኛለሁና ወዮልኝ!**
**መብል የሚሆን ዘለላ፥ ነፍሴም የተመኘችው በመጀመሪያ የበሰለው በለስ የለም።**
**2 ደግ ሰው ከምድር ጠፍቶአል፥ በሰውም መካከል ቅን የለም ሁሉ ደምን ለማፍሰስ ያደባሉ፥**
**ሰውም ሁሉ ወንድሙን በመረብ ለመያዝ ይከታተለዋል።**
**3 እጆቻቸውን ለክፋት ያነሣሉ አለቃውና ፈራጁ ጉቦን ይፈልጋሉ፥ ትልቁም ሰው እንደ ነፍሱ ምኞት ይናገራል**
**እንዲሁም ክፋትን ይጐነጕናሉ።**
**4 ከእነርሱም ሁሉ የተሻለው እርሱ እንደ አሜከላ ነው፥**
**ከሁሉም ቅን የሆነው እንደ ኵርንችት ነው ጠባቆችህ የሚጐበኙበት ቀን መጥቶአል አሁን ይሸበራሉ።**
**5 ባልንጀራን አትመኑ፥ በወዳጅም አትታመኑ የአፍህን ደጅ በብብትህ ከምትተኛው ጠብቅ።**
**6 ወንድ ልጅ አባቱን ይንቃልና፥ ሴት ልጅ በእናትዋ ላይ፥ ምራቲቱም በአማትዋ ላይ ትነሣለችና፥ የሰው ጠላቶች የቤቱ ሰዎች ናቸውና።**

**7:1"ወዮልኝ!"**ይህ የአንድ ግለሰብ ለቅሶ (BDB 47) ነው፤ ምንም እንኳን ወደ ማህበረሰቡ የሚዛመትበት ጊዜ ቢኖርም፡፡ ይህ በመዝሙረ ዳዊት የተለመደው የአጻጻፍ ስልት ነው (ዝ.ከ. መዝ 5፣13፣22፣55፣71)፡፡

ማን እየተናገረ እንደሆነ እርግጥ የሆነ ነገር የለም፤

1. ነብዩ ራሱ
2. ነብዩ የያህዌ ተወካይ ተናጋሪ ሆኖ
3. ነብዩ የእግዚአብሔርን ቅሬታዎች ወክሎ

4.

| | |
|---|---|
| **NASB** | ***"ፍሬ ለቃሚ ሆኛለሁኝ"*** |
| **NKJV** | ***"የበጋ ፍሬ እንደሚሰበስቡት ሆኛለሁና"*** |
| **NRSV** | ***"የበጋ ፍሬ ከተለቀሙ በኋላ ፤ እንደ ቀረው ቃርሚያ ሆኛለሁና ወዮልኝ"*** |
| **TEV** | ***"ምንም ፍሬ እንዳልቀረው ረሃብተኛ ሰውሆኛለሁና"*** |
| **NJB** | ***"የበጋ ጊዜ ሰብሳቢ"*** |

NASB "በጋ"(BDB 884) የሚለውን ቃል ዘሎታል ፤ ይህም ቃል በ"ሙቀት" ይታወቃል፡፡ ይህ የምርት የመጀመሪያ መሰብሰብ ሳይሆን የመጨረሻ ለቀማ ነው፡፡ ያህዌ ፍሬ ለማየት ብዙ ጠብቋል ፤ ነገር ግን ምንም የሚሰበሰብ ምርት አልነበረም!

▣ ***"የዛፍ ፍሬና የወይን ፍሬ ከተለቀሙ በኋላ እንደ ቀረው ቃርሚያ"*** ልክ የተራበ ሰው ምግብ እንደሚፈልግ ሁሉ ሚክያስ ጽድቅን (ወይም ጻድቅ ሕዝብ ወይም ጻድቅ አመራር፤ ማለትም፤ቁ 3) ተርቧል (ዝ.ከ. ማቴ 5:6)፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጽድቅን እንደ ምግብ የማየት ሃሳብ በብዛት ይገኛል (ዝ.ከ. አሞፅ 6:12፣ ዮሐ 15:1-8፣ ፊል 1:11፣ ገላ 5:23)፡፡ በአሜሪካ የአይሁድ ማህበረሰብ (JPSOA) ቁ 1 ሰማሪያን እንደሚያመለክት ይናገራል፡፡ ምግብ ለማግኘት ፈለረገዋል ነገር ግን ሊያገኙ አልቻሉም (ማለትም ፤ምክንያቱም [1] ከበባው ወይም [2] ከእግዚአብሔር የሆነው ርሃብ፤ዝ.ከ. ዘዳ 27-28)፡፡ አአሁማ ይህንኑ ሃሳብ በቁ 7 ላይ ያጠናከረዋል፤ሆኖም ግን እኔ ይህ ዓውድ ከእየሩሳሌም ጋር እንደሚዛመድ አስባለሁ፡፡ በአንድ ጎኑ እነሱ በጣም ዘግይተዋል (ማለትም፤ ጻድቅ ያለመሆናቸው የሚያመጣው መከራ ተፈጽሟል—ምርኮ) እንዲሁም በሌላ በኩል በጣም ቀድመው ተገኝተዋል (ማለትም፤ ወደፊት የሚታደሱበት የተስፋ ቃል ገና አልደረሰም)፡፡

▣ ***"ነፍሴም የተመኘችው በመጀመሪያ የበሰለው በለስ"*** እነዚህ የመጀመሪያ በለሶች በጣም ጣፋጭ እና የሚጠበቁ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን ዋናው ምርት እስከ ሐምሌ ባይደርስም የበለሶቹ የመጀመሪያ ምርት የደረሰው በሰኔ ውስጥ ነበር፡፡ ሰው እነዚህን የመጀመሪያ በለሶች እንደሚናፍቅ ሁሉ ሚክያስ (እንደ እግዚአብሔር ተናጋሪ) ጽድቅን እየናፈቀ ነው፡፡

**7:2** ***"ደግ ሰው"*** ይህ ምንም ሁኔታ የማይገድበውን የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታመኝነት የሚል ትርጉም ላለው የቃል ኪዳኑ ቃል ለሆነው *ሔሴድ* (በሆሴ 2፡19 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ) የተቀጽላ መልኩ ነው (ለምሳሌ ቁ 18፣ 6:8፣ 7:18፣ ኤር 5:1)፡፡ ይህ ቃል ከ"መልካም ሰው" ጋር ትይዩ ነው፡፡ ይህ ምንም እንኳን የሚገኝ ባይሆንም ለቃል ኪዳኑ ታማኝ የሆነን ሰው የሚያመለክት ነው (ለምሳሌ መዝ 12:1፣ ኢሳ 57:1)!

▣ ***"ሁሉ ደምን ለማፍሰስ ያደባሉ"*** ግሱ (BDB 79፤ KB 83) በአብዛኛው በእያሱ እና በመሳፍንት ውስጥ የተጠቀሰ *Qal* IMPERFECT፣ ሲሆን "መውጋት" ተብሎ ተተርጉሟል፡፡ ይህ የአደን ዘይቤ ሲሆን የእግዚአብሔር ሕዝብ ቁንጮ የሆኑትን የወንጀል ጥፋት ዘዴ የሚገልጽ ነው፡፡ (ማለትም ፤ስግብግብነታቸውን ፣ ሃብታቸውን ፣ የመሪዎቹን ኃይለኝነት)፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **NASB** | ***"ደምን ማፍሰስ"*** |
| **NKJV፣ NRSV፣** | |
| **NJB፣** | ***"ደም"*** |
| **TEV** | ***"ግድያ"*** |

ይህ ቃል (BDB 196) በቀጥታ "ደም" ማለት ነው፡፡ ቃሉ ባብዛኛው በስምንተኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ ነብያቶች (አብዛኛውን ሕዝቂል ፤ ዝ.ከ. ሆሴዕ 1:4፣ 4:2፣ 6:8፣ 12:14፣ ዮናስ 1:14፣ ሚክያስ 3:10) ሁከትን እና ሞትን ለመግለጽ የሚጠቀሙበት ነው፡፡

▣ ***"ሰውም ሁሉ ወንድሙን በመረብ ለመያዝ ይከታተለዋል"*** በእያንዳንዱ አጋጣሚ እርስበርሳቸው ይጎዳዱ ነበር፡፡ መርሃቸውም የነበረውም "በማንኛውም ክፍያ ለኔ የተቻለውን ህል ጨምር!" የሚል ሳይሆን አልቀረም፡፡ በእግዚአብሔር አምሳያ የተፈጠሩ ሰዎች ፣ የቃል ኪዳኑ አጋሮች ከንቱ ሆኑ!

**7:3** ***"እጆቻቸውን ለክፋት ያነሣሉ"*** ይህ በሙሉ ኃይል የሚደረገውን ክፋት የሚወቅስ ሌላ ዘይቤ ነው፡፡ ግሱ (VERB (BDB 405፣ KB 408፣ *Hiphil* INFINITIVE CONSTRUCT) አንድን ነገር በደንብ ወይም ሙሉ ለሙሉ መስራት ማለት ነው፡፡ እዚህ ላይ በተለምዶ አንድ ጥሩ ስራን ለመተግበር የተሰራ ነገርን ለመግለጽ የሚያገለግል ቃል ሊታቀደ መጥፎ ተግባር ውሏል!

▣ ***"አለቃውና ፈራጁ ጉቦን ይፈልጋሉ"*** መሪዎቹ ከትክክለኛ ፍርድ ይልቅ ሽልማቶችን (ማለትም ፤ጉቦ፤ዝ.ከ. 3:11፣ ዘጽ 23:8፣ ዘዳ 10:17፣ 16:19፣ 27:25) እየፈለጉ ነበር፡፡

▣ ***"ትልቁም ሰው እንደ ነፍሱ ምኞት ይናገራል እንዲሁም ክፋትን ይጐነጕናሉ"*** ይህ ቁጥር በሙስና የተዘፈቁትን የህግ እና የፖለቲካ ስርዓቶች ይገልጻል (ዝ.ከ. 3:1-12፣ ኢሳ 59:9-12፣ ኤር 8:8-12፣ 22፣ 23፣ 26:12-15)፡፡ ባለጸጋው ሰው ለዳኞች እና ለመንግስት ባለስልጣናት ምን እንደሚፈልግ ይነግርና እነሱም የፈለጉትን አድርገው የተጠየቁትን የሚያገኙበት መንገድ ያዘጋጃሉ፡፡ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝቦች በሙስና የተዘፈቁ ሆነዋል፡፡ አምሳያቸው እና ተግባሮቻቸው ልክ እንደ ሌሎች የወደቁ ሕዝቦች ሆኗል!

*"መጎንጎን"* (BDB 721፣ KB 783፣ *Piel* IMPERFECT) የተባለው ግስ የሚገኘው እዚህ ላይ ብቻ ነው፡፡ የዚህ ቃል ተዛማች መልኩ በ ኢዮኤል ውስጥ እንደ *"መለየት"* ወይም *"ማግለል"* ሆኖ ተጠቅሷል፡፡ ይህ ቃል የኃጥያትን ሃሳብ ከእግዚአብሔር ደንብ (ማለትም፤ ጽድቅ) እንደ መለየት አድርጎ የሚያሳይ ሳይሆን አይቀርም፡፡

**7:4** ይህ አሽሙር (JPSOA ትርጉም) ይመስላል፤ ነገር ግን ወረራ ለማድረግ የሞከሩበት ሁሉም ዝግጅቶች ያለመሳካቱን ከሚገልጸው ሃሳብ ጋር የሚዛመድ ሊሆን ይችላል (ዝ.ከ. ኢሳ 22:5)፡፡ በቁ 4 ውስጥ የትኩረት ለውጥ ያለ ይመስላል፡፡ የመጀመሪዎቹ ሁለት ጽሑፎች ከቁ 2-3 ውስጥ የተጠቀሰውን ርኩሰት የሚገልጹ ናቸው፡፡ ሆኖም ግን ቀጣዮቹ ሦስት ጽሑፎች (1) ነብዮችን (ተመልካች፤ ዝ.ከ. ኤር 6:17፣ ሕዝ 3:17፣ ሆሴ 9:8) ወይም (2) አይሁዳዊያን ለወረራ ያደረጉትን ዝግጅት ሊያመለክቱ ይችላሉ፡፡

▣ **"ይሸበራሉ"** ይህ ቃል (BDB 100) የእግዚአብሔርን ፍርድ ለመግለጽ የሚያገለግል ነው (ለምሳሌ ኢሳ 22:5)፡፡

**7:5-6** እነዚህ ቁጥሮች (1) በአይሁዳዊያን ማህበረሰብ ውስጥ የነበረውን የሙስና ጥልቀት ወይም (2) በወረራው ምክንያት የመጣውን ጭንቅ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ሁሉም ሰው ለግል ጥቅሙ ቆሞ ነበር (ዝ.ከ. ቁ 2-3፣ ኤር 9:4፣ 12:6)፡፡ እውነተኛ ጓደኝነት አልነበረም (ማለትም ፤ምሳ 17:17፣ 27:6፣9)፡፡
ይህ ቁጥር እንደ ትኩረት ሰጪ እና እንደ አንድ ትኩረት የሚሻ ግስ ሆነው የሚያገለግሉ ሁለት ያልተቋጩ ግሶች አሉት፡፡

1. *"አትመኑ"* - BDB 52፤KB 63፤ *Hiphil* IMPERFECTእንደ ትኩረት ሰጪ ያገለግላል
2. *"አትተማመኑ"* - BDB 105፤KB 120፤ *Qal* IMPERFECT used as a JUSSIVE
3. *"ጠብቅ"* - BDB 1036፤KB 1581፤ *Qal IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ) IMPERATIVES (ትዕዛዝ አንቀፅ)*

**7:6 "ወንድ ልጅ አባቱን ይንቃልና"** ግሱ (BDB 614፤KB 663፤ *Piel* PARTICIPLE "በመናቅ" ፣ "በማዋረድ" ወይም "በማሾፍ" ማለት ነው (ለምሳሌ ዘዳ 32:15፣ ኤር 14:21፣ ናሆ 3:6)፡፡ በተጨማሪም ይህ ዘይቤ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የመጨረሻውን ዘመን በሚያመለክት ስሜት ቀርቧል (ዝ.ከ. ማቴ 10:35-36፣ ማር 13:12፣ ሉቃ 12:53)፡፡ እግዚአብሔር ይህ እንዴት እንደሚጎዳ ያውቀዋል(ዝ.ከ. 2:18)፡፡

## ሚክያስ 7:7-8

**7 እኔ ግን ወደ እግዚአብሔር እመለከታለሁ፥ የመድኃኒቴንም አምላክ ተስፋ አደርጋለሁ አምላኬም ይሰማኛል። 8 ጠላቴ ሆይ፥ ብወድቅ እነሣለሁና፥ በጨለማም ብቀመጥ እግዚአብሔር ብርሃን ይሆንልኛልና በእኔ ላይ ደስ አይበልሽ።**

**7:7 "እኔ ግን ወደ እግዚአብሔር እመለከታለሁ"** በቁ 7 እና በቁ 1-6 ያለውን ጠንካራ የተቃርኖ ንጽጽርን ያስተውሉ፡፡ ግሱ
(BDB 859፤ KB 1044፤ *Piel* IMPERFECT) በ COHORTATIVE ስሜት የቀረበ ነው፡፡በእግዚአብሔር ስራ ላይ በትግስት መተማመን የእምነት ማስረጃ ነው (ለምሳሌ መዝ 38:15፣ 39:7፣ 42:5፣ 130:5፣ ኢሳ 8:17፣ ሰቆ 3:25)፡፡

▣ **"የመድኃኒቴንም አምላክ ተስፋ አደርጋለሁ"** በእምነት/ነጻነት ውስጥ በግለሰብ ደረጃ የተቀመጠውን አካል ያስተውሉ፡፡ግሱ (BDB 403፤KB 407) *Hiphil* COHORTATIVE ነው፡፡ እነዚህ ሁለት(ሦስት) ግጥማዊ ጽሑፎች ትይዩ ሲሆኑ ጽኑ ፣ ታማኝ የሆነውን የያህዌን ተከታይ ይገልጻሉ፡፡

▣ **"አምላኬም ይሰማኛል"** ሚክያስ የኃጥያተኞቹን እስራኤላዊያንን ወይም የአይሁዳዊያንን ጸሎት ያህዌ እንደማይሰማ እና ምላሽም እንደማይሰጥ (ለምሳሌ 3:4) ፤ ነገር ግን ያህዌ ቃል ኪዳኑን በእምነት ለሚጠብቁ በእርግጠኝነት ጸሎታቸውን እንደሚሰማ እና እንደሚመልስ (ዝ.ከ. 6:8) ቀደም ብሎ አሳውቋል፡፡

**7:8-13 "ትርጉም ሰጪ ጥያቄ የሚሆነው"** ቁ 7 ከ ቁ 8 ጋር አብሮ የሚሄድ ነው ወይስ አዲስ የግጥም ምት የሚጀምር ነው?" አብዛኞቹ የእንግሊዝ ትርጓሜዎች ቁ 8 ላይ አዲስ ሃሳብ ይጀምራሉ (NKJV፣ NRSV፣ TEV፣ NJB፣ ነገር ግን NASB) ከቁ 8-10 ያሉት ከ11-13 ካሉት ጋር መለያየት የሚኖርባቸው ሳይመስሉ አይቀርም፤ምክንያቱም የመጨረሻዎቹ ሁለት ቁጥሮች ያህዌ በወደፊቱ መታደስ እና አለም አቀፍ ተጽዕኖ ላይ ያለውን ፈቃድ ያንጸባርቃሉ፡፡

**7:8 "በእኔ ላይ ደስ አይበልሽ"** ግሱ (BDB 403፤KB 407) *Hiphpael* COHORTATIVE ነው፡፡

▣ **"ጠላቴ ሆይ"** እዚህ ላይ ያለው ጠላት ወራሪው ሕዝብ ሊሆን ይችላል ፤ ነገር ግን እውነታው ጠላት የነበረው የቃል ኪዳኑ ሕዝብ (የሁሉም ሕዝብ) ኃጥያታዊ ተፈጥሮ ነበር፡፡ ይህ በመዝ 19:12-13 ውስጥ ያለውን ጸሎት ያስታውሰኛል፡፡

▣ **"ብወድቅ እነሣለሁና"** ግሱ (BDB 877፤KB 1086) *Qal* PERFECT ነው፡፡ ይህ የአንድ ግለሰብን መታደስ ወይም የማህበረሰብን ከምርኮ መመለስ ሊያመለክት ይችላል (የሚሆነው እንዲያሻማ የሆነ፤ዝ.ከ. 4:13)፡፡

▣ **"በጨለማም ብቀመጥ"** ግሱ (BDB 442፤KB 444፤*Qal*IMPERFECT) *"መቀመጥ"* ወይም *"መስፈን"* ማለት ነው፡፡ በብሉ ኪዳን ውስጥ ጨለማ ባብዛኛው እንደ *"ብርሃን"* ተቃራኒ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ይህ ቃል የመጨረሻውን ዘመን ሁኔታ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል (ለምሳሌ ኢሳ 9:1፣ 29:18)፡፡ ጸሐፊው በማህበረሰቡ ኃጥያት እና በሚመመጣው ፍርድ ምክንያት ከያህዌ ጋር የነበረው ግንኙነት እንደሚቋረጥ ይሰማዋል፡፡ የፍርድ አስከፊው ጎኑ የእግዚአብሔር መገኘት አለመኖሩ ነው!

▣ **"እግዚአብሔር ብርሃን ይሆንልኛልና"** ይህ ለሚከተሉት ነገሮች መጽሐፍ ቅዱሳዊ አፍራሽ ዘይቤን አመልካች ነው፤ (1) እውነት ከ ሐሰት ፣ (2) ፈውስ እና ጤና ከ ከመበስበስ እና ሙስና ፣ (3) ግብረገባዊ መልካምነት ከ ክፋት ፣ ወይም (4) ደስታ ከ ትካዜ፡፡
ይህ ቁጥር ይህን ብርሃን እንደ እግዚአብሔር አስመስሎ እየገለጸ እንደሆነ ያስተውሉ (ዝ.ከ. መዝ 27:1፣ ኢሳ 60:20፣ 1ኛጢሞ 6:16፣ 1ኛዮሐ 1:5)፡፡ እሱን ማወቅ ፣ እሱን መታዘዝ ፣ እሱን ማገልገል አማኞች ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖራቸውን የግል ግንኙነት ይገነባል (ማለትም ፤እግዚአብሔርን በተመሳሳይ ሁኔታ መምሰል በዮሐ 14:6 ውስጥ)፡፡
በኢሳ 9:2 ውስጥ ሰዎች ታላቅ ብርሃን ያያሉ ይህም ብርሃን በነሱ ላይ ያበራል፡፡ ይህ መለኮታዊ ብርሃን ኢየሱስ ነው (ዝ.ከ. ዮሐ 8:12፣12:35-36፣46)፡፡ ቀጥር 8 በጭንቅ ጊዜ እግዚአብሔር በታማኝነት መገኘቱን የሚጠቅስ ሲሆን ቁጥር 9 ደግሞ አካለዊ የግል ግንኙነት የሚደረግበት የወደፊት ቀን እንደሚኖር ቃል ይገባል፡፡

## ሚክያስ፡ 7:9-13

**9 በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ሥርቻለሁና እስኪምዋገትልኝ ድረስ፥ ፍርድን ለእኔ እስኪያደርግ ድረስ ቍጣውን እታገሣለሁ።**
**ወደ ብርሃን ያወጣኛል፥ ጽድቅንም አያለሁ።**
**10 ጠላቴም ታያለች፥ እኔንም። አምላክህ እግዚአብሔር ወዴት ነው? ያለች በእፍረት ትከደናለች።**
**11 ዓይኖቼ ይመለከቱአታል አሁን እንደ መንገድ ጭቃ ትረገጣለች። ቅጥርሽ በሚሠራበት በዚያ ቀን ድንበርሽ ትስፋፋለች።**
**12 በዚያ ቀን ከአሦርና ከግብጽ ከተሞች፥ ከግብጽ እስከ ወንዙ፥ ከባሕርም እስከ ባሕር፥ ከተራራም እስከ ተራራ ድረስ ወደ አንቺ ይመጣሉ። 13**
**ምድሪቱ ግን በሚኖሩባት በሥራቸው ፍሬ ምክንያት ባድማ ትሆናለች።**

**13ምድሪቱ ግን በሚኖሩባት በሥራቸው ፍሬ ምክንያት ባድማ ትሆናለች።**

**7:9 "በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ሠርቻለሁና"** ሚክያስ (ልክ እንደ ሙሴ ፣ ኢሳያስ እና ዳንኤል) የሚከውነው እንደ ሕዝቡ ተወካይ ሆኖ ነው፡፡ በግል እንዲሁም ደግሞ በማሕበረሰብ ለሚደርስ ጥፋት በቀጥታ በእግዚአብሔር ላይ በግል እና በማህበረሰብ ከምናደርገው አመጽ ጋር የተያያዘ ነው (ዝ.ከ. ዘዳግም 27-28)! ብዙዎቹ የአይሁድ ጻድቆች በአመጸኛ ህብረተሳባቸው ምክንያት ተጎጂ ይሆናሉ፡፡
እንደ ገና በ"እኔ" (NASB) እና በ"እኛ" (TEV) መካከል ተለዋዋጭነት አለ፡፡ይህ ነብይ የህብረተቡን ኃጥያት አምኖ እየተቀበለ ነው (ዝ.ከ. ኢሳ 6)፡፡ ችግሩ ኃጥያት ነው ፤ ውጤቱ ምርኮ ነበር ፤ ነገር ግን መታደስ እርግጥ የሆነው የእግዚአብሔር ተስፋ እና ቃል ኪዳን ነው፡፡

▣ **"እስኪምዋገትልኝ ድረስ"** በተጨማሪም ይህ የህግ አሰጣጥ ዘይቤ በ6:1-5 ውስጥ ይገኛል፡፡ በተለያዩ ምንባቦች ውስጥ እግዚአብሔር እንደ ከሳሽ (ለምሳሌ 6:2) ፣ እንደ ጠበቃ (7:9) እንደ ዳኛ ሆኖ ይከውናል፡፡

▣ ***"ወደ ብርሃን ያወጣኛል"*** ይህ በቁ 8 ጽሑፍ 3 ውስጥ እንዳለው እግዚአብሔርን እንደ ብርሃን የሚገልጽ አቀራረብ አለው፡፡በዚህ አውድ መስረት "ማየት" ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል (ዝ.ከ. 9 ጽሁፍ5፤10 ጽሁፍ 3፤16 ጽሁፍ1፤ዝ.ከ. መዝ 17:15፣ማቴ 5:8፣ እብ 12:14፣ 1ኛዮሐ 3:2፣ ራዕ 22:4)፡፡

▣ ***"ጽድቅንም አያለሁ"*** ጻድቅ ፈራጅ የሆነው የእግዚአብሔር ባህሪ በፍርድ አሰጣጡ ውስጥ ይታያል፡፡በተጨማሪም የምህረት አባት የሆነው ባህሪው ደግሞ በምህረቱ እና በመታደሱ ውስጥ የሚታይ ነው (ማለትም፤ በሞገስ እና በእምነት አሳማኝ ፍርድ አሰጣጡ)፡፡ ለተቀሩት ታማኞች እና ለሰው ዘር የተስፋ ቃሎቹን መልካም ያደርጋል! ይህ በኢዮብ 19:25-27 ወስጥ ካለው የኢዮብ አረፍተነገር ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ጽድቅ የሚለውን ልዩ ርዕስ በሆሴዕ 2፡19 ላይ ይመልከቱ፡፡
**7:10 "ጠላቴም** *ታያለች*" ግሱ (BDB 906፤KB 1157) በመልክ JUSSIVEሲሆን በትርጉም ግን IMPERFECT ነው፡፡

▣ ***"አምላክህ እግዚአብሔር ወዴት ነው"*** የጥንት ጦርነቶች በሙሉ የአገሩን ጣዖታት በጦርነቱ ውስት ያካተቱ ነበር፡፡ አይሁዶች እነሱ ላይ ለፍርድ በተነሱት "ሕዝቦች" በኩል ሆኖ ያህዌ የሚያደርገውን እርዳታ በሚመለከት በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርታቸው ግራ ተጋብተዋል (ዝ.ከ. ዕምባቆም)፡፡ ያህዌ አመጸኛ ሕዝቡን ወደ ራሱ መልሶ ለማምጣት አምላክ የለሽ እኩይ የሆኑ ሕዝቦችን ተጠቅሟል፡፡ አሁንም ቢሆን እነዚያን የተጠቀመባቸውን ሕዝቦችንም ይዳኛቸዋል (ማለትም ፤አሦሪያ፣ ባቢሎን)፡፡ በመጀመሪያ አይሁዶች የእነዚህ እግዚአብሔርን የማያውቁ ሕዝቦች አማልክት ከያህዌ የበለጠ ኃይል እንዳላቸው ያስቡ ነበር ፤ ነገር ግን አውነቱ መጨረሻውን ያበላሸው ኃጥያታቸው (ዝ.ከ. ቁ 9) እንጂ የእግዚአብሔር አቅም ማነስ አልነበረም፡፡ ያህዌ በተጨማሪ ወራሪ ሕዝቦቹ ላይ በመፍረድ ስሙን (ዝ.ከ. ሕዝ 36:22-38) ያስከብራል (ዝ.ከ. ቁ 13)፡፡

▣ ***"እንደ መንገድ ጭቃ ትረገጣለች"* ስሪት** የሆነው "የአደባባይ ጭቃ" (BDB 376 እና 299) ልክ በቁ 17 ላይ "መሬት ይልሳሉ" (ዝ.ከ. ኢሳ 49:23) እንደሚለው ባብዛኛው ሽንፈትን ለመግለጽ የሚያገለግል ዘይቤ ነው(ለምሳሌ 2ኛሳሙ 22:43፣ መዝ 18:42፣ ዘካ 10:5)፡፡

**7:11** ይህ ቁጥር የኢየሩሳሌምን ከተማ የሚያመለክት ይመስላል ፤ ሆኖም ግን "ቅጥርሽ በሚሰራበት" (BDB 124 እና 154 ስሪት) የሚለው ሃረግ አብዛኛውን ጊዜ እንደ ከተማ ቅጥር(ዝ.ከ. አሞፅ 9:11) ሆኖ ሳይሆን የሚያገለግለው እንደ ድንበር አመላካች (ለምሳሌ ኢሳ 54:11) ሆኖ ነው፡፡ ስለዚህ ድንበርሽ የሚለው ምናልባትም የእግዚአብሔርን ሕዝብ በሙሉ የሚገልጽ ዘይቤ ሊሆን ይችላል፡፡ "ቅጥርሽ" የሚለው የከተማውን ጥበቃ አመልካች ነበር፡፡ ያህዌ በማንነቱ የሕዝቡን መሬት እና ማንነት ይመልሳል፡፡

**7:12 "ወደ አንቺ ይመጣሉ"** ይህ ቁጥር እንዴት መተርጎም እንዳለበት የሚተነትኑ ሶስት ዋና ሃሳቦች ሲታዩ ቆይቷል፤ (1)አይሁዶች ከምርኮ ወደ አገራቸው እየተመለሱ ነው (2) ሁሉም ሕዝቦች ወደ ቀድሞ ሁኔታው ለተመለሰው ለእግዚአብሔር ሕዝብ ግብርን ይዘው እያመጡ ነው እና (3) የእስራኤልን ሃሳባዊ ድንበር፡፡

**7:13 "በሥራቸው ፍሬ ምክንያት"** ከሕዝቡ ኃጥያቶች የተነሳ ከተስፋይቷ ምድር ውጪ ፍርድ እና ከፍተኛ ጥፋት ይመጣል (በእስራኤል ኃጥያት ምክንያት በከነዓን ውስጥ እንደነበረው ኃጥያት፤ዝ.ከ. ቁ 9):: ኃጥያት መዘዞች አሉት (ዝ.ከ. ሮሜ 8:19-22)::

## ሚከያስ፡7:14-20

**14 በቀርሜሎስ መካከል ባለው ዱር ብቻቸውን የተቀመጡት ሰዎችህ፥ የርስትህን በጎች፥ በበትርህ አግድ**
**እንደ ቀደመውም ዘመን በበሳንና በገለዓድ ይሰማሩ።**
**15 ከግብጽ ምድር እንደ ወጣህበት ዘመን ተአምራትን አሳያቸዋለሁ።**
**16 አሕዛብ አይተው በጕልበታቸው ሁሉ ያፍራሉ እጃቸውን በአፋቸው ላይ ያኖራሉ፥ ጆሮአቸውም ትደነቍራለች**
**17 እንደ እባብም መሬት ይልሳሉ፥ እንደ ምድርም ተንቀሳቃሾች እየተንቀጠቀጡ ከግንባቸው ይመጣሉ ፈርተውም ወደ አምላካችን ወደ እግዚአብሔር ይመጣሉ፥ ስለ አንተም ይፈራሉ።**
**18 በደልን ይቅር የሚል፥ የርስቱንም ቅሬታ ዓመፅ የሚያሳልፍ እንደ አንተ ያለ አምላክ ማን ነው?**
**ምሕረትን ይወድዳልና ቍጣውን ለዘላለም አይጠብቅም።**
**19 ተመልሶ ይምረናል ከፋታችንንም ይጠቀጥቃል፥ ኃጢአታችንንም በባሕሩ ጥልቅ ይጥለዋል።**
**20 ከቀድሞ ዘመን ጀምረህ ለአባቶቻችን የማልህላቸውን እውነት ለያዕቆብ፥ ምሕረትንም ለአብርሃም ታደርጋለህ።**

**7:14 "የርስትህን በጎች፥ በበትርህ"** ግሱ (BDB 944 I፤KB 1258) QalIMPERFECT ነው::ይህ የመጽሐፉ የመጨረሻ ንዑስ ክፍል ወደ ቃል ኪዳኑ እግዚአብሔር የተጸለየ ጸሎት ነው::የቁ 7ቱ ተስፋ ሰፍቷል! ይህ የእረኝነት እና የንጉሳዊነት ህብር ዘይቤ ነው (ዝ.ከ. መዝ 23 በተጨማሪም ኢሳ 40:11፣ ሚክ 2:12፣ 4:6-7፣ 5:4፣ ዘካ 9:16):: እግዚአብሔር እረኛም ንጉስም ነው:: "በትር" (BDB 986) የሚለው ቃል የንጉሶችን በትር ወይም የእረኛን ዱላ ሊያመለክት ይችላል::

▣

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"ብቻቸውን የተቀመጡት"** |
| **NKJV** | **"ብቻውን የሚኖር"** |
| **NRSV** | **"ብቻቸውን የሚኖሩ"** |
| **TEV** | **"እንዲሁም ተለይተው የሚኖሩ"** |
| **NJB** | **"ተወስነው የሚኖሩ"** |

ይህ ለሚከተሉት ዘይቤ ነው፤

1. የመለየት NJB
2. የህብረት NKJV
3. የብዙህነት
4. የንጽሁነት

▣

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"ፍሬያማ ምድር"** |
| **NKJV** | **"ቀርሜሎስ"** |
| **NRSV** | **"የአትክልት መሬት"** |
| **TEV** | **"ለምለም ግጦሽ"** |
| **NJB** | **"መስከ መሬት"** |

ይህ ቃል (BDB 502) ሊያመለክት የሚችለው (1) ጥሩ የግጦሽ መሬት (ማለትም፤ ከበሳን እና ከገለዓድ ጋር ትይዩ የሚሆን)፣ (2) ጫካ (ለምሳሌ ኢሳ 10:18፣ 29:17፣ 32: 15)፣ ወይም (3) በሰባ ሊቃናት ትርጉም ፣ ፒሽታ እና ቩልጌት ትርጓሜ ውስጥ የተገለጸውን የቀርሜሎስ ተራራን (በለምነቱ የታወቀው) ነው::

▣ **"ይሰማሩ"** ይህ ግስ (BDB 944 I፤KB 1258፤*Qal***IMPERFECT** ነገር ግን በትርጉም **ትኩረት ሰጪ** የሆነ) ከ"እረኛ" (ቁ 1 ጽሑፍ 1) ጋር አንድ አይነት መሰረት ያለው ነው:: የቁ 14 እቅድ ዋንኛ ስሜት ሕዝቦቹ ተጨቁነው እንደነበር ነገር ግን ልክ ያኔ ዘፀዓት ወስጥ በያህዌ ኃይል ነጻ አንደወጡ ሁሉ አሁንም ነጻ ወጥተዋል!

▣ **"በበሳንና በገለዓድ"** ይህ በሰሜን ዮርዳኖስ አቅጣጫ የሚገኝ ለምለም አካባቢ ሲሆን በልምላሜውና በምርታማነቱ የሚታወቅ መሬት ነበር::

▣ **"እንደ ቀደመውም ዘመን"** የቃል ኪዳን መታደስን የሚያመለክት ተምሳሌታዊ ንግግር ነው (ዝ.ከ. ኢሳ 63:11፣ አሞፅ 9:11):: የሚያመለክተውም በዘፀዓት የነበረውን የመጀመሪያ ትውልድ ሕዝብን ነው::

**7:15** እግዚአብሔር በእነሱ ፊንታ ሆኖ የሱን ታሪካዊ ድርጊት ተግባር አሳያቸው (ዝ.ከ. ነህ 9:9-14 [ዘፀዓት]፣ 15-21 [የበረሃው መንከራት]፣ 22-25 [የከነዓን ድል]):: የፍርድ ወቅትም በነበረው በበረሃው የመንከራተት ጊዜ (ዝ.ከ. ዘፀዓት- ዘኍልቁ) አስደናቂ የሆነውን ተስፋ እንዲያታውሱ አጥብቆ ያሳስባቸዋል::

**7:16** የእግዚአብሔርን ሕዝብ ሲያስጨንቁ የነበሩ ሕዝቦች አፍረው ተቀምጠው ነበር (ማለትም፤ "እጆቻቸውን በአፋቸው ላይ ጫኑ" ለምሳሌ መሳ 18:19፣ ኢዮ 21:5፣ 29:9፣ 40:4):: ይህ ደግሞ እንደገና ይፈጸማል ፤ ምክንያቱም የተለወጠው የቃል ኪዳን ሕዝቡ በእሱ ኃይል እና መገኘት ውስጥ ስለሚንቀሳቀሱ ነው (ዝ.ከ. መዝሙር 2)::

**7:17-18** የቲንዳል ትንተና ጥራዝ 23 ሀ በቀይ ባህር ላይ በነበረው የእግዚአብሔር ተዓምር (በሙሴ መዝሙር ውስጥ የተገለጸው) እና በሚክያስ የድል ምስጋና (ገፅ 203) መካከል ማራኪ ንጽጽር አለው፡፡

1. *"መንቀጥቀጥ"*(BDB 919)፤ዘጽ 15:14 እና ሚክያስ 7:17
2. *"እንደ ድንጋይ መሆን"* (BDB 808)፤ዘጽ 15:16 እና ሚክያስ 7:17
3. በፍርሃት ምክንያት የመጣ ያለመነቃነቅ ዘጽ 15:16 እና ሚክያስ 7:16 (የተለየ ቃል)
4. የእግዚአብሐር ኃይለኛ ተግባሮች ዘጽ 15:11 እና ሚክያስ 7:15 (የተለየ ቃል)
5. እስራኤል እንደ እግዚአብሔር ርስት (BDB 635) ዘጽ 15:17 እና ሚክያስ 7:14፣18
6. ተመሳሳይ የሽንገላ ጥያቄ ዘጽ 15:11፤"እንደ አንተ ያለ ማን ነው" እና ሚክያስ 7:18፤"እንደ አንተ ያለ አምላክ ማን ነው"
7. ጠላቶችን ወደ ባህር የሚጥል ዘጽ 15:1፣4-5 እና ሚክያስ 7:19

ብሩስ ዋልቴክ ሲያክል "የሙሴ ዝማሬ የእግዚአብሔርን ድል ወደ ኋላ ተመልሶ ያስታውሳል ፤የሚክያስ ዝማሬ ወደ ፊት በእምነት ስለሚሆነው ታላቅ ነገር ላይ ያመለክታል" (ገፅ 203)፡፡

**7:17 "እንደ እባብም መሬት ይልሳሉ፥ እንደ ምድርም ተንቀሳቃሾች"** ሁለት አማራጮች አሉ (1) የአሸናፊውን እግር መሳም (ዝ.ከ. መዝ 72:9፣ ኢሳ 49:23) ወይም (2) ያልነጹ እንስሳዎች (ዝ.ከ. ዘፍ 3:14፣ ዘሌ 11)፡፡ ይህ ለጦርነት ሽንፈት የሚውል የእብራዊያን ፈሊጣዊ ንግግር ነበር፡፡ ዋናው ጥያቄ ይህ ቁጥር (1) በያህዌ ኃይል እና ለእስራኤል ባለው ፍቅር የተነሳ የሕዝቡን ፍራቻ ያስቀመጠ ነው ወይስ (2) የሕዝቡን መለወጥ የሚገልጽ ነው፡፡ በዓውዱ መሰረት ከታየ ቁጥር 1 ምርጥ አማራጭ ነው ነገር ግን በ አዲስ ኪዳን ዕይታ ከታየ ቁጥር 2 ምርጥ አማራጭ ነው፡፡ እባኮዎን እዚሁ ላይ እያሉ የቦብን የወንጌል አድልዎ በሚክያስ 5:7-9 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

**7:18 "እንደ አንተ ያለ አምላክ ማን ነው"** ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ታላቅነት እና በነብዩ ስም የታወጀ ፤ ይሄውም "እንደ ያህዌ ያለ ማን አለ" የሚል ትርጉም ያለውን ነው (ዝ.ከ. ዘጽ 34:6-7፣ ዘዳ 7:9፣ ነህ 9:17፣ መዝ 103:8-10፣ ኢዩ 2:13)፡፡

▣ **"ይቅር የሚል"** ይህ የእብራዊያን የተለመደ ግስ BDB 669፤KB 724፤*Qal*ቦዝ አንቀጽ) የ(1) ከፍ ከፍ ማለት (ለምሳሌ 4:1)፣ (2) መሸከም (ለምሳሌ 6:16፣ 7:9)፣ (3) መውሰድ (ለምሳሌ 2:2)፣ እና (4) ይቅር ማለት (ለምሳሌ ሆሴ 1:6፣ 14:2) ቅዱሳዊ አጻጻፍ አለው፡፡ በቁ 18 ውስጥ የእግዚአብሔርን መልካምነት እና ይቅርባይነትን የሚገልጹ ተከታታይ ሃረጎች አሉ(ዝ.ከ. መዝ 103:12፣ ኢሳ 1:18፣ 38:17፣ 43:25፣ 44:22)፡፡እግዚአብሔር ይቅር ሲል ፤ ይቅር የተባለውን ኃጥያት መልሶ አያስብም!

አቻ ግሱ "ማለፍ" (BDB 716፤KB 778፤*Qal*ቦዝ አንቀጽ) ሲሆን በ"መርሳት"(ማለትም ፤ከአይን መረቅ፤ከአዕምሮ መራቅ ዝ.ከ. ቁ 19) ስሜት ሲታይ "መውጣት" ፤ "በመካከል ማለፍ "(ለምሳሌ 2:13፣ አሞፅ 5:17) ማለት ነው፡፡

ይህ ተመሳሳይ ግስ በአሞፅ 7፡8 እና 8፡2 በፍርድ ዓይነት ስሜት ተጠቅሷል፡፡ የይቅርታ ስሜት ያለው እዚህ ውስጥ እና በምሳሌ 19፡22 ወስጥ ብቻ ነው፡፡

▣ በ *አብድዩ እና በሚክያስ መጽሐፎች ላይ* የተመቅህ የተርጓሚዎች የመመምሪያ መጽሐፍ ከቁ 18-19 ባለው ውስጥ ለኃጥያት የሚሆኑ ብዙ የእብራዊያን ቃላት እንደተጠቀሱ ይገልጻል፤

1. ነውር (BDB 730፤ማለትም ፤ዘወር ማለት)
2. አመጸኝነት (BDB 833፤ማለትም ፤ማመጽ)
3. ኃጥያቶች (BDB 308፤ማለትም ፤ነጥቡን በመሳት)

ዋናው ነገር ሁሉም የቃልኪዳን ሕዝቡ የቃልኪዳን መተላላፋቸው ይቅር ተብሏል (ገፅ 191)፡፡

▣ **"ቅሬታ"** ይህ በተዳዳጋሚ የሚገለጽ መልዕክት ነው (ዝ.ከ. 2:12፣ 4:7፣ 5:7፣8)፡፡

▣ **"ቊጣውን ለዘላለም አይጠብቅም"** ግሱ (BDB 304፤KB 302፤ *ሂፊል* PERFECT) "ላለመልቀቅ መያዝ" (ዝ.ከ. ዘጽ 9:2) ማለት ነው፡ይህም ሰውኛ ሃረግ ሲሆን የሚገልጸውም እግዚአብሔር ልጆቹን እንደሚቀጣ ወላጅ እንደሆነ ነገር ግን ፈጽሞ አይተዋቸውም፤ ከዚህም ባሻገር የነበረው ህብረት እንዲመለስ አጥብቆ ይሻል (ዝ.ከ. መዝ 103:8)፡፡

በደልን ይቅር የሚል፥ የርስቱንም ቅሬታ ዓመፅ የሚያሳልፍ እንደ አንተ ያለ አምላክ ማን ነው? ምሕረትን ይወድዳልና ቊጣውን ለዘላለም አይጠብቅም።

**7:18**

| | |
|---|---|
| **NASB** | **"በማይለወጥ ፍቅር ይወዳልና"** |
| **NKJV** | **"ምሕረትን ይወድዳልና"** |
| **NRSV** | **"ምህረት ማሳየት ይወዳልና"** |
| **TEV** | **"የማይለወጥ ፍቅርህን በማሳየት ደስ ይልሃልና"** |
| **NJB** | **"ታማኝ ፍቅር ማሳየት ይወዳልና"** |

ግሱ (BDB 342፤KB 339፤*Qal*PERFECT) በተጨማሪ በ ኤር 9:24 እና ሆሴዕ 6:6 ውስጥ ተጠቅሷል፡፡እግዚአብሔር በዚህ ነገር "ደስተኛ" መሆኑን (እና አለመሆኑን ፤ዝ.ከ. ሕዝ 18:23፣32፣ 33:11)ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡

"ምህረት" የሚለው ቃል (BDB 338 I) *ሔሴድ* ነው፤ ይህም በተጨማሪ በ6:8፤ 7:18፣20፤ ሆሴዕ 2:19፤ 4:1፤
6:4፣6፤ 10:12፤ 12:6፤ እና ዮናስ2:8፤ 4:2 ውስጥ ይገኛል፡፡ይህ እንደገና የእብራዊያን የቃል ኪዳን ቃል የሆነው *ሔሴድ* ነው፡፡ ትርጉሙም የማይለዋወጥ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታማኝነት ማለት ነው፡፡በሆሴዕ 2:19 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡፡

ተመልሶ ይምረናል ከፋታችንንም ይጠቀጥቃል፥ ኃጢአታችንንም በባሕሩ ጥልቅ ይጥለዋል።

**7:19** ይህ ከይቅርታ በኋላ ለሚሆን መርሳት ተከታታይ ዘይቤ ነው፡፡እግዚአብሔር ይቅር ሲል በደልን ይረሳል (ዝ.ከ. ኢሳ 1:18፤ 38:17፤ 43:25፤ 44:22፤ መዝ 103:8-14)፡፡ ከአይን የራቀ ከልብ ይርቃል! ምን አይነት ታላቅ የተስፋ ቃል ነው፡፡ ብዙ አማኞች የእግዚአብሔርን ምህረት በህይወታቸው ተለማምደዋል ነገር ግን በደልንም እንደሚረሳ በጭራሽ አያስተውሉም!

**NASB፤NRSV** **"ከፋታችንንም ይጠቀጥቃል"**
**NKJV** **"ከፋታችንንም በቁጥጥር ስር ያደርጋል"**
**TEV** **"ኃጥያታችንንም እግር ስር ይረጋግጥልናል"**
**NJB** **"ጥፋታችንን ይጥላል"**

ይህ ግስ (BDB 461፤KB 460፤*Qal**IMPERFECT***) በዋናነት "*ማስገዛት*"(ለምሳሌ ዘፍ 1:25) ወይም "*እንዲገዙ ማድረግ*" (ለምሳሌ ኤር 34:11፣16፣ ነህ 5:5) ማለት ነው፡፡ እዚህ ላይ የአማኞች ኃጥያት መሰረዙን እና መሸነፉን በምሳሌ የመግለጽ ጥቅም አለው፡፡

**7:20 "እውነት ምሕረትንም"** ሁለቱ የያህዌ ባህሪያት በሕዝቦቹ ላይ መልሰው መንጸባረቅ የሚገባቸው ናቸው፡፡ "እውነት" (BDB 54) በብሉ ኪዳን ላይ የሚያመለክተው *ሃቀኝነትን* ወይም *ታማኝነትን* (በዮናስ3:5 ላይ ልዩ ርዕስ ይመልከቱ) ነው፡፡ ሁለተኛው *ሔሴድ* (BDB 338 I) ወይም ለቃል ኪዳኑ *መታመን* (በሆሴዕ 2:19 ላይ ልዩ ርዕስ ይመልከቱ) ነው፡፡እግዚአብሔር ጻድቅ የሆኑ ሰዎችን *ያፈራል*(ማለትም ፤በብሉ ኪዳን ውስጥ እንዳለው በብቃት ፤ዝ.ከ. ኤር 31:31-34 ሳይሆን አዲስ ኪዳን ውስጥ እንዳለው በእሱ ምህረት እና ጸጋ ዝ.ከ. ሕዝ 36:22-38)፡፡

▣ **"ለያዕቆብ ለአብርሃም ለአባቶቻችን"** በእግዚአብሔር እና በሕዝቡ መካከል በተስፋ ቃሉ ለየት ያለ እና በግዴታዎቹም ለየት ያለ ግንኙነት ነበር፡፡ የዮናስ መጽሐፍን ጨምሮ ከቁጥር18-20 ያለው በማስተሰሪያ ቀን ላይ በአይሁድ ቤተመቅደስ ውስጥ ይነበቡ ነበር፡፡ በአዲስ አመት ቀን ከሰዓት ላይ ዋና አይሁዶች ውሃ ወደ ሚፈስ ቦታ ይሄዱና ከቁ18-20 ያለውን በማነብነብ ኪሶቻቸውን ባዶ ያደርጉ ነበር፡፡ ይሄም*ታሽሊች* ወይም "ይጥለዋል" ይባላል፡፡ አጽንዖት የሚያደርገው የቃልኪዳን ሃላፊነት (ማለትም፤ ኃጥያትን በሙሉ ማስወገድ) ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ምህረት ጭምር ነው!

በዚህ መደምደሚያ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርታዊው ነጥብ የሚያጤነው የእግዚአብሔርን ቸርነት ሳይሆን ነገር ግን በክርስቶስ በኩል የተደረገውን አስደንጋጭ ቃል ኪዳን ጭምር ነው (ዝ.ከ. ዮሐ 14:6)፡፡ እስስራኤል የዳነው በቃል ኪዳኑ ታዛዥነት ነው ወይስ በይሁዳ መታደስ? ትክክለኛው ነጥብ ግን የኢየሱስ አዲስ መልእክት እውነት መሆኑ ነው(ዝ.ከ. ሮሜ 2:28-29፣9-11፣ገላ 3፣ 6:16)

**የውይይት ጥያቄዎች**

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ይህ ምዕራፍ የተጻፋው ለግለሰብ ነው ወይስ በህብረት ውስጥ ላሉ ማህበረሰቦች?
2. *ሔሴድ* የሚባለውን የእብራዊያን ቃል ግለጽ፡፡
3. በቁ 7 እና 8 እንዲሁም ከቁ 1-6 ባሉት መካከል ያለውን ንጽጽር ግለጽ፡፡
4. ለምንድን ነው በእግዚአብሔር ሕዝብ ሁኔታ ውስጥ ሲታይ የቁ 10 ጥያቄ አስፈላጊ የሆነው?
5. በቁ 18 እና 19 ውስጥ የእግዚአብሔርን ሩሩህ ባህሪያት ዘርዝር፡፡

# ተጨመሪ መግለጫ   አንድ

## የባቢሎናዊያን የፋርስና የግሪክ ነገስታት ስርወ-መንግስት እና ክስተቶች

612 አክልበ አክልበ    ነኔዌ በአዲሱ የባቢሎን ሠራዊት እጂ ወደቀች (ናቡከደነፆር)
608    ፈርዖን ኒካው ዳግማዊ የአዲሱን የባቢሎን መንግስት ግዛት ለማስፋፋት ወደ ከርከሚሽ ዘመተ
የይሁዳ ንጉስ ዮስያስ ሊያስቆመው ሞከር]
የዮስያስ መሞት እና ልጁ ኢዮአሃዝ ወደ ዙፋን ለመውጣት ማሰብ
ኢዮአቄም የዮስያስ ሌላው ልጅ በፈርዖን ኒካው ዳግማዊ ትእዛዝ መሰረት በ 3 ወራት ውስጥ ኢዮአሃዝን ተካው
ፍልስጥኤምና ሦሪያ በግብፅ ግዛት ስር
የዮስያስ ተሃድሶ ተቋረጠ
605    ናቡፐላዝሻር የቀሩትን አሦራዊያንን እና ግብፃዊያንን ለመውጋት ጦርን ወደ ከርካሚሽ ይሰዳል
ናቡከደነፆር በፓላስታይን ሜዳ ጎዳና ላይ ሁላቸውንም አሳደዳቸው
ናቡከደነፆር ያባቱን (ናቡፐላዝሻርን) ሞት ሰምቶ ዘውድ ለመጫን ወደ ባቢሎን ተመለሰ
ወደዚያ ሲመለስም ከምረኮኞቹ ውስጥ ዳንኤልንና ከንጉሳን ቤተሰብ ሌሎችን ይዞ ተመለሰ

605 - 538    ባቢሎን በ597 የፓልስታየንን ምድር ተቆጣጠር ፤10፣000 ምረኮኞችን ወደ ባቢሎን አፈለሰ
586    ኢሩሳሌም እና ቤተመቅደስ ፈረሰ ብዙ ምረኮም ተወስዶ ፈለሰ
582    የአይሁድ የደፈጣ ተዋጊዎች ጎዶሊያስን ገደሉ እንደገና ተጨማሪ ብዙ ሰዎች ተማርከው ሄዱ

### ናቡከደነፆርን የተኩ

562 - 560    ሜሮዳክ ክፉው ኢዮአቄምን ከግዞት ለቀቀው (ትክክለኛው የመሲሁን መስመር)
560 - 556    ኔሪግላሳር
556    ላባስኪ ማርዱክ ነገሰ
556 - 539    ናቦኒዳስ፡
ብዙጊዜውን ለሙድ (mood) አምላክ፣ ሲን መቅደስ በመገንባት አሳለፈ፡፡ በዚህም ከ ማረዱክ ካህናት ዘንድ ጥላቻን አተረፈ፡፡
ብዙጊዜውን የሳለፈው የሚነሱትን ተቃዋሚዎችን በማብረድ እና መንግሰቱን በማረጋጋት ላይ ነበር
የመንግስትን ጉዳይ ለልጁ ለቤልሻዛር በመተው ወደ ቴማ ተጓዘ

ቤልሻዛር:
ብዙ ጊዜውን የሳለፈው ሥርዓትን በመግንባት ላይ ነበር
የባቢሎን ትልቁ ሥጋት ሜዲያ ነበር

### የቂሮስ መነሳት

585 - 550    አስታያጂስ የምዲያ ንጉስ ነበር (ቂሮስ ዳግማዊ በማንዳን የልጅ ልጁ ነበር)
550    ቂሮስ ዳግማዊ ፣ ሎሌ ንጉስ፣ ስልጣንን ለመጋራት ናቡኒዱስ ላይ አመጸ ከ
1 ግብፅ
2 ኪረካስ፣ ከሊዲያ ንጉስ ጋርም ስምምነት አደረገ
547    ቂሮስ በሳርዲስ ላይ ዘመተ (የሊዲያ ዋና ከተማ) ተንሻንም ኤስያ በሙሉ ተቆጣጠረ

539    ጎቢያስ ባቢሎንን ያለምንም መቋቋም (ዳን 5፤ የባልሻዛር እንደራሴ፤ ጎቢያስ በተጨማሪ ሜዶናዊው ዳሪዮስ ፣ ዳን 5:31)፡፡
ጥቅምት 11፣ 539    ቂሮስ ከናቦኒዱሰ የጨረቃ ሴት አማልከት ዚን ነፃ እነደሚየወጣ ሆኖ ገባ

### የቂሮስ ስኬት

530    የቂሮስ ልጅ እርሱን ተካው (ካምቢየስ ዳግማዊ )
530 - 522    የካምቢየስ መንገሥ (ኤልፋንቲን ፓፕይሪ)
በ525 ግብፅን ወደ ፋርስና ሜዶን ግዛት ጨመረ
522 - 486    ቀዳማዊ ዳሪዮስ ወደ ግዛት መጣ

የፋርስን ግዛት ከቂሮስ ያውራጃዎች እቅድ ጋር አስተባበረ
እንደ የልዲያው ፍራንክ (ገንዘብ) አዘጋጀ
486 - 465    ቀዳማዊ አርጤክስስ (አስቴር)
የግብፃዊያንን አመፅ ደመሰሰ
ግሪክን ለመውረር አሰበ፣ግን በ465 በተርሞፖሊ በውጊያ ተሸነፈ
ቀዳማዊ አርጤክስስ በ465 ተገደለ

480 የተርሞፖሊ ውጊያ
465 - 424 ቀዳማዊ አርታአረጤክስስ ሎነጊማኑስ (ዕዝራ 7-10፣ ነህምያ እና ሚልክያስ)
ግሪካዊያን በፔሎፓነሲን ጦርነት እስኪገጥማቸው ድረስ ለመስፋፋት ቀጠሉ
ጦርነቱ ለ20 አመታት ቀጠለ
በዚህ ወቅት የአይሁዳውያን ማህበር እንደገና ተመሰረተ

423 - 404 ዳግማዊ ዳሪዮስ
በትልቁ ቤተ መቅደስ የቂጣን በዓል ፈቀደ
404 - 358 አርጤክስስ ዳግማዊ
358 - 338 አርጤክስስ ሦስተኛ
338 - 336 አርሴስ
336 - 331 ዳሪዮስ ሦስተኛ

**ግሪክ**

359 - 336 የመቀዶንያው ፍልጶስ ዳግማዊ ግሪክን መሠረተ
በ336 ተገደለ
336 - 323 አሌክሳንደር ዘ ገሬት(የፍልጶስ ልጅ)
ዳሪዮስ ዳግማዊን በኢሱስ (ISUS) ውጊያ ድል አደረገ
ምስራቅ መድትራኒያንን እና ቅረብ ምስራቅን ከወረረ በኋላ በ323 በወባ በሽታ በባቢሎን ሞተ
የአሌክሳንደር ጀነራሎች ከርሱ ሞት በኋላ ግዛቱን ተከፋፈሉት:
1 ካሳስነድር - መቄዶኒያ እና ግሪክ
2 ሊሲሚካስ - ታራክ
3 ሴሌውካስ ቀዳማዊ - ሦሪያ እና ባቢሎን
4 ቶሎሚ - ግብፅ እና ፓላሰታይን
5 አነቲጎናስ - የትንሹ ኢስያ ክፍለ ግዛት

**ቶሎሚዎች ከሴሉሲድስ ጋር ይጋጠማሉ**

301 ፓላሰታይን ለ100 አመታት በቶሎሚ ግዛት ስር ነበሩ
175 - 163 አነቲዮካስ ኤፒፋነስ
አይሁዳዊያንን ለማዳቀል ፈለገ፣ ጅምናዚዬምን ገነባ
ለአረማዊያን መሰዊያ ሥፍራዎች ገነባ፤ ካህናት በደል ደረሰባቸው
Dec 13፣ 168 በአነቲዮካስ አፒፋነስ በመሰዊያው ላይ አሳማን ሰዋ፡፡ አንዳንዶች የጥፋት ርኩሰት እነደሆነ ይወስዱታል፡፡
167 ማታቲያስ እና ልጆቹ አመፁ፡፡ ማታቲያስ ተገደለ፡፡ይሁዳ ኃላፊነት ወሰደ፡፡
ይሁዳ መቃብያን የተዋጣላቸውን የደፈጣ ተዋጊዎችን ቀጠረ

Dec 25፣ 165 መቅደስ ተመረቀ

**ገዥዎች**

**ባቢሎን ሜዶን**

626 - 605 ናቡከደነፆር ሞተ ("ናቡ ፀሐይን ይጠብቃል")
625 - 585
ሳይረዛረስ
605 - 562 ናቡከደነፆር ዳግማዊ
("ኔቦ፣ ድንበርን ይጠብቃል")
585 - 550
አስታያጋስ
562 - 560 መሮዳክ ከፉው 550
ቂሮስ ዳግማዊ
556 ላባስኪ ማርዱክ
556 - 539 ናቦኒዱስ
ቤልሻዛር
539 - ጎብያስ

**ፋርስና ሜዶን**

550 - 530 ቂሮስ ዳግማዊ (538 ፋርስና ሜዶን አካየሜኒያን ግዛት የተባለውን ሀይል ተቆጣጠረ)
530 - 522 ካመቢሰስ ዳግማዊ (ግብፅ እና ቆጵሮስ ተጨመረ)
522 ጋኡማታ ወይንም ስዩዶ፣ ሰመርዲስ (ለ6 ወራት ነገሰ)
522 - 486 ዳሪዮስ ቀዳማዊ (ሀይታስፔስ)

| | |
|---|---|
| 486 - 465 | አርጤክስስ ቀዳማዊ (አስቴር ባል) |
| 465 - 424 | አርጤክስረስ ቀዳማዊ (እዝራ እና ነህሚያ በፓላሰታይን) |
| 423 - | አርጤክስስ ዳግማዊ |
| 424 - 404 | ዳሪዮስ ዳግማዊ ኖታስ |
| 404 - 359 | አርጤክስረስ ዳግማዊ ምንሞን |
| 359 - 338 | አርጤክስረስ ሦስተኛ ኦኩስ (Ochus) |
| 338 - 336 | አርሴስ (Arses) |
| 336 - 331 | ዳሪዮስ ሦስተኛ ኮዶማኑስ |

**ግሪክ**

| | |
|---|---|
| 359 - 336 | የሜቄዶንያን ፍልጶስ ዳግማዊ |
| 336 - 323 | አሌክሳንደር ዘግሬት |
| 323 - | ጀነራሎች ግዛቱን ተቀራመቱ |
| | 1 ካሳንዲያ - መቄዶኒያ |
| | 2 ሊይስማኩስ - ሦሪያ |
| | 3 ሴሌውካስ ቀዳማዊ - ሦሪያ እና ባቢሎን |
| | 4 ቶሎሚ - ግብፅ |
| | 5 አንቲጎናስ - ትንሹ እሲያ (በ301 አከልበ ሞተ) |

ቶሎሚዎች ፓላሰታይን ተቆጣጠሩ ግን በ175 – 163 ወደ ስሉሲዶች ተሻገረ

| | |
|---|---|
| 175 - 163 | አነቲዮካስ አራተኛ ኤፒፋነስ፣ የስሉሲድ 8ኛ ገዥ |

*አብዛኛዎቹ ቀናትና እና ስሞች የተወሰዱት ከእስራኤላዊያን ታሪክ በዮሃንስ ብራይት (*A History of Israel* by John Bright) ገፅ 461-471 ላይ ነው።

# ተጨመሪ መግለጫ  ሁለት

## የመሶፖታሚያን ኃያላን ግልጽ ታሪካዊ ዳሰሳ

(አብዛኛዎቹ ቀናት ጥቅም ላይ የዋሉት በቅድሚያ ከእስራኤላዊያን ታሪክ በዮሐንስ ብራይት ገፅ 462 ላይ ነው)

1. የአሦር ግዛት(ዘፍ 10፡11)

ሀ ሃይማኖት እና ባህል በስፋት ተጽእኖ ያደረጉት በሱመራን ወይም በባቢሎናዊያን ግዛት

ለ ጊዜያዊ የገዥዎች ዝርዝር እና ግምታዊ ጊዜያት፡

1 1354-1318 - አስሁር-ኡባልት ቀዳማዊ፡

(a) የሂታይቶችን ከተማ ከረከሚሽን አሸንፎ ገዛ

(b) የሂታይቶችን ጫና ማስወገድ እና የአሦሮቹን እነዲያድጉ ፈቀደ

2 1297-1266 - አዳድ-ንራሪ ቀዳማዊ (ኃያል ንጉስ)

3 1265-1235 - ሻልማናንሰር ቀዳማዊ (ኃያል ንጉስ)

4 1234-1197 - ቱኩልቲ-ንኑረታ ቀዳማዊ

- በመጀመሪያ የባቢሎናዊያንን የምስራቅ ግዛት መቆጣጠር

5 1118-1078 - ትግላት ፐልሳር ቀዳማዊ

- አሦራዊያንያ በመሶፖታሚያ ዋና ሃያላን ሆኑ

6 1012- 972 አሹር ራቢ ዳግማዊ

7 972- 967 - አሹር -ሬሽ-እሱይ ዳግማዊ

8 966- 934 - ትግላት ፐልሳር ዳግማዊ

9 934- 912 - አሹር -ዳን ዳግማዊ

10 912- 890 - አዳድ-ንራሪ ዳግማዊ

11 890- 884 - ቱኩልቲ-ንኑረታ- ዳግማዊ

12 883- 859 - አሹር -ናስሪ-አፓል ዳግማዊ

13 859- 824 - ሻልማናንሰር ሣልሳዊ

- የኩዋርካር ውጊያ በ853

14 824-811 - ሻማሺ-አዳድ አምስተኛ

15 811-783 - አዳድ-ንራሪ ሣልሳዊ

16 781-772 - ሻልማናንሰር አራተኛ

17 772-754 - አሹር-ዳን ሦስተኛ

18 754-745 - አሹር-ንራሪ አምስተኛ

19 745-727 - ትግላት ፐልሳር ሣልሳዊ፡

ሀ በ 2 ነገ 15፡19 ላይ በባቢሎናዊያን በዙፋን ስሙ በፑል ተጠርቷል

ለ በጣም ኃያል ንጉስ ነበር

ሐ ግዞተኞችን ህዝቦች ነፃ የማውጣት ፖሊሲውን ጀመረ

መ በ735 አክልበ የ "Syro-Ephramatic League" ምስረታ ነበር፡፡ አላመው እየተበራት የመጠውን የአሦራዊያንን እንቅስቃሴ ለመግታት በዮርዳኖስ ወንዝ ዳርቻ ያሉትን ሀገሮች ከኤፍራጥስ ወንዝ መነሻ ጀምሮ እስከ ግብፅ ሀገር የጦር ኃይሎችን በአንድ ላይ ለማዋሃድ ነበር፡፡ የይሁዳ ንጉስ አሃዝ ለመተባበት ፈቃደኛ አልነበረም እና በእስራኤልና በሦሪያ ተወረረ፡፡ የኢሳያስን ምክር ትቶ ለርዳታ ወደ ትግላት ፐላሳር ሣልሳዊ ደብዳቤ (ዝ.ከ. 2 ነገ 16፣ ኢሳ 7-12) ላይ እይ፡፡

ሠ በ 732 ትግላት ፐልሳር ሣልሳዊ ሦሪያን እና እስራኤልን ወረረ አሸነፋትም በ እስራኤል ዙፋን ላይም ሆሴዕን ንጉስ አድርጎ አስቀመጠ (732-722)፡፡ በሺህ የሚቆጠሩ አይሁዳዊያን ከሰሜኑ እስራኤል ተማርከው ወደ ሜዲያ ተወሰዱ(ዝ.ከ. 2 ነገ 15)፡፡

20 727-722 - ሻልማናንሰር አምስተኛ

ሀ ሆሴዕ ከግብጽ ጋር ስምምነት ፈጥሮ በአሦራዊያን ተማረከ (2 ነገሥት 17)

ለ በ724 አክልበ ሰማሪያን ከበባት

21 722-705 - ሳርጎን ዳግማዊ፡

ሀ ከሦስት አመት በኋላ ከበባው በሻልማናንሰር አምስተኛ ተጀመረ፣ እርሱን የተካው ሳረጎን ዳግማዊ የእስራኤልን ዋና ከተማ ሰማርያን ያዘ፡፡ ከ27፣000 በላይ የሚሆኑ ወደ ሜድ ተወሰዱ፡፡

ለ የህታይት ግዛትም በተጨማሪ ተሸነፈ፡፡

ሐ በ714-711 ሌላ የዮርዳኖስ ዙሪያ ሀገሮች ህብረት እና ግብፅ በአሦር ላይ አመፁ፡፡

ይህ ህብረት "የአሽዳድ አመፅ "the Ashdad Rebellion" ተብሎ ይጠራል፡፡ የይሁዳው ሕዝቅያስ እንኳ በዚህ በመጀመሪያ ተሳትፏል፡፡ አሦር ብዙ የፓላስታይንን ከተሞች ወረረ እና አጠፋ፡፡

22 705-681 - ሰናክሬብ፡

ሀ በ 705 ሌላ የዮርዳኖስ ዙሪያ ሀገሮች ህብረት እና ግብፅ ከዳግማዊ ሳርጎን ሞት በኋላ አመፁ፡፡ ሕዝቅያስ ይህንን አመፅ ሙሉ በሙሉ ደግፏል፡፡ ሰናክሬብ በ701 ወረረ፡፡ አመፁ ተቋረጠ ነበር ግን የሩሳሌም በእግዚአብሔር አደራረግ ተረፈች (ዝ.ከ. ኢሳ 36-39 እና 2ነገ 18-19)፡፡

ለ ስናክሬብ በተጨማሪ የኤላምንና የባቢሎን አመፅ እስወገ፡፡
23 681-669 - እስራሃዶን:
ሀ የመጀመሪያ የአሦራዊያን ገዥ ግብፅ ለመውጋትና ለማስገበር
ለ ለባቢሎን ትልቅ ስሜት ስለነበረው ዋና ከተማዋን ዳግመኛ ሰራ
24 669-633 – አሹርባኒፓል:
ሀ በዕዝራ 4:10 ላይ ኦስናፓር ተብሎ ተጠርቷል
ለ የርሱ ወንድም ሻማሽ-ሹም-ኡኪን የባቢሎን ንጉስ ተደረገ (በኋላ ግን ከሥልጣኑ ወደ የክልል ገዥነት ዝቅ ተደረገ)፡፡

ይህ ከአሦርና እና ባቢሎን መሀከል ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ሰላምን አድረጓል፡፡ ነገር ግን ተዳፍኖ የነበረ የመገንጠል ሀሳብ በወንድሙ (ከሥልጣኑ ወደ የክልል ገዥነት ዝቅ በተደረገ) የሚመራው በ652 ፈናዳ፡፡

ሐ የተቤስ መውደቅ፤ 663 አክልበ
መ ኤላምን ወጋ፤ 653፣ 645 አክልበ
25 633-629 - አሹር -ኢቲል-ኢላን
26 629-612 - ሲን-ሻር-ኢሽኩን
27 612-609 - አሹር -ኡባሊት:
ሀ በምርኮ በሃራም ወደ ሥልጣን የወጣ ንጉስ
ለ በ614 አክልበ የአሸር ውድቀት እና ነኔዌ በ612 አክልበ

II. አዲሱ-የባቢሎን ግዛት:
ሀ 703-? ሜሮዳክ ባልዳድ
- ተደጋጋሚ አመፅ በአሦራዊያን ገዥዎች ላይ ጀመረ
ለ 652 ሻማሽ-ሹም-ኡኪን:
1 የአስራዶን ልጅ እና የአስሁርባኒፓል ወንድም
2 በአሦራዊያን ገዥዎች ላይ ማመፅ ጀመረ ነገር ግን ተሸነፈ
ሐ 626-605 ናቡከደነፆር :
1 የመጀመሪያው አድሲቱ -ባቢሎን ንጉስ ነገሥት ነበር
2 በደቡብ በኩል አሦራዊያንን ወጋ ግን የሜዶኑ ሳያአርጥክራስ (Cyaxares)በስተሰሜን ምስራቅ በኩል ወጋው፡፡
3 የጥንታዊያን አሦር ዋና ከተማ አሹር በ 614 አክልበ ወደቀች እና ኃያሏም አዲሷ ከተማ ነኔዌ በ612 ወደቀች
4 የሦራዊያን ሰራዊት ቅሬታ ወደ ሀራን ተመለሱ፡፡ ንጉስም እስኪኖራቸው ድረስ፡፡
5 በ608 ፈርዖን ኒካው ዳግማዊ (ዝ.ከ. 2ነገ 23:29) እየተስፋፋ ያለውን የባቢሎናዊያንን ሃይል ለመቋቋም የሦራዊያንን ቅሬታ ለመርዳት የግጭት መከላከያ ቀጠና ለመመስረት ወደ ሰሜን ዘመተ፡፡ መልካሙ የይሁዳ ንጉስ ዮስያስ ፣ (ዝ.ከ. 2ነገ 23)፣ በፓላሰታይን በኩል የግብፃዊያንን እንቅስቃሴ ለመግታት ተቃወመ፡፡
በመጊዶ አጭር ውጊያ ነበር፡፡ ዮስያስ ቆሰለና ሞተ (2ነገ 23:29-30)፡፡ ልጁ፣ ኢዮካዝ ንጉስ ሆነ፡፡ ፈርዖን ኒካው ዳግማዊ የአሶራዊያንን የማጥፋት ኃይል ለመግታት ሐራን የደረሰው ዘግይቶ ነበር፡፡ በንጉስ ናቡከደነፆር ዳግማዊ የሚመራውን የባቢሎናውያንን ሃይል ወስዶ በ603 አክልበ በካርከሚሽ በኤፍራጥስ ወንዝ ሙሉ በሙሉ ተሸነፈ፡፡ ወደ ግብፅ ሲመለስ ሳለ ፈርዖን ኒካው ኢሩሳሌም አግኝቶት ስለ ከተማ ጠየቀው፡፡ ኢዮአካዝን ከሶስት ወር በኋላ ተክቶት አፈለሰው በርሱም ፈንታ የኢዮአካዝን ልጅ ዮስያስን በዙፋን ላይ አስቀመጠው(ዝ.ከ. 2 ነገ 23:31-35)፡፡
6 ናቡከደነፆር ዳግማዊ የግብፆችን ሠራዊት ወደ ደቡብ ፓላሰታይን አሳደደ ግን ያባቱን ሞት ሰምቶ ዘውድ ለመጫን ወደ ባቢሎን ተመለሰ፡፡ በዚያኑ አመት ወደ ፓላሰታይን ተመለሰ፡፡ ኢዮአቂምን በይሁዳ በዙፋን ላይ ትቶ በሙቶዎች የሚቆጠሩትን ዜጎች እና ከንጉሳን ቤተሰብ ሌሎችን ይዞ ተመለሰ፡፡ ዳንኤልና ጓደኞቹም የዚህ ፍልሰት ሰለባ ነበሩ፡፡
መ 605-562 - ናቡከደነፆር ዳግማዊ :
1 ከ 597-538 ባቢሎን ፓላሰታይንን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥራ ነበር፡፡
2 በ 597 ከኢሩሳሌም ሌላ ምርኮ ተከሰተ ምክንያቱም የኢያቂን ከግብፅ ጋር መስማማት ነበር (2ነገ 24)፡፡ ናቡከደነፆር ዳግማዊ ከመምጣቱ አስቀድሞ ሞተ፡፡ ወደ ባቢሎን ሲማረክ ልጁ ኢዮአኪን ለሶስት ወራት ብቻ ንጉስ ነበር፡፡ አስር ሺ ዜጎች ሕዝቅኤልንም ጨምሮ ወደ ባቢሎን ከተማ አቅራቢያ ኬባር ግድብ አቅራቢያ ሰፈሩ፡፡
3 በ 586፣ ከግብፅ ጋር በቀጠለው መቀራረብ በኋላ፣ የየኢሩሳሌም ከተማ በናቡከደነፆር (2 ነገ 25) ሙሉ በሙሉ ተደመሰሰች እንዲሁም ከፍተኛ ምርኮ ተከናወነ፡፡ ኢዮአክምን የተካው ሰዴቅያስም ተማረከ ጎዶልያ ገዥ ተደረገች፡፡
4 ጎዶልያ በአይሁዳዊያን ሽምቅ ተዋጊ ሃይላት ተገደለች፡፡ እነዚህ ኃይላት ኤርምያስ ከነርሱ ጋር እንዲሄድ በማስገደድ ወደ ግብጽ ሸሹ፡፡ ናቡከደነፆር ለአራተኛ ጊዜ ወረረ (605፣ 596፣ 586፣ 582) እና የቀሩትን ሊያገኛቸው የቻለውን ሁሉ ማርኮ ወሰደ፡፡
ሠ 562-560 - ሜሮዳክ-ክፉ፣ የናቡከደነፆር ልጅ፣ አመል-ማርዱክ በመባል ይታወቅም ነበር፡፡ (አካዲያን፤ የማርዱክ ሰው)
- ኢዮአቄምን ከወህኒ አስፈታው ግን በባቢሎን መቆየት ነበረበት (ዝ.ከ. 2ነገ 25:27-30፤ ኤር 52:31)፡፡
ረ 560-556 - ኔሪግልሳር (Neriglissar)
- ሜሮዳክ-ክፉን ገደለ፣ ዋርሳው (brother-in-law) የነበረውን
- እርሱ አስቀድሞ ኢሩሳሌምን ደምስሶ የነበር የናቡከደነፆር ጀነራል ነበር(ዝ.ከ. ኤር 39:3፣13)
ሰ 556 - ላባስኪ-ማርዱክ
- እርሱ ኔሪግልሳር ልጅ ሲሆን በልጅነቱ የንጉስነት ማዕረግ ታስቦለት የነበር ግን ከዘጠኝ ወራት ብቻ በኋላ ተገደለ (ቤሮሶስ)፡፡
ሸ 556-539 - ኔቦኒደስ (አካዲያን፣ "ኔቦ ከፍ ያለ ነው"):

1 ኔቦኒደስ እርሱ ከንጉስ ቤተሰብ ሳይሆን የናቡከደነፆርን ሴት ልጅ አገባ

2 ብዙ ጊዜውን ያሳለፈው "ሲን" ለተባለው የጨረቃ አምላክ በቴማ ቤተመቅደስ በመስራት ላይ ነበር፡፡

እርሱ የዚህች አምላክ ሊቀካህን ልጅ ነበር፡፡ ይህ ለማርዱክ "የባቢሎን ዋና አምላክ" ካህናት ጋር ጠላትነትን ፈጥሮበታል፡፡

3 ብዙ ጊዜውን የጠፋው ተቃዋሚዎችን ለማንበርከክ በመሞከር ላይ ነበር (በሦሪያ እና በሰሜን አፍርካ) እና መንግስቱን በማረጋጋት ላይ፡፡

4 የመንግስትን ጉዳይ ለልጁ በመተው ወደ ቴማ ተጓዘ፣ ቤልሻዛር፣ በዋና ከተማ፣ ባቢሎን (ዝ.ከ. ዳን 5)፡፡

*ቀ* ? - 539 - ቤልሻዛር (co-reign)

- የባቢሎን ከተማ ለፋረሳዊያን ጦር እጅ በጎብርያስ ጉቲያም ፈጥና ወደቀች፡፡ የአፍራጥስን ወንዝ መስመር በመዝጋትና አቅጣጫውን በመቀየር እና ወደከተማው በመግባት፡፡ የከታማዋ ካህናትና ህዝቡ ፋርሳዊያንን እነደነፃ አውጪዎችና ለማርዱክ እንደገና መንሰራራት ምክንያት እነደሆኑ አርገው ቆጠሩአቸው፡፡ ጎብርያስ በቂሮስ ዳግማዊ የባቢሎን ከተማ ገዥ ተደርጎ ተሾመ፡፡ ጎብርያስ ምናልባት የሜዶኑ ዳሪዮስ ሊሆን ይችላል ዳን 5:31፤ 6:1 ""ዳሪዮስ" ማለት "የላቀ" ማለት ነው፡፡

III. የፋርስና ሜዶን ግዛት፡ የቂሮስ ዳግማዊ አነሳስ ዳሰሳ (ኢሳ 41:2፣25፤44:28-45:7፤ 46:11፤ 48:15):

*ሀ* 625-585 - ሳያአክሳረስ የሜዶን ንጉስ ባቢሎናዊያን አሶርን እንዲያሸንፉ ያገዘ ነበር፡፡

*ለ* 585-550 - አስታያገስ የሜዶን ንጉስ ነበር (ዋና ከተማው ኢስባቴና ነበር)፡፡ ቂሮስ ዳግማዊ የርሱ የልጅ ልጅ ነበር በ ካመቢይሰል (600-559፣ ፋርስ) እና ማነዳን (ያስታይጋስ ሴት ልጅ፣ ሜዲያ)፡፡

*ሐ* 550-530 - የኤንሻም ቂሮስ ዳግማዊ (ምስራቃዊ ኤላም) የመጸው የንጉስ ሎሌ ነበር:

1 ናቦኒዳስ፣ የባቢሎናዊያን ንጉስ፣ ቂሮስን ደገፈ፡፡

2 የአስቲያገስ ጀኔራል፣ ሀርጳጉስ፣ የቂሮስን አመጽ ለመቀላቀል ሰራዊቱን አስከትሎ ሄደ

3 ቂሮስ ዳግማዊ አስቲያገስን ከዙፋን አወረደ፡፡

4 ናቦኒዳስ፣ ፣ የሃይልን እኩተመጣጣኝነት ለማንሰራራት ከ፡-

*ሀ* ግብፅ

ለ ክሮሳስ፡ ከሊድያ ንጉስ (ትንሹ ኢስያ) ጋር ስምምነት አደረገ

5 547 - ቂሮስ ዳግማዊ በሳርድስ ላይ ዘመተ ( የሊድያ ዋና ከተማ) እና በ546 አከልበ ወደቀች

6 539 - በጥቅምት አጋማሽ ዑግባሩ የተባለው ጀኔራል እና ጎብርያስ፣ ሁለቱም የጉቲያም፣ ከ ቂሮስ ሰራዊት ጋር፣ ያለምንም መቋቋም ባቢሎንን ወሰዱ፡፡ ዑግባሩ ገዥ ተደረገ ግን፣ በጦርነት ቆስሎ በሳምነት ውስጥ ተገደለ፡ ከዚያም ጎብርያስ የባቢሎን ገዥ ሆነ፡፡

7 539 - በጥቅምት መጨረሻ ቂሮስ ዳግማዊ "ታላቁ" እንደነጻ አውጪ ሆኖ በግሉ ቀረበ፡፡ ለዜጎች ያለው መልካም ሥርአት የምርኮን አመታት እንዲገለበጥ ተደርጎ እንደ ሀገራዊ ህግ ተወሰደ፡

8 538 - አይሁዳዊያን እና ሌሎች ባዲሱ ህግ መሰረት ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ እና ቤተመቅደስ እነዲሰሩ ተፈቀደላቸው (ዝ.ከ. 2 ዜና 36:22፣23፤ ዕዝራ 1:1-4)፡፡

በናቡከደነፆር ከያህዌ ቤተመቅደስ ተዘርፈው ወደ ባቢሎን ማርዱክ ቤተመቅደስ የተወሰዱትን የቤተመቀደሱን እቃዎች እነዲመለሱ ስደረገ (ዝ.ከ. ዕዝራ 1:7-11፤ 6:5)፡፡

9 530 - የቂሮስ ልጅ፣ ካመቢየስ ዳግማዊ ፣ እርሱን ተከው በኋላ በዚያው አመት ቂሮስ በዘመቻ ሞተ፡፡

*መ* 530-522 - ካምቢየስ ዳግማዊ መንገሥ

1 በ525 አከልበ የግብጳዊያንን ግዛት ወደ ፋርስና ሜዶን ግዛት ጨመረ

2 ለአጭር ጊዜ ነበር በሥልጣን ላይ የቆየው:

*ሀ* አንዳንዶቹ ራሱን እነደ ገደለ ይናገራሉ፤

ለ ሄሮድታስ ፈረሱ ላይ እየወጣ ሳለ በራሱ ሰይፍ ራሱን እነደቆረጠና በቁስሉ ምክንያት እንደ ሞተ ይናገራል

3 የዙፋን በግልጽና ሰላማዊ መንገድ በ Pseudo-Smerdis (*ጋኡማታ*) መተላለፍ - 522

*ሠ* 522-486 - ዳሪዮስ ቀዳማዊ (ሀይስታፕስ) ወደ ሥልጣን መጣ

1. እርሱ ከንጉሳዊ በተሰብ አልነበረም ግን የጦር ጀነራል ነበር እነጂ
2. ለክልል መንግሥት ገዥነት የቂሮስን እቅድ ተጠቅሞ የፋረስን ግዛት አስተባበረ(እዝራ 5-6፤ በተጨማሪም በሐጌና በዘካሪያስ ጊዜ)
3. እንደ ሊድያ የመገበያያ ገንዘብ አዘገጀ
4. ግሪክን ለመውረር ሞከረ ነገር ግን ወደኋላ ተመለሰ፡፡

*ረ* 486-465 - የዳግማዊ አርጤክስስ መንገሥ:

1 የግብፃዊያንን አመፅ ደመሰሰ

2 ግሪክን ለመውረር እና የፋርሳዊያንን ህልም ለመፈፀም አሰበ ግን በተርሞፖሊ በ480 አከልበ እና በ479 አከልበ በሳልሚስ ጦርነት ላይ ተሸነፈ

3 የአስቴር ባል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሁሻኢሮስ የተባለ በ465 አከልበ ተገደለ

*ሰ* 465-424 - አርጤክስረስ ቀዳማዊ (ሎነጊማኑስ) ነገሰ (ዝ.ከ. ዕዝራ 7-10፤ ነህ፤ ሚል):

1 ግሪካዊያን ፐሎፓንያስ የእርስ በርስ ጦርነት እሲኪገጥማቸው ድረስ መስፋፋትን ቀጠሉ

2 ግሪክ ተከፈለ (አቴናንና - ፐሎፓኒሲያንን)

3 ግሪክ እርስበርስ ጦርነት ለ20 አመታታ ዘለቀ

4 በዚህን ወቅት አይሁዳዊያን ማህበረሰብ ተጠናከሩ
5 የአርጤክስስ ዳግማዊ እና ሴኪያዲያኖስ ለአጭር ጊዜ መንገሥ - 423
ሸ 423-404 - ዳሪዮስ ዳግማዊ (ኖዞስ) ነገሰ
ቀ 404-358 - አርጤክስረስ ዳግማዊ (ምኔሞን)ነገሰ
በ 358-338 - አርጤክስረስ ሳልሳዊ (ኦቾስ) ነገሰ
ተ 338-336 - አርሰስ ነገሰ
ቸ 336-331 - ዳሪዮስ ሳልሳዊ (ኮዶማኑስ)በ331 በኢሱስ እስከ ተደረገው ጦርነት ድረስ ነገሰ እና በግሪካዊያን ተሸነፈ

IV ግብፅ አሰሳ:

ሀ ሂክሶስ (እረኛ ንጉስ - ሴማዊ ንጉስ)-1720/10-1550

ለ 18ኛ ሥርወ-መንግስት (1570-1310):
1 1570-1546 - Amosis
ሀ ቲቤስን ዋና ከተማ አደረገ
ለ Canaan የከነዓንን ምሥራቃዊ ክፍል ወረረ
2 1546-1525 - አምኖፊስ I (አሜነሆትፕ ቀዳማዊ)
3 1525-1494 - ቱተሞሲስ ቀዳማዊ
4 1494-1490 - ቱተሞሲስዳግማዊ - married የቱተሞሲስ ቀዳማዊን ልጅ አገባ፣ ሀትሳፕሱት
5 1490-1435 - ቱተሞሲስ ሣልሳዊ (የሀትሳፕሱት አጎት)
6 1435-1414 - አምኖፊስ ዳግማዊ (አሜነሆትፕ ዳግማዊ )
7 1414-1406 - ቱተሞሲስ አራተኛ
8 1406-1370 - አምኖፊስ ዳግማዊ I (አሜነሆትፕሣልሳዊ )
9 1370-1353 - አምኖፊስ አራተኛ (አከሀናታን)
ሀ አቴን፣ የፀሐይን አምላክ አመለከ
ለ የሃያልምላክ አምልኮን አቋቋመ (አንስ አምላክ)
ሐ ቴል-ኤል-አማረና ደብዳቤዎች የዚህ ጊዜ ናቸው
10 ? ስሜንካሬ
11 ? ቱታንክሃም (ቱታንከሃታን)
12 ? አይ (አይን-አይን)
13 1340-1310 ሃሙራቢ

ሐ 19ኛ ሥርወ-መንግስት (1310-1200):
1 ? ራምሴስ ቀዳማዊ (ራምሴስ)
2 1309-1290 - ሴቲ ቀዳማዊ (ስዞስ)
3 1290-1224 - ራምሲስ ዳግማዊ (ራምሴስ ዳግማዊ )
ሀ ከመሬት ቁፋሮ የተገኘው መረጃ የዘፀአቱ ፈርዖን ሊሆን እንደሚችል ይገምታል፡፡
ለ በሃባሩስ (የዕብራዊያን ወይም የሴማዊ) ባሪያ የአቫሪሲን እና የራምሴስን ከተማ ሰራ
4 1224-1216 - ማርንፕትሃ (ምረንፕትሃ)
5 ? አሜንመሰስ
6 ? ሴቲ ዳግማዊ
7 ? ስፕተሃ
8 ? ቴዎስረት

መ 20ኛ ሥርወ-መንግስት (1180-1065)
1 1175-1144 - ራምሴስ ሳልሳዊ
2 1144-1065 - ራምሴስIV – XI

ሠ 21ኛ ሥርወ-መንግስት (1065-935):
1 ? ሰመንደስ
2 ? ሀሪሆር

ረ 22ኛ ሥርወ-መንግስት (935-725 - ሊቢያ):
1 935-914 - ሺሻክ(ሼሰኖክ ዳግማዊ ወይም ሸሾንግ ቀዳማዊ)
ሀ እስከ ንጉስ ሰለሞን ሞት ቀዳማዊ ኢዮርብአምን ሸሸገ
ለ በ925 ገደማ ፓላሰታይንን ተቆጣጠረ (ዝ.ከ. 1ነገ 14-25፤ 1ኛ ዜና 12)
2 914-874 - ቀዳማዊ ኦሶርኮን
3 ? ኦሶርኮንዳግማዊ
4 ? ሾሸነክ ዳግማዊ
ሰ 23ኛ ሥርወ-መንግስት (759-715 - ሊቢያዊ)

ሸ 24ኛ ሥርወ-መንግስት (725-709)
1 25ኛ ሥርወ-መንግስት (716/15-663 - ኢትዮጵያዊ/ሱዳናዊ(Nubian):
1 710/09-696/95 - ሻባኮ (ሻባኩ)
2 696/95-685/84 - ሸበተኮ (ሸበትኩ)
3 690/689፣ 685/84-664 - ትርሃካ (ታሃራቃ)
4 ? ታንታሙን

ቀ 26ኛ ሥርወ-መንግስት (663-525 - ሳአቲክ):
1 663-609 - ሳሙቲከስ ቀዳማዊI (ሳሙቲክ)
2 609-593 - ኔኮ ዳግማዊ (ኒኮ)
3 593-588 - ሳሙቲከስ ዳግማዊ (ሳሙቲክ)
4 588-569 - አቢሬይስ (ሆፍራ)
5 569-525 - አማስስ
6 ? - ሳሙቲከስ ሳልሳዊ (ሳሙቲክ)

በ 27ኛ ሥርወ-መንግስት (525-401 - የፋርስ):
1 530-522 - ካምቢሰስ ዳግማዊ (የቂሮስ ዳግማዊ ልጅ)
2 522-486 - ዳሪዮስ ቀዳማዊ
3 486-465 - አርጤክስስ ቀዳማዊ
4 465-424 - አርጤክስረስ ቀዳማዊ
5 423-404 - ዳሪዮስ ዳግማዊ

ተ የብዙ ሥርወ-መንግስታት ገለፃ (404-332)
1 404-359 - አርጤክስረስ ዳግማዊ
2 539/8 - 338/7 - አርጤክስረስ ሳልሳዊ
3 338/7 - 336/7 - አርሰስ
4 336/5 - 331 - ዳሪዮስ ሳልሳዊ

*ለተጨማሪ የተለያዩ ዘረ-ሀረጎች Zondervan's Pictorial Bible Encyclopedia፣ ቅፅ 2 ገፅ 231 ተመልከት፡፡

V የግሪክ ዳሰሳ:
ሀ 359-336 - የመቀዶንያው ፍልጶስ ዳግማዊ:
1 ግሪክን መሰረተ
2 በ336 አከልበ ተገደለ

ለ 336-323 - አሌክሳንደር ዳግማዊ "ታላቁ" (የፍልጶስ ልጅ):
1 በኢሱስ ጦርነት የፋርስን ንጉስ፣ ዳሪዮስ ሳልሳዊን አስወገደ፣
2 በ323 አከልበ በወባ በሽታ በ32/33 አመቱ በባቢሎን ሞተ
3 የአሌክሳንደር ጀነራሎች ከርሱ ሞት በኋላ ግዛቱን ተከፋፈሉት:
ሀ ካሳስነድር - መቄዶኒያ እና ግሪክ
ለ ሊሲሚካስ - ታራክ
ሐ ሴሌውካስ ቀዳማዊ - ሦሪያ እና ባቢሎን
መ ቶሎሚ - ግብፅ እና ፓላስታይን
ሠ አነቲጎናስ - የትንሹ ኢስያ ክፍለ ግዛት

ሐ ፓላስታይን ለመቆጣጠር ሴሉሲዶች ከቶሎሚዎች ጋር ይዋጋሉ
1 ሦሪያ (የሴሉሲድ ገዥዎች):
ሀ 312-280 - ሴሌውካስ ቀዳማዊ
ለ 280-261 - አነቲዮካስ ቀዳማዊ ሶተር
ሐ 261-146 - አነቲዮካስ ዳግማዊ ዝኡስ
መ 246-226 - ሴሌውካስ ዳግማዊ ካሊንካስ
ሠ 226-223 - ሴሌውካስ ሳልሳዊ Ceraunus
ረ 223-187 - አነቲዮካስ ሳልሳዊ ታላቁ
ሰ 187-175 - ሴሌውካስ IV ፊሎፓቶር
ሸ 175-163 - አነቲዮካስ IV ኤፒፋነስ
ቀ 163-162 - አነቲዮካስ V
በ 162-150 - ዲሜትሪያስ ቀዳማዊ
2 ግብፃዊያን (የቶሎማዊ ገዥዎች):
ሀ 327-285 - ቶሎሚ ቀዳማዊ ሶተር
ለ 285-246 - ቶሎሚ ዳግማዊ ፍላደልፋስ

ሐ 246-221 - ቶሎሚ ሳልሳዊ ኤቪጅተስ
መ 221-203 - ቶሎሚ IV ፍልዮፓትር
ሠ 203-181 - ቶሎሚ V ኤፒፋነስ
ረ 181-146 - ቶሎሚ VI ፊሎሜትር

3 ሰፊ ዳሰሳ:

ሀ 301 - ፓላሰታይን ለ181 ዓመታታ ከቶሎሚ ሥር ነበረች፡፡
ለ 175-163 - አንቲዮካስ IV ኤፒፋነስ፣ 8ኛው የሴሉሲድ ገዥ የሚቻል ከሆነ አይሁዶችን በጉልበት ለማዳቀል ፈለገ

(1) ጅምናዚዬምን ገነባ
(2) ዜኡስ ኦለይምፒያስ ለተባለ የአረማዊያንን ጣኦት አምልኮ በቤተመቅደስ ውስጥ መሰዊያ ሰራ

ሐ 168 - ታህሳሰስ 13 - በአንቲዮካስ አፒፋነስ በኢሩሳሌም መሰዊያው ላይ አሳማ ተሰዋ
አንዳንዶች የህን በዳንኤል 8 ላይ ያለውን የጥፋት ርኩሰት እነደሆነ ይወስዱታል፡፡


መ 167 - የሞዲን ካህን ማታቲያስ ፣እና ልጆቹ አመፁ፡፡ በጣም የሚታወቁ ልጆቹ መሀከል ይሁዳ መቃብያኑ በጣም ጣዋቂ ነበር፣ "የሀመሩ ይሁዳ"

ሠ 165 - ታህሳስ 25 - መቅደስ ተመረቀ፡፡ ይህ ሃኑካ በመባል ይታወቃል ወይም "የብርሃናት በዓል፡፡"

ለበለጠ ለቀናት አቀማመጥ ችግር ቅደም ተከተል እና ቅድመ ግምት *The Expositors Bible Commentary*፣ ቅፅ 4፣ ገፅ 10-17 ተመልከቱ፡፡

# ተጨመሪ መግለጫ ሦስት

## የሙሉው ብሉይ ኪዳን ሰንጠረዥ
(በቀጣዩ ገጽ)


ሀያሃዋጌ
አርታርጤክስ (ፓ)
አርጤክስስ አውሻሮይስ (ፓ)
ዕዝራ 7-10
ነህምያ
ሀጋሃ
ዳርዮስ I (ፓ)
ካምቢስ II (ፓ)
ቂሮስ II (ፓ)
ሐጌ
ዘካርያስ
ዕዝራ 1-6
ኢዩኤል
አብድዩ
ፋርሲ
ቢልጣሶር(ባ)
ናቡኒዶስ(ባ)
ባቢሎን
ናቡከደንጾር(ባ)
ናቦፖላሳር (ባ)
አሹርባኒጳል
ሂሳርዶን(ሀ)
ስናክሬብ II (ባ)
አሶር
ሳርጎን II (ሀ)
ሻልምናሶር V (ሀ)
ትግላትፒላስረ III (ሀ)
ዮናስ
ሶርያ
ፍልስጤም
ከነአን
ግብጽ
ኢዮብ
ዘፍጥረት 12-50
ዘፍጥረት 1-11
ኤርምያስ
ሕዝቅኤል
ዳንኤል
ናሆም
ኢንባቆም
ሶፎንያስ
አሞጽ
ሆሴዕ
ኤልሳዕ
ኤልያስ
ኢሳይያስ
ሚኪያስ
እስራኤል
ይሁዳ
ዘፀ
ሌዋ
ዘኍ
ዘዳ
ኢያሱ
መሳ
ሩት
ነ እና 2ኛ ሳሙኤል
ነኛ እና 2ኛ ነገስት
ነኛ ዜና
2ኛ ዜና
ምርኮ
የኢየሩሳሌም ቅጥሮች-ነህምያ
ሦስተኛ ምላሽ---ዕዝራ
ሁለተኛ መመለስ-ዘሩባቤል
የመጀመሪያ መመለስ -ሸሽባዛር
ኢ.ገዶልያስ
ኘ. ሰደቂያስ
ነ. ኢዮአኪን
ሐ. ኢዮአቄም
ቸ.ኢዮራም
ተ. ዮስያስ
በ. ምናሴ
ቀ. ህዝቅያስ
ሽ. ኦዝያን
ሰ. የሮብአም
ረ. አክአብ
ሠ. የሮብአም
መ. ሮብአም
ሐ.ሰለሞን
ለ. ዳዊት
ሀ. ሳኦል
የባቢሎን ግንብ (4)
የኖህ የጥፋት ውኃ (3)
የሰው ውድቀት (2)
ፍጥረት (1)
ዶ/ር ቡብ አትሊይ
መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ዓ/አቀፍ 96